በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሂውማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ-ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም

# የባሌ ዞን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አሰለጣጠንና ትግበራ

በ ኤልያስ አድማሱ

ሰኔ 2006
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# በባሌ ዞን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች
# የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር
# አቀራረብ አሰለጣጠንና ትግበራ

በ

ኤልያስ አድማሱ

በተግባራዊ ስነ-ልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎት
ማስተማር መርሀ-ግብር የፍልስፍና
ዶክተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2006
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

**አጠቃሎ**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ከሚገኙ የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጆች ተመርቀው በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዴት እንደሰለጠኑና እየተገበሩት እንደሚገኙ መመርመር ነበር፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ግብ ላይ ለመድረስ የዓይነታዊ ምርምር ዘዴና የገላጭ ምርምር ንድፍ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎችም ከሮቤ የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ አሰልጣኞችና ሰልጣኞች፣እንዲሁም የተመረጡ የክፍል ሃላፊዎች ሲሆኑ ከአራት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራንና የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ ርዕሰ-መምህራን፣ የወረዳና የዞን መምህራን ልማት ተጠሪዎች፣ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ክፍል ሃላፊ፣ የመምህራን ልማት ተጠሪና የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን ተጠሪ በጠቅላላው ሰባ አራት የጥናቱ ተሳታፊዎች በዒላማ-ተኮር፣ በስርዓታዊና በጠቅላይ ንሞና ስልት ተመርጠዋል፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያ የተመረጡ መሳሪያዎች ደግሞ የክፍል ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን-ተኮር ውይይትና የሰነድ ፍተሻ ነበሩ፡፡ የጥናቱ ግኝትም በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የሚሰጠው የስልጠና ግብዓት ጥሩ ቢሆንም ስልጠናው በማስተማሪያ ሞጁል ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ መሆኑ አሰልጣኞችና ሰልጣኞች እንደተፈለገው ችሎታቸውን አውጥተው እንዲጠቀሙ ያለማድረጋቸው፤ የተከታታይ ምዘናቸውም በሌሎች አካላት ግፊት የሚተገበር መሆኑ፣ ሰልጠኞች የተለያዩ ስራዎችን ሲያቀርቡ ቀደም ሲል የተሰሩትን ስራዎች ገልብጠው እንደሚያቀርቡ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ እንደ ክፍተት ታይተዋል፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ደግሞ የመማሪያ ክፍሎች ምቹ አለመሆንና የመቀመጫዎች ችግር፣ በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ያለማግኘት፣ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ የሆነው የተማሪው መጽሐፍ ተማሪዎችን አሳታፊ ሆኖ ያለመገኘት፣ መርሀ-ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ ያለመኖር፣ የትምህርት ሐላፊዎች ድጋፍ ዝቅተኛ መሆንና የመሳሰሉት ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ እንቅፋት በመሆናቸው አቀራረቡ በአግባቡና በተፈለገው ደረጃ አለመተግበሩን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ለነዚህ እንቅፋቶችም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ደረጃ፣ በትምህርት ቤት ደረጃና የሚመለከተው አካል ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

# ምስጋና

ከሁሉ በፊት አስጀምሮኝ ላስጨረሰኝ፣በጊዜው ሁሉን ውብ ላደረገው እግዚአብሄር ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡ በማስከተል የዚህን ጥናት ርዕስ አቅጣጫ ከማስያዝ ጀምሮ ረቂቁን ጽሁፍ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ደጋግመው በማንበብ በማስተካከልና ቃላቱና ሐረጋቱ ተቃንተው መልዕክቱ ለሌሎች እንዲደርስ ላደረጉልኝና ያለማቋረጥ ገንቢ ምክራቸውን ላልነፈጉኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ጌታቸው አዱኛ ከልብ የመነጨ የአክብሮት ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡ በመቀጠል የዚህን የጥናት ርዕስ አሁን የያዘውን ቅርፅ እንዲይዝና በጥናት ወረቀቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች መልካም ግብዓቶች እንዲኖሩት ላደረጉልኝና ገንቢ ምክራቸውን ላልነፈጉኝ ለዶ/ር ታመነ ኪቲላ የአክብሮት ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠል ለ3ኛ ዲግሪ መርሀ-ግብር ተመዘግቤ ለፍፃሜ እስክበቃ ድረስ የሚያስፈልጉኝን ማንኛውንም የሞራልና የማቴሪያል ድጋፎች ላልነፈጉኝ ቤተሰቦቼ፣ ወ/ሮ ገነት በየነ፣ ሜላት ኤልያስና ናትናኤል ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡ በተለይም የቤቴን ክፍተቶች እንዳላስብ ቤተሰብን በመምራት የጀርባ አጥንት ሆና ስታበረታታኝ ለነበረችው ባለቤቴ ወ/ሮ ገነት በየነ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በተጨማሪም ይህን ጥናት ሳከናውን በማንኛውም ድጋፍ ከጎኔ በመሆን ሲያበረታታኝ የነበረ ወንድሜ አቶ አበራ በለጠ እድሜ ይስጥልኝ ፡፡

ለጥናቱ መጠናቀቅ መረጃ በመስጠትና አስፈላጊውን አቅጣጫ ላመላከቱኝ ለሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ አመራር አካላትና የአፋን ኦሮሞ መምህራን፣ ለአሊ ቢራ ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህርና የአፋን ኦሮሞ መምህርት ንጋቷ፣ ለዜይበላ ትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህርና አፋን ኦሮሞ መምህር ዋጋሪ፣ ለሐውሾ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር በየነ፣ ለኪጵጠቴ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርና የአፋን ኦሮሞ መምህር ከዲር እንዲሁም ለባሌ ዞን፣ ለሲና፣ ለሮቤና ለአጋርፋ ወረዳ ትምህርት መምሪያ ሀላፊዎች እንዲሁም ለኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሐላፊዎች ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ማውጫ ገጽ


አጠቃሎ........................................................................................i
ምስጋና........... ......................................................................ii
የይዘት ማውጫ ..................................................................iii
የሰንጠረዥ ማውጫ...........................................................................x
የስዕል ማውጫ ..................................................................xi
የአባሪዎች ማውጫ.......................................................................... xii

ምዕራፍ አንድ፦ መግቢያ....................................................................1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................................................1

1.2. ሰበበ ጥናት ........................................................................15

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........................................................................17

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................18

1.5 የጥናቱ ገደብ........................................................................19

1.6. የጥናቱ ውስንነት........................................................................20

1.7. የጥናቱ አደረጃጀት........................................................................21

1.8. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍችና ምህፃረ-ቃላት.............................................22

ምዕራፍ ሁለት፦ የኢትዮጵያ ትምህርትና የቋንቋ ፖሊሲ ዳራ..............................25

2.1. የቋንቋና የቤተ እምነት ትምህርት በቅድመ 1908 ኢትዮጵያ ..................25

2.1.1. የኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ትምህርት ...............................25

2.1.2. የቁራን ትምህርት........................................................................27

2.1.3. የሚሲዮኖች ትምህርት ........................................................................28

2.2. የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲ በድህረ 1908...............................................29

2.3. የኦሮሚያ መልካዓ ምድራዊ ገፅታና ህዝቦቿ ..............................................36

**ምዕራፍ ሶስት፡- የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ............................................................42**

3.1. የማስተማሪያ አቀራረቦች ..................................................................................42

3.1.1. የመምህር-ተኮር አቀራረብ ...........................................................................44

3.1.2. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ምንነት ...................................................................48

3.1.2.1. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርሆዎች ...........................................................49

3.1.2.2. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አስፈላጊነት ..........................................................52

3.1.2.3. የተማሪ-ተኮርና መምህር-ተኮር አቀራረብ ልዩነቶች ...................................56

3.1.2.4. የመምህራን አሰለጣጠንና ተማሪ-ተኮር አቀራረብ .......................................57

3.1.2.5. ተማሪዎችና የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ..........................................................63

3.1.2.6. የተማሪ-ተኮር አቀራረብና የተማሪው መጽሐፍ ...........................................67

3.2. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የማስተማሪያ ብልሃቶች .........................................................68

3.2.1. ውይይት ...............................................................................................69

3.2.2. ትብብራዊ የመማር-ማስተማር ብልሃት .........................................................72

3.2.3. ግኝታዊ የመማር-ማስተማር ብልሃት ..........................................................75

3.2.4. በፕሮጀክት የማስተማር ብልሃት .................................................................77

3.2.5. ሚና ጨዋታ ..........................................................................................79

3.3. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንቅፋቶች ............................................................................80

3.3.1. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ባህሪያት ................................................................81

3.3.2. የመምህራን አመለካከት ለውጥ ....................................................................82

3.3.3. ባለ ጉዳዮችን ማሳተፍ ...............................................................................83

3.3.4. የመምህራን ስልጠና እጦት ..........................................................................84

3.3.5. አካባቢና ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች ..................................................85

3.3.6. የትምህርት መሳሪያዎች ለአቀራረቡ አመቺ ያለመሆን ........................86

3.3.7. የጊዜ እጥረት ........................................................................87

3.4. በተማሪ -ተኮር አቀራረብ ላይ የሚነገሩ አሉታዊ አስተያየቶች............................87

3.5. የጥናቱ ጽንሰ-ሀሳቦችና ስልተ-ትወራዊ መሰረቶች ..............................................90

3.5.1.የመማር-ፍልስፍናዎች .......................................................................90

3.5.1.1. የጥንታዊ ሰብዓዊነት ፍልስፍና .....................................................91

3.5.1.2. የመልሶ ማዋቀር የትምህርት ፍልስፍና ..........................................92

3.5.1.3.. የተራማጅነት የትምህርት ፍልስፍና.................................................93

3.5.2. የመማር ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች ..................................................................94

3.5.2.1. የግንባታውያን የመማር- ማስተማር አተያይ ...................................96

3.5.2.2. ሰብአዊ ንድፈ ሀሳብና የቋንቋ መምህር ትምህርት ...........................97

3.6. ጽንሰ-ሀሳባዊ ማዕቀፍ .........................................................................99

**ምዕራፍ አራት፡- የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ ....................................................102**

4.1. የጥናቱ አይነት .........................................................................102

4.2. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ ......................................................................106

4.3. የጥናቱ የመረጃ ምንጮችና የንሞና ዘዴ ..........................................................106

4.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ..............................................................108

4.4.1. የክፍል ምልከታ ...........................................................................108

4.4.2. ቃለ-መጠይቅ ...............................................................................110

4.4.3. የሰነድ ፍተሻ...............................................................................111

4.4.4. ቡድን ተኮር ውይይት.......................................................................112

4.5. የመረጃ አስተማማኝነት ........................................................................113

4.6. የመረጃ ትክክለኛነት ........................................................................114

4.7. የሙከራ ጥናት ........................................................................115

4.8. የሙከራ ጥናት ውጤት ........................................................................115

4.9. የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ቅደም ተከተል ........................................118

4.10. ስነምግባራዊ ሁኔታዎች ........................................................................120

**ምዕራፍ አምስት፡- የመረጃ ትንተና፣ ግኝትና ማብራሪያ........................................122**

5.1. የመረጃ ሰጪዎች ዳራ........................................................................123

5.2. የዕጩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የቅድመ ስራ የስልጠና ግብአት ......124

5.2.1. የኮሌጁ የክፍል ውስጥ አደረጃጀት ...............................................125

5.2.2. የመማር-ማስተማር አተገባበር ........................................................126

5.2.3. የዕጩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አተያይ .............132

5.2.4. የኮሌጁ አሰልጣኞች የስራ ላይ ስልጠና ..........................................134

5.2.5. የአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህራን የግምገማ ስልት .......................136

5.2.6. የተመረጡ የኮሌጅ ኃላፊዎች የተማሪ-ተኮር አተገባበር አተያይ ..........137

5.2.7. የዕጩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ግንዛቤ ...........................146

5.2.8. የፕራክቲከም አተገባበር ..............................................................148

5.2.9. በአሰለጣጠን ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ...........................................152

5.3. የአንደኛ ደረጃ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ብልሃቶች አጠቃቀም-----155

5.3.1. የተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የክፍል ውስጥ አደረጃጀት-------------------155

5.3.2. የአፋን ኦሮሞ መምህራን የመማር-ማስተማር ሂደት አተገባበር........158

5.3.3. በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎች ሚና .......................172

5.3.4. በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የመምህራን የምዘና ስልት ..........176

5.3.5. የተማሪው አፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ዳሰሳ...........................177

5.3.6. የመምህራን የስራ ላይ ስልጠናዎች................................................181

5.3.6.1. የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና በትምህርት ሐላፊዎች አተያይ.186

5.3.6.2. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ በትምህርት ቢሮ ሐላፊዎች አተያይ....................................................................195

5.3.7. በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች.................201

5.3.8. ለአፋን ኦሮሞ መምህራን የተደረጉ እገዛዎች ..................................207

5.4. ማብራሪያና ውጤት ...........................................................................212

**ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች................................................221**

6.1. ማጠቃለያ ..........................................................................................221

6.2. የመፍትሄ ሀሳቦች ...............................................................................226

ዋቢ ጽሁፎች ..........................................................................................229

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ገፅ

ሠንጠረዥ አንድ፡ በጣልያን ወረራ ወቅት የነበረው ኢትዮጵያ የቋንቋ ትምህርት .........31

ሠንጠረዥ ሁለት፡ የመምህር-ተኮርና የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ልዩነቶች .......................56

ሠንጠረዥ ሦስት፡ መረጃ የተሰበሰበባቸው ተቋማት፣ ክፍሎቻቸው፤ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያና የጥናቱ ተሳታፊዎች ብዛታቸው...................123

ሠንጠረዥ አራት፡ በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የሚሰጡ የፕራክቲከም ኮርሶች፣ የሚሰጡበት ዓመት፣ የትምህርቱ ትኩረትና የሚፈጀው ጊዜ....................................................................................149

ሠንጠረዥ አምስት፡ በሀውሾ ትምህርት ቤት በክፍል ምልከታ የታዩ የትምህርት ይዘቶች ..........................................................................................168

ሠንጠረዥ ስድስት፡- በሰባተኛ ክፍል በተማሪው የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የምዕራፎች፣ መልመጃዎችና ይዘቶች ...................................179

## የስዕል ማውጫ

ገፅ

ስዕል አንድ፡-በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርት ሲቀርብ የሚገኙ የእውቀት ደረጃዎች ........ 55

ስዕል ሁለት፡-የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ንድፍ ........ 101

ስዕል ሶስት፡- በኮሌጅ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት አሰጣጥ ........ 127

# የአባሪ ማውጫ

ገጽ


አባሪ አንድ፡- የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ ..........247

አባሪ ሁለት፡-ከሮቤ መምህራን ትምህር ኮሌጅ ዲን ጋራ የተደረገ ቃለ-መጠይቅና

መልስ ናሙና ..........250

አባሪ ሶስት፡- በሮቤ/መ/ም/ት/ኮ የአካዳሚክ ም/ዲን ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ ..........252

አባሪ አራት፡-የአፋን ኦሮሞ ትምህርት በኮሌጅ ውስጥ የሚደረገው አሰለጣጠን ..........255

አባሪ አምስት፡-በሮቤ መ/ ት/ ኮሌጅ የሶስተኛ ዓመት የአፋን ኦሮሞ ዕጩ መምህራን

የቡድን ተኮር ውይይትና ውጤቱ ..........259

አባሪ ስድስት፡- በኪጰጠቴ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር ጋር

የተደረገ ቃለ-መጠይቅ ..........263

አባሪ ሰባት፡- በኪጵጠቴ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ከ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ጋራ የተደረገ

የቡድን ተኮር ውይይት ..........268

አባሪ ስምንት፡- ምልከታ የተደረገባ---1ሪያ ክፍሎችና ተማሪዎች ናሙና ..........271

አባሪ ዘጠኝ ፡-በዜይበላ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ- መጠይቅ ..........273

አባሪ አስር፡-በሐውሾ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ ..........274

አባሪ አስራ አንድ፡- ለባሌ ዞን የመምህራን ልማት ኂላፊ የቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ

የአፋን ኦሮሞ ትርጉም፣ ..........278

አባሪ አስራ ሁለት፡-የ7ኛ ክፍል የተማሪው አፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ግምገማ ..........279

አባሪ አስራ ሶስት፡-ለትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅ ..........286

አባሪ አስራ አራት፡- የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት የትብብር ደብዳቤ ..........287

አባሪ አስራ አምስት፡- ከባሌ ዞን የተፃፈ የትብብር ደብዳቤ የአፋን ኦሮሞ ትርጉም ..........288

አባራ አስራ ስድስት፡- በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተማሪዎች ውጤት መመዝገቢያ ቅጽ ..........289

አባሪ አስራ ሰባት፡- የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪዎች ተከታታይ ምዘና መመዝገቢያ ቅጽ ..........290

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለጥናቱ ክንውን መሠረት ሊሆን የሚችል የጥናቱ ዳራ ይቀርባል፡፡ ቋንቋ መማር-ማስተማርን አስመልክቶ በምርምር የተገኙ መረጃዎችና ሀሳቦች ይገለፃሉ፡፡ ቀጥሎም ጥናት አቅራቢውን ለዚህ ጥናት ያነሳሱ ምክንያቶች ሰበበ ጥናት በሚለው ርዕስ ስር ይብራራል፡፡ እንደዚሁም በጥናቱ ዓላማ ስር ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች ይገለፃሉ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሙ ችግሮች ከተፈቱ የትኛው አካል የበለጠ እንደሚጠቀም የጥናቱ አስፈላጊነት በሚለው ርዕስ ስር ይብራራል፡፡ የጥናቱ ወሰን ይህ ጥናት በባሌ ዞን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞ የሚያስተምሩ መምህራንና ስልጠና የወሰዱበት የሮቤ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ላይ ብቻ ውስጥ የተወሰነ እንደሆነ የተገለፀበት ነው፡፡ ከዚህ ውጪም ጥናቱ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጋር የተያያዙ ብዙ ጉዳዮችን መዳሰስ ሲገባው ያልዳሰሳቸውንና መሸፈን የሚገባቸው ቦታዎችን ያለመሸፈኑ የጥናቱ ውስንነት በሚለው ርዕስ ስር ተብራርቷል፡፡ እንደዚሁም የጥናቱ አደረጃጀት፣ የቃላትና ጽንሰ-ሀሳቦች ፍች፣ ትኩረት የሚሰጥባቸው የምዕራፉ ይዘቶች ናቸው፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ተማሪዎች በቋንቋ አጠቃቀማቸው በአንደበተ-ርቱዕነትና በትክክለኛነት (Fluency and Accuracy) በተሻለ መንገድ ከሌሎች ጋራ መግባባት እንዲችሉ በተፈጥሮ ካገኙት ስጦታ በተጨማሪ በትምህርት ቤት ሊማሩት ይገባል፡፡ በትምህርት ቤት የቋንቋ መማር-ማስተማር ሲታሰብ ደግሞ ቅድሚያ የትኛውን ቋንቋ? የሚለው ጥያቄ ሊመለስ ይገባል፡፡

እንደ Stern (1983) አገላለጽ የአፍ-መፍቻ ወይም የመጀመሪያ ቋንቋ፣ ሁለተኛ ቋንቋ፣ የውጭ ቋንቋ የሚሉ ስያሜዎችን በመነጣጠል በተለያየ ባህሪያቸውን ያመለክታሉ፡፡ የመጀመሪያ ቋንቋ ማለት በመጀመሪያ ንግግር የጀመርንበት፣ አፋችንን የፈታንበት፣ የእናት ቋንቋ፣ ጠንካራ ቋንቋ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ዓይነቱ ቋንቋ ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ ሊገኝ የሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዘኛ አፉን የፈታ ሰው ከአካባቢውና በትምህርት የሚያጋጥመውን ፈረንሳይኛ መናገር ከቻለ እንግሊዘኛ የመጀመሪያ ቋንቋው ሲሆን ፈረንሳይኛ ሁለተኛ ቋንቋው ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋ ደግሞ

መጀመሪያ ከለመድነው ቋንቋ ቀጥሎ ከአካባቢ ተጋልጦ ወይም በትምህርት የሚገኝ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ መሠረት ፈረንሳይኛ በእንግሊዘኛ ቋንቋ አፉን ለፈታ ሰው ሁለተኛ ቋንቋው ይሆናል፡፡

ሌላው Stern (1983) ያስረዱት በሁለተኛና በውጭ ቋንቋ መካከል ያሉትን አንድነትና ልዩነት ነው፡፡ ሁለቱም ቋንቋዎች ከአፍ መፍቻ ቋንቋ በኋላ ከመገኘታቸው አንፃር ስያሜያቸው ሁለተኛ ቋንቋ እንዲባሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ልዩነታቸው ደግሞ የውጭ ቋንቋ ለትምህርት ወይም ለአንድ ዓላማ ሲባል መጀመሪያ ከተለመደው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ቀጥሎ የሚማሩት ነው፡፡ ሁለተኛ ቋንቋም ከአካባቢ ተጋልጦ ወይም በትምህርት ሊገኝ የሚችል ነው፡፡ ነገር ግን የውጭ ቋንቋን በአንፃራዊነት የመጀመሪያ ቋንቋ ያልሆነ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ እንግሊዘኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ለሆኑ አገሮች የውጭ ቋንቋ ተብሎ የሚጠራው ለዚያ አገር ተፈላጊው ፈረንሳይኛ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፡፡ ለአንድ አገር የውጭ ቋንቋ የሆነው ለሌላው አገር ደግሞ የአፍ መፍቻ ወይም ሁለተኛ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፡፡

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ቋንቋዎች ሁሉ በመልመድ ወይም በመማር ሊገኙ እንደሚችሉ Krashen (1981ና 1985) ያብራራሉ፡፡ እንደ Krashen (1981ና 1985) ገለፃ "ቋንቋ መልመድ" የሚባለው አንድ ሰው ተፈጥሯዊ በሆነ የተግባቦት ሂደት ውስጥ ቋንቋን ከአካባቢ የሚለምደው ሲሆን ለመዳውም ሆን ተብሎና በንቃት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን አይደለም፡፡ ይህ በአብዛኛው የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚዳብርበት ሂደት ነው፡፡ "ቋንቋ መማር" ግን በንቃት ላይ የተመሰረተና በይሁነኝ የሚተገበር ሲሆን በመደበኛ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ የቋንቋን ህግጋት በዝርዝር በማጥናት የሚከናወን ሂደት ነው፡፡ ሁለተኛና የውጭ ቋንቋዎች በዚህ ትምህርት ሂደት ሊገኙ የሚችሉ ናቸው፡፡

እንደ Stern (1983) አገላለፅ ቋንቋ መማር ማለት የቋንቋ ክሂሎችን ማወቅና ማጎልበትን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ማለት የራሱ የሆነ የትምህርት መርሀ-ግብር ወጥቶለት፣ ትምህርት ቤት በመግባት መደበኛ በሆነ መንገድ የቋንቋውን ህግጋት ስርዓት ባለውና በሙሉ ንቃት ወይም በይሁንታ ማወቅ ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ቋንቋ መማር በቋንቋው የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የመፃፍና የማንበብ ክሂሎችን መገንዘብ ማለት ነው፡፡ የአፍ መፍቻም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋ መደበኛ በሆነ መንገድ

የመማር-ማስተማሩ ሂደት የቋንቋውን ህግጋትና ውስጣዊ መዋቅር አሳውቆ ለተግባቦት ለማብቃት ትልቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ለዚህም ሲባል በተለያዩ የቋንቋ ማስተማር ዘዴዎች በመጠቀም በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲሰጥ ቆይቶ አሁን ካለበት ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ ላይ ተደርሷል፡፡ እንደሌሎች ዘዴዎች ሁሉ የተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የለውጥ ሂደትም ረጅም እድሜን አስቆጥሯል፡፡ በRichardsና Rodgers (1986) አገላለጽ የማስተማሪያ ዘዴዎቹም ብዙ ሲሆኑ የመለወጥ ሂደታቸውም በአንዱ ዘዴ ደካማ ጎን ላይ ማሻሻያዎች እየተተከሉ አሁን ዘመናዊ እስከ ተባለበት ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ላይ ዘልቋል ፡፡

የተማሪ-ተኮር አቀራረብም የዚሁ የተግባቦታዊ የቋንቋ የማስተማሪያ አቀራረብና የዘመኑ የለውጥ ሂደት ውጤት ነው፡፡ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ በፊት የነበሩት የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች በአብዛኛው የመምህራን የበላይነት የሚታይባቸውና ተማሪዎችን በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የማያሳትፉ እንደሆኑ የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ (Tudor፣1996 ፤ Mccombsና Whisler፣1997)፡፡ በምሁራኑ እሳቤ የቋንቋው ትምህርት ገንቢ ሊሆን የሚችለው ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ውስጥ በንቃት እየተሳተፉ እውቀታቸውንና እምቅ ችሎታቸውን ከነበራቸው ልምድ ጋራ እያዋሀዱ በራሳቸው ጥረት ሲማሩ ነው፡፡ ከመምህራን ብቻ ወደ ተማሪዎች የሚተላለፍ የአንድ አቅጣጫ የመረጃ ፍሰት ግን ብቻውን ተማሪውን በቂ ዕውቀት ያስጨብጣል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በፍጥነት ከተፈለገው የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ግብ ላይ መድረስ እንዲችሉ የቋንቋ መማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪን ማዕከል በሚያደርገው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች በመምህራቸው ላይ ብቻ ጥገኛ አይሆኑም፡፡ Jones (2007) እንደሚያብራሩት ለትምህርቱ ገለፃ፣ ለሚሰሩት ተግባራት ፍቃድ፣ ለእርምት፣ ለምክር ወይም ለሽልማት መምህሮቻቸውን ሊጠብቁ ይችላሉ እንጂ የተለያዩ ተግባራትን ለመስራት መምህራንን ለመጠበቅ አይገደዱም፡፡ የሚሰጣቸውን ስራዎች ለመስራት በተለያዩ የማስተማር ብልሃት እርስ በርሳቸው ሀሳብ በመቀባበልና በመግባባት ያከናውናሉ፤ አንዱ ተማሪ ለሌላው ዋጋ ይኖረዋል፡፡እንደ ውይይት፣ ክርክር ሚናጨዋታ ወዘተ የመማር ብልሃቶች ላይ ብቻ የመምህራንን እገዛ ይሻሉ፡፡ ስራዎቻቸውንም በግል፣ በጥንድ፣ በቡድንና ከሙሉው ክፍል ጋር ያከናውናሉ፡፡ በአጭሩ

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርቱ ሲቀርብ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በነፃነትና የራሳቸውን ሀሳብ እየገለፁ በንቃት በመሳተፍ ይማራሉ።

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር የተለያዩ ፋይዳዎች እንዳሉት የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ። ለምሳሌ እንደ Waticnessና et al (2007) ገለፃ በአእምሯዊ ብቃት ማለትም (Cognitively) በንቃት ማሰብን፣ የቀደመ ዕውቀት መገንባትንና አዳዲስ ስያሜዎችን ማምጣትን፣ ከባህሪ አንፃር (Behaviourally) በንቃት መስራትንና ነገሮችን አስተውሎ ማከናወንን፣ ከማህበራዊ መስተጋብር አንፃር ደግሞ (Socialy) ከሌሎች ጋራ ተባብሮ መስራትንና መተጋገዝን ያካትታል። በምሁራኑ አገላለጽ በጥቅል ከሰፈሩት እነዚህ ሀሳቦች በተጨማሪ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ) በአጭር ጊዜ ተጎናፅፈው በነባራዊው ማህበራዊ አውድ ውስጥ መገልገል እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በግንባታውያን ንድፈ-ሀሳብ (Constructivist Theory) ተጠንስሶ በመማር--ማስተማር ሂደት ውስጥ ተግባራዊ እየሆነ የመጣ ትውር ነው። እንደ Xiaome (2010) ማብራሪያ የግንባታውያን ንድፈ-ሀሳብ ተማሪዎች የራሳቸውን ልምድና የቀደመ እውቀት በመጠቀም በጥረታቸው በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እየተሳተፉ በሚያገኙት ትምህርት ራሳቸውን ይገነባሉ። ትምህርት ከመምህራን ወደ ተማሪዎች የሚተላለፍ መረጃ ሳይሆን ተማሪዎች በራሳቸው ዕውቀት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት ተሳትፈው የሚያገኙት ነው። በዚህ መንገድ እየተሳተፉ ለመማር እንዲችሉ መምህራን ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። ይህም የትምህርት ግብዓት የሚገኘው የሚቀርብላቸው ይዘት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚሰጥ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ መምህራን የቋንቋ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እውቀት የሚገበዩበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት በንቃት እንዲሳተፉበት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በአገራችን የቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደትን በተመለከተ ከኢትዮጵያ የትምህርት ታሪክ ጋር አያይዘን ማጤኑ ተገቢ ነው። በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የሐይማኖት ትምህርቶች ይሰጡ እንደ ነበር ብዙ ተመራማሪዎች አረጋግጠዋል። እንደ Tekeste (1990)፣ Teshome (1979)ና Teshome (2006) ማብራሪያ ከዚህ አንፃር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ትምህርት ቅድሚያውን ይይዛል። ከክርስትና እምነት መግባት በመቀጠል የእስልምና ሐይማኖትም በ7ኛው ክፍለ-ዘመን ተከተለ። ከእነዚህ በተጨማሪ ከአውሮፓ የመጡ ወንጌላውያን በስፋትም ባይሆን የካቶሊክ ትምህርት ይሰጡ ነበር (Hailegebrel፣ 1976)። እነዚህ የሀይማኖት ትምህርቶች በወቅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በሰፊው ቢታዩም Amare(1968)፤ Girmaና ሌሎች(1974) የመደበኛነት ስርዓት ያለመያዛቸው፣ ጥቂቶች ብቻ የሚማሩት መሆናቸው በተለይም ሴቶችን የማያሳትፉ መሆናቸው፣ ረጅም ጊዜ የሚወስዱ መሆናቸው፣ በጥልቅ ማሰብንና ለውጥን የሚሹ አለመሆናቸውና ሽምደዳ ላይ ማተኮራቸው፣ ከእምነት ነፃ ያለመሆናቸውና በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ያለማተኮራቸው ለዘመናዊ ትምህርት ወደ አገሪቱ መግባት በምክንያትነት የሚጠቀሱ ናቸው። በአጠቃላይ የመማር-ማስተማር ዘዴዎቹ ሲታዩ ከመምህራን ወደ ተማሪዎቹ እውቀት የሚሸጋገርበት፣ የተማሪዎቹ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መሳተፍ ዝቅተኛ የሆነበት፣ ተማሪዎች የሚሰጣቸውን ትምህርት ብቻ የሚቀበሉበት፣ በመምህራንና ተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት ኢ-ዲሞክራቲክ የሆነበት የትምህርት ስርዓት እንደ ነበር ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን ገለፃ እንረዳለን። በዚህ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች በሚገባ ተምረዋል ተብለው ሊፈረጁ የሚችሉት ያንን የቀረበላቸውን ትምህርት ከዳር እስከዳር በሽምደዳ ከተወጡት ብቻ ነው። ያም ሆነ ይህ በዚህ ዘመን የነበረው የትምህርት ስርዓት ለኢትዮጵያ ዘመናዊ የትምህርት ስርዓት መሰረት ሆኖ አልፏል።

የመጀመሪያው ዘመናዊ የመንግስት ትምህርት ቤት በሚኒሊክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ1908 ዓ.ም ሲጀመር የቋንቋ ትምህርት የውጭ ቋንቋን በማስተማር ላይ የተመሠረተ ነበር። ቋንቋዎቹም ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዘኛ፣ ጣልያንኛና አረብኛ ሲሆኑ የግዕዝ መምህር ከተቀጠረ በኋላ በ1919 ላይ አማርኛንም በዚያው እንዲያስተምሩ ተደረገ። ከዚያ በኋላ በ1941 ዓ.ም አፄ ሀይለስላሴ "በራሳችን ቋንቋ ትምህርቱ ይሰጥ፤ በራሳችንም ቋንቋ እናንብብ፤ እንፃፍም" ብለው በይፋ ተናገሩ። ይሁን እንጂ 1947-1958 ዓ.ም የትምህርት መማሪያ ቋንቋ እንግሊዘኛ ሆኖ አማርኛ ደግሞ እንደ አንድ ትምህርት መሰጠት ሲጀምር ቀስ በቀስ በ1958 የ1ኛ ደረጃ መርሀ-ትምህርት (syllabus) በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ እንደ አንድ ትምህርት እንዲሰጥ ተደረገ (Bloorና wondsen፣ 1996፤ ትምህርት ሚኒስቴር ፣1964)።

ሂደቱ በዚህ እንዳለ በ1930 ራስ ተፈሪ ሀይለስላሴ ተብለው ሲነግሱ የመጀመሪያው የቋንቋ ፖሊሲ በህገ-መንግስት ተዘጋጅቶ ቀረበ፡፡ ህገ-መንግስቱ ስለቋንቋ ብሄራዊነት (National language) የገለፀው ነገር ባይኖርም የተፃፈው ግን በአማርኛ ነበር (Bloorና wondsen 1996 )፡፡ ይህ ሲባል በኢትዮጵያ ውስጥ እስከአሁን ድረስ የቋንቋ ፖሊሲ ባይኖርም በዚያ ወቅት ህገ-መንግስቱ በአማርኛ መፃፉ ታሪካዊ እንዳደረገው ያመለክታል፡፡

በተጨማሪ Cohen (2000)ና McNab (1989) እንደገለፁት በዚህ ወቅት የተዘጋጀው ህገ-መንግስት በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ቋንቋዎችን እኩልነት በማሰብ የተዘጋጀ ፖሊሲ እንደነበረና በዚህም በምኒሊክ ጊዜ ከነበረው ፖሊሲ የተሻለ ሁኔታ እንደ ነበር ይገልፃሉ፡፡ የፖሊሲው ተግባር ከብሄራዊ አንድነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ መንግስት ብሄራዊ እምነትን፣ ባህልና ቋንቋን በማመልከት አንድ አገር፣ አንድ እምነትና አንድ ቋንቋ ባለቤትነት እንዲሰፍን በማድረጉ ፖሊሲው ከአማርኛ ቋንቋ በስተቀር አንዱንም አገር በቀል ቋንቋ የሚያጎለብት አልነበረም፡፡ ነገር ግን ጣልያን ኢትዮጵያን በወረራ ከያዘበት ከ1935–1941 የብሄር ብሄረሰቦችን ቋንቋ በመጠቀም የቋንቋ ትምህርቱ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሰጥ ተፈቀደ፡፡ በዚህ ዘመን በክፍል ውስጥ ሲሰጥ የነበረው የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ በምን ዓይነት ዘዴ እንደሆነ በይፋ የተገለፀ መረጃ ባይኖርም ከላይ እንደተጠቀሰው ከመምህራን ወደ ተማሪዎች የሚተላለፍ ዕውቀት ላይ ብቻ የተመሰረተው የመምህር -ተኮር አቀራራብ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

አጼ ሐይለስላሴ ከስደት ተመልሰው በ1941 ስልጣናቸውን እንደ ገና እንደተረከቡ የመንግስታቸው የቋንቋ ፖሊሲ ለሌሎች የአገሪቱ ቋንቋዎች ትኩረት አለመስጠትን የሚያመላክቱ ሂደቶች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የአገሪቱም የስራ ቋንቋ አማርኛ መሆኑንና በትምህርት ዘርፍም ለ1ኛ ደረጃ በትምህርት ቋንቋነት እንዲሰጥ መመሪያ መስጠታቸውን McNab (1989) ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ ዘመን ያገለግሉ ነበሩት ቋንቋ የማስተማር ስነ-ዘዴዎች የመምህራን የበላይነት የሚታይበትና ተማሪዎችን በትምህርቱ ሂደት የማያሳትፍ እንደ ነበሩ የተለያዩ የአገር ውስጥ ምሁራን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም፣ ምንም እንኳን ትምህርቱ በመምህር-ተኮር አቀራረብ ቢሰጥም በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎች ላይ ያሉ የተማሩ ሰዎች የአገሪቱን ችግሮች ለመፍታት ጥረት ሲያደረጉ እንደነበር ታሪክ ያወሳናል፡

የደርግ መንግስት ወደ ስልጣን እንደ መጣ የሶሻሊስት የትምህርት ስርዓትን እየተገበረ በብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋ መብት መከበር ላይ በመጠኑም ቢሆን መሻሻል አሳይቷል። ደርግ የሶሻሊዝም ርዕዮት የአንድ ብሄርና እምነት ተጽእኖ እንደሌለበት፣ ማንም ሰው በቋንቋው መማርና ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸውን ተወካይ በመምረጥ አካባቢያቸውን ማስተዳደር እንዲችሉ የሚደግፍ አዋጅ ነበረው። የቋንቋ ፖሊሲውም የብሄር ብሄረሰቦችን ቋንቋ ለትምህርት ማዋል የሚል ነበር። ለዚህም ማረጋገጫው ማህይምነትን ለማጥፋት በሚደረገው ዘመቻ አማርኛን ጨምሮ በአስራ አምስት የብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎች የሳባ ፊደልን በመጠቀም ትምህርት እንዲሰጥባቸው መደረጉ ነው። የቋንቋዎቹም ምርጫ ብዙ ህዝብ (90%) የሚናገረው ቋንቋ ተብሎ በBender (1976)ና McNab (1989) በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ወላይታ፣ ሶማሌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጢ፣ ትግሪኛ፣ ትግረ፣ ሲዳማ፣ ሳሆ፣ ግዴዎ፣ አፋር፣ ከፋ፣ ሞቻና ኩናማ ተመርጠው ለመሰረተ-ትምህርት አገልግሎት ውለዋል። ይሁን እንጂ በመደበኛ ትምህርት ውስጥ ከአማርኛ ቋንቋ በስተቀር ለሌሎች የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ትኩረት አልተደረገም። ከማስተማሪያ ዘዴዎች አንጻር በሁለቱም ያለፉት ስርዓቶች እንደ ትምህርት ሚኒስቴር (1994) የመምህራን የበላይነት ሲገለጽበት ስለነበር ተማሪዎች ከመምህራን የሚተላለፈውን እውቀት ብቻ የሚቀስሙበት የትምህርት ስርዓት እንደሆነ ያሳያል። በአጭሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ወይም ተማሪን አሳታፊ የሆነ የቋንቋ ማስተማሪያ አቀራረብ አልነበረም።

የደርግ ስርዓት በኢህአዴግ መንግስት ሲተካ ከዚያ በፊት የነበረው የትምህርት ስርዓት በአዲስ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ ተተካ። በስልጠና ፖሊሲው ሰነድ ላይ የሰፈረው ጭብጥ እንደሚያትተው ያለፈው ዘመናዊው የትምህርት አቀራረብ የመምህራን የበላይነት ያለበት ዘዴ መሆኑ፤ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የማይጠብቅ መሆኑ፣ የብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎች ላይ ትኩረት ያለ ማድረጉ፣ የማህበረሰቡን ችግሮች የማይፈታ ስርዓትን የተከተለ መሆኑ አዲስ የትምህርት ፖሊሲ እንዲቀረጽ መንስዔ ሆነ። እንደ ትምህርት ሚኒስቴር (1994፡3) አገላለጽ፡-

> *የሀገራችን ትምህርት ሁኔታ በዓላማ በይዘት በአቀራረብ በሥርጭት በግባትና በሂደት እንዲሁም በውጤት ሲታይ ተማሪዎች ተገቢውን ትምህርት ቀስመው የችግር ፈቺነት ባሕርይንና ችሎታን እንዲያጎለብቱ አስችሎአቸዋል ለማለት*

> *አያስደፍርም፡፡ የሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል ተገቢውን ባህል በማዳበር ሳይንስና ቴክኖሎጂን በህብረተሰቡ አስሰርፆ አካባቢያቸውን ለመንከባከብ ለማልማትና ማኅበር ኢኮኖሚያዊ ተሳትፏቸውን ለማጠናከር እንዲያስችላቸው ያደረገው አስተዋጽኦ ጎልቶ አልታየም፡፡*

ሰነዱ ለዚህም የትምህርት ስርዓት ለውጥ እንዳስፈለገና ለውጡም ከሚያተኮርባቸው ጉዳዮች አንዱ የመምህራን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት አተገባበር መሆኑን ያስረዳል፡፡ በዚህም መሠረት የቀደሞው የመምህር-ተኮር ማስተማሪያ አቀራረብ ተማሪዎችን በራሳቸው ትምህርት ውስጥ እያሳተፈ በዕውኑ ዓለም የሚገጥማቸውን ችግሮች እንዲፈቱ የሚረዳ ባለመሆኑ በተማሪ-ተኮር የመማር-ማስተማር አቀራረብ እንዲቀየር መደረጉን ያረጋግጣል፡፡ የስርዓተ-ትምህርቱ ለውጥ ዋነኛ ምክንያትም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከላይ የተገለፁትን ችግሮች ሁሉ የሚፈታና የመምህራን ዕውቀት ብቻ የማይጠበቅበት፣ ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት ውስጥ የሚሳተፉበት፣ የችግር ፈቺ ትምህርት የሚቀሰምበትና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የማይገድብ አቀራረብ መሆኑን ሰነዱ ያብራራል ፡፡ በአጠቃላይ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎችን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት በማሳተፍ በፍጥነት ከተፈለገው የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ላይ ያደርሳል ተብሎ ለውጡ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር (1996) እንደገለፀው፣ ከፍትሐዊ አቅርቦት፣ ከጥራትና ተገቢነት አኳያ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ለትምህርቱ እድገት ከፍተኛና ሰፊ ግቦችን አስቀምጧል፡፡ ከሁሉም በላይ ለመምህራን ስልጠና ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በንቃት የሚማሩበት (Active learning)፣ ይዘቱም ችግር ፈቺ የሆነና ተማሪን ማዕከል ያደረገ የመማር-ማስተማር ዘዴዎች የሰፈነበት የትምህርትና የስልጠና አቀራረቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ልዩ ልዩ ስልቶች እንደተነደፉና በአገራችን ውስጥ ያለው የትምህርት ስርዓት አቅጣጫ ተማሪን ያማከለ እንደሆነ አመላክቷል፡፡

አሁን ያለው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ ተግባራዊነት ለመምህራን ስልጠናና በማስተማሪያ መሳሪያዎች አቀራረብ ላይ ለውጥ በማድረግ ተማሪዎችን አሳታፊ እንዲሆን ተደርጓል (ትምህርት ሚኒስቴር፣1994)፡፡ ከዚህ ሰነዶች ውጪም ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በክፍል መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ እየተተገበረ መሆኑን የተለያዩ የአገራችን

ምሁራን በጥናቶቻቸው ገልፀዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ Fisseha (2001)፣ Desta (2001)፣ Derebssa (2006)፣ Tirualem (2003)፣ Taye (2008)፣ Wuduና ሌሎች(2009)፣ Solomon (2009)፣ Yewulsew (2009)፣ Moges (2010)ን መጥቀስ ይቻላል፡፡

አጥኚዎቹ እንዳብራሩት በኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት ውስጥ በስራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ያለው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በዩኒቨርቲዎች፣ በኮሌጆች፣ በአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ማስተማሪያነት እየተሰራበት ቢገኝም የተለያዩ የአተገባበር ችግሮች እንዳሉበት ይፋ አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ Tsegaye (2001) "የተማሪ-ተኮር ትግበራ በጌዴዮ ዞን በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አካሂደው ተማሪዎች በአማራጭነት በትምህርታቸው ውስጥ በአግባቡ አለመሳተፋቸውንና መምህራን ደግሞ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎቻቸውን ችሎታ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ መረዳት አለመቻላቸውን አሳይቷል፡፡ እንደዚሁም ሙሉጌታ (1996) "የተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ የሰርቲፊኬት መርሀ-ግብር እንደታየው"፣ ኤልያስ (1997) "በአዳማና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር" በሚል ርዕስ ባደረጉት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸው የአተገባበር ችግሮች እንዳሉበት ጠቁመዋል፡፡

የኤልያስ (1997) ጥናት አሁን እየተሰራ ካለው ጋር ሲነፃፀር የመጀመሪያው በአዳማና ሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ መፈተሽ ነበር፡፡ ይህ ጥናት ግን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ባሌ ውስጥ በሚገኙ በተመረጡ አራት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፋን ኦሮሞን በሚያስተምሩ መምህራን ላይ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ቀደምቱም ሆኑ ይህ ጥናት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ ማተኮራቸው ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል፤ይሁን እንጂ የቀድሞው በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ላይና በአማርኛ ቋንቋ ላይ የሚያተኩር መሆኑና ይህኛው ጥናት ደግሞ በባሌ ዞን ውስጥ የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን በሚያስተምሩ መምህራን ላይና በክልሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ማተኮሩ የተለያዩ ያደርጋቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ጥናት ለክልሉ ሁለተኛ ቋንቋ በሆነው አማርኛ ላይ የተሰራ ሲሆን ሁለተኛው ለክልሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ በሆነው አፋን ኦሮሞ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በአፍ መፍቻና ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ መካከል ደግሞ ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ በመስኩ ጥናት ያቀረቡ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

ከዚህ ጥናት በፊት በዓለም ላይ ወይም በአፍሪካ እንዲሁም በአገራችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ዙሪያ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ቀጥሎ እነዚህን በውጭ፣በአፍሪካና በአገር ውስጥ የተሰሩትን ጥናቶች ለአብነት እንመለከታቸዋለን ፡፡

ከአገር ውጪ ከተደረጉት ጥናቶች ስንጀምር የJohnsonና Johnson (1989) ተጠቃሽ ነው፡፡ በጥናታቸው ውስጥ የገለፁት ጭብጦች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በራሳቸው እየተነሳሱ እንዱ ከአንዱ ጋር በመስማማት ጥምረት ፈጥረው በትብብር መስራት ይችላሉ ፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚማር ከሆነ ያ ቡድን ከፍተኛ ነጥብ ከማስመዝገብ አልፎ በትብብር በመስራቱ ማህበራዊ ክህሎትን ይጎናፀፋል፡፡ በአንፃሩ በመምህር-ተኮር አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ አብሮ በመስራት ላይ ስለማይተባበሩ ጊዜያቸውንም በጋራ ስራ ላይ ስለማያሳልፉ እርበርስ ያላቸው ግኑኙነት ደካማ ነው፤ውጤታቸውም ደካማ ይሆናል፡፡

የመምህር-ተኮር አቀራረብ የመማሪያ ክፍል የትምህርት አሰጣጥ ቋሚና በገለፃ እንዲሁም በግል ስራ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በ Johnsonና Johnson (1989) ጥናት በሁለት የተማሪ ቡድኖች በተማሪ-ተኮረ አቀራረብና በመምህር-ተኮር አቀራረብ ተመሳሳይ ይዘቶችን ተምረው የመገንዘብ መጠናቸው ተለያይቷል፡፡ በጥናት አቅራቢዎቹ አገላለጽ በመጀመሪያው የT-test chart ገለፃ ሁለቱም ቡድኖች የመጀመሪያ ፈተና ወስደው በማዕከላዊ ውጤታቸው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የተማሩት በውጤት ተሽለው ተገኝተዋል፡፡ ቀጥሎ አንዱ ቡድን በተማሪ-ተኮር አቀራረብና ሌላኛው ቡድን ደግሞ በመምህር-ተኮር አቀራረብ ተመሳሳይ ይዘቶችን እንዲማሩና ተመሣሣይ ፈተና እንዲወስዱ ተደርገው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የተማሩት ቡድኖች ከፍተኛ ነጥብ ማስመዝገባቸውን አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመማር-ማስተማር ብልሃት የቡድን ስራና በጨዋታ በመሆኑ የትምህርቱ አሰጣጥ ቀላል እንደነበር አመልክተዋል፡፡

Johnsonና Johnson (1989) በተጨማሪ ያከናወኑት ጥናት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲማሩ የነበሩትን በመምህር-ተኮር፣ በመምህር-ተኮር አቀራረብ ሲማሩ የነበሩትን ደግሞ

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዲማሩ ሲደረግ በመምህር-ተኮር አቀራረብ ሲማሩ ለነበሩት የቡድን ስራን ለመስራትና በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ለማሳተፍ አስቸጋሪ ሆነባቸው፡፡ በሂደት ግን በተለያዩ ስልጠናዎች በአቀራረቡ በአግባቡ እንዲማሩና ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው ተደርጎ እንደገና ውጤታማ እንዳደረጋቸው ከተማሪዎቹ አረጋግጠዋል፡፡

ሌላው የHuberና Roth (2013) በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ የተደረገው ጥናት ነው፡፡ እንደጥናት አድራጊዎቹ አገላለጽ በጀርመን የትምህርት ስርዓት ውስጥ የግለሰቦች ዕድገትና ራስን ማረጋገጥ (Self actualization) እንዲሁም ግላዊ ኊላፊነት ዋነኛው ማግኛ መንገድ በትምህርት ግብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ምክንያቱም የትምህርቱ ተግባራት ግለሰቦች በህይወታቸው ዘመን ለሚያገኙት እድገት ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተማሪዎች ህይወት ላይ አሻራውን ስለሚያሳርፍ በክፍል ውስጥ በችግር-ፈቺ ዘዴ ተምረው በህይዋታቸው ዘመን የሚያጋጥማቸውንም ተግዳሮቶች ተጋፍጠው የማሸነፍ እድል ያገኛሉ፡፡ በመሆኑም ጥናት አቅራቢዎቹ ትምህርት ቤቶች ይህን የማስተማር አቀራረብ በሰፊው እየተገበሩት እንደሚገኙ አመልክተዋል፡፡ ጥናት በተደረገባቸው ትምህርት ቤቶችና በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው የመማር ብልሀት የቡድን ውይይት ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን በቡድን መማር፤ በግኝታ መማር፤ በፕሮጀክት መማርና ክፍት የመማር ሁኔታም (open learning situations) ሲተገበሩ ይታያል፡፡ እነዚህም ብልሃቶች ለተማሪዎቻቸው ነፃነት ስለሚሰጡ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛሉ፡፡

በአፍሪካም ሌሴቶ ቪክቶሪያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በ"Mamonaheng (2007) የተደረገው ጥናት ከሴሴቶና "ከእንግሊዘኛ ቋንቋ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር የትኛው ቋንቋ የበለጠ ተመራጭ ነው?" የሚል ጥናት ተካሂዷል፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ከሁለቱ ቋንቋዎች ተማሪዎች የትኛውን ቋንቋ ይመርጣሉ? ለምንስ ይመርጣሉ? ሁለቱን ቋንቋዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ ምን ዓይነት ዘዴዎችን ይተገብራሉ? መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሁለቱን ቋንቋዎች ሲያስተምሩ ምን ዓይነት የትምህርት መርጃዎችን ይጠቀማሉ? በዚህ ስር መምህራን በዚህ የተማሪ-ተኮር የትምህርት መርጃ ሲያስተምሩ ምን ዓይነት ፋይዳዎችን አግኝተዋል? ምን ዓይነት

ክህሎትን ተጎናጽፈዋል? ከመምህራንና ተማሪዎች መረጃ ተደግፎ ማየት፤ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ምን ያህል የማስተማሪያ ማቴሪያሉን ሸፍኖታል? መምህራን ምን መረጃ አላቸው?፣በመምህራንና ተማሪዎች የሚጠቀም ሌላ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር ዘዴ ይኖር ይሆን? የሚሉና ሌሎች መሰል መሠረታዊ ጥያቄዎች ነበሩ፡፡ በመጨረሻም የተለያዩ የመፍትሄ ሃሳቦች ተሰጥተው አብቅቷል፡፡

ከአገር ውስጥ አጥኚዎችም ጥቂቶቹን ለአብነት ስንመለከት፣ ለማ (2006*)* "የተማሪ-ተኮር ዘዴ አተገባበር በመንግስት አንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ በምስራቅ ሸዋ ዞን፡፡" በሚል ርዕስ በዞኑ ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን ስለ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተገቢ የሆነ ግንዛቤ እንዳላቸውና፣ተማሪዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረቡን እንዴት በዞኑ ውስጥ እንደሚመለከቱት የዞኑ የትምህርት አመራር አካላት ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራው ያደረጉት ድጋፍ ምን እንደሚመስል፣ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ ለመተግበር የሚያደናቅፉ እንቅፋቶች ምን እንደሆኑ ለመለየት ጥናት አካሂደዋል፡፡ የመፍትሄ ሀሳቡም ለመምህራን ቅድመ-ስራና በስራ ላይ ስልጠና መስጠት ተገቢ መሆኑን፤የትምህርት ቤት የትምህርት መርጃ ማዕከልን በአገር በቀል ማቴሪያሎች ማጠናከር፤ የትምህርት አመራር አካላት እገዛ ማድረግ እንደሚገባቸው፤ የተማሪዎች መማሪያ መፃህፍት ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ በሚመች መንገድ መዘጋጀት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

ሌላው የውል ሰው (2009) የመምህራንና የተማሪዎች አመለካከትና ንቃት የተላበሰ መማር አተገባበር በደብረማርቆስ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ላይ የተደረገ ቅኝት በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናታቸው የመምህራንና ዕጩ ሰልጣኞች ንቃት ለተላበሰ መማር ያላቸው አተያይ ምን ይመስላል? በኮሌጁ ውስጥ ንቃት የተላበሰ የመማር ዘዴ ምን ያህል እየተተገበረ ይገኛል?፤ ንቃት የተላበሰ መማር እንዳይተገበር የሚያደርጉ ምክንያቶች ምንድናቸው? የሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መሪነት ተከናውኗል፡፡ የመፍትሄ ሀሳቦቹም በመምህራን ኮሌጁ ውስጥ የሚገኙት አሰልጣኝና ዕጩ መምህራን ንቃት ለተላበሰ መማር አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው፣ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ልዩ ልዩ ብልሃቶችን እንደሚተገብሩና ለአብነትም የጥንድ ስራዎች፣ የቡድን ስራዎች፣ ውይይት፣ጥያቄና መልስ፣ የገለፃ ዘዴዎች እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ትምህርቱ በአግባቡ ንቃት በተላበሰ መንገድ

እንዳይሰጥ እንቅፋት ናቸው ብለው ከዘረዘሯቸው ውስጥ የተለያዩ ማቴሪያሎች እጥረት (የተማሪው የመማሪያ መፃህፍት፣ መርሃ-ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ)፣ የመምህራን ገለጻ ዘዴን የመጠቀም፣ የጊዜ እጥረት፣ የፍላጎት ማነስ፣ የስልጠና እጦት ይጠቀሳሉ፡፡

Birhanu (2010) ለፍልስፍና ዶክትሬቱ ማሟያ "ንቃት የተላበሰ መማር/የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በሒሳብ ትምህርት በኦሮሚያ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንደታየው" በሚል ርዕስ፡፡ በዩኒቨርሲቲዎቹ ውስጥ ምን ያህል ንቃት የተላበሰን መማር እየተገበሩት እንደሚገኙ፣ የዩኒቨርሲቲዎቹ መምህራን ለንቃት የተላበሰን መማር ያላቸው አተያይ መፈተሽ፣ ለመምህራኑ የተዘጋጁትን ስልጠናዎችና ተያያዥ እገዛዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ተግዳሮት የሆኑ ነጥቦች ምንድን ናቸው፣ በውጤቱም የዩንቨርሲቲ መምህራን ለተማሪ-ተኮር አሉታዊ አመለካከት መያዛቸው፣ በመርሀ-ግብር አነዳደፍ ላይ የግትርነት ባህሪያት መኖሩ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እጥረት መኖርና የትምህርት አካላት ድጋፍ እጥረት ናቸው፡፡ ለዚህም ለመምህራን ስልጠናና የተለያዩ እገዛዎችን ማድረግ ተገቢ እንደሆነ በመፍትሄ ሀሳብነት ተገልፀው ተጠቃለዋል፡፡

ይህ እየተሰራ ያለው የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ደግሞ አፋን ኦሮሞ በትምህርትነት መሰጠት ከጀመረ ሀያ ዓመታትን ብቻ ያስቆጠረ በመሆኑና በአገራችን ውስጥ ከመምህር-ተኮር አቀራረብ ወደ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከተደረገው ሽግግር ጋራ ተመሳሳይ ጊዜ ያለው በመሆኑ በዚህ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አንፃር ፈትሾ ችግሮች ካሉት ለመቅረፍ ጥረት ማድረግ አግባብነት ይኖረዋል፡፡ በጥናቱም የመምህራኑ የተማሪ-ተኮር የክፍል ውስጥ አተገባበር ተፈትሾ ለታዩት ክፍተቶች የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰጥተው በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ የድርሻውን ያበረክታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በአሁን ጊዜ አፋን ኦሮሞ በመማር-ማስተማሩ ሂደት አገልግሎት እየሰጠ ቢገኝም በትምህርቱ አሰጣጥ ጅማሬ ወቅት የተለያዩ ተግዳሮቶች እንደነበሩበት ይነገራል፡፡ ከነዚህ ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱ በቋንቋው የሰለጠኑ መምህራን አለመኖራቸው እንዲሁም Dereje (2010) እንደገለፁት ለአፋን ኦሮሞ የሚስማማውን ፊደል (ቁቤ) መምረጡና ማስተዋወቁ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የመምህራን እጥረት ችግርን ለመፍታት በወቅቱ በተለያዩ የትምህርት ዘርፍ በማስተማር ላይ ከሚገኙ መምህራን መካከል

በመምረጥ፣ በፍላጎትና በምደባ ችግሮቹን ለመፍታት ጥረት ሲደረግ ነበር። ለምሳሌ የአማርኛ ቋንቋ፣ የፊዚክስ፣ የባዮሎጂ መምህራን የአፋን ኦሮሞ ፊደልን በማስተማር ይሳተፉ እንደነበር ሰነዶች ያረጋግጣሉ። ከዚህ ችግር በኋላ በየመምህራን ማሰልጠኛ ተቋሞች የአንድ ዓመት ስልጠና በመስጠትና የአንደኛ ደረጃ የአፋን ኦሮሞ መምህራን እጥረት ለመፍታት ጥረት ተደርጓል። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ውስጥ አፋን ኦሮሞ እንደ አንድ ትምህርት ሲሰጥ በአንደኛ ደረጃ መምህራን እየተሸፈነ መቆየቱንና አሁንም በኦሮሚያ በሚገኙ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ውስጥ መምህራን በዲፕሎማ መርሀ-ግብር በማሰልጠን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመመደብ አፋን ኦሮሞን ማስተማሩ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የተገኙ ሰነዶች ያረጋግጣሉ።ይሁን እንጂ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ረገድ ብዙ መሰራት እንዳለበት ጥናቶች ያሳያሉ።

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን በተመለከተ Derebssa በ(2006) ጥናታቸው እንዳረጋገጡት በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ዘመን ያለው የመማር-ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን አሳታፊ አቀራረብ (Active learning) እንደሆነ ገልፀው ነገር ግን የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት አተገባበር ላይ ክፍተቶች እንዳሉበት ገልፀዋል። የትምህርት ሚኒስቴር (2003) ሰነድም ይህን ከላይ የተብራራውን የጥናት አቅራቢውን ሀሳቦች ያጠናክራል። በተመሳሳይ ሁኔታ Yalew (2004) እንደገለፁት መምህራን በአብዛኛው በክፍል መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ከመተግበር ይልቅ ተለምዷዊውን የመምህር-ተኮር አቀራረብ እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል። Derebssaም (2006) በጥናታቸው እንዳመለከቱት በዚህ ዘመን ተለምዷዊው የመምህር-ተኮር አቀራረብ አንዱ ብልሃት የሆነው የገለፃ (lecture) ዘዴ፣ የመምህራን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በአብዛኛው መናገር፣ ተማሪዎች ለረዥም ጊዜ መምህራንን ማዳመጥ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚስተዋሉ መሆናቸውን ገልፀዋል።

ከላይ በምሁራኑ የተብራሩት ነጥቦች በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም የትምህርት እርከኖች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተተገበረ ነው ቢባልም በጥናት ሲረጋገጥ የተለያዩ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። የተግባሪዎቹ አካላት የክፍል መማር-ማስተማር ሂደት ሲፈተሽ በቡድንና በገለፃ ከማስተማር በስተቀር ብዙ ክፍተቶች ያሉበት መሆናቸውን ያመለክታሉ። ከዚህም በመነሳት ይህ እየተሰራበት የሚገኘው የጥናት ርዕስ "በባሌ ዞን

በአራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ" በሚል ርዕስ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የትምህርትና የስራ ቋንቋ በሆነው በአፋን ኦሮሞ የሚያስተምሩ መምህራንስ እንዴት አቀራረቡን እየተገበሩ እንደሚገኙ ለማጥናት ተችሏል።

## 1.2. ሰበበ ጥናት

በጥናቱ ዳራ ላይ እንደተገለጸው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ አፋን ኦሮሞ የክልሉ የስራና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መማሪያ ቋንቋ ነው። ከዚህም ባሻገር ቋንቋው ራሱ እንደ አንድ ትምህርት ከመሰጠቱም በላይ በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ውስጥም የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ ይሰራበታል ። ይህ በመሆኑ የክልሉ አፍ-ፈት ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መደበኛውን ትምህርት ሲማሩ የሚያውቁትን ቋንቋ በመስማት ሣይደናገሩ እቤት ያሉ ያህል ነፃነት ስለሚሰማቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማርን ጠቀሜታዎች ይጎናፀፋሉ። በሁለተኛ ደረጃም ከትምህርቱ ጅማሬ አንስቶ ጥሩ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችላቸው ከመሆኑ አልፎ ከትምህርቱ ይዘት ጋር እራሳቸውን ለማስተሳሰር ይረዳቸዋል። Bamgbos (1991) እንደሚያስረዱት የእናት ቋንቋ ተመራጩና የመጀመሪያው የትምህርት ቋንቋ ከመሆኑ ባሻገር በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትም አመቺ የሆነ የትምህርት ቋንቋ ነው። ከአለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ድንጋጌ አኳያም የእናት ቋንቋ በመጀመሪያ ደረጃ የትምህር መስጫ ቋንቋ ሆኖ ማገልገል ይገበዋል። ከነዚህ ሁሉ መሰረታዊ ጥቅም በተጨማሪ አንድ ህፃን ልጅ ለትምህርት በደረሰበት ጊዜ በእናት ቋንቋው የመናገርና የመስማት ችሎታን የሚያዳብር በመሆኑ ቋንቋው ህፃኑ ወደ መሰረታዊ ትምህርት የሚያደርገውን ሽግግር በመደገፍ ከፍተኛውን ሚና መጫወት የሚችል ነው።

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ አፋን ኦሮሞ በአፍ መፍቻነት እንዲማሩበት መደረጉና በተለይም ትምህርቱ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዲቀርብ መደረጉ ተማሪዎቹ በሚያውቁት ቋንቋ በመወያየት፣ ሀሳባቸውን በነፃነት በመግለጽ፣ ልዩ ልዩ አውዶችን በመፍጠር መጫወት፣ በአጠቃላይ በመስኩ ጥናት ያደረጉት ምሁራን እንደገለፁት የተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በንቃት መሳተፍ የቋንቋውን ዋናና ንኡስ ክሂሎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጎናፅፈው ከተፈለገው ግብ ይደርሳሉ ተብሎ ይታሰባል።

ስለዚህም መምህራን አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር ማስተማር ዘዴ ሲያስተምሩ በአግባቡ እየተገበሩ መሆናቸውን ጥናት ማድረግና ለታዩት ችግሮች መፍትሄ መፈለግ ተገቢ ነው፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን በሚገኘው በሮቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅና በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከአስራ አራት ዓመታት በላይ በመምህርነት ሲያገለግል ቆይቷል፡፡ በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ጋር በተለያዩ ውይይቶችና ወርክሾፖች፤ አውደ ጥናቶችና ሴሚናሮች በመሳተፍና በማዘጋጀት ተሰብሳቢ መምህራን በመማር ማስተማር ዙሪያ የሚያነሱትን ሀሳቦች ለመረዳት እድሉ ነበረው፡፡ በተለይም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ውስጥ በአግባቡ ስራ ላይ ውሏል የሚሉና በአግባቡ ተግባራዊ አልሆነም የሚሉ መምህራን መካከል የሚነሱ ክርክሮችን አዳምጧል፡፡ በአግባቡ ተግባራዊ እያደረጉ ናቸው ተብሎ በሚነገርላቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥም ቢሆን ፈታኝ ችግሮች እንዳሉባቸው ሲወሳ ለማዳመጥ ችሏል፡፡

ከዚህም ሌላ በሮቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ  የከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP) እጩ ሰልጣኝ በነበረበት ወቅት የስራ ላይ ምርምር (Action Research) ለማከናወን በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራንን የመማር-ማስተማር አተገባበር ሂደቶች ለመቃኘት እድል ነበረው፡፡ በዚህ ወቅት በተጠቀሰው የትምህርት እርከን ውስጥ በተለይም በአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር ሂደት ወቅት የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በተቀመጠለት መርህ አንፃር እያስተማሩበት የሚገኙ መምህራን ቢታዩም  አንዳንድ መምህራን ግን ረዥም ሰዓት ሲናገሩ፣ ለተማሪዎች ተሳትፎ ትኩረት ያለመስጠት ሁኔታ ለማየት ችሏል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች መምህራን ተማሪዎችን በማሳተፍ፣ ልዩ ልዩ ብልሃቶችን ተጠቅመው የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ስራ ላይ እያዋሉት እንደሚገኙ መምህራንና የትምህርት ኃላፊዎች ሲናገሩ አዳምጧል፡፡ በመሆኑም አጥኚው ከላይ የታዩትንና የተሰሙ የክርክር እውነታዎችን በስፋትና በጥልቀት አጥንቶ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል፡፡

በመሆኑም በባሌ ዞን በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን በሚያስተምሩ መምህራን ላይ ትኩረት አድርጎ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዴት እየተተገበረ እንደሚገኝ ጥናት በማድረግ በአተገባበሩ ሂደት ላይ የሚታዩ

ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለመለየት የሚያስችል ጥናት ማድረጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን  በቅድመ ስራ ሥልጠና ላይ የተሰጧቸው ግብዓት  ምን እንደሚመስሉ  በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እንዴት እየተገበሩት እንደሚገኙ፣ እንደዚሁም በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጡ የስራ ላይ ስልጠናዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ  ትግበራ ላይ ያስገኛቸውን ለውጦች  በሚከተሉት ጥያቄዎች መሪነት ለማጥናት ጥረት ተደርጓል፡፡

1. በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር እንዲበቁ የሚሰጣቸውን የስልጠና ግብዓቶች ምንድን ናቸው?
2. አፋን ኦሮሞን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ሲተገብሩ አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ምን ዓይነቶች ናቸው?
3. አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚያስተምሩ መምህራን በተለያየ ጊዜ የተከታተሉዋቸው የስራ ላይ ስልጠናዎች ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ እገዛ አድርገውላቸው ይሆን?
4. አፋን ኦሮሞን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ  የሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ ትግበራ ሂደት ወቅት እንቅፋት የሆኗቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?
5. በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ኃላፊዎች መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን እንዲያስተምሩ ያደረጉላቸው የተለያዩ ድጋፎች ይኖሩ ይሆን?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር  ከሚገኙት የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጆች ተመርቀው አፋን ኦሮሞን በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች  ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዴት እያስተማሩ እንደሚገኙ መመርመር ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ግብ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን የሚያስተምሩ መምህራን አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ቆይታቸው ያገኟቸውን የስልጠና ግብዓቶች ተገቢነትና ተግባራዊነት መፈተሽ ፤
2. በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር የሚጠቀሙባቸውን የማስተማር ብልሃቶች መመርመር፤
3. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በተለያየ ጊዜ የተከታተሉዋቸው የስራ ላይ ስልጠናዎች ለተማሪ-ተኮር ትግበራ እገዛ ማድረግ አለማድረጋቸውን ማረጋገጥ?
4. የጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ሲተገብሩ ያጋጠማቸውን ችግሮች መለየት፤
5. በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ኃላፊዎች የአፋን ኦሮሞ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዲያስተምሩ ያደረጉላቸውን የተለያዩ ድጋፎች መገምገም፤

## 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ

በመስኩ ምሁራን ጥናት ተደርጎ ጠቀሜታው ይፋ የተደረገው፣ በአገሪቱ ትምህርት ባለሙያዎች አስፈላጊነቱ ታምኖበት ተመርጦ በስራ ላይ የዋለውና ተማሪዎችን ማዕከል አድርጎ እየተተገበረ የሚገኘው  የትምህርት አቀራረብ በክፍል መማር-ማስተማር ሂደት ወቅት እንቅፋት ሊሆኑት የሚችሉትን እፀዖች ተከታትሎ መቅረፍ፤ መምህራንም የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተጠቅመው እንዴት እያስተማሩ እንደሚገኙ ማወቅና በአግባቡ በስራ ላይ መዋሉን መከታተል ለማስተማሪያ አቀራረቡ መዳበር የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤

1. ጥናቱ ተማሪ-ተኮር አቀራረብን በመተግበር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለይቶ መፍትሄ የሚጠቁም በመሆኑ የአፋን ኦሮሞ መምህራንን የሚያሰለጥኑ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች እንዲሁም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ መምህራን ለሚያደርጉት የተማሪ-ተኮር የማስተማር አቀራረብ ትግበራ መሻሻል እንደ ግብዓት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤

2. ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በክፍል ውስጥ ከመተግበር አኳያ የሚታዩ ደካማና ጠንካራ ጎኖችን የሚለይና አስፈላጊውን እርምት የሚያመላክት በመሆኑ በተጠቀሰው የትምርት እርከን የሚያስተምሩ መምህራን ልምድ ስለሚያገኙበት ተጠቃሚዎች ናቸው፤

3. መምህራን አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ የሚጎድሏቸውን የተማሪ-ተኮር አተገባበር የስልጠና ግብአቶች እንዲሟሉና ድክመቶች እንዲቀረፉ በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርት ኂላፊዎችና ትምህርት ቢሮ መረጃ የሚሰጥ በመሆኑ ተጠቃሚዎች ናቸው፤

4. በተማሪ-ተኮር አተገባበር መርህ መሰረት አንዱ አስፈላጊ ጉዳይ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ተማሪን አሳታፊ ሆነው ሲገኙ በመሆኑ ከዚህ አንፃር ለስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ባለሙያዎችና የማስተማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች ጥቆማ ይሰጣል፤

5. ወደፊት በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለሚያካሄዱ ተመራማሪዎች የመነሻ ሐሳብ ይሰጣል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ ከሚገኙ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች በተለያየ ጊዜ ሰልጥነው በባሌ ዞን በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ት/ቤቶች ተመድበው አፋን ኦሮሞን በሚያስተምሩ መምህራንና በኮሌጅ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ ዕጩ መምህራን አሰለጣጠን ላይ የተገደበ ነው፡፡ በኮሌጅ ውስጥ ለዕጩ መምህራን የሚሰጠውን የፕራክቲከም ኮርስ ዓላማና አተገባበርና የ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ አንፃር ከማብራራት በስተቀር ለሎች ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራንን አይመለከትም፡፡ ነገር ግን በኮሌጁ ውስጥ ስለሁሉም ትምህርት ክፍሎች ሀሳብ ሊሰጡ የሚችሉ አካላት ተመርጠው መረጃ እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡

በባሌ ዞን ውስጥ 180 አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ቢኖሩም በጥናቱ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች ለመሸፈን የተገኙትን መረጃዎች ለመቆጣጠር ከአቅም በላይ ስለሚሆን ከትምህርት ቤቶቹ ውስጥ በታለመ የንሞና ዘዴ አንድ የመምህራን ትምህርት

ኮሌጅና አራት ትምህርት ቤቶች ላይ የተወሰነ ነው። እንደዚሁም ከመማሪያ ክፍል ደግሞ እንደዚሁም በተለያዩ ኮሌጆች ስልጠና ወስደው በዲፕሎማ የተመረቁት መምህራን በአብዛኛው የሚመደቡት በ7ኛና 8ኛ ክፍሎች ውስጥ ቢሆንም በጥናቱ የተፈተሸው የ7ኛ ክፍል ብቻ ሲሆን ጥናቱ በአፋን ኦሮሞ ትምህርት ላይ ብቻ መወሰኑ አጥኚው የተማሪ-ተኮር የአተገባበር ክፍተቶችን የታዘበው በዚህ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ብቻ በመሆኑ ነው።

## 1.6.የጥናቱ ውስንነት

በዚህ ጥናት ውስጥ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመጠቀም የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ተደርጓል። ሆኖም ግን ስራው በበቂ ሁኔታ ሁሉንም ተያያዥ ነገሮች ሸፍኗል ማለት ስለማይቻል ጥናቱ ውስን የሚሆንባቸው ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. የተወሰኑ ምልከታዎች በማካሄድና ውስን ትምህርት ቤቶችን ብቻ አይቶ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የተማሪ-ተኮር አተገባበር ላይ ድክመት አለ ብሎ መፈረጅ ራሱ ጥናቱን ውስን ያደርገዋል። ከዚህ አንፃር የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ክፍተቶችን ለማወቅ የትምህርት ቤቶችን ቁጥር ማብዛትና የክፍል ምልከታው ጊዜ ቢደጋገም የመረጃው ተዓማኒነት ይጠነክር ነበር።

2. ለዚህ ጥናት የተፈቀደው በጀት በቂ ቢሆን ኖሮ በስፋት ስልጠና ከተሰጠ በኋላ የመምህራንን የተማሪ-ተኮር አተገባበር መፈተሽ ያስፈልግ ነበር። ሆኖም በስፋትና በጥልቀት ሊሰሩ የታቀዱት የምርምር ዓይነቶች ሳይሰሩበት በአይነታዊ ምርምር ላይ ብቻ ባይወሰን የተሻለ ይሆን ነበር።በተጨማሪም በታዩት ክፍተቶች ዙሪያ ለመምህራን ስልጠና ቢሰጥና ከስልጠና በኋላ ያሉት ችግሮችም ቢፈተሹ ተገቢ ይሆን ነበር።

## 1.7.የጥናቱ አደረጃጀት

በዚህ ጥናት ውስጥ ስድስት ምዕራፎች ቀርበዋል። በምዕራፍ አንድ የጥናቱ መግቢያ የቀረበ ሲሆን በዚህ ስር ለጥናቱ መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ የጥናቱ ዳራ፣ ሰበበ ጥናት፣ ዓላማ፣ ጠቀሜታ፣ ገደብ፣ የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍች ይገኙበታል። በምዕራፍ ሁለት ስር ደግሞ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ትምህርትና የቋንቋ ፖሊሲ ዳራ ቀርቧል። በርዕሱ ስር ትምህርት በቅድመ 1908ና ከ1908 በኋላ የቀረቡ ንዑሳን ርዕሶች የቀረቡ ሲሆን በመቀጠልም የጥናቱ ቦታ፣ የኦሮሞ ህዝቦችና የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር አጠቃላይ ዳራ ቀርቧል። በምዕራፍ ሶስት ስር ደግሞ ክለሳ ድርሳን ይገኛል። በምዕራፉ ስር ስለመማር-ማስተማር አቀራረቦች ማብራሪያ ተሰጥቷል። እነዚህም የመምህር-ተኮርና የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አጠቃላይ ገለፃ ከተሰጠ በኋላ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ምንነት፣ አስፈላጊነት፣ መርሆዎች፣ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና የሚሉ ይዘቶች በዝርዝር ቀርበዋል። በማስከተል ለምርምሩ መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ ጽንሰ-ሀሳባዊ መሠረቶች ይቀርባሉ። በዚህ ስር ስለ አፍ መፍቻ ቋንቋ ጠቀሜታና ልዩ ልዩ የቋንቋ ትምህርት ፍልስፍናዎችና ንድፈ-ሀሳቦች ተብራርተው የጥናቱ ማዕቀፍ ይቀርባል።

በምዕራፍ አራት ስር ደግሞ የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ ይቀርባሉ። በመሆኑም የጥናቱ ዓይነት፣ የቦታው አመራረጥ፣ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች፣ ናሙና አመራረጥና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቀርበዋል። በተጨማሪም የጥናቱ መረጃ ሰጪዎች እነማን እንደሆኑ፣ እንዴት ሊመረጡ እንደቻሉ ተብራርቷል። በመጨረሻም የመረጃዎቹ አስተማማኝነት፣ ትክክለኛነት፣የሙከራ ውጤቱ፣ ከዚህም የተገኙ ትምህርቶች የጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተልና አተናተን ተብራርተው ምዕራፉ ይጠናቀቃል ።

በምዕራፍ አምስት የመረጃ ትንተና፣ግኝትና ማብራሪያ ቀርቧል። በዚህ ስር በምዕራፍ አንድ ስር የቀረቡት የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙት መረጃዎች ተተንትነው ማብራሪያ ይሰጣቸዋል። በምዕራፍ ስድስት ስር ደግሞ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበው በአጭሩ የቀረቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች መደምደሚያ አግኝተው ጥናቱ ይቋጫል።

## 1.8. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍችና ምህፃረ-ቃላት

### ሀ. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍች

**የማስተማር አቀራረብ** (Teaching Approach) ፡- ስልተ-ትወራዊ ፅንሰ ሀሳብ እሳቤ ያለው ሆኖ የተለያዩ ዘዴዎችና ብልሃቶችን በውስጡ አቅፎ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መምህራንና ተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ቀንጭበው ተግባራዊ የሚያደርጉበት አቅጣጫነው፡፡

**የተማሪ-ተኮር አቀራረብ**፡- በክፍል የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አብዛኛው ጊዜ የመምህሩ ትኩረት ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሆነና ተማሪዎች ዋነኛ የትምርቱ ተሳታፊ በመሆን በራሳቸው ጥረት የሚማሩበት መንገድ ማለት ነው፡፡

**በንቃት መማር**፡- በቋንቋም ሆነ በማንኛውም ትምህርት የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መምህራንና ተማሪዎች ተሳታፊ ሆነው መማራቸውን ያመለክታል፡፡አንዳንድ ሰዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብና ንቃት የተላበሰን መማር በአንድ ሲፈርጁ ይስተዋላል፡፡ ነገር ግን መጠነኛ ልዩነት እንዳላቸው የመስኩ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ጥናት ውስጥም ልዩነቱን በማሳየት የተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ሆነው መቅረባቸውን ለማመልከት ተሞክሯል፡፡

**የማስተማሪያ ዘዴዎች** (Teaching Methods)፡- በትምህርት ዓላማዎች ላይ ተመርኩዘው ተማሪዎች የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ እንዲያመጡ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መምህራን ትምህርት የሚያቀርቡበት መንገድ ነው፡፡

**የማስተማር ብልሃት** (Teaching Strategy) ፡- ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ተመሳሳይነት ያለውና በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማሩ ሥራ ሲከናወን ተማሪዎች ከተፈለገው ግብ እንዲደርሱ መምህራን የሚከተሉት የአሰራር ስልት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የማስተማር ብልሃት የሚለው ጽን-ሰሀሳብ የማስተማር ዘዴ የሚለውን ፍቺ ይይዛል፡፡ ብልሃት ወይም ዘዴ ሂደታዊ አሰራርን የሚመለከት ሆነው ለትምህርት የሚቀርቡ ማቴሪያሎችን መረጣ፣ አቀራረባቸውንና በአጠቃላይ መማርን እውን ለማድረግ ተግባራዊ የሚያደርግ ስነ-ማስተማር (Pedagojics)

ይይዛል። በዚህ የጥናት  ውስጥ ብልሃት የሚለው ጽንሰ -ሀሳብ  ተግባራዊ ሆኗል። ጥናት አቅራቢው የማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ያለደረገው አንዳንድ ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብም ሆነ ለማስተማር ብልሃቶች ዘዴ በሚል ስያሜ በመጠቀማቸው ይህን ለመለየት ሲባል ነው።

**የማስተማር ስልት** (Teaching Styles)፡- መማር ማስተማሩን ለማካሄድ መምህራን የሚጠቀሙበት ግላዊ ጥበብ ነው፡

**ከፍተኛ ዲፕሎማ** (Higer Diploma)፡- በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ተመድበው የሚያስተምሩ መምህራን የክፍል ውስጥ የትምህርት አቀራረብ በተማሪ የነቃ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ አድርገው እንዲያስተምሩ የሚያግዝ ስልጠና ነው።

**አቀራረብ፡-** የተለያዩ የመማር-ማስተማር ፍልስፍናዎችን፣ ትውሮችን፣ መርሆዎችንና ዘዴዎችን የሚያካትት ሀሳብ ነው።በስሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ  የማስተማር ዘዴዎች ወይም ብልሃቶች ይኖራሉ። የማስተማር ብልሃቶች ስር ደግሞ የቡድን ውይይት፣ ሚና ጨዋታ፣ ችግር ፈቺ የመሳሰሉት ዘዴዎች  ይገኛሉ።

**ስትራቴጂ** ወይም **ቴክኒኮች፡-** በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ እያንዳንዱ ዘዴ ተግባራዊ የሚሆንበት ስልት ነው። በአንድ አቀራረብ ከአንድ በላይ ዘዴዎችን ማግኘት የሚቻል ሲሆን እያንዳንዱ ዘዴ ግን ተግባራዊ የሚሆንበት ስትራቴጂ የሚመሠረት ነው።

**አሰልጣኝ መምህራንና የኮሌጅ መምህራን፡-**በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ በአማራጭነት ወይም በማቀያየር ለመጠቀም ጥረት ተደርጓል።

**ዕጩ መምህራን፣ ሰልጣኞች፣ ተማሪዎች፡-** በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ስልጠና በመውሰድ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ሲሆኑ በተመሳሳይ ፍቺ በአማራጭነት በመውሰድ በስራ ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል።

**ቁቤ፡-** አፋን ኦሮሞ ለጽህፈት የሚጠቀምበት የላቲን ፊደል ስያሜ ነው።

**አፋን፡-** በኦሮሞ ሕብረተሰብ ቋንቋ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ይወክላል።

## ሰ. ሰምህፃረ-ቃላት

**የአካ/ም/ም ዲን፡-** የአካዳሚክና ምርምር ምክትል ዲን

**ኦ/ት/ቢሮ፡-** የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ

**ተሙማ፡-** የተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ

**ት/ሚ፡-** የትምህርትሚኒስቴር

**ት/ቤት፡-** ትምህርት ቤት

**መ/ም/ት/ማ/ኮ/፡-** የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ

**ር/መ/** ፡- ርዕሰ መምህር

**ም/ር/መ፡-** ምክትል ርዕሰ መምህር

**BZFDO፡-** የባሌ ዞን ፋይናንስና እድገትቢሮ(Bale Zone Finance and Development Office)

በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለጥናቱ መከናወን መነሻ የሆኑ ሀሳቦች ቀርበው ጥናቱ ይዞ የተነሳውን ጥያቄዎች ለማሳየት ተሞክሯል ፡፡ በነዚህ ጥያቄዎች መሪነትም በጥናቱ ዓላማ ስር ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች ከተገለፁ በኋላ የአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር ችግሮች ከተፈቱ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት አካላት ተጠቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም የጥናቱ ወሰን ስር የሮቤ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅና አራት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል ውስጥ የተገደበ እንደሆነ ተብራርቷል፡፡ ከነዚህም ሌላ ይህ ጥናት ብዙ ጉዳዮችን አንስቶ መፍትሄ መስጠት ሲገባው ያልሰጣቸውን ጉዳዮችና መሸፈን የሚገባቸው ቦታዎችን ያለመሸፈኑ የጥናቱ ውስንነት በሚለው ርዕስ ስር ሐሳብ ተሰጥቶበታል፡፡ በመጨረሻ የጥናቱ አደረጃጀትና ውስጡ በተደጋጋሚ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት እንዲሁም ምህፃረ-ቃላት ፍች ተሰጥቶ ምዕራፉ ተጠቃሏል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- የኢትዮጵያ ትምህርትና የቋንቋ ፖሊሲ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስር ሁለት ዋና ዋና ርዕሶች ቀርበዋል፡፡ የኢትዮጵያን የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲ ለመረዳት ይቻል ዘንድ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት ውስጥ የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥና የስነ-ዘዴው ሁኔታ በኢትዮጵያ ሲሠጡ ከነበሩት የዕምነት ትምህርቶች ጋር ተያይዘው ይብራራሉ፡፡ የቋንቋና የቤተ-እምነት ትምህርት በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ ስር ከ1908 በፊት የኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን፣ የቁራንና የሚሲዮን ትምህርት አሰጣጥን እንዲሁም የዘመናዊ ትምህርት ጅማሬና በአገራችን አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ ያሉትን የቋንቋና የቋንቋ ትምህርት አሠጣጥን እንመለከታለን ፡፡ በማስከተልም ጥናቱ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ በባሌ ዞን አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበርን የሚመለከት በመሆኑ የኦሮሚያ ክልልን በተለይም የባሌ ዞንን መልካ ምድራዊ ገፅታና ባህለ-ኢኮኖሚ ሁኔታዎች በጥቂቱ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 2.1.የቋንቋና የቤተ እምነት ትምህርት በቅድመ 1908 ኢትዮጵያ

በኢትጵያ ውስጥ የትምህርት ጅማሬ ሲታሰብ ረዥም ታሪክ አለው፡፡ በዚህ የረዥም ዘመን የትምህርት ታሪክ በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን፣ የእስልምና እምነት የሆነው የቁራን ትምህርት፣ የሚሲዮናውያን ትምህርት የራሳቸው ውስጣዊ ድክመቶች ቢኖሯቸውም ለኢትዮጵያ ትምህርት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ማበርከታቸውን አያሌ ፀሐፊያን ይመሰክራሉ፡፡

### 2.1.1.የኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ትምህርት

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የቋንቋና የቋንቋ ትምህርት ከታሪክና ከህዝቡ ልማድ ጋራ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ እንደ Alemayehu (2012) ገለፃ የኢትዮጵያ የትምህርት ታሪክ ወደ ጥንቱ 4ኛ ክፍለ-ዘመን የክርስትና አጀማመር ይወስደናል፡፡ የክርስትና እምነት (በተለይም የኦርቶዶክስ) ከአክሱም ዘመነ መንግስት ጀምሮ ለኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት መሠረት የጣለ እምነት ነው፡፡ የዚህ እምነት ኂላፊነት ህፃናት እንዲጽፉና እንዲያነቡ በቤተክርስትያን ውስጥ መሰረታዊ ትምህርት መስጠት ነበር፡፡ የቤተክርስቲያኒቱ

የትምህርት ስርዓት ዋና ዓላማ ለእምነቱ ማጠናከሪያና ስብከት ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ ለማህበራዊ አገልግሎት ስራ የሚመረጡ ግለሰቦች ከዚሁ ዘርፍ እንዲወጡ እገዛ አድርጓል፡፡ የትምህርት ማስተማሪያ ስነ-ዘዴው ከባድ ስነ-ምግባር (Discipline) ከመጠየቁም በላይ በማዳመጥ፣ ምላሽ በመስጠትና ሽምደዳ ላይ ትኩረት ያደርግ ነበር (Birgit፣ 1988)፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ትምህርት በተለያዩ ደረጃዎች ተከፋፍሎ እንደሚሰጥ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡አንዳንዶች በሶስት ደረጃዎች ሲከፋፍሉት ሌሎች ደግሞ በአራት ይከፈላል ይላሉ፡፡ በሶስት ይከፈላል የሚሉት ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤት፣ መጽሐፍ ቤት ብለው ይዘረዝሯቸዋል ፡፡ እንደ Pankhurst (1969) ያሉት ደግሞ ዜማ፣ ሰዋሰው፣ ቅኔ፣ አዲስና ብሉይ ኪዳን ብለው በአራት ይከፍላሉ፡፡ እነዚህ ትምህርቶች እንደ ቅደም ተከተላቸው 7፣9፣4ና 10 ወይም በአጠቃላይ ከ (4-10) ዓመታት ይፈጃሉ፡፡ እንደ Bovenና Horn (1976) ያሉት ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትምህርት ንባብ፣ ዜማ፣ ቅኔ፣ የግዕዝ ቋንቋ፣ ብሉይና አዲስ ኪዳን፣ ጽህፈት፣ የቤተክህነት የቀን መቁጠሪያን ማወቅ፣ ታሪክ፣ ስነ-ጥበብና የእጅ ስራ የሚሉ ስምንት ክፍሎችን ያሳያሉ፤በተጨማሪም የቀኖናና (የቤተክህነት ስርዓት)፣ የስነ-ፈለክ ጥናት ትምህርቶችም ይሰጡ እንደነበር ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል Meyerና Richter (2003) እንዳመለከቱት ቤተክርስትያናትና ገዳማት በራሳቸው ትምህርት ክፍል ጋር አያይዘው ዘመናዊ ትምህርት ቤት በመክፈት በዓለም ላይ ሲሰጡ የነበሩ ጥንታዊ የትምህርት ዓይነቶች ማለትም እንደ የስነ-መለኮት ትምህርት፣ ታሪክ፣ ግጥም፣ ሙዚቃ፣ ህክምና የመሳሰሉ ይዘት እንደነበራቸው አስረድተዋል፡፡ Pankhurst (1969) በበኩላቸው ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉ ለኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን የትምህርት አስተዋፅኦ ምስክሮች መሆናቸውና ከዚህም ውጪ ቤተክርስትያኒቱ አያሌ የቤተክርስትያን ትሁት መምህራንና በአውሮፓውያን ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ ተማሩ ከሚባሉ ፕሮፌሰሮች በላይ እውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች ስታፈራ እንደነበረ አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የሙዚቃ ቅኝት ባለቤት የሆነው ቅዱስ ያሬድ፣ የኢትዮጵያ መሪ የነበረው ዓፄ ዘርዓ ያቆብ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስትያን በወቅቱ የምታስተምርበት ቋንቋ ግዕዝ መሆኑና የግዕዝ ቋንቋ ከ4ኛው እስከ 9ኛው ክ/ዘመን ድረስ በአክሱም አካባቢ ያግባባ እንደነበር ይነገራል (Birgit፣1988)፡፡ እንደ Meyerና Richter (2003) ገለፃ ቋንቋው እስከ አስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያን እምነት፣ ፍልስፍና፣ ታሪክ፣ ስነ-ምግባርና የተለያዩ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የሚከናወኑበት ቋንቋ እንደነበረና በኋላ  ግን ቀስ በቀስ ለአማርኛ ቦታውን እየለቀቀ እንደ ሄደ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ለአማርኛ ቦታውን እስከ ለቀቀበት ጊዜ በቤተክርስትያን ውስጥ የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ ጉልህ ሚና ሲጫወት እንደቆየና አሁንም እያገለገለ እንደሚገኝ Alemayehu (2012)  ይገልፃሉ፡፡

### 2.1.2. የቁራን ትምህርት

በኢትዮጵያ ውስጥ ከእስልምና ሐይማኖት መስፋፋት ጋራ ተያይዞ ሲሰጥ የነበረው ትምህርት ቁራን ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የአረብኛ ቋንቋ ከፍተኛ ሚና ሲጫወት እንደ ነበር Dereje (2010)  ይስረዳሉ፡፡ ይህ ቋንቋ በብዙ አገሮች እንደ አለም አቀፍ ቋንቋ የሚያገለግል በመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታዮችም በብዛት ይግባቡበታል፡፡ ይህን አስመልክተው Benderና et al (1976)ም ማጠናከሪያ ሀሳብ ሲሰጡ እንደ ክርስትና እምነት ሁሉ የቁራን ትምህርትም ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ማስተማሪያ መሰረት ነው፡፡ በሌላ በኩል HaileGabriel (1976) በበኩላቸው የአረብኛ ቋንቋን ከቁራን ስነ-ጽሁፍና ከእስልምና እምነት ጋራ መለያየት የማይቻል መሆኑን፤ ለአንዳንድ አገሮች አረብኛ እንደ ውጪ ቋንቋ በመሆን ማገልገሉንና አረብኛን ማስተማር አረብኛ ከሚናገሩ አገሮች የሚለይ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ የቁራን ትምህርት በአብዛኛው ሲሰጥ የነበረው የእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች በስፋት በሚገኙበት በምስራቅና ምዕራብ የአገራችን አካባቢዎች ነበር፡፡ Dereje (2010) የፈረንሳይ ፀሐፊ Montandonን (1913)  ጠቅሰው እንደ ገለፁት በምዕራብ ኢትዮጵያ በጅማ ብዙ የእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች ቁራንን በአረብኛ ቋንቋ ያነባሉ፡፡ እንደ ቤተክርስትያን ትምህርት ሁሉ ተለምዷዊው የቁራን ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሶስት ደረጃዎች ውስጥ ያልፋሉ፡፡ ከእነዚህ ደረጃዎች የመጀመሪያው ጠሀጂ (Tehaji) የሚባል ሲሆን በቅድሚያ የአረብኛ ፊደላት ከተለዩ በኋላ ወደ ንባብ የሚሸጋገሩበትና ቁራን የሚነበብበት ደረጃ ነው፡፡ ይህ ደረጃ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቤት ወይም

የንባብ ትምህርት ቤት ከሚለው ደረጃ ጋራ አቻነት ያለው ይመስላል ። ሌላው ደረጃ ባዲያ /Badiya/ (ILM) ይባላል። ይህ ደረጃ የእስልምና ሐይማኖት ስርዓት (Fiqh)ና ነሀዊ (Nahew) የሚባሉ የአረብኛ ሰዋስውን ያካተተ ደረጃ ነው። በሶስተኛው ደረጃ የራስ አስተያየትና ትንታኔ የሚሰጥበት ክፍል ተስፊር (Tesfir) የሚባለው ሲሆን በዚህ ደረጃ ቁራን ውስጥ የሚገኙ ጽሁፎች በሌላ መንገድ የሚገለፁበት፣ ፍልስፍናዎች የሚቀርቡበትና ከፍተኛው የትምህርት ደረጃ ነው (Haile Gabriel፣1976) ። በአጠቃላይ ከላይ የተብራሩት ሀሳቦች በኢትዮጵያ ውስጥ የግዕዝ ቋንቋ በቤተክህነት ውስጥ የእምነት ትምህርት መስጫ እንደሆነ ሁሉ የአረብኛ ቋንቋም ለእስልምና ሐይማኖት ትምህርት ነበር። ሁለቱም ቋንቋዎች ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት መሰረት ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል። አረብኛ ቋንቋ የእስልምና ሐይማኖትን ትምህርት ከማስተማር ባለፈ ይህን ትምህርት የተማሩ ሰዎች የተለያዩ ስነ-ጽሁፎችን እየፃፉ ሀሳቦችን የሚገልፁበትና አሁንም ድረስ በዚህ ቋንቋ መልዕክታቸውን እያስተላለፉ እንደሚገኙ መገንዘብ ይቻላል።

## 2.1.3 የሚሲዮኖች ትምህርት

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት ስርዓት ታሪክ ውስጥ መሰረት ጥለዋል ከሚባሉት የቤተ-ዕምነት ትምህርቶች ውስጥ የሚሲዮናውያን ትምህርት አንዱ ነው። Dereje (2010) እንደገለፁት በጅማሬው አካባቢ የኦርቶዶክስ ክርስትናና የእስልምና ሐይማኖት መጠናከር በኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው በነበሩት ሚሲዮኖች እምነታቸው እንዳይስፋፋ ተጽእኖ አሳድረውባቸው ነበር። በHaileGabriel (1976፣339) ገለፃ መሠረት "የሚሲዮናውያን ትምህርታዊ እንቅስቃሴ እስከ ሃየኛው ክፍለ ዘመን ድረስ እንብዛም አልተስፋፋም ነበር።" ብለው ሲያስረዱ Benderና et al (1976)ና Cooperና McNab(1989) በኢትዮጵያ የታሪክ፣ የባህልና የፖለቲካ ሁኔታዎች ምክንያት የሚሲዮናውያን ትምህርት ቤት እንደፈለገው እንዳይስፋፋ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን አስረድተዋል።

ፖርቱጋል በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ በምስራቅ አፍሪካ ከቀኝ ገዢ አገሮች አንዷ በመሆኗና ለኢትዮጵያ እርዳታ በማድረግ የአህመድ ግራኝን ጦር ድል ከነሱ በኋላ በወቅቱ እንዳይስፋፋ ተግዳሮት የነበረው የሚሲዮናውያን ትምህርት በመሳፍንቱ መለዘብ ዳግም አንሰራራ (Bahiru፣1991)። ከዚህ በኋላ ለፖርቱጋል መንግስት የምስጋና ደብዳቤ በመፃፉ ምክንያት የሮማ ካቶሊክ ሐይማኖት ወደ አገሪቱ መግባት ጀመረ። በወቅቱ

የነበሩትን ንጉስ ሱስንዮስን የሚለውጥ አዲስ እምነት ተጀመረ። ካቶሊክም ይሁን ሌላው እምነት በተጀመረበት አካባቢ እምነታቸውን ከትምህርት ጋራ ማስፋፋት ጀመሩ። Dereje (2010) እንደ ገለፁት ከእምነቱ መስፋፋት ጋራ ብዙ ወጣቶች የትምህርት ዕድል እያገኙ ወደ ውጭ አገር ሊሄዱ ቻሉ። Pankhurst (1969) በበኩላቸው እንዳስረዱት በመጀመሪያ መፅሐፍ ቅዱስን ወደ አፋን ኦሮሞ የተረጎሙት ኦኒስሞስ ነሲብ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ለትምህርት ወደ ሲውድን አገር ሊላኩ የቻሉትም በዚሁ መንገድ ነው።

ቀጥሎም በ1873 የሲውድን ኢቫንጀሊካል ሚሲዮን ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ መሪዎች ለሚሲዮኖች ትምህርት ጥሩ አመለካከት ስላልነበራቸው በጥንቱ የቤተክርስትያን ትምህርትና የትምህርት ይዘቶች የመቀጠል ፍላጎት ያሳዩ ነበር (Pankhurst፣1969፤ Bowen፣1976)። በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የሚሲዮናውያን የሐይማኖት ትምህርቶች አገራችንን በጦርነት ለማገዝ በመጡ የሰራዊት አባላት አማካኝነት በመሆኑ ተጽእኖውም ሆነ የባላባቱ አመለካከት በተወሰነ ደረጃ ሊቀንስ ችሎ ነበር።

አጼ ቴድሮስ (1855-1868) በዘመነ መሳፍንት ስርዓት ወደ ስልጣን እንደ መጡ ወታደሮቻቸውን በተለያዩ ክህሎቶች ለማሳደግ ፍላጎት እንደነበራቸው ይነገራል። በዚህ ምክንያትም እስከ ዘመነ ንግሳቸው ጊዜ ድረስ የተለያዩ ወታደራዊ ስልጠናዎች በአውሮፓ አገሮች ስልጠና ይሰጡ ነበር። አጼ ቴውድሮስም የአገራቸውን ሰዎች ለማሰልጠን በመፈለጋቸው ለእንግሊዝ መንግስት መምህራንንና ኢንጂነሮችን እንዲልኩላቸው በደብዳቤ ቢጠይቁም ዓላማቸውን ሳያሳኩ በ1886 በመቅደላ ላይ አረፉ (Pankhurst፣ 1969)።

በአጠቃላይ ከፀሐፊያኑ እንደምንገነዘበው በዚህ ዘመን ውስጥ የተለያዩ መሪዎች ለዘመናዊ ትምህርት ፍላጎት ቢኖራቸውም ስኬቱ የግድ የአውሮፓውያንን በጎ ፍቃድ የሚሻ ለነበር እነሱ ፍላጎት ስላልነበራቸው የዘመናዊ ትምህርቱም ሳይስፋፋ ቆይቶ ነበር። ያም ሆነ ይህ ሁኔታው ለዘመናዊ ትምህርት መሰረት ጥሎ አልፏል።

## 2.2. የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲ በድህረ 1908

በአፄ ሚኒልክ ዘመነ መንግስት የነበረው የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲም በአፄ ቴዎድሮስ የተጀመሩት የአንድነት ጥንስስ ለውጥ የመጣበትና ያበቃበት ዘመን ነበር። በዚህም

መሰረት ለመንግስታቸው ስራ በብቸኝነት የተመረጠው  የአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ ከዚያ በፊት በማይነገርባቸው ቦታዎች ሁሉ መነገር ጀመረ። በተለይም የአፄው አስተዳደር ወደ ደቡብ እየሰፋ መጥቶ ብዙ ብሄር ብሄረሰቦች ከባላባቶቻቸው ጋር እንዲግባቡበት ተመራጭ ቋንቋ ሆነ። በአጠቃላይ አማርኛ የገዥዎች ቋንቋ የመሆን እድል በማግኘቱ በእምነት ቦታዎችና በስራ ቦታ ሁሉ አማርኛን መጠቀም የሁሉ ሰው ተግባር ሆነ። መንግስቱም የሚከተለው የቋንቋ ፖሊሲ ግልጽ እንዳልነበር ጥናቶች ያስረዳሉ (Mc Nabb 1989፣ Beharu፣1991)።

በዚህ ዘመን አጼ ሚኒሊክ አገሪቱን ዘመናዊ ለማድረግ ከመጓጓታቸው የተነሳ በ1908 ዘመናዊ ትምህርት ቤት ከፈቱ። በዚህ ወቅት በአማርኛ ቋንቋ መፃፍ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሆኖ የመምህራን ምደባ የሚከናወነው ከፈረንሳይና ከግብጽ እንደነበርና የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች  እንግሊዝኛ፣ አረብኛና ጣልያንኛ እንደነበሩ ፀሐፍት ያስረዳሉ። ግዕዝና አማርኛ ደግሞ በትምህርት ዓይነትነት የሚሰጡ ነበሩ (Tekeste፣ 2006፤ Seyoum፣1997፤ Mc-Nab፣ 1987):: በሌላ በኩል Moges (2010)  እንደገለፁት አፋን ኦሮሞና ትግርኛ የአገር ውስጥ ቋንቋዎች በትምህርት ቤት ይሰጡ እንደነበር ጠቁመዋል። በዚሁ ዓመት ውስጥ በሐረር ሌላ ትምህርት ቤት ተቋቁሟል። ከ1913 በኋላ የአጼ ሚንሊክ መሞትና በዓለም አቀፍ ደረጃ የአንደኛ አለም ጦርነት መከሰቱ በወቅቱ የታዩትን ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ወደ ኋላ መጎተት ጀመረ። ከዚሁ ጋር በማያያዝ Bovenና Horn (1976) እንደገለፁት የመጀመሪያዎቹ የምሽነሪዎች ትምህርት ቤቶች ከመንግስት ትምህርት ቤቶች ይልቅ የተበታተኑ በመሆናቸውና  በመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የማስተማሪያ መሳሪያዎች እጥረት በመኖሩ የምሽነሪዎች ትምህርት ቤቶች በስፋት ተጠናክረው ይታዩ ጀመር። ከዚህም በሚንሊክ ሞት ምክንያት የኢትዮጵያ የትምህርት ኋላፊዎች የምሽነሪዎችን የትምህርት እንቅስቃሴዎች ሊቆጣጠሩ ባለመቻላቸው ትምህርት ቤቶቹ የመስፋፋት እድል አግኝተዋል።

በአጼ ሐይለስላሴ ዘመነ-መንግስት (1930-1974) ደግሞ  አንድ ቋንቋ፣ አንድ አገርና አንድ እምነት የሚል ፖሊሲ ተጠናክሮ የቀጠለበት ዘመን ነበር  ሀይለስላሴ "በራሳችን ቋንቋ ትምህርቱ ይሰጥ፤ በራሳችንም ቋንቋ እናንብብ፤ እንፃፍም" ብለው በይፋ በተናገሩት መሠረት ከ1947-1958 ዓ.ም የትምህርት መማሪያ ቋንቋ እንግሊዘኛ ቢሆንም አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት መስጠቱ ተጠናክሮ ቀጠለ (Bloorና wondsen፣1996)።

ከ1958 በኋላ  የ1ኛ ደረጃ መርሀ-ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ እንግሊዝኛ እንደ አንድ ትምህርት እንዲሰጥ ተደረገ (Bloorና wondsen 1996፤ ትምህርት ሚኒስቴር 1964)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ  Getachewና Derib (2006) እንደሚሉት በዚህ ዘመን ውስጥ በሚገባ የተዘጋጀ የቋንቋ ፖሊሲ በህገ-መንግስት ተዘጋጅቶ የቀረበው በ1930 ራስ ተፈሪ ሀይለስላሴ ተብለው የንጉሰ ነገስትነት ዘውድ ከደፉበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ይህ ህገ-መንግስት ስለ ቋንቋ ህጋዊነት ምንም የገለፀው ባይኖርም ተጽፎ የቀረበው ግን በአማርኛ ነበር፡፡

Cohen (2000)፣ Mc-Nab (1989) እንደ መሰከሩት ይህ ህገ-መንግስት የተዘጋጀው የቋንቋና የትምህርትን ፖሊሲ እንዲያካትት በማሰብ እንደሆነና ፖሊሲው ለኢትዮጵዊነት ትልቅ ቦታ እንደሰጠ አመልክተዋል፡፡ በሚንሊክ ጊዜ የነበረው ኢትዮጵያዊነት ባለ ስልጣናትን የሚያቅፍ የነበር ሲሆን በሀይለስላሴ ጊዜ የነበረው ኢትዮጵያዊነት ግን አብዛኛውን ህዝብ የሚያቅፍ በመሆኑ የፖሊሲው ስራ ከብሄራዊ አንድነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ  ለዚህም ሲባል መንግስቱ ብሄራዊ እምነትን፣ ባህልና ቋንቋን በማያያዝ አቋሙን አመላከተ፡፡ ይኸውም "አንድ አገር አንድ እምነትና አንድ ቋንቋ" በሚል አስተሳሰብ ለሁሉም ህዝብ እንዲደርስ ተደረገ Getachewና Derib (2006) ፡፡ በመሆኑም የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲው አለ ቢባልም ከአማርኛ በስተቀር አንዱንም አገር በቀል ቋንቋ አላሳደገም፡፡ ሆኖም ጣልያን ኢትዮጵያን በወረራ ከያዘ (ከ1935–1941 ዓ.ም) በኋላ የብሄር ብሄረሰቦችን ቋንቋ በመጠቀም በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሰጥባቸው ፈቀደ፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ሠንጠረዥ በወቅቱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሲሰጥበት የነበረውን ቋንቋና አካባቢን የሚያመላክት ነው፡፡

**ሠንጠረዥ አንድ፡-  በጣልያን ወረራ ወቅት የነበረው የኢትዮጵያ የቋንቋ ትምህርት ፤**

| ቁጥር | አስተዳደራዊ ክልል | ማስተማሪያ ቋንቋ |
|---|---|---|
| 1 | ኤርትራ | ትግርኛና አረብኛ |
| 2 | አማራ | አማርኛ |
| 3 | አዲስአበባ | አማርኛና ኦሮምኛ |
| 4 | ሐረር | ሐረሪና ኦሮምኛ |
| 5 | ሲዳማ | ኦሮምኛና ከፋቾ |
| 6 | ሶማሊ | ሶማልኛ |

**ምንጭ፡-** Pankhurst, R. **(1974).** Education, language and history: An historical background to post-war *Ethiopia. The Ethiopian Journal of Education.* **Vii (1); 75-97.**

ከሰንጠረዡ መገንዘብ የምንችለው በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ መሪዎች ያልተተገበረው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በጣልያን ወረራ ወቅት መሞከሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያው መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም Unesco (1953) ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ያሳሰበበት ከዚህ ከጣልያን ወረራ ሀያ ዓመት በኂላ መሆኑ ከዚህ አንፃር ዘመኑን ታሪካዊ ያደርገዋል፡፡ በአጭሩ በኢትዮጵያ ውስጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጅማሬ ይህ ዘመን መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

በ1941 አፄ ሐይለስላሴ እንደገና ስልጣናቸውን እንደተረከቡ የመንግስታቸው የቋንቋ ፖሊሲ ግልፅ ሆኖ ወጣ፡፡ ይኸውም ሚሽነሪዎች በትምህርት ዘርፍ የሚሰማሩ ከሆነ ራሳቸውም አማርኛን መማር እንዳለባቸው፣ በትምህርትነትም ሆነ በማስተማሪያ ቋንቋነት በ1ኛ ደረጃ ውስጥ እንዲገለገሉበት እንዲሁም የአገሪቱም የስራ ቋንቋ አማርኛ እንደሆነ በ1944 ዓ.ም መመሪያ ተሰጣቸው፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘመንም ከአማርኛ ቋንቋ ውጪ በሌሎቹ የብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎች ትምህርት እንዲሰጥበት አለመታሰቡን እንመለከታለን፡፡

በዚህን ወቅት የኢትዮጵያ ትምህርት ዓላማዎች እንደ Dereje (2010) አገላለጽ ከጣልያን የመንግስትና የቢሮ ሰራተኞችን ማዘጋጀት ሲባል ነበር፡፡ ስለሆነም እንግሊዘኛ ቋንቋን በመማር የአገሪቱን እድገት ማፋጠን አንደሚቻል አቋም በመያዙና በተለይም የትምህርቱን አወቃቀር፣ የመማሪያ መጽሐፍትና ማጣቀሻ መጽሐፍት እጥረትና በመሳሰሉት ምክንያቶች የስርዓተ-ትምህርት ለውጥ አስፈላጊነቱ እየጎላ መጣ፡፡ ለለውጡ እንዲረዳ የትምህርት ሚኒስቴር አማካሪዎችና የመማሪያ መፃህፍት ከእንግሊዝና ለለውጡም እንዲረዳ እንደ ኬንያና ሱዳን ካሉ የአፍሪካ አገሮች ማምጣት ተጀመረ (Tekeste፣1990)፡፡ በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያ ከጣልያን ጋራ ጦርነት ውስጥ ስለነበረች እንግሊዝ የኢትዮጵያ አጋዥ ሆና ወደ ኢትዮጵያ በመግባቷ መንግስት ከፈረንሳይኛ ማስተማሪያ ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛና አማርኛ በመቀየሩ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ ትምህርት መሰጠት ተጀመረ፡፡ ቀስ በቀስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች በቁጥር እየበዙ በመምጣታቸው ተገቢ ስልጠና የወሰዱ መምህራን እጥረት በማጋጠሙ በትምህርት በኩል ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎች እየተበራከቱ መጡ፡፡

ይህ ወቅት አገራዊና ብሔራዊ አቋም የሚንፀባረቅበት ጊዜ በመሆኑ ወጣቱን ትውልድ የብሄረተኝነት ስሜት ለማነሳሳት እንዲረዳ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ይልቅ አማርኛ ቋንቋን እንዲማሩ ማድረጉ ለታሰበው ዓላማ ተግባራዊነት አጋዥ ሆኖ ተመረጠ፡፡ ይህ ሁኔታ ሁለተኛውና የተከለሰው ህገ-መንግስት እንዲወጣ በማስፈለጉም በ1955 በ(149ኛ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር15፣ አንቀፅ፣ 125 ) አዋጅ ላይ "የኢትዮጵያ የስራ ቋንቋ አማርኛ ሆኖ ተመረጠ፡፡ አዋጁ አረብኛን በመስጊድ፣ ግዕዝን በቤተክርስትያናት አማርኛን በትምህርት ቤቶች ውስጥ ስራ ላይ እንዲውል ፈቀደ፡፡ ከዚህ አዋጅም መረዳት የሚቻለው ሌሎች የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ለምንም ዓይነት አገልግሎት አለመመረጣቸውን ነው (Dereje፣ 2010፤ Seyoum፣1997፤ McNab፣ 1989) ፡፡

ከላይ የተገለፁትን ሀሳቦች Alemayehu (2012) እንደሚገልፁት በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የትምህርትና የቋንቋ ፖሊሲ ሁለት ተፅዕኖዎች ነበሩበት፡፡ አንደኛው ተፅእኖ በፈረንሳይ የሚመራው የቋንቋ ፖሊሲ ሲሆን ሁለተኛው ተፅእኖ ደግሞ የማእከላዊነት ፖሊሲ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከፈረንሳይ የቋንቋ ፖሊሲ አንፃር የፊውዳል ባለስልጣናትን ማዘመን ወይም ዘመናዊ ማድረግ በመሆኑ መንግስት ዋና ዓላማው ተቋማትን ማደራጀት፣ ወታደራዊ ሙያተኞችን የማጠናከር፣ትምህርት ቤቶችንና ዩኒቨርሲቲዎችን የመስራትና የማቋቋም እርምጃዎችን መውሰድ ጀመረ፡፡ Seyoum (1997) በበኩላቸው እነዚህ እርምጃዎች ሁሉ ከአማርኛ ቋንቋ ጋራ እንዲጣጣሙ የታቀዱ በመሆናቸው ለሌሎች የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ትኩረት ያለመደረጋቸውን ያመለክተናል፡፡ Moges (2010) ደግሞ የዘመኑ የቋንቋ ፖሊሲ ሁሉንም የአገር ውስጥ ቋንቋዎች ከመደበኛ ትምህርት ማስወገድና በአማርኛ ቋንቋ መሰረትነት አንድ ቋንቋና አንድ ባህል ማጎልበት ዓላማ እንደነበረው ያስረዳሉ::

ቋንቋና የትምህርት ፖሊሲ አተገባበር በሶሻሊስት ኢትዮጵያ ውስጥ ስንመለከት የዚህን ስርዓት አመሰራረት አብሮ ማጤኑ አግባብ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ከወታደሩ የተለያዩ ክፍለ-ጦሮች የተውጣጡና ራሳቸውን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ብለው (በኋላም ላይ ደርግ የተባሉት) መኮንኖች በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና አርሶአደሮች መራራ ትግል ውስጥ ያነሱዋቸውን ጥያቄዎች ይዞ ምላሽ ለመስጠት የሐይለስላሴን መንግስት ተካ (Mc Nab1989)፡፡ በዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ከነበረው ስርዓት የብሄር በሄረሰቦች መብት

በመጠኑም ቢሆን ለውጥ የታየበትና በመጠኑም የተከበረበት ዘመን ይመስል ስለነበረ የመጀመሪያው የደርግ የቋንቋ ፖሊሲ ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ የሌሎች የብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎችን በመጠቀም ለትምህርት ማዋል ጀመረ፡፡ ከዚህም የተነሳ የሳባ ፊደልን በመጠቀም በአስራ አምስት የብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎች መሰረተ ትምህርት እንዲሰጥ አደረገ፡፡ የቋንቋዎቹም ምርጫ ብዙ ህዝብ የሚናገረው ተብሎ (Benderና et al፣1976) ባስቀመጡት መስፈርት መሰረት አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ወላይታ፣ ሶማሌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጢ፣ትግሪኛ፣ ትግሬ፣ ሲዳማ፣ ሳሆ፣ ግዴዎ፣ አፋር፣ ከፋ፣ ሞቻና ኩናማ ቋንቋዎች ተመረጡ፡፡ እነዚህ ቋንቋዎች ይፃፉ የነበሩት በኢትዮጵክ (ሳባ) ፊደል በመሆኑ ለኩሽቲክ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን ለአንዳንድ ሴሜቲክ ቋንቋዎችም አጠቃቀም ከባድ እንደ ነበር መረጃዎች ያመለክታሉ (Cohen፣ 2000)፡፡ በተጨማሪም ቋንቋዎቹን የሚያስተምሩ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በመሆናቸው ችግሩን የበለጠ ከባድ ማድረጉ የማይቀር ነበር፡፡

የ1980ው ህገ-መንግስት አንቀጽ 2.5 "የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህዝብ ብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎች እኩል ናቸው" በማለት ይግለፅ እንጂ ህገ-መንግስቱ ከዚያ ስርዓት በፊት የነበሩት መንግስታት እንዳደረጉት ሁሉ አማርኛን በብቸኝነት በብሄራዊ ቋንቋነት ይዞ እስከ ስርዓቱ ማብቂያ ዘለቀ፡፡ ለዚህ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው የደርግ መንግስት በ1976 ባወጣው መርሃ-ግብር የብሄር ብሄረሰቦች የቋንቋ እኩልነት እንደተረጋገጠ ቢያውጅም በተግባር ግን ለቋንቋዎቹ ተሰጠ የተባለው መብት በአግባቡ ስራ ላይ ሳይውል በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት መስጫ ቋንቋ አማርኛ ብቻ ተመራጭ ሆኖ እንዲያገለግል ተደርጎ ቀደም ሲል የተዘረዘሩት ቋንቋዎች ለመሰረተ ትምህርት ማስተማሪያ ብቻ ተወስነው ቀርተዋል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር በ1983 ዓ.ም በኢትዮጵያ ጠቅላላ ትምህርት ላይ ያካሄደው የግምገማ ጥናት እንዳረጋገጠው የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የማስተማሪያ ቋንቋ ላይ ድክመቶች መኖራቸውን በተለይም ትምህርቱ አማርኛ ቋንቋ የአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ላልሆናቸው ተማሪዎች ማቅረቡ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አድርሷል (Dereje፣ 2010)፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ Seyoum (1997) እንደገለፁት የተወሰኑት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ይህን አማርኛ ቋንቋን በትምህርት ቤቶች፣ ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውድድርና በስራ ላይ ለመሰማራት እንደ አንድ መስፈርት

መጠቀሙ አግባብነት የሌለው መሆኑን ያስከተለውን ተፅዕኖ ሲገልፁና ሲቃወሙት ቆይተዋል፡፡

በአጠቃላይ በደርግ መንግስት የቋንቋና የትምህርት ስርዓት ሲጤን በቁጥር ብዙ ትምህርት ቤቶችና የትምህርት ተቋማት መከፈታቸው ቀደም ብለው ከነበሩት መንግስታት የተሻለ ሆኖ ታይቷል፡፡ በብሄር ብሄረሰብ ቋንቋ በማስተማር ረገድም ትምህርቱ አማርኛ ቋንቋን ጨምሮ ለመሰረተ-ትምህርት ዘመቻ በአስራ አምስት የብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋዎች መሰጠቱ ሌላው አዲስ ክስተት ነበር፡፡ ሆኖም የቋንቋዎቹ አገልግሎት በመሰረተ-ትምህርት ዘመቻ ላይ ብቻ በመወሰኑ የደርግ መንግስት የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲም ቀደም ብለው እንደነበሩት መንግስታት ሁሉ የአማርኛ ቋንቋን ብቻ ነጥሎ ለስራና ለትምህርት ቋንቋነት ማዋሉ ለሌሎች የብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎች በቂና ተገቢ ትኩረት አለመስጠቱን ያረጋግጣል፡፡

በ1991 ደርግ ከስልጣን ከተወገደ በኋላ የተቋቋመው አዲስ የሽግግር መንግስት የመጀመሪያ ስራው የብሄር ብሄረሰብ መብትና ግዴታ የሚከበርበትን ቻርተር ማርቀቅ ነበር፡፡ የሽግግር መንግስቱ ረቂቅ (1992) “ብሄር ሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን መብት በራሳቸው መወሰን፣ ማንነታቸውን መጠበቅና ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ማሳደግ ይችላሉ”፡፡ የሚል በመሆኑ ቻርተሩ ለብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎችና ማንነት ትኩረት ሰጥቶ ህዝቦች በማንነታቸው እንዲኮሩ ባህላቸውን እንዲያሳድጉና በቋንቋዎች እንዲገለገሉ፤ አንደኛ ደረጃን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውም እንዲማሩ ዕድል ሰጠ (Heughና et al፣ 2007) ፡፡ አዲስ የተነደፈው ትምህርት ፖሊሲም የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ማንኛውም ብሄር ብሄረሰብ በእናት ቋንቋው መማር እንደሚቻል ፈቀደ፡፡ ከዚህም የተነሳ የተለያዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት በስምንት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ማለትም በአፋን ኦሮሞ፣ በሲዳምኛ፣ በትግርኛ፣ በወላይትኛ፣ በሃዲይኛ፣ በከንባትኛ፣ በጌዴዮኛና ከፊችኛ ተዘጋጀ (Dereje፣2010)፡፡ በዚህ መሰረት አፋን ኦሮሞ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማስተማሪያ ቋንቋ የመሆን ዕድል አገኘ፡፡ የተነደፈው የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ ያለፈውን የትምህርት ስርዓት በመጥቀስ መጪው የትምህርት ስርዓት ምን መሆን እንዳለበት መርሀ-ግብሮቹ እንዴት መከናወን እንዳለባቸው የሚጠቁም አቅጣጫ አመለከተ፡፡በዚህ መሰረት፣በትምህርት ሚኒስቴር ሰነድ ላይ የተገለፀው ብዙ ቢሆንም ለአብነት፣

- *በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ትምህርታዊ ጠቀሜታ ስለአለውና ብሔር/ብሔረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ የመጠቀም መብታቸውን ስለሚያረጋግጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትና ተመጣጣኝ ሥልጠና በብሔር/ብሔረሰብ ቋንቋ ይሰጣል፣…*
- *በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ግንኙነት የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል፣…*
- *…የቋንቋ ትምህርቶች በጥራትና በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጡ ተገቢው ጥረት ይደረጋል (ትምህርት ሚኒስቴር፣(1994፣11)* ፡፡ የሚሉ ነበሩ፡፡

ይህም ለሥርዓተ ትምህርት ለውጥ፣ ለሥርዓተ ትምህርት መሣሪያዎች ዝግጅት፣ ለመምህራን ጉዳይና ስልጠና፣ ለትምህርት አደረጃጀት ለውጥ ትኩረት እንዲሰጥባቸው መንገድ ከፈተ፡፡ ስለዚህም በአገሪቱ ውስጥ የሚሰጡ የትምህርት ይዘቶች ተመርጠው በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ላሉ ተማሪዎች በመማሪያ መፃሕፍት አማካይነት እንዲደርሱ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችም እንደዚሁ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎችና እርከኖች በስራ ላይ እንዲውሉና ተማሪዎችም የሚያጋጠማቸውን ችግሮች የመፍታትና የመፍጠር ችሎታ እንዲያዳብሩ እንደዚሁም ለትምህርታቸው ኀላፊነትን ወስደው ለመማር በሚረዳው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዲማሩ ዕድል ሰጠ ፡፡

በርግጥ በ(1994) የትምህርት ሚኒስቴር ሰነድ ከላይ የተሰጡት ዝርዝር ሀሳቦች ቢቀመጡም "…የቋንቋ ትምህርቶች በጥራትና በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጡ ተገቢው ጥረት ይደረጋል…" ተብሎ በተገለፀው መሠረት በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደቱ የተማሪ-ተኮር አቀራረቡ በተቀመጡለት መስፈርቶች መሰረት ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ስለመዋሉ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን በዚህ ጥናት ዳራ ላይ እንደተገለፀው በነ Derebssa (2006)፤ Wuduና ሌሎች(2009) በተለያዩ ጊዚያት ውስጥ በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች እንዲሁም በተለያዩ የትምህርት አይነቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ያመለከቱት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ የአተገባበር ችግሮች መኖራቸውን ነው፡፡ነገር ግን በአፋን ኦሮሞ ትምህርት የተማሪ-ተኮር አተገባበር በአግባቡ ስለመተግበሩ ያመለከተ ጥናት ባለመታየቱ በዚህ ዙሪያ ጥናት ማድረጉ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.3. የኦሮሚያ መልካዓ ምድራዊ ገፅታና ህዝቦቿ

የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር በአዋጅ ቁጥር7/ 1985 በኢትዮጵያ ህገ-መንግስት 1985ዓ.ም እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር በጥንት መጠሪያው ፊንፊኔ ተቋቋመ ፡፡ እንደ Nasise (2009) ገለፃ የኦ/ብ/ክ/መ መልክዓ ምድራዊ ስፋት 363,136 ስኬር ኪሎ ሜትር

ሲሆን ይህ የኢትዮጵያን 34.3% ይሸፍናል፡፡ ኦሮሚያ ከትግራይ በስተቀር ከሁሉም ብሄራዊ ክልሎች ጋር ይጎራበታል፡፡ የመሬት አቀማመጡ ከ500-4377 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ የሚገኝ ነው፡፡ በ2007 የቤቶችና ህዝቦች ቆጠራ መሰረት 27,158,471 ህዝብ የሚኖርበት ሲሆን ከነዚህ ወንዶች 13,676,159 ሴቶች ደግሞ 13,482,312 ናቸው፡፡ በክልሉ አስራ ስምንት ዞኖችና ሶስት መቶ አስራ አንድ ወረዳዎች ይገኛሉ ፡፡

የባሌ ዞን በኦሮሚያ ክልል በደቡባዊ ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኝ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ስር ከሚገኙ ዞኖች ከቦረና በመቀጠል በስፋት የሁለተኛነት ደረጃ ያለው ነው፡፡ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ ከሚገኙት ዞኖች የባሌ ዞን 17.50% የሚሸፍን ሲሆን የድንበር ርዝማኔው ደግሞ 1686 ኪ.ሜ ይሆናል፡፡ የዚህ ዞን መገኛው ደቡብና ደቡባዊ ምስራቅ ኦሮሚያ ሲሆን በምስራቅ ከሱማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በምስራቅ ከምስራቅ ሐረርጌ፣ በሰሜናዊ ምስራቅ፣ ከምዕራብ ሐረርጌና በከፊል ከአርሲ ዞን፣ በሰሜን ከአርሲ፣ በምዕራብ ከምዕራብ አርሲና በደቡብ ከጉጂ ዞን ጋራ የሚዋሰን ነው (BZCTO፣2010፤ BZFDO፣2010) ፡፡

የባሌ ዞን አስራ ስምንት ወረዳዎችና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ሀያ የገጠር ከተሞችና ሶስት መቶ ሀምሳ አንድ የገበሬ ቀበሌ ማህበራት አሉት፡፡ የዞኑ ጠቅላላ ህዝብ ቁጥር 1,418,864 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 87.6% የገጠር ነዋሪዎች ናቸው (FDRE፣ 2008) የዞኑ ነዋሪ በአብዛኛው የኦሮሞ ጎሳ የሆኑ ህዝቦች የሚኖሩበት ነው፡፡ Mindaye (2005) እንዳብራሩት በአብዛኛው ነዋሪው ህዝብ የባሬንቱ ኦሮሞ ጎሳዎች ሲሆኑ በተጨማሪም የሌሎች ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦችም ይገኛሉ፡፡ አፋን ኦሮሞ በዞኑ ውስጥ ከሌሎች የብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋዎች ጋራ ይነገራል፡፡ ፡፡

በዞኑ ውስጥ የተለያዩ ባህላዊና ተፈጥሯዊ የቱሪስት መስህቦች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ የቱሪስት መስህቦች ውስጥ የባሌ ብሄራዊ ፓርክ አንዱ ሲሆን የሚሸፍነው ቦታ 2220 ስ.ኪ.ሜ ሆኖ ከ1500ሜ እስከ 377 ሜ. ከባህር ጠለል በላይ የሚገኝ ነው፡፡ በፓርኩ ውስጥ 64 የእንስሳት አይነቶችና 225 የአእዋፍ አይነቶች ይገኙበታል፡፡ ከ64ቱ የእንስሳት ዓይነት ውስጥ አስራ አንዱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ሲሆኑ ከ225 የአእዋፍ አይነቶች ውስጥ ደግሞ አስራ ስድስቱ በአገራችን ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪም የሶፍ ኦመር ዋሻ፣ የጥንት መስጂድ የሆነው ዲሬ ሼክ ሁሴን፣ የመዳወላቡ፣ ኦዳ ሮባና የመካነ-ህይወት

አቡነ-ተክለሐይማኖት ገዳም በዋናነት የቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎች ናቸው (BZCTO፣ 2010)።

በባሌ ዞን ውስጥ የሚገኙት ወረዳዎች ሀያ ሲሆኑ በዞኑ ዋና ከተማነት የምታገለግለው ሮቤ ከተማ ከአዲስ አበባ በ442 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። በከተማዋ የአንድ የመንግስት መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ (የሮቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ) ይገኛል። በዞኑ ውስጥ 170 አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች በሙሉ አፋን ኦሮሞ በማስተማሪያ ቋንቋነት እያገለገለ ይገኛል።

የአፋን ኦሮሞን ታሪካዊ አመጣጥና እድገት ስንመለከት ቀደም ባሉት ዘመናት በትምህርት ቋንቋነት ከመዋል ይልቅ በንግግር ተግባቦት ላይ ብቻ የተመሰረተ ሆኖ ቆይቷል። እንደ Tilahun (1992) አገላለጽ አፋን ኦሮሞ በሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ ኬንያና በኢትዮጵያ ውስጥም ከ35-40 መቶኛው ህዝብ ይናገረዋል። በተጨማሪ ከኩሽቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ ሁለት ሶስተኛ የሚሆነው ህዝብ የአፋን ኦሮሞ ተናጋሪ ነው (Gragg፣1982) ። መረጃዎቹ እንደሚጠቁሙት ሀረሪ፣ ሲዳማ፣ በርታ፣ ጉሙዝ፣ አኝዋክ፣አማራና ብዙ የኦሮሚያ አጎራባች የሆኑ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች አፋን ኦሮሞን ለተግባቦት ይጠቀማሉ (Mekuria፣1997)። ይሁን እንጂ ቋንቋው በስፋት እንደሚነገረውና ብዙ ህዝብ እንደሚጠቀምበት አልሆነም።

በአፋን ኦሮሞ መፃፍ የተጀመረው በ18ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ነው። በዚህ ወቅት የተማሩት የሙስሊም ኦሮሞ ምሁራን የእምነት ጽሁፎችን አረብኛና የግዕዝ ቋንቋዎችን በመጠቀም ይጽፉ ነበር።ይህ ማለት በአፋን ኦሮሞ ግጥም ለማቅረብ ጽሁፉን በአረብኛ ወይም ግዕዝን በመጠቀም መፃፍ ማለት ነው። በMohammed (1990) አገላለጽ ይህ ሁኔታ አፋን ኦሮሞ በትምህርት፣ በህግ፣ በባህል፣ በኢኮኖሚና በመንግስት አስተዳደር ውስጥ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ይህ ደግሞ በተራው የአፋን ኦሮሞ ጽሁፈት በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ሰፋ ብሎ እንዲታይ ረድቷል። በዚህ ወቅት ሁለት ጀርመናውያን የኦሮሞ ሰዋሰውና የኦሮሞ እንግሊዘኛ መዝገበ-ቃላት እንዳዘጋጁና የአዲስና ብሉይ ኪዳንን ወደ ኦሮሞ ቋንቋ መተርጎማቸው በማስረጃነት ይጠቀሳል (Pankhurst ፣ 1976)።

በ1950ና 1960ዎቹ ውስጥ በምስራቅ ኦሮሚያ ሼክ በክሪ ሰጳሎ የተባለ ሰው የአፋን ኦሮሞ ፊደልን ለማስተማር የነበረው ዕቅድ በተለያዩ ምክንያቶች ቢከሽፍም ኦንሲሞሰ ነሲብና አስቴር ገኖ በተባሉ ሰዎች በአፋን ኦሮሞ የተፃፉ ስራዎች እንደነበሩ መረጃዎች ያመለክታሉ (Mekuria፣1997)። የኦንሲሞስ ስራዎች የእምነትና ዓለማዊ የሆኑ የኦሮሞና ሲውድን መዝገበ-ቃላት፣ እግዚአብሄር ይመስገን፣ የሜጫ ጀግና፣ አዲስ ኪዳን፣ ኦሮሞ አንባቢያንን ቅድሚያ ያስተምራል፣ "የእግዚአብሄር ሰው ሆድ  የእግዚአብሄር ቤት ነው ወይስ የሰይጣን ማደሪያ ነው" የተባሉ ፅሁፎችን የሚይዝ ሲሆን አስቴር ገኖም ከአዕምሮአቸው ያመነጨዋቸው አምስት መቶ የሚሆኑ የኦሮሞ ዜማዎችን፣ ተረቶችንና ታሪኮችን አሳትመዋል (Mekuria፣1995)። በአጠቃላይ በኦሮሞ ምሁራን የተፃፉ ፅሁፎች አፋን ኦሮሞ እንደ ዛሬው የራሱ የሆነ ፊደልና በትምህርት ቤት እንደትምህርት ቋንቋ ሳይሰጥ በፊት በተለያዩ ሌሎች ቋንቋዎች ይጻፍበት እንደነበር እንረዳለን።

በ1991 ደርግ ከስልጣን ከተወገደ በኋላ የተቋቋመው አዲስ ሽግግር መንግስት የመጀመሪያ ስራው የብሄር ብሄረሰብ መብትና ግዴታ የሚያሳይ ቻርተር ማርቀቅ ነበር። የሽግግር መንግስቱ ረቂቅ (1992) ቻርተር “ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን መብት በራሳቸው መወሰንና ማንነታቸውን መጠበቅ እንዲሁም ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ማሳደግ ይችላሉ”። የሚል በመሆኑ ለብሄር ብሄረሰብ ቋንቋና ማንነት ትኩረት ሰጥቶ ህዝቦች በማንነታቸው እንዲኮሩ፣ ባህላቸውን እንዲያሳድጉና በቋንቋቸው እንዲገለገሉ፤አንደኛ ደረጃን  በአፍመፍቻ ቋንቋቸውም እንዲማሩ ዕድል ሰጥቷል Heughና et al (2007)። በህገ-መንግስቱ እንደተገለፀው "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግና ባሕሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው።" በማለት የኢትዮጵያ ህዝቦች በቋንቋቸው መማርና መፃፍ እንዲሁም ቋንቋቸውን ማሳደግ እንዳለባቸው ይገልፃል። በዚህ መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት መማሪያ የሚውሉ ቋንቋዎችን በመምረጥ  ላይ ትኩረት ማድረግ ጀመሩ።

በዚህ መሠረት አፋን ኦሮሞ በኦሮሚያ ክልል ለትምህርትና ለስራ ቋንቋነት ተመረጠ። Heugና et al (2007) እንዳብራሩት በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር አፋን ኦሮሞ የክልሉ የስራ ቋንቋ ሆኖ በመመረጡ ለ1ኛ ደረጃ ትምህርት ማስተማሪያ፣ ለመንግስትና ለግል

የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የመምህራን ማሰልጠኛ ቋንቋ ሆነ። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥም እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት መሰጠት ጀመረ ።

በአሁኑ ጊዜ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል ውስጥ የሚገኙ አስራሁለት የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ስልጠናውን የሚያካሄዱት በአፋን ኦሮሞ ነው። በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ አፋን ኦሮሞን እያስተማሩ የሚገኙት ጂማ ፣መደወላቡ፣ አዳማ፣ ወለጋና ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲዎች ሲሆኑ በመቀሌና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በንዑስ ትምህርትነት ይሰጣል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማስተርስ ደረጃም እየተሰጠ ይገኛል። ከዚህም ውጭ ማንኛውም የመንግስት መመሪያና የሚወጡ ጽሁፎች ቁቤ (የላቲን ፊደል) በመጠቀም እየተፃፉ ይወጣሉ።በTVና የFM ሬድዮ አገልግሎት ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

አፋን ኦሮሞ ከኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር በተጨማሪ በተለያዩ ክልሎችና የከተማ መስተዳደሮች ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ትምህርትነት ይሰጣል። እንደ Heughና ሌሎች (2007) ገለፃ በድሬደዋ፣ በሐረሪና አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች ውስጥ በተለይም በኦሮሞ ልዩ ዞን (ከሚሴ) ውስጥ ከ1ኛ-8ኛ ክፍሎች ትምህርት እየተሰጠበት ይገኛል።

በአጭሩ ከላይ የተብራሩ መረጃዎች ሲጠቃለሉ አፋን ኦሮሞ አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ የተለያዩ ተግዳሮቶች ቢያጋጥሙትም በአሁኑ ጊዜ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ትምህርት እየተሰጠበት ይገኛል። ይህም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መምህራን የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ ቋንቋ በመማር-ማስተማር ስነ-ዘዴ ትግበራ ላይ የተደረጉና የሚደረጉ ጥናቶች፣ ቋንቋውን የሚማሩ ተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉና በፍጥነት ከተፈለገው ዓላማ ላይ እንዲደርሱ ከማድረግ ባሻገር ለቋንቋው እድገትም ወሳኝ ሚና የሚጫወት በመሆኑ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል።

ምዕራፉን ለማጠቃለል በኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት ውስጥ የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲ ከቤተ እምነት ትምህርት እንደሚጀምርና የኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስትያን፣ የቁራንና የሚሲዮን ትምህርቶች በዋነኝነት ይታወቃሉ። በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

ትምህርትና የቁራን ትምህርት እምነትን ከማስተማር አልፈው በወቅቱ በአገሪቱ ውስጥ የሚፈለገውን የተማረ የሰው ሀይል በማዘጋጀት ረገድ ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ እንደነበር ተመልክተናል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት በ1908 ከተጀመረ በኋላ በአገርኛ ቋንቋ ትምህርት እንዲሰጥ የተለያዩ አዋጆችና መመሪያዎች ቢወጡም ከአማርኛ ቋንቋ በስተቀር ሌሎች የአገር ውስጥ ቋንቋዎች በትምህርት ቋንቋነት ተግባራዊ ሳይሆኑ ቆይተው ቀስበቀስ ግን ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሌሎች ብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎችም መሰጠት እንደተጀመሩ፣ በደርግ ዘመን ደግሞ መሰረተ ትምህርት እንዲሰጥባቸው አስራ አምስት የብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎች መመረጣቸውና በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ክልሎች በራሳቸው ቋንቋ መማር እንደሚችሉና አፋን ኦሮሞም እከከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ እየተሰጠ መገኘቱን ተመልክተናል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የሚከናወንበት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በተለይም የባሌ ዞንን መልክዓ ምድራዊ ገጽታ ለማስቃኘት ጥረት ተደርጓል፡፡ እንደዚሁም የዞኑ ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ፣ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት አጀማመርና በአሁን ያለበት ደረጃ ተብራርቷል፡፡ ይህም አፋን ኦሮሞ በታሪካዊ ጉዞው ያሳለፋቸውን ችግሮችና ያስመዘገባቸውን የዕድገት ውጤቶች እንዲሁም በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ አሁን ያለበትን ሁኔታ ማወቁ የጥናቱን ውጤት ከመረዳት አንፃር ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ይታመናል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፡- የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ስር በመማር-ማስተማር አቀራረቦች  የመምህር-ተኮርና የተማሪ-ተኮር እንደሆኑና የሁለቱ አቀራረቦች ምንነት እንዲሁም ባህሪያቸው  ምን እንደሚመስሉ ይብራራሉ፡፡ በመቀጠል ባለንበት ዘመን ውስጥ በተማሪዎች ላይ ፈጣን ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው አቀራረብ የተማሪ-ተኮር መሆኑ፣ መርሆዎቹ ምን እንደሆኑ፣በመማር-ማስተማር ውስጥ እንዴት ሊተገበር እንደሚችል በስፋት ገለፃ ይሰጥበታል፡፡ ከዚያም ለአቀራረቡ የክፍል ውስጥ አተገባበር ስኬት ሊሟሉ የሚገቡ ጉዳዮችና ተግባራት ምን ምን እንደሆኑ፣የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ሂደት ውስጥ በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ብልሃቶች፣ የአቀራረቡ ጠንካራ ጎኖች፣ በአቀራረቡ ላይ የሚሰሙ አሉታዊ ሀሳቦችና ተግዳሮቶች ተዘርዝረው ምዕራፉ በማጠቃለያ ያገኛል ፡፡

## 3.1. የማስተማሪያ አቀራረቦች

የመማር-ማስተማር ተግባር ጅማሬ ረዥም ዘመን እዳለው ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ Cruickshankና etal (1999) እንደገለፁት አብዛኛው የመማር-ማስተማሩ ተግባር ባልተፃፈ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይኸውም ሰዎች ስራቸውን እንደታላላቆቻቸው እንዴት መስራት እንደሚችሉ በማሳየት የተጀመረ እንደነበር ይነገራል፡፡ ስለዚህ ዘመን የተፃፈ ነገር ባለመኖሩ በአፋዊ ስነቃል ብቻ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተግባራቸው ሲተላለፍ ቆይቷል፡፡ በመቀጠል በጥንታዊ ስልጣኔ ዘመን ጽህፈት ከተጀመረ በኂላ በጥንታዊ ግብፅ፣ ቻይና፣ ኮሎምቢያና ሞሶፖታሚያ፣ ባቢሎንና በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ ባሉ አገራት ስለጀግንነት ታሪክ ግጥም በመፃፍ የመማር-ማስተማሩ ተግባር ይከናወን እንደነበረ ይነገራል፡፡ ነገር ግን ከ500-1600 ዓ.ዓ በሮማን ካቶሊክ የሐይማኖት አባቶች  መደበኛ ትምህርት ተጀምሮ ብዙ የእምነት ሰዎችንና የቢሮ ሰዎችን በማፍራት እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ትምህርት መስፋፋት ጀመረ ፡፡ ICDR (1999)ም እንደገለጸው በጥንታዊ የባሪያ አሳዳሪ ዘመን የባላባቶችን ልጆች የሚያስተምሩ ሰዎች የእምነትና መልካም ስነ-ምግባር በማስተማር  የመማር-ማስተማር ተግባር እንደተጀመረ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ የመማር-ማስተማሩ ተግባር በሂደት እያደገ መጥቶ አሁን በሚገኝበት ዘመናዊ አቀራረቦች ላይ ደርሷል፡፡

ከላይ ከተገለፀው ማብራሪያ በጥንት ዘመን የሚያውቀው ለማያውቀው የህይወት ልምዱን ሲያካፍል፣ እውቀት ያላቸው ለሌላቸው የሚያውቁትን ሲያስተምሩ እንደነበር አንዳች ግንዛቤ ሊገኝ ችሏል፡፡ ከዚህ ገለፃም ከአንድ ወገን ለሌላው ወገን እውቀት መተላለፉ ከመምህሩ ወደ ተማሪው የሚሸጋገር እውቀት መኖሩን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመምህር-ተኮር አቀራረብን ያመላክታል፡፡

አንዳንድ የቋንቋ ምሁራን የማስተማሪያ ዘዴን በተለያዩ ምድቦች ያስቀምጣሉ፡፡ ለምሳሌ Kumaravadivelu (2006) አገላለጽ ቋንቋን ለማስስተማር በሚከተሉት ዘዴዎች ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡ እነሱም፡- ቋንቋ-ተኮር ዘዴ፣ተማሪ-ተኮር ዘዴና ትምህርት ተኮር ዘዴ ናቸው፡፡

1.የቋንቋ -ተኮር ዘዴ፡- መሰረታዊ ትኩረቱ በቋንቋ ቅርጽ ላይ ነው፡፡ይህ ዘዴ ከሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ አዳምጦ መናገር ዓይነት ተማሪዎች የማለማመድ እድል ቅድሚያ እንዲያገኙ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ሲባል የታላሚ ቋንቋንውን መዋቅር ከቅርጽ ጀምሮ ከመጠቀም በፊት ይለማመዳሉ፡፡ በአጠቃላይ የፊደል ቅርጽንና ህግጋቱን አውቀው ይተገብሩታል ማለት ነው፡፡

2.ተማሪ-ተኮር ዘዴ፡- ይህ የተማሪ-ተኮር ዘዴ መሠረታዊ ትኩረቱ በተማሪዎች ምርጫ፣ፍላጎትና ሁኔታዎች ላይ ነው፡፡ይህ ዘዴ ከሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ እንደ ተግባቦታዊ ቋንቋ መማር ተማሪዎች በራሳቸው በመግባባት በቋንቋ ተግባቦት አውድ ውስጥ ገብተው ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ የሚያደርግ ነው፡፡ ተማሪዎች በራሳቸው በቅድመ ምርጫ የቋንቋ ሰዋሰው ቅደም ተከተል በመምረጥና በተግባር የሚያውሉበት እድል ይሰጣቸዋል፡፡

3.መማር-ተኮር፡- መማር-ተኮር ዘዴ መሰረታዊ ትኩረቱ በቋንቋ መማር ሂደት እውቀት ላይ ነው፡፡ ይህ ዘዴ በሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ ከተፈጥሯዊ የቋንቋ አቀራረብ ጋር ይመሳሰላል፡፡ተማሪዎች በክፍል ትምህርት ውስጥ ገደብ በሌለው ትርጉም ባለው ውይይትና በችግር ፈቺ ተግባራት በመሳተፍ በስራ ላይ ማዋል ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው የማስተማሪያ ዘዴዎች አያሌ ቢሆኑም የትምህርት መማሪያ አቀራረቦች አንዳንዶቹ በመምህራን የሚመሩ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ተማሪዎች ራሳቸው በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ከዚህ

በመነሳት ሁለት ዓይነት የማስተማሪያ አቀራረቦች እንዳሉ Moore (2001)ና Harmar፣ (1998) ይገልፃሉ፡፡ እነሱም በመምህራን የሚመራው መምህር-ተኮር አቀራረብና ተማሪዎችን በትምህርቱ ሂደት ውስጥ አሳታፊ የሚያደርገው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ናቸው ፡፡ እነዚህን የማስተማር አቀራረቦች ለዚህ ጥናት አስፈላጊ በመሆናቸው ቀጥለን በጥልቀት እንመለከታቸዋለን፡፡

### 3.1.1. የመምህር-ተኮር አቀራረብ

መምህር-ተኮር ወይም መምህር መራሽ አቀራረብ በጣም ጥንታዊና ተለምዷዊ፤ ብዙ መምህራን እየተጠቀሙበት እስከ አሁን ያለ በመምህራን የሚመራ አቀራረብ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ መምህራን በመናገርና በመፃፍ ንቁ ሆነው ተግባራትን የሚያከናውኑበት ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በተቃራኒው ፍዝ ሆነው መምህራንን ይከታተላሉ፤ ከጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስታወሻ ይወስዳሉ (Harmar፣ 1998)፡፡ Nunan (1988)ና Moore (2001) በበኩላቸው በዚህ አቀራረብ ውስጥ በክፍልና ከክፍል ውጭ በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉት መምህራን ብቻ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ በአጭሩ መምህራን በአቀራረቡ ውስጥ ቁልፍ ሰዎችና የክፍሉን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩ፣ የሚመሩና ገለፃ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

መምህር-ተኮር በአዎንታዊያን (Positivist) አተያይ ይደገፋል፡፡ በእነዚህ የአዎንታውያን ቡድኖች አመለካከት ዕውቀት ቋሚ በመሆኑ የማስተማር ግቡ ያንን ቋሚ ዕውቀት ወደ ተማሪዎች ማስተላለፍ ነው፡፡ የዕውቀት ማዕከላት መምህራን ናቸው፤ መምህራን የያዙት መረጃም ቀስ በቀስ ወደ ተማሪዎች ይተላለፋል (Arseneauና Rodenburg፣ 1998፣ 63)፡፡ በተመሳሳይ መንገድ long (2000) እንደሚገልፁት በአዎንታውያን አመለካከት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ልዝቦች ናቸው፡፡ ተግባራቸውም ፀጥ ብሎ ምልከታ ማድረግና ከመምህራን የሚተላለፈውን እውነታዎች ማስታወስ ነው፡፡ መምህራንም ከማስተማር ስነ-ምግባር አንፃር ገለፃው ተገቢ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እውነታዎችን በሽምደዳ መማሩ የተሳካ ያደርጋል ብለው ስለሚያምኑ የመምህራን ተግባራት ከመፃህፍት ወይም ከመርሀ-ትምህርት ላይ ገለፃ መስጠት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተፈላጊና ተገቢ እንደሆነ ሀሳብ የሚሰጡ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል Zulukufና Trombly (2001) በበኩላቸው የመምህር-ተኮር አቀራረብ መምህራን በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች

ፊት ለፊት በመሆን የሚታወቁ እንደሆኑ አስረድተው አብዛኛውን ጊዜ መምህራን በመናገርና በተማሪዎች ተግባራት ላይ ውሳኔ ሰጪዎች ናቸው፡፡ ከላይ የተብራሩትን የመምህር-ተኮር አቀራረብ ባህሪያት አስመልክተው Tudor (1993) ሲያስረዱን በቋንቋ ትምህርት ወቅትም ተመሳሳይነት ቢኖረውም ቀጥለው የቀረቡት ሁኔታዎች ጎልተው ይስተዋላሉ፡፡ አዋቂነት /Knower/ መምህራን በታላሚው ቋንቋና በስነ-ዘዴ ምርጫ ራሳቸውን ዋነኛ አዋቂ እንደሆኑ በመቁጠር፤ ተማሪዎች ምን መማር እንዳለባቸው ወሳኞች ናቸው፡፡

በመምህር-ተኮር አቀራረብ ውስጥ የመምህራን ትኩረት በቀለም ትምህርት ላይ ብቻ በመሆኑ በተዘጋጁት የተማሪዎች መማሪያ መፃህፍትና ሞጁሎች ይጠቀማሉ፡፡ Rosenshine (1979)፣ Eggenና kauchax (1996) ይህን አስመልክተው ማብራሪያ ሲሰጡ በዚህ አቀራረብ ውስጥ መምህራን በተዘጋጁት ማቴሪያሎች ላይ ጥገኛ ስለሚሆኑ ለተማሪዎች የሚሰጡት ተግባራትም ከነዚህ ውጪ አይሆኑም፡፡ ተማሪዎቻቸው በህይወታቸው ዘመን ራሳቸውንና ማህበረሰባቸውን የሚለውጥ ዕውቀት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎቹ የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች በሚፈቱበት ብልሃት እየቀረበላቸው ባለመሆኑና ትምህርቱ በራሳቸው ፈጠራ ያልቀረባላቸው በመሆኑ ነው፡፡

አብዛኛውን ጊዜ መምህራን ራሳቸው የተለያዩ ተግባራትን በማደራጀትና በማሻሻል፣ ተማሪዎቻቸውን እነሱ በፈለጉት አቅጣጫዎች በማነሳሳት፣ በማበረታታትና ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ድርሻቸውን ይወጣሉ፡፡ ከዚህ አንፃር የመምህር-ተኮር አቀራረብን በስራ ላይ ለማዋል የተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ Moore (2001)ና ICDR (1999) እንዳብራሩት በዚህ አቀራረብ ውስጥ የሚተገበሩ ብልሃቶች ጥቂቶቹ ገለፃ ፣ ትዕይንተ ገለፃና ጥያቄና መልስ ሲሆኑ ማብራሪያቸውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**1. በገለፃ /lecture/ ወይም በማብራሪያ ማስተማር ፡-** መምህራን ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙበት ብልሃት ነው፡፡ የዚህ ብልሃት ጠቀሜታው በቁጥር ብዙ ለሆኑ ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊ መልዕክት ማስተላለፍ የሚቻልበት መሆኑ ነው፡፡ በገለፃ ማስተማር መምህራን በመፃህፍት፣ በድረ-

ገጽ፣ በመቅረፀ ድምጽ ወይም በኮምፒውተር በመጠቀም በተማሪዎችና በመምህራን መካከል መስተጋብር ሳይፈፀም ያለ ዕረፍት የሚካሄድ ነው፡፡

በገለፃ ማስተማር የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ከጠንካራ ጎኖች ውስጥ ተማሪዎች ባለፉት ቀናት የተማሩትን በማስታወስ በዕለቱ የሚሰጠውን ትምህርት በመግቢያው ላይ ለመናገር ያስችላል፡፤ ከዚህም ውጪ መምህራን አጫጭር ገለፃን በመጠቀም በመጠኑም ቢሆን ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባራት ውስጥ በማሳተፍ እንዲማሩ ያስችላቸዋል፤ቦታ ካለና ሰሚ ከተገኘ ለብዙ ተማሪዎች ሙሉ መልዕክት ማስተላለፍ ያስችላል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ዕቅድ ለማውጣትና ይዘቶችን ለማደራጀት ጊዜን ሊወስድ መቻሉ፣ የተማሪዎችን ተሳትፎ ገዳቢ መሆኑና ፍዝ እንዲሆኑ ማድረጉ እንደ ደካማ ጎን መውሰድ ይቻላል (Moore፣ 2001)፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳን መምህር ተኮር አቀራረብ ተማሪዎችን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ አያደርግም ቢባል መምህራን በገለፃው መካከል ተማሪዎቹ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ካመቻቹላቸው ተሳታፊ እየሆኑ መማር መቻላቸውን ነው፡፡ በተጨማሪም የዚህን ብልሃት ደካማ ጎን በማወቅ መምህራን ራሳቸውን ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡

**2. ፋታ ባለው ገለፃ የማስተማር ብልሃት /Exposition With instruction teaching Method/ ፡-** ፋታ ባለው ገለፃ ማስተማር መምህራን የትምህርቱን ጭብጥ እየተናገሩ ወይም ለተማሪዎቻቸው መረጃ እየሰጡ በመማር-ማስተማሩ ሂደት መካከል ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያነሳሱበትና ገለፃውን መከታተላቸውን የሚያረጋግጡበት መንገድ ነው፡፡ Moore (2001) እንደገለፁት ይህ ዘዴ መምህራንም የመማር-ማስተማር አካሄዳቸውን በመገምገም የማስተማር ሂደታቸውን ይበልጥ በሚረዱበት መንገድ እንዲቀይሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ብልሃት ተማሪዎችን በማሳተፉ፣ጊዜን በመቆጠቡና እንደሁኔታው የማስተማሪያ መንገዶችን ለመቀያየር በማስቻሉ በጠንካራ ጎኑ ይወሳል፡፡ ይሁን እንጂ የመምህራንን ጥያቄዎችና የተማሪዎችን መልሶች በማዕቀፍ በማቀናጀቱ በተለያዩ መንገዶች አስበው እንዳይመልሱ ሊገድባቸው በመቻሉ ይህ እንደ ደካማ ጎን ያስፈርጀዋል (Moore፣2001) ፡፡ በምሁሩ እንደተገለፀው ይህ ፋታ ባለው ገለጻ ማስተማር ተማሪዎችን በመማር-ማስተማሩ ሂደት

ውስጥ በማሳተፉ ረገድ ከገለፃ ዘዴ ውስጥ የተሻለ በመሆኑ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ከፈለጉ ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል፡፡

## 3. በጥያቄና መልስ የማስተማር ብልሃት (Socratic Teaching method)

በጥያቄና መልስ የማስተማር ዘዴ መምህራን ከተማሪዎች መረጃን አግኝተው በመልሶች ላይ መስተጋብር በመፍጠር የሚተገበር ዘዴ ነው፡፡ Moore (200) እንደገለፁት በጥያቄና መልስ የማስተማር ዘዴ በቀጥታ ለተማሪዎች ትምህርት በመስጠት ላይ የሚያተኩር ሳይሆን ከተማሪዎች መረጃን አግኝተው የሚያስተምሩበት ስልት ነው፡፡ ብልሃቱ ሙሉ በሙሉ ተራክቧዊ ሲሆን በተማሪዎች አነስተኛ ቡድን፣ በጥንድና በተናጠል በተማሪና መምህራን ወይም በተማሪና ተማሪ መካከል ውጤታማ ሆኖ ይተገበራል፡፡

በጥያቄና መልስ የማስተማር ብልሃት ማስተማር የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ከጠንካራ ጎኖቹ ብንነሳ ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት በማሳተፍ እንዲማሩ ያስችላቸዋል፤እያንዳንዱ ተማሪ የድርሻውን እንዲወጣ እድል ይሰጣል፤መምህራን ቅድሚያ በሚገባ እንዲዘጋጁ ያደርጋቸዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ቅድሚያ ዝግጅት ካለደረጉበት ተማሪዎች ስህተት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፤ ዕቅድ ለማውጣትና ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት ጊዜን ሊወስድ መቻሉ፣ አንዱ ተማሪ ምላሽ ከሰጠ በሱ ላይ ጥገኛ ሊሆኑ ይችላሉ (Moore፣2001)፡፡

የምሁሩ ማብራሪያ ሲገመገም በገለፃ ብልሃት የሚጠቀም መምህር በተወሰነ ደረጃ ተማሪዎችን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል የጥያቄና መልስ ብልሃት የተሻለ ነው፡፡ ስለሆነም በትምህርቱ ይዘት ላይ ተመስርቶ ተግባራዊ ለማድረግ ደካማጎኑ ላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በመረዳት ዕቅድ ማውጣት ተገቢ ነው፡፡

## 4. በትዕይንተ ገለፃ የማስተማር ብልሃት (Demonstration Teaching Method)

በትዕይንተ-ገለፃ ማስተማር መምህራን ወይም ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በተማሪዎች ፊት ለፊት የሚታየውን ነገርና ነገሩ ምን እንደሆነ፣ ለተማሪዎች በማሳየትና ማብራሪያ በመስጠት ትምህርቱን የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው፡፡ እንደ Moore (2001) አገላለጽ ይህ ብልሃት ትምህርቱ በተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና ባሉት

ማቴሪያሎች  የሚሰጥበት ነው፡፡ የተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሲባል ትምህርቱን የሚያቀርቡት መምህራን የትምህርት ይዘቱን የበለጠ ግልጽ እንዲያደርግላቸው ይረዳናል ብለው አስበውበት የሚያዘጋጁት የትምህርት መሳሪያ ነው፡፡ ባሉት ማቴሪያሎች ማስተማር የሚባለው ደግሞ ቀደም ተብሎ መምህራን በፈለጉት ጊዜ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ እንዲጠቀሙበት ተዘጋጅተው የተቀመጡ ማቴሪያል ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ የመምህር-ተኮር የማስተማር አቀራረብ ወይም ተለምዷዊው ዘዴ ተማሪዎችን በጥቂቱ  የሚያሳትፍ ስልትም እንዳሉት ከተሰጡት ማብራሪያዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በተለይም እረፍት ባለው ገለፃና በትዕይንተ-ገለፃ ውስጥ የተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መሳተፍ በጥቂቱ ሊታይበት ይችላል፡፡ ምንም እንኳን የመምህር-ተኮር አቀራረብ የመምህራን የበላይነት ቢታይበትም የራሱ የሆኑ ጠንካራ ጎኖች አሉት፡፡ Cruickshankና etal (1999) እንደገለፁት ብዙ መልዕክቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማስተላለፉና ውስብስብ ይዘቶችን ማብራራቱ፣ ከጥንካሬዎቹ የሚጠቀሱ ሲሆኑ ለተማሪ ፍላጎት፣ ነጻነት፣ በጥልቀት ለማሰብ ትኩረት አለመስጠቱ ደካማ እንዲሰኝ አድርጎታል፡፡ በአጭሩ መምህር-ተኮር አቀራረብ ከላይ በተለያዩ ምሁራን እንደተገለፁት በተማሪዎች ላይ ጫና በማድረግ በራሳቸው ትምህርት ላይ ውሳኔ እንዳይሰጡ፣ በነፃነት መማር እንዳይችሉ በመገደብ ከመምህራን ብቻ እውቀት እንዲጠብቁ የሚያደርግ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 3.1.2. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ምንነት

ተማሪ-ተኮር አቀራረብ አንዳንዴ "ህፃናት ተኮር" ተብሎ ይጠራል፡፡ ስያሜውም በክፍል ትምህርት አቀራረብ ወቅት ቅድሚያ ለተማሪዎች ወይም ለህፃናት ትኩረት የሚሰጥ መሆኑን ያሳየናል፡፡ እንደ (Weimer፣2002)፣ Tudor (1996)፣Mccombsና Whisler (1997) አገላለጽ በትምህርት ሂደት ተማሪዎች በነፃነት ወይም በራሳቸው እየተመሩ የሚማሩበት፤ ለትምህርታቸው ኃላፊነትን የሚወስዱበት አቀራረብ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ውስጥ ተማሪዎች የሚታዩት ንቁ ሆነው በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ ስለሚያደርጉ፣ ይህ ከተለመደው የመምህር-ተኮር አቀራረብ ለየት ያደርገዋል፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ቃሉ አዲስ ቢመስልም በተለያዩ የቋንቋ ትወራዎች ውስጥ በሌላ ስያሜ ይጠራ እንደ ነበር የመስኩ ጥናት አድራጊዎች ያብራራሉ (Tudor፣1996)፡፡ ቢሆንም ከዘመናዊነት አንፃር ለምሳሌ እንደ Smith (2004)ና ሌሎች የመስኩ ተመራማሪዎች

እንደሚያብራሩት ተማሪዎች በቡድን ተግባራትና የእርስ በርስ መስተጋብር ውስጥ ተሳታፊ በመሆን በክፍል ውስጥ የነባራዊውን አለም አውድ የሚፈጥሩበት መንገድ ነው፡፡ እኚሁ ምሁር Tourn (1995)ን ጠቅሰው ሲያክሉ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቡድን መስርተው የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ ለመማር-ማስተማር ሂደት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩበት አቀራረብ ነው፡፡ ሁለቱም ብያኔዎች አቀራረቡ ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገና በቡድን ሆነው እርስ በርስ እየተወያዩ ተግባራትን የሚያከናውኑበት መንገድ እንደሆነና በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተመልካች ሳይሆኑ ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበት ሀሳብ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት ተሳትፈው የእርስ በርስ እውቀት የሚከፋፈሉበትና የሚገበያዩበት ትምህርት ማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ውስጥ ተማሪዎች በሚሰጠው ገለፃና መፃህፍት ማንበብ ብቻ እውቀት የሚያገኙበት ሳይሆን መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በሳይንሳዊ መንገድ መመዝገብ፣ በውይይት፣ ነገሮችን በማነፃፀር፣ በመተንተን፣ ማጠቃለያ በመስጠትና ጉዳይን ለማወቅ በመመራመር፣ በክፍል ውስጥ ተግባቦትን በመፍጠርና የመሳሰሉትን ዘዴዎች በመጠቀም ብቃታቸውን የሚያሳዩበት ነው (Weimer፣2002)፡፡ ተማሪዎች አንድ እውነታ ያለው መረጃ ከመምህራን ወይም ከመፃህፍት ሲተላለፍላቸው በንቃትና በፈጣሪነት ጉዳዩን ይተነትናሉ፤ ያስባሉ፤ ይወያያሉ፤ የተረዱትን በተለያዩ መንገዶች ያብራራሉ፤ በቻርትና ግራፎች ይገልፃሉ፤ ዘገባ ያቀርባሉ (ICDR፣1999)፡፡ በአጭሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ሙሉ በሙሉ እየተሳተፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቀረበላቸው ትምህርት ዓላማ ላይ የሚደርሱበት መንገድ ነው፡፡

### 3.1.2.1. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርሆዎች

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚተገበርበት የራሱ የሆኑ መርሆዎች አሉት፡፡ መርህ ማለት የተማሪ-ተኮር-አቀራረብን በስራ ላይ ለማዋል መምህራንና ተማሪዎች ሊያውቁት የሚገባቸው የተግባራት መፈፀሚያ ስልቶችን የሚያሳይ ጽንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ እነዚህንም መርሆዎች Brandsና Ginnis (1986) እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

1. ተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ ማድረጋቸው አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም ሙሉ ሙሉ የውጭያዊ ግብዓት ጫና ሳያስፈልግ በውስጣዊ ችሎታቸው መማር እንደሚችሉ ያሳያል፡፡ ይህ ማለት መምህራን ሁኔታዎችን በማመቻቸት ብቻ ተማሪዎቹ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ሆነው ዕውቀት የሚያገኙበት በመሆኑ የግንባታውያንን ትውር ተግባራዊነት ያረጋግጣል ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች ውስጣዊ ችሎታ ቢኖራቸውም ከአደጉበት ማህበረ-ባህላዊ ሁኔታ አንፃር ደግሞ አቅጣጫን ለማመላከት እገዛ ያስፈልጋቸዋል፡፡ መምህራንም እገዛ ሲያደርጉ ተማሪዎች ካደጉበት ማህበረሰብ ባህልና ልማድ አንፃር መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ማለት ምንም እንኳን ተማሪው ራሱን ችሎ መማር ዕድል መስጠቱ ተገቢ ቢሆንም ተማሪው ያደገበት ማህበረሰብ ያለው ባህልና ልማድ መርሳት የለበትም ማለት ነው፡፡

2. ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ሙሉ ኃላፊነትን ይዘው መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ራሳቸው ከሰሩ ተምረዋልና ያውቃሉ፡፡ አንድን ነገር መማር በግል ውስጣዊ ስሜትና መነሳሳት የሚከናወን በመሆኑ ተማሪዎች እርስ በርስ በሚያደርጉት መስተጋብር መሳተፍ እውቀት የሚያገኙበት ስርዓት እንደሆነ (Vigotisky፣1978) ያመለክታሉ፡፡ በተራ ቁጥር አንድ ላይ እንደተገለፀው ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ሙሉ ሐላፊነት ይዘው ተሳታፊ መሆን እንዲችሉ መምህራን አስቀድመው የሚከተሉት የማስተማር አቀራረብ ምን እንደሆነ አውቀው ለተማሪዎቻቸውም ስልጠና ሊሰጡ ይገባል Mccombsና Whisler (1997)፡፡ ስልጠናው ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን ያለፍርሃት እንዲገልፁ፣የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካት የበኩላቸውን እንዲወጡ፣ ሀሳባቸውን እርስ በርስ እንዲቀባበሉ፣ የራሳቸው ችሎታ እስከምን ድረስ እንደሆነ ስለሚረዱ መማር ማስተማሩን ለማፋጠን ያስችላቸዋል፡፡

3. ትምህርት አግባብ የሚኖረው ተማሪዎቹ ለሚማሩት ነገር ፍቺ በመስጠት ከተገነዘቡ፣ በስርዓተ-ትምህርት መረጣ ውስጥ ከተሳተፉ፣ የመማር-ማስተማሩ ዓላማዎች በችሎታቸው በመምረጥ፣ በመግለጽና በሚያስፈልጉት ነገሮች ውስጥ ስምምነታቸውን ከገለፁ ነው፤ የሚማሩትን ነገር ከሚያውቁት ነገር ላይ መተርጎም

ወይም ፍቺ መስጠት አግባብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ አገሮች በስርዓተ-ትምህርት መረጣ፣ የመማር ማስተማሩን ዓላማዎች በችሎታቸው መምረጥና መግለፅ ለተማሪዎች የተሰጠ መብት ተደርጎ ሲቆጠር አይታይም፡፡ እንኳን ተማሪዎች ትምህርቱን የሚሰጡ መምህራንም በሚዘጋጀው ስርዓተ-ትምህርት ቀረፃ ላይ በበቂ ሁኔታ ተወያይተው ስራ ላይ ያውሉታል ማለት አያስደፍርም፡፡ ሆኖም ግን ለተማሪዎች ይመጥናል ተብለው በስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ባለሙያዎች ተመርጠውና ፀድቀው እየተሰራበት የሚገኙት የትምህርት ዓላማዎችና ማቴሪያሎች ተማሪዎችን ማማከል ይገባቸዋል፡፡

4. መምህራን ለመማር-ማስተማሩ ሂደት ሁኔታዎችን የሚያመቻቹና በትምህርት መርጃነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ከዚያ ውጭ “ያለውን ዕውቀት ለተማሪዎቼ አስተላልፋለሁ” ካሉ የተማሪዎችን ተሳትፎ በመገደብ የአንድ ወገን መረጃ ብቻ ይሆናል፡፡ በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎች ዕውቀት አስተላላፊዎች ሳይሆኑ ተማሪዎች ራሳቸው በራሳቸው እንዲማማሩ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹና የሚረዱ ሆነው መቅረብ አለባቸው፡፡

5. ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ከልምዳቸውና ካላቸው የዕውቀት ዳራ ጋር ማዛመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዕውቀታቸውንና ያላቸውን ልምድ መሳ ለመሳ ማስኬድ ከቻሉ የመማር-ማስተማሩ ሂደት በፍጥነት ከተፈለገው ግብ ላይ ይደርሳል፤ የተማሪ-ተኮር አቀራረብም በአግባቡ ይተገበራል፡፡

በአጠቃላይ በመስኩ ጥናት ካደረጉት ምሁራን የምንገነዘበው የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር መምህራን ብቻ ሳይሆኑ ተማሪዎችም በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ኃላፊነትን ተረክበው የሚሰጣቸውን ተግባራት የሚፈጽሙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እየተሳተፉ ከሚያከናውኑት ተግባራት፣ መልመጃዎችና የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ለወደፊት በነባራዊው ህይወታቸው ውስጥ ለሚያጋጥማቸው ችግሮች መፍትሄ ሰጪ፣ ሓላፊነትን ተረካቢና ተባባሪ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ በአጭሩ ከላይ የተብራሩት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርሆዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት ለተማሪዎች ሙሉ ሆነው ሲገኙ ነው፤ያም ሆኖ እንከን የሌለበት ፍፁም ላይሆን ስለሚችል የክፍል ውስጥ ተግባራዊነቱን በጥናት መቃኘቱ ተገቢ ነው፡፡

### 3.1.2.2. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አስፈላጊነት

በማንኛውም የትምህርት እርከን ውስጥ የሚሰጡት የመማር-ማስተማር ዓላማዎች በተማሪዎች ላይ አንዳች ለውጥ ለማምጣት ሲባል የተዘጋጁ ናቸው፡፡ Ambeluና Geberegzihabher (2011) እንደገለፁት ይህ በተማሪዎች ላይ እንዲመጣ የተፈለገው ለውጥ የተለያዩ ሙያዊ ችሎታዎች የሚገበዩበትን አቅጣጫዎች፣ ችግሮች የሚፈቱበትን መንገዶች፣ ለዘለቄታው በአእምሯቸው ውስጥ ሊቆይ የሚችል ጠቃሚ ነገር የሚቀስሙበት ስርዓት የመፍጠር ጉዳይ ነው፡፡ በዓለም ላይ ለብዙ ዓመታት በስፋት ሲተገበር ከነበረው የመምህር-ተኮር አቀራረብ ይበልጥ ለተማሪዎች ትምህርት መማር ጠቀሜታ አለው ተብሎ የተመረጠው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን የመማር አቅም የሚጨምር እንደሆነ ምሁራን በጥናታቸው አመልክተዋል፡፡ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በማንኛውም የትምህርት እርከን ውስጥ ተግባራዊ እንዲደረግ የሚያሳስቡት ለብዙ ምክንያቶች ነው፡፡ እንደ Ambeluና Geberegzihabher (2011) አገላለጽ እነዚህ ምክንያቶች ለተማሪዎች ምርምርን ለማስተዋወቅና የማሰብ ክህሎት እንዲያጎለብቱ ለማድረግ፣ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት ውስጥ ሀላፊነትን እንዲወስዱና የሚማሩትን ትምህርት አስደሳች እንዲያደርጉት ለማነሳሳት፣ የአካባቢያቸውን ችግሮች ለመፍታትና ለመሳሰሉት ነው፡፡

ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ልዩ ልዩ ተግባራት እያከናወኑ በንቃት ተሳታፊ ከሆኑ በአጠቃላይ መማር እንዲፋጠንና የበለጠ ደግሞ ቋንቋ መማር በተሻለ መንገድ ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በተለምዳዊው የመምህር-ተኮር አቀራረብ መማር-ማስተማሩ ከተከናወነ ውጤቱ የዚህ ተቃራኒ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርቱ ከቀረበላቸው ይበልጥ የትምህርቱን ይዘት አውቀው መረጃዎቹ ለረዥም ጊዜ ከአእምሯቸው ውስጥ እንዲቆይና በህይወታቸው ዘመን ለሚያጋጥማቸው ማንኛውም ነገር ውስጥ እንዲጠቀሙበት ያስችላቸዋል፡፡ ይህን አስመልክተው Bonewellና Eison (1991) እንዳብራሩት ትምህርቱ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሲቀርብ የሚከተሉት ሁኔታዎች ይስተዋላሉ፡፡

- ተማሪዎች ዝም ብለው ከማዳመጥ ይልቅ በተለያዩ ክንዋኔዎች (በማንበብ፣ በመወያየት፣ በመፃፍና በሌሎች ክንውኖች) ውስጥ በመሳተፍ ተግባራት

በማከናወን ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ በስራ አለም ውስጥ የአካባቢያቸውን ችግሮች በመፍታት ረገድ ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋቸዋል።

- የትምህርቱ መረጃዎች ከመምህራን ወደ ተማሪዎች በመተላለፍ ላይ ከማተኮር ይልቅ ክህሎትን በማሳደግ ተግባር ላይ ያመዝናሉ (በመተንተን፣በማዋኂድና በመገምገም) ላይ ማለት ነው።
- ተማሪዎች አመለካከታቸው ተቀይሮ እሴታቸውን በመጠበቅ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል።
- በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርቱ ከቀረበላቸው የተማሪዎች መነሳሳት ከፍተኛ ነው፤
- ተማሪዎች ከመምህሮቻቸው ፈጣን ምጋቤ ምላሽ እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል።

በአጠቃላይ በምሁራኑ የተጠቀሱት እነዚህ ዝርዝር ሀሳቦች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አንድ ትምህርት ከቀረበ ተማሪዎች ሊያገኙ የሚችሉትን ጠቀሜታዎች ናቸው።በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር አያሌ ጠቀሜታዎች እንዳሉት Jones (2007) ሲያብራሩ በተማሪዎች ትምህርት መማር ላይ አንዳች ሐይል የሚጨምር በመሆኑ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪውን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ሌሎች ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከመምህር-ተኮር አቀራረብ ይልቅ ተማሪዎች የሚመርጡት መማርን የሚያፋጥኑ የማስተማሪያ ብልሃቶች (ስትራቴጂዎችን) ይጠቀማል። በመሆኑም Emmaና ሌሎች (2010) እንደገለጹት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርቱ በተለያዩ ዘዴዎችና ብልሃቶች ስለሚቀርብላቸው የመማር-ማስተማሩን ተግባራት በአግባቡ ይከውናሉ።

ይህ አግባባዊ ክንዋኔ ተማሪዎች ከትምህርቱ መጨረሻ ላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ገብተው ችግሮቻቸውን ለመፍታትና በማህበረሰቡ ውስጥ በሚከሰቱ ማናቸውም ሁኔታዎች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል።


ከዚህም ባሻገር ተማሪ-ተኮር አቀራረብ የተማሪና ተማሪን መስተጋብር በማጠናከር ለትምህርቱ ውጤታማነታቸው እንዲተጉ፣ ከሰዎች ጋራ የሚደረጉትን የተግባቦት ክህሎት እንዲያዳብሩ፣ በጥልቀት የማሰብ ክህሎታቸውን እንዲጎናፀፉ፣ በቡድን አብሮ የመስራት፣ ልምድን እንዲያካብቱ፣ ለሚማሩት ትምህርት በጎ አመለካከት እንዲያንፀባርቁና

የመሳሳሉትን ባህሪያት እንዲያጎለብቱ ያግዛቸዋል፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ተሳታፊ ሆነው ሲማሩ Bonwell (2003) እንዳብራሩት ብዙ ጊዜ ከማዳመጥ ይልቅ በማንበብ፣ በመፃፍ፣ በመወያየት ወይም ችግር በመፍታት ላይ ተሳታፊ ቢሆኑ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ተግባራት ውስጥ ተሳታፊ ሆነው ከተማሩ በከፍተኛ ደረጃ የማሰብ ክህሎታቸውን በማሳደግ ትንታኔ በመስጠትና ግምገማ ለማካሄድ ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ሚና ይጫወታል (Orlich et al፣ 2001፤ Breslow፣ 1992፤ Bonewellና Eisen፣1991)፡፡

ስለዚህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከላይ በተገለፁትና ሌሎች መሰል ባህሪያቱ ምክንያት ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያደርግ በመሆኑ ከመምህር-ተኮርአቀራረብ ይልቅ ተመራጭነት አለው፡፡ ይህ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት መሳተፍ የሚኖረው ጠቀሜታ ጉልህ ነው፡፡

ለምሳሌ መማር ሳቢ ሆኖ ተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳትፈው ከተፈለገው ዓላማ ላይ ሊደርሱ የሚችሉት ትምህርቱ ለተማሪዎች ትርጉም ያለው አግባብነት ያለው ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ትርጉም ያለው አግባብነት ያለው ሊሆን የሚችለው ደግሞ የክፍል ትምህርቱ ግልፅና ተማሪዎች ከህይወታቸው ልምድ ጋራ ሲያጣጥሙት ከሆነ ነው፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚሰጧቸው ተግባራትና የተግባራቱ አሰራር በመነሳት በነባራዊው ዓለምና በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ እርስ በርስ የመተባበርና የመተጋገዝ ባህልን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲማሩ ሊያገኙ የሚችሉት ዕውቀት በመቶኛ ተሰልቶ ቀጥሎ በቀረበው ሶስት ማዕዘን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ስዕል አንድ፦በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲማሩ የሚገኙ የእውቀት ደረጃዎች፤**




O'keeffeና Cohan (2011) An Introducation to Student centerd and Active learning For the Information Literacy Practioner. Retrived on April 10/2011 from http:www.google.ocm.ete

ከምስሉ የምንገነዘበው መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በአግባቡ የሚተገብሩ ከሆነ መማር-ማስተማሩ ውጤታማ መሆን ነው፡፡ ምስሉ ተማሪዎችን በመማር-ማስተማሩ ውስጥ የሚያሳትፍ መሆኑንና እንዴት ባለ ተግባር የተሻለ እውቀት መገብየት እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡ ከሁሉም በላይ ያወቅነውን ዕውቀት ለሌሎች ሰዎች የምናስተምር ከሆነ 90% (ከፍተኛ) እውቀት የሚያስጨብጥ መሆኑንና ተግባር እያከናወኑ መማር 75% ዕውቀት ስለሚያስገኝ የተሻለ የመማሪያ መንገድ ሊሆን እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ በውይይት መማር ደግሞ ተማሪዎች እርስ በርስ በመማማር ላይ የሚያተኩሩ በመሆኑ 50% ዕውቀት ያስገኛሉ፡፡ ይህም ብልሃት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ በስራ ላይ እየዋለ መገኘቱ አግባብነት እንዳለው ያስገነዝበናል፡፡ በማየትና በገለፃ ማስተማር ደግሞ 30% ዕውቀት ያስገኛሉ፣በማየትና በገለፃ ማስተማሩ ከሌሎቹ ብልሃቶች አንፃር ዝቅተኛ ቢሆኑም መምህራን በአማራጭነት ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡ በማየትና በማዳመጥ 20%፣ በንባብ የሚገኘው ዕውቀት10%ና በገለፃ 5% ዕውቀት ይገኝበታል፡፡ እነዚህ የመጨረሻዎቹን ደረጃዎች አብዛኛውን ጊዜ የምናገኘው በመምህር-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ቢሆንም መምህራን እንደ ትምህርቱ ባህሪ አቀራረባቸውን በመቀያየር ተጠቅመው ማስተማር ይኖርባቸዋል፡፡

## 3.1.2.3. የተማሪ-ተኮርና መምህር-ተኮር አቀራረብ ልዩነቶች

በመምህር-ተኮርና በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መካከል መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶች አሉ፡፡ Ema and et al (2010) እንደገለፁት በመምህር-ተኮር አቀራረብ፣ ተማሪዎች በክፍል መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳትፎአቸው ፍዝ ነው፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ግን ንቁ ተሳታፊና ለራሳቸው ትምህርት ኋላፊነትን በመውሰድ፣ በስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ውስጥም ተሳታፊ ሆነው የድርሻቸውን ይወጣሉ፡፡ ሁለቱ አቀራረቦች አያሌ ልዩነቶች እንዳሏቸው ብዙ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ የእነዚህን የሁለቱን አቀራረብ ልዩነቶች ከሚከተለው ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

**ሰንጠረዥ ሁለት፡-የመምህር-ተኮርና የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ልዩነቶች ማሳያ ሰንጠረዥ**

| *መምህር-ተኮር አቀራረብ* | *ተማሪ- ተኮር አቀራረብ* |
|---|---|
| •የትምህርት ይዘቶች በተናጠል ይሰጣሉ፤ | •የትምህርቱን ይዘቶች በማዋሃድ ይሰጣል፤ |
| •መረጃዎች በመምህራን ይቀርባሉ፤ | •መምህራን ተማሪዎቻቸው መረጃ እንዲሰጡ መንገድ ያመላክታሉ፤ |
| •ተማሪዎች በሥርዓተ- ትምህርት ዝግጅት ውስጥ ሚና የላቸውም፤ | •ተማሪዎች ሰርዓት- ትምህርት ዝግጅት ውስጥ ይሳተፋሉ፤ ሚና አላቸው ፤ |
| ተማሪዎች የተነገራቸውን እንዳለ ማስታወስ ይጠበቅባቸዋል፤ | • ተማሪዎች ውስጣዊ ችሎታቸውን በመጠቀም ብልሃት ፈልገው እንዲማሩ ይደረጋል፤ |
| •የመማሪያ ክፍሉ ፀጥታ የሰፈነበት ነው፤ | • የመማሪያ ክፍሉ በተማሪዎች ተራክቦና የተለያዩ ተግባራት መፈፀም ይታይበታል፤ |
| •መምህራን የተማሪዎችን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፤ | • የተነሱት ጥያቄዎች በተማሪዎች ትብብርና በመምህራን የጋራ ጥረት ይመለሳሉ፤ |
| • ተማሪዎች ይበልጥ በውጫዊ መነሳሳት ላይ ተመስርተው ይማራሉ፤ | • ተማሪዎች በይበልጥ በውስጣዊ መነሳሳት ላይ ተመስረተው ይማራሉ፤ |
| •ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ለቀለም ትምህርት ነው፤ | • ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራና ተማሪዎች የራሳቸውን ህይወት የሚመሩበት ሙያዊ ትምህርት ላይ ነው፤ |
| • የመገምገሚያ ዘዴው የክፍል ውስጥ ፈተና ላይ የተመሰረተ ነው፤ | • ግምገማው ተማሪዎች ሰርተው በሚያቀርቡት ነገር ላይ በተከታታይ ምዘና የተመሰረተ ነው፤ |
| • ትምህርቱ በውድድር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አንዱ ከሌላው ላይ የመማማር ሁኔታ አይታይበትም፤ | • ትምህርቱ እርስ በርስ መማማር ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ተደጋግፎ መማርን ይጋብዛል፤ |
| • የመማር- ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ የተወሰነ ነው፤ | •የመማር- ማስተማሩ ሂደት በክፍልና ከክፍል ውጪ ባሉ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ ይሰጣል፤ |
| •አንድ ነገር ለመፍጠር ትኩረት አይደረግም፤ | •አዳዲስ ነገሮችን በመፍጠር ላይ ያተኩራል፤ |
| •አዕምሮታዊ ዕውቀት በመገብየት ላይ ያተኩራል፤ | •ለሶስቱም የትምህርት ምድቦች (Domain) ለእውቀት፣ ለአስተሳሰብና አሰራር ለውጥ እኩል ትኩረት ያደርጋል፤ |
| •በውጤት ላይ ያተኮራል፤ | •በሂደት ላይ ያተኩራል፤ |

Weimer, M. (2002). **Learner-centered teaching**: five key changes to practices. San Francisco. CA: Jopssey-Bass.

በሰንጠረዡ ውስጥ የተጠቀሱት ዋና ዋና ነጥቦች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና ምን እንደሚመስል፣ በሁለቱ አቀራረቦች ውስጥ የመማሪያ ክፍሉ ያለውን ሁኔታ፣መምህራን ተማሪዎቻቸውን የሚያነሳሱበት ስልቶች፣ የትምህርቱ ምዘና ሁኔታ፣ የመማር-ማስተማሩ ሁኔታ ያለውን ልዩነትና መምህራን የሚሰጡት የትኩረት አቅጣጫ ለማየት ያስችለናል፡፡ በአጭሩ በሁለቱ አቀራረቦች መካከል በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን አሳታፊና የቀደመ ዕውቀት የሚተገበርበት የትኛው እንደሆነ ከለየን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ይዘን ወደ ጥናታችን ትኩረት እናመራለን፡፡

### 3.1.2.4. የመምህራን አሰለጣጠንና ተማሪ-ተኮር አቀራረብ

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚጠቀሙ መምህራን ከተለምዷዊው መምህር-ተኮር አቀራረብ ለየት ያሉ ተግባራትን ይፈጽማሉ፡፡ እነዚህን ለየት ያሉ ተግባራት የሚያከናውኑባቸውን ብልሃቶች እንዲጨብጡ ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ Murphi (1993) እንደገለፁት አንደኛውና ዋነኛው መምህራን በዚህ አቀራረብ ሲያስተምሩ ተማሪዎችን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት ጉዳይ ነው፡፡ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ በተገቢው መንገድ ከሰለጠኑ ተማሪዎችን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል፡፡ የመማር-ማስተማሩ ሂደት የተለያዩ ትግባራት በግልም ሆነ በቡድን ይከናወኑበታል፡፡ በዚህ ክንውን ውስጥ ተማሪዎች ከተሳተፉ ደግሞ እውቀታቸው ያድጋል፤ የአስተሳሰብ አድማሳቸው ይሰፋል፤ የአሰራር መንገዳቸው ይቀላጠፋል፡፡ እንደዚሁም Smylie et al (1999) ባቀረቡት ጥናት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከመተግበሩ በፊት ለመምህራንና ተማሪዎች ስልጠና መስጠት አስፈላጊ እንደሆነና ይህም መምህራንን ለሚያጋጥማቸው ተግዳሮቶች ቅድሚያ መከላከል እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አሳታፊና ተሳታፊ ሆነው ትምህርቱን እንዲያራምዱ በቂ ስልጠና ሊኖራቸው ይገባል፡፡

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመምህራን ስልጠና ምን መምሰል እንዳለበት ለማሳየት በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፤ እየተካሄዱም ናቸው፡፡ ለምሳሌ Chenge (2007) እንደገለፁት በቻይና ውስጥ በተማሪ-ተኮር አተገባበር ላይ ጥናት አካሂደው መምህራን ተማሪ-ተኮር

አቀራረብን በክፍል ውስጥ በተገቢው መንገድ እየተገበሩ አለመሆናቸውን ገልፀዋል፤ ይህም ክስተት ለመምህራን ተገቢውን የአተገባበር ስልጠና ካለመስጠት የመነጨ እንደሆነ ጠቁመው በተለይም በክፍል ውስጥ የተማሪ ቁጥር በመብዛቱ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሊተገበር አልቻለም ለሚሉ መምህራን ይህን ሊያሳብቡ እንደማይገባቸው አስረድተዋል፡፡ እንዲያውም የተማሪ ቁጥር በበዛባቸው ክፍሎች ውስጥ መምህራን ብዙ አጋዥ ያገኛሉ፡፡ ተማሪዎቹ የመምህራን አጋዦች እንዲሆኑ የንግግር ብቃት ያላቸውን በመጠቀም ችግሮቻቸውን መቅረፍ እንዲችሉ በዚህ ዘርፍ ለመምህራን ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል (Locastro፣2001)፡፡

ምሁራኑ ከገለጹዋቸው ሃሳቦች የምንረዳው የተማሪ ቁጥር በበዛበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር መፍትሄ ሰጪ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር መምህራን በክፍል ውስጥ በማስተማር ሂደት ውስጥ ግትር ሳይሆኑ እንደሁኔታው የማስተማር ስልታቸውን እየለዋወጡ ከተማሪዎቻቸው የመማር ፍላጎትና ብቃት አንጻር የማስተማሪያ ዘዴያቸውን ማጣጣም እንዲችሉ ስልጠና ሊያገኙ ይገባል (Tudor፣ 1996)፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አጠቃቀም ውስጥ ስራቸው የቀለለ ሳይሆን የስራ ጫና እንደሚኖርባቸው ማሳወቁ ተገቢ ነው፡፡

በአጠቃላይ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ክፍተቶችን ለመድፈን ስልጠና መስጠቱ ተገቢ ነው፡፡ Nunan (1988) ከላይ በምሁራኑ የተነሱ ሀሳቦችን በመደገፍ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዋና አመቻቾች በመሆናቸው በፍላጎት አሰሳ ክሂል፣ የኮርስ ዕቅድ በማከናወን፣ ስርዓተ-ትምህርቱን በተለያዩ መንገዶች በመግለጽ፣ ተከታታይ ምዘና በመስጠትና በመሳሰሉት ነጥቦች ዙሪያ ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል ብለዋል ፡፡

ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ማስተማር የራሱ የሆኑ ጥቅምና ጉዳቶች እንዳሉት ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይህን አስመልክተው Hess (2001) እንደገለፁት ለመምህራን ስልጠና ሲሰጥ ብዙ ተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን በጎ ጎኖች፣ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች፣ የክፍል አመራር፣ ስነ-ስርዓት አከባበር፣ የጥንድና የቡድን ስራዎች ለትብብራዊ መማር ድጋፍ መሆናቸውን፣ በጥቂት የሰው ሀይል ብዙ ማስተማር ስለሚቻልበት፣ የተለያዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ስለማነሳሳት አስፈላጊነትና

ስለመሳሰሉት መሆን አለበት። እነዚህን ከላይ በምሁሩ የተገለፁትን ሀሳቦች ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን።

ብዙ ተማሪዎች ያሉበት ክፍል ጠቀሜታዎች እንዳሉት Hess (2001) ሲያብራሩ ተማሪዎች በበዙበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ በቂ የሆነ የተማሪዎች መስተጋብር ይታያል። ከዚህም ውጭ የተለያየ ችሎታ ያላቸው የሰው ሀብት ይገኝበታል ተብሎ ይታሰባል። በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ መምህራን ብቻ ቆሞው ትምህርቱን የሚያቀርቡ ሳይሆን በነዚህ ልዩ ልዩ ችሎታ ባላቸው የተማሪዎች ስብስብ ተጠቅመው እርስ በርሳቸው እንዲማማሩ የማድረግ ዕድል ያገኛሉ። በእንደዚህ ባሉ የመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን ከተማሪዎች ጋር እየተጋገዙ ትምህርቱን ስለሚያቀርቡ ጭራሽ ድካም አይሰማቸውም። Ur (1996)ም እንደዚሁ ያጠኑትን ሀሳብ ተንተርሰው ሲያክሉ ብዙ ተማሪዎች ባለበት ክፍል ውስጥ ከመምህራን እጥረት የተነሳ ሁሉንም ተማሪዎች በሚገባ ተቆጣጥሮ እርምት መስጠት ስለሚከብድ ተማሪዎቹ እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ፣ እንዲተጋገዙና እንዲማማሩ የተለያዩ ብልሃቶችን ቀይሶ ትምህርቱን ማስቀሰም እንደሚቻል ያብራራሉ።

በአንፃሩ ግን ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ መልካም የትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች እንዳሉ ሁሉ የተለያዩ ተግዳሮቶችም መኖራቸው ግድ ነው። ይሁንና “ሕልም ተፈርቶ ሣይተኛ አይታደርም” እንደሚባለው ተግዳሮቶቹን በመፍራት አቀራረቡን ከመጠቀም መቆጠብ አይገባም። ይልቁንም የተግዳሮቶቹን መንስዔዎች በጥናት በመለየት አቀራረቡን ውጤታማ እንዲሆንና ከተግዳሮቶቹ እንዲፀዳ (ፍፁማዊ ባይሆንም) ማድረግ እንደሚቻል መገንዘብ ይጠይቃል። ከዚህም ተግዳሮቶቹን ከመለየት አንፃር፣ Hess (2001) የሚከተሉትን ጉዳዮች ለይተው አመልክተዋል፤

***ሀ. የክፍል አመራር*** ፦ የክፍል አመራር ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመተው በጫጫታ፣ በግል ወሬና ከጓደኞቻቸው ጋራ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ ማምራት አይቀሬ ስለሆነ መምህራን ይህን ሁኔታ በአስተውሎት በመከታተል የመማር-ማስተማሩ ተግባር ስኬታማ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በክፍል አመራር ውስጥ አስቸጋሪ ከሆኑት የስነ-ስርዓት ችግሮች እንዴት ማስጠበቅ እንደሚቻልና የብዙ ተማሪዎችን የጽሁፍ ስራዎች

እንዴት ማረም እንደሚቻል ካለማወቅ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ተግዳሮቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

**ለ. ስነ-ስርዓት አከባበር፡-** የተማሪዎች የስነ ምግባር ችግሮች የሚመነጩት ትምህርቱን ከመሰልቸት የሚመጣ እንደሆነ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት መነሳሳት ካላቸው አብዛኞቹ የስነ-ምግባር ችግሮች ይወገዳሉ፤ የስነ-ምግባር ችግሮች ከተወገዱ ደግሞ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ ስለዚህ የስነ-ስርዓት ጥሰቶች ሲከሰቱ ከምን አንፃር እንደሆነ አጥንቶ መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

**ሐ. የጥንድና የቡድን ስራዎች የአከናወን ብልሃት፡-** የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ በክፍል ውስጥ እንዲተገበር ተማሪዎች በጥንድና በቡድን ስራዎች እየተሳተፉ ትብብራዊ መማርን ማጠናከር ይገባቸዋል፡፡ Jones (2007) እንዳስረዱት ቀጥለው የቀረቡት ብልሀቶች ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተደጋገፉ እንዲማሩ ለማድረግ መምህራን ቅድመ ሁኔታዎችን በሚገባ ማወቅና ስልጠና ማግኘት ይገባቸዋል፡፡ ቅድመ-ሁኔታዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

በትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ የተወሰኑ ጊዜያቸውን በቋንቋው ትምህርት የመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ ማጥፋት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የጥንድና የቡድን ስራዎችን ሲያስተዋውቁ መልመጃዎችን ለማሰራት ለጥቂት ሰዓታት ዕቅድ ማውጣትና ቀስ በቀስ እያለማመዱ በስተመጨረሻ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የተለያዩ መልመጃዎችን እየሰሩ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አቅጣጫ ማስያዝ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሁኔታ የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚጋብዝ በመሆኑ ለስነ-ምግባር ችግሮች የሚጋለጡበትን ጊዜ በመቀነስ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፡፡

በተጨማሪም Jones (2007) ያስረዱት ለተማሪዎች የሚሰጡ ተግባራትንና የቡድን አቀማመጣቸውን በመለዋወጥ በሰዓት መወሰን አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ተማሪዎችን በሰዓት የመገደብ ሁኔታ የስነ ምግባር ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ወደ ትምህርታቸው እንዲያዘነብሉ ያደርጋቸዋል፡፡ መምህራን በተመሳሳይ ክፍሎች ተመሳሳይ የመማር-ማስተማር ሂደቶች እንዲታይ ለማድረግ የክፍሉን ተማሪዎች በቡድን በማደራጀት የተመደበላቸውን ሰዓት በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ስልጠና እንዲያገኙ መደረግ

አለባቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ለተማሪዎች የስራ ድርሻ መስጠትና እንደየ ሁኔታው ድርሻቸውን መቀያየር አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ እንደ ሁኔታ አመቻች፣ እንደ ፀሐፊ፣ እንደ መዝጋቢ፣ እንደሰዓት ተቆጣጣሪ፣ ወ.ዘ.ተ ሆኖ እንዲያገለግል በማድረግ የተሰጠውን ሚና በአግባቡ እንዲከውን በማስቻል የተማሪውን ተሳትፎ ማሳደግ ይቻላል፡፡

መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚግባቡበትና ስራዎቻቸውን የሚያበቁበት ምልክት በማዘጋጀት ከጅምሩ እንዲያውቁት ማድረግ ያስፈልጋል፣ መምህራንም ከተማሪዎቻቸው ጋራ ስለትምህርት ቤታቸው ህግና ደንብ በመወያየትና በቡድን ትምህርት ወቅት ተገቢውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ ትኩረት የሚሹ ብልሃቶች ናቸው፡፡

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚያስተምሩ መምህራን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን ለማሳተፍ የሚችሉት  ራሳቸውን እንደ ሁኔታ አመቻች አድርገው ሲገኙ ነው፡፡ ሁኔታ አመቻች የሚሆኑት ደግሞ በቡድን ስራ ላይም ተገቢ የሆነ መመሪያና ስለሚሰራው ተግባር ማብራሪያ ከመስጠት ይጀምራል፡፡ ቀጥሎም ከእያንዳንዱ ተማሪ የሚጠበቀውን ድርሻ በመግለጽ ሁሉም በአግባቡ መስራታቸውን በመከታተል ግምገማ አካሂዶ ምጋቤ ምላሽ እስከ መስጠት ይደርሳል፡፡ ስራውን ለተማሪዎች ብቻ በመተው ተመልካች ከሆኑ በአተገባበር ላይ ድክመቶች ይከሰታሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ አግባብ ላይ ስልጠና ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡

**መ. በጥቂት ሀብት ብዙ ማስተማር ስለመቻሉ**፡- በማደግ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በተለይም የአፍሪካ ተማሪዎች ሲማሩ በቂ መማሪያ መፃህፍት የሌላቸው በመሆናቸው አብዛኛውን ጊዜ እንደ አማራጭ የሚጠቀሙት ማስታወሻ መውሰድ ነው፡፡ Jones (2007) የመምህራንም ትልቁ የስራ ድርሻ ከጠመኔና ከጥቁር ሰሌዳ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ ሁሌ ማስተዋሻ እንዲጽፉ ከማድረግ የሚሻለው ከተቻለ በፎቶ ኮፒ በመጠቀም ተማሪዎች እየተዝናኑ እንዲሰሩ በሚያደርግ ዘዴ መጠቀም ተገቢ ነው፤ለምሳሌ በቃል ማፃፍ፣ አሳጥሮ ማቅረብ፣ ወ.ዘ.ተ ይመረጣል፡፡ ከዚህም ሌላ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚነጋገሩበትና የሚወያዩበትን ጉዳይ ይዘው እንዲመጡ ማበረታታት፣ ከተለያዩ መጽሄቶች ስዕሎችን በማፈላለግ ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች እንዲማሩባቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸትና በትንሽ ሀብት ብዙ ተማሪዎችን እንዲማሩ ማድረግ ተገቢ ነው፣ ተጨባጭ የሆኑ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ይዞ በመምጣት እየዳሰሱ የቋንቋ ትምህርቱን

እንዲማሩበት ማድረግና ራሳቸው ሀሳቦችን አፍልቀው በትምህርቱ ውስጥ እንደ ግብዓት በመጠቀም ማስተማር ትምህርቱን አሳታፊ ያደርጋል፡፡

በጥቂት ሀብት ብዙ ማስተማር የመምህራንን ፈጣሪነት ይጠይቃል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አንዳንድ መምህራን ይህን ፈጠራ ሳይጠቀሙበት መስራት የሚችሉትን ያህል ሳይሰሩ እንደሚስተዋሉ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ዜና አዳምጠው ወይም ሙዚቃ ሰምተው መልክቱን ለጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ቢደረግ የንግግርና ማዳመጥን ክሂሎች ማስተማር ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የትምህርቱ ዓላማና ይዘቱ ላይ በመመስረት የተለያዩ ተግባራትን በራሳቸው እንዲሰሩ በማድረግ  ከተፈለገው ግብ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃርም ለመምህራን ተገቢ የሆነ ስልጠና ሊኖራቸው ይገባል፤ከሌላቸውም ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

***ሠ. የተለያዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ማነሳሳት፡-*** ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ያልሆኑ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ  ለማነሳሳት የሚከተሉት ስልቶች ጠቃሚዎች ናቸው፡፡ እንደ Jones (2007) ገለፃ መምህራን በመጀመሪያው የትምህርት ጅማሬ ቀን ስለታላሚው ቋንቋ ጠቀሜታዎችና ከእያንዳንዱ ተማሪ ምን እንደሚጠበቅ በማብራራት ትኩረት እንዲጡ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም በአእምሯቸው የሚያስቡትን ታላሚውን ቋንቋ እንዲገልፁ ማበረታታትና በጣም ጠንካራ ተማሪዎች በጣም ከባድ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስራቸውንም በጊዜ ያጠናቀቁትን ተማሪዎች ለይቶ ሌላ ተጨማሪ መልመጃዎችን እንዲሰሩ ማድርግ ተገቢ ነው፡፡

የተለያዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎችን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ለማነሳሳት ሌላው Jones (2007) የገለፁት ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚናገሩበት፣ ሀሳብ በሚሰጡበትና መልስ በሚሰጡበት ጊዜ መምህራን በቅርበት ሆነው ሀሳባቸውን መቀበልና ተማሪዎቹን በአግባቡ አዳምጦ ማበረታታትና የተዘጋጁትን የትምህርት መሳሪያዎች በተማሪዎቹ እድሜ፣ ቋንቋና ችሎታ ጋራ አጣጥመው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡በተጨማሪም ተማሪዎቹ የሚሰሩትን መልመጃዎች በቅደም ተከተል ማዘጋጀትና ጎበዝም ሆኑ ደከም የሚሉ ተማሪዎች እንደ ችሎታቸው በትምህርቱ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ይቻላል፡፡ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ደግሞ ጎበዝ

ተማሪዎችን እንደረዳት መምህራን ወይም እንደ ክፍል አለቃ በመጠቀም ደከም የሚሉ ተማሪዎችን እንዲረዱ ማድረግ፤ የተማሪዎችን የተለያዩ ችሎታዎቻቸውንና ፍላጎቶቻቸውን የሚለኩባቸውን ተግባራት ማዘጋጀት፣ በተቻለ መጠን ተማሪዎች እርስ በርስ ግላዊ መግባባት እንዲፈጥሩ በማድረግ የተለያየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በመጠቀም ትምህርቱን መስተጋብራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በምሁራኑ እንደተብራራው የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተጠቅመን ስናስተምር ለውጤታማ የመማር-ማስተማር አተገባበር መምህራን ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ጥናቶች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ክፍተቶች ውስጥ በስፋት ሲጠቀሱ የነበሩት ከሥልጠና መጓደል አንፃር የሚነሱ ነጥቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም መምህራን ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጋር ተዋህደው መተግበር እንዲችሉ ተገቢ የሆነ ስልጠና ማግኘት በእጅጉ ያስፈልጋቸዋል፡፡

### 3.1.2.5. ተማሪዎችና የተማሪ-ተኮር አቀራረብ

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ በተቀመጠለት መርህ መሰረት ሊተገበር የሚችለው በመምህራን ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችም በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የድርሻቸውን ተሳትፎ መወጣት ሲችሉ ነው፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተግባራቱን ሲያከናውኑ በንቃት እየተሳተፉ የሚማሩበት አቀራረብ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ መምህራን የተለያዩ ብልሃቶችን ተጠቅመው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ ተማሪዎችም ድርሻቸውን ተቀብለው እንደ መምህራን ሆነው ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው፡፡ Mc-Grath (2002) እንደገለጹት ተማሪዎች እንደ መምህራን ሆነው ከማስተማር ባሻገር በራሳቸው ተሳትፎ ተቀባይነት ያለው የትምህርት መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ለሌሎች ጓደኞቻቸው ግንዛቤ ጠቀሜታ ያለው ተግባር መፈፀም ይችላሉ፡፡ በአጭሩ በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተሰጣቸውን ተግባራት በሐላፊነት ስሜት መፈፀም አለባቸው፡፡ እንደ Jones (2007) ገለፃ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመማር-ማስተማር ሂደት ትግበራ ውስጥ ተማሪዎች በሚከተሉት መንገዶች ተሳትፎ ሊያደርጉ ይችላሉ፤ለምሳሌም፡-

1. የግል ሀሳብ ማዘጋጀት፡- ተማሪው ውይይት ከማካሄዱ በፊት ማስታወሻ መያዝ፣ የማዳመጥ ተግባራትን፣ የሰዋስው ወይም የቃላት መልመጃዎችን መስራት ሊሆን ይችላል፣
2. በቡድንና በጥንድ የሚሰሩ ተግባራት መተግበር፡- ተማሪዎች የሰሯቸውን ምላሾች በማወዳደርና በመወያየት፣ ሌሎች የፃፉትን በማንበብ፣ ስለተፃፈው ጉዳይ ለሌሎች በመናገርና ሀሳብ መሰጣጣት ተሳትፎአቸውን ያጎለብታሉ፣
3. በውይይትና ሚና ጨዋታ አብሮ በመሳተፍ ሀሳብ መከፋፈል፡- በዚህ ተግባር ስር ተማሪዎቹ የራሳቸውን አቋምና ልምድ የሚለዋወጡበት ተግባር ይታያል፡፡ ከዚህም ሌላ ከመምህራን ጋር መስተጋብር በመፍጠር፣ ከሙሉው የክፍል ተማሪዎች ጋር መወያየት፣ ጥያቄዎችን መጠያየቅና የመሳሰሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች በመምህራን መመራታቸው አይቀሬ ነው፡፡ Jones (2007) እንደሚገልፁት ተማሪዎችም በጋራ ከመስራታቸው በፊት መምህራን እንዴት በጋራ መስራት እንዳለባቸው፣ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው፣ እንዴት ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ በአጠቃላይ ስለቀረበላቸው ተግባራት መረዳት አለባቸው፡፡ ስራቸውንም ካጠናቀቁ በኋላ ከሙሉው የክፍሉ ተማሪዎች ጋር በመሰባሰብ ከመምህራን ጋር ሀሳብ ይቀባበላሉ፣ ለተጠየቁት ጥያቄዎችም ምላሽ ይሰጣጣሉ፡፡ ተማሪዎች በጋራ ሲሰሩ ብዙ ይናገራሉ፣ ሀሳብ ይቀባበላሉ፣ አንዳቸው ከአንዳቸው ይማራሉ፣ ከመጨነቅ ይልቅ ዘና ብለው ሀሳብ ያመነጫሉ፡፡ የቋንቋውን ትምህርት እንደ እውነተኛ አውድ ይግባቡበታል፤ በሚገባ በመግባባታቸውም ይደሰቱበታል፡፡ ነገር ግን አንዳንዶች የምላስ መተሳሰር፣ በንዴት መናገር፣ መጮህ፣ ብዙ የአነጋገር ስህተት መፍጠር፣ በጋራ መስራት አለመፈለግ ሊያሳዩ ስለሚችሉ ተግባሩ የመምህራንን ብቃት ይጠይቃል፡፡

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ቋንቋን መማር-ማስተማር ለተማሪዎች አያሌ ፋይዳዎች አሉት፡፡ በተለይም የተማሪዎችን የማሰብ አድማስ ማስፋትና የቀረበላቸውን ትምህርት በፍጥነት የመረዳትን አቅም ይሰጣቸዋል፡፡ እንደ Chance (2005) አገላለጽ የሚከናወኑት ተግባራት ግልጽነት በተሞላበት መንገድ የሚሰሩ ከመሆናቸው የተነሳ በህይወታቸው ዘመን የገጠማቸውን ችግሮችን በራሳቸው እንዲፈቱና የማሰብ

አድማሳቸው እንዲሰፋ እድል ያገኙበታል፡፡ ሂደቱ ተማሪዎች እንዲመራመሩ፣ ጽንሰ-ሀሳቦችን እንዲያፈልቁ፣ የራሳቸውን ግንዛቤ ከሌሎች ሀሳቦች ጋር እንዲያቀናጁና በሚሰሩት ስራ ውስጥ እንዲተገብሩ ያግዛቸዋል፡፡ እንደነ Duffyና Kirkley (2004)፣ Kane (2004)፣Kim (2005) ያሉ ፀሐፍት ደግሞ የመማር-ማስተማር ሂደት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲከናወን ተማሪዎች ከሚያገኟቸው ጥቅሞች ውስጥ የሚከተሉትን አብራርተዋል፦

1. **በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ተሳታፊ መሆን፦** የተለያዩ መልመጃዎችን በክፍል ውስጥ በሚሰሩበት ወቅት በመነሳሳት ተሳትፎ በማድረግ የመማር ማስተማሩን ሂደት ያፋጥናሉ፡፡ የትምህርቱ ፍጥነት ሲታይ በተፈለገው የመማር ማስተማር ዓላማ ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያደርሳቸው ይችላል፡፡

2. **የቀደመ ዕውቀታቸውንና ልምዳቸውን መጠቀም መቻል፦** ማንኛውም ተማሪ የቀደመ ዕውቀትና ልምድ አለው፡፡ መማር-ማስተማሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚከናወን ከሆነ ይህን የተማሪዎች ልምድና እውቀት በሚሰሩት መልመጃዎች ውስጥ የመጠቀም እድል ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ መማራቸው በተጨባጩ የኑሮ አካባቢያቸው ነገሮችን በማገናኘትና በማገናዘብ የሚገጥማቸውን ችግሮች በቀላሉ እንዲፈቱ እድል ይሰጣቸዋል ማለት ነው፡፡

3. **አዲስ አስተሳሰብና ግላዊ ግምገማ እንዲጎናፀፉ ማስቻል፦** ይህ ሲባል በአንድ ርዕስ ላይ ከሌሎች የቡድን አባላት ጋራ በመወያየት የራስን ሀሳብ በመስጠትና የሌሎችንም ሀሳብ የመቀበል ሁኔታ እንዲታይባቸው ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም አንድን የትምህርት ርዕስ በተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች የማቅረብን ክህሎት እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡

4. **በተለያዩ ትምህርቶች ተፎካካሪ ሆነው እንዲገኙ ማብቃት፦** ተማሪዎች በዚህ የማስተማር ብልሃት በተለያዩ ትምህርቶች አውድ ውስጥ የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮቶች ከሌሎች ጋራ ሆነው መፍታት እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ ከዚህም በመነሳት የተለያዩ የችግር መፍቻ ብልሃቶች ይጎናፀፋሉ፤በኑሮ አካባቢያቸውም ለሚገጥማቸው ችግሮች መፍትሄ መስጠት ይችላሉ፡፡

5. **ቡድናዊ እገዛና መማር፡-**በትብብራዊ ተግባራት ውስጥ የቡድን ስራዎችና ሌሎች የማስተማር ብልሃቶች ላይ በመተጋገዝ እንዲሰሩ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ባሉበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ግብዓት እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡

6. **በተሰሩት ተግባራት ላይ በሳል ጽብረቃ ማድረግ፡-** ተማሪዎች ያላቸውን ዕውቀትና ልምድ በማዋጣት በአንድ ስራ ላይ ተወያይተውና ተስማምተው ለክፍል ጓደኞቻቸውና ለመምህራቸው ያንን ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ጽብረቃቸውም ጥልቀትና ስፋት ያለው ሊሆን ይችላል፡፡

7. **ለመማር ሀላፊነት መውሰድና የትምህርቱ ዋና ባለቤት መሆን-** በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመማር-ማስተማር ተማሪዎችን በማበረታታት በራስ መመራትና በራስ መነቃቃትን ያጎናጽፋል፡፡ ይህ ደግሞ መማር-ማስተማሩ ውስጥ ሀላፊነትን እንዲወስዱና የትምህርቱ ባለቤት መሆን እንዲችሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህን ሀላፊነት ከወሰዱ ከመምህራን የሚጠብቁት ነገር ሁኔታውን እንዲያመቻችላቸው ብቻ ነው ማለት ነው፡፡

8. **የተግባቦት ክህሎትን ያሳድግላቸዋል፡-** የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለተማሪዎች የተግባቦት ክሂል እድገት ክፍተኛ ዕድል ይሰጣል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ እርስ በርሳቸው በሚያደርጉት መራከብ በመነሳት በነባራዊው ዓለም ውስጥም ሀሳባቸውን ያለአንዳች ተጽእኖ መግለጽ እንዲችሉ ያግዛቸዋል ማለት ነው፡፡ ሀሳብ ብቻ ከመግለጽ በተጨማሪ አንደበተ ርቱዕ በመሆን አሳማኝ ሀሳቦችን እንዲሰጡና እንዲያሳምኑ እድል ያስገኝላቸዋል፡፡

በአጠቃላይ Schwartz and Pollishuke (1991) እንዳብራሩት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዋነኛው ግብ ህፃናት በራሳቸው መወሰን እንዲችሉና የገጠማቸውን ችግሮች ያለማንም እርዳታ የመፍታት ክህሎት እንዲጎናፀፉ ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ አቀራረብ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የመሳተፍና በአእምሮአቸው ውስጥ የፈጠራ ተግባራት እንዲያኖሩ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም Schrenko (1996) በምልከታ አረጋግጦ እንደገለፀው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርትን ማቅረብ እያንዳንዱን ተማሪ እያሳወቀ

ውስጣዊ መነሳሳቱን በመጨመር የሚሰሩትን ተግባራት እንደ ሞዴሊንግ ወስደው ሰፊ ትንታኔ በሚጠይቁ ጥያቄዎች አማካኝነት ማዕከላዊ ሀሳቦች እንዲጨብጡ ያደርጋል። ከዚህም ሌላ ተማሪዎችን ከችግሮች ጋር አጋፍጦ ማስተማር እየተደጋገፉ በሚማሩት ትምህርት ውስጥ ፈጠራን እንዲያጎለብቱ ያደርጋቸዋል።ስለሆነም ተማሪዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ጠቀሜታዎች ተረድተው ከላይ የተዘረዘሩትን ድርሻቸውን በሚገባ መወጣት እንዲችሉ ስልጠና ማግኘት ይጠበቅባቸዋል።

### 3.1.2.6. የተማሪ-ተኮር አቀራረብና የተማሪው መጽሐፍ

የተማሪው-መማሪያ መፃህፍት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን እያሳተፉ ተግባራቱን እንዲከውኑ የሚያግዙ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ይህን አስመልክተው Nunan (1988) እንዳብራሩት ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ የሚዘጋጁ የተማሪው የመማሪያ መፃህፍት ተማሪዎቹ ተግባራትን ያለመምህራን ጣልቃ ተግባራትን ማከናወን እንዲችሉ አሳታፊ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። Derebssa (2006) የስርዓተ-ትምህርት መሣሪያዎች በተለይም የመምህሩ መምሪያና የተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጁ ተማሪዎችን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሂደት ተማሪዎችን እንዲያሳትፉ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል ያሉት ለዚሁ ነው ።ተጨማሪም Nunan (1988) እንደገለጹት በተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ ለተማሪዎች የሚቀርቡ የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶች የፍላጎት ዳሰሳ ተካሂዶባቸው የተመረጡና የተደራጁ መሆን ይገባቸዋል። የፍላጎት ዳሰሳው የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ዳራ፣ ዝንባሌ፣ ችሎታ መሰረት ማድረግ ይኖርበታል። እንደ ቀደመው የመምህር-ተኮር አቀራረብ የይዘት ምርጫው በመምህራን ሣይሆን በተማሪዎች መሆን ይኖርበታል።በዚህ ሁኔታ የሚዘጋጁ የትምህርት መሳሪያዎች የተማሪዎችን ፍላጎትና ዝንባሌ ያገናዘቡ በመሆናቸው ተማሪዎችን በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የማሳተፉ ብቃት በእጅጉ የጎላ ይሆናል። ይህም ማለት መምህራን በሌሉበት ሁኔታ ውስጥ ተማሪዎች የትምህርት መሳሪያዎችን በራሳቸው አንብበው ሀሳብ ሊያመነጩ የሚያስችላቸው ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

በርግጥ በብዙ አገሮች ተማሪዎች ከስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ባለሙያዎች ጋራ ሆነው በማስተማሪያ መሣሪያዎች ቀረፃ ላይ እየተሳተፉ የሚያመቻቸውን ይዘቶች ይመርጣሉ

ብሎ መደምደም ይቸግራል፡፡ከዚህ አንፃር በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው የተማሪውን ፍላጎት፣ የኑሮ ዳራ፣ ወ.ዘ.ተ ጠብቀው የተመረጡ ስለመሆናቸው፤ የተግባራቱ የክብደት ደረጃም በተለያዩ ጥናቶች በጥንቃቄ የቀረቡና ከመተግበራቸው በፊት የተለያዩ ውይይቶች ተደርገውበት የፀደቁ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡

Hutchinsonና Waters (1987) ከላይ የተነሳውን ሀሳብ ሲያጠናክሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ አጠቃላይ የትምህርቱ መርሆች በተማሪዎች የሚወሰን ሊሆን ይገባል፡፡ ስርአተ-ትምህርቱ ሲዘጋጅ ተማሪዎችን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ማሳተፍ እንደሚገባ ማወቅ ተገቢ ነው:: በርግጥ የተማሪ-ተኮር ስርዓተ-ትምህርት ከተለመደው የመምህር-ተኮር አቀራረብ አዘገጃጀት ሂደት ጋር ተመሳሳይነት አለው:: ነገር ግን ቁልፍ ልዩነት ያለው በእያንዳንዱ የስርዓተ-ትምህርቱ አዘገጃጀት ሂደት ውስጥ ከተማሪዎች መረጃ መቀበል ላይ ነው:: የስርዓተ-ትምህርቱ አዘገጃጀት የመምህራንና የተማሪዎችን ትብብራዊ ጥረት እንደሚጠይቅ ባለሙያዎች መገንዘብ አለባቸው (Nunan፣1989):: በአጠቃላይ የዘርፉ ምሁራን እንዳስገነዘቡት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተገቢው መንገድ እንዲተገበር ከተፈለገ የተማሪው የመማሪያ መፃህፍት የራሳቸው ሚና ስላላቸው ተማሪዎችም በዝግጅቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግና በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አሳታፊ ማድረግ ተገቢ ነው::

## 3.2. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የማስተማሪያ ብልሃቶች

የተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ አቀራረብ በክፍል ውስጥ የሚተገበረው የተለያዩ ብልሃቶችን በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህ ብልሃቶች በተለይም ቋንቋን ለማስተማር፤ የመማር-ማስተማሩን ሂደት የሚያፋጥኑ፣ ተማሪዎችን በትምህርቱ ውስጥ የሚያሳትፉ፣ ንቃትን የሚያላብሱ፣ ግላዊ መማርን የሚያጎለብቱ ናቸው (Moore፣2001፤ Derebssa፣2006)፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ የመማር-ማስተማሩን ሂደት ንቃት በተላበሰ መንገድ ለመስጠት የሚያስችሉ አያሌ ስልቶች እንዳሉ የመስኩ ተመራማሪዎች ይገልፃሉ፡፡ ለምሳሌ Leu (2000) በቁጥር ከአርባ በላይ የሚደርሱ ብልሃቶች እንዳሉና እነዚህንም የአንደኛ ደረጃ መምህራን በክፍል ውስጥ ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

Cruickshank and et.al (1999) ደግሞ የማስተማሪያ ብልሃቶች ከሰላሳ አይነቶች በላይ መሆናቸውን ገልፀው ስማቸውን በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡

*ለምሳሌ፡-*

- *አንድን ነገር በገለፃ ማቅረብ*
- *በማነፃፀር መገምገም*
- *ትብብራዊ ተግባራት*
- *በቡድን መፃፍ*
- *ፕሮጀክት*
- *በቻርቶችና ግራፎች መግለጽ*
- *ትዕይንተ-ገለፃ*
- *ጥናትና ምርምሮች*
- *መረጃዎችን መሰብሰብ*
- *ፖስተሮችን መጠቀም*
- *መረጃዎችን እንደ ሁኔታዎች መጠቀም*
- *ኤግዚብሽን*
- *ክርክር*
- *መረጃዎችን ማነፃፀር*
- *ዘገባ መፃፍ*
- *የቃላት ጨዋታ*
- *ቃለ-መጠይቅ (ታሪክ ከሚያውቁት ጋር)*
- *ድራማ*
- *ሚና ጨዋታ*
- *ስዕል መጠቀም*
- *ገለፃን መተንተን*
- *አንብቦ ማብራራት*
- *ማጠቃለያ መስጠት*
- *ማንበብና ማነፃፀር*
- *መረጃን ማደራጀትና መከፋፈል*

*የመሳሰሉት መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡*

Moore (2001) ግን ከላይ የተነሱትን ሀሳቦች ቢደግፉም መማር-ማተማሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በሚከናወንበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ በአብዛኛው በስራ ላይ የሚውሉትን ብልሃቶችና ብልቶች አቅርበዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ለምሳሌ፡-

## 3.2.1.ውይይት

ውይይት ሀሳብን የሚያነቃቃ አመለካከትንና እምነትን የሚፈትሽ በሰዎች መካከል የሚካሄድ መስተጋብር ነው፡፡ በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አስፈላጊ ከሆኑት ዘዴዎች አንዱ ውይይትነው፡፡ Cruickshank,እና etal (1999) እንደገለፁት ውይይት አስተማሪዎችና ተማሪዎች እንዲሁም ተማሪዎችና ተማሪዎች እርስ በርስ በመመካከር መረጃ የሚለዋወጡበት፣ሃሳብ የሚሰጣጡበት፣ አመለካከታቸውን የሚገልፁበት፣ ችግር የሚፈቱበት መስተጋብራዊ ግንኙነት ነው፡፡ የውይይት ብልሃት ውጤታማ የሚሆነው የሌሎችን ሐሳቦች በስርዓት በማዳመጥ፣ ከሌሎች ጋር ተቻችሎ በመስራት፣ የዲሞክራሲ ሥርዓትን ተከትሎ የሌሎችን ግንዛቤና አመለካከት በጥልቀት በመገመምገም፣ ዳራዊ ልምድን ወይም እውቀትን በአግባቡ በመካፈልና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው (Farrant፣1980)፡፡

በመሆኑም በቡድን ውይይት ለማስተማር መምህራን የቡድን አደረጃጀቱ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በቡድኑ ውስጥ ጎበዝ ተማሪዎች ብቻ ተፅእኖ እንዳያደርሱ ከጎበዞቹ፣ ከደካማዎቹ፣ ከመካከለኞቹ እንዲሁም በፆታ በኩልም ከሴቶችና ከወንዶች የተመጣጠኑ ሆነው እንዲደራጁ ማገዝ ተገቢ ነው፡፡ Moore (2001) በበኩላቸው በውይይት ብልሃት የማስተማር ሂደት ውስጥ ውይይቱን ለመተግበር ሁለት ዓይነት ግቦች እንዲኖሩት ተደርጎ መቅረብ እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ የመጀመሪያ ግብ በቀላሉ የማይመለሱና ሰፊ መልስ ያላቸው ጥያቄዎችን በማቅረብ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለማውጣት እንዲችሉ በማድረግ፤ ለምሳሌ፡- ለኤድስ መስፋፋት ምክንያቶች ምን እንደሆኑ እንዲያብራሩና እንዲነጋገሩ፤ የዓለም ህዝብ ቁጥር መጨመር መንስኤውና የወደፊት ዕጣው ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲያስረዱና እንዲተነብዩ የሚጋብዙ የጥያቄ ዓይነቶችን በማቅረብ በክርክርና በውይይት ማስተማር ይቻላል፡፡ ይህም ተማሪዎች የሌሎችን ሐሳብ መቀበልና የራስንም አስተያየት መስጠት እንዲሁም ማረምና ማሻሻያ ሀሳብ ለመስጠት እንዲችሉ ያግዛል፡፡

ሁለተኛው የውይይት ግብ ደግሞ ለውይይቱ ግላዊ ሀሳብን በመጨመር ዋናው ነጥብ የሚተኮርበትን ጉዳይ ማንሳት ነው፡፡ ለምሳሌ ስለረሀብ፣ ስለሙዚቃ፣ ስለምርጫና ስለመሳሰሉ ጉዳዮች እንዲወያዩ በማድረግ ማስተማር ይቻላል፡፡

የውይይት ብልሃትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሁኔታዎች አልተመቻቹም ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም፡፡፡ የተማሪዎች መቀመጫ ስርዓቱ በሚፈለገው ሁኔታ አለመደራጀት፣ የተማሪዎች ዕድሜ፣ የተማሪዎች ልምድ፣ ወዘተ ከግምት ውስጥ ከገባ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ICDR (1999)ም ውይይት በተወሰኑ ቡድኖች ወይም በክፍሉ በሙሉ መከናውን የሚቻል ቢሆንም በሶስት መንገዶች መከናወን እንዳለበት ይመክራሉ፡፡ እነዚህም የአቀራረብ መንገዶች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ውይይት (Prescribed Discussions)፣ ጥብቅ ውይይት (Guided Discussions)፣ ልቅ ውይይት (Open Discussions) የሚባሉ ናቸው፡፡

1. **በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ውይይት** ፡- ይህ የውይይት አይነት ተማሪዎች ሊያውቁት በሚገባ የትምህርት ይዘትና ሊደርሱበት በሚገባ የትምህርቱ ዓላማ ላይ ትኩረት አድርጎ ለውይይት የሚጋብዝ ነው፡፡ይህ አይነት ውይይ ሁል ጊዜ አስቀደሞ

ስለይዘቱና የመጨረሻ ግቡን በማሰብ፣ በውይይቱ ጣልቃ በመግባት ወደተፈለገው አቅጣጫና ግብ እንዲያመራ መምራት፣ የውይይቱን ውጤት በማጠቃለልና የተደረሰበትን ሁኔታ በማጠናቀር የመሄድ ባህርይ አለው፡፡ይህም ማለት መምህራን በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች ማወቅ ወደሚገባቸው የትምህርት ዓላማ እንዲያመሩ ለማድረግ በውይይቱ ውስጥ ተሳታፊ ሆኖ መምራት መቻል መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

2. **ጥብቅ ውይይት፡-** ይህ የውይይት ዓይነት ቀደም ተብሎ ተማሪዎች ማወቅ የሚገባቸው የትምህርት ይዘቶች ውስጥ ሊያተኩሩበት በሚገባ ቁልፍ ነጥብ ተለይተው እንዲወያዩበት የሚደረግበት ነው፡፡ ጥብቅ ውይይት ከሚገለጽባቸው ባህሪያት፣ ለተማሪዎች ቁልፍ ነጥብ ወይም ቁልፍ ጥያቄዎችን በማቅረብ ጉዳዩን ለቡድን ውይይት ክፍት ማድረግ፣ ውይይቱ ከተጀመረ በኋላ የውይይቱ ሂደት ካልተበላሸና ጊዜ ካልወሰደ በስተቀር ጣልቃ አለመግባትና እያንዳንዱ ተሳታፊ የውይይት ነጥቦቹን መረዳት አለመረዳቱን ማረጋገጥ፣ በውይይቱ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች ከቡድናቸው ውስጥ ተመርጠው የደረሱበትን ማጠቃለያ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸቱና በውይይቱ ሂደት ውስጥ የተወያዮቹን ስሜት በማይነካ መልኩ ከመምህራን ተገቢ አስተያየት መስጠትን ያጠቃልላል፡፡

3.**ልቅ ውይይት፡-** ልቅ ውይይት ሦስተኛው በውይይት የማስተማር መንገድ ሲሆን ተማሪዎች ያለመምህራን እርዳታ ወይም ድጋፍ ራሳቸውን ችለው የመወያየት፣ ርዕስ መርጠውና ተወያይተው ከተፈለገው ግብ ላይ የሚደርሱበት የውይይት ዓይነት ነው፡፡

ልቅ ውይይት ከሚታወቅባቸው ባህሪያት መካከል፣ በውይይቱ ርዕስና በውይይቱ አካሄድ ህግና ደንብ ላይ ስምምነትን ይጠይቃል፡፡ የውይይቱ መርሆዎች ካልተዛቡ በስተቀር ውይይቱ ከተጀመረ በኋላ ጣልቃ መግባት የማይቻል መሆኑን፣ በውይይቱ መጨረሻ ላይ የተነሱ ሀሳቦችን በማድነቅ የራስን አስያየት ማከል መቻሉንና ተማሪዎቹም ውይይታቸውን እንዲገመግሙና ለሚቀጥለው ጊዜ የሚወያዩበትን ርዕስ እንዲያውቁ ማድረግ ዋና ዋናዎቹ የልቅ ውይይት ባህሪያት ናቸው፡፡

የቡድን ውይይት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አያሌ ፋይዳዎች እንዳሉት የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ። ለምሳሌ Jonsen (2007) እንደገለጹት፣ የውይይት ዘዴ በተለይም ለቋንቋ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው። ትምህርቱን ለማፋጠን፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለማሳደግና አመለካከትን ለመለወጥ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። የተለያዩ ክሂሎችን በውይይት ማስተማር ቢቻልም የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች ከፍተኛውን ቦታ ይይዛሉ።

በአጠቃላይ የውይይት ዘዴ ጠቀሜታዎች ጎላ ብለው ቢታዩም የራሱ የሆኑ ደካማ ጎኖች እንዳሉትም ይገለፃል። ከጠንካራ ጎኖቹ አንፃር ሲታይ ውይይት ለመምህራን ሆነ ለተማሪዎቹ ነፃ ሆነው ሀሳብ በመስጠት፣ ተግባቦትን በመፍጠር፣ ፍራቻን በማስወገድ፣ በመከባበር፣ በመቻቻል፣ በመስማማትና በመሳሰሉት መንገዶች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳትፈው በትምህርቱ አመርቂ ውጤት ለማግኘት ማስቻሉ በውይይት ማስተማርን ያበረታታል። በአንፃሩ ግን ውይይት ለተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ የተሳታፊነት እድል መስጠቱና በተለይም ቡድኑ በተገቢው መንገድ ካልተዋቀረ ዓላማ ወደ ሌለው አቅጣጫ በመውሰድ ጊዜንና ጉልበትን በከንቱ እንዲባክን ስለሚያደርግ እንደ ደካማ ጎኖቹ ይታያሉ (Cruickshank እና etal፣1999፤ Moore፣ 2001) ። ይሁን እንጂ ከላይ ምሁራኑ የገለፀዋቸው የውይይት ደካማ ጎኖች ከመምህራን ድክመት ጋራ የተያያዘ በመሆኑ በቡድን ውይይት ተጠቅመው መማር-ማስተማሩን ሲያካሄዱ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ በማድረግ ቡድኑን ማደራጀትና ሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማገዝ ችግሮቹን ማቃለል ይችላሉ።

### 3.2.2.ትብብራዊ የመማር-ማስተማር ብልሃት

ትብብራዊ የማስተማሪያ ብልሃት ተማሪዎች በትናንሽ ቡድንና በጥንድ ተግባራትን ሲያከናውኑ እርስ በርስ በመረዳዳት በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ብልሃት ነው። በዚህ ብልሃት ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባራት ሲያከናውኑ ቅይጥ ወይም ውሁድ ችሎታን መጠቀም አለባቸው (Cruickshankና etal፣1999፤ Moore፣ 2001) ። ቅይጥ ወይም ውሁድ ችሎታ ሲባል በቡድን ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ አባላት የሀሳብ ተሳትፎ ጥምረት መጠየቅን ይመለከታል።

ትብብራዊ መማር በትምህርት ውጤት ላይ አዎንታዊ ግብ አለው። በተለይም በጥልቀት የማስብ ችሎታን ለማጎልበት፣ ለተማሪዎች የእርስ በርስ ግኑኝነት፣ በተማሪዎች መካከል

ጓደኝነትን ለመፍጠር፣ከተለያዩ ማህበረሰብ አባላት ጋር በስምምነት ለመስራት፣ በራስ ለመተማመን፣ራስን ለማወቅና ለመሳሰሉት ጠቀሜታ ይኖረዋል (Askewና Carnell፣1998)።

በትብብራዊ የማስተማር ብልሃት በመጠቀም የመማር-ማስተማሩን ሂደት በተገቢው ሁኔታ ለመተግበር በቡድን አመሰራረት ወቅት የአባላት ቁጥር ከአራት እስከ ስድስት ቢሆን ይመረጣል። በቡድን ምስረታ ወቅት በክፍል ውስጥ የሚኖረውን የተማሪዎች በችሎታ መለያየት (ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ) በማመጣጠንና በማቧደን ስራቸውን በመተጋገዝ ወይም በመረዳዳት እንዲሰሩና እንዲማሩ ማድረግ ተገቢ ነው (Moore፣2001፤ Cruickshank etal 1999፤Ruddell፣1997)። ትብብራዊ የመማር-ማስተማር ብልሃት የሚታወቀው ተማሪዎች በትናንሽ ቡድኖች ተመድበው በጋራ የትብብር ስራቸውን የሚያከናውኑበት፤ የቡድን ተግባራቱ ግብ-መር /Goal Directed/ ነው። በተጨማሪም ትብብራዊ የማስተማር ብልሃት ማህበራዊ መስተጋብር የሚገለጽበትና፣ ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ላይ ተመስረተው አንዱ ተማሪ ሌላውን በመርዳት የሚማማሩበት ነው።

በትብብራዊና በውይይት መማር ብልሃት መካከል ልዩነት አለ። እንደ Moore (2001) ና Cruickshanketal (1999) አገላለጽ ልዩነታቸውም በትብብራዊ መማር ተማሪዎች ያላቸውን ሀሳቦች በቀረበላቸው የመማር-ማስተማር ተግባራት ላይ በመመስረት በመተጋገዝና በመረዳዳት የሚያከናውኑት ሲሆን የቡድን ውይይት ደግሞ የአንድ ተወያይ ግላዊ አመለካከትና እምነት የሚፈትሽበት፣ የአንዱ አመላካከት ሌላው ላይ በአዎንታዊ ይሁን በአሉታዊ ጎኑ ሊንፀባረቅ የሚችልበት መስተጋብር ነው። በሌላ አገላለጽ የትብብራዊ መማር ተማሪዎች በሚያከናውኑት ተግባራት ውስጥ ኋላፊነትን በመቀበልና ሀሳባቸውን በማዋጣት የየድርሻቸውን የሚወጡበት ብልሃት ነው። በቡድን መማር ብልሃት ደግሞ በቀረበላቸው አንድ ርዕስ ላይ በመመስረት የራስን አመለካከትና እምነት ለሌሎች በማቅረብ ላይ ያተኩራል።

በአጠቃላይ ተማሪዎች በቡድን ትብብር ከሰሩ ማህበራዊ ተግባቦትን ያጎለብታሉ፣ እርስ በርስ ሀሳብንና ዕውቀትን ይቀባበላሉ፣ ከተለያዩ ሰዎች ጋር ጓደኝነትን ይፈጥራሉ፣ የአብሮነት ባህሪን ያሳድጋሉ፣ በልዩነቶቻቸው ላይ በመቻቻል አዎንታዊ አመለካከት ያሳድጋሉ።

ለምሳሌ በጾታ፣ በትምህርት፣ በውጤትና በዘር ልዩነት አያሳዩም፡፡ በመሆኑ በትብብራዊ የመማር ዘዴ ተማሪዎች ከሌሎች ዘዴዎች ይልቅ ከፍተኛ የትምህርት ውጤት ያስመዝግባሉ፣ የተሻለ የእርስ በርስ ግንኙነትን እንዲፈጥሩ ያደርጋቸዋል፣ ጊዜያቸውን በሙሉ በተግባር ላይ እንዲያውሉ ይረዳቸዋል፣ ለትምህርታቸውና ለክፍላቸው ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል (Moore፣ 2001)፡፡

ትብብራዊ የመማር ብልሃት በትምህርት ቤቶች ውስጥ አስፈላጊ ነው ከሚባለው ብልሀት አንዱ ነው፡፡ እንደ Moore (2001)፣ Ruddell (1997)፣ Cohen (1986፣) አገላለፆች በተለይም በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ውጤታማ ብልሃት እንደሆነ ይስማሙበታል፡፡ ትብብራዊ የመማር ብልሃት በቡድን ስራ ውስጥ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይገለፃል፡-

### 1. የኀላፊነት ውክልናን ለተማሪዎች በመስጠት

የሀላፊነት ውክልና ሲባል መምህራን ተማሪዎች ከመናገራቸው ይልቅ ችግራቸውን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ፣ ስራቸውን እንዴት መምራት እንዳለባቸውና ከስህተት እንዴት እንደሚጠበቁ፣ በአጠቃላይ በራሳቸው እንዲመሩ ውክልና ወይም ሀላፊነትን መስጠት ማለት ነው፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመማር-ማስተማር ብልሃት ውስጥ ለተማሪዎች ሀላፊነትን በመስጠት ሁሉ ነገር ከራሳቸው እንዲፈልቅና መማሩን ራሳቸው እንዲመሩት ያግዛል፡፡

### 2. ኀላፊንትን በማካፈል መማር

ይህ ኀላፊንትን በማካፈል መማር የትብብራዊ መማር አንዱ ብልሃት ነው፡፡ Cohen (1986) እንደገለፁት ተማሪዎች ያለሌሎች ተባባሪ አካላት ተሳትፎና እገዛ በቡድናቸው ውስጥ የአንድ ሰው ስራ ፍጹማዊ አይደለም የሚል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ትብብራዊ ብልሃት ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በመደጋገፍ፣ አንዱ ሌላውን በመምራት፣ አቅጣጫን በማመልከት የእያንዳንዱን ተማሪ ጥረትና ሀላፊነት የሚጠይቅ ነው፡፡ Ruddell (1997) እንደሚያስረዱት በተማሪዎች መካከል ሀላፊነትን ማከፋፈል አንዱ ተማሪ ከሌላው መማር እንዲችልና በጥልቀት በማሰብ ከፍተኛ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡

### 3. ድብልቅ ችሎታ ያለው ቡድን በመመስረት

በትብብራዊ መማር ብልሃት ቡድን ሲመሰረት የክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በፆታ፣ በችሎታ፣ በፍጥነት ደረጃና በመሳሰሉት አሰባጥሮ በማቧደን የተውጣጣ ችሎታቸውን አቀናጅተው በመማር-ማስማሩ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ ይጠይቃል። የተማሪዎችን በችሎታ መለያየት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም በየራሳቸው ልምድና እውቀት አስተዋፅኦ በማድረግ የትምህርቱን ውጤት ህብረታዊ ያደርጉታል። መልመጃዎች በዚህ ስብጥር ችሎታ ባለው ቡድን ሲከናወኑ ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ከሌላው በተሻለ መንገድ በትግበራው ላይ እንዲሳተፉ፣ ስለቋንቋና ስለራሳቸው ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ ተግባቦታዊ ክሂልን እንዲያሳድጉ፣ በውሳኔ ሰጪነት፣ አብሮ የመስራት ብቃትን በማጎልበት በትምህርታቸው ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል (Nunan፣1992)።

ትብብራዊ የመማር ዘዴ የራሱ የሆነ ጥንካራና ደካማ ጎኖች አሉት። Cruickshank እና etal (1999) እንዳብራሩት፣ተማሪዎችን ዘና በማድረግ መረጃ እንዲለዋወጡ፣ ጥሩ የትምህርት ውጤት እንዲጎናጸፉ፣ በተነሳሳ ስሜት እንዲማሩ በማድረግ ረገድ ክፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። በአንፃሩ ደግሞ አስቸጋሪ ሰራዎች በተማሪዎች ብቻ መፈጸማቸው በመምህራን ዘንድ በአዎንታዊ አመለካከት መታየቱ፤ የተማሪዎች በስራ መተባበር ሁሌ አለመታየቱ፣ በቡድን ውስጥ አንድ ጠንካራ ተማሪ ካለ እሱን መጠበቁ፣ ሌሎች በውስጡ እንዳይሳተፉ ማድረጉ በደካማ ጎንነቱ የሚጠቀሱ ናቸው።

## 3.2.3. ግኝታዊ የመማር-ማስተማር ብልሃት

ግኝታዊ መማር-ማስተማር ሲበየን ተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ ከራሳቸው ልምድና ግንዛቤ አንፃር ትርጉም እየሰጡ የሚማሩበት መንገድ ነው። Cruickshankና et al (1999)እና ICDR (1999) ሲያብራሩ ተማሪዎች የራሳቸውን አእምሮታዊ ችሎታ በመጠቀም አዳዲስ ነገሮችን ሊማሩ የሚችሉበት ብልሃት እንደሆነ ያስረዳሉ። እንደዚሁም Moore (2001)፣ Callahanና Clark (1988)፣ Borich (1988) ተማሪዎች በችግር ፈቺ ተግባራት ላይ በመሳተፍ እውቀታቸውን ወይም ክሂሎታቸውን የሚያሳድጉበት ብልሃት ነው በማለት የምሁራኑን እሳቤ ያጠናክራሉ። በጥቅሉ ግኝታዊ የመማሪያ ብልሀት ተማሪዎች ሆን ብለው

ሳይንሳዊ መንገድን ተጠቅመው ችግርን በመፍታት በሂደቱ ውስጥ እውቀት የሚያገኙበት መንገድ ነው፡፡

ትምህርታዊ ጥቅሞቹን አስመልክቶ በግኝታዊ ዘዴ መማር ተማሪዎች በነፃነት በማሰብና በራሳቸው ተነሳሽነት ዕውቀት የመገብየት እድል የመስጠት፣ እውቀት የሚገበዩበትን መንገድ እንዲያውቁ የማድረግ፣ በራሳቸው ግንዛቤ መረጃ መሰብሰብ፣ በማደራጀትና በማንቀሳቀስ እውቀት የሚያገኙበት ትምህርታዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ተማሪዎች በጥልቀት የማሰብ ክሂል ወይም ስፋት ያለው ሀሳብ /Higher- order thinking/ እንዲኖራቸውና የተለያዩ ጽንሰ-ሀሳቦችን በመተንተን፣ በማብላላትና በመገምገም እውቀቱ ሊገኝ ይችላል፡፡

Richardsና Rodgers (2001) የግኝታዊ ብልሃትን ፋይዳ ሲገልጹ አእምሯዊ ብስለትን ይጨምራል፣ ከውጪያዊ(Extrinsic) መነሳሳት ወደ ውስጣዊ (intrinsic) መነሳሳት እንዲቀየር ያደርጋል፤ ጥያቄዎች በመጠየቅ ለመማር ያስችላል፣ የማስታወስ ሂደት ይቆጥባል፡፡ በICDR (1999) እንደተብራራው መምህራን በዚህ ብልሃት ክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ተማሪዎቻቸው የሚከተሉትን ተግባራት ማከናውን እንዳለባቸው ይመከራል፡፡

- ቁልፍ ፅንሰ-ሀሳቦችንና መርሆዎችን ማወቅ እንደ ሚኖርባቸው፣
- መምህራን የማስተማሪያ መሳሪዎችን ሲያዘጋጁ ንድፈሀሳቦችንና መመሪያዎችን ማዕከል በማድረግ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ግንኙነት እንዲፈጥሩ መርዳት እንዳለባቸው፣
- ተማሪዎች የመርሆዎችን ምንነት በመረዳት ወደ ተወሰኑ ፅንሰ ሀሳቦች እንዲሸጋገሩ መፍቀድ፣
- ውስጣዊ መነሳሳትን ከውጫዊው መነሳሳት ጋር ማጣጣም፣
- መምህራን ሁሉንም መልስ ከመስጠት ይልቅ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እንዲፈልጉ ማዘጋጀት፣

በዚህ ብልሃት አማካይነት ተማሪዎች የራሳቸውን የአእምሮ ችሎታ በመጠቀም አዳዲስ ነገሮችን ሊማሩ እንደሚችሉ መዘንጋት የለባቸውም፡፡

የዚህ ዓይነት የማስተማር ብልሃት ተማሪዎች የገጠሟቸውን ችግሮች በመለየት ለችግሮቹ የመፍትሔ ሀሳቦችን የሚፈልጉበት፣ የመፍትሄ ሀሳቦችን የሚያደራጁበት፣ መረጃዎችን

የሚሰበስቡበትና የሚተነትኑበት፣ በመጨረሻም የመረጃውን አስተማማኝነት በመፈተን ከአንድ ተጨባጭ እውነታ ላይ የሚያደርሱበት ብልሃት ነው፡፡

ግኝታዊ የመማር ብልሃት ስራ ላይ ሊውል የሚችለው በሶስት ደረጃዎች ነው፡፡ አንደኛው በጥንቃቄ የተመራ ምርምር ሲሆን ደረጃው የመምህራን እገዛ ታክሎበት የሚተገበር የምርምር ማስተማሪያ ዘዴ በመሆኑ የተማሪዎች ተሳትፎ አናሳ ነው፡፡ የተሻሻለው ግኝታዊ ምርምር ማስተማሪያ ዘዴ ሁለተኛው ደረጃ በመሆኑ የመምህራን እገዛ ቢታከልበትም አብዛኛውን ስራ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የሚያከናውኑበት ነው፡፡ ነፃ የምርምር ደረጃ ግን ከርዕሱም መገንዘብ እንደምንችለው ከርዕስ መረጣው እስከ ማጠቃለያና መፍትሔ ሀሳብ መስጫው ድረስ የመምህራን እገዛ የሌለበትና ተማሪዎች ነፃ ሆነው በራሳቸው ጥረት በመፍትሔ ፍለጋ ሂደት የሚሳተፉበት መንገድ ነው (Moore፣ 2001)፡፡

በአጠቃላይ በተማሪ- ተኮር አቀራረብ መምህራን ግኝታዊ የመማር ብልሃትን ተጠቅመው በክፍል ውስጥ ሲያስተማሩ በተገቢው መንገድ መምራት እንዳለባቸው Borich (1988) Callahanና Clark (1988) አበክረው ይመክራሉ፡፡ የማስተማሪያ ብልሃቱ በአግባቡ በጥቅም ላይ ከዋለ ትምህርቱ የበለጠ ትርጉም ሰጪ፣ በተማሪዎች አእምሮ እንዲቆይና አይረሴ እንዲሆን ይረዳል፤ መነሳሳት፣ ፍላጎትና እርካታን ይጨምራል፤ የአእምሮ የማሰብ ችሎታ እንዲያድግና መረጃዎችንና ችግር-ፈቺ ክሂሎችን እንዲያጎለብቱ ያደርጋል፣ ትምህርቱን እንዴት እንደሚማሩና እንዴት እንደሚያደራጁ ያስተምራል፣ ተማሪዎች በአዲስ አውድ ችግር እንዲፈቱ ያግዛቸዋል፤ ይህ ደግሞ መማር-ማስተማሩን ያፋጥናል፣ ለተማሪዎች ነፃነትን ያጎናጽፋል፣ የተፈጥሮ ችሎታቸውን በዕውቀት ላይ እንዲያውሉ ያግዛል፣ በእርስ በርስ ግንኙነት ጊዜ አዎንታዊ አመለካከትን እንዲፈጥሩ ያደርጋቸዋል፡፡

በግኝታዊ የመማር ብልሃት መማር አሉታዊ ጎኖችም አሉት፡፡ Cruickshankና etal (1999) የግኝታዊ ብልሃትን አሉታዊ ጎኖች የሚገልፁት ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ነው፡፡ ለምሳሌ በመምህራን በኩል ከብልሃቱ ጋር አለመተዋወቅና ለመተግበር ልምድ ያለመኖር፣ የተዘጋጀውን ትምህርት ለመሸፈን የጊዜ እጥረት መኖር፣ ሁሌ የታሰበው ውጤት ሊገኝ አለመቻል፣ ከመምህራንም ሆነ ከተማሪዎች በራስ የመተማመን መንፈስ መቀነስ፣ ተማሪዎች በስህተት ውስጥ ሲወድቁ እርምት ካልተደረገ ወደባሰ ስህተት ሊመሩ

እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ አሉታዊ ጎኖች የብልሃቱ መሠረታዊ ችግር ስላይደሉ በመምህራን ስልጠና መፍትሄ ሊያገኙ የሚችሉ ድክመቶች ናቸው፡፡

### 3.2.4.በፕሮጀክት የማስተማር ብልሃት

ፕሮጀክት ማለት ረዥም ጊዜ ተወስዶበት ታቅዶ የሚሰራ ስራ ወይም ተግባር ማለት ነው፡፡ እንደ Cruickshankና etal (1999)ገለፃ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ በመሆን በራሳቸው የታያቸውን፣ወይም የተሰጣቸውን ስራ ወይም የቀረበላቸውን ችግሮች በግል ወይም በጥንድ አለያም በቡድን ጊዜ ወስደው መፍትሄ የሚሰጡበት ብልሃት ነው፡፡ ይህ ብልሃት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ብዙ ጊዜ ስራ ላይ ይውላል፡፡

የፕሮጀክት ሰራ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ የተያያዘበት በብዙ ምክንየቶች ነው፡፡ Tudor (1996) እንደገለፁት ከነዚህ ምክንያቶች አንዱ በመማር- ማስተማሩን ሂደት ውስጥ ኀላፊነትን ከመምህር-ተኮር ወደ ተማሪ-ተኮር ለማሻገር ነው፡፡ በተጨማሪ ተማሪዎች የፕሮጀክት ስራን በራሳቸው በነፃነት በመተግበር ለተከሰቱ ችግሮች መፍትሄ የሚያገኙበት መንገድ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት ውስጥ ኀላፊነት እንዲወስዱ ያደርጋቸዋል ማለት ነው፡፡ Cruickshankና et al (1999) ከላይ የተነሱትን ነጥቦች በማጠናከር ተማሪዎች የራሳቸውን ርዕስ መርጠው በመረጡት ርዕስ ዙሪያ ለመፃፍ፣ ጥናት ለማድረግና ሪፖርት ለማቅረብ ያስችላቸዋል፡፡ ፕሮጀክቱን በመምረጥ ብቻም ሳይሆን የተማሩትን ነገር በማቀናበር ረገድም በፕሮጀክት ማስተማር ብልሃት ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ በአጠቃላይ ይህ ብልሃት ተማሪዎች በነፃነት ራሳቸውን ችለው በልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ ተሳትፈው የመማር ማስተማር ሂደትን እንዲያፋጥኑ የሚያደርግ በመሆኑ መምህራን ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

በፕሮጀክት የማስተማር ብልሃት መምህራን በመማር- ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እንዲያስወግዱ ያደርጋቸዋል፤ የተማሪዎቻቸውን ግላዊ ብቃትና ፍላጎት ለማሰስ ይጠቅማቸዋል፤ የተማሪዎቻቸውን ግላዊ ውሳኔ ይረዱበታል፤ ተማሪዎቻቸው በምርጫቸው መማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ያደርጋቸዋል፡፡ እንደዚሁም የተለያዩ ነገሮችን ለማደራጀት፣ ብዙ እንዲያነቡ፣ ዘና እያሉ እንዲማሩ፣ በሚገባ

ያቀዱትን እንዲፈጽሙ፣ ከውድቀት ውስጥ እንዳይገቡና ለመሳሰሉት ሁኔታዎች ይጠቅማቸዋል (Cruickshankና et al.1999፣ Ruddell፣ 1997፤ ICDR፣1999) ፡፡

እንደሌሎች የማስተማር ብልሃቶች ሁሉ በፕሮጀክት የማስተማር ብልሃትም ውጤታማነት የሚፈታተኑ ችግሮች አሉት፡፡ Cruickshankና et al (1999)ና ICDR (1999) እንደሚሉት ረጅም ጊዜ መውሰዱ፣ ተማሪዎችን በቀላሉ በብልሃቱ ተጠቅሞ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ለማሳተፍ አስቸጋሪ በመሆኑና የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ለማወቅ የሚያስቸግር መሆኑ የሚጠቀሱ ፈታኝ ችግሮች ናቸው፡፡ከእነዚህ ፈታኝ ችግሮች ውስጥ በትምህርት ክፍለጊዜ ማነስና የማስተማር ብልሃቱ ረዥም ጊዜ ጠያቂ መሆኑ፤ ለተለያዩ ማቴሪያሎች መግዣ ወጪ ጠያቂ መሆኑ፣በፕሮጀክት ለማስተማር የመምህራኑን ስልጠና ጠያቂ መሆኑ የዚህ ጥናት ወረቀት አቅራቢም ያምንበታል፡፡

### 3.2.5.ሚና ጨዋታ

ሚና ጨዋታ የሚለው ፅንሰ ሀሳብ ማንኛውም እንቅስቃሴ ሆኖ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በማህበረሰቡ ውስጥ ሊከሰት የሚችሉትን ጉዳዮች በመውሰድ አስመስለው ተግባራትን የሚከውኑት የማስተማሪያ ብልሃት ነው፡፡ Ur (1996) እንደገለፁት የሚና ጨዋታ የማስተማር ብልሃት ለተማሪዎች የሚቀርበው የትምህርት ይዘት ለተማሪዎች ግልጽ ሆኖ መረዳት እንዲችሉ በድራማ መልክ በራሳቸው በተመረጡ ተማሪዎች እየቀረበ የሚማሩበት ነው፡፡ ይህ ሲባል በድራማና በሚና ጨዋታ መካከል ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን መዘንጋት የለብንም፡፡ Jonsen (2007) ም ሲያብራሩ የሚና ጨዋታ በድራማ መልክ ማስተማር ነው፡፡ ተጨዋቹ የስራ ድርሻውን እንዴት እንደሚያከናውን፣ እንዴት ስሜቱን መግለጽ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ይህ ብልሃት ሌላው ስሙ ማህበራዊ ድራማ ወይም ስነ -ልቦናዊ ድራማ በመባልም ይታወቃል፡፡

ሚና ጨዋታ በተማሪዎች መካከል የተግባቦት ችሎታ ለማሳደግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ የሙያ አጠባበቅ ስልጠና፣ ወይም እንደ ሻጭና ገዢ፣ የአስተዳደራዊ ስልጠናና የመሳሰሉት ጭብጦች ላይ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ አውድ መፍጠር ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የሚና ጨዋታ የሌሎችን ስሜት ለመካፈል፣ አንዱ እንደተሰማው በውስጣዊ ስሜት እንዲሰማና አመለካከትን ለማንፀባረቅ ጠቀሜታ አለው (Petty፣1993))::

Matthews and et al (1985) በበኩላቸው ሲገልፁ ሚና ጨዋታ የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ከፍ ለማድረግ ጠቀሜታ ያለው ብልሃት በመሆኑ መምህራን በዚህ መንገድ የክፍል ትምህርት ለማቅረብ ሲፈልጉ በሚገባ ዝግጅት ሊያደርጉበት ይገባል ። ይህን ብልሃት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የተማሪዎችና መምህራንን ተራክቦ ይጠይቃል። የክፍሉ ድባብ ደግሞ ከመምህራን ትኩረት ውጭ ሆኖ አይን አፋር ተማሪዎችም ከሚና ተጫዋቾች ቡድን ትምህርት በመውሰድ እነሱም በተራቸው ለመስራት ተሳታፊ ሆነው ማሳየት ይኖርባቸዋል ።

Weimer (2002) እንደሚሉት፣ በሚና ጨዋታ መምህራንና ተማሪዎች የተጨዋቹን አመለካከት ይረዱበታል፤ ተማሪዎች በራሳቸው እንዲተማመኑና በወደፊት ስራቸው ላይ ራሳቸውን እንዲችሉ ይረዳቸዋል፤ በገሃዱ ዓለም ተግባራት ውስጥ ሐላፊነትን እንዲወጡም ያስችላቸዋል። በሚና ጨዋታ የማስተማር ብልሃት እንደ ሌሎቹ የማስተማር ብልሃቶች ሁሉ ጠንካራና ደካማ ጎን አሉት።ጠንካራ ጎኑ ተማሪዎች በራሳቸው እንዲተማመኑ፣ኂላፊነትን መቀበልና ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረጉ ነው። በሌላ በኩል ደካማ ጎኖቹ በሚገባ ታቅዶበት ወደ ተግባር ካልተገባ ውጤት አልባ ይሆናል። ለመለማመድና ለመስራት ጊዜን ይፈጃል፣ ሁሉንም ተማሪዎች የማሳተፍ የጊዜ እጥረት ይኖራል ። በአጭሩ የሚና ጨዋታ የማስተማር ብልሃት ቋንቋን ለማስተማር ለተማሪዎች ልዩ ልዩ ድርሻ በመስጠት እንዲጫወቱ በማድረግ ንግግርንና ማዳመጥን ማስተማር ይቻላል።

በአጠቃላይ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ወቅት እነዚህ ከላይ በምሁራን የተጠቀሱት ብልሃቶች ብቻ ናቸው ብሎ መወሰን አስቸጋሪ ነው።መምህራን ከተማሪዎች ጋራ በሚገናኙበት ጊዜ እንደ ሁኔታው አመቺነት ሌሎች ብልሃቶችንም ቀያይረው ሊያስተምሩበት ይችላሉ። ምክንያቱም ተማሪዎች በትምህርት ሂደት ተሳትፎአቸው፣ በችሎታቸውና ከመጡበት ዳራቸው አንፃር የማስተማር ብልሃቶች ሊለዋወጡ ይችላሉና ነው።

## 3.3. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንቅፋቶች

አንድን አዲስ የትምህርት ስርዓት በትምህርት ቤት ውስጥ በፍጥነት በስራ ላይ ለማዋል አስቸጋሪ ነው። የተማሪ- ተኮር አቀራረብም ከትምህርት ስርዓት ለውጦች አንዱ አካል በመሆኑ በትምህርት ቤት ውስጥ በስራ ለመተግበር የተለያዩ ውስብስብ ተግዳራቶች ያጋጥማሉ (Moore፣ 2001፤ Hess፣ 2001) ። በተማሪ-ተኮርም ሆነ በመምህር-ተኮር

አቀራረብ የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት በተለያዩ ምክንያቶች ይገደባል፡፡ Cruickshankና etal (1999) ዘርዝረው እንዳቀረቡት፣ በአንደኛ፣ በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በምልከታ መሳሪያነት በተሰበሰበው የመረጃ ጥናት የመማር-ማስተማሩን እንቅፋቶች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ሥር በማጠቃለል አስፍረዋል፡፡እነሱም ከግለሰቦች ባህሪያት ጋር የተያያዙ ምክንያቶች፣ ከትምርት ልምዶች ጋር የተያያዙ ምክንያቶች፣ በስብዕና ተጽዕኖ ጋር የተያያዙ ምክንያቶችና ከተለያዩ አውዶች ጋር የተያያዙ ምክንያቶች፣ናቸው፡፡

Leu (1998)ና (2000) ደግሞ የተማሪ -ተኮር እንቅፋቶች ናቸው ብለው የዘረዘሯቸው ሰው ፈጠርና ከሰዎች ውጪ ያሉ ተጽዕኖዎች በማለት ከፍለው ያስረዳሉ፡፡ ሰው-ፈጠር /Human Factor/ የተባሉት ዕንቅፋቶች የመምህራን፣ የትምህርት ቤትና የተቋማት ሀላፊዎች ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ አለመሆን፣የመምህራን ስልጠና ከዘዴው አተገባበር ጋር ተጣጥሞ አለመካሄድ ናቸው፡፡ ከሰዎች ወጪ ያሉ እንቅፋቶች የተባሉት ደግሞ የመማሪያ ክፍሎች ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማሪያ አመቺ አለመሆን ሲሆን በዚህ ስር የክፍሉ መጠን- የአካባቢ ሁኔታ፣ የሥርዓተ-ትምህርት መሳሪያዎች፣ የክፍል ውስጥ አደረጃጀትና የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ በተማሪ-ተኮር ዘዴ ለማስተማር አመቺ አለመሆን ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በ Leu (1998)ና (2000)፣ Moore (2001)፤ Hess፣ (2001) በጥናት አስደግፈው እንዳቀረቡት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በክፍል ውስጥ መማር- ማስተማር ሂደት ሊገደብ የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡፡

### 3.3.1. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ባህሪያት

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከተለምዷዊው የመምህር-ተኮር አቀራረብ የሚለይበት የአተገባበር ባህሪ አለው፡፡ ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ልዩ ልዩ ተግባራት እያከናወኑ በንቃት ተሳታፊ እየሆኑ ከተማሩ ትምህርቱ እንዲፋጠን ያደርገዋል፤የበለጠ ደግሞ ቋንቋ መማር በተሻለ መንገድ ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ስለዚህ ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርቱ ከቀረበላቸው ይበልጥ የትምህርቱን ይዘት አውቀው መረጃዎቹን

ለረዥም ጊዜ ከአእምሯቸው ውስጥ እንዲቆይና በህይወታቸው ዘመን በሚያጋጥማቸው ማንኛውም ነገር ውስጥ እንዲጠቀሙበት ያደርጋቸዋል፡፡

አንድ ለውጥ በስራ ሲተረጎም ከአካባቢ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ ሲሄድ ውጤታማ ይሆናል፡፡ Farrant (1980) እንደሚገልጹት፣ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ግቡን ሊመታ የሚችለው አቀራረቡ ከመምህር-ተኮር ወደ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተሸጋግሮና የመምህራን ስልጠና በአግባቡ ከተለያዩ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ ሲጓዝ ነው፡፡ ለውጡ ግልጽ የሆነ ዓላማዎች ሲኖሩትና የተማሪዎችን ባህልና ዳራ ያገናዘበ ሲሆን እንደዚሁም ለውጡን ለመተግበር በቂ የሆነ የትምህርት መሳሪያዎች ካሉት ዓላማው ከግብ ይደርሳል፤ ካልሆነ ግን ይገደባል፡፡ አሊያም ተግባሪው አካል(መምህራን፣ተማሪዎች፣ር/መምህራንና ጉዳዩ የሚመለከታቸው) በሚገባ ስልጠና ወስዶ የለውጡን ባህሪያት ሲረዳ ነው፡፡ Leu (1998) በበኩላቸው እንደሚያስረዱት፣ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በባህሪው ከሌላው የተለመደው የክፍል ውስጥ ባህሪያት ይለያል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች በቡድን ሆነው ሲወያዩ የስነ-ስርዓት ችግር የተከሰተ ይመስላል፣ ተማሪዎች ፍላጎታቸውን ሳይደብቁ መግለፃቸው ያልተለመደ አካሄድ በመሆኑ ራሳቸውን ከለውጡ ጋር ላልተዘጋጁ መምህራን ችግር ሊሆን ይችላል፡፡

Bonewellና Eison (1991)እንደሚገልፁት ትምህርቱ በኮሌጅ የመማሪያ ክፍል ውስጥ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ  ሲቀርብ የሚከተሉት ሁኔታዎች ይስተዋላሉ፡፡ ተማሪዎች ዝም ብለው ከማዳመጥ ይልቅ በተለያዩ ተግባራት ማለትም በማንበብ፣ በመወያየት፣ በመፃፍና በልዩልዩ ድርጊት በመፈፀም ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፤የትምህርቱ መረጃዎች ከአንዱ ወደ ሌላው በማስተላለፍ ላይ ከማተኮር ይልቅ ክህሎትን በማሳደግ ተግባር (በመተንተን፣ በማዋኂድና በመገምገም) ላይ ያተኩራሉ፡፡ተማሪዎች አመለካከታቸውን በመቀየር እሴታቸውን በመጠበቅ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፤የተማሪዎች መነሳሳት ከፍተኛ ነው፤ተማሪዎች ከመምህሮቻቸው ፈጣን ምጋቤ ምላሽ ማግኘት ይፈልጋሉ፤ በመሆኑም በመማር-ማስተማር ሂደት መካከል መምህራን ተማሪዎች እንዴት መማር እንደሚገባቸው ተረድተው ትምህርቱን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 3.3.2. የመምህራን አመለካከት ለውጥ

የመምህራን አመለካከት በክፍል ውስጥ ለሚሰጡ የመማር-ማስተማር ተግባር ተፅዕኖ ያደርጋል። Tudor (1996) እንደገለፁት የተማሪ- ተኮር አቀራረብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተለያዩ ለውጦችን በማምጣት ለሶስት ዓስርተ ዓመታት በስራ ላይ ውሏል። ለምሳሌ ተማሪዎች በተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ማህበራዊ ግንኙነት በሚያደርጉበት ወቅት ተግባቦትን እንዴት መፍጠር እንደሚችሉ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ የቋንቋ ትምህርቱ ይሰጥ ነበር። በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ መምህራን ከለውጡ ጋር ግጭት ውስጥ ገብተዋል። በተለይም ከአዳዲስ የመማሪያ መፃህፍት ጋር አለመጣጣም፣ የመምህራኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለውጥ አለመረዳት፣ የቋንቋ ማስተማር መርሀ-ግብሩ አዲስ ግብ መያዝ፣ የመምህራንና የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ግንኙነት ሁኔታዎች የግጭቱ መንስዔዎች ናቸው።

በተጨማሪም Birhanu (2010) ሲያብራሩ አንዳንድ መምህራን በአግባቡ ኃላፊነታቸውን ቢወጡም አንዳንዶች ደግ ሚናቸውን በአግባቡ ተግባራዊ የማድረግ አዝማሚያ አይታይባቸውም። እነዚህ ሐላፊነትን በብቃት መወጣት ያልቻሉ መምህራን ለተማሪዎች ስነ-ስርዓት መጓደል መሪ መሆናቸውና መማር-ማስተማሩን በማደናቀፍ የተማሪ-ተኮር ትግበራ ላይም እንቅፋት ሊፈጠሩ ይችላሉ።

በአጠቃላይ መምህራን የአንድ ለውጥ ቁልፍ ሚና ተጨዋቾች በመሆናቸው የለውጡን ሁኔታ በጥልቀት በመረዳት በጥሩ አመለካከት ተቀብለው ወደ ትግበራው መጓዝ እንደ ሚኖርባቸው የመስኩ ምሁራን ይመክራሉ። በዚህ ምክንያት መምህራን ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አዎንታዊ አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል። በተጨማሪም የለውጡ ግላዊ ዕቅድና የለውጡን እንቅፋቶችና ገዳቢዎችን በመለየት መፍትሄ መፈለግ ይኖርባቸዋል (Mc Combsና Whisler፣1997) ።ይህ ከሆነ በተማሪዎች ላይ እንዲታይ የሚፈለገው ለውጥ በአጭር ጊዜ ሊመጣ ይችላል ተብሎ ይታሰባል።

### 3.3.3. ባለ ጉዳዮችን ማሳተፍ

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የብዙ ሰዎችን ድጋፍ የሚፈልግ የመማር- ማስተማር አቀራረብ ነው። ብዙውን ጊዜ በዚህ አቀራረብ የመማር-ማስተማሩ ሂደት በመምህራንና በተማሪዎች

የሚገታ ቢመስልም ከእነዚህ ውጪ የሌሎች ተሳታፊ አካላትን ማለትም የተማሪዎች፣ የቅርብ ወዳጆችና ወላጆች፣የትምህርት አስተዳደር አካላት፣ በህብረሰብ ውስጥ ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች፣ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች፣ የአስተዳደር አካላትና የፓለቲካ ስልጣን ያላቸውን ሰዎች ትብብራዊ ተሳትፎ ይጠይቃል (Tudor፣1996፣ Mc combs ና Whisler 1996):: እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አካላት በተማሪ-ተኮር ሰርዓተ- ትምህርት እቀዳ፣ ትግበራና ግምገማ ውስጥ በመሳተፍ የተማሪ- ተኮር አቀራረብን ለውጥ በአግባቡ እንዲጎለብት እገዛ ያርጋሉ፡፡

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የብዙ ሰዎችን ድጋፍ በመፈለጉና በተለያዩ እርከኖች ላይ የሚገኙ አካላት ስለሚሳፉበት አቀራቡ ውሁድ ወይም ቅይጥ ሞዴል እንዲባል አድርጎታል (Brendesና Ginnis፣1986)፡፡ ይህ አቀራረብ ግብ መቺ እንዲሆን ሊያደርጉ የሚችሉት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ሲሳተፉበት በመሆኑ የሁሉንም አካላት ንቁ ተሳታፊነት ይጠይቃል፡፡ Leu (2000) እንደገለፁት ተቋማትና ርዕሳነ-መምህራን በመምህራን የሚሰራውን ስራ ካልተረዱ ግጭት ሊከሰት ይችላል፡፡ በተለይ ትምህርቱ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲሰጥ በቡድንና በጥንድ ተማሪዎች በተሰጣቸው ተግባራት ላይ ውይይት ሲያደርጉ ጫጫታና ሁካታ ቢከሰት ይህ ሁኔታ ከተለመደው የመምህር-ተኮር የክፍል አቀራረብ የተለየ በመሆኑ ተሳታፊዎች ይህን በአግባቡ ካላወቁት በትግበራው ላይ ችግር ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከላይ ምሁራኑ እንዳብራሩት ሁሉ የዚህ ጥናት አቅራቢም በመማር-ማስተማር ተግባር ባይሳተፉም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ተሳታፊ መሆናቸውን ይረዳል፡፡ በተለይም ከትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የትምህርት አመራሮች ለመምህራን ሁኔታዎችን ካላመቻቹ የትምህርቱ ዓለማ ከታቀደው ግብ ላይ መድረስ የማይቻል በመሆኑ እገዛቸው አስፈላጊ ነው፡፡

### 3.3.4. የመምህራን ስልጠና እጦት

የትምህርት ባለሙያዎች እንደሚመክሩት ትምህርት ስኬታማ ሊሆን የሚችለው በማህበረሰቡ ውስጥ አንዳች ለውጥ መምጣት እንዲቻል ከመርሀ-ትምህርት ቀጥሎ በሙያው የሰለጠኑ መምህራን ሲኖሩ ነው፡፡የሰለጠኑ መምህራን በትምህርት ውስጥ ከፍተኛ እድገት ለማምጣት በር ከፋች ናቸው (Smith፣1987)፡፡ መምህራን የድርሻቸውን ምኞትና እምነት ውጤታማ ለማድረግ ማስተማርን እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ግብ

ማለም ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህ ዓይነቱ የስርዓታዊ ለውጥ መሰረቱ የሰለጠኑ የመምህራን አውቀትና ክህሎት ነው (Richards፣1990)፡፡ በተጨማሪ Bruner (1996) የሰጡት እስተያየት የመምህራን ብቃትና ስልጠና ስለመማርና የሰው ልጅ ባህሪ ትውረታዊ እውቀት እንዲላበሱ ያደርጋል፡፡ ከዚህ እውቀት በመነሳት የትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀትና የማስተማር ዘዴዎች አጠቃላይና ዝርዝር አተገባበር ስልቶች ላይ ተገቢ እውቀት ይጎናፀፋሉ፡፡ Kakkar (1995)ም መምህራን የትምህርት ጥራትን በተፈለገው መጠን ማምጣት እንዲችሉ ስልጠና ማግኘት እንደሚገባቸው በአጽንኦት ያብራራሉ፡፡ በተመሳሳይ መንገድ Squazzin ና Graan (1998) እንደገለፁት በመማሪያ ክፍል ውስጥ መልካምና ውጤታማ ትምህርት ለመስጠት በሚገባ የተዘጋጁ ብቃት ያላቸው መምህራን ሊኖሩ ይገባል፡፡ ብቃት ሲባልም በስነ-ትምህርት ባለሙያነታቸውና በውጤታቸው ማለት ነው፡፡ መምህራን የመጣውን አዲስ የማስተማር ለውጥ ተቀብለው ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉት በቂ ስልጠና ካገኙ ብቻ ነው፡፡ Nunan (1992) ይህን አስመልክተው ሲገልፁ ለመምህራን ሙያቸውን የሚያጎለብቱበት እድል ሳያመቻች ስኬትን መመኘት ውጤቱ ባዶ ይሆናል፡፡ መምህራን የእያንዳንዱ የትምህርት አቀራረብ ለውጥ አቀንቃኝ በመሆናቸው በአሰለጣጠን ስርዓት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡

የመምህራን አስለጣጠን ሁኔታ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጋር ካልተጣጣመ በአተገባበር ላይ ችግር ሊከሰት ይችላል፡፡ Tudor (1996) እንደሚሉት መምህራን ቀደም ሲል የሰለጠኑበት አቅጣጫና የተማሪ - ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር አቅጣጫ ካልተጣጣመ አተገባበሩ ሊደናቀፍ ይችላል፡፡ Farrant (1986) ከላይ የተነሱትን ሀሳቦች ሲያጠናክሩ መምህራን በክፍል ውስጥ ትምህርቱንና ተማሪዎችን ለማገናኘት የመጨረሻዎቹ በመሆናቸው ወሳኞች ሊባሉ ይገባል፡፡ በዕውቀት ማነስ የተነሳ አዲሱን አቀራረብ በተገቢው መንገድ ካልተገበሩት እንቅፋቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ሁኔታ እንዳይከሰት የሥራ ላይ ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የስራ ላይ ስልጠና መምህራን ቀደም ሲል የሰለጠኑበትን መንገድ ከአዲሱ አቀራረብ ጋር እንዲስማሙ ያግዛቸዋል፡፡ Tudor (1996)ም እንደገለፁት፣ የተማሪ- ተኮር አቀራረብ ሊተገበር የሚችለው መምህራን ቀጥለው በተመለከቱት አቅጣጫዎች በቂ ስልጠና ካገኙ ብቻ ነው፡፡ ስልጠናው በፍላጎት አሰሳ ክህሎት፣ በትምህርት እቀዳ ክህሎት፣ በማስተማር ክህሎት /Educational Skills/ን እንደ ሁኔታው በመቀያየር ወይም አብሮ በመሄድ /Flexibility/ና ተጣጥሞት በመፍጠር፣

የመማሪያ ክፍሉን ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር በማስማማት ጥሩ አውድ እንዲፈጠር ለማድረግ፣ እንዲሁም የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት ክፍል መምህራን ያላቸውን አመለካከት ማስቀየር ነው፡፡

አንዳንድ መምህራን በራሳቸው የመተማመንና የሙያ ብቃት ጉድለት አለባቸው፡፡ Birhanu (2010) ሲያብራሩ አንዳንዶች መምህራን ሲያተምሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማራቸውን ቢደሰቱበትም በራሳቸው የመተማመንና የብቃት ጉድለቶቹ እንደሚገድቧቸው ይናገራሉ፡፡ እነዚህን ጉድለቶች በስራ ላይ ስልጠናና እርስ በርስ በሚያደርጉት መስተጋር ሊያስወግዷቸው እንደሚችሉ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ የማስተማር እውቀታቸውን ለማስፋትና የሚጠቀሙበትን የመማር-ማስተማር ግብዓቶች በአግባቡ ለመጠቀም ብሎም በራስ እንዲተማመኑ ለማድረግ የሥልጠና አስፈላጊነት ከዚህ በመለስ ነው ሊባል አይችልም፡፡

### 3.3.5. አካባቢና ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ምክንያቶች

ተማሪ-ተኮር የማስተማር አቀራረብ ሊያደናቀፉ ከሚችሉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ አካባቢና ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ምክንያቶች መማር-ማስተማሩ የሚከናወንበት ቦታና ሰዓት አመቺነት፣ የአየር ሁኔታ፣የመማሪያክ ክፍል ሁኔታ፣ትምርት ቤቶ የሚገኝበት አካባቢና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ለምሳሌ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችን በትብብር የመስራት የሚጠይቅ በመሆኑ አንድ መምህር በጣም ሞቃት በሆነበት ሰዓት መስኮት በሌለውና ንፁህ አየር በማያስገባ መማሪያ ክፍል ውስጥ በውይይት ማስተማር ቢፈልግ ሁኔታው አያመቸውም፡፡ተማሪዎች ይጨናነቃሉ፡፡በዚህ ምክንያት ከተፈለገው የትምህርት ዓላማ ላይ ለመድረስ ያዳግታቸዋል፡፡ አንድ የመማሪያ ክፍል በቂ መብራትና ንጹህ አየር የማያስገባ ከሆነ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ ችግር ሊከሰት እንደሚችል መገመቱ አግባብነት አለው (Mc combsና Whisler፣1996፤ Moore፣ 2001)፡፡

የማስተማሪያ ጊዜ የመምህራንን የመማር-ማስተማር ሂደት ይገድባል፡፡ Cruickshankና et al (1999) እንደገለጹት፣ የማስተማሪያ ሰዓት በመምህራን ላይ ከተከሰተ የሚፈለገውን የማስተማሪያ ብልሃቶች መርጦ ለማስተማር አዳጋች ይሆንባቸዋል፡፡ ሰፊ የማስተማሪያ ጊዜ ያላቸው መምህራን ቀጥተኛ ያልሆነ የመማር-ማስተማር አቀራረብን በተገቢው መንገድ

ለመጠቀም ይችላሉ። ይህ ማለት በምርምር፣ በውይይት፣ በፕሮጀክትና በመሳሰሉት የማስተማሪያ ዘዴዎች ለመጠቀም ይችላሉ። የጊዜ እጥረት ካለባቸው ግን ያቀዱትን ትምህርት ለመጨረስ በመምህር-ተኮር አቀራረብ ብቻ ለማስተማር ይገደዳሉ። ስለዚህ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ እንቅፋት ከሚፈጥሩ ምክንያቶች ውስጥ ጊዜ በተገለፀው መንገድ ተጽዕኖ እንዳያደርስ የሚያስተምሩትን ትምህርት በጥንቃቄ በማቀድና በመምረጥ ተግባራዊ ሊያደርጉት ይገባል።

### 3.3.6. የትምህርት መሳሪያዎች ለአቀራረቡ አመቺ ያለመሆን

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንደ ተፈለገው ተግባራዊ ላይሆን ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ የማስተማሪያ መሳሪያዎች አመቺ ያለመሆን ነው። Farrant (1980) እንደሚሉት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር በማስተማሪያ መጽሐፎች ውስጥ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ከተማሪዎች ዳራ ጋር ተገቢነት ከሌላቸው፣ የመማሪያ መጽሐፎች ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ካልተመጣጠነ፣ ስዕሎች፣ቻርቶች፣ ፖስተሮች፣ ፊልሞችና የመሳሰሉት እንደ ተፈለገው ካለመኖር የተነሳ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ እንዳይተገበር እንቅፋት ይሆናሉ። Nunan (1988)ና Leu (2000) እንደሚገልፁት የሥርዓተ- ትምህርት መሳሪያዎች የሚባሉት እንደ መርሀ-ትምህርት፣ መማሪያ መፃህፍትና የመምህሩ መምሪያ ተሟልተው ካልተገኙና ተማሪዎችን አሳታፊ ካልሆኑ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ግቡን እንዳይመታ ያደርጉታል። ይህም እነዚህ የስርዓተ-ትምህርት መሳሪያዎች ለተማሪ-ተኮር አተገባበር አመቺ ሆነው መገኘት እንዳለባቸው ያመለክታል።

### 3.3.7. የጊዜ እጥረት

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መማር ከመምህር-ተኮር አቀራረብ በላይ በመማር-ማስተማር ሂደት ላይ ረጅም ጊዜን ይጠይቃል። Birhanu (2010) እንዳብራሩት ለምሳሌ በመምህር-ተኮር አቀራረብ ሰፊውን ይዘት በአጭር ጊዜ ማብራራት ሲቻል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ግን ብዙ ሰዓትን ይፈጃል። ምክንያቱም ተማሪዎች ያቀረቡትን በማዳመጥና ሌሎች ተግባራትን ሰርተው እንዲያቀርቡ የሚያደርግ አቀራረብ በመሆኑ ነው። በዚህ ዙሪያም የመስኩ ምሁራን ቅሬታ ያሰማሉ። ምክንያቱም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የተሰጠው ክፍለ ጊዜና የመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚከናወንበት ጊዜ ያለመጣጣም ሁኔታ ስለሚታይ

ነው፡፡ በአገራችንም ይህ ሁኔታ በሰፊው እየተነገረ እንዳለ በመስኩ ጥናት ያቀረቡት ይናገራሉ፡፡ Taye (2008)፣ Solomon (2009)ና Yewulsew (2009) በጥናታቸው ውስጥ ከላይ የተገለፀው መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ እንዳይተገበር ከሚያደርጉት አንዱ ተግዳሮት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ በርግጥ አንዳንድ መምህራን በአግባቡ በመርሀ-ትምህርት ውስጥ የቀረቡትን ክፍለጊዜ እንደሚጠቀሙ ቢሰሙም አንዳንዶች ግን ከላይ እንደተገለፀው በቂ ክፍለጊዜ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ የጊዜ እጥረት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ ተጽዕኖ አድራሽ ነው፡፡

## 3.4. በተማሪ -ተኮር አቀራረብ ላይ የሚነገሩ አሉታዊ አስተያየቶች

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጽንሰ-ሀሳብ ሲወሳ በተማሪዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የመምህራንን የስራ ድርሻ የዘነጋ የሚያስመስሉ አስተያየቶች ይነገራሉ፤ ነገር ግን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ የሚፈጸመው በተማሪዎች ብቻ ሳይሆን መምህራንን ጨምሮ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን አቀራረቡን ከመተግበር አንፃር አነስተኛ ሚና እንዳላቸው ተደርጎ መታየቱ አግባብነት የለውም Smith (2004)፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ከፍተኛ የስራ ጫና ያለው በመምህራን ላይ እንደሆነ አለመታሰቡ ፅንሰ-ሐሳቡን በአግባቡ ካለመረዳት የመነጨ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲማሩ መምህራን የትምህርት አደራጆች፣ አመቻቾች እንደዚሁም የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡መማርን የሚከውኑት ተማሪዎች ይሁኑ እንጂ የመማሩ ፍፃሜ ተገቢነት የሚለካው መምህራን ባደራጁዋቸው፣ ባቀናጁዋቸውና ባመቻቹዋቸው የመማር ስርዓት ነው፡፡ ይህን ከላይ የተገለፁትን የመምህራንን የስራ ድርሻ ሳይረዱ የተማሪዎች ስራ እንደሆነና የመምህራንን ተግባራት አቅልሎ መመልከቱ አሉታዊ አስተያየት ነው፡፡

ይህም አስተያየት አሉታዊ ጎን ልንለው እንችላለን፡፡ ተጨማሪም ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ሲሳተፉ በተመሳሳይ መንገድ ከመምህራንና ከተለያዩ መፃህፍት የተለያዩ መረጃዎችን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሁሉም መረጃ ሰጪ አካላት ጋር የሚጣጣሙ ይሆናሉ፡፡ ይሁን እንጂ የተገኙትን መረጃዎች አወሳሰድና አምኖ መቀበል ላይ ችግር ሊያጋጥም ስለሚችል ይህ አንዱ የተማሪ-ተኮር አሉታዊ ጎን ሊሆን ይችላል፡፡

ሌላው Smith (2004) በተማሪ-ተኮር አሉታዊ አንደምታ ብለው የጠቀሱት ቴክኖሎጂን በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚያጋጥመው ችግር ነው፡፡ ዘመኑ መረጃ በኮምፒዩተር እንደ ውሃ የሚፈስበት በመሆኑ ይህ ሁኔታ ያልተሟላላቸው በተለያዩ ቦታዎች የመረጃ ክፍተት ይታይባቸዋል፡፡ ይህን ለማሟላት ኮሌጆች፣ ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ብዙ ክፍያ ይፈጽማሉ፣ኪራይ ይከፍላሉ፡፡ ተማሪዎችም ራሳቸውን ለቴክኖሎጂው በማስገዛት፤የቴክኖሎጂ ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ሳይሟላላቸው ሲቀር በራስ የመተማመን ብቃታቸው ይወርዳል፤የፍራቻ መንፈስም ይፀናወታቸዋል፡፡ ከዚህ የተነሳ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እንቅፋት ይገጥማቸዋል፡፡ በተጨማሪም የተማሪ ቤተሰቦችና አዋቂዎች እንደሚሉት ልጆቻቸው ከማህበራዊ ግንኙነት የራቁት፣ ቤተሰቦቻቸውን የማያዳምጡት፣ ሁሌ በኮምፒተውር ላይ ጊዜያቸውን ስለሚያሳለፉ ነው፡፡ ወላጆች ይህን ይበሉ እንጂ ተማሪዎቹ ጭንቀት እንደሌለባቸው፣ ደህና ሁኔታን እንደሚያሳዩ፣ ከሌሎችም ጋር መስተጋብር የሚፈጽሙ እንደሆኑ፣ የትኩረት መጠናቸው እንዳልቀነሰ Smith (2004) በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ ከዚህ ምሳሌ የርቀት ትምህርት በተማሪ-ተኮር ሲሰጥ አስፈላጊ የሆኑ መለዋወጫዎች ቴክኖሎጂውን ለማገዝ በቂ አይደሉም፣ የስልጠናው ጊዜም በቂ አይደለም፣ መምህራንም የጊዜ እጥረት ሊያጋጥማቸው ይችላል፣ በአጠቃላይ ተማሪ-ተኮሩን ለመተግበር የነገሮች የእርስ በርስ መደጋገፍ አናሳ መሆኑ እንደ ደካማ ጎን የሚወሰድ ነው፡፡ከላይ ምሁሩ በጥናታቸው ያስቀመጡት ሀሳቦች ሰዎች ስለ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚናገሩት አሉባልታ ሀሳቦች ሲሆኑ የሀሳቦቹ እውነታነት በጥናት ሲረጋገጥ ትክክለኛና ትክክል ያልሆኑ እንዳሉ ያሳየናል፡፡

በሌላ በኩል መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ያላቸውን ሚና ያለማወቅ ይታያል፡፡ ለዚህም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለምንም ስልጠና በዚህ አቀራረብ እንዲያስተምሩ መደረጉ ማስረጃ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚቀርበው ትችት እውነታውን ያላገናዘበ በመሆኑ የመምህራኑን ሚና በስልጠና ማጠናከሩ የግድ አስፈላጊ ነው (Smith፣2004)፡፡

Zulukufና Trombly (2001)እንደሚሉት ሌላው ትችት ተማሪዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ የአተገባበር ስልትን በሚገባ ካላወቁት በስነ-ምግባር ረገድ ከቁጥጥር ውጪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ Nunanም (1988) እንደዚሁ ተማሪዎች የማስተማሪያ አቀራረቡን በጥሩ አመለካከት ካልተቀበሉት የተለያዩ ችግሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ በመግለጽ የምሁራኑን እሳቤ ያጠናክራሉ፡፡ ለአብነትም በቱርክ በኢኖኑ /Inonu/ ዩኒቨርስቲ የነበረው የክፍል ውስጥ

ትምህርት አሰጣጥ  በመምህር-ተኮር አቀራረብ ላይ የተመሰረተው የመማር-ማስተማር ሂደት ቀስ በቀስ ወደ ተማሪ- ተኮር አቀራረብ ለመለወጥ ጥረት ሲደረግ ተማሪዎች አካሄዱን ለመቀበል መቸገራቸውን አብራርተዋል፡፡ እንዲያውም የክፍል ውስጥ መማር-ማስተማሩን በመረበሽ የማስተማሩን ሂደት ለማደናቀፍ ጥረት ያደርጉ እንደነበርና ከዚያም ለተማሪዎቹ ተገቢው ገለፃ እየተሰጠ በማለማመድ አቀራረቡን ቀስ በቀስ እየወደዱት መምጣታቸውን በዋቢነት አቅርበዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር ለተማሪዎች ተገቢ ሥልጠና ካልተሰጠ አተገባበሩ ችግር ሊገጥመው እንደሚችል ያመለክታል (Zulukufና Trombly (2001)፡፡

በአንዳንድ ጥናቶችም እንደተረጋገጠው ተማሪዎችም የመምህራንን ሙያ ዝቅ የማድረግ ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህን አስመልክተው Birhanu (2010) ማብራሪያ ሲሰጡ አንዳንድ ተማሪዎች በተለይም በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ  መምህራን ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ባህሪያት አንፃር ተማሪዎች የሚሰሩትን ተግባራት ባለመናገራቸው ወይም ማቅረባቸው ከዕውቀት ማነስ የመነጨ መሆኑን  የሚሰሙ አሉታዊ ንግግሮች ይደመጣሉ፡፡እንደዚሁም ሁሉም ተማሪዎች እንደተፈለገው በየቡድናቸው ውስጥ በንቃት ተሳትፈው ተግባራትን አይፈፅሙም አልያም ትብብር አያሳዩም፤ በአጭሩ በመማር ማተማር ሂደቱ መካከል የራሳቸውን ጉዳይ ያከናውናሉ፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ አንደምታ አለው፡፡ ከዚህም የተነሳ በመስኩ ምሁራን እንደተገለፀው በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር ከትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት ሁሉ ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

## 3.5. የጥናቱ ጽንሰ-ሀሳቦችና ስልተ-ትወራዊ መሰረቶች

በዚህ ርዕስ ስር የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አሁን የደረሰበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት የተለያዩ ፍልስፍናዎችና የመማር ንድፈ-ሀሳቦች ምን ምን እንደነበሩ ማሳየትና ተግባራዊነቱን ለመፈረጅ የሚያስችሉን ጽንሰሀሳባዊ መሰረቶች ይብራራሉ፡፡

### 3.5.1. የመማር-ፍልስፍናዎች

የሰው ልጅ በረጅም ዘመን ታሪኩ ኑሮን ለማሸነፍና የሚያጋጥሙትን ልዩ ልዩ ችግሮች ለመቋቋም በአጠቃላይ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት ባደረጋቸው ውጣ ውረዶች

የተለያዩ ፍልስፍናዎችና አይዲዮሎጂዎች ባለቤት ለመሆን ችሏል፡፡ ከእነዚህ ፍልስፍናዎችና አይዲዮሎጂዎች ደግሞ የተለያዩ እሴቶች መንጭተዋል፡፡ ከነዚህ መካከል የትምህርት ስርዓት ትምህርታዊ እሴቶች ዋነኞቹ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከነዚህ አስተሳሰቦች በመነሳት Clark (1987) የSailbekን (1982) ጥናት መሠረት በማድረግ በዝርዝር የሚያቀርቡትና፣ Nunan (1988)፣ Richards (2006)፣ Rechardsና Renady (2002)ና ሌሎች ተመራማሪዎች እማኝ እንደሚሆኑት፣ ሰፋፊ የትምህርት ፍልስፍናዎች አሉ፡፡ እነዚህም የጥንታዊ ሰብዓዊነት (Classical Humanism) የትምህርት ፍልስፍና፣ የመልሶ ማዋቀር (Reconstructionism) የትምህርት ፍልስፍናና የተራማጅነት (Progressivism) የትምህርት ፍልስፍና ዋና ዋና ናቸው፡፡ እነዚህ ፍልስፍናዎች ከቋንቋ መማር-ማስተማር በተለይም ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጋር ግኑኝነት ስላላቸው ለዚህ ጥናት መሰረት ስለሆኑ ቀጥለን አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን፡፡

#### 3.5.1.1. የጥንታዊ ሰብዓዊነት ፍልስፍና

የጥንታዊ ሰብዓዊነት (Classical-Humanism) ፍልስፍና በምዕራቡ የትምህርት ስርዓት ታሪክ ዋነኛ ሞዴል ሆኖ ለዘመናት ሲሰራበት የኖረ ነው፡፡ መነሻው የነፐሌቶና አርስቶትል የዕውቀት ቲዎሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ ፍልስፍና መሰረት መምህራን የሚታዩት እንደ ዕውቀት ባለፀጋ ወይም ሊቅ ነው፡፡ መምህራን የመማሪያ መፅሐፍ ይዘቶችን ያለችግር ማስተማር የሚችሉ አቅም ያላቸውና ተማሪዎችን ዕውቀት አስጨብጠው ለቁምነገር የሚያበቁ ሆነው ይታያሉ፡፡ የተማሪዎች ተግባር ደግሞ ዕውቀት መገብየትና የዚያን ዕውቀት ውስጣዊ ህግጋት በማወቅ ያገኟቸውን እውቀቶችና ህግጋት በአዳዲስ አውዶች ላይ በተግባር ማዋል ነው፡፡ ተመራጭ የመማር-ማስተማር ስነ-ዘዴያቸው መምህር-መር (Teacher-centerd) የሚባለው ነው( Harris፣ 1977፤ Cangeና lee 2001፤Clark፣ 1987፤ White፣ 2003) ::

የጥንታዊ ሰብዓዊነት (Classical Humanism) የትምህርት ፍልስፍና አተያይ ለዘመናት ከላይ በተገለጸው መንገድ እየተተገበረ ቢዘልቅም በመስኩ ሲመራመሩ ከነበሩት ምሁራን ትችት አላመለጠም፡፡Clark (1987)፣ Richardsና Renadyን (2002) እንዲሁም Kellyን (1989) ጠቅሰው እንዳስረዱት በጥንታዊ ሰብዓዊነት ስርዓተ-ትምህርት፣ የመምህሩ ሚና፣ የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫ ከኊላው ተከስተው ተቀባይነት እያገኙ ከመጡት ፍልስፍናዎች

ጋራ አለመጣጣሙ አንዱ ትችት ሲሆን፤ የተማሪዎችን ግላዊ ችሎታዎች፣ ችግሮችና የመማር ሂደትን ውስብስብነት ግምት ውስጥ የማያስገባ፣ ዓለም አቀፋዊነትንና ባህለ-ብዙነትን ባለማገናዘብ አንድን ባህል ብቻ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር የሚጥር በመሆኑ ተግባራዊነትና ውጤታማነት የጎደለው የትምህርት ፍልስፍና በመሆን ይወቀሳል። ፍልስፍናው ተማሪዎች አረፍተ-ነገር እንዴት እንደሚመሰርቱ በደንብ ማወቃቸውንና፤ በቂ ሊባል የሚችል የቃላት እውቀት ማዳበር ቢችሉም ተግባቦታዊ የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ አላስቻላቸውም። በመሆኑም በተማሩት ቋንቋ ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም፣ የሚሉና ሌሎች መሰል ትችቶች እየበዙበት በመምጣታቸው ከ1960ዎቹ መጨረሻና ከ1970ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ተቀባይነቱ እየቀነሰ የመጣ ፍልስፍና ነው፡

### 3.5.1.2.የመልሶ ማዋቀር የትምህርት ፍልስፍና

ከጥንታዊ-ሰብዓዊነት (Classical Humanism) የትምህርት ፍልስፍና በመቀጠል በ19ኛ መቶ ክፍል ዘመን ብቅ ያለው የመልሶ ማዋቀር (Re-constructionism) የትምህርት ፍልፍና ነው። ፍልስፍናው የማህበረሰብ ችግርን የሚፈታ፣ የሚታደግና ለችግሮች መፍትሄ በመስጠት ረገድ ለማህበረሰብ ለውጥ ተገቢነት ያለው ፍልስፍና እንደሆነ በመታመኑ Brameld በተባለ ምሁር በ1920ዎቹና በ1930ዎቹ በአሜሪካ ትምህርት ስርዓት ውስጥ የገባ ፍልስፍና ነው (Ornsteinና Hunkins፣2004)። በዚህ ፍልስፍና አተያይ መማር እውን ሊሆን የሚችለው ተማሪዎች ችግር በመፍታት ሂደት ውስጥ ከአካባቢያቸው ጋራ ተራክቧዊ ግንኙነት ሲፈጥሩ ነው። የትምህርቱ መጀመሪያ መሆን ያለበት ተማሪዎችን የሰው ልጅ ከሚያጋጥሙት ችግሮች ጋራ ማጋፈጥ ነው (Clark፣1987)።

የመልሶ ማዋቀር የትምህርት ፍልስፍና ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ለትምህርቱ ዓላማ ዳር መድረስ ስለሆነ ዓላማ-ተኮር ነው። በ (Clark፣ 1987) ዋቢ እንደተደረገው ሳቢያና ውጤት አባት የሚባለው Tayler (1949) አንድ ስርዓተ-ትምህርት በትምህርቱ መጨረሻ እንዲታይ የተፈለገውን ባህሪ እንዲያስገኝ ሆኖ መቀረጽ እንዳለበት አመላክተዋል። Ornsteinና Hunkins (2004 የማስተማሪያ ስነ-ዘዴውን አስመልክተው እንደሚያስረዱት በዚህ ፍልስፍና ውስጥ የተለያዩ ዘዴዎች ተግባራዊ እንደሚደረጉና ዘዴዎቹም ተማሪዎችን በቀጥታ በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሚያሳትፉ መሆን እንዳለባቸው ይገልፃሉ። በአጠቃላይ ግን በጅምላ፣ በአነስተኛ ቡድንና በግላዊ የማስተማር ዘዴዎች በተለዋዋጭነት ይዘወተራሉ።

ይህ ማለት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች በአንድነት፣ በቡድንና በግላዊ ተሳትፎ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በመሳተፍ ሊታይ ወደ ተፈለገው የትምህርቱ ዓላማ ላይ መድረስ መቻላቸውን ያሳያል፡፡

ይሁን እንጂ Clark (1987) እንደሚገለፁት፣ መምህራንና ተማሪዎች የመማር-ማስተማሩ ሂደት ከሚከናወንበት ክፍል ውጭ የተዘጋጀን የትምህርት ተግባር ብቻ ፈፃሚ በማድረግ የመምህሩን ሚና ከሚገባው በታች ስለሚቀንስ ከዲሞክራሲ እይታ አንጻር ይተቻል፡፡ እንደዚሁም ዓላማ-ተኮር በሆነው ስርዓተ-ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ለሚታሰቡ የትምህርት ልምዶች ውጤቶች ግልጽ የሆነ ባህሪያዊ ዓላማዎች ለመንደፍ አስቸጋሪ ነው በመባሉ፣ ተከታታይነት ያለው የትምህርት አደረጃጀት መከተሉ፣ ለውስብስብ የትምህርት ልምዶች ባህሪያዊ ውጤቶችን በግልፅ ማመላከት አለማስቻሉና በተጨባጭና ኢ-ተጨባጭ ፍላጎቶች መካከል ልዩነቶች አለመፍጠሩ የፍልስፍናው ተፈላጊነት እየቀነሰ ሄደ፡፡

### 3.5.1.3. የተራማጅነት የትምህርት ፍልስፍና

የተራማጅነት (Progressivism) የትምህርት ፍልስፍና አሜሪካ በቀል ሆኖ በዋናነትም ከኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ጋራ ተያይዘው ለመጡ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት ሲባል በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያና በ20ኛ መቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ መስፋፋት የጀመረ የስነ-ትምህርትን፣ የፖለቲካንና የማህበራዊ ተሃድሶን አስፈላጊነት የሚደግፍ ፍልስፍና ነው፡፡ እንደ Ornsteinና Hunkins (2004) አስተያየት ለአመለካከቱ መዳበር በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጆን ዱዊ ያበረከቱት አስተዋጽኦ በተለይም ከቤተሙከራ ጋር በተያያዘ የነበረውን ልምድ መሰረት በማድረግ ዱዊ ያፈለቀው ሁሉ-አቀፍ ንድፍ ለዚህ ፍልስፍና መሰረት መያዝ በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ የዱዊ ሁሉአቀፍ ንድፍ በወቅቱ የነበረውን የትምህርት ትውሮችና የመማር-ማስተማር ብልሀቶች በመፈተን ለሁሉም ሰዎች ሊስማማ የሚችለውን ንድፍ ማውጣት ነበር፡፡

የተራማጅነት (Progressivism) የትምህርት ፍልስፍና አመለካከቶችና መርሆዎች፣ ትምህርት ማህበራዊ ሂደትና ማህበራዊ ተሀድሶን በማምጣት ረገድ ቀዳሚውና ውጤታማው ነው፤ በመሆኑም ትምህርት ቤቶችም የማህረሰቡን ነባር ልምዶች እንዳሉ ከመቀበልና ከመጠበቅ በላይ በግለሰቦች በኩል አጠቃላይ ባህሉን የሚቀርፁ የማነጽ ተግባር

የሚከውኑ ናቸው፡፡ Clark (1987)ም እንደሚሉት ይህ የተራማጅነት የትምህርት ፍልስፍና አመለካከቶችና መርሆዎች፣ የተማሪውን አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ባህርይ እንዳለ ወስዶ ሁሉ-አቀፍ ማንነቱን በማዳበር ምሉዕ ሰው ማድረግ ላይ ያተኩራል፡፡ ለዚህም ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ መንገድ የሚያመቻች ነው፤ መምህራን ደግሞ እውቀት አስተላላፊዎች ሳይሆኑ የመማር ሁኔታዎችን የማመቻቸት ሚና ይኖራቸዋል፡፡

ይህ ማለት ተማሪው ውስጣዊ የመማር ብቃት አእምሮውን፣ ስሜቱንና ማህበራዊ ተግባቦቱን በመጠቀም በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን ትምህርት በራሱ አጎልቶ ብቁ እንዲሆን ማድረግ መቻልን ያመለክታል፡፡ ይህ የተማሪዎች ብቃት ከመምህራን ወደ ተማሪዎቹ የሚተላለፍ ሳይሆን በተማሪው ጥረት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያስረዳል፡፡ የተራማጅነት የትምህርት ፍልስፍና ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳትፎ በማድረግ በራሳቸው ጥረት እውቀት እንዲገበዩ የሚያበረታታ ሲሆን መምህራን ደግሞ እንደ ሁኔታ አመቻች በመሆን ተማሪዎቹን የሚያግዙበት ዘዴ በመሆኑ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጋራ የሚመሳሰሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ምንነትን በምዕራፍ ሶስት ውስጥ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

ይህ የተራማጅነት የትምህርት ፍልስፍና አያሌ አዎንታዊ አስተዋጽኦዎች ቢያበረክትም በምሁራን የሚተችባቸውን ምክንያቶች እንዳሉ ያስረዳሉ(Clark፣1987፤Ornsteinና Hunkins፣ 2004) ፡፡ አንዱ በፍልስፍናው ላይ የተሰጠው ትችት በአመለካከት ረገድ ልቅ ግብ (Open-ended view) ያለው በመሆኑ የማህበረሰቡን ሰፋፊና አጠቃላይ ግቦች ከማዕከላዊና አካባቢያዊ የመንግስት መዋቅሮች ጋር በእጅጉ የተቆራኘውን የትምህርት ስርዓት ከተማሪዎቹ ፍላጎት አንፃር ለመተለምና ለመተግበር አለመቻሉ፤ እንዲሁም የተማሪዎችን ባህል-ዳራ ያላገናዘበ በመሆኑ፣ይህም ፍልስፍና እያደር ተፈላጊነቱ እየቀነሰ ሄደ፡፡

## 3.5.2. የመማር ንድፈ-ሀሳባዊ መሰረቶች

ዘመናዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ንድፈ ሀሳቦች በአለም ላይ እየፈነጠቁ የመጡት በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በተካሄደ ንድፈ-ሀሳባዊና ተግባራዊ ጥናቶች ሲሆን የመጀመሪያዎቹ

ተግባራዊ ጥናቶች በአመዛኙ በእንስሳት ላይ የተደረጉ ናቸው፡፡ የመማር ትውሮቹ በስያሜም ሆነ በአይነት የተለያዩና በርካታ ሲሆኑ ባህሪያዊነት፣ ግንዛቤያዊነትና ሰብዓዊነት ተብለው ይጠቀሳሉ፡፡ ባህሪያዊነት (Behavaralism) አካባቢያዊ እይታን በመጠቀምና የብሪቴይንን አመሳሳይ (Associationist) የፍልስፍና ፈለግ መሰረት በማድረግ የዳበሩት የፓቭሎቭን ኮንዲሽኒንግ፣ የዋትሰንን ባህሪያዊነት፣ የትሮንዳይክን አያያዥ (Connectionist)ና የስኪነርን ተግባራዊ ኮንዲሽንኒግ (Applied Condictioning) ትውሮችን ያካትታል፡፡ የባህሪያዊነት ንድፈ ሀሳብ፣ በአንድ ውስን ቀስቃሽና ሊታይ በሚችል ውጪያዊ ምላሽ ተዛምዶ ላይ ያተኩራል፡፡በተጨማሪም ተግባራዊና ሙከራዊ ስልተ-ትውርን የሚከተል ነው፡፡

ባህሪያዊነት የመማርን ውጤታማነት በእንስሳት ላይ በተካሄደ የሙከራ ጥናት፣ በምልከታ በሚደረስበት ውጫዊ ሁነት የማረጋገጥ አዝማሚያ የሚከተል፣ ውስብስብ የሆነው የቋንቋ ትምህርት ከክፍል ውስጥ ክንውን እጅግ በቀለለው ቤተ-ሙከራ የመማር ተግባር ለማጠቃለል የሚሞክር ነው፡፡ የባህሪያዊነት ስነ-ልቡና ምሁራን የመማር ትውር አቀንቃኞች በግልፅ ለሚታየው ውጫዊ (Overt) ሁኔታ እንጂ በሚማረው አካል አእምሮ ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት ትኩረት አለመስጠታቸው የጋራ ባህሪያቸው ነው፡፡ ስለሆነም በባህሪያውያን አተያይ የመማር ስነ-ልቡና ማለት የተማሪውን ውስጣዊ ሂደት፣ ንቁ እቀዳ፣ ማሰብንና ሆን ብሎ ማከናወንን የማይመለከት የመማር ክስተት ነው (Stern፣1983)፡፡

አእምሮታዊ (Cognitivesm) የፒያዠን የዕድገት ስነ-ልቡና ትውርንና የጌስታልትን ፅንሰ-ሀሳቦች መሰረት አድርጎ የተፈጠረ ነው፡፡ ይህ ንድፈ-ሀሳብ በብሉያት ጌስታልት ትውር በ20ኛው መቶ የመጀመሪያ ሩብ መገባደጃ የተከሰተውና ለባህሪያውያን ንድፈ-ሀሳብ መቋረጥ የሆነው “በማስተዋል የመማር ትውር ” (Insight learning) መሰረት አድርጎ የተስፋፋ ነው፡፡ የጌስታልት ቴራፒ፣ በመጀመሪያዎቹ የግንዛቤ ትውሮች የግንዝቡ አለም ስርዓት ወደ አዕምሮ የሚደርስበትን ሁኔታ ለማወቅ በነበረው ፍላጎት በጌስታልት ትውር የተጀመረውን ችግር ፈች መማር መነሻ አድርጎ የተመሰረተ ንድፈ-ሀሳብ ነው፡፡ አእምሮታዊ የመማር ትውር የተቆለፈው የአዕምሮ ሳጥን (Black box of the Mind) መከፈትና ግንዛቤ ማግኘት እንዳለበትና ተማሪውም እንደ ኮምፒውተር ሁሉ መረጃን የሚያሳልጥ ሆኖ መታየት እንዳለበት ያምናል፡፡

አእምሮታዊ የመማር ትውር በተጠቀሱት መሰረተ-ሀሳቦች መነሻነት የተመሰረተ፣ በመማር ትርጉማዊነት፣ፍችም ንቁ ገጠመኝና ትርጉም አዘል ምልክቶች (ትዕምርቶች) ወይም እሳቤዎች በግለሰቡ አእምሮታዊ መዋቅር ሲካተቱና ሲሰናሰሉት የሚፈጠር ነው። በትውሩ ዋና አቀንቃኞች በጌስታል ስነ-ልቡና ምሁራንና በኡዝቤል መሰረት መማር ትርጉም ባለው የሰዎች እንቅስቃሴ የሚከናወንና በሂደቱ የሚገኘው አዲስ እውቀት በግንዛቤ መዋቅር ውስጥ ከተያዘው በሜንጦ የሚተሳሰርበት ሂደት ነው። እንደ ፒያዠም አባባል መማር "በተያዘው መማር ልምድ ላይ የተገነባ ለውጥን፣ራስን መሆንና መቀረፅን የሚያስከትል የዕድገት ሂደት ነው (Kafman፣2004) :: በአጠቃላይ በዚህ ትውር መሰረት ለመማር የሚቀርቡት የትምህርት ይዘቶች የተማሪዎች ተሳትፎን ይፈልጋሉ። ተሳትፎ ትምህርቱን በማፍጠን በተፈለገው የትምህርት ዓላማ ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያደርስ መሆኑን ያስገነዝበናል፡

## 3.5.2.1. የግንባታውያን የመማር- ማስተማር አተያይ

የግንባታውያን ትውር ጅማሬ በሃያኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ውስጥ በትምህርት ሊቁ John Deweyና በስነ-ልቦና ምሁሩ Vygotsky ንድፈ-ሀሳባዊ ፅሁፎች ተጽዕኖ የተገኘ ነው:: እነዚህ ጽሁፎች ነገሮች እንዴት ትርጉም እንደሚሰጡ፣ ተግባቦትና መረዳት በማህበራዊ እንቅፋቶች ሊታወኩ እንደሚችሉ የሚገልፁ ናቸው። ለዚህም የJohn Dewey ፍልስፍና በመማር-ማስተማር ውስጥ ዲሞክራሲ አስፋላጊ ጉዳይ በመሆኑ ተማሪዎች በሂደቱ ውስጥ ፍላጎታቸው ተጠብቆ የቀረባላቸውን ተግባራት በራሳቸው እያከናወኑ ከተማሩ ሰፊ ዕውቀትን ሊያጎናጽፋቸው ይችላል ያሉት ሀሳብ እውን ይሆናል (Brown፣ 2007)። በዚህ ምሁር አመለካከት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለተማሪዎች በነፃነት መማር አመቺ በመሆኑ ትምህርትን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማቅረቡ ተገቢ ነው።

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ መሰረቱን የጣለው በግንባታውያን ትውር ላይ ነው። በተለይም ተማሪዎች በተሻለ መንገድ ሊማሩ የሚችሉት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የቀረቡትን ተግባራት በማከናወንና ልምድ በመካፈል ነው የሚለው ፍልስፍና ላይ ነው (Brown፣ 2007)። የግንባታውያንን ንድፈ-ሀሳብ አስመልክቶ የVygotsky (1978) ገለፃ እንደሚያስረዳው ትርጉም ያለው እውቀት የሚገኘው ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው ካሉ ሰዎች ወይም እርስ በርስ በሚያደርጉት ተራክቦ ነው። ይህ ተራክቦ ደግሞ ትንታኔን፣ ግንዛቤን፣ ተጠየቅን (Logic) ያስከትላል። Brown፣ (2007) በበኩላቸው እንደሚያስረዱት ግንባታዊያን

እንደሚያምኑት እውቀት በቀላሉ ከመምህራን ወደ ተማሪዎች የሚተላለፍ ሳይሆን ተማሪዎቹ ራሳቸው በአእምሮአቸው ተጠቅመው በትምህርቱ ሂደት ውስጥ በንቃት ተሳታፊ ሆነው የሚያገኙት ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ውስጥ የመምህራን ተግባራት ተማሪዎች ለትምህርቱ እንዲነሳሱ ማበረታታት፣ በቀረበላቸው ትምህርት ችግሮች ዙሪያ ማወያየት፣ ፕሮጄክቶችን ከተማሪዎች ጋር መስራት፣ ምርምር ማካሄድ፣ በትብብራዊ መማር ውስጥ እገዛ ማድረግ፣ ተግባራትን ማዘጋጀት፣ መማርን መምራት ወዘተ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ አቀራረብ የተማሪዎች ሚና ካሉበት ነባራዊ ዓለም ጋር ግንኙነት በመፍጠር መራከብ ነው፡፡ ይህ እውነታ ለመገንዘብ፣ በጉዳዮች ላይ በጥልቀት ለማሰብ፣ በስራዎቻቸው ላይ እርስ በርስ ለመገማገም፣ ስለትምህርታቸውና አካባቢያቸው ትንታኔ ለመስጠትና ለመተርጎም ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ ያስችላቸዋል፡፡

### 3.5.2.2.ሰብአዊ ንድፈ ሀሳብና የቋንቋ መምህር ትምህርት

የሰብዓዊነት ንድፈ-ሀሳብ ከግንዛቤያዊ ንድፈሀሳብ ይበልጥ ለሰብዓዊ ስሜቶች ቅድሚያ የሚሰጥ፣ እውቀትን በማስተማር ሳይሆን የመማር እንዴትነትን በማስተማር ላይ የሚያተኩር ትውር ነው፡፡ ለመማር ወሳኙ ጉዳይ ከስጋት ነፃ የሆነ አካባቢ መፍጠር ነው፡፡ ትውሩ የመምህራን ሚናም መማርን ማመቻቸት መሆኑን ይቀበላል፡፡ እንደ Rodgers (1998) አገላለጽ መማር ተማሪውን ማዕከል ያደረገና ግለሰባዊ ነው፤ ለመማር አእምሮአዊና ስሜታዊ ፍላጎቶች ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የሰብዓዊ የቋንቋ መማር ትውርም የሚፈተሸውም ከዚህ በመነሳት ነው፡፡

የሰብአዊ ንድፈ-ሀሳብ መሰረታዊ መለያው ግለሰብ እራሱን እንደ ቻለ አካል በሚለው አተያይና በሌሎች በማይመራ ለግል ለውጥ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ ነው፡፡ ወደ ህልውናም የመጣው በስፋት የሚታወቀውን የስነልቦናና ስነ ልሳናዊ ትንተና አዎንታዊ አቀራረብ ለመቋቋም ነው፡፡ እድገቱ በ1950ዎቹ መጨረሻ አካባቢ በአሜሪካና አውሮፓ ከነበረው ግዙፍ ማህበረሰባዊ እንቅስቃሴ ሊነጠል የማይችል ነው፡፡ የሰብዓዊ ንድፈ ሀሳብ የቋንቋ ትምህርት ለሰዎች ሰብዓዊ መብት ቅድሚያ በመስጠት በክፍል ትምህርት ወቅት ተማሪዎች ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲስተናገዱ የሚያሳስብ ንድፈ-ሀሳብ ነው፡፡ ተማሪዎችም በትምህርታቸው ሂደት ውስጥ በነፃነትና የውስጣቸው ፍላጎት ተከብሮላቸው ከተማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ጥብቅና የሚቆም ነው፡፡ ስለዚህ ሰብአዊ ንድፈ ሀሳብ

የተግባር ነፃነትንና ግለሰባዊ ፍላጎትን ያከብራል፡፡ መማር መወሰን ያለበት በውስጣችን እንጂ ናሙናን መሰረት ያደረገ የትምህርት አቀራረብ እንደሚያራምደው በውጫዊ ሁኔታዎች ቁጥጥር ልናስኬደው አንችልም፡፡

በሰብዓዊ ንድፈ-ሀሳብ  የመምህራንና የተማሪዎች ግንኙነት እድገትን ለማፋጠን እንደ መረዳዳት የሚታይ ነው፡፡ የሰብአዊ አመለካከት ራስ-መር እድገትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የስልጠና ፍላጎቶቻችንን በመዳሰስ የመምህራንን ትምህርት በመርሀ- ትምህርት ብቃት በኩል ሊያሳድግ ወይም ሊያሻሽል የሚያስችል የትምህር ሞዴል ነው፡፡ ይህም የራስ እርማትንና በቡድን ውስጥ በንቃት መሳተፍን ያጠቃልላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በስፋት ግንዛቤ ያገኘው የቋንቋ መምህራን ትምህርት፣ በቀጣይ የተለያዩ የማንቂያ ስልቶችንና ተጨማሪ የስልጠና መልኮችን በመጠቀም ራሳቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉበትን መሳሪያ ሊያስታጥቃቸው ይችላል፡፡

የሰብአዊ ንድፈ ሀሳብ ተፅዕኖ ጎልቶ የወጣው በ1970ዎቹ የቋንቋ ለመዳ ንድፈ ሀሳብ ከባህሪያዊነት ግንባታ ወደ ሆነው የቋንቋ አመለካከት ባደረገው ለውጥ ነው፡፡ ሰብአዊ አመለካከት በመምህራን ትምህርት ላይ መሰረታዊ አቅጣጫን አመልክቷል፡፡ በዚህ አቅጣጫ የተማሪዎች ሁለንተናዊ ማንነት ስፍራ ያለው በመሆኑና ተማሪዎችም ከሁሉም በላይ በሁሉም ሁኔታዎች፣ በተለይም በመደበኛ የትምህርት ሂደት ግምት ማግኘታቸውም ሆነ ይህንኑ ማወቃቸው የሞዴሉ ጠቃሚ ጎን ተደርጎ ይወሰዳል ፡፡ በቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚካሄደው የለውጥ ጣልቃ ገብነት የመምህሩን ማንነትና አመለካከት ከመረዳት መጀመር አለበት፡፡ በማንኛውም ደረጃ ላይ የመምህራንን እድገት ስናስብ የመምህሩን ሁለንተናዊነት ማሰብ ያስፈልጋል፤ ይህ ማለት የግል ታሪካቸው፣ ስሜታዊና ማህበራዊ አካባቢያቸውን፣ እንዲሁም ቴክኒካልና በግልፅ የተቀመጠ ሚናቸውን ማካተት ያሻል (Roberts ፣1998)፡፡ ተማሪዎች በትምህርቱ ይዘትና አካሄድ ላይ ውሳኔ የመስጠት ድርሻ መያዛቸው ተገቢነት ቢኖረውም እንደ Belና Gilbert (1996) እምነት  ተማሪዎች በማደግ ላይ ያሉ በመሆናቸው ፍፁም የሆነ  ወሳኝነት የሌላቸውና ከፊል የሆነ ውክልና ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በዚህ አባባል ተማሪዎች በራሳቸው ሁሉንም የትምህርት ልምድ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከማድረግ ይልቅ መምህራን እገዛ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡

## 3.6. ጽንሰ-ሀሳባዊ ማዕቀፍ


የተለያዩ ጥናት አድራጊዎች ለምርምራቸው መሰረት የሚያደርጉት ፅንሀ-ሳባዊ ማዕቀፍና ንድፈ-ሀሳቦችን ነው፡፡ይህ ፅንሰ-ሀሳባዊ ማዕቀፍና ንድፈ-ሀሳቦችን መጠቀሙ የሚከናወነውን ስራ አቅጣጫ ማሳየትና እንደ መመሪያ ለመጠቀም ያስችላል፡፡ ጥናቱ የሚያጠነጥንበትን አቅጣጫና ስራው አቅጣጫውን እንዳይለቅ ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡ ይህን አስመልክተው Creswell (2009) ሲያስረዱ ተመራማሪዎች ሁሌ በአሀዛዊ ምርምር ንድፈ-ሀሳቦችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመፈተን ገለፃ እየሰጡበት የምርምራቸውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳሉ፤ መላምቶች ያረጋግጣሉ ወይም ያፈርሳሉ፡፡ በአይነታዊ ምርምር ውስጥ ደግሞ ጥናት አድራጊዎች ንድፈ-ሀሳቦች አጠቃቀም ላይ የልምጥነት ባህሪ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ጥናት አድራጊዎቹ በምርምራቸው ውስጥ እንደ መጨረሻው ግብ አድርገው ትውሮችን በማፍለቅ የጥናታቸውን አቅጣጫ ማሳየት ይችላሉ፡፡ የአንድን ምርምር ጽንሰ-ሀሳባዊ ማዕቀፍ ለማመልከት አራት አካሄዶችን መጠቀም ይቻላል፡፡ ለእነዚህ አራቱ አካሄዶች ማሳያ በትልመ-ጥናታቸው የሚከተሉትን አቅርበዋል፡-

- አንደኛው፣ ለመረጃ ስብሰባና ትንተና የሚያገለግሉ ንድፈ-ሀሳቦች እንዲሁም ጠቃሚ የሆኑ ተላውጦዎች (variables) በአሀዛዊው ምርምር ውስጥ ሊሰሩ ለታቀዱትና በመላምቶች ዙሪያ ሰፊ ገለፃ የሚያስፈልግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እዚህ ላይ ጥናት አድራጊዎቹ ምርምራቸውን ለማከናወን ከንድፈ-ሀሳብ ይጀምራሉ፡፡
- ሁለተኛው አካሄድ፣ ጥናት አድራጊው ሙሉ አቅጣጫውን በሚያመለክትበት ሁኔታ ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ማለት አጥኚው ከብዙ ጉዳዮቹ ውስጥ የትኛው ጉዳይ ጥናቱን በሚገባ ማሳየት እንደሚችል በመምረጥና በመወሰን እንደ መመሪያ አድርገው የሚመሩበት አካሄድ ነው፡፡
- ሶስተኛው ከንድፈ-ሀሳቡ አጠቃላይ ሞዴል ወይም ከሌሎች መረጃዎች በመነሳት ሰፊ ማብራሪያ የሚፈልጉና የምርምሩን የመጨረሻ ግቦች የሚያሳዩበት አካሄድ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለንድፈ-ሀሳባዊ መሰረት ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት ከጥናቱ ተሳታፊዎች የሚገኙ መረጃዎች ናቸው፡፡
- በአራተኛው መንገድ ጥናት አድራጊው ንድፈ-ሀሳቦችን መሰረት አድርጎ የሚንቀሳቀስ ሳይሆን ያለውን ልምድና የመረጃ ሰጪዎችን ሀሳብ ተጠቅሞ ሰፊና ጥልቅ ማብራሪያ ያለውን ማዕከላዊ ሁኔታ መግለፅ ነው፡፡

በዚህ መሰረት ለዚህ ሊደረግ ለታሰበው ጥናት እንደ ማዕቀፍ ሆነው የሚያገለግሉት በሁለተኛውና ሶስተኛው ተራ ቁጥሮች ላይ የተገለፁት አካሄዶች ናቸው፡፡ ይህ ማለት ከላይ ከተመለከትናቸው ልዩ ልዩ ፍልስፍናዎችና የመማር ትውሮች የዚህ ጥናት መነሻ ሀሰቦችን እናገኛለን ማለት ነው፡፡ በሌላ አባባል የጥናቱ ተተኳሪ መምህራንና ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ወቅት ያላቸውን ሚና በማሳየት የጥናቱን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በተለይም ከግንባታውያንና ከሰብዓዊ ንድፈሀሳቦች አተያይ አንፃር መምህራን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲተገብሩ፣ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ መሆናቸው፣ በነፃነት የተሰማቸውን መግለፅ መቻላቸው፣ ውሳኔ ሰጪ መሆናቸው፣ በችግር-ፈቺ ተግባራት መሳተፋቸው፣ በቡድን ውስጥ ሀሳብ ሰጪ መሆናቸው የራሳቸውን የመማር ስርዓት ፈጣሪ መሆናቸው ትልቅ ሥፍራ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው ሞዴል መምህራንና ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ያላቸውን ሚናና ተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ እንዲተገበር መሟላት የሚገቡትን አላባውያን ያመለክታል፡፡

**የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ሞዴል**

**ስዕል ሁለት፡-የመምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሚና**




ስዕል ሁለት የሚያመለክተው የአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር ሂደት ሲካሄድ መምህራንና ተማሪዎች የሚያካሄዱት ክንዋኔዎችና የጥናቱን ትኩረቶች ነው፡፡ በሰብአዊና ግንባታውያን ትውረቶች መሰረት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው እነዚህ በሳጥኖቹ ውስጥ የተዘረዘሩ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚታዩ ከሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያው መሳሪያዎች የተዘጋጁት እነዚህን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ ስር የምርምሩ አይነት ምን እንደሆነና ለምን ሊመረጥ እንደቻለ የመስኩ ምሁራን ስለተመረጠው የጥናት ዓይነት የዘረዘሯቸው ባህሪያትና በዚህ ጥናት ውስጥ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ ይገለፃል ። በማስከተል አጥኚው ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀመባቸውን መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና ለምን ሊመረጡ እንደቻሉ በመስኩ ጥናት ባደረጉት ምሁራን አስተያየት ተደግፎ ይቀርባል። እንዲሁም ለዚህ ጥናት መረጃ ሰጪ ናቸው ተብለው የተመረጡ ተጠኚዎች እነማን እንደሆኑና እንዴትስ ሊመረጡ እንደቻሉ በዝርዝር ይገለፃል። በመቀጠል የጥናቱን አስተማማኝነት ለመጠበቅ አጥኚው የተጠቀመባቸውን ዘዴዎች፣የሙከራ ጥናትና ውጤቱ፣የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተልና የቢሮና ስነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች ተብራርተው ምዕራፉ ይቋጫል።

## 4.1. የጥናቱ አይነት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ከሚገኙ የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጆች ተመርቀው በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዴት እያስተማሩ እንደሚገኙ መመርመር ነው። አጥኚው ከዚህ አጠቃላይ ግብ ላይ ለመድረስ አይነታዊ ምርምር /Qulitative Research/ና የገላጭ ምርምር /Describtive Research/ ንድፍ በመጠቀም የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርጓል። የገላጭ ምርምር ውስጥ ደግሞ ስያሚ ንጥል ንሞና (Reputational Case Sampling)፣ ስርዓታዊ፣ ዓላማ-ተኮር፣ ጥቅልና የአመቺ የንሞና ዓይነቶችን በመጠቀም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችሏል። ምክንያቱም አይነታዊ የምርምር ዘዴና የገላጭ ምርምር ንድፍ የተመረጡበት ምክንያት ጥናት አድራጊው ናሙና በመረጠበት ቦታዎች በመገኘት በጥልቀት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል አካሄድን ሲከተል ትረካን በመጠቀም ስለሚያብራራበት ነው። ይህን አስመልክተው Cohen et al (2000)ና Dorneyei (2007) እንደሚገልፁት በተለያዩ ክስተቶችና ለክስተቶቹ ምክንያት ይሆናሉ ተብለው በሚታሰቡ ጉዳዮች ወይም ተለዋዋጮች መካከል ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን ለማጥናት የሚያስችል የምርምር አይነት በመሆኑ ነው።

በተመሳሳይም ያለው፣አይነታዊ ምርምር እንደ አሃዛዊ ምርምር የጠነከረና የዳበረ ሳይንሳዊ ሂደትን የማይከተል የምርምር አይነት መሆኑን በመናገር ስለዚህ የምርምር ዘዴ ሂደት እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> *እንደ መጠናዊ ምርምር አይነታዊ ምርምር በተወሰኑ ተለዋዋጮች ላይ የሚያተኩር ሳይሆን ተመራማሪው አንድን ችግር ይወስድና ውሱን የሆኑ የችግሩን ባለቤቶች በመምረጥ ያነሳውን ችግር በጥልቀትና በስፋት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመዳሰስ መረጃዎችን የሚሰበስብበትና የሚተነተንበት ሲሆን በንሞና ሂደትም የጠናከረና የዳበረ ሳይንሳዊ ሂደትን አይከተልም (ያለው፣2004፣20)፡፡*

ከላይ በምሁሩ እንደተብራራው በዚህ ጥናት ውስጥ ዓይነታዊ ምርምር  ተግባራዊ ሲደረግ ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ በተወሰኑ ትምህርት ቤቶችና መምህራን ላይ ትኩረት በማድረግ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለመተንተን እንዲመረጥ አድርጎታል፡፡

ይህ የምርምር አይነት ከተግባራዊ ስነልሳን ጋር ያለውን ተያያዥነት በተመለከተ ከ1970ዎቹ ጀምሮ በተግባራዊ ስነልሳን ውስጥ ተቀባይነቱ እየጨመረ መምጣቱን፣ ለዚህም ምክንያቱ ማንኛውም ከቋንቋ ትምህርትና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በማህበራዊ፣ ባህላዊና ሁኔታዊ ጉዳዮች ላይ የሚወሰን ስለመሆኑ በተመራማሪዎች ዘንድ የነበረው ግንዛቤ እያደገ በመምጣቱ ተግባራዊ ስነልሳን ለአሃዛዊ የምርምር አይነት ብቻ ሳይሆን ለአይነታዊ ምርምርም ጭምርም ቦታ መስጠቱን Dorneyei (2007) ይገልጻሉ፡፡

አይነታዊ ምርምር ከአሃዛዊ ምርምር የሚለይባቸው በርካታ መለያ ባህርያት እንዳለው የተለያዩ የመስኩ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡ ከእነዚህ Dorneyei (2007)ና  Best (1999) የዚህ ምርምር መለያ ባህርያት ናቸው በማለት በዋናነት የሚጠቅሷቸውም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ተለዋዋጭነት፡-የአይነታዊ የምርምር ዘዴን ዋና ዋና ባህርያት በመግለጽ ረገድ አብዛኛዎቹ የምርምር ስራዎች በምርምሩ ክፍትነት (openeness) ባህርይ ላይ አጽንኦት በመስጠት ይጀምራሉ፡፡ ይህም ማለት በዚህ ምርምር ሂደት ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑት ተግባራት ሳይዛነፉ የሚከናወኑበት አይደለም ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በጥናቱ ሂደት ለሚከሰቱ አዳዲስ ክስተቶች ምላሽ ለመስጠት በየደረጃው የማስተካከያ ስራዎች ሊከናወኑ ይችላሉ

ማለት ነው፡፡ ይህ የአይነታዊ ምርምር ተለዋዋጭነት ባህርይ በምርምሩ ሂደት ለሚነሳ፣ በሚለወጥም ሆነ ሊሻሻል በሚችል የምርምሩ መሪ ጥያቄ ላይ እንኳን ሳይቀር ተግባራዊ ሊሆን ይችላል::

አይነታዊ የምርምር አይነት ከሚጠቀምባቸው መረጃዎች አኳያም ከአሃዛዊ ምርምር አይነት የተለየ ነው፡፡ ለዚህ የምርምር አይነት በመረጃነት የሚያገለግሎትም ከቃለ መጠይቅ፣ ከጽሁፍ ሰነዶች፣ ከፎቶግራፍና ከቪዲዮ ምስሎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው (Dorneyei፤ 2007፤ Best ፣1999)፤ Cohen et.al ፣2000) ::

የአይነታዊ ምርምር አላማው ክስተቶችን በተፈጥሮ ከሚከሰቱት አንጻር መግለጽ በመሆኑ በምርምሩ ወቅት በተጠኚዎቹ ላይ ተጽእኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ተለዋዋጮችን /variables/ በምንም መንገድ መጠቀም አይቻልም፡፡ ስለምርምሩ ተፈጥሮአዊ አውድ ወይም ሁኔታ ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት ተመራማሪው ምርምሩ በሚካሄድበት አውድ ውስጥ አዘውትሮ መገኘት እና ከተጠኚዎቹ ጋር ለረጅም ጊዜ የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር ይኖርበታል (Dorneyei 2007):: በዚህ ጥናት ውስጥም ተግባራዊ የሆነው ከተጠኚዎች ጋራ ግንኙነት በመፍጠር የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት ተሞክሯል፡፡

የተሳታፊ ትርጉም፡- የዚህ ምርምር ትኩረት በግለሰብ ሃሳብ (opinion) ፣ ልምድ እና ስሜት ላይ በመሆኑ ግቡ ጥናቱ በሚካሄድበት ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የጥናቱን ተሳታፊዎች ሃሳብ ማግኘት ነው፡፡ የዚህ እይታ መነሻም "የሰዎች ባህርይ የተመሰረተው ሰዎች ስለነገሮች በሚሰጡት ትርጉም ላይ ነው" በሚለው የአይነታዊ ምርምር መሰረታዊ መርሆ ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ልምዳቸው እና ተግባራቸው ትርጉም የሚሰጡት ቀጥተኞቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች ብቻ ናቸው፡፡ ስለዚህም የአይነታዊ ምርምር ተመራማሪዎች ማህበራዊ ክስተትን ለመመልከት የሚጥሩት ከጥናቱ ተሳታፊዎች አንጻር እና "ተሳታፊ" የሚለው ቃል የያዘው ጽንሰ ሃሳብ በአይነታዊ ምርምር ውስጥ ልዩ ስፍራ አለው ከሚለው እይታ አኳያ ነው (Dorneyei ፣2007)፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም መመረጡ ከላይ በተጠቀሱት ሀሳቦች አንፃር ነው፡፡

አነስተኛ የናሙና መጠን፡-በአግባቡ የሚከናወን አይነታዊ ምርምር በጣም አድካሚ በመሆኑ ለምርምሩ የበለጠ አስፈላጊ የሆኑ የተመረጡ ጥቂት መረጃዎች አገልግሎት ላይ የሚውሉ ስለሆነ ከአሃዛዊ ምርምር አንጻር በጣም አነስተኛ ነው፡፡

ትርጉማዊ ትንተና፡- አይነታዊ ምርምር ከመሰረቱ ትርጉማዊ ነው፡፡ ይህም ማለት የምርምሩ መረጃዎች ትንተና የሚካሄደውና በመጨረሻ ላይ የሚገለጸው ተመራማሪው በሚያደርገው

ገለጻ ነው ማለት ነው፡፡ከላይ በምሁራኑ በተገለፁት ሀሳቦች ምክንያት በዚህ እየተደረገ ላለው ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

በተጨማሪም Gay et al (2009)፣ Lodicoና et al (2010) እንደገለፁት ተመራማሪው በአይነታዊ የምርምር ለማጥናት የፈለገውን ጉዳይ እንዴት እንደሆነ ለምን እንደዚያ እንደሆነ በጥልቀት በመፈተሽ ያቀርባል፡፡ መረጃዎቹን ተንትኖ የሚያቀርበውም በትረካ ወይም በገላፃ መንገድን ነው፡፡ የተመራማሪው ትኩረት አንድን ችግር በመለየት፣ የችግሩን ባለቤቶች በመምረጥ ያነሳውን ጉዳይ በጥልቀትና በስፋት ከተለያዩ አቅጣጫዎች መሰብሰብና መተንተን ነው፡፡ ተመራማሪው ከልምዱ በመነሳት መረጃ ይኖራቸዋል ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች በመምረጥ በጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሊያደርግም ይችላል፡፡ ከዚህ የተነሳ ግለ-ሀሳባዊነት (Subjectivity) ጎልቶ ሊንፀባረቅበት ይችላል (Creswell፣ 2012) ፡፡ ስለዚህ ተመራማሪው በተወሰነ ጉዳይ ላይ በማተኮር፣ በጣም ውስን ቁጥር ያላቸውን የጥናት ተሳታፊዎች ብቻ በመውሰድ ያነሳውን ችግር ከተለያዩ አቅጣጫዎች በጥልቀት ለመመልከት ይገደዳል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ከተመረጡት የምርምር ንድፍ ውስጥ ንጥል ምርምር ይገኝበታል፡፡ Fred ና Perry (2005) እንደሚገልፁት ንጥል ምርምር የአንድን ግለሰብ፣ ቡድን፣ ተቋም፣ ቤተሰብ፣ ኢንዱስትሪ ህይወት ወይም ተግባር ከተለያዩ መስፈርቶች አንጻር በጥልቀት ለማጥናት የሚያስችል የምርምር አይነት መሆኑን ሲበይኑ Cohen et al (2000) ደግሞ በእንቅስቃሴ ላይ ስለሚገኝ አንድ ነጠላ ጉዳይ የሚደረግ ጥናት እንደሆነና ነጠላ ጉዳይ የሚሉትም ለምሳሌ፡- አንድ ህጻን፣ አንድ ቡድን፣ አንድ ማህበረሰብ ሊሆን እንደሚችል የሚገልጹ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚህ ብያኔ አንፃር በዚህ ጥናት ውስጥ በአንድ ኮሌጅና በአራት ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረገው ጥናት ሊመረጥ ችሏል፡፡

Cohen et.al (2000) እንዳብራሩት ንጥል ምርምር በአንድ በተወሰነ አውድ ውስጥ በሚካሄድ ትምህርት ላይ ተጽእኖ በሚያሳድሩ በርካታ ባህላዊ ሁኔታዎችና በመምህራን፣ በተማሪዎች እንዲሁም የትምህርት ጉዳይ በሚመለከታቸው ሌሎች ሰዎች መካከል ስላለው መስተጋብር ለማወቅ በአንድ ተማሪ፣ በአንድ ክፍል ወይም በአንድ ትምህርት ቤት ላይ የሚካሄድ ጥናት መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ ሀሳብ በመነሳት በተደረገው ጥናት ውስጥ ውስን ትምህርት ቤትና ኮሌጅ በመምረጥ ጥናቱ ሊከናወን ችሏል፡፡ በመሆኑም እንደተብራራው በባሌ ዞን በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው

እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተጠቅመው መማር-ማስተማሩን ሲተገብሩ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ምን እንደሆኑና እንዴት እያስተማሩ እንደሚገኙ፣ ጥንካሬያቸውና ድክመታቸው ምን እንደሆነ፣ መረጃውን በናሙና ከተመረጡ ትምህርት ቤቶች ተሳታፊዎች በመሰብሰብ በትረካ ለመተንተን የሚያስችል በመሆኑ ይህ የምርምር ዓይነት ተመርጧል ፡፡

## 4.2. የጥናቱ ቦታ አመራረጥ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን በአንደኛ ደረጃ በሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን ላይ ሲሆን ጥናቱ በአይነታዊ የምርምር ዘዴ የተካሄደ ነው ፡፡ ጥናት አቅራቢው የባሌ ዞንን የመረጠበት ሁለት ምክንያቶች ነበሩት፡-

- በዞኑ ውስጥ ከአስራ አምስት ዓመታት በላይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሮቤ መምህራን ማስልጠኛ ተቋም በመምህርነት ሙያ ማስተማር (Pedagogy) መምህርነት፣ በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛና የስነ-ትምህርት (Education) መምህር በመሆን እንደዚሁም በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ መምህርነት ሲያገለግል በመቆየቱና በዞኑ ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚከናወኑ የመማር-ማስተማር ሂደቶችን በሚገባ ለመረዳት በመቻሉ፤
- በባሌ ዞን ከሚገኙ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ጋራ በወርክሾፖች፣ በአውደ ጥናቶችና በተለያዩ ስልጠናዎች ላይ በመሳተፉና ስልጠናም በመስጠት መምህራኑ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን እንቅፋቶች የማዳመጥ ዕድል ገጥሞታል፡፡ በተለይም በተማሪ-ተኮር ትግበራ ሂደት ውስጥ የሚታዩትን ክፍተቶች ለመታዘብ በመቻሉ የጥናቱ ቦታ ባሌ ዞን እንዲሆን ወስኗል፡፡ ስለዚህ የጥናቱ የቦታ ምርጫም በDornyei (2007)ና መሰረት በአመቺ /Convenience/ የናሙና አመራረጥ ሥርዓት የተከተለ ነው

## 4.3. የጥናቱ የመረጃ ምንጮችና የንሞና ዘዴ

ለተጠቀሰው የጥናት ርዕስ መረጃ ለመሰብሰብ ከሮቤ መምህራን ትምህርት ማስልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ከአፋን ኦሮሞ ትምህርት ክፍል የአፋን ኦሮሞ መምህራንና የ3ኛ ዓመት ሰልጣኝ የአፋን ኦሮሞ ተማሪዎች፣ የኮሌጁ ዋና ዲንና የአካዳሚክ ምክትል ዲን፣ የመምህርነት

ሙያ አሰልጣኝ መምህርና የፕራክቲከም ክፍል ኃላፊ በመረጃ ምንጭነት የታቀፉ ናቸው፡፡ ከነዚህም በተጨማሪም ሰልጣኞች የሚሰለጥኑባቸውን የመምህርነት ሙያ አተገባበር የሚያሳዩ ሰነዶች ና በመቅረፀ-ድምጽና መቅረፀ-ምስል የታጀበ የክፍል ምልከታ ናቸው ፡፡ መምህራን ደግሞ ስለሚያስተምሩበት የመማር-ማስተማር አቀራረብ፣ ዘዴዎች (ብልሃቶች)፣ ስለሚያስፈልጋቸው ግብዓቶች፣ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ስለሚያጋጥማቸው ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው መረጃ አላቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ሁለቱ የአፋን ኦሮሞ መምህራን በጠቅላይ ንሞና ተመርጠው በመረጃ ምንጭነት ቀርበዋል፡፡ በዕጨ መምህራን በኩል ከ3ኛ ዓመት የአፋን ኦሮሞ ሰልጣኞች መካከል ለቡድን-ተኮር ውይይት የተመረጡበት በስርዓታዊ የንሞና ዘዴ ነው፡፡ ይህ የስርዓታዊ ንሞና አመራረጥ ለቡድን ተኮር ውይይት የሚፈለጉት የተማሪዎች ቁጥር ከ47 ተማሪዎች አስር ብቻ ናቸው፡፡አስሩን ተማሪዎች ለመምረጥ የተማሪዎቹን ቁጥር በአምስት ልዩነት ዘርዝሮ ማመልከት ተችሏል፡፡ለምሳሌ 5፣10፣15፣20፣25፣30፣35፣40፣45፣47 ተመርጠው ለቡድን ውይይት ቀርበዋል፡፡

ለጥናቱ ከተመረጡት የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን በየትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የሚከናወኑ የመምህራንን ተግባራት በቅርበት የሚከታተሉ፣ የየዕለት ስራቸውን የሚገመግሙ፣ የመንግስት መመሪያዎችንና ደንቦችን የሚያስፈጽሙ በመሆናቸው በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በዓላማ -ተኮር ንሞና አራት ርዕሳነ መምህራን ተመርጠዋል፡፡

ለጥናቱ የተመረጡት የአንደኛ ደረጃ የአፋን ኦሮሞ መምህራን በባለፈው የትምህርት ስርዓትና አሁን ባለው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተመርቀው በ7ኛ ክፍል ለጥናቱ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እያስተማሩ የሚገኙት ናቸው ፡፡ ስለሆነም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ7ኛ ክፍል መምህራንን በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ለመመረጥ ተችሏል፡፡ ከትምህርት ቤቱ የተመረጡ ተማሪዎችም በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የክፍል ምልከታ ከተደረገባቸው ክፍሎች ውስጥ ነው፡፡ ለቡድን ተኮር ውይይት የተመረጡበት በስርዓታዊ የንሞና ዘዴ ነው ፡፡

በተጨማሪም ለመረጃ ሰጪነት ከተመረጡት ተሳታፊዎች ውስጥ የሶስት ወረዳ የመምህራን ልማት ተጠሪዎችና ከባሌ ዞን ትምህርት መምሪያ የመምህራን ልማት ተጠሪ ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት በወረዳቸው ስር ለሚገኙ የአፋን ኦሮሞ መምህራን የስራ ላይ ስልጠናና

የተለያዩ ድጋፎች ማድረግ አለማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ሲባል በዓላማ-ተኮር ንሞና ሊመረጡ ችለዋል፡፡

ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክፍል ሐላፊ፣ የመምህራን ልማት ሐላፊና የአፋን ኦሮሞ ትምህርት የቡድን ተጠሪም መረጃ ሰጪዎች ናቸው፡፡ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክፍል ሐላፊና በቢሮው የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን ተጠሪ የአፋን ኦሮሞ የመማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማሪያነት እንዲመች የተደረጉ ጥረቶች መኖር አለመኖራቸውን ለማረጋገጥና የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ላይ የነበረው የተማሪዎች ተሳትፎ ምን እንደሚመስል መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ከሚል እሳቤ የተመረጡ ናቸው፡፡ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የመምህራን ልማት ሐላፊና ሌሎች ባለሙያዎች በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ መምህራን ስለተሰጣቸው የሥራ ላይ ስልጠና ይዘትና አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ በማሰብ በዓላማ-ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

## 4.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### 4.4.1. የክፍል ምልከታ

ይህን ጥናት ለማከናወን ከተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ምልከታ ሲሆን ይህም ለቀዳማይ መረጃዎች መሰብሰቢያነት የተመረጠ ነው፡፡ ምልከታ ማህበራዊ ተራክቦ ወይም ክስተት ባለበት ቦታ በአካል በመገኘት ሁሉንም ሁኔታ ለመመልከት ወይም ለመስማት ተመራጭ ስልት ነው (kumar 1999ና ያለው 2001)፡፡ መረጃ ሰብሳቢው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልጋቸው ተጠኚዎች ጋር በመገኘት የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት እያየና እየሰማ በመመዝገብ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡

ምልከታ ከበርካታ ሁኔታዎች አንፃር በጣም ተመራጭ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው Kumar (1999) ይህንኑ በምሳሌ ሲያብራሩ ስለአንድ ማህበራዊ ተራክቦ ለማጥናት ብንፈልግ፣ የግለሰብን ባህሪያት ወይም ማንነት /Personality/ ለማጥናት ብንፈልግ ወዘተ ምልከታ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ይልቅ ተመራጭ ነው፤ ግለሰቦች ሲጠየቁ

በቂና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ላይሆኑ ስለሚችሉና ለመመለስ በቂ ግንዛቤ ላይኖራቸው ስለሚችል በምልከታ ተጠቅሞ ግልጽ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ትክክለኛውን የመምህራንና የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተራክቦና የሚፈፀሙ ተግባራትን አውዳዊ ምልከታ በማድረግ ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ምልከታውን ለማከናወን ባለ አምስት የክፍል መከታታያ መስፈርት የያዘ ማረጋገጫ ቅጽ /Checklit/ ተዘጋጅቶ በቅጹ መሰረት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ በቅጹ ላይ የቀረቡት ይዘቶች የመማሪያ ክፍል አደረጃጀት፣ የመምህራንና ተማሪዎች ተግባር፣የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በተመለከተ እንዲሁም የመምህራን የምዘና ስልትን ያየዘ የNunan (1988) መስፈርቶችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡

በቅጹ ላይ የክፍል ውስጥ አደረጃጀት መስፈርት ስር በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ተገቢ የወንበርና የጠረጴዛ መኖር አለመኖር፣ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ንጽህናና ምቹ መሆንና ተያያዥ ነጥቦች ተካተውበታል፡፡ የመምህራንና የተማሪዎች ተግባርን በተመለከተ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ የሚተገብሩትን ብልሃቶችና ተማሪዎችን ለመርዳት የሚያከናውኑትን ማንኛውንም እንቅስቃሴ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ የተማሪዎች ተግባራት አስመልክቶ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ከመምህራን ተግባራት በተጓዳኝ ተማሪዎች የሚያከናውኑትን ተግባራትና ተሳታፊነትን ያመለክታል፡፡ የትምህርት መሳሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ፣ ትምህርቱ የሚሰጥባቸውን የመማሪያ መጽሐፍትና ሞጁሎችን ጨምሮ ሌሎች ተመሳሳይ መሳሪያዎችን የሚዳስስ ነው፡፡ የተማሪዎች ምዘና በተመለከተ የመምህራንን የተከታታይ ምዘና ውጤት መሙያና የተማሪዎች ማስታወሻ መያዣ ደብተሮች የሚተኮርባቸው ናቸው፡፡ እንደዚሁም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተግባራት አገማገም፤ የክፍል ስራዎች፤ የቤት ስራዎችና የሙከራ ስልቶች አቀራረቦች ተቃኝተዋል፡፡

በክፍል ውስጥ የሚደረጉት የመምህራንና የተማሪዎች ተራክቦዎች ምልከታ አድራጊው እንደተመለከተው የምልከታውን ክስተት በቪዲዮና መቅረፀ ድምጽ አስደግፎ መሰብሰቡ ለሚሰጠው የውሳኔ ሐሳብ ተጨባጭባጭነት ከማረጋገጡም በላይ አጥኚው የነበረውን እውነታ አይቶ ወዲያው ከአንድ ድምዳሜ ላይ ከማድረሱ በፊት የተቀረፀውን ቪዲዮና መቅረፀ-ድምጽ ደጋግሞ በማየትና በማዳመጥ ሁኔታዎችን በአግባቡ እንዲመረምር እድል

እንዲያገኝ ይረዳዋል፡፡ ባለሙያዎችም ቪዲዮውን ተመልክተውና የተቀረፀውን አዳምጠው አስተያየታቸውን በመስጠት የበለጠ ተጨባጭ የሆነ ውሳኔ (ድምዳሜ) ላይ እንዲደርሱ ይረዳቸዋል፡፡ የተለያዩ የመስኩ ባለሙያዎች Allwright (1980) ፣Mc-Donoughና Shaw (1993)፤ Gay et al (2009) በገለፁት መሠረት ቀረፃው ምልከታ ሊደረግባቸው የታሰቡትን ክፍሎች ሁሉ የሚያጠቃልል ሳይሆን የተለያዩ ምሁራን ሀሳብ በሰጡበትና የአይነታዊ ምርምር ስነ-ምግባር በሚያዘው መሰረት ፍቃድ በተገኘባቸው ክፍሎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ቀረፃው ፍቃድ ከተገኘባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በዓላማ-ተኮር ንሞና በተመረጡና ውስን በሆኑ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ላይ ተከናውኗል፡፡ በቀረፃው የተወሰዱት የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደቶችና ክንዋኔዎች ወደ ፅሁፍ ተለውጠው በገለፃ ተብራርተው በጥናት ወረቀቱ መጨረሻ በመረጃነት በአባሪነት ቀርበዋል፡፡

### 4.4.2. ቃለ-መጠይቅ

ቃለ-መጠይቅ አንድ ተመራማሪ መረጃ ከሚያገኝባቸው መሳሪያዎች ውስጥ ከባለ ጉዳዮቹ ጋራ በግንባር በመገኘት በቃል የሚደረግ ውይይት ነው፡፡ Flick (2006)ና Dornyei (2007) ሦስት የቃለ መጠይቅ ዓይነቶች ማለትም ውስን ቃለ-መጠይቅ (Structured interview)፣ ከፊል ነፃ ቃለ-መጠይቅ (Semi structured interview)ና ነፃ ቃለመጠይቅ (Unstructured interview) መኖራቸውን ይዘረዝራሉ፡፡ በዚህ ጥናት ለጠያቂውም ሆነ ለተጠያቂው በከፊል ነፃነት በመስጠት መረጃውን ለመሰብሰብ ስለሚያስችል የተመረጠው ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ በመረጃ ሰጪነት የተገለፁት አካላት መካከል በሮቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ስልጠና እየሰጡ ያሉ የአፋን ኦሮሞ መምህራን፣ በኮሌጁ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ክፍል ተጠሪ፣ የኮሌጁ ዋናና ምክትል ዲንና የተመረጡ የክፍል ሐላፊዎች፣ ከኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር የትምህርት ቢሮ ደግሞ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ኀላፊ፣ የአፋን ኦሮሞ ስርዓተ-ትምህርት ተጠሪና በቢሮው የመምህራን ልማት ተጠሪዎች፣ ከባሌ ዞን የዞኑና የወረዳዎች የመምህራን ልማት ኀላፊዎች፣የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራንና የአፋን ኦሮሞ መምህራን በዒላማ-ተኮር ንሞና ተመርጠው ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸዋል፡፡ ቃለ-መጠይቁም ሲካሄድ ሂደቱን በተገቢው መሰረት ለመረዳት እንዲቻል በቪዲዮና በመቅረፀ-ድምጽ ከተቀረፀ በኋላ በተገኙት መረጃዎች ላይ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ የቃለ-መጠይቁ ይዘቶች ወደ ፅሁፍ ተቀይረው በምርምር

ፅሁፉ መጨረሻ ላይ በአባሪ ሁለት፣ሶስት፣አራት፣ስድስት፣ዘጠኝ ፣አስር ላይ ለናሙና ቀርበዋል፡፡

### 4.4.3. የሰነድ ፍተሻ

በዓይነታዊ ምርምር ውስጥ ከሚጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ መዛግብት /ሰነዶች/ አንዱ ነው፡፡ Creswell (2009) እንዳሉት ከሰነድ የሚገኝ መረጃ በዳህራይ /Secondary/ መረጃነት ያገለግላል፡፡ በተጨማሪም ያለው (2000፣191)

> *በትምህርት ሚኒስቴር እየተዘጋጁ የሚወጡ ዓመታዊ ዘገባዎች፣ ስለአስተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ፣ አዲስ ስለተቀጠሩት መምህራን ቁጥር፣ …በየዓመቱ የሚሰራጩ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻህፍትና ሌሎች መጠናዊ መረጃ ይባላሉ፡፡*
>
> *ከዚህ ውጭ በዝርዝር ሀተታ የቀረቡ መዛግብት በዓይነታዊ መረጃ ምንጭነት ይመደባሉ፡፡* ብለዋል፡፡

ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሰረት ከስርዓተ-ትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ የተማሪው መጽሐፍ በሰነድነት ተወስዷል፡፡ በመሆኑም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን ስለማሳተፋቸው ተፈትሿል፡፡ በተጨማሪም በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመምህራን የተከታታይ ምዘና መሙያ ቅጽ በሰነድ ፍተሻው ስር ተካቷል፡፡ ይህም ለተማሪ-ተኮር ትግበራው መረጃ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በዚህ መሰረት ታትመው በተማሪዎች እጅ የሚገኘው የተማሪው አፋን ኦሮሞ መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የቀረቡ ተግባራት መምህራን በሌሉበት ተማሪዎቹ ራሳቸው መልመጃዎችን በመከወን ሀሳባቸውን እንዲያፈልቁ እንደሚያግዟቸውና እንደማያግዟቸው በመዳሰስ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ግምገማው በይዘቶቹ ተገቢነትና ተገቢ ያለመሆን ላይ የሚያተኩር ሳይሆን የመጽሐፉ ተግባራት ተማሪዎችን በትምህርቱ ሂደት ውስጥ አሳታፊ ስለማድረጋቸው፣ ትግበራው ከትምህርት ቤት ውጪ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር የሚያያዝ ስለመሆኑ፣ ተማሪዎች ያላቸውን እውቀት ለጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ የሚያደርጓቸው ስለመሆናቸው፣ የተማሪዎችን የውሳኔ ሀሳብ የሚጠይቁ ስለመሆናቸው፤ የነበራቸውን እውቀት ከአዲሱ ጋራ አነፃጽረው ሀሳብ እንዲሰጡ የሚጋብዟቸው ስለመሆናቸውና

በአጠቃላይ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ከተማሪዎች የሚጠበቀውን ባህሪያት የሚያስፈጽሙ መሆናቸውን በመዳሰስ ገለፃ ተሰጥቶበታል፡፡

## 4.4.4. ቡድን ተኮር ውይይት

ቡድን-ተኮር ውይይት ለዚህ አይነታዊ ምርምር አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የቡድን-ተኮር ውይይትን ምንነት በተመለከተ Dornyei (2007)፣ Flick (2009)፣ Natash Mack (2005)፣ Patton (2002) እና ያለው (2001) ቡድን ተኮር ውይይት ስሙ እንደሚያመለክተው ከጥቂት ሰዎች ጋር በተመሳሳይ ወይም በተወሰነ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ውይይት ሲሆን በውይይቱም ከ6-12 የሚሆኑ ሰዎች ሊሳተፉ እንደሚችሉና ከግማሽ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት በሚፈጅ ጊዜ ሊከናወን እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከሌሎች  የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በአንፃራዊነት ሲታይ ጊዜንና ገንዘብን ቆጣቢ በመሆኑ ለተለያዩ ዓላማዎችና በተለያዩ መስኮች በጥቅም ላይ ሲውል ይታያል፡፡ ውይይቱ የሚካሄደው በችግሩ ዙሪያ በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን ወስዶ በማወያየት ሲሆን ተሳታፊዎች ለሚነሳው ጥያቄ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ያላቸውን ተሞክሮዎች የሚገልፁበት ሥርዓት ነው፡፡ Dornyei (2007) እንደገለፁት  የቡድን ተኮር ውይይት የራሱ የሆኑ ሁለት ባህሪያት አሉት፡፡ እነዚህ ሁለቱ ባህሪያት በአንድ ቡድን ውስጥ የሚታቀፉ ሰዎች ተመሳሳይ ወይም የተለያዩ ስለመሆናቸውና በቡድኑ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር ስለመወሰን የሚያወሱ ናቸው፡፡

በቡድን ተኮር ውይይት የአጥኚው ሚና ግድብ ነው፡፡ ልክ እንደ አንድ ከፊል ውስን መጠይቅ አቅራቢ ሰፊ ድርሻ የለውም፡፡ የውይይቱ መሪ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ከእርሱ የሚጠበቁ በርካታ ሚናዎች አሉ፡፡ እነኚህን ሚናዎች Flick (2009)፣ Dornyei (2007፣132)፤Natashaና et al (2005)ና ያለው (2001) በዝርዝር አቅርበዋቸዋል፡፡ አጥኚው በውይይቱ ሂደት ወቅት ለቡድኑ በየደረጃው ጥያቄዎችን ያቀርባል፤ ውይይቱ ከተነሳው ነጥብ ውጭ እንዳያፈነግጥ ያደርጋል፤ በውይይቱ የሚነሱ ሀሳቦችን በደንብ ያዳምጣል፤ ውይይቱ በጥሩ መንፈስ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ውይይቱን አንድ ወይም የተወሰኑ ተሳታፊዎች ብቻ እንዳይቆጣጠሩት ጥንቃቄ ያደርጋል፤ ገለልተኛ ተሳታፊዎች በውይይቱ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ያበረታታል፣ ይገፋፋል፤ሁሉም  የጥናቱ ተሳታፊዎች በሚነሱ ነጥቦች አማካይነት ስሜታቸው እንዳይጎዳ ያደርጋል፤ ተቃራኒ ሀሳቦች

ሲነሱ የሀሳብ መበላለጥ ሳይሆን የአመለካከት ልዩነት እንደሆነና ሁሉም ጠቃሚ ሀሳብ እንዳነሱ መግለጽና ግልፅ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ማብራራት ይጠበቅበታል፤ ሁሉንም በእኩል ዓይን የሚያይ እንጂ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያተኩር መሆን የለበትም፤ ተሳታፊዎቹ በውይይቱ የበለጠ ነፃነት እንዲሰማቸው ይጥራል፣ እንዲሁም በሁኔታዎች ሁሉ ግትር ያልሆነ፣ ዓላማውን ያልሳተ፣ የሰዎችን ስሜት ቶሎ መገንዘብ የሚችልና አሳማኝ ሊሆን ይገባዋል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ይህ ከላይ የተብራራው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በስራ ላይ ሲውል የቡድን ውይይት ባህሪያት ሁሉ ተተግብረዋል፡፡ ለዚህ ጥናት ከታላሚው መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ዕጩ መምህራንን፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ምልከታ ከተደረጉባቸው መማሪያ ክፍሎች የተመረጡ ተማሪዎችን፣ አፋን ኦሮሞ የሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አተገባበር፣ አሰለጣጠን፣ ችግሮችና ምዘና ዙሪያ በማወያየት የሚፈለገውን  መረጃ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

## 4.5. የመረጃ አስተማማኝነት

አንድ ምርምር በተለያዩ መንገዶች በመረጃ ከተደገፈ ውጤቱ አስተማማኝ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት በምልከታ፣ በመጠይቅ፣ በቡድን-ተኮር ውይይት፣ በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተደጋግፈው ተመሳሳይ  ውጤት ካስገኙ ተዓማኒነታቸው ይረጋገጣል፡፡ የዚህን ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ በመጠቀም የተገኘው መረጃ አስተማማኝነት ለማሳየትም ጥናት አቅራቢው አንድን ባህሪ በተለያየ ጊዜ በተለያየ መንገድ በመለካት ወይም በመፈተሽ ተመሳሳይ ውጤት ማግኘት ተችሏል፡፡ ያለው (2001)፣ Cohensና et al (2000)፣ Creswell (2009)፣ Lodicoና et al (2006) የመረጃ አስተማማኝነትን ሲገልፁ፣ አንድን ባህሪ ወይም ነገር በአንድ መለኪያ በመጠቀምና በተደጋጋሚ በመለካት የሚገኘው ውጤት ተመሣሣይ፣ ቋሚ፣ ወጥ ወይም የማይለወጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ይህም ሲባል አንድ ባህሪ ወይም ነገር በተመሳሳይ ሁኔታ በአንድ መለኪያ ሁለት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ቢለካ የሚገኘው የልኬት ውጤት ተመሳሳይ ከሆነ መለኪያው የሰጠው መረጃ አስተማማኝነት አለው ማለት ነው ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የጥናቱን

ውጤት ተዓማኒነት ለማጎልበት ከላይ የተብራሩትን መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እርስ በርስ በማመሳከር ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡

ሌላው የመረጃ አስተማማኝነትን ለመወሰን ሚጠቅመው የንጥል ጥናት ባህርይ ነው፡፡ የንጥል ጥናት ዓይነተኛ ባህርይ ስለሚያጠናው ነገር ማጠቃለያ መስጠት ሳይሆን የተጠኚውን ባህርይ በጥልቀት መመርመርና ማወቅ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ጥናት ውስጥም የተወሰኑ የመምህራን ቁጥርና ትምህርት ቤቶችን ይዞ በጥልቀት በመመርመር የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበራቸውን ለማሳየት ተችሏል፡፡

## 4.6.የመረጃ ትክክለኛነት

በዚህ አይነታዊ ምርምር የመረጃ ትክክልኛነት እንዲረጋገጥ በጥናት አቅራቢው ፍላጎትና ስሜት በመመራት ከመደምደሚያው መድረስ ሳይሆን በተመረጡ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ላይ ተመስርቶ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በሚያስገኙት ውጤቶች መሰረት ብቻ ተወስኗል፡፡ ያለው (2001)፣ Cohensና etal (2000)ና Creswell (2009) የመረጃ ትክክለኛነት ሲያረዱ ትክክለኛነት ማለት አንድ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የታቀደውን መረጃ በታሰበው መንገድ፣ በተቃና፣ በተሟላና በተገቢ ሁኔታ ለመሰብሰብ እንዳስቻለ የሚያመለክት መሆኑን አብራርተዋል፡፡ ይኸውም ተመራማሪው በራሱ ግለ-ሀሳባዊነት ሳይመራ፣ የተገኘውን መረጃ መሠረት አድርጎ ችግሩን በትክክል መፍታት የሚያስችል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ እንዲችል ያደርገዋል፡፡

የመረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አራት መንገዶችን መምረጥ ይቻላል፡፡ እንደ ያለው (2001) አገላለፅ ግልብ፣ ይዘት-ተኮር፣ መስፈርት-ተኮርና ትውረት-ተኮር የትክክለኝነት መለኪያ መንገዶች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ትክክለኛነት የተረጋገጡት በይዘት ተኮር ትክክለኝነት (Content Validity)ና ትውረት ተኮር ትክክለኛነት ነው፡፡ ምክንያቱም በመለኪያው ውስጥ ይበልጥ ትክክለኝነትን የሚያሳይ ስርዓታዊ ሂደትን ወይም ግልጽ አሰራርን የሚከተሉ በመሆናቸው ነው፡፡ ሂደቱ በመለኪያው ውስጥ የሚካተቱ ጥያቄዎች የሚለኩትን ባህሪ አጠቃላይ ይዘት ሊወክሉ የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ በተጨማሪም የመረጃዎቹን እውነተኛነት ለማረጋገጥ

በዓይነታዊ ምርምር ውስጥ በስራ ላይ የሚውለው የመስቀለኛ የማመሳከሪያ ዘዴ (Triangulation Method) በመሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ በስራ ላይ ውሏል።

## 4.7. የሙከራ ጥናት

የሙከራ ጥናት በአንድ ምርምር ውስጥ ዋናው ጥናት ከመካሄዱ በፊት ለዋናው ጥናት ግብዓት እንዲሆን የተዘጋጁትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የምንፈትንበት ሂደት ነው። ይህ ሲባል ከዋናው ጥናት ጋራ በማንኛውም ነገር አቻ የሆነ አውድ ማለት ነው። የሙከራ ጥናትን አስፈላጊነት አስመልክተው Yin (1994) ሲያብራሩ ጥናት አቅራቢው የመረጃ ስብሰባ ዕቅዱን ፍንትው አድርጎ ማሳየትና የምርምሩን የአሰራር ማዕቀፍ በዋናው ጥናት ላይ አጉልቶ ማመልከት እንዲችል እድል ይሰጠዋል። በመሆኑም የሙከራ ጥናት ተከናውኖ የምርምሩን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሲባል በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ በቡድን-ተኮር ውይይትና በሰነድ ፍተሻ ከተለያዩ መረጃ ሰጪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ተብራርተው ቀርበዋል። የሙከራ ጥናቱ ውጤትም በዋናው ጥናት ላይ ምን ምን ሊካተት እንደሚገባ አቅጣጫ አመላክቷል፤ግብዓቶችም ተገኝተዋል።

## 4.8.የሙከራ ጥናት ውጤት

ለዚህ ጥናት ግብዓት ማግኛ ተብሎ የተከናወነው ሙከራዊ ጥናት ተመራማሪው ያላያቸውን ጉዳዮች በአስተውሎት እንዲያይና ትኩረት የሚሹ ነጥቦችን በአግባቡ እንዲመረምራቸው በማመልከቱ በዋናው ጥናት ውስጥ ተሟልተው እንዲቀርቡ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት አስችሏል። በተጨማሪም በቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ ያልተካተቱ ነጥቦች ተካተው፣ የማያስፈልጉ ነጥቦች ደግሞ እንዲወገዱ ተደርገዋል። በአጠቃላይ የምርምሩን አካሄድ በመፈተሽ ትክክለኛና የጠራ የአሰራር መንገድ ተመርጦ በስራ ላይ እንዲውል አግዟል።

የሙከራ ጥናቱ በባሌ ዞን በወይብ ሸንተረርና ቱሉ ዲምቱ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከዋናው ጥናት ጋራ አቻ በሆነ ሁኔታ ተከናውኗል። በዚህ መሰረት ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ ከዞን እስከ ወረዳ የመምህራን ልማት ሀላፊዎችና የየትምህርት ቤቶቹ ርዕሳነ-መምህራን ድረስ ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸው መረጃዎች ተገኝተዋል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡባቸው መሳሪያዎች ያላቸው ደካማና ጠንካራ ጎኖች ተለይተው በዋናው ጥናት ውስጥ ምን ማሻሻያ

ሊደረግባቸው እንደሚገባና እንዴት ስራ ላይ ማዋል እንደሚቻል መልካም ግብዓቶች ተገኝተዋል፡፡

## 1. ምልከታ

ለክፍል ውስጥ መማር-ማስተማር ሂደት በተዘጋጁት የምልከታ መከታተያ ቅፆች ላይ የሰፈሩት ነጥቦች መምህራን በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የሚያከናውኑዋቸውን ተግባራት ለማመልከት የተዘጋጁ ነበሩ፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቹ ተግባራት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑ ባለመሆናቸው ከቅጹ ውስጥ ሊወገዱ እንደሚገቡ ትምህርት ተገኝቶበታል፡፡ ለምሳሌ በጥያቄ ቁጥር 2.4 ላይ የሰፈረው "የትምህርቱ መግቢያ የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ዳስሷል፡፡" የሚለው የተማሪዎቹን ፍላጎት ለመለካት አንዳች ልዩ መለኪያ ስለሚያፈልግና በጥያቄው ውስጥ ይህንን የሚለካ መስፈርት ባለመኖሩ ተወግዷል፡፡ በጥያቄ ቁጥር 3.6 ስር "ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ከተግባራቱ ጋር ተዋህደው ቀርበዋል" የሚለውም አንድም ትምህርት ቤት ቴክኖሎጂን የሚጠቀምበት አቅም ስለሌለው ለምልከታው ከቅጽ ላይ ተሰርዟል፡፡

ሌላው ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች ውስጥ በመጀመሪያው ቀን ክፍል ተገብቶ ተግባራዊ ከማድረግ ይልቅ ከተማሪዎች ጋራ በተለማመዱበት በሁለተኛው ምልከታ ጀምሮ በመቅረፀ ድምፅ በመታገዝ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚከናወኑ ሁነቶችን እንዳለ ወስዶ በትንተና ከድምዳሜ ላይ መድረሱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይኸው ተግባራዊ ሆኗል፡፡

በክፍል ውስጥ ምልከታ ተግባር ላይ ጥናት አቅራቢው ብቻ መሳተፉ በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ቀረፃ ላይ በሚገባ ትኩረት አድርጎ ሁኔታዎች ለመከታተል እንደሚያስቸግር ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህ በዋናው ጥናት ላይ ይህን ሁኔታ ለመቆጣጠር ሌላ ሰው በመቅረፀ-ድምጽ ቀረፃ እንዲያካሄድና አጥኚው በመስፈርቱ መሰረት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ስለታመነበት ይኸው ተከናውኗል፡፡

## 2. ቃለ-መጠይቅ

ለኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክፍል፣ ለመምህራን ልማት ሐላፊና የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን እንዲሁም በባሌ ዞን የሮቤ ወረዳ የመምህራን ልማት ኂላፊ

ቃለ-መጠይቅ በቪዲዮ ቀረፃ አለመታገዙ በጥናቱ ላይ እንደመረጃ ጉድለት እንዲታይ አድርጎታል፡፡ ስለዚህ በዋናው ጥናት መስተካከል እንደሚገባ ግንዛቤ ተገኝቷል፡፡ ሌላው ለተጠኝዎች የቀረቡት ቃለ-መጠይቆችም ተጠኝዎቹ ከሰጧቸው ምላሾች በመነሳት ሌሎች ጥያቄዎችን ማቅረብ እንደሚገባ ትምህርት ተገኝቶበታል፡

## 3. የፅሁፍመጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ የሞሉት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ በየግላቸው እንዲሞሉልኝ ተገልፆላቸው ነገር ግን የሚያተምሯቸው መምህራን ምን መሙላት እንዳለባቸው ከመጠቆማቸውም በላይ እርስ በርስ ተገለባብጠው መሙላታቸው ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በዋናው ጥናት ከጽሁፍ መጠይቅ ይልቅ በክፍል ምልከታና በቡድን ተኮር ውይይት የጥናቱ ዋና መረጃ መሰብሰቢያ ተደርጎ ስራ ላይ ማዋል እንደሚገባ ከውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡

## 4. ቡድን-ተኮር ውይይት

በአሊቢራ ትምህርት ቤት ከተደረጉት የመምህራን የቡድን ተኮር ውይይት መልካም ግብዓቶች ተገኝተዋል፡፡ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እንዴት እየተገበሩት እንደሚገኙና በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎ ከሚጠበቀው በላይ እንደሆነ ገለጸዋል፡፡ እንደዚሁም በአግባቡ ተግባራዊ የማያደርጉበትን ምክንያት በግልፅ አብራርተዋል፡፡ በመሆኑም ይህ የቡድን ተኮር ወይይት ጥልቅ መረጃ ሊያስገኝ ስለሚችል በዋናው ጥናት ጊዜም ተግባራዊ መደረግ እንዳለበትና ልጠቀምበት የሚገባ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መሆን እንዳለበት ትምህርት ተገኝቶበታል፡፡ በሙከራ ጥናቱ የቡድን -ተኮር ውይይት ለማካሄድ ሰፊ ዝግጅትና በውይይቱ መነሳት ስለሚገባቸው ነጥቦች ይዞ መቅረብ ተገቢ እንደሆነ ትምህርት ተገኝቶበታል፡፡

## 5. የሰነድ ፍተሻ

በዚህ ጥናት ውስጥ ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች የተሰጡ መመሪያዎች፣ የተፃፉ ዘገባዎችና የተማሪው የአፋን ኦሮሞ የመማሪያ መፃህፍት ተዳሰዋል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ እነዚህንና መሰል ሰነዶችን በአግባቡ መጠቀም እንዳለብኝና በማስተማር ዘዴ ላይ ብቻ ማተኮሩ የሚገኘውን መረጃ ቁንጽል ሊያደርገው እንደሚችል ትምህርት ተገኝቶበታል፡፡ እንደዚሁም ርዕሳነ-መምህራን፣ ም/ር/መምህራንና ሌሎች የትምህርት ሐላፊዎች፣ የመምህራን ሱፐር

ቫይዘሮች (ገምጋሚዎች) በመሆናቸው መምህራን እውነታውን በግልጽ ለመናገር ስለሚፈሩ እነዚህ አካላት ከመምህራን ጋር በሚደረግ የቡድን-ተኮር ውይይት ውስጥ መካተት እንደሌለባቸው አሳማኝ ትምህርት ተገኝቶበታል፡፡

## 4.9. የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ቅደም ተከተል

የዚህ ጥናት ዓላማ በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን ውስጥ በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተጠቅመው በክፍል ውስጥ እንዴት እያስተማሩ እንደሚገኙ ማወቅና ያላቸውን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የአተገባበር ሁኔታ መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በመጀመሪያ ከተማሪ-ተኮር አተገባበር ጋራ ተያያዥነት ያላቸውን ምርምሮች፣ ጥናታዊ ጽሁፎችና ጆርናሎችን በማሰባሰብ በቂ የሆነ መረጃ ለማግኘት ጥረት ተድርጓል፡፡ በመቀጠል ለጥናቱ አቅጣጫ ጠቋሚ የሆኑ ጥያቄዎችና ርዕስ ተመርጠ፡፡ በሶስተኛ ደረጃ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተዘጋጅተው ለሙከራ ጥናት ቀርበዋል፡፡ ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ የተመረጡትም የክፍል ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን-ተኮር ውይይት፣ የሰነድ ፍተሻ ናቸው ፡፡

የክፍል ምልከታው የተከናወነው በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የአፋን ኦሮሞ የመማሪያ ክፍልና በተመረጡት አራቱ ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ የክፍል ምልከታው በተዘጋጀው የማረጋገጫ ሰንጠረዥ (checklist) ላይ ተመስርቶ የተከናወነ ሲሆን ከኮሌጁ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ ክፍልና የአራቱ ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች ጥናቱ ያተኮረባቸው ናቸው፡፡ የክፍል ምልከታው ሰላሳ ክፍለ ጊዜ ፈጅቷል፡፡

በሁሉም የመማሪያ ክፍሎች የአፋን ኦሮሞ ትምህርት በሳምንት ሶስት ክፍለ ጊዜ ያሉት ሲሆን አንድ ክፍል ለሁለት ሳምንት የመታየት እድል አግኝቷል፡፡ ለአምስቱ ክፍሎች በጠቅላላው ለአንድ ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ ደቂቃዎች ምልከታ ተደርጓል፡፡ ምልከታው ሲከናወን የመጀመሪያዎቹ ቀናት ላይ ቀረፃ ሳይካሄድ ከተማሪዎች ጋር አብሮ በመቀመጥ የሚከናወኑ ተግባራትን በመከታተል እስከ ክፍለ ጊዜው ማብቂያ ቆይቶ መውጣት ነበር፡፡ በሁለተኛው፣ በአራተኛውና በስድስተኛው ክፍለ ጊዜ ግን ትክክለኛው የመምህራንና

ተማሪዎች ተራክቦ በመቅረፀ-ድምጽ ተቀርፆ መረጃው ሊሰበሰብ ተችሏል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በመጀመሪያው ቀን ምልከታ በጥናት አድራጊው በመማሪያ ክፍል ውስጥ መገኘት የተነሳ የመምህራንና ተማሪዎች የመማር-ማስተማር ተሳትፎ ወትሮ ከነበረው ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ስለሚችል የሚከሰቱ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ሲባል ነው፡፡

የምልከታው ተሳታፊ ጥናት አቅራቢውና ለቀረፃ የሰለጠነ ረዳት ምልከታ አድራጊ ጋራ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የመማሪያ ክፍል ምልከታ በኮሌጅ ውስጥ የሶስተኛ ዓመት መማሪያ አንድ ክፍል ብቻ በመሆኑ ያለ ምርጫ ሲወሰድ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ግን በዕጣ ናሙና ነው፡፡ ምልከታ ከተደረገባቸው ክፍሎች ስድስቱ ክፍለ ጊዜ የተከናወኑት ተግባራት ሁሉ በመቅረፀ- ድምፅ ተቀርፀው በአባሪው ክፍል ቀርበዋል፡፡

በጥናቱ ቃለ-መጠይቅ ተግባራዊ የሆነው ከምልከታ በፊትና ከምልከታ በኋላ ነው፡፡ ከምልከታ በፊት የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ የተለያዩ ክፍል ኃላፊዎችና የተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ-መምህራን እንዲሁም የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ተተኳሪ ኃላፊዎች በተማሪ-ተኮር አተገባበር ዙሪያ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ከሰላሳ እስከ አንድ ሰዓት ያህል ተግባራዊ ሆኗል ፡፡ ከምልከታ በኋላ ደግሞ አፋን ኦሮሞ መምህራንና የተመረጡ የወረዳና የዞን ትምህርት መምሪያ የመምህራን ልማት ኃላፊዎች ጋር ተደርጓል፡፡ ቃለ-መጠይቁ የተወሰኑት በመቅረፀ-ድምጽ ተቀርፀው ወደ ጽሁፍ ተቀይረው በአባሪ ክፍል ላይ ይገኛሉ፡፡

የቡድን ተኮር ውይይት ተግባራዊ የሆነው የክፍል ምልከታ ከተደረገባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የተመረጡ ሰልጣኞችና ተማሪዎች የመማር-ማስተማሩ እንዴት ሲከናወን እንደነበር ከምልከታው ውጤት ጋር ለማመሳከር ሲባል ነው፡፡ ውይይቱም በኮሌጅና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተከናወነ ሲሆን ሂደቱም በመቅረፀ-ድምፅና መቅረፀ-ምስል ተቀርፆ ወደ ጽሁፍ ተቀይሮ ለናሙና በአባሪ አምስትና ሰባት ላይ ይገኛል፡፡

የሰነድ ፍተሻ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በተማሪው እጅ የሚገኘው የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መፃህፍና በኮሌጁና በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለማስተግበር ታስቦ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የተላለፉ መመሪያዎችና ቅፆች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ የተማሪው

መጽሐፍ በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ ሞጁል እንዲሁም በኮሌጁ ውስጥ የፕራክቲከም መተግበሪያ መመሪያዎች በዚህ የሰነድ ፍተሻ ስር የተካተቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከክፍል ምልከታ በኋላ በመማር-ማስተማር ብልሃቶችና አጠቃላይ በመምህራን ላይ የታዩ ክፍተቶችን በጥልቀት ለማጤን ይህ መረጃ መሰብሰቢያ እንደ ማመሳከሪያነት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

የመረጃ ትንተናውን ቅደም ተከተል ስንመለከት ቅድሚያ በክፍል ውስጥ ምልከታ የታዩት መረጃዎች በጭብጥ በጭብጣቸው ከተተነተኑ በኋላ የቃለ-መጠይቅና የቡድን-ተኮር መረጃዎች በጭብጦቹ ስር ቀርበዋል፡፡ በመቀጠል በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው በጭብጡ ስር ቀርበዋል ፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙት መረጃዎች በምዕራፍ አንድ ላይ የተገለፁትን የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ በጥያቄዎቹ ስር ሊነሱ የሚገባቸው አንኳር ነጥቦች ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡

ይህ ጥናት ሲከናወን መረጃ የተሰበሰበበት ቋንቋ አፋን ኦሮሞ ሲሆን ወደ አማርኛ ተቀይሮ አሁን የያዘውን ቅርጽ እንዲይዝ ያደረገው የጥናቱ አቅራቢ ነው፡፡

## 4.10. ስነምግባራዊ ሁኔታዎች

ማንኛውም ተመራማሪ ጥናት ለማድረግ ሲነሳ ግምት ውስጥ ሊያስገባው ከሚገባው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የፍቃድና ስነ-ምግባራዊ ሁኔታዎችን ተግባሪዊ ማድረግ መቻል ነው፡፡ ይህ ማለት እንደ Cohen et al (2005)ና Mack et al (2005) አገላለጽ ጥናት አድራጊው ምርምር ለማድረግ ሲነሳ በሚያጠናው ጉዳይ ላይ ፍቃድ ማግኘትና ለመረጃ ሰጪዎች አክብሮት መስጠት እንዳለበት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ከሰነድና ከግለሰቦች የተገኙ ምስጢሮች መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ተመራማሪው በአንድ ድርጅት ወይም ተቋማት ውስጥ ምርምር ለማድረግ ሲነሳ መወጣት ከሚገባቸው ኋላፊነቶች ውስጥ የምርምሩን ሙያ አውቆ ከበጀት መዳቢ አካላትም ይሁን ከሌሎች ጋር ተባባሪ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ከተደረጉት ስነ ምግባራዊ ሁኔታዎች ውስጥ ቅድሚያ ርእሱ እንደፀደቀ መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለመሄድ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የትብብር ደብዳቤ በማፃፍ ተጀመረ፡፡ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮም በባሌ ዞን ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች "ለሚመለከተው ሁሉ " በሚል ርዕስ ትብብር እንዲያደርጉልኝ ተፃፈልኝ፡፡ ከዚያም ምንም እንኳን የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮም ለትምህርት ቤቶች ቢጽፍም የባሌ ዞን ትምህርት መምሪያም ለተመረጡት የወረዳ ትምህርት ቤቶችና ትምህርት ቤቶች ደብዳቤ ጽፈውልኝ ጥናቱ ተከናውኗል፡፡

የተጠኚዎችን ማንነት በመረጃ ትንተናው ላይ ላለመጥቀስ እውነተኛ ያልሆኑ ስሞችን በመጠቀም ለማመልከት ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያለፍላጎታቸውና ከስምምነታቸው ውጪ መረጃ ለመውስድ የማያስፈልግ መሆኑን አምነውበት በራሳቸው ስምምነት ብቻ ለመረጃ መስጠት ትብብር እንዲያደርጉ ስምምነት ላይ በመደረሱ በዚሁ መሰረት ተከናውኗል፡፡

## ምዕራፍ አምስት፡-የመረጃ ትንተና፣ ግኝትና ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለጥናቱ በተመረጡ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው በተገኙት ውጤቶች ዙሪያ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ ወደ ትንተናው ከማምራታችን በፊት የመረጃ ሰጪዎች ማንነትና ዳራቸው ይቀርባል፡፡ በማስከተል መረጃውን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ በዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በቡድን-ተኮር ውይይት፣ በቃለ-መጠይቅ፣ በሰነድ ፍተሻ የተገኙ ምላሾች በዓይነታዊ ምርምር ባህሪያት መሰረት ይተነተናሉ፡፡

ለዚህም በሮቤ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ዕጩ ሰልጣኝ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ ያገኙት የስልጠና ግብዓት ምን እንደሚመስል፣ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ሲሰጥ በክፍል ውስጥ ሲከናወኑ የነበሩት የመማር-ማስተማር ተግባራትና የአሰልጣኞች ትምህርት አቀራረብ እንዲሁም የሰልጣኝ ዕጩ መምህራን በመማር-ማስተማር ሂደቱ ውስጥ ያላቸው ሚና ተፈትሸው አንዳች ድምዳሜ ያገኛሉ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የመማሪያ ክፍል አደረጃጀት፣ መምህራንና ሰልጣኞች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ያላቸው ሚና፤ እንዲሁም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበርና ተያያዥ ጉዳዮች በኮሌጁ ዋናና ምክትል ዲኖች፣ የመምህርነት ሙያ አሰልጣኝ፣ የተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ አስተባባሪ አተያይ እንዲሁም የመምህርነትን ሙያ የሚያጎናጽፈው የፕራክቲከም ኮርስ ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ሂደት ለማስቃኘት ይሞከራል፡፡ ከዚህም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ፍንጭ ለማግኘት ይቻላል፡፡

በማስከተል ከቅድመ ስራ ስልጠና በኋላ በባሌ ዞን አንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ምን እንደሚመስል፣ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራሮች ለመምህራኑ ሲሰጡ የነበረውን የስራ ላይ ስልጠናና ሌሎች እገዛዎች ይፈተሻሉ፡፡ በመጨረሻም መምህራን አፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸው የማስተማር ብልሃቶችና በዚህ ሂደት ውስጥ ያጋጠማቸው ተግዳሮቶች ይተነተናሉ፡፡ በአጭሩ በምዕራፍ አንድ ውስጥ የተነሱ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ያገኛሉ፡፡

## 5.1.የጥናቱ ተሳታፊዎች መገኛ፣ብዛት፣ዳራና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

በዚህ ርዕስ ስር በተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተዓማኒነት እንዲኖራቸው ከጥናቱ ተሳታፊዎች ማንነት ጋራ መቅረባቸው አግባብነት አለው፡፡ በመሆኑም በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ውስጥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ-ሦስት፡- መረጃ የተሰበሰበባቸው ተቋማት፣ የተቋሚቱ ክፍሎች፤ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያና የጥናቱ ተሳታፊዎችና ብዛታቸው፡፡**

| ተቁ | የመምህራን ማ/ኮ/ የትምህር ቤቱ ስም | ወረዳ | ምልከታ የተደረገባቸው ክፍሎች | መረጃ መሰብሰቢያው መሳሪያ | የጥናቱ ተሳታፊዎች | ጠቅላላ የተሳታፊዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሮቤ መ/ም/ ት/ኮሌጅ | ሮቤ | 3ኛ ዓመት | -የክፍል ምልከታ፣ -ቃለመጠይቅ፣ ቡድን-ተኮር ውይይት፣ -ሰነድ ፍተሻ ለምሳሌ፡- .የማስተማሪያ ሞጁል .የተከታታይ ምዘና መመዝገቢያ ቅጽ የፕራክቲከም መከታተያ ሞጁል | የአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህራን የኮሌጁ ዲኖች ለመምህርነት ሙያ አሰልጣኝ መምህር፣ ለተሙማ አስተባባሪ ለ3ኛ ዓመት ሰልጣኞች | 22 |
| 2 | አሊቢራ አ/ደ/ት/ቤት | ሮቤ | 7ኛ ክፍል | የቡድንተኮር ውይይት፣ ምልከታ፣ ቃለ- መጠይቅ፣ | ተማሪዎችና የአፋን ኦሮሞ መምህር | 11 |
| 3 | ዘይበላ አ/ደ/ት/ቤት | ሮቤ | 7ኛ ክፍል | ቃለ-መጠይቅ የክፍል ምልከታ የቡድን-ተኮር ውይይት | .ርዕሰ -መምህር . መምህር .ተማሪዎች | 11 |
| 4 | ኪጽጠቴ አ/ደ/ት/ቤት | ሮቤ | 7ኛ ክፍል | የክፍል ምልከታ፣ ቡድን-ተኮር ውይይት ቃለ-መጠይቅ | ርዕሰ -መምህር የአፋን ኦሮሞ መምህር ተማሪዎች | 12 |
| 5 | ሀውሾ አ/ደ/ት/ቤት | ሲናና | 7ኛ ክፍል | የክፍል ምልከታ የቡድን-ተኮር ውይይት ቃለ-መጠይቅ | ርዕሰ -መምህር የአፋን ኦሮሞ መምህር ተማሪዎች | 11 |
| 6 | የዞን ትምህርት ቢሮ | ሮቤ | - | ቃለ-መጠይቅ | ለመምህራን ልማት ተጠሪ | 1 |
| 7 | የወረዳ ትምህርት ቢሮ | ሮቤ፣ ሲናና አጋርፋ ወረዳዎች | - | ቃለ-መጠይቅ | ለመምህራን ልማት ኂላፊዎች | 3 |
| 8 | ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ | አ.አ | - | ቃለ-መጠይቅ | ስርዓተ ትምህርት ዝ/ተጠሪ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን ባለሙያ ለመምህራን ልማት ተጠሪ | 3 |
| | | | | | ጠቅላላ | 74 |

ከሰንጠረዡ የምንረዳው በዚህ ጥናት ውስጥ ለመረጃ ሰጪነት የተመረጡት በኮሌጅ ውስጥ ስልጠና እየሰጡ ያሉ ሁለት የአፋን ኦሮሞ መምህራን፣ ሁለት ቡድን ዕጩ መምህራን ማለትም የፕራክቲከም ዘገባ አቅራቢዎችና በአፋን ኦሮሞ የመማር-ማስተማር ሂደት ዙሪያ የቡድን-ተኮር ተወያዮች፣ የኮሌጅ ዋናና የአካዳሚክ ምክትል ዲን፣ የመምህርነት ሙያ አሰልጣኝ መምህርና የተሙማ አስተባባሪ፣ ሲሆኑ ሁለቱ የዕጩ መምህራን ቡድን ተወያዮች ጨምሮ በጠቅላላው 22 አባላት ከመም/ት/ኮሌጅ ተመርጠዋል፡፡

ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ መምህራን፣ተማሪዎች፤ የትምህርት ቤት ርዕሳነ-መምህራን፣ ሲሆኑ ከኪጽጠቴ፣12፤ ከዜይበላ፣11፤ ከአሊቢራ፣11፤ከሐውሾ11 በጠቅላላው 45 ተሳታፊዎች ተመርጠዋል ፡፡ በተጨማሪም የሶስት ወረዳና አንድ የዞን የመምህራን ልማት ተጠሪዎች 4 ተሳታፊዎችና ከኦሮሚያ ትምርት ቢሮ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክፍል ሃላፊ፣ የቢሮው የመምህራን ልማት ተጠሪና የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን ተጠሪ መረጃ ሰጪዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ 74 የጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ ከነዚህ 33 ሴቶች 41 ወንዶች ናቸው፡፡

በትምህርት ደረጃ ረገድ ሁለተኛ ዲግሪ 7፣ድግሪ9፣ዲፕሎማ 4፣ የኮሌጅ ሶስተኛ ዓመት ተማሪዎች 16፣ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች 38 ናቸው፡፡ የሁለተኛ ዲግሪዎቹ ከመምህራን ኮሌጅ ስድስት ተሳታፊዎች ሲሆኑ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አንድሰው ናቸው፡፡ የወረዳና የዞን መምህራን ልማት ተጠሪዎች እንዲሁም ሶስት የትምህርት ቤቶች ርዕሳነ-መምህራን የመጀመሪያ ድግሪ ያላቸው ናቸው፡፡ አራቱ የአፋን ኦሮሞ መምህራን ዲፕሎማቸውን ይዘው ቀጣይ ትምህርት እየተማሩ የሚገኙ ናቸው፡፡

## 5.2. የዕጩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የቅድመ ስራ የስልጠና ግብዓት

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራንን የክፍል ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን ከማየታችን በፊት በጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ውስጥ የቀረበው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የቅድመ ስራ ላይ የስልጠና ግብዓት ምን እንደሚመስል በናሙና በተመረጠው የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ ከተለያዩ አካላት

መረጃዎች ተሰብስበው ቀርበዋል። በምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ ቀጥሎ በቀረበው መንገድ እንመለከታለን።

### 5.2.1. የኮሌጁ የክፍል ውስጥ አደረጃጀት

የክፍል ውስጥ አደረጃጀት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የራሱ የሆኑ ተጽእኖ ሊያደርስ ይችላል። በተለይም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተግባራዊ ሲሆን የሚችለውም ተማሪዎች ዘና ብለው ሲማሩና መምህራንም ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚችሉት ትምህርቱ የሚሰጥበት አውድ አመቺ ሲሆን ነው። አንድ የመማሪያ ክፍል በቂ መብራትና ንጹህ አየር የሚያስገባ ከሆነ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ችግር ሳይከሰት በፍጥነት ትምህርቱ ከተፈለገው ግብ ይደርሳል (Mc-combsና Whisler 1996፤ Moore፣ 2001)። ከዚህ አንፃር ከላይ በተጠቀሰው የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ በምልከታ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤

ስልጠና የሚካሄድባቸው የመማሪያ ክፍሎች ጽዱና ሳቢ ናቸው። በየመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙት ወንበሮች ቀላልና በተፈለገው ጊዜ በተለያዩ አቅጣጫዎች ለማስቀመጥና ለመደርደር የሚያስችሉ ናቸው። ሰልጠኞቹ በክብ፣ በ"ሀ" ቅርጽ፣ በቀጥታ መስመር፣ በተርታ፣ በጥንድና በቡድን፣ ተቀምጠው በውይይት ሲሰሩ መምህራን እንደፈለጉት በቡድኑ መካከል ለመዘዋወር ያስችላቸዋል። ይህ ሁኔታ ደግሞ መምህራን ትምህርቱን ሲያቀርቡ በተለያዩ ብልሃቶች ለመተግበር ምቹ ይሆናል። ይህም ማለት ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አንፃር የመማሪያ ክፍሎቹ ምቹ ናቸው ማለት ይቻላል። የመማሪያ ክፍሉን ወለል፣ ኮርኒስ፣ የመስኮቶቹ ስፋት፣ የጥቁር ሰሌዳው ጥራት፤ ሰልጣኞች በማንኛው የአየር ሁኔታ ውስጥ ሳይጨናነቁ በሚገባ ለመማር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል (ሮ/መ/ት/ኮ፣ በ8/02/06 ዓ.ም፣ 3፡20-4፡10 ሰዓት)።

የመማሪያ አካባቢ ለትምህርት አሰጣጥና ተማሪዎችን አነሳስተው በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው በመስኩ ጥናት ያደረጉት ምሁራን ይመክራሉ። ከዚህ አንፃር በታላሚው የመምህራን ማስልጠኛ ኮሌጅ ክፍሎች ውስጥ ለተማሪዎች ሁሉ በቂ ክፍተት ያለው፣ መቀመጫዎቹ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ በመሆናቸው መምህራን በቡድን ውስጥ እየተዘዋወሩ እገዛ ለማድረግ የሚያመቻቸው

ይመስላል፡፡ በክፍሉ ውስጥ ወንዶች 19 ሴቶች ደግሞ 28 በጠቅላላው 47 ተማሪዎች ያሉበት በመሆኑ የተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ጋራ የተመጣጠነ ነው፡፡ ይህም በተማሪ-ተኮር አፋን ኦሮሞን ለማስተማር ለሚሰጠው ሁኔታው አመቺ እንደሆነ ያመለክተናል፡፡

የክፍል ውስጥ አደረጃጀት ሁኔታ በተመለከተ ምን እንደሚመስል ለአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህር ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣

> *በሮቤ መ/ም/ማ/ኮሌጅ ውስጥ መማር-ማስተማር ለማካሄድ ምቹ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ከክፍል ውስጥ መቀመጫዎችና የመማሪያ ክፍል ሁኔታው ተማሪዎችን የሚስቡ ናቸው፡፡ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ መምህራን በተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች ተጠቅመው ለማስተማር የሚገድቧቸው ነገሮች አይስተዋሉም፣የተማሪ-ተኮር አቀራረብንም ለመተግበር ሁኔታዎች የተሟሉ ናቸው (ኡምሳ ቃበቶ፣/17/07/04፣* ከ5፡00-5፡30 ሰዓት) ፡፡

በማለት በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ ያለውን የክፍል አደረጃጀት መልካምነት ገልጸዋል፡፡

በአጭሩ በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ውስጥ የመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚተገበርበት የመማሪያ ክፍል ሁኔታ አመቺ መሆኑ በምልከታ የታየው በአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህሩም ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጧል፡፡


### 5.2.2. የመማር-ማስተማር አተገባበር

በምልከታ በታየው የሮቤ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት የሚሰጥበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩት አሰልጣኝ መምህር ትምህርቱን ሲያቀርቡ ከትምህርቱ መግቢያ እስከ ማጠቃለያ ድረስ በምልከታ ለመቃኘት ተችሏል፡፡ በምልከታውም የመማር-ማስተማሩ ሂደት ሲከናወን መምህራንና ተማሪዎች የራሳቸውን ሚና መወጣታቸውንና የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተቀመጠለት መርህ መሰረት መተግበሩን ማመልከት ይቻላል፡፡

በምልከታ አንድ፡-በ8/02/06 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡20 ሲሆን የአፋን ኦሮሞ መምህሩ ለዕጩ ሰልጣኞቻቸው ሠላምታ ከሰጡ በኋላ የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ "የማዳመጥ ሂደት" የሚለውን ፃፉ፡፡ በማስከተል ተማሪዎች የአፋን ኦሮሞ መማሪያ

ሞጁላቸውን ገጽ7  እንዲያወጡ አዘዙና የማዳመጥ ሂደትን የሚያመላክት ስዕል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሳሉ፡፡

**ስዕል ሶስት፡- በኮሌጁ ክፍል ውስጥ በምልከታ የታየው የትምህርት ይዘት ፤**




በስዕሉ ላይ በተመለከተው መሠረት የማዳመጥ ሂደት ከላይ ወደታችና ከታች ወደ ላይ የሚጓዝ መሆኑን ካመለከቱ በኋላ ከላይ ወደታችና ከታች ወደ ላይ የማዳመጥ ሂደቶች (Dhaggeeffachuu "Olii-gadee"ና "Dhaggeeffachuu asii olii") ያላቸውን ልዩነቶች ተወያይተው እንዲናገሩ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ በምልከታው መሠረት በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ሰባት ቡድኖች በአንዱ ቡድን ውስጥ ካሉት ሰባት አባላት ጋራ ለአስር ደቂቃ በሞቀ ውይይት ሲራከቡ  መምህሩም  በተማሪዎቻቸው መካከል እየተዘዋወሩ እገዛ ሲያደርጉ ተስተውለዋል፡፡ መምህሩ በተማሪዎቹ ቡድን መካከል ተሳታፊ ሆነው ሀሳብ በመስጠት፣ በግል ለተጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠትና ማበረታቻ ሲሰጡ ተስተውለዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከቆዩ በኋላ ለውይይት የተመደበላቸውን ደቂቃዎች መጠናቀቁን ገልፀው ሁሉም ተማሪዎች በቡድናቸው ውስጥ የተወያዩትን የትምህርት ይዘት ጭብጥ ለመምህራቸው እጅ እያወጡ እንዲናገሩ አዘዙ፡፡ በትዕዛዛቸው መሰረት ከየቡድናቸው እጅ እያወጡ ሀሳብ መስጠት ተጀመረ፡፡ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በሚያቀርቡበት ሰዓት መምህራቸው በበኩላቸው ዋና ዋና ነጥቦችን በመምረጥ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስታወሻ ይጽፉ ነበር፡፡በዚሁ መሰረት ሁሉም ተማሪዎች ከየቡድናቸው ሀሳባቸውን እያቀረቡ በዕለቱ የተመደበላቸው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በመጠናቀቁ በሚቀጥለው ቀን ከዚሁ እንደሚቀጥሉ አሳስበው በዕለቱ ትምህርት ላይ ግልፅ ያልሆነ ነገር ካለም በቀጣይ ክፍለ-ጊዜ እንደሚመለስ ተናግረው በ4፡10 ሲሆን ትምህርቱን አበቁ (ሮ/መ/ም/ት/ኮ፣በ8/02/06 ዓ.ም፣3፡20-4፡10 ሰዓት)፡፡

በዕለቱ የመማር-ማስተማሩን አውድ ስንመለከት ዕጩ መምህራን በንቃት ሲሳተፉ ለማስተዋል ተችሏል፡፡ በአርባ ደቂቃዎች ውስጥ ወደ አስራ አምስት ደቂቃ አካባቢ መምህራቸው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በመናገራቸው ተማሪዎቻቸው ከተናገሩት ጊዜ አንሶ ታይቷል ፡፡ መምህሩ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አንድ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተግባሪ የሚያከናውናቸውን መርሆዎች ተከትለው በስራ ላይ ሲያውሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በተማሪዎች የሞቀ ተሳትፎ ምክንያት ሊደረግ የታቀደው የእለቱ ትምህርት ግምገማ ሳይተገበር መቅረቱና ሰልጣኞች እየተናገሩ እያሉ በጥቁር ሰሌዳ ላይ መምህሩ ሲጽፉ ለተናጋሪዎች ንግግር ትኩረት ሳይሰጥ የተመደበው የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ሊጠናቀቅ ችሏል፡፡ይህም ምንም እንኳን የተመቻቸ መማሪያ ክፍልና የማሰልጠኛ ሞጁል ቢኖሩም የጊዜ አጠቃቀም ላይ ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

ምልከታ ሁለት፡- በዕለቱ መምህሩ ያለፈውን የትምህርት ርዕስ በእሳቸው ጠያቂነት በዕጩ ሰልጣኞች አስታዋሽነት ጀመሩ፡፡ ለምሳሌ "እስቲ በባለፈው ክፍለ-ጊዜ የተማርነው ስለምን ነበር?" በማለት ጠይቀው ብዙ ተማሪዎች ምላሽ ለመስጠት እጅ አወጡ፡፡...ቅድሚያ ሴቷ "ባለፈው ስለማዳመጥ ሂደት ነው የተማር ነው፡፡ የማዳመጥ ሂደት ሲባል በሁለት እንደሚከፈል..."በማለት ስትናገር በመምህሩ ጣልቃ ገብተው "ይበቃል ይበቃል" በማለት ለሁለተኛው ወንድ ተማሪ እድል ሰጡ፡፡ ተማሪውም " ቀደም ብላ... እንደተናገረችው ባለፈው የተማርነው የማዳመጥ ሂደት የሚል ሲሆን በዚህ ስር ሁለት ሀሳቦች አንስተን፣ በቡድን ተወያይተንበትና የተወያየንበትን ነጥቦች ተናጋግረን ነው ያበቃነው፡፡" ብሎ እንደጨረሰ መምህሩም "ትክክል ነው?" ብሎ ለሙሉ ክፍል ጥያቄ አቅርበው "አዎ" የሚል ምላሽ ካገኙ በኋላ በራሳቸውም ዋና ዋና ነጥቦችን በማንሳት አስታውሰዋል፡፡

በመቀጠልም "የዕለቱን ትምህርት በመማሪያ ሞጁላችሁ (ከገጽ፣9-13) ላይ የሚገኘውን ምንባብ በሚገባ ካነበባችሁ በኋላ ከዚያ ቀጥለው የቀረቡትን ተግባራት ተወያይታችሁ እንድትሰሩ በማለት" አሳስበው "እንደተለመደው ስራውን የምንሰራው በቡድን ስለሆነ እንደ አቀማመጣችሁ ሰባት ሰባት ሆናችሁ ተደራጁ "ብለው አዘዙ፡፡ ተማሪዎችም በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ስለማዳመጥ ሂደት በተለያዩ ምሁራን የተነገሩትን አስተያየቶች ለይተው በማንበብ በእያንዳንዱ ሀሳብ መካከል የሚገኙ ልዩነቶችን ተረድተው የደረሱባቸውን ጭብጦች እንዲያቀርቡ በታዘዙት መሰረት ለአስራ አምስት ደቂቃዎች የሞቀ ውይይት አከናውነው ከየቡድኑ ያገኟቸውን ቁምነገሮች ተራ በተራ እየተነሱ እንዲናገሩ ተደረገ፡፡

በዚሁ መሰረት ስለ ስነ-ልቡናዊ ስነ-ልሳን አመለካከት፣ ስለ ባህሮታዊያን፣ ስነ-ልቦናውያን፣ ስለ ጌስታልቶችና አይምሮታውያን አመለካከት ያነበቧቸውንና የደረሱባቸውን ሀሳቦች በቡድን ተወካዮቻቸው አማካኝነት ገለፁ፡፡ መምህራቸውም የራሳቸውን ሀሳብ በተጨማሪ አክለውበት የዕለቱ የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ሊጠናቀቅ በተቃረበበት ሰዓት የግምገማ ጥያቄዎችን አቅርበው ተማሪዎቹም እጅ በማውጣት ምላሽ ሰጥተውበት በሚቀጥለው ትምህርት ቀን እንደሚገናኙ በማሳሰብ ለእለቱ የተመደበው ክፍለ-ጊዜ ተጠናቀቀ (ሮ/መ/ም/ት/ኮ፣ በ10/02/06 ዓ.ም፣ ከ3፡20- 4፡10 ሰዓት)፡፡

በምልከታ ሁለት እንደታየው መምህሩ የአፋን ኦሮሞ የመማር-ማስተማር ሂደት አቀራረቡን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርህ መሰረት እየተገበሩት ነበሩ፡፡ ምክንያቱም ሰልጣኞች በቡድን ተደራጅተው በተሰጣቸው ተግባራት ላይ እየተወያዩ ሲማማሩ በነበረበት ወቅት መምህሩ በተወያዮቹ መካከል እየተዟዟሩ ይረዷቸው ነበር፡፡ ተማሪዎችም በቡድን የተወያዩበትን በተወካዮቻቸው አማካኝነት ዘገባ ሲያቀርቡ፣ ጥያቄዎችን ሲመልሱና በመማር-ማስተማሩ ሂደት ሲሳተፉ መታየታቸው ተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተግባር ማሳየታቸውን ያመለክታል፡፡

የአፋን ኦሮሞ መምህሩ የማስተማር ብልሃት ምርጫ የተመሰረተው በተዘጋጁት የአፋን ኦሮሞ የማስተማሪያ ሞጁሎች ላይ ነው፡፡ በሞጁሎቹ ላይ የቀረቡት መልመጃዎችና ትዕዛዛት መምህሩ በምን ዓይነት የማስተማር ብልሃት ትምህርቱን ማቅረብ እንደሚገባቸውና የተማሪዎች ድርሻ ምን እንደሆነ ፍንጭ ሰጪዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በዕለቱ የቀረቡት መልመጃዎች ተማሪዎች ተወያይተውበት የደረሱበትን ጭብጥ ለክፍላቸው ሪፖርት እንዲያደርጉ የሚል በመሆኑ የዕለቱም ትምህርት በዚያው መንገድ ተከናውኗል፡፡

በሮቤ የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራን በትምህርት ክፍላቸው ስር የሚያሰለጥኗቸውን ዕጩ መምህራን እንዴት እያሰለጠኑ እንደሚገኙ መረጃ ይኖራቸዋል፡፡ የመምህራኑ የመማር-ማስተማሩ ሂደት እንዴት እንደሚተገበር በክፍል ምልከታ ከታየው ውጪ አፋን ኦሮሞ ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በቅድሚያ ለቋንቋ ስትሪም ኀላፊና ለአፋን ኦሮሞ መምህር (አሰልጣኝ) ዕጩ መምህራንን እንዴት እንደሚያሰለጥኗቸውና ክህሎቱን ከየት እንዳገኙ ላቀርብኩላቸው ጥያቄ የሰጡኝ ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

*የመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪን ያማከለ (ተማሪ-ተኮር ) ሲሆን በንቃት ላይ የተመሰረተ የመማር-ማስተማር ሁኔታ ነው፡፡ ስለዚህ የኛ መምህራን በተለይም የከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP) የሚል መርሀ-ግብር በመኖሩ ከዚያ በምናገኘው እውቀት ወደ ስራ እንቀይረዋለን ማለት ነው (ቱምሳ ቃበቶ፣ /17/07/04፣ ከ5፡00-5፡30 ሰዓት) ፡፡*

በኮሌጁ የአፋን ኦሮሞ መምህር አገላለፅ በግቢው ለመሰልጠን  የሚገቡ ዕጩ መምህራንን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እያሰለጠኑ መሆናቸው ነው፡፡ አሰልጣኝ መምህራኑ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር አቅማቸውን ያጎለበቱት በኮሌጁ ውስጥ በሚሰጠው የከፍተኛ ዲፕሎማ መርሀ-ግብር በተገኘው ስልጠና ነው፡፡

በመቀጠል ለዚሁ የአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህር በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙባቸውን የማስተማር ብልሃቶች ምን እንደሚመስሉ ተጠይቀው ሲመልሱ፣

*… በዚህ በኩል የምንጠቀመው ብልሃቶቻችን “Modular Approach” ነው፡፡ ከዚህ ውጪም የተለያዩ ተግባራት ተሰጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ቤተ-መፃህፍት ይገባሉ፣ የተለያዩ ቦታ ሄደው የተሰጣቸውን መረጃ ሰብስበው ዘገባ ያቀርባሉ፣ በሞጁሉ ላይ ደግሞ ትኩረት ስናደርግ የቀረቡትን ስራዎች የሚያጠናክሩ መልመጃዎች እንሰጣቸዋለን፡፡ በሞጁሉ ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነዚያ በሞጁሎቹ ውስጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተመስርተን ካስተማርን በኋላ ያንን ስራ የሚያጠናክሩ ፕሮጀክቶች እንሰጣቸዋለን፡፡ ወይም አንድ ርዕስ አዘጋጅተን በዚያ ርዕስ ላይ ተመስርተው ከሰሩ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻቸው ሪፖርት እንዲያቀርቡ እናደርጋለን (ቱምሣ ቃበቶ፣17/07/04 ከ4፡00-5፡00 )፡፡*

በኮሌጁ የአፋን ኦሮሞ መምህር አገላለጽ በመምህራን ኮሌጁ ውስጥ አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ተዘጋጅተው በቀረቡ የማስተማሪያ ሞጁሎች ላይ ባለው አካሄድ ነው የተመሰርተው፡፡ በማስተማሪያ ሞጁሎች ውስጥ የተለያዩ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መልመጃዎች በተለያዩ ብልሃቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተብለው የቀረቡ በመሆናቸው ሰልጣኞቹ አንብበው በቀረበላቸው ትዕዛዝ መሰረት ሲሰሩ ይታያሉ ወይም መምህራኑ ተግባራቱን እንዲሰሩ ያደርጓቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በምልከታም ወቅት የመምህሩ የማስተማር አቀራረብና የተማሪዎች ክንዋኔዎች በመማሪያ ሞጁላቸው ላይ ተዘጋጅተው የቀረቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንደ Derebssa (1998) አገላለጽ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መምህራን የሚጠቀሙበት የማስተማር ዘዴዎችና ብልሃቶች ሊወሰኑ የሚችሉት በትምህርቱ ዓላማ፣ ይዘትና በተማሪዎች ዳራ ነው:: በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ውስጥ አሰልጣኝ መምህሩ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች በተዘጋጁ የማስተማሪያ ሞጁሎች ላይ መመስረታቸው አግባብ ቢሆንም ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ አንፃር መምህራንም የራሳቸው ፈጠራ ታክሎበት ተማሪዎችም  አዳዲስ ነገሮችን ሊፈጥሩ የሚችሉባቸውን ብልሃቶች ሊመርጡ ይገባል፡፡ ከመምህራኑ ፈጠራም ሰልጠኞቻቸውም በተራቸው ነገሮችን ወደ መፍጠር እንዲያዘነብሉ ያደርጋቸዋል፡፡

ሰልጣኞች አፋን ኦሮሞን ሲማሩ የቡድን ስራቸውን የሚያቀርቡበትን ብልሃት በተመለከተ ከላይ የአፋን ኦሮሞ መምህሩ ተጠይቀው የሚከተለውን ብለዋል፤

> *ይህን ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት የቡድን አደራጅ፣ ፀሐፊና አባላት ይኖራሉ፡፡ አሁን እንግዲህ ያ የቡድን አደራጅ ሁሉም የቡድኑ አባላት ተሳታፊ በመሆን ስራውን እንዲያቀርቡ ያደረጋል…፡፡ የቡድን ኂላፊው ሁሌ በቡድን ኂላፊነት መቀጠል የለበትም፡፡ ፕሮጀክቱን የክፍሉ የቡድን አባላት ሁሉ ተሳታፊ ሆነው እንዲማሩ እናደርጋለን ፡፡ ከዚያም ውጭ የቤት ስራ ወይም ቴስቶች ልንሰጥ እንችላለን ፡፡ ይህንንም ሰርተው ሲመጡ የሚፃፍ ከሆነ በግላቸው ሊጽፉ ይችላሉ፡፡ ወይም መስክ ወጥተው በኮሌጁ አንድ ቦታ ወይም ለወደፊት ሊመደቡበት ወደሚችሉት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሄደው ያዩትንና የተገነዘቡትን ዘገባ ያቀርባሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ሁሉ ማንኛውም ከክፍሉ የቡድን አባላት ተሳትፎ ውጪ በግልም የተለያዩ ተግባራትን እንደሚያከናውኑ መገንዘብ አለብን፡፡ ሰልጣኞቹ አንዳንዴ ቡድን መምራት፣ ፀሐፊ መሆን ተራ አባል ሆነው መሳተፍና በመሳሰሉት እንዲሳተፉ እናደርጋለን ( ዓለሙ ጫላ፣* /17/07/04 ከ4፡00-5፡00 )፡፡

የቡድን አመሰራረቱን ስንመለከት በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ቡድኖችን የሚያስተባብሯቸው የቡድን አደራጅ፣ ፀሐፊና አባላት አሉ፡፡ ይህ የቡድን አደራጅ ሁሉም የቡድኑ አባላት ተሳትፈው ስራውን እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡ ይህም ሁሉም የቡድኑ አባላት ተራ በተራ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል፡፡ የቡድን ኂላፊውም ሁሌ በቡድን ኂላፊነት መቀጠል እንደሌለበትና ፕሮጀክቱን የክፍሉ የቡድን አባላት ሁሉ ተሳታፊ ሆነው እንዲማሩ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ አንፃርም የቡድን አደረጃጀት ስልታቸው ተማሪዎች በአግባቡ በመማር-

ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ስለሚያደርጋቸው ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አንፃር ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

### 5.2.3. የዕጩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አተያይ

አሰልጣኝ መምህራን በክፍል ውስጥ ልዩ ልዩ የማስተማር ብልሃቶችን ተጠቅመው ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎች ደግሞ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ አቀራረብ ደግሞ የተማሪ-ተኮር መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተለያዩ ብልሃቶችን በመጠቀም የመማር-ማስተማሩ ሂደት በአንድ ወገን ብቻ የሚተገበር ሳይሆን መምህራንና ተማሪዎችን የራሳቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል፡፡ Fernና et al (2005) እንደገለፁት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የመምህራንና የተማሪዎችን ስምምነት ይጠይቃል፡፡ ስምምነቱም መምህራን ትምህርቱን ሲያቀርቡ በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመጠቀም እንደሁኔታ አመቻች ሆነው ካገለገሉና ተማሪዎችም በመማር-ማስተማሩ ሂደቱ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን በቀረበላቸው ዘዴዎች ተግባራትን ማከናወን ከቻሉ ስምምነት ተፈጠረ ማለት ነው፡፡

በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ 3ኛ ዓመት ዕጩ ሰልጣኞች ሲሰለጥኑ በነበሩበት ዓመታት የአፋን ኦሮሞ መምህራን ሲጠቀሙበት የነበረውን የማስተማር ብልሃቶች ምን እንደሚመስሉ በቡድን-ተኮር ውይይት ላይ ጥያቄ አቅርቤላቸው የሚከተለውን ብለዋል፣

> *…አፋን ኦሮሞን በተለያዩ ብልሀቶች እየተማርን እንገኛለን፡፡ ለምሳሌ በውይይት፣ በጥያቄና መልስ፣ በክርክርና አንዳንዴ ደግሞ ሊነሱ ይችላሉ ተብለው ለሚታሰቡ ሀሳቦች በጥልቀት በመነጋገር እየተማርን እንገኛለን፡፡…ይህም ተማሪዎች ራሳችን በራሳችን ሀሳቦችን አደራጅተን፣ በመምህሩ ላይ ጥገኛ ሳንሆን እርስ በርሳችን ትምህርት እየተሰጣጣን እውቀት የምንገበይበት መንገድ ነው ማለት ነው፡፡ …የትምህርት ርዕስ ለተማሪዎች ይሰጥና እያንዳንዳችን በዚያ ርዕስ ላይ በቡድን ሆነን በጥልቀት ተወያይተን ሀሳብ ካመነጨን በኋላ ከየቡድኑ የተወያየንበትን ሀሳቦች አቅርበን በመጨረሻ መምህራን በተነሱት ሀሳቦች ዙሪያ ማጠቃለያ ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዴ ተማሪዎች ይጋበዙና ማጠቃለያ እንዲሰጡ ያደረጋሉ፡፡ …አቀራረቡ የሚተገበርበት መንገድ ከይዘት ይዘት ሊለያይ ይችላል፡፡ ከዚህ በመነሳት አንዳንዴ በቡድን የምንሰራው ስራ ሊኖር ይችላል፤ በግል መስራት አለ፤ ሌሎችን ብልሃቶች ልንጠቀም እንችላለን፡፡ በዚህ አቀራረብ መማራችን*

*ተማሪዎች ራሳቸው የዕውቀት ምንጭ እንደሆኑ በማሰብ ሀሳባችንን እንድንሰጥ እንደረጋለን፡፡ (አቡ፣8/02/06 ከ 5፡00-6፡00 ) ፡፡*

ከላይ በተመለከትነው በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ3ኛ ዓመት የተማሪዎች የቡድን ተኮር ውይይት ተሳታፊዎች እንደተናገሩት በኮሌጁ ውስጥ አፋን ኦሮሞን ሲማሩ መምህራን የተለያዩ ብልሃቶችን መጠቀማቸው በክፍል ምልከታም ተረጋግጧል፡፡ መምህራን ትምህርቱን ሲያቀርቡ በመጀመሪያ በተወሰነ ደረጃ የትምህርቱን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከፃፉ በኋላ በመማሪያ ሞጁላቸው ላይ የሚገኙትን የትምህርቱን ይዘቶች እንዲያወጡና በቡድን ተወያይተው ወይም በመማሪያ ሞጁሉ ውስጥ በቀረቡት መመሪያዎች መሰረት የቀረበላቸውን ተግባራት እንዲሰሩ ያደረጋሉ፡፡ የተሰሩት ስራዎች በተላለፈላቸው ትዕዛዝ መሰረት በተማሪዎቹ አቅራቢነት ቡድን በቡድን ለመምህሩ ይቀርባሉ፡፡ በመጨረሻም በመምህሩ ወይም ተማሪዎች እጅ እያወጡ ማጠቃለያ በመስጠት የዕለቱን ትምህርት ያበቃሉ፡፡

በአሰልጣኝ የአፋን ኦሮሞ መምህር ከላይ እንደተብራራው በክፍል ውስጥ የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን ወይም ዘዴዎችን ለመተግበር መስፈርት ተቀምጦለት ሁሉም መምህራን በተመሳሳይ መንገድ ይተገብሩታል ተብሎ ሳይሆን ተወያይ ተማሪዎችም እንደተናገሩት አቀራረቡ የሚተገበርበት ሊለያይ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አንዳንዴ በቡድን የሚሰሩት ስራ ሊኖር እንደሚችል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በግልና በሌሎችን ብልሃቶች ትምህርቱ ይቀርባል እንጂ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመሆኑ ብቻ መቀያየሩ ግዴታ አይደለም፡፡ በተጨማሪም በተፈለገ ጊዜ የመምህር-ተኮር አቀራረብም ሊተገበር እንደሚችል መታወቅ አለበት፡፡

በተወያዮቹ ማብራሪያ መሰረት አፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በቡድን የተወያዩበትን በቡድን ተወካዮቻቸው አማካይነት ዘገባ ያቀርባሉ፡፡ በምልከታዬ እንደተረጋገጠውና መምህሩ የመረጧቸውን የማስተማሪያ ሞጁሉን ለመቃኘት እንደተሞከረው የዕለቱን የትምህርት ይዘቶች ለማስተማር የተጠቀሙበት የማስተማሪያ ብልሃት በሞጁሉ ላይ የተሰጠው ትዕዛዝ "በቡድን ተወያይታችሁ..." እንድትሰሩ ስለሚል የተከናወኑ ተግባራት በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰሩ ስለመሆናቸው አረጋግጫለሁ፡፡ ስለዚህ በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጁ ውስጥ አሰልጣኝ መምህራን የሚመርጡዋቸው የማስተማሪያ ብልሃቶች ምርጫ ከይዘት ይዘት ሊለያይ እንደሚችል

መረዳት ይቻላል። በተጨማሪም በማስተማሪያ ሞጁሉ ላይ የቀረቡት ትዕዛዛት መምህሩ ትምህርቱን በምን ዓይነት የማስተማር ብልሃት ወይም የማስተማር ዘዴ ትምህርቱ ማቅረብ እንዳሚኖርበት ይወስኑታል። ሞጁሉ የመምህሩን የማስተማር ብልሃት ምርጫ የሚወስነው ከሆነ የፈጠራ ሁኔታና የመስራት አቅሙንም ሊገድበው ይችላል።

## 5.2.4. የኮሌጁ አሰልጣኞች የስራ ላይ ስልጠና

በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ ዕጩ መምህራንን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ በአግባቡ ለማሰልጠን አሰልጣኞችም የስራ ላይ ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል። የመምህራንን ስልጠና አስመልክተው Smith (1987) የሰለጠኑ መምህራን በትምህርት ውስጥ ከፍተኛ እድገት ለማምጣት በር ከፋች ናቸው ያሉትም የተማሪ-ተኮር አቀራረብም ይሁን ሌላ ለውጥ ያመጣል በተባለ መንገድ ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ለማሳየት ነው። ከዚህ አንፃር በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህራን የተለያዩ ብልሃቶችን ተጠቅመው እንዲያስተምሩ ክህሎቱን እንዴት እንዳገኙ ለአፋን ኦሮሞ መምህሩ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፣

> *በሮቤ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ተመድበው የሚመጡ አሰልጣኝ መምህራን በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የቅድመ-ስራ ላይ ስልጠና አግኝተዋል። በኮሌጅ ውስጥ ከተመደቡ በኋላ ደግሞ በተለያዩ መርሀ-ግብሮች ስልጠና ያገኛሉ። ከመርሀ-ግብሮቹ ውስጥ እንደ አብነት የሚጠቀሰው የከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP) ትምህርት ነው። ይህ ትምህርት ደግሞ መምህራን የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ንቃት የተላበሰን መንገድ ስራ ላይ እንዲያውሉ፣ የተለያዩ የተማሪዎች አገማገምና የምዘና ዘዴዎችን፣ በክፍል መማር-ማስተማር ውስጥ የቡድን አመሰራረትን፣ የክፍል ውስጥ ቁጥጥርን፣ በመሳሰሉ ስልጠናዎች ብቃታቸው እንዲያድግ ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ በራሳችን መምህራን የስታፍ ውስጥ ስልጠና (In-Satff Training) ያገኛሉ። ይህም የስታፍ ውስጥ ስልጠና በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በልዩልዩ ብልሃቶች አጠቃቀም፣ በተከታታይ ምዘና፣ በICT፣ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ፣ በተከታታይ ምዘና ዙሪያ ልምድ ባላቸው መምህራን እርስ በርስ ይሰለጣጠኑበታል። በዚህ መንገድ በኮሌጃችን የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪ-ተኮር አቀራረብን እየተገበሩት ይገኛሉ (ዓለሙ ጫላ፣*/17/07/04 ከ4፡00-5፡00 )።

በኮሌጁ የአፋን ኦሮሞ መምህር አገላለጽ በማሰልጠኛው ውስጥ የአሰልጣኞች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እውቀት መገኘት መሰረቱ የመምህራኑ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት፣ የከፍተኛ ዲፕሎማ መርሀ-ግብር፣ የስታፍ ውስጥ ስልጠና በኮሌጁ ውስጥ መኖር የመምህራንን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር እውቀታቸውን እንዲያሳድጉ አድርጓቸዋል፡፡ የአሰልጣኞች ስልጠና ማግኘት የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር ብቁ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ ሰልጣኞችም በዚያው መንገድ ግብዓት እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡

በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ውስጥ ለአፋን ኦሮሞ መምህሩ የኮሌጁ የአፋን ኦሮሞ መምህራን የስራ ላይ ስልጠና እንዴት እንደሚያገኙ በተጨማሪነት ለቀረበላቸው ጥያቄ

> … በአንድ ስትሪም ውስጥ የተለያዩ ኮርሶችን የሚያስተምሩ መምህራን በራሳቸው የትምህርት ዘርፍ ያገኙዋቸውን ልምዶች ለሌሎች ጓደኞቻቸው ያካፍላሉ፡፡ የቋንቋ መምህራን ከሳይንስ መምህራን ልምድ መውሰድ… በተጨማሪም በየትምህርት ዘርፉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮና አልፎ አልፎም ትምህርት ሚኒስቴር ጠርተውን ስልጠና ይሰጡናል፡፡ ለምሳሌ በፕራክቲከም አተገባበር፣ በተከታታይ ምዘናና በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ዙሪያ ያሰለጥናሉ፡፡ (ዓለሙ ጫላ፣/17/07/04 ከ4፡00-5፡00) ፡፡

ይህም ሀሳብ በኮሌጁ ውስጥ ዕጩ መምህራንን የሚያሰለጥኑ መምህራን በተለያዩ መንገዶች የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር ክህሎት ያገኙ በመሆናቸው ዕጩ መምህራኑን ለማሰልጠን ብቃት ያላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ዕጩ መምህራኑም ከመምህራኑ ያገኙትን ግብዓቶች በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመድበው ሲያስተምሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በአግባቡ ተግባራዊ ያደርጉታል ማለት ነው፡፡

> *…እኛ እንደ አፋን ኦሮሞ መምህራን የተለያዩ ስልጠናዎችን ከተለያዩ ተቋማት እናገኛለን፡፡ እነዚህ ተቋማት መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲሆኑ እንደ አሜሪካ መንግስት እርዳታ ድርጅት (USAID)ና መሰረታዊ ትምህርት ለሁሉም (Beso) ድጋፍ ስልጠና ወስደን የአንደኛ ደረጃ መምህራንን እናሰለጥናለን፡፡ በሌላ በኩል እኛም እንደ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የእንግሊዘኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ማዕከል (Elic) የሚባል በመኖሩ በዚህ ክፍል ስር የስልጠና ሰነድ ተዘጋጅቶ ለአንደኛ ደረጃ መምህራን ስልጠና እንሰጣለን* (ዓለሙ ጫላ፣ /17/07/04 ከ4፡00-5፡00) ፡፡

አሰልጣኝ መምህራንም ለራሳቸው በቂ የሆነ የአሰለጣጠን ዕውቀት የሚያገኙት ከተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በከፍተኛ ዲፕሎማ ነው፡፡ መምህራኑ ለራሳቸው ብቻ እውቀቱን አግኝተው የሚያበቁ ሳይሆኑ እነዚህ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በትምህርት

ዘርፍ ላይ የገንዘብ ድጋፍ ሲያደርጉላቸው  በኮሌጁ ዙሪያ ለሚገኙ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ስልጠና እንደሚሰጡ ያስገነዝቡናል፡፡

ለመምህራኑ የሚሰጠው ስልጠና በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ላይ ከሆነ በዚያ አካባቢ በተለይም (በሮቤና ጎባ ከተሞች ዙሪያ) ለሚገኙ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በአግባቡ እንዲተገብሩ ሊረዳቸው ይችላል ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሰናል፡፡ መምህራኑ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበርን ስልጠና ያገኙት ደግሞ በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ በትምህርት ላይ ድጋፍ በሚሰጡ ድርጅቶች አማካኝነት ነው ፡፡

## 5.2.5. የአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህራን የግምገማ ስልት

መምህራን ትምህርቱን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያቀርቡ ሊከተሏቸው የሚገቡ የተማሪዎች የግምገማ ስልቶች ይኖሯቸዋል፡፡ እንደ መምህር-ተኮር አቀራረብ የግምገማ ስልት በፈተናዎች ላይ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን እንደ አገላለጽ በተከታታይ ምዘና ላይ ተመስርቶ የሚተገበር ነው (Puhl ፣1997)፡፡ የተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች በተለያዩ ሁሉ አቀፍ ብቃታቸው የሚመዘኑበት ስልት ነው፡፡ ለምሳሌ በዝግበ-ጥናት ( portfolio)፣ ንግግር በማቅረብ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ በተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች መሳተፍ አንፃር ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ በሮቤ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ አሰልጣኝ መምህራን ዕጩ ሰልጣኞችን የሚገመግሙበትን ብልሃት ለማወቅ በምልከታና በቃለ-መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

በክፍል ውስጥ ምልከታና በኮሌጁ የሬጅስትረር ቢሮ ቅፅ ላይ ከሰፈሩት ሰነዶችና  ከኮሌጁ የሶስተኛ ዓመት ተማሪዎች ቡድን-ተኮር ውይይት  እንደተገኘው መረጃ መምህራን ሲጠቀሙበት የሚገኙት የግምገማ ስልት የሚተገበረው በተከታታይ ምዘና  ነው፡፡ የተከታታይ የምዘና ስልት ተማሪዎች በሚሰሩት የተለያዩ ተግባራት ላይ ተመስርቶ የሚተገበር ምዘና ነው፡፡ ለምሳሌ የኮሌጁ መምህራን ሁሉ ተማሪዎቻቸውን የሚመዝኑበት ቅጽ ላይ የሰፈረው የቤት ስራዎች፣ ፕሮጀክቶች፣ የክፍል ስራ፣ የጉብኝት ሪፖርቶች፣ ዝግበ-ጥናቶች፣ ጽሁፍ ማቅረብ፣ የቢጤ ማስተማር፣ሙከራዎችና ማጠቃለያ ፈተናዎች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ አሰልጣኝ መምህር ከነዚህ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ በፈለጉት መንገድ ተማሪዎቻቸውን ሊመዝኑ ይችላሉ፡፡ ይህ የምዘና ስልት በኮሌጁ ውስጥ እንደ ህግ

ተደርጎ ሁሉም አሰልጣኞች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርባቸው መምህራን ይናገራሉ። ምዘናው በተከታታይ ምዘና የሚተገበር ሲሆን ሙከራዎችን ጨምሮ 70% ሲያካትት 30% ደግሞ ማጠቃለያ ፈተናን ያካትታል።

በመምህራን ኮሌጅ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ ተማሪዎችን ለመመዘን የሚጠቀሙት ብልሃት ምን እንደሆነ ለአፋን ኦሮሞ መምህር ጥያቄ አቅርቤላቸው

> *...አፋን ኦሮሞን በማስተምርበት ወቅት ተማሪዎቼን በተከታታይ ምዘና እየገመገምኳቸው ነው። ይሄንንም እንድጠቀም ኮሌጁ የተከታታይ ምዘና ውጤት መመዝገቢያ ቅጽ ራሱ አዘጋጅቶ በዚያ መሰረት ተግባራዊ እያደረኩኝ እገኛለሁ። ይህ ማለት የመጨረሻው ማጠቃለያ ፈተና 30% ሲሆን 70%ቱ በተለያዩ መንገዶች የሚያልቅ ነው። ለምሌ በቡድን ስራ፣የቤት ስራ፣የክፍል ስራ፣ ፕሮጀክት፣ወረቀት ማቅረብና በመሳሰሉት ነው* በማለት ምላሽ ሰጥውኛል*(ዓለሙ* ጫላ፣17/07/04፣ከ4፡00-5፡00 )።

እንደ መምህሩ አገላለጽ ተማሪዎች እንደቀድሞው የመምህር-ተኮር አቀራረብ በፈተና ብቻ ብቃቱ ተለይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት ሳይሆን የተማሪዎቹ ብቃት በልዩ ልዩ መንገዶች ተፈትሾ ለመጨረሻ ውጤት ይደርሳሉ ማለት ነው። Hubaና Freed (2000) እንደገለፁት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሂደት ውስጥ ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ መደረጉ አግባብ ነው። ይህ ተከታታይ ምዘና በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መኖሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አንዱ ክፍል ሊኖር እንደሚችል ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል። በመሆኑም ከዚህ አንፃር ዕጩ መምህራኑም ትምህርታቸውን አጠናቀው በአንደኛ ደረጃ ውስጥ ተመድበው አፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩ በቂ ግብዓት ስላላቸው ተግባራዊ ሊያደርጉት ይችላሉ ያስብላል።

## 5.2.6. የተመረጡ የኮሌጅ ሐላፊዎች የተማሪ-ተኮር አተገባበር አተያይ

በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራን በምን አይነት የማስተማር አቀራረብ ስልጠና እየሰጡ እንደሚገኙ ለኮሌጁ ዋና ዲን ቃለ-መጠይቅ አቅርቤላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል።

> *በሮቤ መ/ት/ማ/ኮ/ ውስጥ መማር-ማስተማሩ የሚካሄድበት መንገድ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ወይም ንቃት በተላበሰ መንገድ ነው። ንቃት*

*በተሳበሰ ማለት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በመሳተፍ እውቀት የሚገበዩበት ስለሆነ ነው። ይህ በሌላው ስሙ ተማሪ-ተኮር ማለት ነው። በአጭሩ በተብራራው መንገድ ስለሚማሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እየተገበርን ነው። ይህ ሲባል በቀድሞውና በተለምዶአዊው የመምህር-ተኮር አቀራረብ ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ መምህራን ንቁ በመሆን ተማሪዎች በበኩላቸው ፍዝ ሆነው መማር-ማስተማሩ ይከናወን ነበር። በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ግን መምህሩ ሁኔታ አመቻች፣ ማብራሪያ ሰጪ፣ረጂ የሆነበት ስርዓተ-ትምህርት ነው። ስለዚህ በዚህ አቀራረብ ማስተማሩ የግድ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት ውስጥ ተሳታፊ ሆነው እየተማሩ ናቸው። እኛም እነዚህ ዕጩ መምህራን በተገለፀው መንገድ ሰለሰለጠኑ ከምረቃ በኋላ በተመደቡባቸው ትምህርት ቤታቸው ውስጥ በሰለጠኑበት መንገድ ያስተምራሉ ብለን እናስባለን (ታደሰ* ቢርቢርሶ፣ /17/07/04 ፣ከ4፡00-500 ሰዓት)።

በኮሌጁ ዲን አገላለጽ መሰረት በሮቤ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የሚገቡ ዕጩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስልጠና እየተሰጣቸው ይገኛል። ዕጩ መምህራኑ በራሳቸው ትምህርት ውስጥ ኋላፊነት በመውሰድ እርስ በርሳቸው እየተደጋገፉ እየተማሩ ይገኛሉ። በዚህ መንገድ ሰልጥነው ከወጡ በኋላ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ስራ ሲሰማሩ በሰለጠኑበት መንገድ እነሱም ያስተምራሉ ተብሎ ይታሰባል። ምክንያቱም ስልጠናው በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መምህራን ምን ምን ተግባራት ማከናወን እንደሚገባቸውና በአንፃሩ ደግሞ ተማሪዎች ምን መስራት እንዳለባቸው የሚያመላክት በመሆኑ በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን ክህሎት ተክነው ለወደፊት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚመደቡበት ወቅት ተግባራዊ ሊያደርጉት ይችላሉ የሚል ነው።

እንደ ሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ዋና ዲን ሁሉ ለአካዳሚክና የምርምር ም/ዲንም ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርቤላቸው የሚከተለውን ብለውኝ ነበር።

*በኮሌጃችን ውስጥ የመማር ማስተማሩ-ሂደት ተማሪን ማዕከል በሚያደርገው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተከናወነ ነው። እያንዳንዱ መምህር የተዘጋጀለትን ሞጁል ሲያስተምር ተማሪዎች በራሳቸው በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እየተሳተፉ እንዲማሩ ያደርጋል። በመማሪያ ሞጁሉ ላይ የቀረቡት መመሪያዎችና የትምህርት ይዘቶች ራሳቸው ተማሪን ማዕከል አድርገው ስለተዘጋጁ ሰልጣኝ መምህራኑ*

*በቡድን በቡድን ሆነው ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ ለሚያስተምሯቸው መምህራን ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡ የሚቀርቡት ተግባራት በቡድን ብቻ ላይሰሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን እና ከሙሉው የክፍል ተማሪዎች ጋራ ሊሆን ይችላል፡፡ በሞጁሉ ውስጥ የቀረቡት ትዕዛዛት ተማሪዎቹ በምን አይነት የመማር ብልሃቶች መማር እንደሚገባቸው ጥቆማ ስለሚሰጡ በዚያው መሰረት ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ተግባራቱን ያከውናሉ፡፡ ስለዚህ በኛ ኮሌጅ ውስጥ የመማር-ማስተማሩ ሂደት እየተተገበረ ያለው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው (አብዳ ጃኖ ፣ በ*8/02/06 *ዓ.ም፣* ከ4፡00-4፡30)*፡፡*

በኮሌጁ አካ/ም/ዲን አገላለጽ በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ የመማር-ማስተማሩ ሂደት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተተገበረ መሆኑን ነው፡፡ መምህራን ይህን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲተገብሩ ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ ያስመሰክራሉ፡፡ መምህራን አቀራረቡን ለመተግበር የሚጠቀሙበት ብልሃቶች በመማሪያ ሞጁሉ ውስጥ የቀረቡት መመሪያዎችና የትምህርት ይዘቶችን መሠረት በማድረግ እንደሆነ ነው፡፡ በሐላፊው አስተያየት በአፋን ኦሮሞ መምህሩም ቃለ-መጠይቅ ምላሽ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም በሮቤ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ የመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መምህራን የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ቀደም ብለው በተለያዩ ኮሌጆች ውስጥ የሚያስተምሩ አሰልጣኝ መምህራን እንደየትምህርት ዓይነቶቹ ባዘጋጇቸው ሞጁሎች ውስጥ ባቀረቡት የትምህርቱ ይዘቶችና መመሪያዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአፋን ኦሮሞ ትምህርት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመተግበር ላይ መሆኑና መምህራን የሚጠቀሙባቸው የማስተማር ብልሃቶች ደግሞ ተዘጋጅተው በቀረቡ ሞጁሎች ውስጥ ያሉ መልመጃዎችና መመሪያዎች ናቸው፡፡

በኮሌጁ ዲኖች የተብራሩ ነጥቦች ላይ ተጨማሪ ጥያቄ ለቋንቋ ስትሪም ተጠሪና የአፋን ኦሮሞ መምህር በማቅረብ የአፋን ኦሮሞ ትምህርትን እንዴት እየሰጡ እንደሚገኙ ለቀረበላቸው ጥያቄ እንደሚከተለው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

*በኮሌጃችን ለማንኛውም የቋንቋ መምህራን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ማሻሻያ ስልጠና ይሰጣል፡፡ እንደ አፋን ኦሮሞ መምህራንም ተማሪን ማዕከል ባደረገ የማስተማር ዘዴ ወይም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመጠቀም በክፍል ውስጥ ሰልጣኞችን እናሰለጥናለን፡፡ ይህን ስል ዝም ብለን አይደለም፤ መሰረት*

> *ይኖረናል፡፡ መሰረታችንም እንድናስለጥንበት የተዘጋጁልን ሞጁሎች ናቸው፡፡ የምናስለጥንበት ሞጁሎች ምንም እንኳን ተማሪዎች በዝግጅቱ ውስጥ ባይሳተፉበትም በኦሮሚያ ውስጥ ከሚገኙት አስራ ሁለቱም መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች በተውጣጡ የአፋን ኦሮሞ መምህራን ተማሪን ማዕከል ባደረገ መንገድ እናዘጋጃለን፡፡ በእነዚያ ሞጁሎች ላይ የቀረቡት መልመጃዎች ሰልጣኞቹ በምን ዓይነት መንገድ መልመጃዎቹን መስራት እንደሚገባቸው ትዕዛዛት ቀርበዋል፡፡ በሞጁሎቹ ውስጥ በቀረቡት መመሪያዎች መሰረት ተማሪዎቹ ተግባራቱን ሲያከናውኑ ከተፈለገው ግብ ላይ እንደሚደርሱ ይታሰባል (*ታደሰ ቢርቢርሶ፣ /17/07/04 ፣ከ400-5፡00) ፡፡

በማለት በአፋን ኦሮሞ ትምህርት ክፍል አካባቢ እየተተገበረ የሚገኘውን የመማር-ማስተማር አቀራረብ ሁኔታ ገልፀውልኛል፡፡

በቋንቋ ስትሪም ተጠሪና የአፋን ኦሮሞ መምህር አገላለጽ በኮሌጁ ውስጥ የሚሰለጥኑት ዕጩ መምህራን ስልጠና የሚወስዱት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው፡፡ የአፋን ኦሮሞ መምህራንም በተጠቀሰው መንገድ ሰልጥነው ይመረቃሉ፡፡ በአቀራረቡ ውስጥ እንደመሰረት ሆኖ የሚመራቸው ተማሪዎቹ የሚማሩባቸው የኮርሶቹ ሞጁሎች ናቸው፡፡ በኦሮሚያ ውስጥ አፋን ኦሮሞ የሚያስተምሩ መምህራን ከሁሉም የኦሮሚያ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተውጣጥተው ተማሪዎቹ የሚሰለጥኑባቸውን ሞጁሎች ያዘጋጃሉ፡፡ ይህን ሲያዘጋጁም ተማሪን ያማከሉ ሆነው እንዲቀርቡ ይደረጋሉ፡፡ ዕጩ መምህራኑ ከዚህ ስልጠና በኋላ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በተመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋሉ ማለት ነው፡፡ ይህም በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በማሰልጠኛ በነበሩበት ወቅት የሚያገኙት የተማሪ- ተኮር አቀራረብ ትግበራ ግብዓት እንደሚጎናፀፉ ያስረዳናል፡፡

የስነ-ትምህርት (Pedagogics) መምህር ዕጩ መምህራን ለወደፊት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ተመድበው ሲያስተምሩ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪዎቻቸውን እንዴት ማሳተፍ እንደሚችሉ፣ የሰለጠኑበትን ትምህርት ለወደፊት እንዴት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደሚያስተምሩ፣የተለያዩ ዘዴዎችን እንዴት እንደሚተገብሩ የሚያሰለጥኑ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የሰለጠኑበትን ትምህርት እንዴት በተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች ተጠቅመው ማስተማር እንዳለባቸው አቅጣጫ አመላካች ከመሆናቸው ባሻገር

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለተማሪዎች ያለውን ጠቀሜታና በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ እንዴት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት አሰልጥነው የሚያበቁ በመሆናቸው ቃለ-መጠይቅ አቅርቤላቸዋለሁ፡፡

የቃለ-መጠይቁም ይዘት በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጁ ውስጥ ዕጩ መምህራን እንዴት እየሰለጠኑ እንደሚገኙና አሰልጣኝ መምህራኑስ በስራ ላይ ስልጠና አቅማቸውን እንዴት እየገነቡ እንዳሉ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሻቸው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

> *በዚህ ግቢ (በኮሌጁ) እየተሰጠ የሚገኘው የማስተማር ስነ-ዘዴ ተማሪን ያማከለ ነው፡፡ ተማሪን ያማከለ ደግሞ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማለት ነው፡፡ ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት በመሳተፍ የሚማሩበትና ያላቸውን እምቅ ችሎታ የሚያወጡበት መንገድ ነው፡፡ ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተለያዩ ብልሀቶች ስራ ላይ እየዋሉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ብልሃቶች የትምህርቱ ይዘቶች በሚያመቻቸው መንገዶች በመጠቀም ከተለያዩ ስልጠናዎች ባገኘነው መሰረት እኛም እናሰለጥንበታለን (ኩምሳ ቃበቶ፣ በ/17/07/04 ፣ከ5፡00-5፡30 ሰዓት )፡፡*

ከላይ በመምህርነት ሙያ መምህሩ የተብራሩት ሀሳቦች በኮሌጁ ውስጥ ስልጠና እየተሰጠ የሚገኘው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብም ሲተገበር የተማሪዎችን ውስጣዊ ችሎታ እንዲያወጡና ይህንንም በንቃት ተሳታፊ በመሆን የሚተገብሩት መሆኑንም ገልፀዋል፡፡ በዚህ ሀሳብ ከላይ የኮሌጁ ዲኖች፣ የቋንቋ ስትሪም ኀላፊና የአፋን ኦሮሞ መምህር እንደገለፁት ሁሉ የኮሌጁ የመማር-ማስተማር ሂደት እየተከናወነ ያለው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው፡፡ አቀራረቡ ሲተገበርም የተለያዩ የማስተማር ብልሃቶችን በመጠቀም ነው፡፡የማስተማር ብልሃቶቹ ሲተገበሩ በትምህርት ይዘቶቹ አመቺነት ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ነገር ግን የክፍል ምልከታ በምናከናውንበት ወቅት ከታዩት የማስተማር ብልሃቶች ውስጥ የቡድን ውይይትና የግል ስራ ነበር፡፡

ለእኚሁ የመምህርነት ሙያ መምህር የአሰልጣኞች የስልጠና አገኛኘትን በተመለከተ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

> *በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር በተለያዩ መንገዶች ስልጠና እናገኛለን፡፡ ከነዚህ ውስጥ በከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP) ስልጠናና ከዚህ ውጪም በተከታታይ የመምህራን ሙያ*

*ማሻሻያዎች (CPD) ስልጠናዎች ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ ባገኘነው ስልጠና ከእኛ አልፈን በአካባቢያችን የሚገኙትን የአንደኛ ደረጃ መምህራንን ለማሰልጠን የሚያስችለን ዕውቀት ስላለን ስልጠና እየሰጠናቸው እንገኛለን (ኩምሳ ቃበቶ ፣በ/17/07/04፣ከ5፡00-5፡30 ሰዓት)፡፡*

በኮሌጁ የመምህርነት ባለሙያው አገላለፅ አሰልጣኝ መምህራን የሥራ ላይ የሚያገኙባቸውን ሁኔታዎች ሲያስረዱ ራሳቸውን ብቁ ለማድረግ በተለያዩ መንገዶች ስልጠና ያገኛሉ፡፡ በተለይም ከፍተኛ ዲፕሎማና ተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ (CPD) በቂ የሆነ የአሰለጣጠን ዕውቀት ያገኙባቸው መርሀ-ግብሮች ናቸው፡፡ በዚህ ባገኙት ዕውቀት የኮሌጁንም ይሁን በአካባቢያቸው ያሉ የአንደኛ ደረጃ መምህራንንም ለማሰልጠን መቻላቸውን አስረድተዋል፡፡ ይህ ደግሞ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለመምህራን ኮሌጁ ቅርበት ያላቸው በመሆናቸው የስልጠናው ተጠቃሚዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በአግባቡ እንዲተገብሩ ሊረዳቸው ስለመቻሉ በቀጣይ ለማየት እንድንጓጓ ያደርገናል፡፡

የመምህርነት ሙያ ስልጠናው የአፋን ኦሮሞ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዲያስተምሩ ምን ዓይነት እገዛ እንዳደረገላቸውና የሰለጠኑባቸው የመማር ብልሃቶች ምን አይነቶች እንደሆኑ ለማወቅ እንዲረዳኝ ለኮሌጁ የስነ-ትምህርት አሰልጣኙ ተጨማሪ ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር፡፡

*…መምህራን በዚህ ብልሃት ይጠቀማሉ ማለት አስቸጋሪ ቢሆንም እንግለፀው ከተባለ መምህራን በስራ ላይ ስልጠና፣ በዩኒቨርሲቲ ቆይታ፣ በከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP) ስልጠና፣ በስታፍ ውስጥ ስልጠና ያገኙትን ስልጠናዎች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ጥበባቸውን ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ተግባራዊ የሚያደርጉበት ጥበብ ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል፡፡ ቢሆንም እንደ አጠቃላይ ስንወስደው እንደ የመምህራን ሙያ ትምህርት ክፍል ተመሳሳይ ኮርስ የምናስተምር መምህራን በየትምህርቱ ምዕራፍ ምን መስራት እንደ አለብን ማዕቀፍ (ማንዋል) አዘጋጅተን በዚያ እየተመራን በክፍል ውስጥ እንተገብራለን፡፡ በየትኛው የመማር-ማስተማር ዘዴ መጠቀም እንደአለብን፣ ተከታታይ ምዘናን እንዴት መጠቀም እንደ አለብን፣ እናወጣለን፡፡ እንደ አብነት ከመማር-ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ እረፍት ያለው ገለፃ መጠቀም፣ በቡድን ውይይት፣ በጓደኛ ማስተማር (Peer Teaching) በፕሮጀክት የማስተማርዘዴ፣ በሙከራዊ ዘዴ ማስተማር፣ በፓናል ውይይትና በመሳሰሉት ተግባር ላይ እናውላለን፡፡ ይሁን እንጂ የአተገባበር ጥበቡን የትምህርቱና*

ይዘቱ ሊወስነን ይችላል፡፡ የአፋን ኦሮሞ መምህራንም ይህን ያደርጋሉ ብዬ አምናለሁ (ኡምሳ ቃበቶ፣ በ/17/07/04 ፣ከ5፡00-5፡30 )፡፡

የስነ-ትምህርት መምህሩ አገላለጽ በኮሌጅ ውስጥ ተመድበው ስልጠና የሚሰጡ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር ከትምህርታቸው የራሳቸው የቀደመ ጥበብ ያላቸው መሆናቸውንና ይህንንም ጥበብ በከፍተኛ ዲፕሎማ፣ በስታፍ ውስጥ ስልጠና እንደሚያዳብሩትና ዕጩ መምህራኑን ለማሰልጠን እንደሚጠቀሙበት አብራርተዋል ፡፡ ዕጩ መምህራንም በማሰልጠኛ ኮሌጁ ውስጥ በሙያ ሳይንስ ትምህርት ያገኙትን ዕውቀት በተመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚያስተምሩት ትምህርት ላይ ይተገብሩታል ማለት ነው፡፡ የአፋን ኦሮሞ መምህራንም በዚሁ መንገድ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ስራ ላይ ያውሉታል ብለው ስለሚያስቡ ትምህርቱ እገዛ አድርጎላቸዋል ባይ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ሁሉም መምህራን በተመሳሳይ መንገድ ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ እንደማይታሰብና የእያንዳንዱ የማስተማሪያ ብልሃት ትግበራ የሚወሰነው በትምህርቱ ይዘት፣ በመማሪያ ክፍሉ ሁኔታና በተማሪው ዳራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ከላይ ለቋንቋ ስትሪም ተጠሪና የአፋን ኦሮሞ መምህር ለሆኑትም ጥያቄ አቅርቤላቸው በቡድን ውይይት፣ በፕሮጀክት፣ በሚና ጨዋታ፣ በገለፃ፣ እያሳዩ በማስተማር ብልሃቶች መሆናቸውን ተናግረው የሚያሰለጥኑባቸው ሞጁሎችም ለሚጠቀሙባቸው የማስተማር ብልሃቶች አቅጣጫ ጠቋሚ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ በአጠቃላይ ከቃለ-መጠይቁ ምላሽ የምንገነዘበው በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ውስጥ የስልጠና አሰጣጡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመሆኑ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የአፋን ኦሮሞ መምህራንም ሰልጥነው ከወጡ በኋላ በሰለጠኑበት መንገድ አቀራረቡን ተግባራዊ ያደርጉታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጁ ውስጥ የመምህራን ተከታታይ ሙያ ማበልጸጊያ (CPD) አስተባባሪ በኮሌጁ ውስጥ አሰልጣኝ መምህራንና በአካባቢው ለሚገኙ የአንደኛ ደረጃ መምህራን በተመረጡ ርዕሶች ላይ የስራ ላይ ስልጠና እንዲሰጥ የሚያስተባብሩና የሚሰጡም ናቸው፡፡ በቢሯቸው ተገኝቼ የተከታታይ ሙያ ማበልጸጊያ ኣላማና ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ምን ጠቀሜታ እንዳለው ጥያቄ አቅርቤላቸው ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

*የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ማለት በስራ ላይ የሚገኙ መምህራን በሚያስተምሩት ትምህርት ዙሪያ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመፍታት በተከታታይ የሚያሰለጥኑበት ስልት ነው። ይህ ሲባል በዩኒቨርሲቲ፣ በኮሌጆች፣ በሁለተኛና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ መምህራን በስራ ላይ በተከታታይ እየሰለጠኑ ሙያቸውን የሚያሳድጉበት መርሀ-ግብር ነው። በዚህ የሙያ ማበልጸጊያ መርሀ-ግብር ልምድ ያላቸው መምህራን ልምድ የሌላቸውን ሊያሰለጥኑ የሚችሉበትም መንገድ ነው። ዓላማውም በስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ መምህራን በተለይም የአንደኛ ደረጃ መምህራን የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅ ሲባል የሚሰጡ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን ተከታትለው በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ሆነው በተከታታይ ሙያቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ ነው (ተሰማ ተሬሳ፣* /20/07/04፣ ከ4፡00-5፡00 ሰዓት) ።

በተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ አስተባባሪው አገላለጽ መምህራን በስራ ላይ ሆነው የመማር-ማስተማር ችግሮች ለመፍታት የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ስልጠና በሁሉም የትምህርት ደረጃ ላሉ መምህራን ፋይዳ አለው። መርሀ-ግብሩም በማዕከል ተዘጋጅቶ በቀረበ ማንዋል የመምህራንን ችግር ይቀርፋል ተብሎ በታሰበ ሰነድና ልምድ ያላቸው ልምድ ለሌላቸው መምህራን እውቀት የሚያሻግሩበት ነው። ተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ስልጠና ከሚሰጥባቸው ዓላማዎች ውስጥ አንዱና ዋናው የትምህርት ጥራት እንዲጠበቅ ነው። ከትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ተግበራት መካከል አንዱ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር ነው (Derebssa፣1998፤ Amare et al፣2006) ። የትምህርት ጥራት ሲባል በኮሌጁ ውስጥም ሆነ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች በችግር ፈቺ ተግባራት ውስጥ ተሳታፊ ሆነው ከሚያገኙት ልምዶች የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግሮች እንዲፈቱ ማስቻል ነው።

በማስከተል ለአስተባባሪው በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጁ የተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ ስልጠና መርሀ-ግብር ይዘቶች በምን ላይ እንደሚያተኩሩና ስልጠናውን የሚወስዱ መምህራን እንዴት እንደሚገኙ ጥያቄ አቅርቤላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

*በዚህ መርሀ-ግብር የሚሰጡት ስልጠናዎች ተቀጥረው በየትምህርት ቤቱ የሚመደቡትን መምህራን አቅጣጫ ከማስያዝ ይጀምራል። ከዚያም በየትምህርት ቤታቸው ውስጥ*

*ሊሰሩ የሚገባቸው ነገሮች ሁሉ የአሰራር መንገዶቹን ማመላከት ድረስ ይደርሳል፡፡ ለአብነት አንድ መምህር በትምህርት ቤት ውሎው መስራት የሚጠበቅበት ስራዎች ምን እንደሆኑ፣ የስራ ላይ ምርምር /Action Research/ አሰራር፣ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ፣ ለተከታታይ ምዘናና በመሳሰሉት ነጥቦች ላይ ይሰለጥናሉ፡፡ ለእነዚህም ስልጠናዎች በባሌ ዞን፣ በምዕራብ አርሲ ዞን፣ በሻሻመኔና በጉጂ ዞኖች ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እኛ ልናሰለጥን ያቀድነውን የሰው ቁጥር መልምለው እንዲልኩልን እናደርግና ማዕከላዊ ቦታ መርጠን የኛ መምህራን በቦታው ድረስ ተገኝተው ያሰለጥኗቸዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የአንደኛ ደረጃ መምህራንን እናሰለጥናለን (ተሰማ ተሬሳ፣/20/07/04 ፣ከ4፡00-5፡00 ሰዓት)፡፡*

ከዚህ ከአስተባባሪው የምንገነዘበው ነገር  የሚሰጡት የስልጠና ይዘቶች አዳዲስ መምህራንን አቅጣጫ ከማስያዝ ይጀምራል፡፡ ሌላው መምህራን በትምህርት ቤት ውሏቸው መስራት በሚገባቸው ልዩልዩ ተግባራት ላይ ያተኩራል፡፡ ስልጠናው ከባሌ ዞን፣ ከምዕራብ አርሲ ዞን፣ ከሻሸመኔ ወረዳና ከጉጂ ዞን ተመልምለው ለሚመጡላቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ይሰጣል፡፡

በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጁ የተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ መርሀ-ግብር ስልጠናን ስንመለከት ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ መምህራን ስልጠና መስጠቱ እንደ አንድ ትልቅ ግብዓት ሊወሰድ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ግን ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተሙማ ስልጠና የሚሳተፉት መምህራን በትክክል ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋራ የተገናኙ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የለም፡፡ ሌላው በተሰጠው ስልጠና ላይ ተሳትፈው ተመልሰው በትምህርት ቤቶቻቸው ጓደኞቻቸውን ያሰለጠኑ መምህራን ስለመኖራቸውና አለመኖራቸው ተጨባጭ መረጃ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል የሚሰጠው የስልጠና ጊዜ አጭር በመሆኑ በአግባቡ ተግባራዊ ሆኗል ወይም አልሆነም ብሎ ለመደምደም አሁንም መረጃ የለም፡፡ ምክንያቱም በዚህ ተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ ማስተባበሪያ ክፍል የተሰጡት ስልጠናዎች በተጨባጭ ተግባራዊ መሆናቸውን ለወደፊት ለማጥናት ከማቀድ በስተቀር ይህ መረጃ እስከ ተሰበሰበበት ድረስ በጥናት ተደግፎ የቀረበ ሰነድ አልተገኘም፡፡

ከላይ በኮሌጁ የመምህራን ሙያ ሳይንስ የሚያስተምሩ መምህር፣ የአፋን ኦሮሞ መምህርና የቋንቋ ስትሪም ተጠሪ፣ እንዲሁም የመምህራን ሙያ ማበልፀጊያ አስተባባሪ አገላለፅ በማሰልጠኛ ኮሌጁ ውስጥ የሚሰጡ ስልጠናዎች ሁሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ ይሆናሉ ማለት አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱም በትምህርት ቤቶች ውስጥ የማይተገበሩ ብዙ ነገሮች እንዳሉ ብዙ መረጃዎች አሉ፡፡

በተጨማሪም ለተግባር ልምምድ የወጡ ዕጩ መምህራን የሚያጋጥሟቸው የተለያዩ ሁኔታዎች መኖራቸውን እኔም አብሬ በትምህርት ቤት በመገኘት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ለምሳሌ በትምህርት ዕቅድ ቅጽ፣ በተማሪዎች ቁጥጥር፣ በመማር-ማስተማር ዘዴዎች አተገባበር ወዘተ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ ስለዚህ ስልጠናው በትምህርት ቤቶች ውስጥ በአግባቡ ተግባራዊ መሆኑን በጥናት እስካልተረጋገጠ ድረስ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደርጉታል ብሎ ማሰብ ወደ ስህተት ሊመራን ይችላል፡፡

## 5.2.7. የዕጩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ግንዛቤ

ዕጩ መምህራን በኮሌጅ ውስጥ እያሉ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ላይ የቅድመ-ስራ ስልጠና ወስደው ተመልሰው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተግበራዊ ማድረግ የሚችሉት በአቀራረቡ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ሲኖራቸው ነው ፡፡ አዎንታዊ አመለካከት ሊኖራቸው የሚችለው ቀደም ብለው የነበራቸውን የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ ለማምጣታቸው ማረጋገጫ ሲኖር ነው፡፡ ይህን በማስመልከት ለዕጩ መምህራን የቡድን-ተኮር ውይይት ላይ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መማር ያለውን ፋይዳና እስከ 3ኛ ዓመት ድረስ አፋን ኦሮሞን ሲማሩበት በነበረበት ወቅት ያስገኘላቸው ጥቅሞች ምን እንደሆኑ ለተጠየቁት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሾች

> *በአሁኑ ሰዓት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማሬ ያገኘሁት ጥቅሞች ለምሳሌ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሆኜ በዚህ አቀራረብ አልተማርኩም ነበር፡፡ በግሌ ተምሬ በግሌ አሳርሜ ውጤት አገኝ ነበር፡፡ እዚህ ኮሌጅ ከገባሁ ጊዜ ጀምሮ ግን በግሌ ስሰራ የነበረው አካሄዱ ተቀይሮ የኔ እውቀት ለሌሎች ጓደኞቼ የጓደኞቼ ሀሳብ ደግሞ ለእኔ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ ይህን በህብረት ያገኘሁትን እውቀት በማጎልበት እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ (ህይወት፣*8/02/06፣ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)፡፡

*...እዚህ ኮሌጅ ከቦረና፣ከባሌ፣ከምዕራብ አርሲ፣ከአርሲ ተሰባስበን የመጣን ነን፡፡በክፍል ትምህርቱ ሂደት ወቅት በቡድን ስንማማር ባህሎቻችንንም የምንለዋወጥበት ሁኔታ አለ፡፡ በአፋን ኦሮሞ ትምህርት ወቅት የምንጠቀምባቸው ቃላት እንደ ዘዬ አይነቶችን ሳይቀሩ አካባቢያችን ስለሚያመለክቱ ይህንንም እንድናወቅ አግዞናል፡፡ ለምሳሌ እኔ ከቦረና ስለመጣሁ የባሌ ተማሪዎች እንዴት አይነት ቃላት እንደሚጠቀሙ ትምህርት አግኝቻለሁ፡፡ እነሱም ከኔ ትምህርት አግኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የማናውቃቸውን ቃላት እንዲሁም ባህል እንድንለዋወጥ አግዞኛል ማለት እችላለሁ (ታሪኩ፣*8/02/06፣ ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)፡፡

*...በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማሬ በግሌ ያገኘሁት ነገር በአራቱም የቋንቋ ክህሎት በሚገባ መሻሻሎች ማሳየት እንድችል አግዞኛል ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ እርስ በርስ ስንደማመጥ የማዳመጥን ክህሎት አሳድጋለሁ፡፡ ስናገር ንግግሬን አሻሽላለሁ፤በጽህፈት በኩልም እንደዚያው ነው፡፡ በንባብም የተለያዩ የቤት ስራዎችን ለመስራት ከተለያዩ ጽሁፎች ከርዕሴ ጋራ የሚመሳሰሉትን ጽሁፎች በማንበብ አቀናጅቼ አቀርባለሁ፡፡ የዚህ ሁሉ አካሄድ በኔ ላይ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለውጥ ስላመጣልኝ ነው፡...የተለያዩ የዘዬ አነጋገሮችን ከተለያዩ ዞኖች አውቂያለሁ፣ ለምሳሌ በቦረና አነጋገር ውስጥ አይነኬ የሆነው ቃል በባሌ ውስጥ ሁሉም የሚጠቀሙበት መደበኛ ቃል መሆኑን አስተምሮኛል፡፡ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪው እንደ አንድ የዕውቀት ምንጭ በመሆኑ በትምህርቱ ውስጥ ትኩረት ማግኘቱ እንደፈለግሁት የራሴን ሀሳብ ለመስጠት ረድቶኛል፡፡ ይህ ሁኔታ አቅጣጫዎች ሁሉ ወደ ተማሪዎች በመሆናቸው የኔ አስተዋፅኦ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ቦታ እንዳለው አመላክቶኛል (አለሚቱ፣* 8/02/06፣ ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)፡፡

በማለት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መማራቸው ያስገኘላቸውን ጥቅም ገልፀዋል፡፡ ይህ የተማሪዎች ማብራሪያ አሁን ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው በዚህ አቀራረብ መማራቸው ምን ያህል ለውጥ እንዳመጣላቸው በሚገባ መረዳታቸውን ያስገነዝበናል፡፡ ይህ ደግሞ ከኮሌጅ ተመርቀው ወደ ስራ ከተሰማሩ በኋላ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሲመደቡ በዚህ ለውጦናል ባሉት መንገድ ባገኙት የቅድመ ስራ ግብዓት የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በአግባቡ ሊተገብሩ ይችላሉ፡፡ በእርግጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ብቻ ብቸኛው የለውጥ ማምጫ መንገድ ነው ተብሎ ባይወሰድም የመምህር-ተኮር አቀራረብም በራሱ መንገድ ፋይዳ እንዳለው በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ Moore (2002) እንዳብራሩት የመምህር-ተኮር አቀራረብ እንደ አንድ የማስተማር ብልሃት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ከነዚህ ውስጥ ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ብዙ ይዘቶችን በመዳሰስ

እውቀት እንዲገበዩ ማስደረጉ ነው፡፡ እነዚህ ዕጩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በህይወታቸው ለውጥ ያመጣላቸው ብቸኛው መንገድ እንደሆነ ማሰባቸውና ስለ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ አጉልተው መናገራቸው ምናልባት የመምህር-ተኮር አቀራረብም እንደ አንድ የማስተማሪያ አቀራረብ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ግንዛቤ ሳያገኙ ቀርተው ይሆናል፡፡

እንደ ዕጩ መምህራን አገላለጽ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማራቸው ካገኟቸው ጥቅሞች ውስጥ በአራቱም የቋንቋ ክህሎት በሚገባ መሻሻሎች ማሳየት መቻላቸው አንዱ ነው፡፡ የተማሪ-ተኮርን አቀራረብ ሳይረዱ በፊት እርስ በርሳቸው ትኩረት አይሰጣጡም ነበር፡፡ ነገር ግን ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከተረዱ በኋላ ሲደማመጡ የማዳመጥ ክህሎትን፣ ሲነጋገሩ ንግግራቸውን እንደሚያሻሽሉ፤ ከሚጽፉት የጽህፈት ክሂልንና በንባብም የተለያዩ የቤት ስራዎችን ለመስራት ከርዕሳቸው ግኑኝነት ያላቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ጋራ የሚመሳሰሉትን ጽሁፎች በማንበብ አቀናጅተው ለማቅረብ አስችሏቸዋል፡፡ ይህን ለውጥ ሊያመጣላቸው የቻለው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለመማር መቻላቸው ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪው እንደ አንድ የዕውቀት ምንጭ በመሆን በትምህርቱ ውስጥ ትኩረት ማግኘቱ እንደፈለጉት የራሳቸውን ሀሳብ ለመስጠት እንዳስቻላቸው እንረዳለን፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ሰልጣኞች በማሰልጠኛ ኮሌጁ ውስጥ ያገኙት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የስልጠና ግብዓት አንዳች ለውጥ ያስገኘላቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡ ከዚህ በመነሳት ለወደፊት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ተመድበው አፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩ አቀራረቡን በአግባቡ ስራ ላይ ሊያውሉት ይችላሉ ብሎ ማጠቃለል ያስችላል፡፡

### 5.2.8. የፕራክቲከም አተገባበር

በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም የመምህራን ማሰልጠኛ ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ ሊሰለጥኑ የሚገቡ የአንደኛ ደረጃ ዕጩ መምህራን መውሰድ የሚገባቸው ኮርሶች በቋንቋ ላይ ልዩነት ቢኖራቸውም በሌላው ተመሳሳይነት ይታያል፡፡ በተለይም የመምህርነት ሙያን እንዲላበሱ የሚያደርገው የተግባር ልምምድ /የፕራክቲከም/ ኮርሶች በሁሉም ቦታ ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በዚህ ኮርስ ዕጩ መምህራኑ በኮሌጁ ውስጥ ሆነው ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግቢ እውቀት ቀሰማ ጀምሮ እስከ አንድ የትምህርት ዓይነት ውስደው ማስተማር መቻል ድረስ የሚያበቃቸውን ስልጠና ያገኛሉ፡፡

ዕጩ መምህራኑ በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ  ውስጥ በሚቆዩባቸው ሶስት ዓመታት ውስጥ በተለያዩ የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ከሚሰጣቸው ትምህርቶች በተጨማሪ ከአንደኛ ዓመት ጀምረው የመምህርነት ሙያ የሚያጎናጽፋቸውን የፕራክቲከም ኮርሶች ያገኛሉ፡፡ ፕራክቲከም ዕጩ መምህራን በንድፈ-ሀሳብ የተማሩትን ስልጠና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ወደ ተግባር የሚለውጡበት ሂደት ነው፡፡ ይህም ትስስር ከስልጠና በኋላ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመድበው የሚያስተምሯቸውን ተግባራት እንዲለማመዱ ያደርጋቸዋል፡፡ ኮርሱ ዕጩ መምህራኑ በማሰልጠኛ ኮሌጅ ከገቡ ጊዜ ጀምሮ እስከ ምረቃ ጊዜያቸው ድረስ የሚተገበር ነው፡፡ የኮርሱን አጠቃላይ ይዘት፣ የሚሰጥበትን ዓላማና ወቅት ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

**ሰንጠረዥ አራት፡- በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የሚሰጡ የፕራክቲከም ኮርሶች፣ የሚሰጡበት ዓመት፣ የትምህርቱ ትኩረትና የሚፈጀው ጊዜ**

| *ተ.ቁ* | *የመምህርነት ኮርሶች* | *የሚሰጥበት ዓመት* | *የትምህርቱ ትኩረት* | *የሚፈጀው ጊዜ* |
|---|---|---|---|---|
| 1 | *ፕራክቲከም አንድ* (Prac. 201) | 1ኛ ዓመት | ከትምህርት ቤቶች ጋር መተዋወቅ | 4 ሳምንታት |
| 2 | *ፕራክቲከም ሁለት* (Prac. 202) | 2ኛናለማታው 3ኛ ዓመት | *በአማካሪዎች ስር ሆኖ መስራት* | 4 ሳምንታት |
| 3 | ፕራክቲከም ሶስት (Prac. 301) | 3ኛ ዓመት 1ኛ ሴሚስተር | የትምህርት ቤቶን አማካሪዎች ማገዝ | 4 ሳምንታት |
| 4 | ፕራክቲከም አራት (Prac. 30) | 3ኛዓመት 2ኛ ሴሚስተር | ራስን ችሎ ማስተማር | 4 ሳምንታት |

በሰንጠረዡ ውስጥ ዕጩ መምህራን ከፕራክቲከም አንድ እስከ አራት ድረስ ምን ምን ጉዳዮች ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ  እንደሚከተለው  ተብራርተዋል፡-

***ፕራክቲከም አንድ ኮርስ ቁጥር*** (Prac. 201)፡- ይህ ኮርስ በአንደኛ ዓመት  አንደኛ ሴሚስተር የሚሰጥ በመሆኑ ዕጩ መምህራኑ  የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለአራት ሳምንታት በመመልከት ስለትምህርት ቤት አጠቃላይ ዕውቀት እንዲያገኙ የሚረዳ ነው፡፡ በዚህ ኮርስ አማካኝነት ሰልጣኞቹ ወደፊት የሚሰማሩባቸውን ትምህርት ቤቶች በሚገባ እንዲተዋወቁ ይደረጋሉ፡፡ ለዚህም የትምህርት ቤቶቹን አቀማመጥ፣ የመማሪያ ክፍል አደረጃጀት፣የመማር-ማስተማር ሂደት፣ተጓዳኝ ትምህርቶችና ክበባትን፣የመርጃ መሳሪያዎች ማበልፀጊያ ክፍልና የመሳሰሉትን ይጎበኛሉ፡፡ በተጨማሪም በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መምህራንን የሚያስቸግሩ ጉዳዮችን በመመልከት እነሱ መምህራን ሲሆኑ ችግሮቹን

ለመፍታት እንዲችሉ ግብዓት ይሆናቸዋል ተብሎ ይታሰባል። ሰልጣኝ መምህራኑ ይህንን ልምምድ  በተከታታይ ለአራት ሳምንታት ከተመለከቱ በኋላ ወደ ኮሌጁ ተመልሰው የተመለከቱትን ሁሉ በጽሁፍ ዘገባ ያቀርባሉ። በዚህ ምልከታም ዕጩ መምህራኑ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመድበው ስራ ላይ ከመሰማራታቸው በፊት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት በመመልከትና በመለማመድ ወደ መማር-ማስተማሩ አቀራረብ ሲሸጋገሩ በቀላሉ የሰለጠኑበትን ተግባራዊ ሊያደርጉ ይችላሉ፤የተማራ-ተኮር አቀራረብንም ለመተግበር ጥሩ ግብዓት ያገኛሉ ማለት ነው።

***ፕራክቲከም ሁለት በአማካሪዎች (Mentor) ስር ሆኖ መስራት*** (Prac. 202)፡- ይህ ኮርስ ለሁለተኛ ዓመት መደበኛ ዕጩ መምህራንና ለሶስተኛ ዓመት የማታው መርሀ-ግብር  እጩ መምህራን የሚሰጥ ሲሆን በዚህም ማወቅ የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች የአማካሪያቸውን የመማሪያ ክፍል መመልከትና አማካሪያቸው የሚያስተምሩባቸውን የትምህርት መሳሪያዎች መገምገም ነው። በአጭሩ የኮርሱ ዓላማ ትምህርትን ማቀድና በትምህርት አሰጣጥ ሂደት እግረ መንገዳቸውን የትምህርት መሳሪያዎችን መገምገም ላይ ትኩረት ያደርጋል።

***ፕራክቲከም ሶስት የትምህርት ቤቶችን አማካሪዎችን (Mentors) ማገዝ***  (Prac.301)፡- ይህ ኮርስ በአንደኛው ሴሚስተር ለሶስተኛ ዓመት ዕጩ መምህራን የሚሰጥ ነው። ትኩረቱ የመምህራን ተግባራት የሆኑትን እንደ የክፍል ስራዎች፣ የፈተና ወረቀት ማረም፣ የተማሪዎችን የክፍል ቁጥጥር ማከናወን ወይም ስም መጥራት፣ የክፍል ውስጥ መቀመጫዎችን ማስተካከል፣ ቴስቶችን መስጠትና  ቲቶሪያል ለሚማሩ ተማሪዎች በተለይም ለሴቶች እገዛ እንዲያደርጉ መርዳት ነው። ይህ ኮርስ በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ቢያንስ ለአስራ አምስት ቀናት ተሰጥቶ ወደ ኮሌጅ በሚመለሱበት ወቅት ዝግበ-ጥናት (Portofoliyo) በማዘጋጀት ጽብረቃ እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ነው።

ከላይ የተጠቀውን የፕራክቲከም (Prac. 301)  ኮርስ አስመልክቶ የ3ኛ ዓመት የአፋን ኦሮሞ እጩ ሰልጣኞች በተለያዩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመድበው ያከናወኑትንና የተመለከቱትን የተለያዩ ተግባራት አከናውነው ዘገባቸውን ሲያቀርቡ  ከኮሌጁ አሰልጣኝ መምህርና አማካሪ ጋር በመሆን በክፍል ውስጥ በመገኘት ለማዳመጥ ችያለሁ። በአቀራረባቸው ላይ መሰረት አድርገው የሚያነሱት መረጃ በፕራክቲከም (Prac. 301) ሞጁል ውስጥ የቀረቡ ቅፆች ሆነው ከክፍል ውስጥ የማስተማር አቀራረብ እስከ

ተመለከቷቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ትምህርትን ጠንካራና ደካማ ጎን ግምገማ የሚደርስ ነው፡፡

ከመማር-ማስተማር አቀራረብ አንፃር በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውስጥ እንዴት በንቃት እንደሚሳተፉ፣ መምህራኑ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ተግባራዊ ሲያደርጉት የነበረውን የማስተማር ብልሃት ተመልክተው በተገቢው መንገድ ስለመተግበሩና ያለመተግበሩ አስተያየት እንዲሰጡበት የሚያደርግ ነው፡፡ በአጭሩ ሰልጣኞቹ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሄደው ምን እንደተማሩና ምን እንደታዘቡ የሚያመለክቱ ተግባራት ናቸው፡፡ ሰልጣኞቹ ዘገባቸውን ሲያቀርቡ ከተቆጣጣሪው አሰልጣኝ መምህር ጥያቄዎች በተጨማሪ እኔም ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አንፃር የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ችያለሁ ፡፡

***ፕራክቲከም አራት ራስን ችሎ ማስተማር፤ቁጥር (Prac. 302) ፡-*** ይህ ኮርስ ዕጩ መምህራኑ ወደ ስራ ሲሰማሩ የሚያስተምሩትን የትምህርት ዓይነት ወስደው በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተግባር የሚያስተምሩበት የተግባር ልምምድ መርሀ-ግብር ነው፡፡ ኮርሱ ዕጩ መምህራኑ ከተመደቡባቸው ትምህርት ቤቶች ጋር የትምህርት ዕቅድ በማውጣት የተግባር ልምምድ የሚያደርጉበት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ዕጩ መምህራኑ ቀስ በቀስ ራሳቸውን ችለው የሚያስተምሩበትና በንድፈ-ሀሳብ ደረጃ የተማሩትን ማንኛውንም ተግባር በክፍል ውስጥ የሚከውኑበት ነው፡፡ ይህ የማስተማር ልምምድ ለአራት ሳምንታት በተከታታይ ከተሰጠ በኋላ ያለፉት የማስተማር ሂደቶች ምን እንደሚመስሉ የሚፈተሹበት ነው ማለት ይቻላል::

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ተማሪዎች በንድፈ-ሀሳብ የተማሩትን በተግባር ልምምድ በማጠናከር የመማር-ማስተማር ሂደትን የሚያጠናክሩበት በመሆኑ በዚህ መስክ ዕጩ መምህራን ይህን መፈፀማቸው አግባብነት አለው፡፡ይህም በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በሚያስተምሩት ትምህርቶች ውስጥ እንዲተገብሩ መልካም ግብዓት ይሆንላቸዋል፡፡

### 5.2.9. በአሰለጣጠን ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ በተማሪ ተኮር አቀራረብ  አፋን ኦሮሞ ትምህርት ሲሰጥ ብዙ ጊዜ የሚከሰቱ ተግዳሮቶች መኖር አለመኖራቸውን ለአፋን ኦሮሞ መምህር ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። " ይህን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከመተግበር አንፃር ምን አይነት ችግሮች ገጥሟችሁ ያውቃል?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ

> *በዚህ በኩል አንድን ስራ በምናከናውንበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ እንከን ሳይኖር እፈጽመዋለው ማለት አስቸጋሪ ይሆናል። አንዳንድ ዕጩ መምህራን የሚሰጣቸውን የጽሁፍ ስራ በሌሎች ዕጩዎች እያሰሩ የሚመጡበት ጊዜ አለ። ሆኖም እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲከሰት የምንቆጣጠረው ወረቀቱን ለሚያቀርበው ዕጩ መምህር የተለያዩ መስቀለኛ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንደርስባቸው እንደገና አዲስ ስራ እንዲሰሩ እናደርጋቸዋለን (ዓለሙ ጫላ፣ /17/07/04፣ከ4፡00-5፡00 ሰዓት) ።*

በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ ዕጩ መምህራን የሚሰጣቸውን ስራዎች ራሳቸው ከመስራት ይልቅ ሌሎች ጓደኞቻቸውን ማሰራታቸው እንደ ተግዳሮት የታየ መሆኑን ከመምህሩ ቃለ-መጠይቅ ምላሽ ለማወቅ ይቻላል። በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርት ሲቀርብ ተማሪዎች በራሳቸው ችሎታ የሚያውቁትን ያህል መግለጽ ይገባቸዋል እንጂ በሌላ ተማሪ ላይ ጥገኛ መሆናቸው እንደ ችግር መነሳቱ አግባብ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ  የራሳቸውን ችሎታ በመጠቀም ያገኙትን ዕውቀት ለሌሎች ጓደኞቻቸው ያሻግራሉ እንጂ ለነጥብ ብቻ ብለው ጽሁፍ ገልብጠው ለመምህራን ማቅረብ የለባቸውም። ይህን ሁኔታ ለማስወገድ ለተማሪዎችም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል ማለት ነው ።

በመምህራን ኮሌጅ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲቀርብ የተለያዩ ተግባራት ሲሰጡ የተለያዩ እንቅፋቶች እንደሚያጋጥሟቸው በቡድን-ተኮር ውይይት የተሳተፉ ዕጩ መምህራን ገልፀዋል። ለምሳሌ፡-

> *በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስንማር የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ይኖራሉ። ለምሳሌ ከድክመቱ ብንጀምር ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎችን ሁሉ ተሳታፊ አያደርግም። ምክንያቱም በቡድን ውይይትም ይሁን በሌሎች ዘዴዎች ስንማር ደፋሮችና ተናጋሪዎች ተጽእኖ ስለሚያደርሱ አይን-አፋሮችና ንግግር ላይ የሚያዘግሙ*

*ሳይሳተፉበት ይቀራሉ፡፡ እነዚህ ተሳታፊ ያልሆኑ ተማሪዎች ባለመሳተፋቸው ከነሱ የሚጠበቀውን ሀሳቦች ያጎድላሉ (ተ3፣*8 /02/ 06፣ ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)

*ሌላኛው የተማሪ-ተኮር ውይይ ተሳታፊ ዕጩ መምህር ደግሞ …እንደኔ ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ውስጥ ተሳትፎ ጥረት በሚያደርጉ ተማሪዎች ላይ ብቻ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ቡድን ተግባር እንዲሰራው ሲደረግ በዚያ ቡድን ውስጥ የቡድኑ መሪ አወያይ፣ሀሳብ ሰጪ፣ ፀሀፊም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ በሁሉም ቦታ ላይ በሚያደርገው ተሳትፎ ለራሱ ሰፊ ዕውቀት እንዲያገኝ ያደርገዋል ማለት ይቻላል፡፡ በስተመጨረሻም ስራውን ሪፖርት ለማድረግ ከዚያ ተማሪ የተሻለ አቅራቢ ስለማይኖርና የስራው ሁኔታ ውጤት ስለሚያስገኝ ቡድኑን ወክሎ ዘገባውን ያቀርባል፡፡ ይህን የሚያደርግ ተማሪ እውቀቱ እየጨመረ ሲሄድ ተሳታፊ ያልሆኑት ግን ባለመሳተፋቸው ከነሱ የሚጠበቀውን ሳያወጡት ይቀራሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ድክመት መሆኑን ያሳያል (ተ4፣*8 /02/ 06 ፣ ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)፡፡ ሲል የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ደካማ ጎኖች አስረድተዋል፡፡

*እንደ ዕጩ መምህራ አገላለጽ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የቡድን ውይይት ወይም ሌሎችን ብልሃቶች ሲጠቀሙ ሁልጊዜ የቡድን አወያይ፣ ሁልጊዜ ሀሳብ ሰጪ ወይም ፀሐፊ ሆኖ የሚሳተፉ ተማሪዎች በአቀራረቡ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ የማይሳተፉ ተማሪዎች ግን ተጠቃሚ ያለመሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ ይህም በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች ጥቅም ስለሚያገኙበት የመሳተፍን አስፈላጊነት ተገንዝበዋል፡፡ ይህም ለወደ ፊት በስራ ላይ ሲሰማሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በሚገባ ለመተግበር የሚያበቃቸውን እውቀት ማግኘታቸውን ያስረዳናል፡፡ ዕጩ መምህራኑ በቡድን ውይይት ያብራሩት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መሳተፍ አስፈላጊና ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑን መገንዘባቸው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የማስተማሩን ሐላፊነት ሲወስዱ ለተማሪዎቻቸው ተሳትፎ ማድረግ ይተጋሉ ማለት ነው፡፡ በሌላ መልኩ ግን የመማር-ማስተማሩ ሂደት በተወሰኑ ተማሪዎች ተሳትፎ የሚካሄድ ከሆነ የብዙ ተማሪዎችን የዕውቀት ግብይት የሚያውክ ይሆናል፡፡ ዘገባዎች በአወያዩ ወይም በፀሐፊው የሚሠሩና ለውይይት የሚቀርቡ ከሆነ የሌሎቹ ሐላፊነትን ወስዶ የመማር ዕድል በእጅጉ የተገደበ ነው ወይም ጭራሹኑ የለም ማለትን ያመለክታል፡፡ ዐይነ-አፋርና ለመሳተፍ ቁርጠኝነቱ የሌላቸው ተማሪዎች በመማር-ማተማሩ ሂደት ውስጥ ተገቢ ቦታ አላገኙም ይህ ደግሞ በተራው የተማሪ-ተኮር ስለመኖሩ ጥያቄ ያጭራል፡፡*

በተጨማሪም ሰልጣኞች በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ እንደችግር ያነሱት የቡድን ውይይት ሂደት ላይ የሚከተለውን አክለዋል፡-

> *…አንድ ስራ ለአራት ወይም ለአምስት እንዲሰራ ሊሰጠን ይቻላል፡፡ ይህን ስራ ተቀምጦ በጋራ የመስራት ችግር በአንዳንድ ተማሪዎች ላይ ይታያል፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዓላማ ደግሞ ተማሪዎች በቡድን ትብብር እየሰሩ አንዱ ለሌላው ያለውን እውቀት እንዲያካፍልና የድርሻቸውን እንዲወጡ ያዛል፡፡ ሆኖም የአንዳንድ ተማሪዎች ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል፡፡ በቡድን ከመስራት ይልቅ በግል መስራትን የመምረጥ ሁኔታ አለ፡፡ የቤት ስራም ቢሆን በስምምነት የመስራት ሁኔታ አይስተዋልም፡፡ ሁሉም በአንድነት በስራው ላይ የመረባረብ ችግር አለ፡፡ ቡድን ስራ ላይም ሁሉም ተማሪዎች ካልተገኙ ሁለት ወይም ሶስቱ ተማሪዎች ሰርተው ምንም ነገር ያልሳተፉ እንደሰሩ ተደርገው ስማቸው ተመዝግቦ ለመምህራን ይቀርባል፡፡ ይህ እንግዲህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ውስጥ ያጋጠሙኝ ችግሮች ናቸው፡፡ (አህመድ ፣8/02/06 ፣ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)፡፡*

ከላይ በዕጩ መምህሩ የተገለፀው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ወቅት አንዳንዶቹ በጋራ የመስራት ችግር አለባቸው፡፡ ከችግሮቹም መካከል ያላቸውን እውቀት ለሌሎች ማካፈል ያለመፈለግና በተሰጠው ስራ ላይ ሳይሳተፉ በጋራ እንደሰሩ ሆነው መቅረብ ከተቀመጠለት የተማሪ-ተኮር መርህ አንፃር የጎደለ ነገር መኖሩን ያሳያል፡፡ Duffyና Kirkley (2004)፣ Kane (2004)ና Kim (2005) የገለፁትን ሁሉም ተማሪዎች በቡድናቸው ውስጥ እንደተፈለገው በንቃት ተሳትፈው ተግባራትን አይፈፅሙም አልያም ትብብር አያሳዩም፤ በአጭሩ በመማር ማስተማር ሂደቱ መካከል የራሳቸውን ጉዳይ ሲፈጽሙ ይስተዋላል የሚለውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ የራሱ አሉታዊ አንደምታ እንዳለው ያስገነዝባል፡፡

እንደ Stead (2005) አገላለፅ ስልጠና መስጠት ለአንድ ትምህርት ስኬት በየደረጃው ለሚገኙ መምህራን በየትኛውም የማስተማር ዘዴ ትግበራ ላይ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በርግጥ ሥልጠናው ለመምህራን ብቻ ተሰጥቶ የሚያበቃ መሆን የለበትም፤ የትምህርቱ ዋና ባለቤት የሆኑ ተማሪዎች ከሥልጠናው የሚጋሩዋቸው ግንዛቤዎች መኖር ያስፈልጋል፡፡ ይህም የተመረጠው የማስተማር ዘዴ ለትምህርታቸው ያለው ጠቀሜታ፣የተማሪዎቹ ድርሻ ምን መሆን እንዳለበትና እንዴት ሊማሩ እንደሚገባ ግንዛቤ ማስጨበጥ መምህራን

ከሥልጠና ያገኙትን የማስተማር ዘዴ ትግበራ በአግባቡ እንዲከውኑት ያግዛል፤ውጤቱም የሁለቱ የጋራ ይሆናል፡፡

## 5.3. የአንደኛ ደረጃ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ብልሃቶች አጠቃቀም

በዚህ የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄ የአፋን ኦሮሞ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ ምን ዓይነት ብልሃቶችን እንደሚጠቀሙ ለማወቅ የየትምህርት ቤቶቹ የክፍል ውስጥ አደረጃጀት፣የአፋን ኦሮሞ የመማር-ማስተማር አተገባበር፣ የአፋን ኦሮሞ መምህራኑ የስራላይ ስልጠና አገኛኘት፣ የመምህራን የተማሪዎች አገማገም ስልት፣ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች አስተያየት፣ የተመረጡ የትምህርት ኃላፊዎች የሰጡትን አስተያየቶች፣የተማሪው የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ዳሰሳ፣ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መምህራኑን ያጋጠማቸው ተግዳሮቶችና ለመምህራኑ የተደረጉ እገዛዎች መሠረት በማድረግ ይተነተናሉ፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጭብጦች በውስጣቸው በምዕራፍ አንድ ስር የተነሱ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ያቀፉ በመሆናቸው በመምህራን ኮሌጅ ስር የተነሱት ጭብጦች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በአጭሩ በምዕራፍ አራት ላይ እንደተገለፀው በንሞና የተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ7ኛ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች፣ርዕሳነ-መምህራን፣የመምህራን ልማት ተጠሪዎች፣ የተመረጡ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የክፍል ኃላፊዎች ለጥናቱ የመረጃ ምንጮች ሲሆኑ የተገኙትን መረጃዎች በጭብጥ በጭብጣቸው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ፡

### 5.3.1. የተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የክፍል ውስጥ አደረጃጀት

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ክንዋኔን ከመቃኘታችን በፊት ትምህርቱ የሚሰጥበት መማሪያ ክፍልና አካባቢ ምን እንደሚመስል መቃኘቱ አግባብ ነው ፡፡ ቅድሚያ ቅኝቱን ከኪጽጠቴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ስጀምር በምልከታ የታየው የ7ኛሀ መማሪያ ክፍል ንጽህና ጥሩ የመማር አውድ ፈጣሪ ነው፡፡ በተጨማሪም ንፁህ አየር ሊያስገባ የሚችል ሰፋፊ መስኮቶች፣ የተስተካከለ ወለልና ኮርኒስ በመልካም ድባብ የመማር-ማስተማር ሂደት እንዲከናወንበት አጋዥ እንደሆኑ ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን የተማሪዎች ቁጥር ከተደረደሩት ወንበሮች አንፃር ሲታዩ ተማሪዎች በቡድን ሆነው ለመወያየትና መምህሩ በተማሪዎች መካከል እየተዟዟሩ

እገዛ ለማድረግ ጥበቱ ሊያውካቸው ይችላል፡፡ ይህን የምልከታዬን ውጤት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በክፍሉ ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህር ትምህርቱን ሲያቀርቡ ክፍሉ አመቺ ስለመሆኑ ጥያቄ አቅርቤላቸው፡፡

> *…ችግር የፈጠሩብኝ የመቀመጫና የአግዳሚዎች ሁኔታ ነው፡፡ አግዳሚዎችና መቀመጫዎች ከተማሪዎች ቁጥር ጋራ ስለማይመጣጠኑ ማስታወሻ ለመውሰድ ያስቸግራል፡፡ እኛ በክፍል ውስጥ የምናስተምራቸው ተማሪዎች በቁጥር ከ50-70 ይደርሳሉ፡፡ (ባጫ መገርሳ ፣በ/07/09/05 ፣ከ7፡00-8፡00 ሰዓት) ፡፡*

እንደ መምህሩ አገላለጽ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር ከወንበሮቹ በላይ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር አዳጋች መሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአሊ ቢራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ የመማሪያ ክፍል አደረጃጀት ለመፈተሽ /በ18/07/2004 ምልከታ አድርጌ የመማሪያ ክፍሎቹን አመቺነት ለመቃኘት ሞክሬያለሁ፡፡

> *በምልከታው የ7ኛ ክፍል አጠቃላይ አደረጃጀት፣ የወንበርና የመደገፊያው አደራደርና የተያያዙና እንደ ተፈለገው ለማንቀሳቀስ ክብደት ያለው ይመስላል፡፡ የመማሪያ ክፍሉ ሰፋ ያለ በመሆኑ መምህራን ሳይጨናነቁ በተማሪዎቻቸው መካከል እየተዟዟሩ እገዛ ሊያደርጉላቸው የሚያስችል ነው፡፡ ተማሪዎች የሚቀመጡበት አግዳሚዎች አንዱ ለሶስት ተማሪ ተብሎ የተዘጋጀ ቢሆንም በምልከታ እንደታየው አንድ አግዳሚ ላይ ለአራት ተማሪዎች የሚቀመጡ በመሆኑ ዘና ብለው ለመቀመጥና ትምህርታቸውን ለመማር ምቹ አይደለም፡፡ የክፍሉ ሁኔታ ሲቃኝ የተሰባበረ የሲሚንቶ ወለል ያለው ሲሆን የክፍሉ መጠን ከያዘው የክፍሉ ተማሪዎች አንፃር ስፋት ያለው በመሆኑ ተማሪዎች የቡድን ውይይት ሲያካሄዱ መምህራን እንደፈለጉት እንዲንቀሳቀሱ ያስችላቸዋል፡፡ የመስኮቱ ስፋት በተፈለገው መጠን አየር ስለሚያስገባ በሙቀት ሰዓት ተማሪዎቹ ድካም ሳይሰማቸው ትምህርቱን በንቃት እንዲሳተፉ አግዟቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ መማሪያ ክፍሉ ኮርኒስ ያለው በመሆኑ በፀሐይ ወቅት የቆርቆሮ ግለት እንዲቀንስና በብርድ ጊዜ ሙቀት እንዲሰጥ ስለሚያግዝ የመማር-ማስተማሩ ሂደት ከዚህ አንፃር ችግር ያለበት አይመስልም፡፡ ነገር ግን የአግዳሚዎቹ መያያዝ መምህሩ የመቀመጫ አደራደርን ለወጥ አድርጎ በተለያዩ የማስተማር ብልሃት ማስተማር ቢፈልግ በፍጥነት ተግባራዊ*

*ማድረግ ሊያስቸግረው ይችላል (አሊ ቢራ፣ /በ18/07/2004፣ ከ6፡30-7፡10 ሰዓት)፡፡*

በምልከታ የታየው የመማሪያ ክፍል ስፋት ያለው ቢሆንም ተማሪዎች በአንድ መቀመጫ ለአራት ሲቀመጡ ተስተውሏል፡፡ ተማሪዎች ሳይጨናነቁ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉት ሁኔታዎች ሲያመቻችላቸው ነው፡፡ መምህርቷ በተለያዩ ብልሃቶች ለማስተማር ቢፈልጉ የመቀመጫዎቹ ክብደት ሊያንቀሳቅሳቸው እንደማይቻል ለመመልከት ተችሏል ፡፡ ስለዚህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትገበራው ከዚህ አንፃር የለም ማለት ነው፡፡

ሌላው ምልከታ የተደረገበት የሐውሾ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ቤት ከሮቤ ከተማ አስራ አምስት ኪሎ ሜትር የሚርቅና በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት ተመርቀው የሚያስተምሩ መምህር ያለበት ነው፡፡ እኚህ መምህር በትምህርት ቤታቸው ውስጥ አፋን ኦሮሞን እንዴት እያስተማሩ እንደሚገኙ ለሁሉም የአንደኛ ደረጃ መምህራን ምልከታ ስጠቀምበት የነበረውን የክፍል ውስጥ የመከታተያ ቅጽ ተጠቅሜ ምልከታ አድርጌ ያገኘሁት ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በሐውሾ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በምልከታ የታየው የአፋን ኦሮሞ የመማሪያ ክፍል ግርግዳ በጭቃ የተለጠፈና እሱም ከእርጅና የተነሳ ምርጊቱ ረግፎ ውጪ የሚከናወኑ ማናቸውም ነገሮች በክፍል ተቀምጦ በቀዳዳዎቹ ለማየት ያስችላል፡፡ ወለሉ ያልተስተካከለ ፒስታ መንገድ ይመስላል፡፡ የመማሪያ ክፍሉ ግርግዳ ተማሪዎች ሰርተው ወይም እንዲማሩበት ተብሎ የተለጠፈበት ነገር አይታይም፡፡ አፈር በመሆኑ ከመጥቆሩ የተነሳ በብርሀንም ቢሆን ጭለማ ያለ ይመስላል፡፡ የተማሪዎቹ መቀመጫና መደገፊያ የተያያዙ በመሆናቸው በተፈለገ ጊዜ የአቀማመጥ ለውጥ ቢያስፈልግ በፍጥነት ለማንሳት ያስቸግራል፡፡ መምህራንም ተማሪዎችን ለመርዳት ጥረት ሲያደርጉ እንደፈለጉት ለመዘዋወር ያዳግታቸዋል፡፡ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ያሉት ሰባት ቡድኖች ሲሆኑ በእያንዳንዱ ቡድን ፊለፊት የአፋን ኦሮሞ የመማሪያ መጽሐፉ በበቂ ሁኔታ ይገኛል (ሐውሾ፣ /በ22/03/2006፣ በ2፡40-3፡20)፡፡

በዜይበላ ትምህርት ቤትም በ28/07/04 በተደረገው ምልከታ የአፋን ኦሮሞ መምህር የመማር-ማስተማር አቀራረባቸውን ከማመልከታችን በፊት ትምህርቱ የሚሰጥበትን

የመማሪያ ክፍል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር አመቺ ስለመሆኑ መቃኘቱ አስፈላጊ ነው፡፡

ትምህርት ቤቱ የመማሪያ ክፍል ወለል አፈር ሲሆን ግርግዳው በጭቃ የተለሰነ መሆኑ ተስተውሏል፡፡ አደረጃጀቱን በተመለከተ የተማሪዎቹ መቀመጫ በሌሎች ትምህርት ቤቶች እንደተገለፀው የተያያዙ አግዳሚና መደገፊያ ያለው ነው፡፡በመቀመጫዎቹ ላይ አራት ተማሪዎች ስለሚቀመጡ የመጣበብ ሁኔታዎች ይስተዋላል፡፡ በክፍሉ ውስጥ መብራት ስለሌለ መስኮት ካልተከፈተ በቀር ይጨልማል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በመጽሐፋቸው ላይ የቀረቡትን መልመጃዎች አንብበው ለመስራት ወይም ለመፃፍ ያስቸግራቸዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ በዚያው ክፍል ውስጥ የሚማረውን ተማሪ "ለመሆኑ በዳመና ጊዜ እየፃፋችሁ ለመማር ትችላላችሁ?" ብዬ በጠየኩት መሰረት "መስኮቱ ካልተከፈተ በስተቀር በደንብ ማንበብ ወይም መፃፍ አንችልም፡፡ መስኮቱ ሲከፈትም በተለይ በዝናብ ጊዜ ብርድና ውሽንፍር ካለ ለመማር አያመቸንም፡፡" በማለት መልስ ሰጥቶኛል (ዜይ/ት/ቤት፣ በ28/07/04፣ በ4፡20-5፡00ሰዓት)፡፡

ከላይ በምልከታው እንደተብራራው የትምህርት ቤቱን የ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ የመማሪያ ስንመለከት ለመማር-ማስተማር ተግባር አመቺ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በሌሎች ትምህርት ቤቶች እንደታየው ሁሉ የመማሪያ ክፍሉ በቂ ብርሃን ያለመኖር የመቀመጫዎቹ ሁኔታ እንዲሁም የክፍሉ ወለል ተማሪዎች ዘና በማለት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያደርጉ ባለመሆናቸው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ ተጽዕኖ አድራሾች መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ ቢሆንም ተማሪዎች ከችግሮቹ ጋራ አብረው በመኖር ሁኔታውን በመለማመዳቸው እየተማሩበት ቢገኙም ትግበራው አለ ማለት አይቻልም፡፡

### 5.3.2.የአፋን ኦሮሞ መምህራን የመማር-ማስተማር ሂደት አተገባበር

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን ለማረጋገጥ በምልከታ ከታዩት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንዱ ኪጽጠቴ አንደኛ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ አፋን ኦሮሞ የሚያስተምሩት መምህር በቀድሞው የትምርት ስርዓት (በደርግ) ስልጠና ወስደው እንግሊዘኛና አማርኛ ቋንቋ ሲያስተምሩ ቆይተው ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ የአፋን ኦሮሞ መምህር ሆነው በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የሰሩ ናቸው፡፡ እኚህ መምህር በሚያስተምሩበት

7ኛሀ ገብቼ በምልከታ አንድ ላይ አጠቃላይ ከክፍል የውስጥ አደረጃጀት ጀምሮ የዕለቱን ትምህርት እስከሚያጠናቅቁ ድረስ ያሉትን ሁነቶች እንደሚከተለው እናያለን፡፡

በቅድሚያ እኚህ መምህር በቀድሞው ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ስልጠና ወስደው ወደ መምህርነት የገቡ በመሆናቸው ምናልባት በአፋን ኦሮሞ መምህርነት ሲቀየሩ ችግር ገጥሟቸው ከሆነ እንዲገልፁልኝ "በዚያ ጊዜ የደርግ ስርዓት የነበረበት የትምህርትና የአሰለጣጠን ሁኔታ ከአሁኑ ይለያል፡፡ ለመሆኑ እንዴት ነው አፋን ኦሮሞን እያስተማሩ የሚገኙት?" ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ፡-

> *…እኔ አፋን ኦሮሞን ያለምንም ችግር በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እያስተማርኩ ቆይቻለሁ፡፡ ቋንቋው የራሴ በመሆኑና ደስ ብሎኝ ስለማስተምር ችግር ገጥሞኝ አያውቅም፡፡ በመጀመሪያ በአማርኛ ቋንቋ ስልጠና ወስጄ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥም የማስተምረው አማርኛን ነበር፡፡ በኋላ ላይም 7ኛና 8ኛ ክፍልን እንግሊዘኛ ቋንቋ ነበር የማስተምረው፡፡ ይህን አፋን ኦሮሞን ስለምናገር እንጂ ስልጠና ወስጄበት አይደለም የማስተምርበት፡፡ ልክ አፋን ኦሮሞ በክልሉ ውስጥ እንደ አፍ መፍቻ በትምህርትነት እንዲሰጥ ከተባለ በኋላ ደስ ብሎኝ ስላስተማርኩት በሁለቱ ስርዓት ውስጥ የነበረው የስልጠና ልዩነት ምንም ችግር አልፈጠረብኝም (ባጫ መገርሳ፣ /07/09/05 ፣ከ7፡00-8፡00 ሰዓት) ፡፡*

እንደ አፋን ኦሮሞ መምህሩ አገላለጽ ለመጀመሪያ ጊዜ አፋን ኦሮሞን ማስተማር የጀመሩት ያለምንም ስልጠና ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የገጠማቸው ችግር እንደሌለ እያስተማሩ የሚገኙትም በተማሪ-ተኮር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ስልጠናውን በቀድሞ ስርዓተ-ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ቢወስዱም አፋን ኦሮሞ የራሳቸው ቋንቋ በመሆኑ ያለምንም ችግር በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እያስተማሩ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ላይ ስልጠና ወስደው በአፋን ኦሮሞ እንዲያስተምሩ መደረጋቸው በወቅቱ የነበረውን የአፋን ኦሮሞ መምህር ችግር ለመፍታት መፍትሄ ቢሆንም ቋንቋዎቹ መካከል ያሉትን ህግጋት ሳይረዱ ያለ ስልጠና አፋን ኦሮሞን ለማስተማር መሞከር አያሌ ክፍተቶች እንዲከሰቱ ሊያደርግ ይችላል፡፡

እኚሁ መምህር አፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙት የመማር-ማስተማር ብልሃት ምን እንደሆነ ጠይቄያቸው የሰጡኝ ምላሽ ፡፡

*...እኔ አፋን ኦሮሞን የማስተምርበት ብልሀቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ አንዳንዴ ተማሪዎችን ዘና በማድረግ፣ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ በተቀረፀው ትምህርት ላይ ብቻ ተወስኜ ሳይሆን በጥልቀት ከትምህርቱ ጋር ተያያዥ ከሆኑት ነገሮች ጋር አያያዤ በስነ-ቃል፣ በተረት፣ በእንቆቅልሽ ጋር አያይዤ እንዲማሩ አደርጋለሁ፡፡አንድ ቀን ትምህርቱን ካቀረብኩኝ ሌላ ቀን በመልመጃ ላይ ትኩረት አደርጋለሁ፡፡ ያንንም የመልመጃ ስራ አርማለሁ፡፡ ተማሪዎችም በዚህ አቀራረቤ ደስ እያላቸው ነው (ባጫ መገርሳ፣/07/09/05 ፣ ከ7፡00-8፡00 ሰዓት) ፡፡*

እንደ አፋን ኦሮሞ መምህሩ አገላለጽ አፋን ኦሮሞን በተለያዩ ብልሃቶች እያስተማሩ መገኘታቸውንና ይሄንንም መጠቀማቸው ተማሪዎቻቸውን ዘና እያደረጉ ለማስተማር መቻላቸውን ያስረዳሉ ፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ያሉትን የትምህርት ይዘቶች በመቀየር ተማሪዎች በሚፈልጉት መንገድ እንደሚያስተምሩ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ደስ እያላቸው እንዲማማሩ ለማድረግ ችለዋል፡፡ መምህሩ በተናገሩት መሰረት ተማሪዎችን ዘና በማድረግ ማስተማራቸው ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርህ አንፃር ተገቢ ነው፡፡ ይኸውም የተለያዩ ብልሃቶችን ተጠቅመው ማስተማራቸው የመማር-ማስተማር ግባቸውም እንዲፋጠን ያደርጋቸዋል፡፡ነገር ግን ተማሪዎችን ዘና በማድረግ ብቻ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተተግብሯል ማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ ይልቅ ተማሪዎች እንዲማሩት የቀረበላቸውን ይዘቶች በተማሪዎቹ እንዲቀርብ ተደርጎ ዘና የሚያደርጉ ተግባራት እንዲያክሉበት ቢደረግ የተሻለ ይሆናል፡፡

ከዚህ ገለጻቸው በመነሳት በመጨረሻ የእኝህን የአፋን ኦሮሞ መምህር የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር በምልከታ ለማረጋገጥ እንድወስን አድርጎኛል፡፡

ምልከታ አንድ፡- የትምህርቱ ትኩረት የግብርና ልማት በሚለው ምንባብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ መምህሩ ይህን የትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከፃፉ በኋላ የግብርና ልማት (Misooma Qonnaa) የሚለውን የትምህርት ርዕስ ማብራራት ጀመሩ፡፡ "የግብርና ልማት ማለት በሁለት እንደሚከፈል፣ እርሻ ማረስና እንሰሳት ማርባት እንደሆነ፣ እርሻ ማረስ ደግሞ በሁለት እንደሚከፈልና ባህላዊና ዘመናዊ አስተራረስ መሆናቸውን ራሳቸው አብራሩ፡፡ ከዚህ በኋላ...ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆነው በመማሪያ መፃፋቸው ውስጥ ገጽ 68 ላይ በሚገኘው ምንባብ ላይ እንዲወያዩና ከምንባቡ የተገነዘቡትን ነጥቦች በቡድናቸው የተረዱትን እዲያብራሩ አዘዙ፡፡...እንግዲህ "ስትወያዩ ድምጽ አታሰሙ ቀስብላችሁ" መሆን

አለበት፡፡ ለአስር ደቂቃ ሁሉም ምንባቡን እያነበቡ፣ እየተነጋገሩ ሰዓታቸው አለቀ (ባጫ መገርሳ፣/07/09/05 ፣ ከ7፡00-8፡00 ሰዓት)፡፡

መምህሩ ገና በትምህርቱ አጀማመር ላይ ለተማሪዎች ጥያቄ ወይም አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ ሲገባቸው ከተማሪዎቻቸው ቀድመው ገለፃ በመስጠት ጀመሩ ፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር የመምህሩ ንግግር በትምህርቱ መግቢያ ላይ ቢያስፈልግም የሳቸው ረዝሞ ተገኝቷል፡፡ ለምሳሌ ስለ ግብርና ልማት ምንነት በተማሪዎቹ የቀደመ ዕውቀት ሊገለፅና ሊብራራ ይገባል እንጂ መምህሩ መግለፅ አልነበረባቸውም፡፡ በተማሪው አፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በቅድመ-ንባብ ጥያቄ ለአንባቢ ተማሪዎች የቀረቡት "የአስተራረስ አይነቶች ምንድን ናቸው?፣ በአካባቢያችሁ ሰዎች የተሰማሩባቸው አስተራረስ ምን አይነቶች ናቸው?፣ የግብርና ልማትን ለማፋጠን ከገበሬዎቻችን የሚጠበቀው ምንድን ነው? ከግብርና አይነቶች ውስጥ የትኛውን አይነት ትወዳለህ? ለምን?" (ገጽ68) የሚሉ ሲሆኑ መምህሩ ግን እነዚህን ጥያቄዎች አልፈው የእለቱን የትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ወደ ማብራሪያ ገቡ፡፡ ይህም የተማሪ-ተኮር አተገባበር ክፍተት እንዳለ ያሳየናል፡፡ እርግጥ በአንድ ትምህርት ውስጥ የቀረቡ አዳዲስ ጽንሰ-ሀሳቦች ካሉ በመምህራን ማብራሪያ መጀመሩ አግባብ ቢሆንም ስለግብርና ልማት የተወሰኑ ነጥቦች በገጠር ተማሪዎች አንደበት ሳይነገር ወደ ገለፃ መግባታቸው ክፍተታቸውን ያመለክታል፡፡

ሌላው በዚሁ በምልከታ በታየው መማሪያ ክፍል ውስጥ ፣መምህሩ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ ትዕዛዝ ከሰጡ በኋላ፣ በየቡድኖቻቸው ውይይቱን ሲያካሄዱ ድምፅ ማሰማት እንደሌለባቸውና "ቀስ ብላችሁ ተወያዩ" ማለታቸው የተማሪ-ተኮር አቀራረብን የመማሪያ ክፍል ውስጥ ባህሪያትን በአግባቡ ካለመረዳት የመጣ ይመስላል፡፡ መማር-ማስተማሩ በውይይት ብልሃት የሚቀርብ ከሆነ የተማሪዎች ድምፅ መሰማት አይቀሬ ነው፡፡ ተማሪዎች ላይ ጫና ሳይደረግ የውስጥ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ከተፈለገ በፀጥታ ተወያዩ መባል የለባቸውም፡፡ ይህም የመምህሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ክፍተት ነው፡፡ ይህን አስመልክተው Zulukufና Trombly (2001) እንደገለፁት በመጀመሪያ በቱርክ ውስጥ በሚገኘው ኢኒኖ ዩኒቨርሲቲ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር እንደተጀመረ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ውይይት ሲያካሄዱ የክፍሉን ድባብ የተረበሸ ይመስል ስለነበር የዩኒቨርሲቲ ኃላፊዎች ሣይቀሩ ለአቀራረቡ ጥሩ አመለካከት እንዳልነበራቸው አመልክተዋል፡፡ በጥናታቸው እንዳረጋገጡት ግን ቀስ በቀስ ሁሉም ኃላፊዎች ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ

የክፍል ውስጥ ባህሪያት ስልጠናና ግንዛቤ እያገኙ ሲመጡ አመለካከታቸው እየተለወጠ መምጣቱን አስረድተዋል፡፡ በአጭሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የርስበርስ መራከብን የሚጠይቅ በመሆኑ ድምጽ መቀነስና መጨመር በራሱ በተማሪው እንጂ በመምህር የሚወሰን መሆን አይችልም፤ አይገባምም፡፡ ተማሪዎች በነፃነት የተሰማቸውን መነጋገር እንዲችሉ ሊገደቡ አይገባም፡፡ በተለይም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የንግግር ክሂል ማደግ የሚችለው ተማሪዎች በአንድ መልመጃ ላይ አውድ ፈጥረው በነፃነት መነጋገር ሲችሉ በመሆኑ መምህሩ ተማሪዎቻቸውን መገደብ የለባቸውም፡፡

በሌላ በኩል መምህሩ ለተማሪዎቻቸው ትዕዛዝ ሲያስተላለፉ በቡድን ሲወያዩ ስለ ባህላዊ አስተራረስ በሚገባ እንዲያስረዱ የሚጠይቅ ሲሆን ተማሪዎች ይህን ርዕስ ሊገልፁ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰበው ክፍል ውስጥ የሚገኙ አብዛኛው ተማሪዎች ራሳቸው የገጠር ልጆች ስለሆኑና ስለባህላዊ አስተራረስ ብዙ የሚያውቁት ነገር እንዳለ እንደሆነ አድርገው ነው ፡፡ " ሁላችንም የገበሬ ልጆች ነን" በማለት በሐረግ ገለፁ…በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ሁሉም ከተለያዩ ዳራ የተገኙ መሆናቸውና ሁሉም የገጠር ልጆች ሳይሆኑ ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተገኙ መሆናቸውን በመምህሩ ዘንድ ከግምት ውስጥ ያለመግባቱ ተስተውሏል፡፡

ተማሪዎች በተሰጣቸው የቡድን ስራ ላይ እየተወያዩ በነበሩበት ወቅት መምህሩ አንዳንድ ነጥቦችን ይናገሩ ነበር፡፡ንግግራቸውም ስለዘመናዊና ባህላዊ አስተራረስ ምንነት፣ የባህላዊ አስተራረስ ምን ያህል ጉልበት ጨራሽ እንደሆነ…ከተናገሩ በኋላ ተማሪዎች የተወያዩትን እንዲናገሩ ጋበዟቸው፡፡

ከቡድን ሀ.ሴት ተማሪ እየፈራች ተነስታ …ባህላዊ አስተራረስ እ…እ.. ስትል እንዳትፈራ በመምህሯ እየተበረታታች ቡድን አንድን በመወከል የተወያዩበትን ስለባህላዊ አስተራረስ ምንነት አቀረበች፡፡ መምህሩ በበኩላቸው የተማሪዋን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በሰፊው ገለፃ ሰጡ፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎቻቸው መናገር የሚገባቸውን ብዙ ነጥቦች ራሳቸው አብራሩ፡፡

መምህሩ ቀጥለውም ከላይ ቡድን አንድ ያቀረቡትን ስለባህላዊ አስተራረስ ከቡድን ሁለት ውስጥ ሀሳብ እንዲሰጡ ጠየቁ፡፡ በዚህ ጊዜ አንዲት ሴት ተማሪ እጅ አወጣች፤ ተፈቀደላትም፡፡ ተማሪዋ የቡድን አንድ ተወካይ እንደተናገረችው ሁሉ ስለባህላዊ

አስተራረስና ከብት እርባታ መናገር ስትጀምር ሀሳቧን ሳያስጨርሷት "በጣም ጎበዝ" ብለው አሁንም ራሳቸው በሰፊው አብራርተው ከዚያው ቡድን ውስጥ ተጨማሪ ሀሳብ ጠየቁ፡፡

…የቡድን ሁለት ተናጋሪዋ ሀሳቧን ማቅረብ እንደጀመረች አርፋጅ ተማሪዎች ወደ ክፍል እንዲገቡ ስለተፈቀደላቸው ንግግሯ የተረበሸ ይመስላል፤ ቢሆንም ግን ቀጠለችበትና ሀሳቧን ጨረሰች፡፡

መምህሩ ተማሪዋ የተናገረችውን ደግመው

> …ስለከብት እርባታ፣ ስለፈረስ፣ ስለላም፤ ስለበሬ፤ ወዘተ ከገለፁ በኋላ እነዚህን ሁሉ አንድ ላይ ማርባት እንደማያስፈልግ ገለፁ፡፡ ለምሳሌ ከከብት የሚፈለገውን ወተት፣ ስጋ፣ ቆዳ፣ ይህ ሁሉ በቂ ምግብ ከሌላቸው ፋይዳ እንደማይገኝባቸው አስረዱ፡፡ ከታመሙ ህክምና የማያገኙ ከሆነ፣ንፁህ ውሃ የማያገኙ ከሆነ ፣30 ፣40፣ 50 ከብቶች አሉት መባሉ ብቻ ፋይዳ እንደሌለው ተናገሩ፡፡ ስለዚህ ከከብቶቹ ጥቅማጥቅሞች ቢገኙም ከላይ ከተብራሩት ነጥቦች አንፃር የሚገባውን ያህል ፋይዳ እንደማይገኝበት ተናገሩ (ባጫ መገርሳ፣/07/09/05 ፣ ከ7፡00-8፡00 ሰዓት)፡፡

በማስከተል "ስለ ባህላዊ አስተራረስ ስለጨረስን አሁን ደግሞ ወደ ዘመናዊ አስተራረስ እንለፍ" አሉ፡፡…"ስለባህላዊ አስተራረስ በዚያኛው ቡድን በሚገባ ተብራርቷል፡፡ እስቲ በዚህ በኩል ያላችሁ ደግሞ (በሌላኛው ረድፍ ያሉትን ማለታቸው ነው) ስለ ዘመናዊ አስተራረስ ግለፁልን ?" በማለት መመሪያ ሰጡ፡፡

ከቡድን "ሐ" ሴት ተማሪዋ መናገር ጀመረች…ስለዘመናዊ አስተራረስ…እንግዲህ ለዘመናዊ አስተራረስ ይህ ቡድን በሚገባ ጠቀሜታውን ገልፀዋል፡፡…በወንድ ተማሪ…ስለዘመናዊ አስተራረስ ተጨማሪ ሀሳብ ተሰጠ…"እስቲ ከሌላ ቡድን ተጨማሪ ከየትኛውም ቡድን ተጨማሪ ሀሳብ ካለ ስለ ዘመናዊ አስተራረስ ግለፁ" አሉ፡፡ …አንድ ተማሪ እጅ ሲያወጣ ተፈቀደለትና…ሌሎች ከሱ ቀደም ብለው እንደተናገሩት ይህም ተማሪ ተጨማሪ ሀሳብ ሰጠ፡፡ "እስቲ የቀረ ነገር ካለ"… ብለው …ነገር ግን ራሳቸው መናገር ጀመሩ፡፡ "ለምሳሌ ዘመናዊ አስተራረስ እናንተም እንደተናገራችሁት በትራክተር፣ በማዳበሪያ…" ጥያቄ ጠይቀው ራሳቸው መናገር ጀመሩ፡፡ ከላይ ተማሪዎች ስለባህላዊ አስተራረስ በተናገሩት ነጥቦች ላይ ሰፊ ማብራሪያ ሰጡ፡፡ "በባህላዊ አስተራረስ ምርት ሲሰበሰብ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ አንድ

ሰው እያረሰ እያለ ዝናብ ይመጣበታል፡፡ያ ዓመቱን ሲለፋበት የነበረው በአንድ ቀን ሊበላሽበት ይችላል፡፡…ዘመናዊው አስተራረስ ግን እንደዚያ አይነት ችግሮች የሉበትም፡፡" በዚህ ላይ…በትምህርቱ የንባብ ትንተና ውስጥ በመግባት ሰፊ ጊዜ ወስደው ገለፁ፡፡

> *በዘመናዊ አስተራረስ መንገድ የተለያዩ አዝርዕቶችና ተክሎች ይተከላሉ፡፡ …እነዚህ ተሸጠው አገራችን ወደ ውጭ ልካ ምንዛሪ ታገኝበታለች፡፡ የግብርና ልማት በስሩ ሰፊ ነገሮችን ይዞ የሚገኝ ዘርፍ ነው፡፡ ለዚህ ነው መንግስትም በአምስት አመቱ መሪ ዕቅድ ውስጥ ለግብርናው ዘርፍ ትኩረት የሰጠው፡፡ ለእንዱስትሪና ለህይወታችንም መሰረቱ ግብርና ነው፡፡በተለያዩ መንገዶች ዘመናዊ አስተራረስ ትልቅ ገቢዎችን እያስገባ በመሆኑ ብዙ ባለሀብቶችም እየተሰማሩበት ነው፡፡ ገበሬዎች በውድድር እየተሸለሙበት ነው፡፡…*በማለት ማብራሪያ ይሰጡ ነበር *(ባጫ መገርሳ፣/07/09/05 ፣ ከ7፡00-8፡00 ሰዓት)፡፡*

በማለት በተማሪዎች ባሉበት ደረጃ ማወቅ የማይገባቸውን ሰፊ ሀሳብ በራሳቸው ይሰጡ ነበር፡፡ ቀጥለውም "…እንግዲህ ጥያቄ ወይም ያልተረዳችሁት ነገር ካለ" ብለው ጠይቁ፡፡ወይም "ከውይይታችን መካከል ሾልኮ ያመለጠ ነገር ካለ ለማዳመጥ ዝግጁ ነኝ" በማለት ተማሪዎችን በፈገግታ ተመለከቱ፡፡

…እዚያ ማዶ እሺ በጣም ጥሩ አሉና የተማሪውን ሀሳብ ማዳመጥ ቀጠሉ፡፡ጥያቄው የሚለው "የባህላዊው የከብት እርባታ በከብት ብዛት መታየቱ ጠቀሜታ የለውም የሚባለው ለምንድነው ?" አሉ፡፡

ተማሪውም "እንዲያውም ጥቅም የለውም ምክንያቱም እንደተነጋገርነው የሚገኘው ምርት በኋላ ቀር መንገድ በመሆኑ ቁጥር እንጂ ሌላ ጥቅም የለውም፡፡ቀንድ ከመቁጠር በስተቀር ሌላ ፋይዳ የለውም፡፡"ብሎ ሀሳብ ሰጠ፡፡

"አስቲ ሌላ ቡድን?" ብለው ጠየቁ፡፡ "እሺ"…አሉ ለሌላ ተማሪ እድሉን ሰጥተው፡፡ ተማሪውም" አለውም የለውምም" በማለት እንደ ጀመረ "አቦ አስደስተኸኛል…?"፡፡ "ኋላቀር ቢሆንም ያርስበታል፣ወተቱን ያገኛል፣ይህም ጥቅም ነው፡፡ " ብሎ…ሀሳቡን እንደገለፀ እንግዲህ የዛሬው ትምህርት በዚህ ላይ ያበቃል ብለው የሰዓታቸውን ማብቃት ተናገሩና እኔም ከክፍል ወጣሁ፡፡

በአጠቃላይ በምልከታ ከታየው የመማር-ማስተማር ሂደት የምንገነዘበው መምህሩ በቡድን ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ በተግባር የሚያስመስክሩ እንደሆኑ ከሀሳብ አቅራቢዎች ሴት ተማሪዎች ለማየት ተችሏል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎቻቸው እየተናገሩ እያለ ሀሳባቸውን ያለማስጨረስ ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ ክፍተት የፈጠረ ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪዎች ቡድናቸውን ወክለው ሀሳብ ለማቅረብ ሲነሱ መምህራቸው ደግሞ በመናገር ጣልቃ በመግባታቸው ሀሳባቸውን ሲያቋርጡ ተስተውለዋል፡፡ ሌላም በመማሪያ ክፍል በመምህሩ የትምህርት አቀራረብ የታዩት ግድፈቶች ተማሪዎች መናገር የሚገባቸውን ሀሳቦች ራሳቸው ሰፊ ጊዜ ወስደው ማብራራታቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ መምህሩ በትምህርት አቀራረባቸው ውስጥ ተማሪዎች እንዲናገሩ ከመፍቀድ ይልቅ ወደ ራሳቸው ገለፃ ትኩረት ማድረጋቸው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተተገበረ ያለ እንዲመስል አድርጓቸዋል፡፡ ሌላው በመምህሩ ላይ የታየው ክፍተት ሁሉንም ተማሪዎች ከአንድ አይነት የኑሮ ዳራ የተገኙ (የገበሬ ልጆች እንደሆኑ) አድርገው መውሰዳቸው ነው፡፡ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በዕውቀት፣ በባህል፣ በቋንቋ፣ በችሎታ ልዩነት እንዳላቸው ያለማጤ ናቸው ነው፡፡

ሌላው ምንባቦች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚቀርቡት ቋንቋን ለማስተማር ተብለው ነው፡፡ ምንባቡ ሲነበብ የንባብ ክሂልን፣ ተማሪዎች ሲወያዩበት ንግግርና ማዳመጥን እንዲሁም የሚፃፍ ነገር ካለ የፅህፈት ክህሎትን እንዲጎናፀፉ ተብለው ነው፡፡ በአጠቃላይ የተማሪዎቹን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማሳደግ ነው፡፡ ነገር ግን በዕለቱ የታዩት የመምህሩ የማስተማር አቀራረብ የእርሻ መምህር እስኪያስመስለው ድረስ በምንባቡ ማብራሪያ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ይህም በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የታየ ክፍተት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

የዕለቱ የትምህርት ርዕስ "በሽታን ማስታመም" (Wal'aansa Dhukubaa) የሚል ሲሆን ተማሪዎች በዚህ ስር የቀረበውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት "ያለፈውን ትምህርት ማስታወስ " የሚል በመምህሩ የትምህርት እቅድ ላይ ተጽፏል፡፡ ይህን የማስታወስ ተግባር በተማሪዎች ምላሽ መስጠት ይተገብሩታል ተብሎ ሲጠበቅ ነገር ግን መምህሩ ራሳቸው "ባለፈው የተማርነው …" በማለት ከተናገሩ በኋላ ዛሬ ደግሞ "በሽታን ማስታመም የሚለውን ምንባብ አንብበን ከውስጡ የወጡ ጥያቄዎችን እንመልሳለን" በማለት በአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሀፍ /ገጽ፣73/ እንዲያወጡ አዘዙ፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ *በቅድመ*

ንባብ ጥያቄ የቀረቡትን ጥያቄዎችን መምህሩ እያነበቡ ተማሪዎች እጅ እያወጡ እንዲመልሱ ለማድረግ /"የታመመ ሰው ምን ይሰማዋል?/፣/ የታመመ ሰው ምን የማድረግ ግዴታ አለበት?/ ፣ /ራስን ማከም ማለት ምን ማለት ነው?/" ብለው ጠየቁ፡፡ በዚህ ጊዜ አምስት ተማሪዎች እጅ አውጥተው የሚያውቁትን ሀሳብ ተራ በተራ ከተናገሩ በኋላ ወደ ዕለቱ ምንባብ አመሩ፡፡

ተማሪዎችም ምንባቡን በተናጠል ሆነው አንቀጽ በአንቀጽ አንብበው ካበቁ በኋላ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በቡድን መስራት ጀመሩ፡፡ የተማሪዎቹ የቡድን አመሰራረት በየወሩ የሚቀያየርና በአንድ ላይ የሚቀመጡበት በመሆኑ በማደራጀቱ ስራ ላይ ጊዜ አላጠፉም፡፡ በመሆኑም (ገጽ፣74) በመልመጃ ሁለት Aና B ስር የሚገኙትን በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን ምላሽ እንዲሰጡ የሚል በመሆኑ በቅድሚያ በ "A" ስር የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ተናጠል መልሰው በ "B"ስር የሚገኙትን ደግሞ ከምንባቡ የተገነዘቡትን በጽሁፍ አዘጋጅተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡ በመሆኑም ሁሉም ተማሪዎች በግል ያገኙትን ግንዛቤ ለመጻፍ ጥረት ያደርጉ ጀመር፡፡ ለአስር ደቂቃ በዚህ አይነት ተግባር ከቆዩ በኋላ እንደገና ተራ በተራ ሰባት ተማሪዎች የፃፉትን እንዳነበቡ በዕለቱ የተዘጋጀው የትምህርት ክፍለጊዜ በማብቃቱ በሚቀጥለው ቀን ከቆሙበት እንደሚያስጀምሯቸው ቃል ገብተው አበቁ (ባጫ መገርሳ፣ /10/09/05 ፣ከ7፡10-8፡00 ሰዓት)፡፡

በዕለቱ የተሰጠውን የትምህርት አቀራረብ ስንፈትሽ ለአምስት ደቂቃ ያለፈውን ትምህርት ማስታወስ፣ ለአስራ አምስት ደቂቃ ምንባቡን ማንበብ፣ ለአስር ደቂቃ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን መስራትና ያገኙትን ግንዛቤ ለመፃፍ አስር ደቂቃ ፈጅቶባቸዋል፡፡ ተማሪዎችን እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡና እንዲጽፉ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ቀደም ባለው ምልከታ በተማሪዎች ውይይት ትምህርቱን ቢያቀርቡም በዚህ ዕለት ግን በተናጥልና በቡድን ተጠቅመውባቸዋል፡፡ በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል እየገቡ እገዛ ለመስጠት ጥረት ሲያደርጉም ተስተውለዋል፡፡ በዘህ በኩል ጠንካራ ጎናቸው ጎልቶ ቢታይም የዕለቱን ትምህርት በአግባቡ ባለማቀዳቸው የተነሳ የሁሉንም ተማሪዎች ሀሳብ ሳይቀበሉና እጅ ያወጡትን ሳያስተናግዱ ሰዓታቸው በማለቁ ትግበራው ክፍተት እንዲያሳይ አድርጓቸዋል፡፡

ከዚህ ምልከታ በኋላ የታዩት ሁኔታዎች በዕቅዳቸው የተደገፈ ለመሆኑና ለሌሎች ከምልከታ ያመለጡትን ጉዳዮች ከመምህሩ ለማረጋገጥ በአሁኑ ጊዜ አፋን ኦሮሞ በምን

አይነት የማስተማር አቀራረብ እየተሰጠ ይገኛል? ብዬ ጠይቂያቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

> *በአሁኑ ሰዓት እንደትምህርት ቤታችንና እንደ መንግስትም ትኩረት ተደርጎበት ትምህርቱ የሚሰጠው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ሳስተምር ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በማስተምረው ትምህርት ይዘት ላይ በቡድን ተወያይተው ዘገባ እንዲያቀርቡ አደርጋለሁ፡፡ ይህን ዘገባ ከተቀበልኳቸው በኋላ መስተካከል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ሀሳብ ሰጥቼ ትምህርቱን እያቀረብኩ እገኛለሁ፡፡ ይህን ግንዛቤ በመጨበጤ ያለምንም ችግር እየሰራሁበት እገኛለሁ* (ባጫ መገርሳ፣ በ/07/09/05 ፣ከ7፡00-8፡00 ሰዓት)፡፡

ከተሰጠው ምላሽ የምንገነዘበው መምህሩ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አተገባበር የሚያስተምሩ መሆናቸውንና እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ እንደትምህርት ቤታቸውም የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እየተገበሩት እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡አቀራረቡን ሲተገብሩ የሚጠቀሙበትን ብልሃት ደግሞ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በተሰጣቸው ይዘት ላይ ተወያይተው ዘገባ እንዲያቀርቡ እንደሚያደርጉና ከዘገባው በኋላ መስተካከል በሚገባቸው ነገር ላይ ሀሳብ እንደሚሰጡ ተናግረዋል፡፡ ይህ ገለፃ መምህሩ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የቡድን ውይይትን እንደሚያዘወትሩና በተማሪዎች የሚቀርቡ ዘገባዎች ላይ ተማሪዎችን ሳያሳትፉ በራሳቸው ማስተካከያ ሀሳቦች መስጠታቸው በአተገባበሩ ሂደት ላይ ክፍተት መኖሩን ያመለክታል፡፡ ሁልጊዜ የቡድን ውይይትን መጠቀምና ሁልጊዜ የተማሪዎችን ዘገባ ማዳመጥ የመምህሩ የማስተማር ብልሃት ተመሳሳይ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለተማሪዎች ዘገባ ማስተካከያ ደግሞ ራሳቸው ከመናገራቸው በፊት ለተማሪዎች እድል ቢሰጥ አግባባዊ ትግበራ ይሆናል፡፡

በሐውሾ አንደኛ ትምህርት ቤትም የአፋን ኦሮሞ መምህር በ7ኛ ክፍል ትምህርቱን ሲያቀርቡ በዕለቱ ያቀዱት የቡድን ስራዎችን ሲሆን ይህንንም ትምህርት ለማቅረብ የተጠቀሙበት የማስተማር ብልሃት፣ በመጀመሪያ ተማሪዎች እንደፈለጉት እንዲቀመጡ ከፈቀዱ በኋላ በዕለቱ በስምንት ቡድን የሚሰሩ ስራዎችን ለማከፋፈል ለተማሪዎቹ ከአንድ እስከ ስምንት ቁጥር ሰጡ፡፡ በማስከተል ቁጥር አንድ የተሰጣቸው በአንድ ቡድን፣ ቁጥር ሁለት በቡድን ሁለት፣ ሶስት የተሰጣቸውም በቡድን ሶስት…እስከ ስምንት በዚያ መንገድ እንዲቀመጡ አደረጉ፡፡ ቀጥሎም በጥቁር ሰሌዳ ላይ የተፃፉትን በተሰጣቸው የቡድን ቁጥር መሰረት እንዲሰሩ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ጽሁፉ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙት ስምንት

ቡድኖች የሚሰሩትን ለይቶ የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን የቃላት ክፍሎች ከፃፉ በኂላ ሁሉም በየቡድናቸው በተሰጣቸው ስራዎች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉና በአስር ደቂቃ ውስጥ ተወያይተውበት በየቡድናቸው የተወያዩበትን እጅ እያወጡ ዘገባ እዲያቀርቡ የሚል ነው፡፡

**ሠንጠረዥ አምስት፡ በሀውሾ ትምህርት ቤት በክፍል ምልከታ የታዩ የትምህርት ይዘቶች**

| *ቡድን* | *የሚሰሩ የቡድን ስራዎች* | |
|---|---|---|
| | *በአፋን ኦሮሞ* | *የአማርኛ ትርጉም* |
| አንድ | Maqa Ibsoota | የስም ገላጮች |
| ሁለት | Maqaa | ስም |
| ሶስት | Sagalee Jabaa | የሚጠብቁ (ጠባቂ ድምጽ) |
| አራት | Jechoota Tishoo | ጥምር ቃላት |
| አምስት | Sagalee hudhaa | የላንቃ ድምፆች |
| ስድስት | Sagalee irrabutaa | የሚገደፉ ድምፆች |
| ሰባት | Akka galumsaatti hiika kennuu | አውዳዊ ፍቺ |
| ስምንት | Hima Ijaaruu | አረፍተነገሮችን መመስረት |

ተማሪዎችም እንደታዘዙት በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ተወያይተው ካበቁ በኂላ የደረሱበትን እጅ እያወጡ መናገር ጀመሩ፡፡ የቡድን ውይይት በሚያደርጉበት ወቅት መምህራቸው እነሱን ለማበረታታትና እገዛ ለማድረግ ሲዟዟሩ የመማሪያ ክፍሉ ጥበትና አግዳሚዎች መተላለፊያውን በመዘጋጋት እንቅፋት ሆኖባቸዋል፤ሆኖም ግን ተማሪዎች ተራ በተራ የተወያዩበትን ዘገባ ሲያቀርቡ፣ እርምት ሲቀበሉ፣ ሀሳብ ለመስጠት ሲጥሩ ተስተውለዋል፡፡

በዕለቱ የነበረውን የመማር-ማስተማር ሂደት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የመማሪያ ክፍል ተማሪዎች ዘና ብለው መምህሩ ደግሞ በቡድን ውይይት መካከል እየተዟዟሩ እገዛ ማድረግን የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ግን ሁኔታው ከዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ መምህሩ በአንድ ወገን ያሉትን ተማሪዎች ብቻ ሲረዱ ተስተውለዋል፡፡ ተማሪዎቹም ምልከታ ለማድረግ በዚያ ክፍል ውስጥ እንደምገባ የተነገራቸው ይመስል በዚያ ሁኔታ ውስጥ ተሳትፏቸው ተደናቂ ነበር፡፡ በመማሪያ መፃህፍት ስርጭት በኩል ለሁሉም ተማሪዎች የተዳረሰ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን ስናጤን ከመማሪያ ክፍሉ ጥበት፣ የውስጥ አደረጃጀት ችግሮች አንፃርና የተማሪዎች በክፍል ውስጥ

መብዛት የተነሳ  የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተቀመጠለት መርህ አንፃር ተተግብሯል ለማለት ያስቸግራል።

በዜይበላ ትምህርት ቤትም መረጃ የሰጡት የአፋን ኦሮሞ መምህር የሰላሳ ዓመት አገልግሎት ያላቸው ሲሆኑ የመምህርነት ስልጠና የወሰዱት በቀድሞው የትምህርት ስርዓት ነበር። በሂደት ግን በክረምት የስራ ላይ ስልጠና በአፋን ኦሮሞ ማስተማር ዲፕሎማ የያዙ ናቸው። በመሆኑም በተለያዩ የትምህርት ስርዓት በማስተማራቸውና ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አንፃር አጥጋቢ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው በመታሰባቸው በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር አቀራረባቸውን በምልከታ ለማየት ተሞክሯል። መምህሩ የክፍል ምልከታ ማድረግ  እንድችል ፈቅደውልኝ  ከገባሁ በኋላ  የሚከተሉት ሁኔታዎች መመልከት ተችሏል።

…የዕለቱ የትምህርት ርዕስ ደብዳቤ አፃፃፍ (Xalayaa Barreessuu) መሆኑን ጠቁመው የትምህርቱን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ። ቀጥለውም  "በቀረቡት ርዕሶች ላይ በየቡድናችሁ ተወያዩ " ብለው በአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ /ገጽ፣85/ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች አሳወቁ። ጥያቄዎቹም "/ደብዳቤ ጽፋችሁ ታውቃላችሁ?/፣/ ለማን ፃፋችሁ?/፣ /ለምን ፃፋችሁ?/፣ /የተፃፉት ደብዳቤዎች ሁሉ ተመሳሳይ መልዕክት አላቸው ወይስ ልዩ ልዩ መልዕክት አላቸው?/፣ /አላቸው ካላችሁ ልዩነታቸው ከምን ከምን ላይ ነው? /፣ /ደብዳቤ ሲፃፍ መነሻና መድረሻቸው ምንድነው?/ ና /ሰዎች ደብዳቤ ጽፈውላችሁ ያውቃሉ? " (ዜይበላ ፣ በ/29/09/04፤ከ8፡00-9፡00 )። የሚሉ ናቸው።

መምህሩም ከላይ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይተው እንዲሰሩ ካዘዙ በኋላ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በቡድን መወያየት ጀመሩ። በቡድን እርስ በርሳቸው ሲራከቡ በሚያሰሙት ድምፅ መምህሩ የመቆጣት ባህሪ ያሳዩ ነበር። እንዲያውም ሲወያዩ በሚያሰሙት ጫጫታ  "አትረብሹ" ብለው በቁጣ ስሜት  ተናገሩ። ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ በፀጥታ እያንሾካሾኩ መወያየቱን ቀጠሉ። ከአስር ደቂቃ ውይይት በኋላ ከየቡድናቸው ዘገባ ማቅረብ ጀመሩ። ተማሪዎች በየቡድኑ የተወያዩባቸውን ሪፖርት ሲያደርጉ በመጨነቅ ስለሚናገሩ የመምህሩ  ፍራቻ ያለባቸው ይመስላል። ተማሪዎች ዘገባ ሲያቀርቡ የማበረታቻና የማመስገን ቃላት  ሳያሰሙ የዕለቱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ በማብቃቱ ለመውጣት ተገደድኩ።

የዕለቱ የመማር-ማስተማር ሂደት ሲገመገም መምህሩ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርሆዎች አንፃር ትምህርቱን ተግባራዊ እንዳላደረጉት መረዳት ተችሏል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቻቸውን በነፃነት ወደ ትምህርቱ ማስገባት ሲገባቸው ማስፈራራቱና መቆጣት አግባብ አልነበረም፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርቱ ሲቀርብ ተማሪዎች ፍራቻ ሳይሰማቸው የሚያውቁትን ሀሳብ የመናገር መብት አላቸው፡፡ ምሁራንም ይህ ተግባራዊ እንዲሆን ይመክራሉ፡፡ ለምሳሌ Jones (2007) እንደገለፁት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርት የሚያቀርብ መምህር ተማሪዎቹን በአባታዊ ወይም ወንድማዊ መንፈስ ተማሪዎቹን መቅረብ፣ መርዳትና ማነሳሳት ይጠበቅበታል ፡፡ በዚህ መማሪያ ክፍል ውስጥ ይህ ተግባራዊ አልሆነም፡፡ ምክንያቱም  መምህሩ የተማሪ-ተኮር የክፍል ውስጥ ባህሪያትን በአግባቡ ያለመረዳት ሁኔታ ያለባቸው ይመስላል፡፡ ሌላው መምህሩ ከተማሪዎች ጋራ በመራኮብ ብዙ ቁምነገሮችን ከማስጨበጥ ይልቅ እሳቸው ዝምታን መርጠዋል፡፡የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የተማሪዎችና የመምህራንን ተራክቦ ቢጠይቅም እኚህ መምህር ግን ራሳቸው ከመናገር የተቆጠቡ ይመስላሉ፡፡

በዚህ ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍል ውስጥ የታዩትን ክፍተቶች ከመምህሩ አንደበት ለመረዳት በቀድሞ ስርዓተ-ትምህርት ስልጠና ወስደው በአዲሱ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ ሲያስተምሩ ያጋጠምዎት ችግር ይኖር ይሆን ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ "አዎ ምንም ችግር አልፈጠረብኝም፡፡" ብለው ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡ እሳቸው ችግር የለም ቢሉኝም በተግባር ሲታዩ  ከላይ እንደተብራራው ችግሩ ጎልቶ ይታያል፡፡

በዚሁ ትምህርት ቤት ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማሩ  እንዴት እየተከናወነ እንደሚገኝ መረጃ ይኖራቸዋል በማለት ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር፡፡እሳቸውም፤

> *በአጠቃላይ በትምህርት ቤታችን እየተተገበረ የሚገኘው የመማር-ማስተማሩ አቀራረብ እንደ ትምህርት ዓይነቱ ሊለያይ ይችላል፡፡ በሳይንስ ትምህርት ውስጥ የሚቀርብ የማስተማር ዘዴ በቋንቋ ላይ አጥጋቢ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም፡፡ በማህበራዊ ሳይንስም የሚተገበር የማስተማሪያ ዘዴ ይኖራል፡፡ ያም ሆነ ይህ በኛ ትምህርት ቤት ውስጥ እየተተገበረ የሚገኘው የማስተማር ዘዴ ተማሪን ማዕከል ያደረገው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው፡፡ ይህን አቀራረብ ለመተግበር በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት ዘዴ፣ በምልከታ ዘዴ ሊኖር*

*ይችላል። ይህ በተለይ ለማህበራዊ ሳይንስ በጣም ስራ ላይ እየዋለ የሚገኝ ነው። በሳይንስ ትምህርት ረገድም በሙከራዊ ዘዴና በጥያቄና መልስ የማስተማር ዘዴና የመሳሰሉት በስራ ላይ እየዋሉ ይገኛሉ (እሸቴ ድሪባ፣ በ/29/09/04፤ከ8፡00-9፡00 )።*

በርዕሰ መምህሩ አገላለጽ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ እንደ ትምህርት ዓይነቱ የሚለያይ ቢሆንም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተተገበረ ይገኛል። አቀራረቡን በሁሉም ትምህርቶች በተመሳሳይ መንገድ ስራ ላይ ማዋል እንደማይቻልና የሳይንስ ትምህርት አሰጣጥ ከቋንቋ ሊለይ ስለሚችል ተመሳሳይ አይሆንም።ያም ሆነ ይህ መተግበሩን ይናገራሉ።

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን በክፍል ውስጥ ለማረጋገጥ በአሊ-ቢራ ትምህርት ቤት የ7ሀ የአፋን ኦሮሞ መምህርት የዚህ ጥናት ተተኳሪ ናቸው ። መምህርቷ በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በአፋን ኦሮሞ ማስተማር ዲፕሎማ ያላቸው ናቸው።

ያቀረቡት የዕለቱ የትምህርት ይዘት ስለ "ምዕላድ፣ ምንነቱና የምዕላድ አይነቶች " ነበር። መምህርቷ ወደ ክፍል እንደገቡ በአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከገጽ 82-83 ባለው እንዲገልፁ አዘዙ። ቀጥለው በባለፈው ዕለት ስለ ምዕላድ ያስተማሩ መሆናቸውን አስታውሰው በዕለቱ ደግሞ ከዚያ የሚቀጥለውን ስለነፃ ምዕላድና ጥገኛ ምዕላድ ምንነት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የሚገኙት ጥያቄ አቀረቡ። ሁሉም ተማሪዎች ቀደም ብሎ በተመሰረተው በቡድናቸው ለ10 ደቂቃ ያህል እንዲወያዩበት በገለፁት መሰረት ተማሪዎች በሹክሹክታ መወያየት ጀመሩ። በመቀጠል ከየቡድናቸው አንዳንድ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ በመጠየቃቸው በቡድን ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ ማቅረብ ጀመሩ። በክፍል ውጥ ከሚገኙት ስምንት ቡድኖች መካከል ስድስቱ ሀሳባቸውን በተወካዮቻቸው እንዳቀረቡ የራሳቸውን ሀሳብ ለአስር ደቂቃ ያህል በማከል አቀረቡ። እንደ ገና መልመጃ ሶስት ላይ ያሉትን ጥያቄዎች የክፍል ስራ እንዲሰሩ አዘው በተማሪዎች ቡድን መካከል እየተዘዋወሩ እገዛ ሳያደርጉ የዕለቱ የትምህርት ሰዓት አበቃ። (አሊ ቢራ፣ 2004፣6፡30-7፡10 ሰዓት)

በአጠቃላይ በዕለቱ የነበረው የመማር-ማስተማሩ ሂደት ሲገመገም መምህርቷ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ተመስርተው የተዘጋጁበትን የትምህርት ርዕስ ለውይይት ማቅረባቸው አግባብ ነው። ነገር ግን ተማሪዎች መናገር የሚገባቸውን ሀሳቦች ሣያስጨርሷቸው ራሳቸው ረዥም ጊዜ ወስደው መናገራቸው ቅድሚያ ለተማሪዎች የሚለው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርህ

ተተግብሯል ማለት አይቻልም ። በተጨማሪም በተማሪዎች የቡድን ውይይት መካከል እገዛ ለማድረግ ከመዘዋወር ይልቅ አንድ ቦታ ቆመው በመጠበቅ ላይ ጊዜ ሲያጠፉ ተስተውሏል። ይህ ሁኔታ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አግባብ አንፃር ትክክል አይደለም። በተማሪዎች በኩል በቡድን ሆነው በመወያየት ሐሳባቸውን መግለጽ መቻላቸው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ብልሀቶች ውስጥ እንደ አንዱ ስለሚታይ ተገቢነት አለው። ነገር ግን ሁሉም የቡድን መሪዎች ሀሳባቸውን ሳይናገሩ የተመደበላቸው የዘገባ ጊዜ ማብቃቱ የእለቱ ትምህርት በጥንቃቄ ካለመታቀድ የመነጨ ይመስላል። በመሆኑም ከተጠቀሱት ተግባራት አንፃር በዚህ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአፋን ኦሮሞ መምህርቷ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ ያለመተግበሩን ያመለክታል።

የአንደኛ ደረጃ መምህራን የመማር-ማስተማር ተግባራት ሲገመገም በሁሉም ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ እያደረግን ነን ቢሉም በክፍል ምልከታ በታዩት መማሪያ ክፍሎች ውስጥ በቡድን ተማሪዎች እንዲወያዩ ከማድረግ ውጪ ሌሎች ብልሃቶችን ሲተገብሩ አልታዩም።

### 5.3.3. በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎች ሚና

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚማሩ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚሰሩት ተግባራትና እርስ በርስ ከሚያደርጉት ተራክቦ የተነሳ በመጪው ማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ ከሰዎች ጋራ በስራ መተባበርን፣ በውሳኔ ሰጪነትና ችግር ፈቺ ተግባራት ላይ የመሳተፍ ችሎታን ከመጎናፀፍ አንፃር ጠቀሜታ እንደሚኖረው በምዕራፍ ሶስት ላይ የመስኩ ተመራማሪዎች ዋቢ በማድረግ ለማሳየት ተሞክሯል። ከዚህ ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳታፊነት አንፃር በምልከታ ከታዩት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የአፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩ ተማሪዎቹ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ምን ተግባር ሲፈጽሙ እንደነበር ተቃኝቷል። በዚህ መሰረት በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውስጥ በትምህርቱ መግቢያ ላይ መምህራን ገለፃ ሲሰጡ ተማሪዎች አድማጭ ሆነው ተገኝተዋል። በቡድን የተሰጣቸውን ተግባራት ሲያከናውኑ ተማሪዎች ተሳታፊ ሆነው ሀሳብ ሲሰጡ ለማስተዋል ችያለሁ። በዚህ ወቅት ለመምህራቸውም ሆነ እርስ በርሳቸው ሀሳባቸውን ሲያቀርቡ ያለምንም ፍራቻ ይገልፁ ነበር። ነገር ግን በዜይበላ ትምህርት ቤት ተማሪዎች

በፍራቻ መንፈስ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተሳትፎ ሲያደርጉ የመምህራቸው ምጋቤ ምለሽ ሊታይ አልቻለም፡፡ በኪጽጠቴ ትምህርት ቤትም በመጀመሪያው ምልከታ አንዷት ቡድኗን ወክላ ሀሳቧን ልታቀርብ የነበረች ተማሪ በመጀመሪያ በፍራቻ የምትናገረውን መጀመር አቅቷት በመምህሯ ማበረታቻ ቃል ልትቀጥል ችላለች፡፡ ይህ ማበራታቻ ቃል በፍርሃት ወደ ተሳታፊነት ለማይገቡት ተማሪዎች መልካም ነገር ነው፡፡ በተማሪ-ተኮር ትግበራም ተመራጭ ነው፡፡

በኪጽጠቴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምልከታ ከተደረገበት የመማሪያ ክፍል በአመቺ ንሞና ዘዴ በተመረጡ አስራ ሁለት ተማሪዎች ጋር የቡድን ተኮር ውይይት ተደርጎ በአፋን ኦሮሞ የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ መምህራቸው እንዴት ትምርቱን እንደሚያቀርቡላቸው ለማወቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> *እንደክፍላችን የአፋን ኦሮሞ መምህራችን ስለምንማረው ትምህርት አንዳንድ ነጥቦችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከፃፉ በኋላ በቡድን በቡድን ሆነን እንድንወያይበት ያደርጉና የተሰጠንን ጉዳይ አብስለን እናቀርባለን (አብዲ፣በ07/09/05 ፣ከ7፡00- 8፡00 ሰዓት)፡፡*

> *…የኔ ሐሳብ እንደ ትምህርት ቤታችን አፋን ኦሮሞን ስንማር በመማሪያ መፃህፍ ውስጥ የቀረቡትን እንደ መመሪያው አየተወያየንበት የምንማር ሲሆን ከመጽሐፉ ውጪም አንዳንድ የሚጠቅመን ጉዳይ ላይ እየተወያየን እንማራለን፡፡ ትምህርቱንም ልዩልዩ ዘዴዎች በመፍጠር 1ለ 5 በሚባል ቡድን አመሰራረት እየተማርን እንገኛለን (ለሚ፣ በ07/09/05 ፣ ከ7፡00- 8፡00 ሰዓት) ፡፡*

> *…የዚህ የትምህርት ግብረ-ሐይል ፋይዳው በትምህርት ደከም የሚሉ ተማሪዎችን በዚያ ቡድን ውስጥ በማወያየት የመማር አቅማቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያደርግ ነው (ተማም፣በ07/09/05፣ ከ7፡00-8፡00 ሰዓት)፡፡*

እንደ ተማሪዎቹ አገላለጽ የአፋን ኦሮሞ መምህራቸው ትምህርቱን ሲያቀርቡላቸው በዕለቱ የሚያስተምሩትን የትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከፃፉ በኋላ የተፈለገውን ነጥብ በስፋት እንዲያብራሩና በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎች በቀረበው መመሪያ መሰረት በቡድን እየተወያዩበት እንዲማማሩ ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ከመማሪያ መፃህፍት ውጪም ለተጨማሪ እውቀት ለውይይት የሚያቀርቧቸው ርዕሶችም እንዳሉ ተናግረዋል፡፡ በመሆኑም እኚህ መምህር አዘውትረው የሚጠቀሙበት የማስተማር ብልሃት ወይም ዘዴ ውይይት መሆኑ ነው፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ የሚተገበሩ አያሌ ብልሃቶች ቢኖሩም እየተተገበረ የሚገኘው ግን የውይይት ብልሃት ነው፡፡

በመምህራቸው የትምህርት አቀራረብ ውስጥ ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ውስጥ አንድ ለአምስት የሚባል የቡድን አመሰራረት ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ የቡድን አመሰራረት ደካማ ተማሪዎችን በጎበዝ ተማሪዎች በመጠቀም እንዲበረቱ የሚያደርግ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘመን በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ ጠቃሚ ዘዴ ነው ተብሎ ተቀባይነት በማግኘቱ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የአፋን ኦሮሞ መምህሩ ይህን ግብረ-ሀይል በመጠቀማቸው የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ ስለማድረጋቸው በተጨባጭ የተገኘ መረጃ የለም፡፡

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ ትግበራ በመምህራንና ተማሪዎች ሚና ተሳትፎ ካልተደረገበት ውጤት አልባ እንደሚሆን የመስኩ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተማሪዎች የቡድን-ተኮር ውይይት አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲማሩ እንዴት እየተገበሩት እንደሚገኙ ለማወቅ ለዜይበላ ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የቡድን-ተኮር ውይይት ጥያቄ ቀርቦላቸው የተገኙ ምላሾች በሚከተሉት ሁኔታዎች ቀርበዋል፡፡ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎቹ በቁጥር አስራ ሁለት ሲሆኑ የተመረጡትም በአመቺ ንሞና ነው፡፡

> *በመጀመሪያ አመሰግናለሁ፣ የአፋን ኦሮሞ መምህራችን የሚያስተምሩን በማወያየት፣ገለፃ በመስጠት አንዳንዴ ደግሞ እኛው ተማሪዎች እርስ በርስ እንድንማማር በማድረግ ነው፡፡ በአጠቃላይ እኛ ከሰራን በኋላ ተጨማሪ ሀሳብ በመስጠት ያጠቃልላሉ፡፡ (አቤ፣28/07/2004 ፣ከ5፡00-6፡00 ሰዓት፡፡)*
>
> *መምህራችን አፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩ መማሪያ መጽሐፋችን እንድና ወጣ ያዙንና ምንባብም ከሆነ በመደዳ ተራበተራ እንድናነብ ያደርጉናል፡፡ከዚያም ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት ያሰሩናል፡፡ የሚያሰሩን ደግሞ አንዳንዴ በግል ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ግን በቡድን ነው (በለጡ፣28/07/2004 ፣ከ5፡00-6፡00 ሰዓት፡፡)*
>
> *...መምህራችን አፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩን በመማሪያ መጽሐፍ ላይ የሚገኙትን ጥያቄዎች ወይም ምንባብ ላይ በመመስረት ነው፡፡ አንድ ቀን ምንባብና ከምንባቡ የሚወጡ ጥያቄዎችን ሲያሰሩን ሌላ ቀን ደግሞ ሌሎች ጥያቄዎችን እንድንሰራ ያደርጉናል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ የቤት ስራ ሰጥተውን በሚቀጥለው ቀን የቤት ስራውን ተራ በተራ እየሰራን እንድንማር ያደርጉናል፡፡ በትምህርቱ ላይ በመመስረትም ታሪክ ይነግሩናል፡፡ በዚህ ምክንያት አፋን ኦሮሞን መማር ደስ ይለኛል(ሳፊ፣(ሳፊ፣28/07/2004 ፣ከ5፡00-6፡00 ሰዓት፡፡)*

*ከላይ ጓደኞቼ እንደተናገሩት መምህራችን የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መፃሐፍ ይዞ የማይመጣ ተማሪ ከክፍል ስለሚያስወጡ ሁላችንም መጽሐፍ ይዘን እንገባለን፡፡በዚህ መጽሐፍ ላይ ተመስርተው ነው ትምህርቱን የሚያስተምሩን፡፡መጽሐፉ ላይ የሚገኙት የጥያቄዎቹ ትዕዛዛት አንዳንዴ በቡድን፣በጥንድ ወይም በቡድን የሚሰሩ መሆናቸውን ጥቆማ ስለሚሰጡ በዚያ መሰረት ያስተምሩናል፡፡ አፋን ኦሮሞ የራሳችን ቋንቋ በመሆኑ ጥያቄዎቹን አንብበን እንሰራለን፤እናስተምራለን፤አድርጉ ያሉንን ነገሮች እናደረጋለን፡፡ (መሰረት፣28/07/2004፣ከ5፡00-6፡00 ሰዓት፡፡)*

ከተማሪዎቹ ውይይት የምንገነዘበው የዜይበላ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር ትምህርቱን ሲያቀርቡ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ተመስርተው መሆናቸውን ነው፡፡ በውይይቱ ሀሳብ የሰጡት ተማሪዎች እንደገለፁት ክፍል ገብተው ሲያስተምሩ በተናጠል፣በጥንድ ወይም በቡድን ተወያይተው እንዲሰሩ ያደርጓቸዋል፡፡በሌሎች ትምህርት ቤቶች እንደተመለከትነው ሁሉ በዚህ ትምህርት ቤትም አብዛኛውን ጊዜ በቡድን ማስተማር ጎልቶ ይታያል፡፡የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ የሚተገበሩ ሌሎች ብልሃቶች እንዳልታዩ ያመለክታል፡፡ይህ ሁኔታ ደግሞ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ ያልተተገበረ መሆኑን ያሳየናል፡፡

እንደተማሪዎቹ አገላለጽ የአፋን ኦሮሞ መምህሩ ታሪክም እየተናገሩ እንደ ሳፊ የአፋን ኦሮሞ ትምህርትን እንዲወዱ የሚያደርጉበት ጊዜም አለ፡፡ ከዚያ ባለፈ ግን በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡት ትዕዛዛት ስለሚመሯቸው አንዳንዴ ምንባብና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ሲሰሩ ሌላ ጊዜ የቤት ስራ ካልሆነም የክፍል ስራ እያሰሩ ትምህርቱን ያቀርባሉ፡፡በዚህ ምክንያት የመምህሩ የፈጠራ ችሎታ ሊታይ አልቻለም፡፡

ለተማሪዎቹ የቡድን ተወያዮች በዚህ መንገድ አፋን ኦሮሞን መማራችው ያስገኝላችው ጠቀሜታዎች መኖር ያለመኖራቸውን ለማወቅ ላቀርብኩላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

*…እኔ ከሰራሁ በኋላ መምህራችን ስለሚያሰሩን ትምህርቱን እንደ ክለሳ እቆጥረዋለሁ (ፋጡማ፣28/07/2004፣ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)፡፡*

*…ከመምህሬ ጋር ሐሳብ እንድለዋወጥና ከተማሪዎች ፊት ለፊት ወጥቼ ያለፍርሃት እንድናገር አድርጎኛል ፣በተጨማሪም ከክፍል*

*ጓደኞቼ ጋር ያለፍርሃት ሀሳብ እንድለዋወጥ አድርጎኛል (ለሚሳ፣28/07/2004፣ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)፡፡*

*የራሴ ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አሳውቆኛል፤ ...ለወደፊት ደግሞ ምንምን መስራት እንደአለብኝ አሳውቆኛል፡፡የመጀመሪያ ቋንቋዬ አማርኛ ነበር ነገር ግን ሁሌ በቡድኔ ውስጥ በመሳተፌ አፋን ኦሮሞ እንዳሻሽልና የኦሮሞን ባህል በሚገባ እንድረዳ አድርጎኛል በተጨማሪም በአፋን ኦሮሞ ማንበብ፣ መፃፍና መመራመር እንድችል አድርጎኛል (ረድኤት፣28/07/2004፣ ከ5፡00-6፡00 ሰዓት)፡፡*

ከተማሪዎቹ አገላለጽ፣ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን መማራቸው ንግግራቸውን እንዳሻሻለላቸውና በዚህም ሁኔታ ደስተኞች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ የተማሪዎቹ መልሶች አፋን ኦሮሞን በሚገባ መናገር የማይችሉ ተማሪዎች ሣይቀሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ብልሃት የሆነውን የቡድን ውይይት ተጠቅመው መማራቸው የአፋን ኦሮሞ ንግግራቸው ተሻሽሎ እንደሚገኝ ያሳያል፡፡ ይህም ሁኔታ Weimer (2002) የተማሪ-ተኮር ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ከተፈለገው ግብ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋል ያሉትን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ ነገር ግን ትምህርቱ በቡድን ውይይት ብቻ ተማሪዎች እንዲራከቡ መደረጉ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ክፍተት እንዲፈጠርበት አድርጎታል፡፡

## 5.3.4. በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የመምህራን የምዘና ስልት

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሂደት ውስጥ መምህራን ተማሪዎቻቸውን የሚመዝኑበት ብልሃት አላቸው፡፡ በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ በምን አይነት መስፈርት ተግባራዊ ሲያደርጉ እንደነበር በ (5.2.5 ርዕስ) ሥር ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ይህ ጥናት ታላሚ ባደረጋቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች እንደተሰበሰበው መረጃ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በተለያዩ መንገዶች ይመዝናሉ፡፡ ምዘናን አስመልክቶ ተማሪዎቻቸውን እንዴት እየመዘኑ እንደሚገኙ ለኪጵጠቴ ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል አፋን ኦሮሞ መምህር ላቀርብኩላቸው ጥያቄ ሲመልሱ

*በክፍል ውስጥ ምዘናውን የምናካሄደው የተከታታይ ምዘና ብልሃት ነው፡፡ ይኸውም በሙከራዎች፣ በፈተና፣የቤት ስራ በመስጠት፣ የክፍል ስራዎች፣ የቡድን ስራዎችና ፕሮጀክቶች*

*ይገኙበታል። በዚህ ነው ተማሪዎቻችንን የምንመዝነው። በነዚህ በተለያዩ መንገዶች ከመቶ እስከ 60% ድረስ ጨርሰን በመጨረሻም 40%ቱን የማጠቃለያ ፈተና በመስጠት እንለያቸዋለን። ብለዋል* (ባጫ *መገርሳ* በ/07/09/05፣ ከ7፡00-8፡00 *ሰዓት)።*

በተመሳሳይ ሁኔታ የሀውሾ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህርም የተማሪዎች የምዘና ስልታቸው በተከታታይ ምዘና ላይ የተመሰረተ መሆኑን አብራርተው ይህም የክፍል ተሳትፎን፣ የቡድን ስራዎችን ፣ የቤት ስራዎችን ወዘተ እንደሚያጠቃልልና ተማሪዎች ከፈተና ውጪ የሚመዘኑበት ስልት መኖሩን ገልፀዋል። የማጠቃለያው ፈተና ከመቶው 30% ብቻ እንደሆነ፣ 70%ቱ ልዩ ልዩ የተማሪዎችን ተሳትፎዎች የሚያተኩርና ተማሪዎቻቸውን በዚህ ሁኔታ እንደሚመዝኑ ገልፀዋል። በአሊቢራና ዜይበላ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን የምዘና ስልትም ከላይ በሁለቱ ትምህርት ቤቶች እንደተገለፀው በተከታታይ ምዘና ስልት ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

በአራቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ መምህራን የሚጠቀሙበት የምዘና ስልት ተከታታይ ምዘና ቢሆንም የኪጵጠቴውና አሊ ቢራው መምህራን እስከ 60% ድረስ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ሲያደርጉ የሐውሾውና የዜይበላው ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን ደግሞ 70% ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ከመምህራኑ መልስ ለመረዳት ይቻላል። ምንም እንኳን የ10% ልዩነት ያለው ቢሆንም ከትምህርት ቤቶቹ ርዕሰ መምህራን ከትምህርት ቤቶቹ የተገኙት የምዘና መመዝገቢያ ቅፆች ላይ ያሉት መስፈርቶች የተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥ ማለቅ ያለበት 70%ቱ ነው። ይህ በመምህራኑ መካከል ያለው ልዩነት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይም የአተገባበር ልዩነት ሊፈጥር ይችላል።

### 5.3.5. የተማሪው አፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ዳሰሳ

የአፋን ኦሮሞ መምህራንን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ለማረጋገጥ ከክፍል ውስጥ ምልከታ፤ ከቃለ-መጠይቅ፣ ለተማሪዎች በቀረቡት የቡድን ተኮር ውይይትና በሰነድ ትንተና መረጃዎች ተሰብስበዋል። በሰነድ ትንተና ከተፈተሹት መረጃዎች ውስጥ አንዱ የ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ የተማሪው መጽሐፍ ነው።መማሪያ መጽሐፉ መምህራንና ተማሪዎችን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አሳታፊ መሆን አለመሆኑን

አረጋግጦ ከመደምደሚያ ላይ መድረስ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሲዘጋጁ መምህራንና ተማሪዎችን አሳታፊ መሆን እንዳሚገባቸው በክለሳ ድርሳን ስር የተመለከትናቸው የመስኩ ምሁራን ይመክራሉ፡፡ ለምሳሌ Nunan (1988)፣ McComb'sና Whisler (1997) እንደገልፁት ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ የስርዓተ-ትምህርት መሳሪያዎች መዘጋጀት ያለባቸው ተማሪዎችን ማዕከል ባደረገና ፍላጎታቸውን ጠብቆ ተግባራቱን በራሳቸው እውቀት መማር እንዲችሉ ተደርገው መቅረብ ነው፡፡ ስለዚህ የቀረቡት ይዘቶች መምህራንና ተማሪዎችን አሳታፊ ሆነው መዘጋጀታቸውን፣ የቀረቡት ትዕዛዛት ተማሪዎች በምን ዓይነት ብልሃት መስራት እንደሚገባቸው ፍንጭ የሚሰጡ ስለመሆናቸው፣ የመመሪያዎቹ ግልጽነትና የተለያዩ ክህሎቶችን የሚያጎናጽፉ ስለመሆናቸው በመፈተሽ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ አንፃር የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ላይ ሀሳብ መስጠት አስፈላጊ ጉዳይ ነው ፡፡

በጥናቱ የተዳሰሰው የመማሪያ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ1996 ዓ.ም ለ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ በዚህ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ የተማሪ-ተኮር አተገባበር የተግባራት አሳታፊነት አንፃር ስንመለከት መምህራን በቃለ-መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት "ትምህርቱን በተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች እናቀርባለን" ያሉትን ምላሽ ለማረጋገጥ ሲባል ነው፡፡ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች መምህራኑ ካብሯሯቸው ሐሳቦች ጋር መጣጣም አለመጣጣማቸውን ለመፈተሽ ከመጽሐፉ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ምዕራፍ ድረስ ያሉት የመጻህፉ መልመጃዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር በሚመች መልኩ መቅረብ አለመቅረባቸውን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

የአፋን ኦሮሞ መማሪያ የተማሪው መጽሐፍ 24 ምዕራፎችና 107 ገፆች አሉት፡፡አዘጋጆቹ ደግሞ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፉ ሲታይ ከምዕራፍ አንድ እስከ ሃያ አራት ድረስ በግላዊ ተሳትፎ የሚሰሩ መልመጃዎች 80% በመሆናቸው ከፍ ብለው ተገኝተዋል፡፡ በቡድን ተወያይተው የሚሰሩት ደግሞ 22% ሲሆኑ በመጠኑ አነስ ብለው ተገኝተዋል፡፡ በክርክር፣ በድራማና በዘገባ አቅርቦት ተደግፈው ለክፍሉ ተማሪዎች የሚቀርቡት መልመጃዎች ደግሞ በጥቂቱ ታይተዋል፡፡ ሙሉ መረጃውን ከሚከተለው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

### ሠንጠረዥ ስድስት፡- በሰባተኛ ክፍል የተማሪው የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ምዕራፎች፣ መልመጃዎች የማስተማሪያ ብልሃቶች

| ተ.ቁ | ምዕራፍ | መልመጃዎች | በግል የሚሰሩ | በጥንድ የሚሰሩ | በቡድን የሚሰሩ | ከሙሉው ክፍል ጋራ የሚሰሩ | በክርክር የሚማሩት | ያልታወቁ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምዕራፍ አንድ | 6 | 4 | 1 | - | 1 | - | |
| 2 | ምዕራፍ ሁለት | 8 | 8 | - | - | | - | |
| 3 | ምዕራፍ ሶስት | 10 | 9 | 1 | - | | - | |
| 4 | ምዕራፍ አራት | 7 | 7 | - | - | | - | |
| 5 | ምዕራፍ አምስት | 9 | 8 | 1 | - | | - | |
| 6 | ምዕራፍ ስድስት | 9 | 5 | 3 | 1 | | - | |
| 7 | ምዕራፍ ሰባት | 10 | 6 | 3 | 1 | | 1 | |
| 8 | ምዕራፍ ስምንት | 6 | 5 | 1 | - | | - | |
| 9 | ምዕራፍ ዘጠኝ | 9 | 6 | 3 | | | - | |
| 10 | ምዕራፍ አስር | 5 | - | 2 | 3 | | - | |
| 11 | ምዕራፍ አስራ አንድ | 8 | 8 | - | - | | - | |
| 12 | ምዕራፍ አስራ ሁለት | 6 | 5 | 1 | - | | - | |
| 13 | ምዕራፍ አስራ ሶስት | 6 | 6 | - | - | | - | |
| 14 | ምዕራፍ አስራ አራት | 8 | 7 | 1 | - | | - | |
| 15 | ምዕራፍ አስራአምስት | 8 | 8 | - | - | | - | |
| 16 | ምዕራፍ አስራ ስድት | 6 | 4 | 1 | 1 | | - | |
| 17 | ምዕራፍ አስራ ሰባት | 9 | 6 | 2 | 1 | | - | |
| 18 | ምዕራፍ አስራ ስምንት | 6 | 6 | - | - | | - | |
| 19 | ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ | 6 | 6 | - | - | | - | |
| 20 | ምዕራፍ ሀያ | 5 | 3 | 1 | 1 | | - | |
| 21 | ምዕራፍ ሀያ አንድ | 5 | 4 | 1 | - | | - | |
| 22 | ምዕራፍ ሀያ ሁለት | 5 | 4 | 1 | | | - | |
| 23 | ምዕራፍ ሀያ ሶስት | 6 | 5 | 1 | | | - | |
| 24 | ምዕራፍ ሀያ አራት | 3 | 3 | - | | | - | |
| | ጠቅላላ | 166(100%) | 133(8o.1%) | 23(34.9%) | 8(122%) | 1(1.52%) | 1(1.52%) | |

ከሰንጠረዥ ስድስት የምንገነዘበው በ7ኛ ክፍል የተማሪው የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች በጠቅላላው 166 (100%) ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 133 (80.1%) መልመጃዎች በግል የሚሰሩ ሲሆኑ 23 (34.9%) መልመጃዎች ደግሞ በጥንድ የሚሰሩ ናቸው፡፡ በቡድን ውይይት የሚሰሩ ደግሞ 8 (12.12%)፣ ሲሆኑ ከሁሉም የክፍሉ መማሪያ ክፍል ተማሪዎች ጋር የሚሰሩት መልመጃዎች ደግሞ 1 (1.52%) እንዲሁም በክርክር የሚማሩት 1(1.52%) መልመጃ ተመልክተዋል ፡፡ ስለሆነም የአፋን ኦሮሞ መምህራን በቃለ-መጠይቁ ምላሽ ላይ በተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እየተገበርን ነን ብለው ቢናገሩም ከመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች አቀራረብ አንፃር ግን በተለያዩ ብልሃቶች የሚሰሩ መልመጃዎች በጣት የሚቆጠሩና እንደሌሉ የሚያመለክቱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ጥያቄ መጠያየቅ፣ አስተያየት መሰጣጣትና የመምህራን

አስተያየት የሚሰጥባቸው መልመጃዎች ስለመኖራቸው የመልመጃዎቹ መመሪያዎች ላይ የተገለፁ ትዕዛዛት ያመለክታሉ፡፡

ምሣሌ፡- Yaada armaan gadii gabaasaa Walhubachiisaa.

ከዚህ በታች በቀረቡት የአረፍተነገሮች ሀሳብ በአጭሩ እርስ በርሳችሁ ተገነዛዘቡ፡፡(ገጽ፣27)

Bineensa yookiin beeyladaa beektu tokko filadhuutii Waa'ee bineensichaa gumee qopheessi. gumee qopheessite hiriyaa keetiif kenni.Inni yookiin isheen kan qopheesse/ssite immo ati fudhadhu. Booda gumee walii kennitan irratti keyyattoota lama lama barreessaatii barsiisaadhaaf dhiyeessaa.

የምታውቀውን አንድ የቤት ወይም የዱር እንስሳ መርጠህ ስለዛ እንስሳ አስተዋጽኦ አዘጋጅ፤ ያዘጋጀኸውን አስተዋጽኦ ለጓደኛህ ስጠው፡፡ እሱ ወይም እሷ ያዘጋጁትን አንተ ውሰድ ፡፡ በመቀጠል በተሰጣጣችሁ አስተዋጽኦ ላይ ሁለት ሁለት አንቀፆች ፃፉና ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡ (ገጽ፣84)፡፡ዓይነቶች ናቸው፡፡

ከሠንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተማሪዎቹ ግላዊ ተሳትፎ የሚገለፅበት መልመጃዎች በቁጥር በዝተው ታይተዋል፡፡ በዚህ ግላዊ ተሳፎ ውስጥ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች የሚያሳድጉ ተግባራት ተካተዋል፡፡ ለምሳሌ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በምዕራፍ አስር (ገጽ፣45-47) ስር የቀረቡት መልመጃዎች በንግግርና ውይይት ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎችን በማቅረብ ይጀምራሉ፡፡ በማስከተል የውይይት ስርዓት መመሪያዎችን በዝርዝር እናገኛለን፡፡ ከዚያም በቀረቡት የውይይት ስርዓት መመሪያዎች መሰረት መልመጃ አንድ (ገጽ፣46) ተማሪዎች በቡድን ሆነው ውይይት እንዲያደርጉ ትዕዛዙ ተጽፏል፡፡ በዚህ ስር ስለ ውይይት ደንብና ስርዓት፣ ተወያዮች እንዴት ወደ መቋጫ ሀሳብ ማምራት እንደሚገባቸው እንደ ትምህርት ርዕስ ቀርቧል፡፡ በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች በህይወታቸው ዘመን ውይይት ማከናወን እንደሚገባቸው ተጨባጭ ትምህርት ተሰጥቶበታል ማለት ይቻላል፡፡ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ የማስተማሪያ ብልሃቶች ውስጥ ከተዘረዘሩት መካከል ውይይት በርዕስነት ለተማሪዎች መቅረቡ ለወደፊት የሚማሩትን የትምህርት ይዘቶች በአግባቡ ለመማር እንዲችሉ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ለቡድን ስራም እንደ ስልጠና ሊቆጠር እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

በመልመጃ ሁለት (ገፅ፣46) ላይ የንግግር ስርዓት መመሪያ ቀርቧል። ይህም ርዕስ እንደ መልመጃ አንዱ የውይይት መመሪያ በቀረበላቸው የንግግር መመሪያ መሠረት ተማሪዎች በአንድ ርዕስ ላይ ተዘጋጅተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ የቀረበ ትዕዛዝ ነው። ተማሪዎች በነፃነትና በራሳቸው በመተማመን ንግግር እንዲያደርጉ ማስቻል አንዱ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታ በመሆኑ በዚህ ዓይነት መቅረቡ ተገቢነት ይኖረዋል። ሌሎቹ መልመጃዎች ለምሳሌ መልመጃ ሶስት፣ አራትና አምስት በግል ግንዛቤ የሚሰሩ ተግባራት ናቸው። ይህም በግል የሚሰሩ ተግባራት ቢሆኑም የግል ስራን ለሌሎች ጓደኞች ማንበብና የሌሎችንም ስራ ማዳመጥ እንዲሁም የተረዱትን ድምፆች ለይቶ ማውጣት በመሆኑ በጥልቀት የቋንቋውን ድምፆች የሚያስለዩ ተግባራትን ያካተቱ ናቸው። በዚህ ረገድ የተማሪዎች በመማር-ማተማር ሂደት ውስጥ ተሳታፊነተ አነስ ያለ ቢመስልም መጠነኛ የሆኑ በጎ ጎኖች አሉት።

ከላይ ከተነሱት ነጥቦች አንፃር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ተማሪን በትምህርቱ ሂደት በማሳተፍ በኩል በወይይትና ንግግር ስርዓት በመጠኑ ቢኖሩም በአብዛኛው ጉድለቶች እንዳሉዋቸውም የሚያመለክቱ ነጥቦች ተስተውለዋል። አንዳንድ መልመጃዎችን ለማሰራት ለምሳሌ በ (ገጽ፣77) ላይ የተሰጡ ትዕዛዛት ስለማይለዩና ውይይቱ በቡድን ወይም በጥንድ ወይም ከሙሉው ተማሪ ጋር መሆኑን ስለማያመለክቱና አንድ ምዕራፍ ሙሉ በሙሉ በግል ስራ ብቻ መሸፈኑ፣ እንደድክምት የሚጠቀስ ነው። ከዚህም ባሻገር ተማሪዎችን ከአካባቢያቸው ጋር የሚያገናኙ ተግባራትና ከተማሪዎች ባህላዊ ዳራ ጋራ የተያያዙ መልመጃዎች የተካተቱበት አይደለም። በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ከሚተገበሩ የማስተማር ብልሃቶች መካከል በመጠኑም አልተካተተበትም።

## 5.3.6.የመምህራን የስራ ላይ ስልጠናዎች

የስራ ላይ ስልጠና መምህራን ዕውቀታቸውን በየጊዜው እያደሱ መማር-ማስተማርን በተፈለገው መንገድ እንዲተገብሩት ያደርጋል። Murphi (1993) እንደገለፁት አንደኛውና ዋነኛው መምህራን በዚህ አቀራረብ ትምህርት ሲያቀርቡ ተማሪዎችን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የስልጠና ግብዓት ያስፈልጋቸዋል። ከዚህ አንፃር በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በስራ ላይ እያሉ ስልጠና ማግኘት ይጠበቅባቸዋል። ይህን አስመልክቶ በባሌ ዞን ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራን

በተለያየ ጊዜ ያገኟቸው ወይም የተከታተሉዋቸው የስራ ላይ ስልጠናዎች ስለመኖራቸውና እነዚህም ስልጠናዎች ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ እገዛ አድርገውላቸው እንደሆነ ለማወቅ ከተተኳሪዎቹ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራንና ርዕሳነ-መምህራን በቃለ-መጠይቅ መረጃ ተሰብስቦ ምላሽ ተገኝቷል፡፡

በመጀመሪያ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዙሪያ የስራ ላይ ስልጠና ማግኘት አለማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ለአራቱም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለዜይበላ፣ ለኪጽጠቴ፣ ለአሊቢራና ለሓውሾ የአፋን ኦሮሞ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ የስራ ላይ ስልጠና ስለመውሰዳቸው ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ከዜይበላ ት/ቤት ምላሽ ሲሰጡ

> *በኔ በኩል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቶኝ አያውቅም፡፡ በተለይም በአፋን ኦሮሞ ማስተማር ዙሪያ ምንም ስልጠና አላገኘሁም፡፡ ያው እንግዲህ መምህር ስለሆንን በዚያው የቅድመ ስራ ስልጠና እያስተማርኩ እገኛለሁ...*(ዋጋሪ ዳዲ፣ በ/28/07/04 ፣ከ5፡00-5፡40 *ሰዓት)፡፡*

በዜይበላ ትምህርት ለአፋን ኦሮሞ መምህራን መምህሩ ስልጠና ያለመሰጠቱንና በቅድመ ሥራ ስልጠናውን እያስተማሩ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡ ይህንኑ ጥያቄ በሐውሾ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለአፋን ኦሮሞ መምህር አቅርቤ ያገኘሁት መልስ

> *...አንዱ በኮሌጅ ደረጃ ያገኘሁት ስልጠና ሲሆን ሌላው አንድ /ኢማጂናይዴ/ የሚል ድርጅት በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብና በተከታታይ ምዘና ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቶኛል፤ ስልጠናውም በቡድን ውይይት አመሰራረት ላይ፣ በተማሪ-ተኮርና በተከታታይ ምዘና ላይ የተመሠረተ ነው (ባዩ ቀልቤሳ፣በ/10/02/06 ፣ከ4፡00-5፡00 ሰዓት) ፡፡*

በዚህ የአተገባበር ክህሎታቸውን እንደገነቡ ገልፀውልኛል፡፡ ሌላው የዜይበላና አሊቢራ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህራንን በአፋን ኦሮሞ ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ ምንም አይነት የስራ ላይ ስልጠና እንዳላገኙ ገልፀዋል፡፡

ከአራቱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን መካከል የሐውሾ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአፋ ኦሮሞ መምህር የሰራ ላይ ስልጠናውን "ኢማጂናይዴ" የሚል ድርጅት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራና በተከታታይ ምዘና ዙሪያ ስልጠና እንደሰጣቸው አመልክተዋል፡፡

የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና በየጊዜው በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተግባራዊ መሆን የሚገባቸው የተለያዩ የማስተማር ብልሃቶችና ስልቶች በተገቢው መንገድ ተግባራዊ

እንዲሆኑ የሚያደርግ ቁልፍ መንገድ  በመሆኑ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን እንደተገለፀው በአፋን ኦሮሞ ትምህርት ማስተማር ዙሪያ ያገኙት የስራ ላይ ስልጠና እንደሌለ ቢናገሩም በሐውሾ ትምህርት ቤት ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምር መምህር ግን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራና በተከታታይ ምዘና ዙሪያ ስልጠና እንዳገኙ ገለፀዋል፡፡ ይህም በአሰለጣጠን ላይ ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡

የዜይበላ ትምህርት የአፋን ኦሮሞ መምህር የሥራ ላይ ስልጠና መውሰድ አለመውሰዳቸውን ለማወቅ የትምህርት ቤታቸውን ርዕሰ መምህር ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም፤

> *…በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ላይ የስራ ላይ ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ወደ ትምህርት ቤታችን የሚመደቡ መምህራን ከመምጣታቸው በፊትም ሆነ በማሰልጠኛቸው ውስጥ ስልጠና ስለወሰዱ ይህን ተጠቅመው እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ በቋንቋ መምህራን በኩልም የእንግሊዘኛ ማሻሻያ ስልጠና ይሰጣል፡፡ ነገር ግን የአፋን ኦሮሞ መምህራን ተብሎ ተለይቶ ለየብቻ የሚሰጥ ነገር የለም፡፡ በሒሳብ ትምህርትና በተፈጥሮ ሳይንስ ላይም በትምህርቱ አሰጣጥ ላይ በBESO ፕሮጀክት ድጋፍ በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኩል የሚሰጡን የሙያ ማበልፀጊያ አሉ፡፡ በእነዚህ ሙያ ማሻሻያዎች ድጋፍ አማካኝነት መምህራን የማስተማር ብቃታቸውን እያሳደጉ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በትምህርት ቤታችን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እንዲተገብሩት ከወረዳ ትምህርት ቢሮም ቁጥጥር ስለሚያደርጉ እኛም በትምህርት ቤታችን ውስጥ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል አድርገናል (*ቶሎሳ በከሬ፣በ/28/07/04፣ከ3፡00-4፡00 ሰዓት)፡፡

በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እንደተገለፀው  በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የተማሪ-ተኮር እየተተገበረ መገኘቱና መምህራን ይህን አቀራረብ ተግባራዊ የሚያደርጉበት የስልጠና ግብዓት በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ እያሉ ያገኙት መሆኑ ነው፡፡ ከኮሌጅ ውስጥ ካገኙት የስልጠና ግብዓት በተጨማሪም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ማሻሻያ መርሀ-ግብር ውስጥ ከቋንቋ መምህራን መካከል እየተመረጡ ስልጠና የሚወስዱበት ሁኔታ እንዳለ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ስልጠናው ለቋንቋ መምህራንና ለተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት መምህራን ተብሎ ይሰጣል እንጂ ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ተብሎ አይሰጥም፡፡ ይህም ስልጠናው ለብቻው ተለይቶ ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ካልተሰጠ የተማሪ-ተኮር አተገባበር ትግበራ ላይ በተለይም የመምህሩን ሚና ከማሳየት አንፃር፣ በተለይም በተማሪዎች አሳታፊነት፣ ሁኔታ

አመቻችነት፣ ቅድሚያ ሰጪነት፣ የተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች አጠቃቀምና የተማሪዎች ምዘና ክፍተቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ክፍተት ካለ ደግሞ አቀራረቡ በተገቢው መንገድ አይተገበርም ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራር አካላት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ እንዲተገበር ቁጥጥር ማድረጋቸው መምህራኑ በራሳቸው ፍላጎት አይተገብሩትም ወይ? ወደ ሚለው ድምዳሜ ያደርሰናል፡፡ ይኸውም ርዕሰ መምህሩ "…የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እንዲተገብሩት ከወረዳ ትምህርት ቢሮም ቁጥጥር ስለሚያደርጉ እኛም በትምህርት ቤታችን ውስጥ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል አድርገናል …" ብለው የተናገሩት ሀሳብ ከመምህራኑ ይልቅ ወረዳው ቁጥጥር በማድረጉ በሚገባ ተተግብረዋል እንዲሉ አስገድዷቸዋል፡፡ የተማሪ-ተኮር በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ እንዲተገበር ግዴታ ሳይሆን የመምህራን የተለመደ ስራ ሊሆን ይገባል፡፡

ሌላው የመምህራን ስልጠናን አስመልክተው ሀሳብ የሰጡት የአሊ ቢራ ትምህርት ቤት ር/መምህር ናቸው፡፡ በትምህርት ቤታቸው ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ስልጠና ስለመስጠታቸው ለማወቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> *የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አስመልክቶ እንደ ትምህርት ቤታችን በሁሉም መምህራን ጉድለቶች ቢታዩም ባላቸው ችሎታ ስራ ላይ እያዋሉት ይገኛሉ፡፡ በአንዳንድ ክፍሎች ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር ብዛት ስላለው እንደተፈለገው ባይሆንም ያለመታከት መምህራን እየተገበሩት ይገኛሉ፡፡ …ከወረዳችን ስለተማሪ-ተኮርም ይሁን ስለ ሌላ ጉዳይ እንዳንድ መምህራንና የትምህርት ቤቶች ጽህፈት ቤት ባለስልጣናት ተመልሰው እንዲያሰለጥኑን ወደ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ወይም ወደ ባሌ ዞን ትምህርት መምሪያ ወይም ወደ ሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ይሄዱና ሲመለሱ ሲያሰለጥኑን አይስተዋልም፡፡ በአጠቃላይ የኛ መምህራን የተማሪ-ተኮር አተገባበር የስራ ላይ ስልጠና አግኝተው ሳይሆን በራሳቸው ተነሳሽነት ብቻ እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ምክንያቶቹን ባናውቅም የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ዝቅተኛ ሆኖ መገኘት ይስተዋላል፡፡ (ከዲር አብዳ፣ በ/9/08/04-ከ8፡00-፡00 ሰዓት)፡፡*

እንደ ርዕሰ መምህሩ አገላለጽ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን በሰለጠኑበት መንገድ የተማሪ-ተኮርን እየተገበሩት እንደሚገኙና ነገር ግን በአንዳንድ ክፍሎች የተማሪዎች ቁጥር መብዛት የተነሳ በተፈለገው መንገድ ያስተምራሉ ማለት

እንደማይቻል ገልፀዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በክፍል ውስጥ መብዛት መምህራን አጋዥ ሀይል እንዳገኙ ሊቆጥሯቸው እንደሚገባ የተገለፀውን ሀሳብ ያልተረዱ መሆናቸውን ያመለክተናል፡፡

ሌላው በር/መምህሩ የተገለፀው በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የመምህራን የእርስ በርስ መማማርና የስራ ላይ ስልጠና መርሀ-ግብር መምህራን ያሉባቸውን የመማር-ማስተማር ችግሮች የሚቀርፍ ስልት እንደሆነ ያልተረዱት ይመስላሉ፡፡ የተማሪ ቁጥር በበዛበት መማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን እንዴት ማስተማር እንደሚችሉ ስልጠና ሊሰጣቸው እንደሚገባ Chenge (2007) በምዕራፍ ሶስት ላይ የተገለፀውን እንድናስብ ያደርገናል፡፡ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ራሳቸው ችግሩን መፍታት ባይችሉ በአካባቢያቸው ከሚገኝ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ጋራ ግንኙነት በመፍጠር ለታዩት ክፍተቶች ምላሽ ሲሰጡ አልተስተዋለም፡፡

ሌላው ር/መምህሩ የተናገሩት “አንዳንድ መምህራንና የትምህርት ኃላፊዎች ስልጠና እንዲወስዱ ተመርጠው ስልጠና ከወሰዱ በኋላ ሲመለሱ አያሰለጥኑንም፣ የኛ መምህራን የተማሪ-ተኮርን ለመተግበር የስራ ላይ ስልጠና ሳይወስዱ ያስተምራሉ” ያሉት ሲቃኝ

የትምህርት ሐላፊዎች በሰለጠኑበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሌሎችን ማሰልጠን የሚገባቸው ከሆነ ማሰልጠን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሁሉንም ጉዳይ ተመልሰው የሚያሰለጥኑ ብቻ ተደርጎ ሊታሰብም አይገባም፡፡ አንዳንዴ የሐላፊዎችን የማስተዳደር አቅም ለመገንባት ሲባል የሚሰጡ ስልጠናዎች እንዳሉ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ተማሪዎች የመማር ፍላጎት የላቸውም ለተባለው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ ሊተገበር የሚችለው ተማሪዎች በመነሳሳት በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ሲሳተፉ እንደሆነ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ በተገለፀው መንገድ መምህራን ተማሪዎች ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ አመለካከታቸው መልካም እንዲሆን የራሳቸውን ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ውስጥ በማስተማር ብልሃቶችና የተማሪዎች ሚና ምን መምሰል እንደሚገባ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ድርሻቸውን ማወቅ አለባቸው፡፡

በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ቃለ-መጠይቅ የቀረበላቸው መምህራን እንደተናገሩት በተለያዩ ትምህርቶች ላይ ለምሳሌ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ማሻሻያና በተፈጥሮ ሳይንስ

ትምህርቶች ማስተማር ላይ ብዙ ጊዜ ስልጠና ቢሰጥም ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ተብሎ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ የተሰጠ ልዩ ስልጠና ውስን ነው፡፡ ይህም የሚያሳየን መምህራን በራሳቸው እውቀት በመመራት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ያስተምራሉ ማለት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ በተማሪ-ተኮር መርሆዎች መሰረት ብዙ የአተገባበር ክፍተቶች እየሚያደርግ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

### 5.3.6.1. የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና በትምህርት ሐላፊዎች አተያይ

የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማር- ማስተማር ሂደት ውስጥ ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በባሌ ዞን ትምህርት መምሪያ የመምህራን ልማት ተጠሪ ለዚህ ጥናት መረጃ ሰጪ ተደርገው ተወስደዋል፡፡ የመምህራን ልማት ማለት መምህራን ስራ ላይ እያሉም ይሁን ለተወሰኑ ዓመታት ወይም ለተወሰኑ ወራት የማስተማር አቅማቸውን እንዲያሳድጉ የተለያዩ ስልጠናዎችና ትምህርቶችን እያገኙ ሙያቸውን በአግባቡ እንዲያሳድጉ ማስቻል ነው፡፡ ስለዚህም ለኃላፊው በዞኑ ውስጥ የሚገኙት መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በክፍል ውስጥ እየተገበሩት ስለመሆናቸው ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፣

> *አዎን መምህራን ተገቢ በሆነ መንገድ የተማሪ-ተኮርን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ እየተገበሩት ይገኛሉ፡፡ በሚገባ እየተገበሩት መገኘታቸውን ከየወረዳ ትምህርት ቤቶች የሚደርሱን የስራ ሪፖርቶች ያረጋግጡልናል፡፡ በተጨማሪም ስለተማሪ-ተኮርአቀራረብ ትግበራ ለመምህራን ስልጠና ስለምንሰጥ ከተሰብሳቢዎቹ መምህራን ከምናገኘው ምላሾች ስለተግባራዊነቱ መረጃ እንገኛለን (*ጥላሁን *ነገዎ*፣/7/09/2004 ፣ከ8፡00-8፡30 ሰዓት)፡፡

በማለት በባሌ ዞን ውስጥ የሚገኙ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተተገበረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በምልከታ በታዩት የአፋን ኦሮሞ የመማሪያ ክፍል ውስጥ የታየው ሁኔታ ኃላፊው ከተናገሩ ተቃራኒ ሁኖ በተገቢው መንገድ ያለመተግበሩን አመልክቷል፡፡ መምህራኑም እያስተማሩ የሚገኙት በቡድን ውይይትና በተናጠል ነው ፤ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መፃፍም ተማሪዎችን አሳታፊ ሆኖ የተዘጋጀ አይደለም፤ እነዚህንና ሌሎች ችግሮችን በጥናት ላይ ተመርኩዘው ሳያረጋግጡ ተተግብሯል መባሉ አግባብ አይደለም፡፡

የመምህራን የሥራ ላይ ስልጠናን በተመለከተ በዞኑ ውስጥ ለሚያስተምሩ የአፋን ኦሮሞ ይሁን ለሌሎች  መምህራን መስጠት አለመሰጠቱን ለማወቅ ለዞኑ የመምህራን ልማት ተጠሪው ጥያቄ አቅርቤላቸው ሲመልሱ፤

> *ለመምህራን የሥራ ላይ ስልጠና እየተሰጠ ነው፡፡ የሚሰጠው ስልጠናም በተለያዩ ርዕሶች ላይ ቢሆንም በአብዛኛው በተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ (CPD)፣ በእርስ በርስ መማማር (Instaff Trainig) በተለያዩ መማር- ማስተማር ችግሮች ዙሪያ፣ በስራ ላይ ምርምር (Action Reasearch)፣ በተማሪ-ተኮር አቀራረብና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ላይ ስልጠና እየሰጠናቸው ነው ፡፡*
>
> *ስልጠናውም መምህራኑ በሚገኙበት ወረዳ፣ በዞን ትምህርት ቢሮና በተጨማሪም የሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ወይም የኮሌጁ መምህራን የአንደኛ ደረጃ መምህራኑ ባሉበት ወረዳ ድረስ እየሄዱ ይህን ተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲወስዱ ይደርጋሉ(*ጥላሁን ነገዎ፣/7/09/ 2004፣ ከ8፡00-8፡30 ሰዓት)፡፡

በማለት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ መምህራን በምን አይነት መንገድ ስልጠና እየተሰጣቸው እንደሚገኙ አብራርተዋል፡፡ በዚህ በኋላፊው ገለፃ መሰረት  የአንደኛ ደረጃ መምህራን የመማር-ማተማር አቀራረባቸውን ክህሎት የሚያጎለብቱበት የተለያዩ ርዕሶች ቢሆኑም የተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ አንዱ ነው፡፡ በተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ ስር መምህራን በስራ ላይ የሚያጋጥማቸው ችግሮች ውስጥ በመምረጥ ችግሩ እየተፈታ ተግባራዊ የሚያደርጉበት ብልሃት ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የተማሪ-ተኮር አተገባበርና የተከታታይ ምዘና ስርዓት ተግባራዊነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በመሆኑም የመምህራን ስልጠናው የሚሰጥ ቢሆንም ይህ ስልጠና ለነማን እንደሚሰጥ ባለመለየታቸው ሌላ ጥያቄ እንዳቀርብላቸው ገፋፋኝ፡፡

ሌላው ለዞኑ የመምህራን ልማት ተጠሪው አፋን ኦሮሞ ለሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብና በተከታታይ ምዘና ትግበራ ዙሪያ የሰጡት የስራ ላይ ስልጠና መኖር አለመኖሩን የሚጠይቀው ጥያቄ ነው፡፡ተጠሪውም ሲመልሱ፡-

> *የስራ ላይ ስልጠናው እየተሰጠ የሚገኘው በአብዛኛው ለሳይንስ መምህራን ነው፡፡ ምክንያቱም መንግስት ትኩረት አድርጎ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ለሳይንስ ትምህርት በመሆኑ እኛም ከቋንቋ መምህራን ይልቅ በሳይንስ ትምህርት ላይ ትኩረት አድርገን እየሰራን እንገኛለን፡፡ ለቋንቋ መምህራን እስከ አሁን ስልጠና ባንሰጥም በሮቤ*

> *መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በተለያየ ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና እየተሰጣቸው ይገኛል፡፡ በኛ ቢሮ በኩል ግን ከላይ እንደ ተገለፀው ይሁን እንጂ በትምህርት ቤታቸው እርስ በርስ እንዲማማሩ ተደርጓል፡፡ ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ለብቻ ለይተን ስልጠና አልሰጠናቸውም ነገር ግን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስልጠና በተለያየ ጊዜ በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም እንደ ቋንቋ መምህራን የመማር-ማስተማሩን ሂደት አስመልክቶ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በኩልም የሚሰጡት ስልጠናዎች ላይ ደግሞ እነዚህ መምህራን ይምጡና ስልጠና ይውሰዱ ተብሎ አይለያይም፡፡ ነገር ግን በደፈናው ሁለትም ይሁን ሶስት መምህራን በዚህ ቀን በሚሰጠው ስልጠና ላይ ይሳተፉ ተብሎ ጥሪ ሲደረግ እኛ ተመልሰው ሌሎችን ሊያሰለጥኑ የሚችሉ መምህራንን መምረጫ መስፈረት አዘጋጅተን እንልካቸዋለን፡፡ እንግዲህ በዚህ አይነት ነው መምህራን አቅማቸውን እያሳደጉ የሚገኙት (ጥላሁን ነገዎ፣ /7/09/04፣ ከ8፡00-8፡30 ሰዓት )፡፡*

ብለው የዞኑ መምህራን ሙያቸውን እያሳደጉ የሚገኙበትን መንገዶች አብራርተዋል፡፡ በዚህ በኋላፊው አነጋገር ውስጥ ሁለት የተጋጩ ሀሳቦች ይታያሉ፡፡ በመጀመሪያ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እየተገበሩት መገኘታቸውን ከወረዳ ሪፖርቶች እንደሚያገኙና በመምህራን ስልጠና ወቅት የተማሪ-ተኮርን በክፍል ውስጥ እንደሚተገብሩት ከንግግራቸው እንደሚረዱ ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል ስልጠናው ከቋንቋ መምህራን ይልቅ ለሳይንስ መምህራን ትኩረት እየተደረገ መገኘቱንና ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ተብለው ተለይተው ስልጠና የሚያገኙ ሳይሆን በቋንቋ መምህራን ስም እንደሚሰለጥኑ አብራርተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚያመለክተን ስልጠናው በቋንቋ መምህራን ስም ለሁሉም ከተሰጠ በአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ ግንዛቤ ያግኙ እንጂ በእናት ቋንቋ፣ በሁለተኛ ቋንቋና በውጭ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ መካከል ስለመኖሩ የሚያውቁት ነገር አለመኖሩ ነው ፡፡ ስለዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ ለመተግበርና ክፍተቶችን ለመድፈን ገና ብዙ የሚቀሩ ጉዳዮች መኖራቸው ግልጽ ነው ፡፡

በሐላፊው አገላለጽ ለሳይንስ መምህራን ቅድሚያ ስልጠና እንደሚሰጡና ለቋንቋ መምህራን በተለይም ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ስልጠና እንዳልተሰጠ ገልፀዋል፡፡ ይህን ሀሳብ ሲናገሩ ከመንግስት ፖሊሲ ጋር በማገናኘት ነው፡፡ ይኸውም የመንግስት ትኩረት ለሳይንስ በመሆኑ እነሱም ትኩረታቸው በሳይንስ መምህራን ስልጠና ላይ ነው፡፡ መንግስት ለሳይንስ ትኩረት የሰጠው ከማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶች ብዛት ይልቅ የሳይንስ ትምህርቶችን ማብዛት ለማለት ነው እንጂ በጥራት ደረጃ ሁሉም ትምህርቶች በጥራት መሰጠት እንዳለባቸው

ይገልፃል፡፡ ስለዚህ ኋላፊው ይህን ሀሳብ መስጠታቸው ፖሊሲውን በሚገባ ካለመረዳት እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ለአፋን ኦሮሞ መምህራን በዞኑ በኩል ስልጠና ባይሰጡም በመምህራን ኮሌጅ በኩል እንደሚሰጣቸው መሆኑና የተማሪ-ተኮር አቀራረብም በአፋን ኦሮሞ መምህራንም ይሁን በሌላው በክፍል ውስጥ እየተተገበረ ይገኛል ብለው መናገራቸው ትክክል አይመስልም፡፡ ምክንያቱም በክፍል ውስጥ ምልከታ በታዩት ትምህርት ቤቶች ውስጥ አያሌ ተግዳሮቶች መኖራቸውን ከላይ ለመመልከት ችለናል፡፡

ከዞኑ ትምህርት ቢሮ የመምህራን ልማት ሐላፊው ከላይ የሰጡኝን ሐሳብ መሰረት በማድረግ በባሌ ዞን ከሚገኙ የተመረጡ ወረዳዎች ለሚገኙ የመምህራን ልማት ተጠሪዎች ተመሣሣይ ጥያቄ አቅርቤ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ከሮቤ ወረዳ ሐላፊ ጋር በተስማማነው መሰረት መቅረፀ ድምፄን አዘጋጅቼ ቃለ-መጠይቅ ላደርግላቸው በቢሮአቸው በር ላይ ጠበቅሁዋቸውና ቢሮ እንደገቡ ጥያቄዬን በወረዳው የሚገኙ መምህራን የስራ ላይ ስልጠና እያገኙ ስለመሆናቸው በማቅረብ ጀመርኩኝ፡፡ እሳቸውም፤

> *…እንደተፈለገው በቂ ባይሆንም የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮና በትምህርት ስራ ላይ ድጋፍ በሚሰጡ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በኩል ይሰጣል፡፡ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስልጠና ክፍል አንዳንዴ እስከ ሻሸመኔ ድረስ ጠርተው ስልጠና ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም የሮቤ መምህራን ኮሌጅ ከአሜሪካ የትምህርት ድጋፍ ሰጪ ድርጅት (BESO/USID) ጋር በመተባበር አንዳንዴ ተጠርተው ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ስልጠናው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ፣ በተከታታይ ምዘና፣ በተካታታይ ሙያ ማበልፀጊያ ስልጠና ያገኛሉ* (ተስፋዬ ሶሬሳ፣ በ/15/09/04 ፣ ከ2፡50- 3፡30 ሰዓት)፡፡

በሮቤ ወረዳ የመምህራን ልማት ተጠሪው አገላለፅ በቂ ባይሆንም በየትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመድበው ለሚያስተምሩ መምህራን በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮና በትምህርት ሥራ ላይ ድጋፍ በሚሰጡ ድርጅቶች በኩል ስልጠና እንደሚሠጣቸው ነው፡፡ ስልጠናውም በተማሪ-ተኮርና በተከታታይ ምዘና፣ በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ላይ እንደሆነ ግልፀዋል፡፡ ነገር ግን ጥቂትም ቢሆን የሚለው ሐሳባቸው አሉታዊ አንደምታ አለው፡፡ይህም ስልጠናው ብዙ ጊዜ እንደማይሰጥና የተፈለገውን ያህል እንደማይሆን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመድበው የሚያስተምሩ መምህራን በወረዳቸው በኩል በቂ

ስልጠና እንደማያገኙ ያመለክታል፡፡ በቂ ስልጠና ካላገኙ በመማር-ማተማር ሂደት ውስጥ በተለይም የተማሪ-ተኮር አተገባበር ላይ የአተገባበር ክፍተቶች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡

እንደ ሮቤ ወረዳ የመምህራን ልማት ኂላፊው ገለፃ ከየትምህርት ቤቶቹ ተመርጠው ስልጠና የተሰጣቸው መምህራን በተሰጣቸው ስልጠና መሰረት በክፍል መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ነው፡፡ የተማሪ-ተኮርም በዚያው መንገድ ተግባራዊ ይሆናል ብለን እናስባለን በማለት በወረዳቸው ውስጥ እየተከናወነ ያለውን ነግረውኛል፡፡ ከዚህ ከወረዳው የመምህራን ልማት ኂላፊው ገለፃ በመነሳት ለመሆኑ በእርስዎ አስተሳሰብ በየትምህርት ቤቶቹ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተግባራዊ ሆኗል ብለው ያስባሉ? የአፋን ኦሮሞ መምህራንስ ይህን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በክፍል ውስጥ እየተገበሩት ስለመሆናቸው የሚያውቁት ነገር ካለ ቢገልፁልኝ፣ በማለት ጠይቂያቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

> *እኛ ስልጠና ስንሰጣቸው ይተገብሩታል ብለን እያሰብን ነው፡፡ በትምህርት ቤታቸው ውስጥም ስራ ላይ ስለ ማዋላቸው የትምህርት ቤታቸው ርዕሳነ መምህራን ክትትል ያደርጉባቸዋል፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብም እያስተማሩ መሆናቸውንም የስራ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ ስለዚህ ተተግብሯል ብዬ ብንናገር ውሸት ነው አያስብለኝም፡፡ የአፋን ኦሮሞ መምህራንም እንደ ሌሎች መምህራን ሁሉ ተግባራዊ ያደርጉታል ብዬ አስባለሁ፡፡ (*ተስፋዬ ሶሬሳ፣ በ/15/09/04 ፣ከ2፡50-3፡30 ሰዓት) ፡፡

እንደኂላፊው አገላለጽ ለመምህራን ስልጠና ሲሰጡ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ተመልሰው እንደሚተገብሩት በማሰብ ነው፡፡ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ በርዕሳነ-መምህራን ክትትል እንደተተገበረ መነገሩ አግባብ አይደለም፡፡ ይህ ሀሳብ ሥልጠና የወሰዱት መምህራን በትምህርት ቤታቸው ሄደው ስልጠናውን መስጠት አለመስጠታቸውን የሚቆጣጠሩበት ስልቶች እንደሌላቸው ያስረዳል፡፡ የተለያዩ ግብዓቶች ሳይሟሉ፣ማቴሪያሎች ሳይቀርቡ፣ የመማሪያ ክፍል በአግባቡ ሳይደራጅ፣መምህራን ተገቢ የሆነ ስልጠና ሳያገኙና የመምህራን እጥረት ሳይፈታ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተተግብሯል መባሉ ለይስሙላ ብቻ መናገር ይሆናል፡፡

ስለአፋን ኦሮሞ መምህራን ስልጠና መውሰድ አለመውሰድ ኂላፊው ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ፤

*…የአፋን ኦሮሞ መምህራን ለብቻቸው ተጠርተው ስልጠና አልተሰጣቸውም፡፡ ነገር ግን ሁሉም መምህራን በመምህርነታቸው በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እንዲፈቱ የሚያደርጋቸው የመምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ነው፡፡ ይህ ስልጠና ደግሞ በስራ ላይ የሚገኙ መምህራን እርስ በርስ ስልጠና እንዲሰጣጡ የሚያደርግ በመሆኑ ብዙ መምህራን እየተጠቀሙበት ነው፡፡ የአፋን ኦሮሞ መምህራንም በስራ ላይ ሆነው የወሰዱት ስልጠና ይኸው ነው፡ በዚህም ሌሎች ትምህርቶችን እንደሚያስተምሩ መምህራን ሁሉ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ ያደርጉታል ብለን እናስባለን* (ተስፋዬ ሶሬሳ፣ በ/15/09/04 ፣ከ2፡50-3፡30 ሰዓት )፡፡

በሐላፊው ገለፃ መሰረት ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ተብሎ የሚሰጥ ስልጠና ባይኖርም ሁሉም መምህራን ችግሮቻቸውን የሚፈቱበት የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንደተሰጣቸው ገልፀዋል፡፡ በዚህ ስልጠና መሰረት በተማሪ-ተኮር አቀራረብም ትግበራም ይፈፀማል ብለዋል፡፡ የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ስልጠና መምህራን ብቃታቸውን የሚያሻሽሉበት ቢሆንም በተማሪ-ተኮር የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሳያተኩር የሚሰጥ ነው፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ የራሱ የሆኑ ብልሃቶችን ጠያቂ በመሆኑ በአንድነት መጨፍለቅ አግባብ አይደለም፡፡ በአጭሩ ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ስልጠና አልተሰጠም ማለቱ የተሻለ ይሆናል፡፡ በዚህ ሀሳባቸው ከዞኑ መምህራን ልማት ኃላፊው ምላሽ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

በተጨማሪም ለሮቤ ወረዳ ትምህርት ቢሮ የመምህራን ልማት ሐላፊው በተማሪ-ተኮር አተገባበርና የመምህራን አሰለጣጠን አስመልክተው ጠቅለል ያለ ሀሳብ እንዲሰጡኝ ጠይቂያቸው፣

*የመምህራን ስልጠና በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በመምህራን ስልጠና የመምህራንን የተማሪ-ተኮር ትግበራ ደካማ ጎን ይቀርፋል፡፡ አንዱ ከአንዱ ይማራል፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከትምህርት ጥራት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህን አቀራረብ በአግባቡ በስራ ላይ ማዋል የሚቻለው መምህራን የስራ ላይ ስልጠና ካገኙ ብቻ ነው፡፡ እኛ ደግሞ እንደ ወረዳችን እንደፈለግነው ስልጠና ለመስጠት በጀት የለንም፡፡ ለመምህራን ጥሪ ስናቀርብ የመጀመሪያ ጥያቄያቸው የውሎ አበል ክፍያ ነው፡፡ ክፍያ ከሌለው ችግር ነው፡፡ ስለዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ተቋማት እገዛ ካላደረጉልን በስተቀር አቅማችን የተገደበ ነው፡፡ ጠቀሜታውን እያወቅነው ሁኔታዎች ይገድቡናል፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ወቅት ትልቅ ስራ እየተሰራ ያለው በመምህራን ተከታታይ የሙያ*

*ማሻሻያ ስልጠናና ለተማሪ-ተኮር ስልጠናም በዚሁ ላይ ተደግፈን ችግሮቻችንን መፍታት ተገቢ ይሆናል (*ተስፋዬ ሶሬሳ፣ በ/15/09/04፣ከ2፡50-3፡30 ሰዓት)*።* ብለዋል።

የመምህራን ልማት ተጠሪው የስልጠናን ጠቀሜታና ከዚህ ጋር ተያይዘው የገጠማቸውን ችግሮች ገልፀዋል። ከችግሮቹ ውስጥ የበጀት አለመኖር በዚያ ሰበብ በተፈለገው መጠን ስልጠና መስጠት አለመቻላቸውን ነው ። ለስልጠናው በጀት የሚበጅተው የራሳቸው ክፍል ሆኖ እያለ ከሌላ ድጋፍ አድራጊ መጠበቅ ተገቢ አይደለም ። ከበጀት እጥረትና ከስልጠና እጥረት የሚመነጩ ችግሮች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ መሆናቸው በግልጽ ይታያል።

ሌላው የሲናና ወረዳ የመምህራን ልማት ተጠሪ የሆኑ ኃላፊም በተማሪ-ተኮር አተገባበር ላይ ያላቸውን ሀሳብ እንዲሰጡኝ በወረዳችሁ ውስጥ የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤት አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በምን ዓይነት አቀራረብ እያስተማሩ እንደሚገኙ ቃለ-መጠይቅ አድርጌላቸው ነበር። እሳቸውም፤

*በዚህ ወረዳ ውስጥ መማር-ማስተማሩ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል። ምክንያቱም ወረዳችን ልምድ ያላቸው ነባር መምህራን ያሉበት በመሆኑ ስራዎችን በሚገባ እየሰሩ ይገኛሉ። አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራንም ይሁን ሌላ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን በአሁኑ ጊዜ ውጤታማ አቀራረብ ነው በሚባለው የተማሪ-ተኮር ተጠቅመው እያስተማሩ እንደሚገኙ ከየትምህርት ቤቱ የሚመጡልን መረጃዎች ያመለክታሉ (*ተሻለ ኖኖ፣በ/24/07/04 ከ3፡25-4፡30 ሰዓት) ።

በማለት መልስ ሰጥተዋል።

እኚህ የመምህራን ልማት ተጠሪ ቀደም ብለው ሌሎች ኃላፊዎች እንደገለፁት ሁሉ የመማር-ማስተማር ሂደት በመልካም ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑንና የአፋን ኦሮሞ መምህራንም የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በአግባቡ እየተገበሩት መገኘታቸውን ይናገራሉ። ይህ የመምህራን የተማሪ-ተኮር ትግበራ በልምድ ማደግ የተገኘ እንደሆነም ይገልፃሉ። የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በማስተማር ልምድ ብቻ የሚተገበር ሳይሆን በምዕራፍ ሶስት ላይ እንደተገለፀው የመምህሩ አመለካከት፣የተማሪዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ባህሪያትን መገንዘብ፣የማቴሪያል እገዛና ምቹ አካባቢን ጠያቂ ነው። ከዚህ አንፃር ኃላፊው ይህን ያልተረዱት ይመስላሉ።

ከዚሁ ከተናገሩት ምላሽ ተነስቼ ኂላፊውን እነዚህ ልምድ ያላቸው መምህራን በቀድሞው ስርዓተ-ትምህርት የተመረቁ በመሆናቸው በአሁኑ ጊዜ ካለው የትምህርት ስርዓት ጋራ በተለይም ከተማሪ-ተኮርና ተከታታይ ምዘና ተግበራት ጋራ የመጣጣም ደረጃቸው ምን እንደሚመስል ለጠየኳቸው ጥያቄ፣

> *በዚህ ወረዳችን የሚገኙ መምህራን በአሮጌው ትምህርት ፖሊሲ የተመረቁ ቢሆኑም በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በሚደረጉ የርስ በርስ መማማርና በሚላክላቸው መመሪያዎች የማስተማር አቀራረብ መንገዳቸውን ለውጠው፤ አዲሱን ተቀብለው በተፈለገው መንገድ ለማስተማር አቅም አግኝተዋል። በተጨማሪም ለብዙ የቋንቋ መምህራን የአፋን ኦሮሞ መምህራንን ጨምሮ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስልጠና እንዲያገኙና ራሳቸውንም እንዲለውጡ ሁኔታዎች ይመቻችላቸዋል። በሌላ በኩል በመምህራን የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ልምድ ያላቸው መምህራን ልምድ የሌላቸውን በማሰልጠን የመማር-ማስተማሩን-ሂደትና ችግሮቻቸውንም እንዲፈቱ እየተደረገ ነው። ከዚህ ውጪ የአፋን ኦሮሞ መምህራን አብዛኛዎቹ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ከተለያዩ ኮሌጆች የተመረቁ ናቸው። ሁሉም በአሁኑ ሰዓት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የማስተማር ብቃት አግኝተዋል ማለት ይቻላል (ተሻለ ኖኖ በ/24/07/04 ከ3፡25-4፡30 ሰዓት)።*

በሲናና ወረዳ የመምህራን ልማት ተጠሪው አመለካከት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአፋን ኦሮሞ መምህራን ተተግብሯል ማለት ነው። ይህ የመምህራኑ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የትግበራ ምንጭ መምህራን በቅድመ ስራ ስልጠና ማግኘትና በመካከላቸው የሚካሄደው ልምድ ልውውጥ ነው። በቀድሞው የትምህርት ስርዓት የሰለጠኑ መምህራን በወቅቱ ያለምንም ስልጠና በመመሪያ ብቻ የአፋን ኦሮሞ ትምህርትን ያስተምሩ እንደነበርና በአሁኑ የትምህርት ፖሊሲ የተመረቁት መምህራን ደግሞ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስልጠና ወስደው የሚወጡ ናቸው። በዚህ ምክንያት ተማሪ-ተኮር አቀራረብን የመተግበር ችግር የለባቸውም። በኂላ ግን በየትምህርት ቤታቸው እርስ በእርሳቸው በሚሰጣጡት ስልጠና ተማሪ-ተኮርን የመተግበር ችሎታቸውን ማሳደጋቸውን የተሰጠው መልስ ያመለክታል።

ከሐላፊው መልስ መረዳት የሚቻለው የተማሪ-ተኮርን ከመተግበር አንፃር በቀድሞ ስርዓተ-ትምህርት የተመረቁ መምህራን በአዲሱ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር ያካበቱት ልምድና ስልጠና ጠቀሜታ ቢኖራቸውም የነበራቸውን የማስተማር አመለካከት መቀየርና ከአዲሱ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ትልቅ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። በምዕራፍ

ሶስት ስር በቀረበው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ሂደት ውስጥ  የስራ ላይ ስልጠናና ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ አመለካከትን ለማስቀየር ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የተገለፀውም ለዚሁ ነው፡፡ የመምህራኑ የተማሪ-ተኮር አተገባበር ብቃትም የሚለካው በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በሚያከናውኑት ተግባር ስለሆነ  በክፍል ምልከታ ማረጋገጡ የተመረጠ ነው፡፡

እንደዚሁም ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ለሚገኙ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚያስተምሩ መምህራን የስራ ላይ ስልጠና መስጠት አለመስጠታቸው እንዲያስረዱኝ የጠየኩት የአጋርፋ ወረዳ የመምህራን ልማት ተጠሪ ጥያቄ አቅርቤላቸው በሰጡኝ መልስ ላይ፣ "አዎን አልፎ አልፎ ስልጠና ይወስዳሉ” (መስፍን ሽብሩ፣ በ/9/08/04፣ ከ3፡45-4፡30 ሰዓት) ብለው ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

ሐላፊው “አልፎ አልፎ ስልጠና ይወስዳሉ” ያሉት አገላለጽ ስልጠናው በበቂ ሁኔታ ያለመሰጠቱን የሚያመለክት አንደምታ አለው ፡፡ ይህ ሀሳብ  የሮቤ ወረዳ የመምህራን ልማት ተጠሪውም “ይብዛም ይነስም ስልጠና ይሰጣል” ካሉት  ሀሳብ ጋር ተመመሳሳይ በመሆኑ በበቂ ሁኔታ የስራ ላይ ስልጠና እንደማይሰጥ አመላክቷል፡፡ በማስከተልም ስልጠናውን እነሱ ይሰጡ እንደሆነ ወይም ሌላ አካል እንዳለና  ስልጠናው የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ምንምን እንደሆኑ ደግሜ ላቀረብኩላቸው ጥያቄዎች፤

> *…ስልጠናውን ለመስጠት እኛ የበጀት እጥረት ስላለብን በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ በአሜሪካ የትምህርት ድጋፍ /USID/ና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኩል ይሰጣል፡፡ ስልጠናውን የወረዳችን ሱፐርቫይዘሮች አብረው ይወስዱና መልሰው ይህን ስልጠና ላላገኙ መምህራን ይሰጣሉ፡፡ ስልጠናው የሚሰጥባቸው ርዕሶችም መምህራን እርስ በርስ የሚሰለጣጠኑበት (Instaff Traing) መንገዶች፣ በሳይንስ ትምህርት አሰጣጥ፣ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበርና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ላይ ነው…የተፈለገውን ያህል እንኳን ባይሆን ስልጠናው አለ፡፡ ለምሳሌ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አንዳንድ መምህራንን ጠርቶ ሰልጥነው ተመልሰው ደግሞ ሌሎች መምህራንን እንዲያሰልጥኑ የሚደረግበት ሁኔታ አለ፡፡  እኛ ደግሞ እነዚህ ሄደው ስልጠና የወሰዱትን መምህራን ስልጠናውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ሁኔታዎችን እናመቻችላቸዋለን፡፡ በአሁኑ ጊዜ በብዛት በሳይንስ ትምህርት ላይ ትኩረት ስለተደረገ የሳይንስ ትምህርቶችን በተማሪ-ተኮር እንዲያስተምሩ የሚል ርዕስ ላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡ (መስፍን* ሽብሩ፣ በ/9/08/04 ፣ ከ3፡45-4፡30 ሰዓት )፡፡

በሐላፊው አገላለጽ በየትምህርት ቤቶች ለሚገኙ መምህራን የተለያዩ ስልጠናዎች ቢሰጣቸውም በቂ አለመሆኑን ይገልፃሉ፡፡ የስልጠናው በቂ ያለመሆን ጉዳይ ደግሞ ከበጀት ምደባ ጋራ የተያያዘ ነው፡፡ ከላይ በሮቤው መምህራን ልማት ሐላፊው እንደተገለጸው ስልጠናን እየፈለጉ አቅም ማጣት ሆኖባቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ በመምህራን የክፍል ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ የጉዳዩ ባለቤቶች ትኩረት አድርገው ስልጠናውን ለሁሉም መምህራን በስፋት እንዳላዳረሱና የሚሰጠውም ስልጠና የግብር ይውጣ ዓይነት እንደሆነ ከየአቅጣጫው የተሰበሰቡ መረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡

## 5.3.6.2..የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ በትምህርት ቢሮ ሐላፊዎች አተያይ

በባሌ ዞን በተመረጡ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርትቤቶች ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን ለማጥናት የሚረዱ መረጃዎችን ለማግኘትና የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ልዩ ልዩ ክፍሎች ለመረጃ ሰጪነት ተመርጠዋል፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የመምህራን ልማት ተጠሪ፣ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክፍል ኃላፊና በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን ባለሙያዎች በዋናነት የተተኮረባቸው ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ እነዚህን አካላት በተናጠል በአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ ቃለ-መጠይቅ አቅርቤላቸው የተለያዩ ምላሾች ሰጥተውኛል፡፡

በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ተጠሪ የሆኑትን ሀላፊ በቢሯዋቸው አነጋግሬያቸዋለሁ፡፡ በ5/2/2005 ከጠዋቱ 3፡45 ላይ እንደተገናኘን ማንነቴን ከየት እንደመጣሁና ለምን ዓላማ ወደ እሳቸው እንደሄድኩ ገለጽኩላቸው፡፡ ለዓላማዬ መሳካትም እሳቸው የሚሰጡኝ ምላሽ እየተደረገ ላለው ጥናቴ አስፈላጊነቱን ካብራራሁላቸውና ስምምነታቸውን ካገኘሁ በኋላ መቅረፀ-ድምጼን ከቦርሳዬ ለማውጣት በመዘጋጀት ላይ እንዳለሁ ለመቀረጽ ፍላጎት እንደሌላቸው ነገር ግን የፈለኩትን ጥያቄ ለመመለስ እንደ ተዘጋጁ ፈቀዱልኝ፡፡ ከምርምር ስነ-ምግባር አንፃር ጥናቱ በመረጃ ሰጪዎች ፍላጎት መሰረት መከናወን ስለሚገባው እሺ.ታዬን ገለጽኩላቸውና ወደ ቃለ-መጠይቁ አመራሁ፡፡

በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስ/ት/ዝ/ ክፍል ሐላፊ ከሌሎች ከተለያዩ የትምህርት ቡድን ተጠሪዎች ጋር ሆነው ለብቻ በአንድ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የሂሳብ፣ የፊዚክስ፣ የኬሚስትሪ፣የአፋን ኦሮሞ፣ የእንግሊዘኛ፣ የአማርኛ ወዘተ ተጠሪዎች የትምህርት ቡድን

ናቸው፡፡ በእነዚህ የትምህርት ቡድኖች  መካከል የስ/ት/ዝ/ኂላፊ መቀመጫ ቦታ ይገኛል፡፡ ለእኔም የምቀመጥበት ቦታ ሰጥተውኝ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ተዘጋጀሁ፡፡

የመጀመሪያው ለስ/ት/ዝ/ኂላፊው በአሁኑ ሰዓት በአገራችንም ሆነ በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ እየተተገበረ ያለው ስርዓተ-ትምህርት በየትምህርት ቤቶቹ በምን አይነት አቀራረብ እየተሰጠ እንዳለ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

> *በአሁኑ ሰዓት በአገራችን በስራ ላይ እየዋለ የሚገኘው ስርዓተ-ትምህርት ብቃት-ተኮር /Competence Based/ ነው፡፡ ይህ ማለት ተማሪው ሊመዘን የሚገባው በሚሰራው ስራ ብቃት እንጂ በሚያመጣው ውጤት ላይ በመመስረት አይደለም፡፡ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎችም ለተማሪዎች እነዚህን በተግባር የሚገለፁ ክህሎቶችን የሚያጎናጽፉ ሆነው በመቀረጽ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓትም ይህ ሁኔታ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተገለጸ ነው፡፡ ስለዚህ በትምህርት ሚኒስቴርና በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በኩል የተዘጋጁት የተማሪዎች መማሪያ መፃህፍት ተማሪዎችን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አሳታፊ ሆነው ተዘጋጅተዋል፣ እየተዘጋጁም ናቸው፡፡ ይህን ያልኩበት ምክንያት አንዳንድ መፃህፍት በአሁኑ ጊዜ ታትመው ለየትምህርት ቤቶች ተሰራጭተዋል፡፡ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መፃህፍት፣ የአካባቢ ሳይንስና አማርኛ መማሪያ መፃህፍት ገና አልደረሱንም፡፡ የታተሙና ያልታተሙ መፃህፍት አሉ ያልኩትም ለዚህ ነው (*ሁንዴ በቀለ፣ /5/02/05 ከ3፡45-4፡30 ሰዓት) ፡፡

በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ኂላፊ አገላለጽ በአሁኑ ጊዜ ተማሪውን በውጤቱ ሳይሆን በብቃቱ  እንዲመዘን የሚያደርግ ስርዓተ-ትምህርት በተማሪ-ተኮር በኩል እየተተገበረ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎች ይህን የተማሪዎችን ብቃት እንዲያጎለብቱ ሆነው የሚቀርቡ መሆናቸውንና እነዚህም ብቃት የሚያጎለብቱት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ የሚገለጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ተዘጋጅተው የሚቀርቡት የተማሪው መማሪያ መፃህፍት ተማሪዎችን እንዲያሳትፉ ሆነው ተዘጋጅተዋል እንዳንዱም እየተዘጋጁ ናቸው ብለዋል፡፡

በሐላፊው አገላለጽ የተማሪዎቹ ብቃት እየጎለበተ የሚገኘው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው ላሉት ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተተግብሯል ተብሎ ሊነገር የሚችለው ከላይ የተመለከትናቸው የክፍል አደረጃጀት፣ የማቴሪያል አቅርቦት፣ የመምህራን ስልጠናና የመሳሰሉት ጉዳዮች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ መማሪያ መፃህፍቱ በተለይም እስከአሁን

እየተማሩበት የሚገኘው የ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ተማሪዎችን አሳታፊ ሆኖ የተዘጋጀ አይደለም፡፡ምናልባት ለወደፊት የሚዘጋጁት አሳታፊ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል፡፡ ለዚህም ይሆናል የባለስልጣኑ ምላሽም  አንዳንድ መፃህፍት ገና ተሰራጭተው በተማሪዎች እጅ ያልገቡ መሆናቸው የገለፁት፡፡ በምልከታ በታዩት 7ኛ ክፍሎች የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ግን በ1996 ዓ.ም ታትሞ በተማሪዎች እጅ ያለው የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ በበቂ ሁኔታ ቢገኝም የመምህሩ መምሪያና መርሀ-ትምህርት እንደሌለ  ከአፋን ኦሮሞ መምህራን የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህ የመማሪያ መፃህፍት አቅርቦት ችግር ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንቅፋቶች አንዱ በመሆኑ ከዚህ አንፃርም ተተግብሯል ማለት አይቻልም፡፡

ባለስልጣኑ ከሰጡት ምላሽ በመነሳት ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመማሪያ መጻህፍት ለየትምህርት ቤቶቹ መድረስ አለመድረሳቸውን በክልል ደረጃ የሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት ስለመኖራቸውና በዝግጅታቸው ላይ ያለው የተማሪዎች ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ጉጉት አደረብኝና ጠየኳቸው፡፡ እሳቸውም:-

> *በአዲስ መልክ የተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ሙሉ በሙሉ ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛው እርከን ትምህርት ቤቶች አልተሰራጨም፡፡ ...የአፋን ኦሮሞ የተማሪው መማሪያ መፃህፍትም ታትመው አልመጡልንም፡፡ የኛ ባለሙያዎች እየተነጋገሩበት ይገኛሉ፡፡...ሌሎቹን መማሪያ መፃህፍት ግን የመርሀ-ትምህርቱ አፅም ለኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ይላክና እኛ እንደ ክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ አሻሽለን እያዘጋጀን እንገኛለን፡፡ ...በክልል ደረጃ የሚገኙት ደግሞ እኛ በየክልላችን መምህራን ኮሌጆች ባለሙያዎች መርጠን እንዲያዘጋጁልን እያደረግን ነው፡፡ የሂሳብ ትምህርቶችና የአካባቢ ሳይንስ መማሪያ መፃህፍት በዚህ ዓይነት እየተዘጋጁ ናቸው፡፡ ስለሆነም በራሳችን ባለሙያዎች እየሰራን እንገኛለን እንጂ ተማሪዎች በዝግጅቱ ውስጥ ተሳትፈው አያውቁም፡፡ በቀረበልን መርሀ-ትምህርት ላይ ብቻ ተመስርተን እናዘጋጃለን (*ሁንዴ በቀለ፣/5/02/05 ፣ከ3፡45-4፡30 ሰዓት)፡፡/

በኋላፊው ገለፃ  መሠረት በአዲስ መልክ የተዘጋጁት መማሪያ መፃህፍት ይህ መረጃ እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ ሙሉ በሙሉ ያልተሰራጩ መሆኑ ነው ፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የመማሪያ መፃህፍት ተሟልተው ለተማሪው ካልደረሱ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ ክፍተት ሊፈጠር ይችላል ፡፡

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የስርዓተ-ትምህርት አዘገጃጀት አግባብ መሰረት ተማሪዎች መሳተፍ እንደሚኖርባቸው Nunan (1988) ይመክራሉ፡፡ በኃላፊው ገለፃ መማሪያ መፃህፍቱ ሲዘጋጁ በኮሌጅ ባለሙያዎች እንጂ የተማሪ ተሳትፎ እንደሌለ ነው፡፡ ከዚህ አንፃርም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ መርህ አለመተግበሩን ያመለክታል ፡፡

ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ክፍል ኃላፊ በመቀጠል ከአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን ኃላፊ ጋር በአፋን ኦሮሞ ትምህርት አሰጣጥና የመማሪያ መፃህፍት አዘገጃጀት ላይ ጥያቄ አቅርቤላቸው፡፡ በመጀመሪያ ጥያቄ እንደ አፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን ሐላፊነታቸው ምን ስራዎችን እንደሰሩና የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽህፍትስ ለየትምህርት ቤቶች ስለመሰራጨታቸው ለማወቅ የቀረበ ነበር፡፡ እሳቸውም፣

> *እኔ በቢሮው ውስጥ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ባለሙያ ነኝ ፡፡ የስራ ድርሻዬ በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ የሚሰጠው የአፋን ኦሮሞ ትምህርት በትምህርት ሚኒስቴር መርሀ-ትምህርት መሰረት በተመደበለት ክፍለ-ጊዜና በተዘጋጀለት መማሪያ መፃህፍት መሰረት ከአንደኛ ክፍል እስከ ኮሌጆች ድረስ እየተሰጠ መገኘቱን መከታተልና የሚዘጋጁ ማቴሪያሎችም ካሉ ማዘጋጀት እንዲሁም ስልጠና ካስፈለገም በስራችን ለሚገኙ መምህራን ስልጠና መስጠት ነው፡፡ ነገር ግን ለቦታው አዲስ በመሆኔ ስልጠናውን ባልሰጥም በአሁኑ ሰዓት የሚዘጋጁትን የአንደኛ ደረጃ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጻህፍት እየገመገምኩ ነው፡፡ የመገምገሚያ መስፈርቴም በስነ-ዘዴ ዙሪያ ተማሪዎችን አሳታፊ መሆን እንዳለበት፣ የአካባቢያችን ማህበረ-ባህል ሁኔታ ማንፀባረቁን፣ መርሀ-ትምህርቱን ተከትሎ መዘጋጀቱን፣ እየፈተሽኩ ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስ የሰራሁት ተግባራት እነዚህ ናቸው (ነገሪ ጫላ፣ /5/02/05 ከ4፡30-5፡30 ሰዓት )፡፡*

በአፋን ኦሮሞ ትምህርት ቡድን ሐላፊው አገላለጽ የስራ ድርሻቸው በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚሰጠውን የአፋን ኦሮሞ ትምህርት በመርሀ-ትምህርቱ ዕቅድ መሰረት እየተሰጠ መገኘቱን መከታተልና ስልጠናም ካስፈለገ መስጠት ነው፡፡ ነገር ግን ሐላፊው ይህን ቢሉም ለቦታው አዲስ በመሆናቸው ለወደፊት ለመታተም የተዘጋጁትን የአፋን ኦሮሞ የተማሪው መጽሐፍ ከመገምገም ውጪ በአግባቡ ወደ ስራ ያልገቡ መሆናቸውን ለመረዳት እንችላለን፡፡

በማስከተል ስለ አፋን ኦሮሞ መማሪያ የተማሪው መጽሐፍ ስርጭት ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፣

> *የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መፃህፍት ስርጭት አስመልክቶ በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ አጥንተን ለትምህርት ሚኒስቴር ብናቀርብም በጨረታና ውጭ ታትምው ይመጣሉ ከሚባለው ሁኔታ አንፃር*

> *በመዘግየታቸው እስከ አሁን ድረስ (2005 ዓ.ም ማለታቸው ነው) ታትመው ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አልተሰራጩም (ነገሪ ጫላ፣ /5/02/05 ከ4፡30-5፡30 ሰዓት) ፡፡*

በባለሙያተኛው አገላለጽ እስከ አሁን ድረስ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ የተማሪው መጽሐፍ ለየትምህርት ቤቶች አልተሰራጩም፡፡ ተማሪዎችን በአግባቡ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያሳትፉ መማሪያ መፃፍት መዘጋጀት ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ወሳኝ ናቸው፡፡ በፍጥነት በተማሪዎች እጅ ያለመግባታቸው ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ በዚህ ክፍል ው የተሰጠው እገዛ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የመምህራን ልማት ተጠሪ ሌላው የጥናቱ መረጃ ሰጪ ናቸው፡፡ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ያገኙት ስልጠና አወሳሰድ፣ በምን በምን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ እንደሆኑ ስልጠናዎች የሚሰጣቸው መምህራን የትኞቹ እንደሆኑና በመሳሰሉት ነጥቦች ላይ ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር፡፡

በአሁኑ ጊዜ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ መማር-ማስተማሩ የሚከናወንበት አቀራረብ ምን እንደሆነና አቀራረቡን ለማጠናከር ለመምህራን ምን ዓይነት ስልጠና እየተሰጣቸው እንደሚገኝ ጠየኩኝ፡፡ እሳቸውም በክልሉ ስለሚከናወነው የመማር-ማስተማር አቀራረብ፡-

> በአሁኑ ጊዜ በክልላችን በሚገኙት ትምህርት ቤቶች ውስጥ እየተከናወነ የሚገኘው የመማር-ማስተማር ሂደት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው፡፡ የአንደኛ ደረጃ መምህራኑ በተማሪ-ተኮር እያስተማሩ መገኘታቸውን ከራሳቸውም የምንሰማበት ሁኔታ አለ፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ቢሮ በኩልም እያረጋገጥን እንገኛለን *(ድሪባ ጫላ፣ /5/02/05፣ከ5፡30--6፡30 ሰዓት) ፡፡* ብለዋል፡፡

እንደ ኀላፊው ገለፃ በአሁኑ ጊዜ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድር ውስጥ በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተተገበረ ነው፡፡ ከላይ የዞኑና የተመረጡት ወረዳዎች የመምህራን ልማት ተጠሪዎች ከገለፁት ሀሳቦች ጋራ በመስማማት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተተገበረ መሆኑን አመልክተዋል ፡፡ ማረጋገጫቸው ግን ከመምህራኑና በቢሮው በኩል መሆኑንም ገልፀዋል፡፡

ሌላው በኋላፊው የተገለፀው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተተግብሯ መባሉ አግባብ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ከላይ ለማብራራት እንደተሞከረው ተተግብሯል ተብሎ ለመናገር ሊሟሉ የሚገባቸው አያሌ ክፍተቶች ሲሟሉ ነው፡፡ የመማሪያ ክፍል ጀምሮ እስከ መማሪያ መፃህፍት ስርጭት ድረስ በተገቢው መንገድ ያለመሟላታቸው፤የመማሪያ ክፍል በአግባቡ ያለመደራጀቱና ሌሎች ክፍተቶች ከተለያዩ መረጃ ሰጪዎች ከተገኙት ሀሳቦች ተተግብሯል ብሎ መናገር አይቻልም፡፡

በማስከተል ሀላፊው ለመምህራን የተለያዩ ስልጠናዎች ስለመስጠታቸውና ማን ስልጠናውን እየሰጠ እንዳለ ገልፀው ነበር፡፡

> *ለመምህራን በተለያዩ ርዕሶች ላይ ስልጠና እንሰጣቸዋለን፡፡ ለምሳሌ በተማሪ-ተኮር አተገባበር፣ በተከታታይ ምዘና፣ በስራ ላይ ምርምር አተገባበርና በመሳሰሉት ላይ እናሰለጥናቸዋለን፡፡ ከዚህም ውጭ ከመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ጋራ ግኑኝነት ስላለን እነሱም በበኩላቸው የሚሰጡት ስልጠና አለ ፡፡ በተለይም በመምህራን ተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ /CPD/ በኩል በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ስልጠናው ይሰጣል፡፡ በአጠቃላይ በክልላችን ውስጥ ከመቶ ሺህ መምህራን በላይ ስለሚገኙ ሁሉንም ጠርተን ማሰልጠን ባንችልም ከየትምርትቤቶቹ ተመልምለው ተመልሰው ጓደኞቻቸውን ሊያሰለጥኑ የሚችሉትን መምህራን ትምህርት ቤታቸው ወይም ወረዳቸው መርጠው እንዲልኩልን አድርገን እናሰለጥናቸዋለን (ድሪባ ጫላ፣ /5/02/05፣ ከ5፡30-6፡30 ሰዓት)፡፡*

ከመምህራን ልማቱ ሐላፊ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በተለያዩ ርዕሶች ላይ ለመምህራን ስልጠና መስጠቱን ነው፡፡ ስልጠናው ደግሞ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ያተኮረ መሆኑና በተለይም  በስራ ላይ ምርምር አተገባበር፣ እንዴት የሳይንስ ትምህርት እንደሚሰጥ፣ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበርና ተከታታይ ምዘና ላይ ያተኩራል፡፡ ስልጠናው በቢሮ ብቻ የሚከናወን ሳይሆን በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆችም በኩል እንደሚሰጥ ግልጽ አድርገዋል፡፡

ሐላፊው መምህራን በተለያዩ ርዕሶች ላይ ስልጠና እየሰጠን ነው ቢሉም ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች መምህራን የተገኙት መረጃዎች ስልጠና አለማግኘታቸውን ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ አንፃርም የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ክፍተት መታየቱን ማየት ተችሏል፡፡

በማስከተል ኃላፊው ለተማሪ-ተኮር አቀራረብና የአፋን ኦሮሞ መምህራን በኩል ያሉትን ስልጠናዎች በተመለከተ ገልፀው ነበር፣

> *የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ብለን ለብቻ ለይተን አናሰለጥንም፡ ፡ ለብቻ የአፋን ኦሮሞ መምህራን ብለን አሰልጥነንም አናውቅም። ነገር ግን በሳይንስ መምህራን ትምህርት አሰጣጥ፣ በተከታታይ ምዘና እንዲሁም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ማሻሻያ ላይ እናሰለጥናለን (ድሪባ ጫላ፣ /5/02/05፣ ከ5፡30-6፡30 ሰዓት) ፡፡*

በአጭሩ የመምህራን ልማቱ አጠቃላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ከማተኮር ባለፈ በቋንቋ መምህራን በተለይም በአፋን ኦሮሞ ትምህርት አሰጣጥ ላይ የተደረገ ስልጠና እንደሌለ ያስረዳናል። ይህ ሁኔታ ደግሞ የአፋን ኦሮሞ መምህራን እንደ ሳይንስ ትምህርት መምህራን ሁሉ ተገቢውን ስልጠና ካላገኙ በተማሪ-ተኮር አተገባበር ላይ ክፍቶች ሊታዩ እንደሚችሉ ያረጋግጣል ፡፡

## 5.3.7. በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

በክፍል ውስጥ ተማሪ-ተኮርን ለመተግበር የተለያዩ እንቅፋቶች እንደሚያጋጥሙ በክለሳ ድርሳናት ስር ተመልክተናል። በዚህ መሰረት በባሌ ዞን ውስጥ በሚገኙ ተጠኚ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአፋን ኦሮሞ የመማር-ማስተማር ሂደት ወቅት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ ችግሮች መኖር አለመኖራቸውን ለማወቅ የምታስተምሩበት የመማሪያ ክፍል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር አመቺ ነው? በማለት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ

> *…ይህ በብሎኬት የተሰራው የመማሪያ ክፍል (እያሳዩኝ) 7ኛ ክፍል የማስተምርበት በማሪያ ክፍል በጣም አመቺ ነው። ይህ ክፍል በመንግስት በጀት ደረጃውን ጠብቆ የተሰራ ነው። ወንበሮቹም በተመሳሳይ መንገድ ለክፍሉ እንዲመቹ ተደርገው የተሰሩ ናቸው። ሌላው ለምሳሌ እዚያ ያለው ከጭቃ (ህዝብ አዋጥቶ የሰራውን እያመለከቱ) በዝናብ ጊዜ ጭቃ ይሆናል፣ በበጋ ጊዜ ደግሞ አቧራማ ነው። በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ውስጥ ለማስተማር በጣም ያስቸግራል (ባጫ መገርሳ፣በ/07/09/05፣ ከ7፡00-8፡00 ሰዓት) ፡፡*

እንደ መምህሩ አገላለጽ የሚያስተምሩበት የመማሪያ ክፍሎች ሁለት አይነቶች ሲሆኑ በመንግስት የተሰራው የመማሪያ ክፍልና መቀመጫዎቹ ለመማር-ማስተማር ሂደት

እንዲመቹ ሆነው የተሰሩ በመሆናቸው ይህ ለስራቸው አመቺ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ሌለኛው ግን ከጭቃ የተሰራው በዝናብ ጊዜ ጭቃ፣በበጋ ደግሞ አቧራ በመሆኑ በውስጡ ለማስተማር እንደማያመቻቸው አመልክተዋል፡፡የመማሪያ ክፍል ምቹና ጽዱ ከሆነ በመማር-ማስተማር ተግባር ለሚሳተፉት መምህራንና ተማሪዎች መነሳሳት እንዲጨምር ያደርጋል፤ትምህርቱም ሳቢ ይሆናል Leu (2000) ያሉት በታየው የዜይበላ ትምህርት ቤት ሊታይ ችሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለኪጽጠቴ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ ያጋጠማችሁ ችግሮች ካሉ ቢገልፁ በማለት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሰጡኝ ምላሽ፡

> *ለማስተማር ሁሌ መታደስ አስፈላጊ በመሆኑ በተወሰነ ደረጃ የማስተማር ብቃት ይጎድለኛ ይሆን ብዬ እሰጋለሁ፡፡ ሌላው ለብዙ ጊዜ የመማሪያ መጽሐፍት እጥረት ነበረብን ነገር ግን ከ2005 ዓ.ም በኋላ በመጠኑ ተቀርፏል፡፡ እንደገና የክፍለጊዜ ብዛት (Work load) እንደተፈለገው ሊያሰራኝ አልቻለም፡፡ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ድረስ አስተምራለሁ፡፡ እንግዲህ በዚህ የክፍለ ጊዜ ብዛት ምክንያት እንደፈለኩት ተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ አላደረኩም ብዬ አስባለሁ፡፡ …ተማሪዎች በዚህ ባሉበት የትምህርት ደረጃ ዕድሜያቸው አስራ ስድስት ነው፡፡ ትልቁ ዕድሜያቸው ማለት ነው፡፡ በዚህ ላይ የገጠር ልጆች ናቸው፡፡ አጠገባቸው የሚቀመጡትን ሴቶችና ጓደኞቻቸውን የማጫወት፣ እርስ በርስ መላፋት ሁኔታ ይታያል፡፡* (ባጫ *መገርሳ*፣ በ/07/09/05፣ ከ7፡00-8፡00 *ሰዓት* )*፡፡*

የሚል ነበር፡፡

ከመምህሩ ምላሽ የምንገነዘበው ለመማር- ማስተማር ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸውና በዚህም ጉድለታቸውን ማጎልበት ያለመቻላቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ብዙ ክፍለ-ጊዜ በመያዛቸው እንደተፈለገው በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎ እንዲጨምር አለማድረጋቸው አመልክተዋል፡፡ ሌላው ከተማሪዎች የስነ-ምግባር ችግር መፍታት ያለመቻል ነው፡፡ ለተጠቀሱት ሶስት ችግሮች የመፍቻ መንገድ የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት ነው፡፡ ይህ ካልሆነ በራሳቸውም እንደተብራራው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራው ችግር አለበት ማለት ነው ፡፡

ለሐውሾው ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ያጋጥሟቸው ችግሮች ስለመኖራቸው እንዲያብራሩልኝ ጠይቄ የሚከተለውን ምላሽ አግኝቻለሁ፤

> *…ተማሪዎች ለመምህራን ጥሩ አመለካከት የላቸውም። ምክንያቱም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስናስተማር ሁሌ በራሳቸው ሀሳብ እንዲያመነጩ፣ እንዲወያዩ፣ ቅድሚያ እንዲናገሩ ስለምናደርግ መምህራን እውቀት እንደሌላቸው አድርገው የመቁጠር ሁኔታ ይታያል። የተማሪ - ቤተሰብ በበኩላቸው ልጆቻችንን አንድ ላይ በማጎር ታያላችሁ የሚል ሀሳብ አለ። ይህ ሁኔታ እንደ ችግር አድርጌ ወስጄዋለሁ። ሌላው ደግሞ በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች በቁጥር መብዛት የሁሉንም ተማሪዎች ሀሳብ ሳልቀበል ለትምህርቱ የተዘጋጀው ክፍለ ጊዜ ይጠናቀቃል። የማቴሪያል አቅርቦት ችግርም አለ። የተማሪው መማሪያ መፃህፍት በበቂ ሁኔታ ቢኖርም የመምህሩ መምሪያና የትምህርቱ መርሀ-ትምህርት የለም። አንዳንድ በትምህርቱ ይዘቶች ውስጥ የሚያጋጥሙንን ችግሮች ለመፍታት ስንፈልግ ችግር ያጋጥመናል። እኔ አሁን ሀያ ስድት ክፍለጊዜ በሳምንት አስተምራለሁ፣ በቀን ከአምስት ክፍለጊዜ በላይ ማለት ነው።ከ5-8ኛ ክፍል አስተምራለሁ ከዚህ በመነሳት በተፈለገው መጠን ተማሪዎችን አስተምሪያለሁ ለማለት እቸገራለሁ (ባዩ ቀልቤሳ፣በ/10/02/06 ፣ከ4፡00-5፡00 ሰዓት) ።*

በመምህሩ አገላለፅ በአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ያጋጠሟቸው ችግሮች ሲጠቃለሉ የተማሪዎችና ቤተሰብባቸው ለመምህራን ጥሩ አመለካከት ያለመኖር፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ቁጥር መብዛት የተነሳ እንደፈለጉት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለመሳተፍ፣ የትምህርት መሳሪያዎች በተለይም መርሀ-ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ ያለመኖር፣ በአንድ ሰው እየተሸፈነ የሚገኘው የክፍለ-ጊዜ መብዛት እነዚህ የተዘረዘሩት ችግሮች ለመማር-ማስተማር ሂደት በተለይም ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ትላልቅ ችግሮች መሆናቸው በዚህ ጥናት ወረቀት በምዕራፍ ሶስት ላይ በተለያዩ ምሁራን ተብራርቷል። በመሆኑም እነዚህ ሁኔታዎች እያሉ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተተግብሯል ማለት አይቻልም።

በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ላይ ያሉትን ችግሮች ለመፈተሽ ሌላው መረጃ የተሰበሰበው በአሊ ቢራ ትምህርት ቤት አፋን ኦሮሞን ከሚያስተምሩ መምህርት ነው። በትምህርት ቤታቸው ውስጥ አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ ያጋጠማቸው ችግሮች መኖር ያለመኖራቸውን ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ብለዋል፤

*ብዙውን ጊዜ ችግሮች የሚታዩት በአተገባበር ሂደት ላይ ነው። እነሱም፦የክፍል ተማሪዎች በቁጥር በብዛት መኖር፣የተማሪዎች መቀመጫ ለቡድን ውይይት አመቺ አለመሆን፣መርሀ-ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ ያለመኖር፣ በአግባቡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር እንቅፋቶች ናቸው (ብርቄ ፈይሳ፣በ/03/10/04 ፣ከ9፡00-10፡00 ሰዓት)*

በማለት አብራርተዋል።

በተጨማሪም በዚሁ ትምህርት ቤት ውስጥ የ7ኛሀ ክፍል ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን ሲማሩ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ያጋጠማቸው ችግሮች ካሉ እንዲያስረዱኝ ለቡድን ውይይት ተሳታፊ ተማሪዎች አቅርቤ የሰጡኝ ምላሾች የሚከተለውን ይመስላሉ።

*መምህራን በጋራ እንድንሰራቸው ያቀረቡልንን ተግባራት ተማሪዎች እኩል ተሳትፈውበት አይሰሩትም፤ በብዛት ጎበዝ ተማሪ ብቻ የሚሰጡትን መልመጃዎች በተደጋጋሚ ይሰራል፤ ሌላው ደግሞ እርስበርስ ያለመደማመጥ ሁኔታ ይታያል። (አደም በክሪ፣ በ/03/10/04 ፣ ከ8፡00-9፡00 ሰዓት)*

*ተማሪዎች በተፈለገው መሰረት በቡድን ውስጥ ያለመሳተፍ ሁኔታ ይታያል፤ የተሰጡንን መልመጃዎች ቶሎ ቶሎ ሰርተን ለመምህራችን ስናቀርብ እሳቸው ደግሞ ቶሎ አያርሙልንም (ጫልቱ ቶላ፣ በ/03/10/04 ፣ከ8፡00-9፡00 ሰዓት) ።*

*…አንዳንድ ተማሪዎች ቶሎ ቶሎ አብሮ የመስራት ችግርና ስራዎችን በሰዓቱ ያለማስረከብ ሁኔታ አለ፤ አንዳንድ ተማሪዎች ደግሞ በቂም ነገር ውስጥ ይረብሻሉ (ጌቱ ከበደ፣ በ/03/10/04 ፣ ከ8፡00-9፡00 ሰዓት)።*

*…የቡድን ስራ ሲሰጠን በሌላው አንዱ ሌላው ላይ የመለጠፍ ሁኔታ ይታያል፤ መምህራችን የእኛን ሀሳብ የመቀበል አለመፈለግ ሁኔታ ያታያል፣ የመቀመጫ ችግሮች፣ ተማሪዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጥቅምን ያለመረዳት የሚታዩ ችግሮች ናቸው (ፋጡማ አሊ፣ በ/03/10/04 ከ8፡00-9፡00 ሰዓት)።*

በተማሪዎቹ ማብራሪያ የተገለፁትን ጭብጦች ስንተነትነው አፋን ኦሮሞን በቡድን ሲማሩ ሁሉም ተማሪዎች በእኩል ደረጃ ተሳትፎ አድርገው መልመጃውን እንደማይሰሩት ነው። እንደዚህ ያለ ሁኔታ እንደሚያጋጥም የስነ-ትምህርት ባለሙያዎች ያስረዳሉ። በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ሁሉ እኩል የመማር ችሎታ እንደሌላቸው ያብራራሉ።

በመሆኑም ግን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርቱ ሲቀርብላቸው ጎበዝ ተማሪዎች ከደካሞቹ ጋራ ተጣምረው በቡድን ተግባራትን ሲያከናውኑ ደካማውም ሆነ ጎበዙ ያላቸውን ዕውቀት አዋጥተው በመፃፍ የመማማር ተግባራትን መከወን እንደሚኖርባቸው ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን ለማሳተፍ ማወቅ የሚገባቸው መሠረታዊ ነገሮች ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ በቡድን ተሳትፎ ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች እንዴት መሳተፍ እንደሚገባቸው፣ እንዴት ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ፣ ተማሪዎቹ በሚገኙበት እድሜ ምን ዓይነት ባህሪያትን እንደሚያሳዩ ከስነልቦና አንፃር ማወቅና እንዲሳተፉ ማድረግ የመምህሩን ዕውቀት ጠያቂ ነው፡፡ ይህን እውቀት ያለማግኘት ተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተገበረ ማለት ዘበት ይሆናል፡፡

ይህንኑ ለኪጵጠቴ፣ሐውሸና አሊቢራት ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን የቀረበውን ጥያቄዎች ለዜይበላ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር አቅርቤላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

> *…የተማሪ-ተኮርን ለመተግበር የተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ መብዛት የለባቸውም፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው የተማሪዎች አግባብ ከሀምሳ መብለጥ እንደሌለበት የትምርት ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን በዜይበላ ትምህርት ቤት ውስጥ እስከ ሰባ ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችን በተፈለገው መንገድ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ለማሳተፍ አዳጋች ሆኖብኛል (ዋጋሪ ተሉሳ፣ በ/28/07/04፣ከ3፡00-4፡00 ሰዓት) ፡፡*

በተገለፀው ትምህርት የአፋን ኦሮሞ መምህር ሀሳብ ተማሪዎች ብዙ በሆነባቸው ክፍሎች ውስጥ የተማሪ-ተኮርን በአግባቡ ለመተግበር እንደሚያዳግታቸው ምሳሌ በመስጠት ያብራሩት እንጂ በምዕራፍ ሶስት ስር በተገለፀው መሰረት ለመምህራንና ለተማሪዎች ተገቢ የሆነ ስልጠና በመስጠት ችግሩ መቅረፍ እንደሚቻል የመስኩ ባለሙያዎች ይመክራሉ፡፡ይህን አስመልክተው Hess (2001) እንደገለፁት ለመምህራን ስልጠና ሲሰጥ ብዙ የተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን በጎ ጎኖች፣ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች፣ የክፍል አመራር፣ ስነ-ስርዓት አከባበር፣ የጥንድና የቡድን ስራዎች ለትብብራዊ መማር ድጋፍ መሆናቸውን፣ በጥቂት የሰው ሀይል

ብዙ ማስተማር ስለሚቻልበት፣ የተለያዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ስለማነሳሳት አስፈላጊነትና ስለመሳሰሉት መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር ተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር የተማሪዎች ብዛት ሊገድበን እንደማይችል የግንዛቤ እጥረት እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው በምልከታዬ ያረጋገጥኩት የአፋን ኦሮሞ መምህር ተማሪዎች ሲወያዩ በሚያሰሙት ጫጫታ "አትረብሹ" በማለት ተማሪዎችን በቁጣ ሲያስደነግጡ ለማየት በመቻሌ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ መምህሩ የተማሪ-ተኮር የክፍል ውስጥ ባህሪያትን በአግባቡ ካለመረዳት የመጣ ችግር በመሆኑ ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ያስገነዝበናል፡፡

ሌላው በትምህርት ቤት ውስጥ የታየው ችግር መምህራን በያዙት የሳምንት ክፍለ-ጊዜ ብዛት የተነሳ በተፈለገው መንገድ የተማሪ-ተኮርን ለመተግበር ከባድ እንደሆነባቸው ነው፡፡ አንድ መምህር በሳምንት ከሃያ አራት እስከ ሰላሳ ክፍለ-ጊዜ ይዞ ተማሪዎችን እንደተፈለገው በትምህርት ውስጥ አሳትፋለሁ ማለት ሊከብድ ይችላል፡፡ በኪጵጠቴና በሀውሾ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ምልከታ በማደርግበት ወቅት የገጠመኝ ጉዳይ ከዚህ ነጥብ ጋራ ተመሳሳይ ነው፡፡ አንድ መምህር ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ አፋን ኦሮሞን ያስተምራል፡፡ ትምህርት ቤቶቹ በቅጥር ወይም በዝውውር መምህራንን እንዲመደቡላቸው ለወረዳ ትምህርት ቢሮ ጥያቄ ቢያቀርቡም ከወረዳው በጀት ወይም ቦታ የለንም የሚል ምላሽ በመሰጠቱ ከአቅም በላይ የሆነ የአፋን ኦሮሞ መምህራን እጥረት እንዳለ ተመልቻለሁ፡፡ ከዚህ ችግር የተነሳ ሁሌ መምህራን በተፈለገው መንገድ ትምህርቱን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር እንዳልቻሉ ይገልፃሉ፡፡

አንድ መምህር በቀን ብዙ የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ከያዘ ከድካሙ የተነሳ ተማሪዎችን በተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች ለማስተማር ሊከብደው ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎችን በንቃት በማሳተፍ ተማሪ-ተኮርን ይተገብራሉ ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የመምህራን ዝግጅት ጠንካራ ሊሆን የሚችለው የሳምንት ክፍለ ጊዜ ጥቂት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ የተማሪ-ተኮርን ከመተግበር ይልቅ ትምህርቱ በመምህር-ተኮር አቀራረብ እንዲቀርብ በር ይከፈታል ፡፡

### 5.3.8. ለአፋን ኦሮሞ መምህራን የተደረጉ እገዛዎች

በአንድ የትምህርት ስርዓት ላይ ለውጥ ተደርጎ ያ ለውጥ ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ በተወሰኑ አካላት ተሳትፎ ብቻ ከታለመው ግብ ሊደርስ አይችልም፡፡ ይህን አስመልክተው Mccombs and Whisler (1997) የተማሪ-ተኮር በተወሰኑ አካላት ተሳትፎ ብቻ ተግባራዊ ይሆናል ማለት አስቸጋሪ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ከመምህራንና ተማሪዎች በስተጀርባ የሌሎች በትምህርት ዙሪያ ድጋፍ የሚሰጡ አካላት እገዛ ይፈልጋል፡፡ በዚህ ጥናት ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከመማር-ማስተማሩ በስተጀርባ የሌሎች አካላት እገዛ ምን እንደሚመስል በቃለ-መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡

አፋን ኦሮሞን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ጉድለቶች ሊኖሩብዎ ይችላል ይህንንም ጉድለቶች አሉብኝ ብለው አስበው ከሆነ እነዚህን ጉድለቶች ለመቅረፍ ምን ቢደረግ የተሻለ ይሆናል ብለው ያስባሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ የኪጵጠቱ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር የመለሱት

> *በኮሌጅ መምህራን፣በዘርፉ እውቀት ካላቸው ምሁራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዙሪያ ስልጠና ባገኝ አሁን ከማስተምረው በላይ በሚገባ አስተምራለሁ ብዬ አስባለሁ፡፡እኔም ዕውቀቱን አግኝቼ ለተማሪዎቼ ሙሉ ዕውቀት እንዲያገኙ አደርጋለሁ* (ባጫ መገርሳ በ/07/09/05፣ ከ7፡00-8፡00 *ሰዓት)፡፡* በማለት ነበር፡፡

ከዚህ መምህር ሀሳብ የምንገነዘበው በስልጠና ረገድ በትምህርት ኀላፊዎች በኩል እገዛ ያልተደረገላቸው መሆኑን ነው፡፡ ስልጠና እንዲሰጥና በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ክፍተቶች ዙሪያ መምህሩ ብቻ ተጠያቂ ሊሆን እንደማይችልም ያመለክታል፡፡ የትምህርት ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራንና ሌሎች ኀላፊዎችም የአፋን ኦሮሞ መምህራን ያሉባቸውን ችግሮች ነጥለው በመለየት በዚያ ክፍተት ላይ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሟቸው የሚያግዙ መሆን እንዳለባቸው የሚመኙ ናቸው፡፡

ለሐውሾ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ ያጋጠምዎት የነበሩት ችግሮች ምንድን ናቸው? ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄዎች

> *…የተማሪው መማሪያ መፃህፍት በበቂ ሁኔታ ቢኖርም የመምህሩ መምሪያና የትምህርቱ መርሀ-ትምህርት የለም፡፡ አንዳንድ በትምህርቱ ይዘቶች ውስጥ የሚያጋጥሙኝን ችግሮች ለመፍታት ስንፈልግ ችግሮች አሉ ፡፡ እኔ አሁን ሀያ ስድት ክፍለ-ጊዜ በሳምንት*

> *አስተምራለሁ፣ በቀን ከአምስት ክፍለ-ጊዜ በላይ ማለት ነው (ባዩ ቀልቤሳ ፣በ/07/09/05 ፣ከ4፡00-5፡00 ሰዓት) ፡፡*

በማለት ያሉባቸውን ጉድለቶች አብራርተዋል፡፡

በዚህ መሠረት የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ቢኖርም የመምህሩ መምሪያና መርሀ-ትምህርቱ ተካተው አልቀረቡም፡፡ ከዚህ አንፃር ከትምህርት ቤቱ ከፍተኛው የትምህርቱ አገዛው አናሳ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከዚህም ሌላ በመምህሩ ላይ ከፍተኛ የሆነ የክፍለ ጊዜ ጫና መኖሩ ከመምህራን ቅጥር ጋራ የሚሄድ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በጀትና የሰው ሐይል ጠያቂ ነው፡፡ በመሆኑም ችግሮቹ በትምህርት ቤቱ ብቻ ወይም በወረዳው ብቻ ሊፈታ ስለማይችል ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ የሆኑትን አካላት ጠያቂ ነው፡፡ ችግሮቹ በጋራ ካልተፈቱ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተተግብሯ ብሎ መናገር አይቻልም፡፡

ሌላው በዚህ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር እንደችግር ያነሱት ነጥቦች

> *…የሚነበቡ ማቴሪያሎች ችግር፣የመምህራን ስልጠና በየጊዜው ቢሰጥ፣የሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ የሚሳተፉት ሠልጣኞች ከመማር-ማስተማር ጋራ በቀጥታ የተያያዙ መሆን ሲገባቸው ቀጥታ ተያያዥ ያልሆኑ ሰዎች ስልጠና የመውሰድ ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡ ይህ ሁኔታ መሻሻል ይኖርበታል (ባዩ ቀልቤሳ፣ በ/07/09/05፣ ከ4፡00-5፡00 ሰዓት)፡፡ የሚሉ ናቸው፡፡*

የሚነበቡ ማቴሪያሎች ችግር የተባለው ከመማር-ማስተማሩ ሂደት ባሻገር ተማሪዎች ዕውቀታቸውን የሚያሰፉበት የተለያዩ ጽሁፎች በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያለመኖራቸውን ለመግለጽ ነው፡፡ ንባብ ለማንኛቸውም ተማሪ ትልቅ ዕውቀት ማግኛ መንገድ እስከሆነ ድረስ በዚህ ረገድ ይህ አለመኖሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይም አሉታዊ አንደምታ አለው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በመምህሩ ብቻ ላይ የሚተው ጉዳይ ሳይሆን የትምህርት ቤቱ አመራር አካላትን ተሳትፎ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

ሌላው በመምህሩ የተነሳው ነጥብ በመማር-ማስተማር ዘዴዎች ላይ አንዳንዴ ስልጠና ቢሰጥም በዚያ መርሀ-ግብር ላይ ተሳታፊ የሚሆኑት ከመማር-ማስተማር ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከአንድ ወረዳ ቢሮ ውስጥ የሚሰራው ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ስልጠና ወስዶ ተመልሶ ቢሮው ውስጥ የሚቀመጥ ከሆነ ፋይዳ የለውም፡፡ ነገር ግን ስልጠናውን ወስዶ በሰለጠነበት መንገድ

ስልጠናውን ላላገኙት መምህራን ከሰጠ አንዳች አስተዋጽኦ እንዳበረከተ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ካለበለዚያ ስልጠና ወስዶ ተመልሶ ሌላውን ካላሰለጠነና ቢሮ የሚገባ ከሆነ መምህራን ሰልጥነዋል ተብሎ ሊነገር አይገባም፡፡ ይህም ማለት ሥልጠና ሲሰጥ አግባብ ላለው የሥልጠናውን ውጤት ተግባራዊ ማድረግ ለሚችል ባለሙያ መሆን ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

እንደዚሁም የአሊ ቢራ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርም

> …የመማሪያ ክፍሉ በአግባቡ ተማሪዎች እንዲሳተፉበት ባያደርግም፣ የተለያዩ አቅርቦቶች ባይሟሉም፣የተለያዩ ጉድለቶች ቢኖሩብንም የመማር-ማስተማሩ አቀራረብ ተማሪ-ተኮር ነው ማለት ይቻላል (አበበ መርጊያ፣ *በ/03/10/04፣ ከ9፡00-10፡00 ሰዓት*)፡፡

እንደሌሎች ትምህርት ቤቶች ሁሉ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር እንቅፋት የሆኑ ችግሮች በመምህራን ብቻ የሚፈቱ ሳይሆኑ የሌሎችን አገዛ የሚፈልጉ መሆናቸውን ያመለክታል ፡፡ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርም ያነሷቸው ነጥቦች አንዳንዶቹ ከራሳቸውም በላይ የሆኑና የወረዳና የትምህርት መምሪያን ብሎም የትምህርት ቢሮን እገዛና ድጋፍ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪ-ተኮር አቀራረብን አልተገበሩም፣ ይህ ጉዳይ በርግጥ የመምህራን ችግር ነው ብሎ መደምደም የሚያመች አይደለም፡፡ በዚህ ሁኔታዎች ባልተሟሉላቸው ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር ጥረት ስለማድረጋቸው ከአፋን ኦሮሞ መምህራን ጋር ከተካሄደው ውይይት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አንዱ የቡድን-ተኮር ተሳታፊ

> *…ተማሪዎች እንደ ፕሮጀክት በተሰጣቸው ስራ ላይ በራሳቸው የሀገር ሽማግሌዎች፣ የገዳ አባቶች፣ የአገር ሀላፊዎች፣የጤና ባለሙያ ጋ ሄደው የሚያቀርቡት ነገር አለ፡፡ ለምሳሌ በ7ኛክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ (ገጽ፣23) ላይ ስለ /ኤች አይ ቪ / መንስኤና አሰረጫጨቱ ከባለሙያ ጠይቻቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አድርጉ የሚል አለ፡፡ ጥያቄውን ለመስራት ተማሪዎቹ እስከ ጤና ጣቢያ ድረስ ሄደው ባለሙያዎችን ጠይቀው፣ መጽሐፍ አንብበው* አቀናጅተው መጥተዋል…፡፡(ብርቄ ፈይሳ፣ *በ/03/10/04፣ ከ9፡00-10፡00 ሰዓት )* ፡፡

በርግጥ በተሰጠው ምሳሌ ከቡድን ውይይት ተሳታፊ መምህርት የምንገነዘበው በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡትን ትምህርት ተጨባጭ ለማድረግ ብቻቸውን ሊያሳኩት ስለማይችሉ

ከሌሎች አካላት ጋራ ጥምረት በመፍጠር ተማሪዎቹ የተፈለገውን ዕውቀት እንዲጨብጡ ጥረት ማድረጋቸውን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል ለአሊ ቢራ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር በትምህርት ቤታቸው ውስጥ በአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እንዴት እየተተገበረ እንደሚገኝ ለማወቅ ባቀረብኩላቸው ጥያቄ ምላሽ

> …እንደ ትምህርት ቤታችን የወንበሮች ምቹ ያለመሆንና በስነ-ምግባር ሁሉም ተማሪዎች ጥሩ ናቸው ማለት ባይቻልም… (አበበ *መርጊያ፣በ/03/10/04 ፣ከ9፡00-10፡00 ሰዓት*)፡፡

ያሉትን ሀሳቦች ስንመለከት የወንበሮቹ አለመመቸት ከበጀት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በጀቱ በሌላ አካል የሚመደብ በመሆኑ ከትምህርት ቤቱ አቅም በላይ ነው፡፡ ይህ የሌሎች እገዛ አናሳ መሆኑን ሲያመለክት፣ የተማሪዎቹ የስነ-ምግባር ችግር ደግሞ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋራ በመረባረብ በመምከርና ከራሳቸው ከተማሪዎች ጋራ በመወያየት የሚመጣ መፍትሄ ነው፡፡ በአጭሩ ከክፍል ውስጥ መማር-ማስተማር ጎን እነዚህ የተጠቀሱት አካላት እገዛ አለመኖር ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ክፍተት ፈጣሪ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የሐዋላፊዎችን እገዛ አስመልክቶ ለዜይበላ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ለቀረበላቸው ጥያቄ፣

> *…በሒሳብ ትምህርትና በተፈጥሮ ሳይንስ ላይም በትምህርቱ አሰጣጥ ላይ በBESO ፕሮጀክት ድጋፍና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በኩል የሚሰጡን የሙያ ማበልፀጊያዎች አሉ፡፡ በእነዚህ ሙያ ማሻሻያዎች ድጋፍ አማካኝነት መምህራን የማስተማር ብቃታቸውን እያሳደጉ ይገኛሉ (እሸቴ ድሪባ፣29/09/04፣8፡00-9፡00 ሰዓት)፡፡*

በርዕሰ መምህሩ ማብራሪያ መሰረት ለትምህርት ቤታቸው መምህራን በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅና *በBESO ፕሮጀክት* ድጋፍ በተለያዩ ትምህርቶች አተገባበር ላይ ድጋፍ ሲደረግላቸው እንደነበር ገልፀዋል ፡፡ ይህ በBESO ፕሮጀክትና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ድጋፍ የተለያዩ ሙያ ማበልፀጊያ እገዛዎች መሰጠታቸው ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ አንፃር አግባብነት አለው፡፡

ስልጠና እየተፈለገ ነገር ግን በበጀት እጥረት ምክንያት እንዲቀር መደረጉ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስልጠና አንፃር ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የሚከሰትና እየተከሰተም ያለበት ሁኔታ ግልጽ ነው፡፡ በተለይም በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ግንባር ቀደም ተሰላፊ የሆኑት መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር ስልጠና ማግኘት እንዳለባቸው ምሁራን በእጅጉ ይመክራሉ፡፡ ተማሪዎችም ቢሆኑ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እንዴት ተሳትፎ ማድረግ እንደሚገባቸው ግንዛቤ እንዲያገኙ ሊሰለጥኑ ይገባል፡፡ ሆኖም ግን ከበጀት እጥረት የተነሳ ሳይተገበር መቅረቱ ለመምህራን የሚደረገው እገዛ አናሳ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሮቤ ወረዳ የመምህራን ልማት ተጠሪ የተገለፀው ሀሳብ የተማሪ-ተኮርን ለመተግበር ከነሱ አልፎ ከበጀት ጋራ የተያያዙ የሌሎች ሴክተሮች እገዛ የሚፈልግ በግልፅ ይታያል ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሚሰጡ ስልጠናዎች በቂ ያለመሆናቸውን የአጋርፋ ወረዳ የመምህራን ልማት ተጠሪ የሆኑትን ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ የስልጠና አሰጣጥ በጠየኳቸው ጊዜ ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡ የስልጠናውም በቂ ያለመሆን የሚመነጨው የስልጠና ቀናት ከማጠር የመጣ ምክንያት ነው፡፡ የስልጠናው ቀን ማጠር ደግሞ ከሚከፈለው የውሎ አበል ክፍያ ጋራ የተያያዘ ነው፡፡ በአንድ መልኩ በቂ ጊዜ አለመመደብ ፣በሌላ መልኩ ደግሞ የስልጠናው አግባብነትና አነስተኛ መሆን እንደዚሁም ሥልጠናው ለሚገባ ሰው አለመሰጠቱ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተግባራዊነት የሚገባ እገዛ አለመኖርን አስከፊ አድርጎታል፡፡

ከላይ የመተንተኛ ጭብጦቹን ሀሳቦች ለማጠቃለል ስንሞክር ከክፍል አደረጃጀት አንፃር በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ ምቹ የመማር-ማስተማር ሂደት የሚከናወንበት ሁኔታዎች ያሉ በመሆናቸው በአንፃራዊነት የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር ያስችላቸዋል፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚታየው ሁኔታ ደግሞ የኮሌጁ ተቃራኒ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በግብዓትነት የተገኙት ስልጠናዎች ተግባራዊ ሊሆኑ እንዳልቻሉ ያመለክታሉ፡፡ ሌላው በመማር-ማስተማር አተገባበር አንፃር የአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህራን በተዘጋጀላቸው የማስተማሪያ ሞጁል ያስተምራሉ ፡፡ የመማሪያ ሞጁሉ ደግሞ ሰልጣኞችን እንዲያሳትፍ ተደርጎ የተዘጋጀ በመሆኑ ተማሪ-ተኮርን ለመተግበር ያመቻል፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መፅሐፉ ተማሪዎችን አሳታፊ ሆኖ አልተዘጋጀም፡፡ የመማር-ማስተማሩ ተግባርም በተማሪዎች በአንድ ክፍል መብዛት፣ ከመቀመጫዎች አለመመቸት፣ ከአፋን ኦሮሞ መምህራን ተገቢ

ስልጠና ያለማግኘትና ከመሳሰሉት ሁኔታዎች አንፃር የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር አስቸጋሪ ሁኔታዎች ተስተውለዋል፡፡

በመምህራን ስልጠና ረገድ በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ በከፍተኛ ዲፕሎማ፣ በእርስ በርስ ስልጠናና በሌሎች ድጋፍ ሰጪ አካላት ለአፋን ኦሮሞ መምህራን የስራ ላይ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ግን የአፋን ኦሮሞ መምህራኑ በቅድመ ስራ ስልጠና ላይ ብቻ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ በተማሪዎች የግምገማ ስልት በኩል በኮሌጅና ትምህርት ቤቶችም ተመሳሳይ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ በአጠቃላይ በቅድመ ስራ ስልጠና የተገኙት ግብዓቶች በአንደኛ ደረጃ ላይ ከተለያዩ ሁኔታዎች አንፃር ተግባራዊ ያለመሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ በመምህራን እገዛ በኩል ደግሞ በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ አሰልጣኞቹ ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆን በአንደኛ ደረጃ በኩል አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአንደኛ ደረጃ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በቀድሞ ስርዓተ-ትምህርት የተመረቁት መምህራንም ሆኑ በአዲሱ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ የተመረቁት ከሁኔታዎች አለመሟላት የተነሳ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ሊተገብሩ አልቻሉም፡፡ በስልጠና በኩል ብቻ ከአንድ ትምህርት ቤት የስራ ላይ ስልጠና ለማግኘት እንደቻለ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 5.4.ማብራሪያና ውጤት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በባሌ ዞን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መመርመር ነበር፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስና የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይረዳ ዘንድ ከመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአሰልጣኝ መምህራን ቃለ-መጠይቅ፣ ከዕጩ መምህራንና የክፍል ኃላፊዎች፣ ከተመረጡ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራንና የትምህርት አመራር አካላት እንዲሁም ከተማሪዎችና ከሰነድ ፍተሻ የተለያዩ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡

በዚህ አይነታዊ ምርምር የተጠኑት አራት ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ የ7ኛ ክፍል መምህራንና በክፍሉ ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም በባሌ ዞን ውስጥ የሚገኘው

የሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ ስራ ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመቅረፀ-ድምጽ የታገዘ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የቡድን ተኮር ውይይትና የሰነድ ትንተና ናቸው፡፡ በእነዚህ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ለአብነት እየተወሰዱ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

የመጀመሪያው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን ለማስተማር እንዲበቁ የሚሰጣቸው የስልጠና ግብዓቶች ምንድን ናቸው? የሚል ሲሆን ለዚህም ጥያቄ ምላሽ ማግኘት በኮሌጁ ውስጥ የሚያሰለጥኑ የአፋን ኦሮሞ አሰልጣኝ መምህራንና የ3ኛ ዓመት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምልከታና ቃለ-መጠይቅ እንዲሁም በቡድን ተኮር ውይይትና የፕራክቲከም ሰነዶች ላይ በመመስረት የአሰለጣጠን ግብዓቶችን ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከኮሌጁ አመራሮች ዋናና ም/አካ/ዲን፣የመምህራን ሙያ ማበልፀጊያ አስተባባሪ እንዲሁም ከስነ-ትምህርት አሰልጣኝ መምህር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ለተነሳው መሰረታዊ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ተደርጓል፡፡

ከላይ የተነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ከዕጩ መምህራን ስልጠና የሚወስዱበት የመማር-ማስተማር አውድ የሚከናወንበት የመማሪያ ክፍል ወለል፣ ኮርኒስ፣ የመስኮቶቹ ስፋት፣ የጥቁር ሰሌዳው ጥራት፤ ሰልጣኞች በማንኛው የአየር ሁኔታ ውስጥ ሳይጨናነቁ በሚገባ ለመማር እንዲችሉ ስለሚያደርጋቸው ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አዎንታዊ ግብዓት ታይተዋል፡፡ የመማሪያ አካባቢ ሳቢ ከሆነ የሚሰጠው ትምህርት በሚገባ ለተማሪዎች እንዲደርስና በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በንቃት ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በአግባቡ ተሳታፊ በመሆን ስልጠናውን ከተወጡ ደግሞ በተራቸው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በቂ ግብዓት በማግኘታቸው ተግባራዊ ለማድረግ አቅም ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በታላሚው የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ለተማሪዎች ሁሉ በቂ ክፍተት ያለበት፣ መቀመጫዎቹ ተንቀሳቃሽ፣ ክፍሉ መምህራን በቡድን ውስጥ እየተዘዋወሩ እገዛ ለማድረግ የሚያመች ነው፡፡ ምልከታ በተደረገበት የ3ኛ ዓመት የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ሰልጣኞች መማሪያ ክፍል ውስጥ ወንዶች 19 ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ 28 በጠቅላላው 47 ተማሪዎች ያሉበት ክፍል በመሆኑ የተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ጋራ

የተመጣጠነ ነው፡፡ ይህም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን ለማስተማር ለሚሰጠው ሁኔታው አመቺ እንደሆነ ያመለክተናል፡፡

በምልከታ በታየው የኮሌጁ የአፋን ኦሮሞ የመማር-ማስተማር ሂደት አቀራረብ ሲጤን መምህሩ ትምህርቱን ሲያቀርቡ የነበረው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርህ መሰረት እየተገበሩት መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ሰልጣኞች በቡድን ተደራጅተው በተሰጣቸው ተግባራት ላይ እየተወያዩ ሲማማሩ በነበረበት ወቅት መምህሩ በተወያዮቹ መካከል እየተዟዟሩ ይረዷቸው ነበር፡፡ ተማሪዎችም በቡድን የተወያዩበትን በተወካዮቻቸው አማካኝነት ዘገባ ሲያቀርቡ፣ ጥያቄዎችን ሲመልሱና በመማር-ማስተማሩ ሂደት ሲሳተፉ መታየታቸው ተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተግባር ማሳየታቸውን ያመለክታል፡፡ በመማሪያ ክፍሉ የመማር-ማስተማሩን ተራክቦ ስንመለከት ሰልጣኝ መምህራን (ተማሪዎች) በንቃት ሲሳተፉ መምህሩ ደግሞ ቁጥብ ሆነው ጥያቄና አስተያየት ሲሰጡ ለማስተዋል ተችሏል፡፡ ለክፍለጊዜው ከተመደበው ሐምሳ ደቂቃ መካከል ተማሪዎች በመናገር ያሳለፉት ሰላሳ አምስት ደቂቃዎች በመሆኑና የመምህራቸው የንግግር ጊዜ ተማሪዎች ከሚናገሩት ጊዜ አንሶ ተገኝቷል፡፡ መምህሩ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አንድ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተግባሪ የሚያከናውናቸውን መርሆዎች ተከትለው በስራ ላይ ሲያውሉ በምልከታው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በተማሪዎች የሞቀ ተሳትፎ ምክንያት ሊደረግ የታቀደው የእለቱ ትምህርት ግምገማ ሳይካሄድ ለዕለቱ የተመደበው የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ሊጠናቀቅ ችሏል፡፡ ይህም የዕለቱ የትምህርት አሰጣጥ ላይ የሰዓት ቁጥጥር ችግር እንደ ክፍተት እንዲታይ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ሰልጣኞች ባገኙት የስልጠና ግብዓት ለወደፊት ሌላ ችግር እስካላጋጠማቸው ድረስ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ሊተገብሩ ይችላሉ ብለን እንድናስብ ያደርገናል፡፡

ስልጠናን በተመለከተ በኮሌጁ ውስጥ ዕጩ መምህራንን የሚያሰለጥኑ መምህራን ለራሳቸው ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር ግኑኝነት በመፍጠር ስልጠና እንደሚያገኙና በተጨማሪም የእርስ በርስ ስልጠና አቅማቸውን ከመገንባባት አልፈው በአካባቢያቸው የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራንን እንደሚያሰለጥኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡ይህም ለአንደኛ ደረጃ መምህራን ከማሰልጠኛ ካገኙት ስልጠና ተጨማሪ ግብዓት ሊሆናቸው እንደሚችል ያሳየናል፡፡

በማሰልጠኛ ኮልጁ ውስጥ አሰልጣኝ መምህራን የሚጠቀሙበት የማስተማር ብልሃቶችን በተመለከተ ተዘጋጅተው በቀረቡት የማስተማሪያ ሞጁሎች ላይ ተመስርተው እንደሚተገበሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይኸውም በማስተማሪያ ሞጁሎች ውስጥ የተለያዩ መልመጃዎች ሲቀርቡ በቀረበላቸው ትዕዛዛት መሰረት ሠልጣኝ መምህራኑ ተግባራቱን እንዲሰሩ ያደርጓቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህም ለቀጣይ የስራ ዘመናቸው ግብዓት ሆኖ እንደሚያገለግላቸው ለመገንዘብ ያስችላል፡፡ ነገር ግን በሞጁሉ ውስጥ የቀረቡት ትዕዛዛት ተማሪዎች ነፃ ሆነው በፈለጉት መንገድ ሀሳቦቻቸውን እንዲያወጡ የሚገድባቸው ይመስላል፡፡ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ሂደት ውስጥ የመምህሩ የመፍጠር ችሎታ እንዳይታይ ከተደረገ ተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግብሯል ማለት አይቻልም፡፡ በዚህ መሰረት በማስተማሪያ ሞጁል ላይ በመመስረት የማስተማር ብልሃቶችን ለመምረጥ መቻል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ ክፍተት እንዳለ አመልክቷል፡፡

በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ውስጥ አሰልጣኝ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመገምገም የሚጠቀሙበት የግምገማ ስልት የተከታታይ ምዘና ነው፡፡ የተከታታይ የምዘና ስልት ተማሪዎች በሚሰሩት የተለያዩ ተግባራት ላይ ተመስርቶ የሚተገበር ምዘና ነው፡፡ ለምሳሌ የኮሌጁ መምህራን ሁሉ ተማሪዎቻቸውን የሚመዝኑበት ቅጽ ላይ የሰፈረው የቤት ስራ፣ ፕሮጀክቶች፣ የክፍል ስራ፣ የጉብኝት ሪፖርቶች፣ ዝግበ-ጥናቶች፣ጽሁፍ ማቅረብ፣የቢጤ ማስተማር፣ሙከራዎችና ማጠቃለያ ፈተና ናቸው፡፡ በእርግጥ የአፋን ኦሮሞ መምህሩ በቅፁ ላይ ተመስርተው የሰልጣኝ መምህራንን ውጤት ተግባራዊ ማድረጋቸውን በማየትም ሆነ በቃለ-መጠይቅ ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡ እያንዳንዱ አሰልጣኝ መምህር ከነዚህ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ላይ በመመስረት ተማሪዎቻቸውን ይመዝናሉ፡፡ ይህ የምዘና ስልት በኮሌጁ ውስጥ እንደ ህግ ተደርጎ ሁሉም አሰልጣኞች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርባቸው መምህራን ይናገራሉ፡፡ ተከታታይ ምዘናው ሙከራዎችን ጨምሮ 70% ሲያካትት 30% ደግሞ የማጠቃለያ ፈተና ነው፡፡

በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን አስመልክቶ በኮሌጁ የተለያዩ ክፍል ውስጥ በሐላፊነት እያገለገሉ የሚገኙ አካላት ለቀረባላቸው ጥያቄ ምላሽ ሰልጣኞች በኮሌጁ ውስጥ ተገቢውን ግብዓት እንደሚያገኙና ከተመረቁ በኋላ በሚመደቡበት ትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ግምት እንጂ በርግጠኝነት ለመናገር መድፈር አልቻሉም፡፡ በተለይም በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን

ትምህርት ከተግባር ጋር የሚያገናኘው የፕራክቲከም መርሀ-ግብር የበለጠ ሰልጣኞችን ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋራ እንደሚያስተዋውቅ ከግንዛቤ ላይ ተደርሷል ፡፡ ሰልጣኞቹ በትምህርት ቤት ውስጥ የመምህራን የስራ ተግባር ምን እንደመሚመስልና አጠቃላይ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን እንዴት ማሳተፍ እንደሚቻል ጽብረቃ ሲያካሄዱ በተጨባጭ ማየት የተቻለው ይህ ሁኔታ ነው፡፡ይህም ሰልጠኞች በማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ እያሉ የሚያገኙት ቁልፍ ግብዓት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ሰልጣኞች ያገኟቸው ግብዓቶች እንዳሉ በጠንካራ ጎኑ ቢቀመጥም በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ጉድለቶችም ተስተውለዋል፡፡ በምልከታ ከታዩት በአፋን ኦሮሞ መምህር ላይ ከተከሰቱ ክፍተቶች ውስጥ የቡድን ውይይት ተግባራዊ ማድረጋቸውና፣ በተወሰነ ደረጃ ገለፃ ማብዛታቸው ነው፡፡ የአፋን ኦሮሞ መምህራን ጋር ከተደረገው ቃለ-መጠይቅና ከ3ኛ ዓመት የአፋን ኦሮሞ ዕጩ መምህራን የቡድን-ተኮር ውይይት ለመረዳት እንደተቻለው ሰልጣኞች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ወቅት አንዳንዶቹ በጋራ የመስራት ችግር አለባቸው፡፡ ይህ ማለት ያላቸውን እውቀት ለሌሎች ማካፈል ያለመፈለግና በተሰጠው ስራ ላይ ሳይሳተፉ በጋራ እንደሰሩ ሆነው መቅረብ ናቸው፡፡ ይህን አስመልክተው እነ Duffyና Kirkley (2004)፤ Kane (2004)፤ Kim ( 2005) ማብራሪያ ሲሰጡ ተማሪዎች ሁሉ እንደተፈለገው በቡድናቸው ውስጥ ወይም በመማር-ማተማር ሂደት ውስጥ በንቃት ተሳትፈው ተግባራትን አያከናውኑም፡፡ አንዳንዴ በመማር ማስተማር ሂደቱ መካከል የራሳቸውን ጉዳይ ሲፈጽሙ ይስተዋላል፡፡ ለዚህ ክስተት መፍትሄም Stead (2005) እንደገለፁት ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ሲተገብሩ የሚጠቀሙበት ብልሃቶች ምን ዓይነቶች እንደሆኑ የሚጠይቀው ሲሆን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በመቅረፀ-ድምጽ የተደገፈ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በአፋን ኦሮሞ መምህራን ቃለ-መጠይቅ፣ በተማሪዎች የቡድን-ተኮር ውይይትና የሰባተኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ የይዘት ዳሰሳ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ በውጤቱም፣ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ለመተግበር የተለያዩ የማስተማር ብልሃቶች እንዳሉ ምሁራን ቢገልፁም የመማሪያ ክፍል ጥበት ከተማሪዎች ቁጥር ጋር አለመመጣጠን፣ የመቀመጫዎች ማነስና የተሰባበሩ መሆን፣

የመማሪያ ክፍል ንፅህና መጓደል፣ የመማሪያ ክፍል ብርሃን አለመኖር፣ የመማሪያ ክፍል ወለልና ግርግዳ ሳቢ ያለመሆን ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ መማር- ማስተማር ችግር የፈጣሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ምክንያቱም መምህራኑ በተማሪዎቻቸው መካከል በመዘዋወር እገዛ እንዳያደርጉ የተማሪዎቹ ብዛት፣ የመቀመጫዎችና የመደገፊያዎቹ የማያመች ሆኖ ታይቷል፡፡

የአፋን ኦሮሞ መምህራን በአራቱም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተግባራዊ የሚያደርጉት የማስተማር ብልሃት በብዛት በቡድን ውይይትና ገለፃ ላይ ያመዘኑ ናቸው ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ "ተማሪ-ተኮር ማለት በቡድን ውይይት ማስተማር ነው" ወደ ሚል መደምደሚያ እያመራ ያለጉዳይ ነው ፡፡ እነዚህም መነሻ የሚያገኙት ከመርሀ-ትምህርት ወይም ከመምህሩ መምሪያ ወይም ከመማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ ነገር ግን በጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መርሀ-ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ እንደሌላቸው ተመልክቷል፡፡ ከዚህም ጋራ ተያይዞ ለአፋን ኦሮሞ ማስተማሪያ የተዘጋጀው መጽሐፍ በበኩሉ መምህራንና ተማሪዎችን የሚያሳትፉ ይዘቶችን ያላካተተ መሆኑም ሌላው ክፍተት ነው፡፡ Nunan (1988) እንዳብራሩት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር የሚዘጋጁት የትምህርት መሳሪያዎች መምህራንና ተማሪዎችን አሳታፊ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡ Hutchinson and Waters (1987) ከላይ የተነሳውን ሀሳብ ሲያጠናክሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ አጠቃላይ የትምህርቱ መርሆች ተማሪዎች የሚሳተፉበት ሊሆን እንደሚገባ አብራርተዋል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ በተጠኚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ብልሃቶች በሥራ ላይ ስለመዋላቸው ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎች አልተገኙም፡፡ አለ ከተባለም የቡድን ውይይትና በጣም በጥቂቱ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

ሶስተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በተለያየ ጊዜ ያገኟቸው ወይም የተከታተሉዋቸው የስራ ላይ ስልጠናዎች ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ እገዛ አድርገውላቸው ይሆን? የሚል ነበር፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው የተደረሰበት ውጤት እንደሚያመለክተው በውጤቱም በተፈለገው መጠን ስልጠና ያለመሰጠቱንና ከዚህም የተነሳ የተለያዩ የአተገባበር ክፍተቶች ሊታዩ እንደቻሉ ተመልክቷል፡፡ ከተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በቃለ-መጠይቅ እንደተገኘው መረጃ ከአንድ ትምህርት ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር

በስተቀር የስራ ላይ ስልጠና እንኳን እንዳላገኙና በዚህም ምክንያት የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እንደተፈለገው እንዳልተገበሩት ለመረዳት ተችሏል፡፡ በየትምህርት ቤቱ ስልጠና ቢሰጥም ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ተብሎ የተሰጠ የስራ ላይ ስልጠና እንደሌለና ከተሰጠ እንኳን ለሚመለከተው ባለሙያ ያለመሰጠቱን ከየትምህርት ቤቶቹ ርዕሳነ መምህራን ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ Tudor (1996) እንደገለፁት፣ የተማሪ- ተኮር አቀራረብ ሊተገበር የሚችለው መምህራን በፍላጎት አሰሳ ክህሎት፣ በትምህርት እቀዳ ክህሎት፣ በትምህርት ክህሎት /Educational Skills/ እንደ ሁኔታው በመቀያየር ወይም አብሮ በመሄድ /Flexibility/ና ተጣጥሞት በመፍጠር፣ መማሪያ ክፍሉን ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር በማስማማት ጥሩ አውድ እንዲፈጠር በማድረግ፣ በተማሪዎች ቁጥር መብዛት ላይ ክፍል ያላቸውን አመለካከት በማስቀየር ላይ ትኩረት ሰጥቶ በማሰልጠን ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት አቅጣጫ ክህሎት አግኝተው የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በአግባቡ ለመተግበር እንዲችሉ ስልጠና ማግኘት እንደሚኖርባቸው ቢታመንም ይህ ሁኔታ አለመሟላቱ በመምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር ላይ ያስከተለው ለውጥ የሌለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

አራተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ ትግበራ ሂደት ወቅት እንቅፋት የሆኗቸው ችግሮች ምንድን ናቸው? የሚል ሲሆን ለዚህም ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት  በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት መረጃዎች ተሰብስበው የተተነተኑ ሲሆን በውጤቱም የተለያዩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተግዳሮቶች ታይተዋል፡፡ በክፍል ውስጥ ምልከታ የተስተዋሉት ችግሮች የመማሪያ ክፍሎች ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ያለመመጣጠን፣ የመማሪያ ክፍል ለመማር-ማስተማር ሂደት አመቺ ያለመሆን፣ የተማሪዎች መቀመጫና መደገፊያዎች አስቸጋሪ መሆን፣ የመምህራን የስራ ላይ ስልጠና እጦት፣ የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎች (መርሀ-ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ) ያለመኖር፣ ከፍተኛ የትምህርት ማስተማሪያ ክፍለ ጊዜ ብዛት ጫና፣ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በተገቢው መንገድ  እንዳይተገብሩ ያደረጓቸው ችግሮች ናቸው፡፡

በተማሪዎች በኩል ደግሞ መምህራን በጋራ እንዲሰሯቸው የተሰጣቸውን  ተግባራት እኩል ተሳትፈውበት ያለመስራት ሁኔታ፣ በብዛት ጎበዝ ተማሪ ብቻ የሚሰጡትን መልመጃዎች

በተደጋጋሚ መስራት፣ እርስ በርስ ያለመደማመጥ ሁኔታ፣ ተማሪዎቹ በተፈለገው መሰረት በቡድን ውስጥ ያለመሳተፍ፤ የአንዳንድ ተማሪዎች የስነ ምግባር ችግር፣አንዱ ተማሪ በሌላው ላይ የመለጠፍ ሁኔታ፣ ስራዎችን በሰዓቱ ያለማስረከብ፣ ዕቅድ ያለመኖር፣ተማሪዎች የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጥቅምን ያለመረዳትና የመሳሰሉ ችግሮች ናቸው፡፡ ይህም Leu (2000)ና Nunan (1988) እንደገለፁት የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ለመተግበር ከትምህርት ጋር የተያያዙ አካላት ሁሉ ስልጠና ካልተሰጣቸው  በአተገባበሩ ላይ እንቅፋት ሊፈጠር እንደሚችል የገለፁት ሁኔታ ታይቷል፡፡

አምስተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት Hላፊዎች የአፋን ኦሮሞ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን እንዲያስተምሩ ያደረጉላቸው የተለያዩ ድጋፎች ይኖሩ ይሆን? የሚለው ነበር፡፡ ለዚህ መሰረታዊ ጥያቄ ምላሽ ለመሻት መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ በቡድን-ተኮር ውይይትና በሰነድ ትንተና ተሰብስበው ድጋፍ ያለበትና የሌለበት ሁኔታ እንደሚታይ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ የተማሪዎች፣ የቅርብ ወዳጆች፣ የትምህርት አስተዳደር አካላት፣ በህብረሰብ ውስጥ ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች፣ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች፣ የአስተዳደር አካላትና የፓለቲካ ስልጣን ያላቸውን ሰዎች ትብብራዊ ተሳትፎን ይጠይቃል ሲሉ Tudor (1996)፣ Mccombsና Whisler (1996)  አብራርተዋል፡፡ በነዚህ ምሁራን ማብራሪያ መሠረት ከላይ የተጠቀሱት አካላት በተማሪ-ተኮር ሰርዓተ- ትምህርት እቀዳ፣ ትግበራና ግምገማ ውስጥ በመሳተፍ የተማሪ- ተኮር አቀራረብን ለውጥ በአግባቡ እንዲተገበር ያደርጉታል፡፡

በዚህ ጥናት በምዕራፍ አንድ ውስጥ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ በክፍል ምልከታ፣ በመምህራን ቃለ-መጠይቅ፣ በተማሪዎች የቡድን ውይይት፣ በርዕሳነ መምህራን ቃለ-መጠይቅ፣ በመምህራን ልማት ተጠሪዎችና በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ልዩ ልዩ ክፍል ኃላፊዎች የተነሱ በተናጠል ሲታዩ አንዱ ከአንዱ ጋራ በመተጋገዝና የገጠሟቸውን ችግሮች በጋራ የመፍታት ጉድለቶች ተስተውለዋል፡፡

ለምሳሌ በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍሎችና መቀመጫዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች በትምህርት ቤቱ ሐላፊዎች ብቻ የሚፈቱ ሣይሆኑ የሌሎችን አካላት እገዛ ይጠይቃል ፡፡

Tudor (1998) እንደገለፁት የተማሪ-ተኮር አቀራረብን በአግባቡ ለመተግበር የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ አካላትን እገዛ ይጠይቃል፡፡ የመምህራን ስልጠና ችግር ከውሎ አበል ክፍያ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት በትምህርት ዙሪያ በጀት ከሚመድቡ አካላት ጋር ተባብሮ ያለማቀድ ክፍተት በሚገባ ይስተዋላል ፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚከሰቱ የተማሪዎች የስነምግባር ችግሮች በአጠቃላይ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር መፍትሄ ለማፈላለግ ከትምህርት ቤቶች ውጭ ከልዩ ልዩ ማህበረሰቦች (ወላጆች፣ታዋቂ ሰዎች፣ የፀጥታ ክፍሎች፣ ወዘተ) ተሳትፎ የሌለ መሆኑን የተሰጡ መልሶች ያመለክታሉ፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተዳሰሱትን ሀሳቦች ለማጠቃለል በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ ምቹ የመማር-ማስተማር ሂደት የሚከናወንበት ሁኔታዎች ያሉ መሆኑ፣ ለመምህራኑ ተገቢ የሆኑ የስራ ላይ ስልጠናዎች መሰጠታቸውን፣ የፕራክቲከም ትግበራው በአግባቡ ተግባራዊ መሆኑና የተለያዩ ሁኔታዎች ሊሟሉላቸው በመቻሉ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሊተገብር እንደሚችል መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ደግሞ የመማሪያ ክፍሎች አመቺ ያለመሆናቸው፣ ለመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ያለመሰጠቱ፣ የተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ መብዛት፣ የተለያዩ አካላት እገዛዎች አናሳ ከመሆን የተነሳ የአፋን ኦሮሞ መምህራኑ የተማሪ-ተኮር አቀራብን ሊተገብሩ እንዳልቻሉ መረጃዎቹ አመልክተዋል፡፡ በአጠቃላይ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሊተገበር የሚችልበትን ሁኔታና ላይተገበር የሚችልበትን ምክንያቶች በማጣቀስ ምዕራፉ ተቋጭቷል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

በዚህ በየምዕራፉ የተነሱት ዋና ዋና ነጥቦች አጠር ተደርገው ከተዳሰሱ በኋላ በተገኙት ማብራሪያና ውጤት ላይ በመመስረት የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰጥቷል ፡፡ ምዕራፉ የመፍትሄ ሀሳቦቹንም ለመስጠት ቅድሚያ በምዕራፍ አንድ ላይ የተነሱትን የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች በማመላከት በእያንዳንዳቸው ስር የተገኙ ክፍተቶችና ክፍተቶቹን ለመሙላት ሊደረጉ የሚገባቸውን ተግባራት በመጠቆም ይቋጫል፡፡

## 6.1. ማጠቃለያ

ትምህርት አንድን ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ በአሰራሩና በአስተሳሰቡ ላይ ለውጥ አስገኝቶ አካባቢውን እንዲለውጥ የሚያደርግ መሳሪያ ነው፡፡ ይህ የእድገት መሳሪያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ግለቦችን ሊለውጥ የሚችለው ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት ተሳትፈው እውቀታቸውንና ችሎታቸውን ከነበራቸው ልምድ ጋራ አዋህደው ሲገኙ ነው (Mccombsና Whisler 199)፡፡ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ከቀረበላቸው ትምህርት ግብ ላይ ደርሰው ለውጥ ያመጡበታል ተብሎ በዘርፉ ጥናት ባደረጉት ምሁራን ድጋፍ ያገኘ የማስተማሪያ አቀራረብ ነው፡፡ በአገራችንም ፖሊሲ በመንደፍ ይህ አቀራረብ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆንና ተማሪዎችም የራሳቸውንም ይሁን የአገራቸውን ችግሮች መፍታት እንዲችሉ በመደረግ ላይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ እንደ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ዘዴ ተደርጎም እየተወሰደ ይገኛል፡፡ መምህራንም ለተግባራዊነቱ የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም ግን ይህ ተግባራዊ እየሆነ የሚገኘው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ በተለያዩ የውጭ አገሮችና የአገር ውስጥ ምሁራን ጥናቶች ተፈትሸው ይፋ እንደተደረገው የክፍል መማር-ማስተማር ሂደት ወቅት የተለያዩ ክፍተቶች ታይተውበታል፡፡ በዚህ ጥናትም ይህ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

ክፍተቶቹም በአቀራረቡ ዙሪያ ለመምህራን በቂ ስልጠና ያለመስጠት፣ በየደረጃው ለሚማሩ ተማሪዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ያለመስጠት፣ በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በዝቶ መገኘት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለመገኘትና የመሳሳሰሉት ናቸው፡፡ በዚህ አይነታዊ ምርምርም በባሌ ዞን በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ

ትግበራ ጥናትም በአፋን ኦሮሞ መማር -ማስተማር ሂደት ውስጥ በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የስልጠና አሰጣጡ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ መርህ አግባብ ቢተገበርም ሰልጣኞች ተመርቀው ወደ ተመደቡበት ትምህርት ቤት ከደረሱ በኋላ በአግባቡ እንደማይተገበሩት ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአጭሩ ከላይ ከተዘረዘሩት የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ክፍተቶች በአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ሊታይ ችሏል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በባሌ ዞን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መመርመር ነበር፡፡ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ተጠኚ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን ለማስቃኘት የተነሱ መሰረታዊ ጥያቄዎች፣

- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን ለማስተማር እንዲበቁ የሚሰጣቸው የስልጠና ግብዓቶች ምንድን ናቸው?
- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ሲተገብሩ የሚጠቀሙበት ብልሃቶች ምን ዓይነቶች ናቸው?
- በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በተለያየ ጊዜ ያገኟቸው ወይም የተከታተሉዋቸው የስራ ላይ ስልጠናዎች ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ እገዛ አድርገውላቸው ይሆን?
- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ ትግበራ ሂደት ወቅት እንቅፋት የሆኗቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?
- በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ኀላፊዎች መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን እንዲያስተምሩ ያደረጉላቸው የተለያዩ ድጋፎች ይኖር ይሆን? የሚሉ ነበሩ፡፡

በዚህ አይነታዊ ምርምር ውስጥ የተጠኑ ትምህርት ቤቶች አራት ሲሆኑ የተጠናው መማሪያ ክፍል ደግሞ 7ኛ ክፍል ነው፡፡ በዚህ መማሪያ ክፍል ውስጥ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ዋና ትኩረቱ

ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተሰብስበው የተተነተኑ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፡-

- በኮሌጁ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማሩ ሂደት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ በመሆኑ ለሰልጣኝ መምህራን እንደ መልካም ግብዓት ሊወሰድ ይችላል፣
- አሰልጣኝ መምህራኑም አቅማቸውን ለመገንባት በቅድመ ስራ ከተማሩት ትምህርት ባሻገር የስራ ላይ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በተለይም በኮሌጁ ውስጥ ለአስር ወራት በቋሚነት የሚሰጠው የከፍተኛ ዲፕሎማና የሲፒዲ ስልጠና መርሀ-ግብር አሰልጣኝ መምህራን ለራሳቸውም ሰልጥነው በኮሌጁ ዙሪያ ለሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራንም ከፍተኛ አስዋጽኦ እንደሚያደርጉ ለመረዳት ተችሏል፣
- በኮሌጁ ውስጥ መማር-ማስተማሩ ሂደት የሚከናወንበት አውድ አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር አመቺ ነው፣
- በኮሌጁ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራኑ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚያደርጉት የማስተማር ብልሃት ምርጫ ቀደም ተብሎ በተለያዩ ኮሌጆች ውስጥ ትምህርቱን በሚያስተምሩ መምህራን አማካኝነት የተዘጋጁ ሞጁሎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ምንም እንኳን Nunan (1988) በገለፁት መሰረት ተማሪዎችም በስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው የተባለው ሀሳብ ባይተገበርም በመምህራኑ የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ሰልጣኞችን አሳታፊ አድርጓቸዋል፣
- በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች የቡድን አደረጃጀት ከመርህ አንፃር ተገቢ ነው ፤ የመቀመጫ አደራደሩም እንደተፈለገው ቡድን ሊመሰርቱ በሚያስችል መንገድ ነው፡፡ተማሪዎችም በግብረ-ሃይል በመደራጀት ማንኛውንም ተግባር በጋራ የመስራት ልምድ በማጎልበት ላይ እንደሚገኙ ለመረዳት ተችሏል፣
- ተማሪዎች የሚገመገሙት በተከታታይ ምዘና መሆኑና የአፋን ኦሮሞ አሰልጣኞችም ይህን ተግባራዊ እያደረጉት እንደሚገኙ ለመረዳት ተችሏል፣
- በፕራክቲከም ኮርስ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ጋራ ግንኙነት መፍጠሩ መማር-ማስተማሩን የበለጠ ተጨባጭ እንዲሆን ማድረግ በመሆኑ የሚበረታታ ተግባር እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፣

- በኮሌጁ ውስጥ አንዳንድ ተማሪዎች በሌሎች ተማሪዎች ላይ ጥገኛ የመሆን ባህሪን እንዳላቸውና የተሰጣቸውን ተግባር በቡድን ሳይሰሩ እንደሰሩ ተቆጥረው ስማቸውን የማስመዝገብ ሁኔታ ይታያል፡፡ እንደዚሁም የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ቤት ምልከታ ዝግበ ጥናት ሲያቀርቡ አንዱ የሰራውን ወይም ቀደም ብለው ትምህርታቸውን የጨረሱ ተማሪዎች የፃፉትን ተመልሰው የመገልበጥ ሁኔታ ይታያል፣
- በመምህራን ትምህርት ኮሌጁ ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራን የሚተገብሩት የማስተማር ብልሃት በአብዛኛው ገለፃና የቡድን ውይይት ሲሆን ሌሎች የማስተማር ብልሃቶች የተዘነጉ መሆናቸው ተረጋግጧል፣ ቀሪዎቹ  አራቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ከአንደኛ ደረጃ የአፋን ኦሮሞ መምህራን የተገኙ መልሶች በሚከተለው ሁኔታ ተጠቃለዋል፡-
- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማሩ ሂደት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን የራሳቸውን ጥረት ሲያደርጉ የተስተዋለ ሲሆን ተማሪዎችም በክፍል ውስጥ የተሰጣቸውን ተግባራት በመከወንና ሀሳብ ለመስጠት ጥረት ሲያደርጉ ተስተውለዋል፣
- በስራ ላይ ስልጠና ረገድ ለሳይንስ መምህራን ሳይንስን እንዴት ማስተማር እንደሚገባቸው ስልጠና ቢሰጥም ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ግን አፋን ኦሮሞን እንዴት ማስተማር እንደሚገባቸው የተሰጠ ስልጠና የለም፡፡ ከአራቱ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ትምህርት ቤት የሚያስተምረው መምህር ብቻ በተማሪ-ተኮር አቀራረብና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ስልጠና እንዳገኘና በዚህ ረገድ ስልጠናው በቂ አለመሆኑ ታይቷል፣
- በተማሪ-ተኮር አቀራረብም ይሁን በሌላ ርዕሰ ጉዳይ ስልጠና ተዘጋጅቶ ጥሪ ሲደረግ ከአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ተሳታፊ ያለመሆናቸው ሁኔታ ይታያል፣
- በምልከታ ከታዩት አራቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሁለቱ አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር የሁኔታዎች አስቸጋሪነት ተስተውለዋል፡፡ በተለይም የመማሪያ ክፍል ጥበትና የተማሪዎች ቁጥር ጋር አለመመጣጠን፣የመቀመጫዎች ማነስና የተሰባበሩ መሆን፣  የመማሪያ ክፍል ንፅህና መጓደል፣ የመማሪያ ክፍል ብርሃን አለመኖር፣ የመማሪያ ክፍል ወለልና ግርግዳ ሳቢ ያለመሆን  ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ መማር- ማስተማር ችግር የፈጣሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ምክንያቱም መምህራት

በተማሪዎቻቸው መካከል በመዘዋወር እገዛ እንዲያደርጉ የተማሪዎቹ ብዛት፣ የመቀመጫዎችና የመደገፊያዎቹ የማያመች ሆኖ ተገኝቷል፣

- መምህራን ተማሪዎች በጋራ እንዲሰሯቸው የሚሰጧቸውን ተግባራት እኩል ተሳትፈውበት ያለመስራት ሁኔታ፤ የሚሰጡትን መልመጃዎች ጎበዝ ተማሪዎች ብቻ በተደጋጋሚ መስራት፤ እርስ በርስ ያለመደማመጥ ሁኔታ፣ ተማሪዎቹ በተፈለገው መሰረት በቡድን ውስጥ ያለመሳተፍ፤ የአንዳንድ ተማሪዎች የስነ ምግባር ጉድለት ፣ አንዱ ተማሪ በሌላው ላይ ጥገኛ የመሆን ሁኔታ፤ ስራዎችን በሰዓቱ ያለማስረከብ፣ ዕቅድ አለመኖር ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ እንቅፋት መሆናቸው ተመልክቷል፣
- የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ከባህሪው አንፃር ለተማሪዎች ሀሳብ ቅድሚያ መስጠት መሆኑን ባለመገንዘብ ተማሪዎች አንዳንድ ነጥቦችን ቅድሚያ እንዲናገሩ ሲደረግ ከመምህሩ ችሎታ ማነስ እንደሆነ በማሰብ ተማሪዎች በመምህራን ላይ አሉታዊ ስሜት መፍጠራቸው ተረጋግጧል፣
- በሁሉም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ1996 ዓ.ም የታተመው የአፋን ኦሮሞ መማሪያ የተማሪው መጽሐፍ በበቂ ሁኔታ ቢገኝም የመርሀ-ትምህርትና የመምህሩ መምሪያ በመምህራኑ እጅ ያለመገኘቱ በስራቸው ላይ እንቅፋት እንደሆነባቸው ለመገንዘብ ተችሏል፣
- አንዳንድ መምህራን ለተማሪዎች ሀሳብ ቅድሚያ ሳይሰጡ ለረዥም ጊዜያት ገለፃ የመስጠት ሁኔታ ታይቷል፣
- በ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መፃህፍ ውስጥ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ አግባብ አንፃር ሲገመገሙ ተማሪዎችን አሳታፊ ሆነው የተዘጋጁ አይደለም ፡፡ ከመልመጃዎቹ ውስጥ ተማሪዎች በግላዊ ተሳትፎ የሚሰሯቸው እንጂ በሌሎች ብልሃቶች የሚተገብሯቸው አለመሆናቸው ተስተውሏል፡፡
- ለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ የተማሪዎች የቅርብ ወዳጆች፣ የትምህርት አስተዳደር አካላት፣ በህብረሰብ ውስጥ ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች፣ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች፣ የአስተዳደር አካላትና የፖለቲካ ስልጣን ያላቸውን ሰዎች ትብብራዊ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አንፃር በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥና ከተለያዩ የትምህርት አካላት አንፃር ድጋፉ ከአነስተኛ በላይ እንደሌለ ከሚቆጠርበት ደረጃ ላይ ደርሶ ተገኝቷል፡፡

## 6.2.የመፍትሄ ሀሳቦች

በምዕራፍ አምስት ስር በተካሄዱት ትንታኔና ከላይ በተነሱት ማጠቃለያ ነጥቦች በመመስረት የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡-

- የመምህራንን የስልጠና ግብዓት በተመለከተ በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ የሚሰለጥኑ ዕጩ መምህራን በሰለጠኑበት መንገድ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር እንዲችሉ ለማድረግ በተከታታይ ለሁለት ወይም ለሶስት ወራት  በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይተው እንዲሰሩ ቢደረግና ተመልሰው ደካማና ጠንካራ ጎናቸው ላይ ግምገማ ቢደረግ በተሻለ ሁኔታ ግብዓት ሊሆናቸው ይችላል፣
- በኮሌጅ ውስጥ የሚያስተምሩ አሰልጣኝ መምህራን ስልጠና ለመስጠት ብቃት ያላቸው ቢሆንም በአተገባበር ሂደት ወቅት ተማሪዎች በቅድሚያ መስራት የሚገባቸውን ተግባር ራሳቸው ቀድመው እንዳይሰሩ ከከፍተኛ ዲፕሎማ በተጨማሪ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዙሪያ በትምህርት ሚኒስቴር ወይም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ተከታታይ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፣
- በመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ውስጥ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስልጠና ሲዘጋጅ ስልጠና አዘጋጆቹ ቅድሚያ ከመምህራን ላይ የፍላጎት ዳሰሳ ቢያደርጉና ስልጠናውም ለሁሉም ትምህርት ቤት ተወካዮች የሚሰጥበት ሁኔታ ቢመቻች፣
- በአንደኛ ደረጃ ለአፋን ኦሮሞ መምህራን ቀጥተኛ ስልጠና አለመሰጠቱ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ስልጠናው በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ወይም በመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ወይም የወረዳ ትምህርት ቢሮ ሲዘጋጅ በቀጥታ ከመማር-ማስተማሩ ጋራ ግኑኙነት ያላቸው መምህራን በአግባቡ ተሳትፈው ስልጠና ማግኘታቸውና ተመልሰውም በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ተግባራዊ ስለማድረጋቸው የሚያረጋግጡበት ስልት ሊኖራቸው ይገባል፣
- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አፋን ኦሮሞን ለሚማሩም ሆነ አጠቃላይ ትምህርት ለሚማሩ ተማሪዎች ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበርና  ባህሪያቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና  ቢሰጣቸው በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ከመምህራንም ሆነ እርስ በርሳቸው ያላቸውን መቀራረብ የተሻለ ስለሚሆን የትምህርት ቤቶች  አመራር አካላት ከዚህ ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፣

- በአሁኑ ሰዓት ታትመው በተማሪዎች እጅ የሚገኙ የተማሪዎች የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን አሳታፊ በማድረግ በቂ ዕውቀት የሚያስጨብጡ አይደሉም። ስለዚህ የሚቀርቡት የትምህርት ይዘቶች ተማሪዎችን በተለያዩ የማስማር ብልሃቶች አሳታፊ ሆነው ተግባራትን ሊከውኑ የሚችሉበትን ሥርዓት በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የስርዐተ-ትምህርት ዝግጅት በኩል ቢዘጋጅ፣
- የመምህራን ስልጠና ሲዘጋጅ መምህራን ስልጠናው በሚሰጥበት አቅጣጫ አንዳች ለውጥ ያመጣሉ ተብሎ ታስቦ ነው። በትምህርት ላይ ድጋፍ የሚያደርጉት አካላትም ከቆሙለት ዓላማ አንፃር መምህራኑ ሊደርሱበት ከሚገባው ግብ ላይ ለማድረስ እገዛ ያደርጋሉ። በመሆኑም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ አንፃር ከመምህራን ስልጠና ውጤት የሚጠብቁት የትምህርት አመራራሮች ከድጋፍ ሰጪ አካላት ጋራ የጠበቀ ግኑኝነት በመፍጠር በቂ በጀት እንዲመድብላቸው ቢያደርጉ፣
- በሁሉም ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራን እጥረት ይታያል። ከዚህም የተነሳ መምህራኑ ብዙ ክፍለ-ጊዜን በመያዝ በማስተማር ላይ የመሰልቸት ባህሪ እንዲታይባቸው ሆነዋል። ስለዚህ የወረዳ ትምህርት መምሪያ የመምህራን እጥረት ባለበት ትምህርት ቤት ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መምህራንን በበቂ ሁኔታ ሊመደቡ የሚችሉበት ሁኔታ ቢፈጠር፣
- በጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ ክፍሎች ተማሪዎችን ዘና በማድረግ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በተነሳሽነት መሳተፍ እንዲችሉ ሆነው አልተገኙም። በመሆኑም እንደ አደጉት አገሮች ሁሉ ነገር የተመቻቸ ባይሆንም የአገራችን ኢኮኖሚ በሚፈቅደውና የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የትምርት ቤቶቹና የመማሪያ ክፍሎቹ ሳቢነት የሚሻሻልበት ሁኔታ በሚመለከተው ክፍል ቢመቻች፣
- በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር ከአግባብ በላይ በመሆን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያደረሰ በመሆኑ በዚህ መስክ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ መብዛት ባለው ጠቀሜታዎች ላይ የወረዳ ትምህርት ቢሮዎች ለመምህራን ስልጠና ቢሰጥ፣

## 6.3.ለወደፊት ሊጠናበት የሚገቡ ርዕሶች

1. ምርምሩ ከከተማ ርቀው በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ባለበት አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን በማነፃፀር ጥናት ጥሩ ውጤት ሊታይ ይቻል ነበር። ምክንያቱም በመምህራን ኮሌጅ አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ መምህራን  የተለያዩ ስልጠናዎችን የማግኘት ሰፊ ዕድል ሲኖራቸው ከከተማ ርቀው የሚገኙት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ መምህራን ደግሞ ከውሎ አበልና  ከመረጃ ክፍተት ጋር በተያያዘ ምክንያት  የስራ ላይ የስልጠና ግብዓት የማግኘት ዕድላቸው ውስን በመሆኑ በሁለቱ መካከል የሚገኘውን ልዩነት ማየት ለመቻል  ጥናት ቢደረግ፤

2. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ ለመምህራን ስልጠና ከተሰጠ በኋላ ከስልጠና በኋላ አተገባበራቸውን በመፈተሽ በተገኘው ውጤት ላይ እንደገና ከተተኳሪ መምህራን ጋራ ውይይት ተደረጎ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ቢደረግ፤

## ዋቢ ጽሁፎች


Aggarawal, J.C.(1996). ***Principles, Methods &Techniques of Teaching.*** NewDelhi Vicas P ublishing House PVTltd.

Alemayehu Jote (2012) ***The Contribution of Mother-Tongue Education to Promote Indige nous Knowledge of Agriculture: The Case of Bale Zone in Oromia Region***.Addis A baba University; PHD Thesis (Unpublished).

Allwright,D.(1980). ***Obervation in Language Classroom***.London:Longman.

Amare and et al .(2006)"***Ethiopia Pilot Study of teaching Professional Development, Qualit y Education,Teaching and learning Perceptions and Practice***."IER .AAU.

Ambelu Tebabal and Gebregzibher kahssay. (2011).***The effect of Student-centerd Approach in Improving Students' graphical Interpretion Skills and Conceptual Understandi ng of kinematical Motion***.Feburary, Bahirdar university.

Arseneau, R, & Rodenburg, D. (1998). ***The Development Perspectiv****e.*Cultivating ways of t hinking: Five Perspectives on Teaching in Adult and Higher Education. Malabar, FD Krieger.

Askew,s and Eileen,c. (1998). ***Transformining learning individual and Global Change***.Lon don: Redwood Books.

Asefa Jalata. (1993). ***Oromia and Ethiopia: State Formation and Ethnonational Conflict .***( 1968-1992). Boulder: Lynne Reinner

Bahiru Zewdie .(1991). ***A History of Modern Ethiopia.***1855-1974 London:janes curry.

Bale Zone Cultural and Tourism Office (BZCTO).(2010) ***Culture and Tourism of Bale Zone*** . BZCTO, Robe.

Bale Zone Finance and Develo*pment Office (BZFDO).(2010) .****Physical Geography of Bale Zone****.* BZFDO, Robe.

Bamgbose, A. (1991). ***Language and the Nation: The Language Question in Sub-Saharan Africa. Edinburgh:*** Edinburgh University Press.

Barrow, K. & Leu, E..(2008). ***Issue Paper Perceptions of Ethiopian Teachers and Principles on Quality of Education,***(2006).Retrieved November 8, 2008 from < Pdf.usaid. gov/pdf_docs/PNADH772.pdf/.>.

Baxter, P. T. W.( 1983) . ***The Problem of the Oromo or for the Oromo****?* In I. M. Lewis (ed., ***Nationalism and Self-determination in the Horn of Africa.*** pp. 129-49.Ithaca and London: Ithaca Press.

Bell B. and Gilbert, J. (1996).***Teacher development: a model from science education.*** London: Falmer Press.

Beker, C.(1988). ***Key Issues in Bilingualism and Bilingual education***. Clevedon, Avon: Multilingual Matters.

Bender, M. L. (1976) .***The Non-Semitic Languages of Ethiopia****.* African Studies Center, Michigan State University.

Benson,C.(2005). ***The Importance of Mother Tongue-based Schooling for Educational Quality***. Paper Commissioned for the EFA Global Monitoring Report 2005, The Quality Imperative. UNESC.

Best, J. (1999). ***Research in Education***. New Delhi: Printic-Hall of Indian

Bilimoria,D. &Wheeler,J.V.(1995). *Learning-centere deducation: a guide to resources and implementation.* ***Journal of Management Education***. 29(3), 402-428.

Birgit N. (1988) .***Traditional Wisdom and Modern Development: A Case Study of Traditional Prenatal Knowledge among elderly Women in N/Showa, Ethiopia.*** Institution of International Education: University of Stockholm, Sweden.

Birhanu Moges.(2010). ***Active learning Approach in Mathematics Education at Universities in Oromia,Ethiopia.*** (Unpublished) PhD Dissertation, University of South Africa.

Biiroo Barnoota Oromiyaa (BBO). (1996). ***Barnoota Afaan Oromo Kitaaba Barataa Kutaa*** *7*.BBO, Finfinnee.

Bloor, T. & Wondwosen Tamrat. (1996). ***Issues in Ethiopian language policy and edcation*** **.**Journal of Multilingual and Multicultural Development 17(5): 321-338.

Bonwell, C.C and Eison.LA .(1991). ***Active Learning Creating Excitement in the Classroo m***.Washington: George Washington University Press.

Bonewell, C (2003)***Active Learning: Creating Excitement in the Classroom.*** Fromhttp://www .Macom b CCmius/ are/D hMa terialsactivelearning htm. Accessed on March,2009.

Borich,G. (1988). ***Effective Teaching Methods***.Columbus: Merrin publishing Company.

Boven, J. D. and N. E. Horn .(1976) Language Education.In Bender, M. L. (1976) ***The Nn-Semitic Languages of Ethiopia.***African Studies Center, Michigan State University.

Bowen.J.D .(1976). ***Historical Backgraound of education in Ethiopi***a.InM.L. Bender.J.D.Bowen. R.L.Cooper. C.AFergusen(eds.).***Language in Ethiopia.***(pp305-323).London:Oxford University Press.

Brendes,D.and Ginnes,p.(1986)***. A guide to student-centerd learning***.London:Simon and chuster Education.

Breslow, L.(1999).***"New Research Points to the Importance of using Active learning in the Classroom"http:***//web,mit.edu/ta/library new researchhtml (Retrieved onMarch16,2)

Brown, D.(2007).***Principles of Language Learning and Teaching.*** New York:Longman.

Bruner. lS .(1996). ***Towards a Theory oflnstruction.*** Cambridge: Harvard University Press

Burnes,A. (1999). ***A Collaborative Action Reasearch For English language Teachers***.Cambridge: C.U.P.

Calvet,L-J .(1998). ***Language Wars and Linguistics Politics***. Oxford: oxford university press, Translated by Michel petheram.

Celce-Murcia, M.(Ed.). (1991). ***Teaching English as a second or foreign language***. (2nd ed.). New York: Newbury House.

Callhan and Clark (1988).***Teaching in Middle and secondary Schools Planning for competence***. Newyork: Macmillan Publishing Company.

Capel, et al. (1995). ***Learning to Teach in the Secondary Schools.*** London: Rouldge.

Chang,bok-M.and Lee,J. (2001). ***Korean Curriclum Reforms and the Progressivism***. Retrived On April21,2010 From http://www.google calur/psa:is Soruce:web and at.

Chauhan,S.S.(1983). ***Innovation in Teaching Learning Process***. (2nd ed)Shimila:Vicas.

Chenge.u .(2007). ***How to adopt Learner-centerd approach in Chinese EFL context.InternationalJournal of Language Society and Culture***. URL:WWW.edu.uts.edu.au/users/journalisn1327-774x Hebepolytechnic University, China.

Clark,J.L,.(1987).***Curriculum Renewal in School Forign Language Learning***. Oxford:Oxfod Univarity Press.

Chance, P.( 2005). ***Learning and Behavior: Active learning***. (5th Edition), New York: Wadsworth Publishing.

Cohen et.al .(2000) .***Research in Education***. New York:Lowrence Manion and Keith Morrs.

Coombs, P.H. (1985).***The World Crisis in Education: The View from the Eighties.*** New York, Oxford: Oxford University Press.

Council of Europe. Language Policy Division. (2003). ***Guide for the development of language policies in Europe: From linguistic diversity to plurilingual education*** (Excutive Version). Strasbourg: Council of Europe.

Cooper, R.L (1976). Government language policy. In Bender, ML, JD Bowen, CA Cooper, and CA Ferguson. (Eds.). ***Language in Ethiopia***. London: Oxford University Press.

Crawford, J.W.(2000).***Language policy***. Retrieved on September 16, 2005 from LanguagePolicyWebsiteat http://ourworld.compuserve.com/homepages/JWCrawford/langpol.htm

Creswell J. W.(2009). ***Research Design***. 3rd ed. USA: SAGE Publications.

__________(2012). ***Educational Research: Planning,Conducting and Qualitative Research.*** 4rd ed. USA: Pearson,www. pearson highered.com.

Cruickshank and etal.(1999).***The act of Teaching. Boston:***Mc Graw-Hill Companies,INC.

Cummins, J. and Swain. (1986). ***Mother Tongue Maintenance for Minority Language Children: Some Common Misconceptions. Form2***. London:Language Inspectorate: Spring.

Daniel shibeshi and Abebayehu Taddese.(2006).***Instructional Language policy in Ethiopia Motivated by politics or Theeducational needs of children. "in Planning and changing*** ''vol.37.No3&4,2006.PP.156-168.

Derebssa Dufera (1998) Planning Education Under a Decentralized System. In Asgedom et al. (eds). 1998. ***Quality Education in Ethiopia****: Visions for the 21st Century.* Addis Ababa: Institute of Educational Research, Addis Ababa University.

________(2006).Tension between traditional and modern teaching-learning approaches in Ethiopian primary schools. ***Journal of International Cooperation in Education,*** Vol. 9,No1, 12-18, April.

Dereje Terefe. (2010) .***The Implementation of the Multilingual Education Policy in Ethiopia: The Case of Afaan Oromoo in Primary Schools of Oromia Regional State.(*** Unpublished Ph D Dissertation), University of Jyvaskyla.

Desta Abera.(2001).***Implemention of Problem Solving Approach in the second Cycle Primary School of Tigray.***Addis Ababa University; M.A. Thesis (Unpublished).

Dewey .(2002).***Constructivist Learning Theory***. Retrieved from the World Wide Web November 2, 2002 from http://www.artsined.com/teachingarts/Pedag/Dewey.html

Dornneyei,Z. (2007) ***Research Methods in Applied Linguistics.***New Youka Oxford University Press.

Duffy, T.M. & Kirkley, J. (2004). ***Learner-centred theory and practice in distance education: Cases for higher education.*** Mahwah, NJ: Lawrence Erblaum.

Eggen,P.D and Kauchax. (1996).***Strategies For Teachers Teaching Contents and Thinking Skills***.(3rd ed) U.S.A: Simon Schuster Company.

Ema,D, Attard,A, Koen,G Roobert,S.(2010).***Student-centerd Learning.***An Insight in to Theory And Practice Bucharest.

Emenanjo, E.N. (1990). ***Multilingualism: Minority Languages and Language Policy in Nigeria. Port Harcourt****:* Central Books Ltd.

Engle, P (1975). ***The Use of Vernacular Languages in education. Papers in Applied Linguistics***. Bilingual Education Series No.3. Arlington: Center for Applied Linguistics ***Expansion Strategy Towards Quality, Equity and Reform.*** A Paper for the2005/ 06 Fulbright New Century Scholarships, UB. USA: State University of New York.

Farrent,J.S.(1980). ***Principles and Practice of Education***.New edition. Longman. Longman group ltd.

Fasold, R. W. (1984) ***The Sociolinguistics of Society.*** Oxford: Blackwell.

Fisseha Abereha.(2001).***Hambering Factors To Implement Active Learning in Some selecte d Second cycle Primery School of centeral zone in Tigeray.***Addis Ababa University; M.A. Thesis (Unpublished).

Flick .(2009).***An Introduction to Qualitative Research.(***4th ed).London:SAGEPublicationLtd.

Frazee, M.B. et al. (1995) .***Integrated Teaching Methods: Theory Classroom Approach., an d field based Connections.*** New York:Mc Graw Hill Inc.

Fred,L. and Perry, J.(2005). ***Research in Applied Linguisitics***. London: Lowrence Eribaum Assocation.

Freeman,l (1986). ***Teaching and Principles in Language Teaching.*** Oxford: Oxford Univars ity pres.

Gaum, A. (2002). ***Language Culture and Curriculum:*** Language Policy in the Primary Scho ols of the Western Cape.' At http://wcape.gov.za/

Gay, L.R. & Airasian, P .(2000). ***Educational research: competencies for analysis and appl ication. Sixth Edition.*** New Jersey: Merrill Prentice- Hall

Gay, L. R.,Mills, G. E.,& Arasian, P. (2009). ***Educational research: Competencies for analy sis and application***,(9th ed.). Upper Saddle River, NJ: Prentice Hall.

Getachew Anteneh and Dirb Ado. (2006) . Language policy in Ethiopia: History and current Trends. ***Journal of Education and science***. Offical Journals of Education Faculity R PO, Jimma University, vol.2,No.1. (pp37- 61)

Getachew, Adunya (2008).***The Nature & Practice of Teacher Education Via Distance Lear ning in Ethiopia***. The case of Addis Ababa University &Educational Media Agency. Norwich, UK.

Girma Amare. (19670). Aims and Purpose of Ethiopian Church Education. In ***Ethiopian Jo urnal of Education I***: 1-11, H S I University, Addis Ababa.

Gragg, G. (1976) ***Oromo of Welega***. In Bender, M. L. (1976) The Non-Semitic Languages of Ethiopia. African Studies Center, Michigan State University.

Halperin, D. (1994). ***Changing College Classrooms.***Sanfransisco: Jersey- Bass.

Haile Gabriel Dagne (1976). *Non-government schools, in M.L. et al.* (eds.), ***Language in Eth iopia London***: Oxford University Press.

Harmer, J. (1998).***The practice of English Language Teaching***. London: longman.

Harmin, M. (2006). ***Inspiring Active learning .A complete hand book for Today's teachers***. assocation for Supervision and curriculum Development. Verjinia, U.S.A.

Harris, A. (1977).***The possiblitity of A Core Curriculum***. In Oxford Review of Education.R etrived On April, 20, 2010 from http:WWW.google.com.et.

Hess, N. (2001).***Teaching large multilevel classes***. NewYork: Cambridge University Press.

Heugh, K., Berhanu B., C. Benson, and Mekonnen A . (2007). ***Study on Medium of Instructi on in Primary Schools in Ethiopia.*** (Research Final Report commissioned by the Mi nistry of Education). Addis Ababa,

http://en.wikpedia.org/wiki/qualitative research

http://mara-e-econtent management.com/archives

http://www.ehow.com/list-7607707-types-qlaitative research-design-htm

Huba and Freed.(2000).***Teacher centerd Vs Learner-centerd pardiam***.Retrived on10/23/201.

Huber, G. L., & Roth, J. H. W. (1994). ***Case studies of active learning at a gymnasium and thre elementary schools in Germany.*** Report prepared for the meeting of the OECD/ CERI study group, Paris, November Retrived on 8/8/20113.

Hutchinson,T and,Alan w .(1987). ***English for specific purpose:Alearning-centerd Approac h***. Cambridge: C.U.P.

ICDR,(1999).***Teacher Education Hand Book***. ICDR:Addis Ababa: ourael Printing press.

Jacobs, G. M. & Hall, S. (2002**)**. ***Implementing Cooperative Learning***. In J. C. Richards (Ed s.), ***Methodology in Language Teaching***: An Anthology of Current Practice. Cambri dge: Cambridge University Press.

Johnson, D. W., & Johnson, R. T. (1989), ***Co-operation and competition***: Theory and Re-sea rch. Edina, MN: Interaction Book Co.

Jones,L.(2007).***The student Centerd-Classroom.*** Cambridge: Cambridge University Press.

Jones, T.J. (ed.) (1925). ***Education in East Africa. Report of the Second African Education Commission.***New York Phelps-Stokes Fund, and London: Edinburgh House Press.

Kakkar, S.B. (1995). ***Changing Perspectives in Education.*** New Delhi: Vikas Put d.

Kane, L.(2004). ***Educators, learners and active learning methodologies.*** International Journ al of Lifelong Education, 23(3):275-286.

Kim,J.(2005). ***The effects of a constructivist teaching approach on student academic achie vement, self-concept, and learning strategies.*** Asia Pacific Education Review,6 (1): 7-19.

Krahen, S. (1981). ***Second language Acqusition and Second language learning.*** New York: Pregmon press.

Krashen, S. D. (1985**)**. ***The imput hupothesis: issues and implications***. Harlow: Longman.*L anguage in Ethiopia* London: Oxford University Press.

Kumar R. (1999). ***Resarch Methodology***.London: SAGE Publications.Mack Natasha and Ot hers. 2005. Qualitative Research Methods. A Data Collector's Field Guide. USA: http ://www.fhi.org. E-mail: Publications @ fhi.org.

Kumaravadivelu,B. (2006). ***Understanding Language Teaching***. From Method To Post Met hod.London: San Jose State University.

Labov, W.(1982). Objectivity and commitment in linguistic sciences: The case of Black Engl ish trial in Ann Arbor. ***Language in Society,*** 11-165-201

Larsen-Freeman, D. (1986). ***Techniques and principles in language teaching.*** New York: Oxford University Prss.

Lema Dadi.(2006) ***.Application of Learner-centerd Method in Government Second Cycle Primary School of East shoa Zone*** Addis Ababa University; M.A. Thesis (Unpublished).

Leu, E .(1998) .***Designing Integrated Curriculum Materials for Primary Education****:* a Paper Presented at the Workshop in Oromia. Education Bureau. (Unpublished)

______(2000). ***The New Curriculum Issue of Theory and Practice For Teacher Education .*** Abbiyi Addi College of Teacher Education BESO project. (Unpublished)

Lightbown, P,& Spada, N. (1993). ***How languages are learned****.* Oxford:Oxford University Prs.

Littlebear, D. (1997). ***Effective Language Education Practices and Native Language Survival.*** U.S.A. Native American Language Press.

Littlewood. w.(1981). ***Communicative Language Teaching***. Cambridge: Cambridge University Press.

Locastro, V. (2001). ***Teaching English to Large Classes: Large Classes and Student Learnig***. TESOL Quarterly, 35(3), 493-496.

Lockheed and Verspoor, A.( 1991). ***Improving Primary Education in Developing Countries.*** World Bank/Oxford University Press.

Lodico.et al.(2006). ***Methods inEducational Reasearch. From Theory to Practice.***Jossey-Bass,Sanfrancisco, CA 94103-1741 www.josseybass.com

Long,M. (2000). ***The Psychology of Education****.* London: Rout Ledge Flamer.

LukõÖ,I(2006). ***Language policy and Process of nation - building in Ethiopia****.* Ivan.lukas@gmail.com

Mamonaheng A. M. (2007). ***Investigating the learner-centred approach in language teaching in Lesotho.*** Master of Education Victoria University .

Mack, N. et al.(2005). Qualitative research methods: A data collector's field guide. USA: Family Health International.Mc-Grath, I.(2002).***Materials Evaluation and Design for language Teaching.***Great Britain;Edinburgh Univarsity Press.

Matthews, et al.(eds) . (1985) ***At the Chalkface: Practical Techniques in Language Teaching.*** Edward Arnold.

Mc Combs, B. L. & Whistler, J. S. (1997). ***The Learner-Centered Classroom and School. Strategies for Increasing Student Motivation and Achievement.*** Sam Francisco: Jossey Bass Publishers.

Mc Donough.J and C.Shaw.(2003).***Materials and Methods in ELT****(2nd ed.)*.Oxford:Black Well,Pub.Inc.

Mc-Grath, I.(2002).***Materials Evaluation and Design for language Teaching***.Great Britain; Edinburgh Univarsity Press.

Mc Nab, C. (1987). ***Language Planning for Education in Ethiopia: Policy Development and Implementation Processes.*** Stockholm: Stockholm University.

Mc Nabb,C.(1989). ***Language Policy and Language Practice: Implementation Dilemmas in Ethiopia.*** Ph D thesis: Stockholm: Institue of International Education.

Mekuria Bulcha (1996) The Survival and Reconstruction of Oromo National Identity. In Baxter et al. (eds.) (1996) ***Being and Becoming Oromo: Historical and Anthropological Enquiries***. Lawrenceville, NJ: The Red Sea Press Inc.

Meyer, R. and R. Richter (2003). ***Language Use in Ethiopia: from a Network Perspective:*** R***esults of a Sociolinguistic Survey Conducted among High School Students.*** Frankfurt: Peter Lang.

Mindaye Abebe. (2005) ***.The Oromo of Bale: A Historical Survey to 1974. (*** Unpublished) MA Thesis, Addis Ababa University, College of Social Science.

Ministry of Education and Fine Arts. (1964). ***Elementary School Curriculum*** (Years I-VI). Addis Ababa:MEFA.

Ministry Of Education.(1991). ***Policy decision on the use of nationality languages as medium of instruction.*** (Amharic guideline), Addis Ababa.

______(1994). ***Transitional government of Ethiopia****:* ***Education and training policy.*** Addis Ababa, Ethiopia: Educational Materials Production and Distribution Agency(EMPDA).

______.(1994). ***Education and Training Policy***. Addis Ababa. MOE

______.(2003). ***A national Curriculum Guide Line for Pre-service Teacher Education Pro grams***. Addis Ababa, Ethiopia,.

Ministry of Youth, Sports and Culture. (2003). ***The Federal Democratic Republic of Etiopia Cultural Policy***. Addis Ababa: Birhanena Selam Printing Enterprize.

Moges Yegezu.(2010). ***Language Ideologies and Challenges of Multilingual Education in Ethiopia: The Case of Harari Region***. Addis Ababa: OSSREA.

Mohammed Hassen (1990) ***Oromo of Ethiopia: A History (1570-1860).*** **African Studies Se ries**. Cambridge: Cambridge University Press.

Moore, K. (2001).***Classroom teaching skills***. Newyor:McGraw-Hill College.

Mujis, D. (2004).***Doing Competetive Research in Education with SPSS***. New Delhi, Sage P ublications.

Murphy,D (1993). ***Developing Alearner-centerdApproach" In Guidelines Journey .***(Vol.15 No1.pp12-20)

Nasise,C.(ed)(2009). ***OromiyaToday.***Apocket guide.Publication of Oromiya PresidantOffice.

Neveile (undated). ***Educational Research: Some basic concepts and terminology***. UNSCO I nternational Institution for Educational Planning.

Nielson,H. and Cummings, W.K. (1997). ***Quality Education for All: Community Oriented Approach.*** London: Garland Publishing Inc.

Nunan, D. (1992). ***Collborative Language learning and Teaching***.Cambridge:Cambridge U niversity Press

_______(1988). ***The learner-centred curriculum: a study in second language teaching.*** Ca mbridge: Cambridge University Press.

_______(1989). ***Understanding language classrooms: A guide for teacher-initiated action.*** Englewood Cliffs, NJ: Prentice Hall. private ltd.

Ogutu, E. A. (2002). ***An African language classroom discourse: Two challenges of the inst ructor***. In V. Webb and L. Gangla (Eds.),2nd International Conference on African La

nguages: Promoting education, science, and technology through African languages ( pp. 161-167). University of Pretoria.

O'keeffe,M.,Cohan,p.(2011). ***An Introducation to Student centerd and Active learning For the Information Litercy Practioner.*** retrived on 10/29/2011.

Okombo,D..(2001). ***Language policy: The forgotten parameter in African development and governance strategies***. Nairobi: School of Journalism VON.

Orlich, D et al .(2001). ***Teaching Strategies: A Guide to Better Instruction (***16thed) Boston: Hough ton Mefflin Company.

Ornsten, A.and Honkins,F.(2004).***Curriculum Foundations,Principales, and Issues***.London. Pearson.

Oromia Bureau of Planning and Economic Development (OBPED) (2000) ***Physical and Socio-Economic Profile of 18 Districts of Oromia Region.*** OBPED.

Pankhurst, R. (1969). ***Lnguage and Education In Ethiopia***. ***historical background topost-war Period.***Addis Ababa,HSTU.

________.(1974).***Education, language and history: An historical background topost-war Ethiopia***. Ethiopian Journal of Education Vol. VII, No.1.

____(1976).***The beginning Of Oromo Studies in Europe***. Africa XXX 1(2),171-206. Rome.

Patten, A. (2001). ***Political theory and language policy***. ***In Political Theory*** 29(5),691-75.

Petty, G. (2001). ***Teaching Today. A Practical Guide***: Nelson Thornes.

Prah, K. K. (2002). ***Facing the future: towards the usage of African languages in scientific and technological education and development***. In V. Webb and L. Gangla (Eds.), 2nd ***International Conference on African Languages***: Promoting education, science, and technology through African languages (pp. 205-212). University of Pretoria.

Puhl.A .(1997). Develop, Not Judge: Continuous Assessment in ESLClassroom.Englishaching Forum***: A Journal for Teacher of English Outside the UnitedStates***, Vol.35, No.2.

Renaud, S et al. (2007). ***Student-Centered Teaching in Large Classes with Limited Resources,*** N o.3 English Teaching Forum.

Richards, JC. (1990). The Dilemma of Teacher Education in Second Language Teaching in Richards and Nunan (Eds) ***Second Language Teacher Education.*** Cambridge:Cambridge University Press.

Rechards, J.C. (1994) ***Educating Second Language Children: The Whole Child, the Whole Curriculum, the Whole Community***. U.S.A. Cambridge University Press

Richards, J. C. & Lockhart, C. (1994). **Reflective teaching in second language classrooms.** Cambridge: Cambridge University Press.

Richards and D.Bohlke .(2011)***.Creating Effective Language Lessons .***Cambridge**,**Cambridge Univer sity Press.

Richards, J. C. & Rogers, T. S. (1986). **Approaches and methods in language teaching:** A description and analysis.Cambridge,UK:Cambridge University Press

Richards,J.c. & Renardy,W.A.(ed)(2002).***Methodology in Language Teaching. An Anthology of Current Practice.*** Cambridge:Cambridge University Press.

Richards, J.c. (2006).***Curriculum Developmentin Language Teaching.***Cambridge : Cambridge University Press.

Roberts, J. (1998): ***Language teacher education*****. London: Arnold.**

Robinson, C. (2006). **Languages and literacies. Journal of Adult Education and Development**. No. 66, 167-202.

Rogers, C. (1961).***On becoming a person: a therapist's view of psychotherap.*** Boston: Houghton-Mifflin

Ruddel,M.(1997)***Teaching Content Reading and Writing***.(2nd ed).Boston:Avicom Company.

Saulnier, B., Landry, J., Longenecker, J., & Wagner,T. (2008), **"*From Teaching to Learning : Learner-Centered Teaching and Assessment inInformation Systems Education.*"** Journal of Information Systems Education, Vol. 19, No. 2, pp. 169-174.

Schiffman, H.(2005)."***Language policy: introductory remarks***" retrieved on September 18, 2005 from Ling.

Senior, R. (2006). ***The experience of language teaching***. New York:Cambridge University Press.

Seyoum Hameso. (1997). ***The language of education in Africa: The key issues.Language, Culture and Curriculum*** 10 (1): 1-13

Silberman, M (1996). ***Active Learning 101 Strategies to teach any Subject***. Boston:Ally and Bacon.

Sirak Demelash (2000). ***"Learner-centered Instruction in Teacher Training In of Amhara Region",*** (M.A. Thesis). Addis Ababa University.

Smith,R. (2004).***Student–centerd Learning***(File://A:Student-centerd%20 Learninhtm .

Smith, J (1987) (ed). ***Educating Teachers: Changing the Nature of Pedagogical Knowledge*** .London: The Falmer Press.

Smylie, M. et al (1999). ***Preparing Teachers as Agents of Change.*** Chicago: NSSE.

Solomon Worku.(2009)"**Exploring the status of the learner-centerd Approach in EFL cla sses.Grade 8 in Focus".**(M.A. Thesis). Addis Ababa University.

Spolsky, B (1986). **Language and education in Multilingual Setting.** Cleve don, Avon: Mu ltilingual Matters.

Squazzin, T. and Graan, M.V. (eds). (1998) "***Education Reforms and Innovations in Namib ia:How best can Changes in Classroom Practice be Implemented and Supported"*** P roceeding from the 1998 NIED Educational Conference,Okahandia: 13-16October, N amibia.

Stead, D.R. (2005). ***A review of the one-minute paper***. ***Active Learning in Higher Educatio n***, 6(2):118–131.

Stern H.H(1983).***Fundamental Concepts of language teaching***.Oxford:Oxford University pr ss.

Taye Geresu (2008) ***"Perception and Practices of Active Learning in EFL Classroom"*** Ad dis Ababa University; M.A. Thesis (Unpublished)

Tekeste Negash (1990) ***The Crisis of Ethiopian Education: Some Implications forthe Nation Building,*** Uppsala Reports on Education, 29. Uppsala University.

___________(2006) ***Education in Ethiopia: From Crisis to the brink of Collapse,*** Uppsala: Nordic Africa Institute, Discussion Paper 33

Teshome Wagaw. (1979).***Education in Ethiopia**: **Prospects and Retrospects***. University of Michigan, New York.

Teshome Yizengaw ( 2006). ***Implications of the Ethiopian Higher Education Expansion Strategy Towards Quality, Equity and Reform.***A Paper for the2005/ 06 Fubright New Century Scholarships, UB. USA: State University of New York

The Danish Education Network (2008) *"**Mother-Tongue and Bilingual Education**."* A Collection of Conference Papers. Copenhagen, Denmark.

The Federal Democratic Republic of Ethiopia .(FDRE) (1995) ***Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,*** Addis Ababa: FDRE.

____(2002). ***The Education and Training Policy and its Implementation***. Addis Ababa. OE

_____ (1996). ***The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia****:* Results for Oromoia Region, 1 (IV). Addis Ababa: FDRE.

_____ (1999).***The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia Results at Country Level***. Vol. II, Analytical Report. Addis Ababa: CSA.

_____ (2008).***The 2007 Population and Housing Census Results of Ethiopia***. Addis Ababa: Populations Census Commission.

The Revised Constitution of (1955).Proclamation 149 and its ***Negarit Gazeta***15(2), Article 1.

The World Bank . (2005). ***Education in Ethiopia: Strengthening the Foundation for Sustainable Progress*** . USA:Washington, D.C.

Tibbets, J.et al. (1968). ***Teaching in the Developing Nations: A Guide for Educators***.U.S.A. Wadsworth Publishing Company Inc., Belmont, Californi.

Tirualem Ayalew(2003).***The Classroom Practices of Learner-centerd Approach In Second Cycle Primary School of Addis Abeba.*** Addis Ababa University; M.A. Thesis (Unpublished).

Transitional Period Charter of Ethiopia. (1992).Addis Ababa: TGE

Tsegaye Obse .(2001)***Learner-centerd Approach in Large Classes***.A Survey in 13 selected in 1st Primary Schools in Gedeo Zone(Snnp).Addis Ababa University; M.A. Thesis (Unpublished).

Tudor, I. (1993). Teacher Role In Learner-centred CLassroom.***ELT Journal*** (vol.47,no.1),Oxford : Oxford University Press.

Tudor, I. (1996). ***Learner-centredness as Language Education*** .Cambridge: Cambridge University Press.

Tyler,R.W. (1949). ***Basic Principles of Curriculum and Inovation***.Chicago:Chicago University Press.

UNESCO. (1951). ***The Use of vernacular languages in education*****:** The Report of the UNESCO meeting of specialistsc pp. 688-716

______ .(1953).**T*he Use of Vernacular Languages in Education***: Monographs on Fundamental Education. Paris: UNESCO. University of Michigan, New York.

______ .(2000) ***Change in Continuity: Concepts and Tools for a Cultural Approach to Development***. Culture and Development Series. Paris: UNESCO.

**______.(**2003**).*Education in multilingual world, Paris*:** UNESCO position paper (also available at www. unesco.org/education

Ur,P. (1996). ***A course in language teaching: Practice and theory***. Cambridge: Cambridge UniversityPress.

Vygotsky, L. (1978). ***Mind in Society: the Development of HigherPsychological Processes***. Cambridge: Harvard University Press.

Watkins.C, Eileen.C& Caroline.L. (2007). ***Effective Learning in Classrooms***.London:A SAGE Publications Indian pvt Lt.

Weimer, M. (2002). ***Learner-centered teaching: five key changes to practice***. San Francisco ,CA: Jossey-Bass.

White, R. (2003).***The ELTCurriculum:Design,Innovation,Managemen*****t**.Berlin Black Well Publishing LTD.

Weinstein, B. 1983. ***The Civic Tongue: Polotical Consequences of Language Choices.*** New York: Longman Inc.

Wolff, H. E. (2002). ***Language planning implementation in Africa. In V. Webb and L. Gan gla (Eds.), 2nd International Conference on African Languages: Promoting educa tion, science, and technology through African languages*** (pp. 242-263). University of Pretoria

World Bank .(2005).***In their own Language Education Notes***.June2005.

Woube Kassaye.(2002). ***Analysis of Culture for Planning Curriculum***: The Case of Songs p roduced in the Three Main Languages of Ethiopia,PhD:University of Joensuu,Finland

Wudu.Meles,Tefera.T and Woldu,A.(March),(2009). A Practice of Learner-centerd Methods in Primary school of Ethiopia. ***Journal of Education and science***. vol.4, No.2.(pp27-44.)

Xiaomei,y.(2010).***The Globalaization And Localization of Learner-centerd Strategy From an International Horizon.***China,Gadao University Of Social Science and Tecnology.

Yalew Endawek. (2004). ***Beliefs, Knowledge and Practice of Learner-Centered Approach i n Schools of Ethiopia.*** The Ethiopian Journal of Education **42**,17-24.

Yewulsew Melak. (2009). ***Investigating Teachers' and students' Beliefs And Practices Tow erds Active Learning In EFL Classes***:Debremarkos College of Teacher Education In Focus .Addis Ababa University; M.A. Thesis (Unpublished)

Yin,R.K. (1994).***Case study research:Design and Method*****s**.(2nd ed).Thousand Oaks,Ca:Sage.

Zhung,J. (2010).The changing Role of Teachers in Development of Learner Autonomy Base d on Servey of English Dorm Activity.***Jornal of LanguageTeaching And Research*** **.** Vol,1,No 5,pp591-595,September,2010.

Zulkuf, M and Christine,T. (2001).***Creating Learner-Centerd Teacher Education Progra*****m**. http://Exchnges. State.gov/forum/vol139/no3/P28.htm.

**ሙሉጌታ ይታየው** (1996) "**የተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፤በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሰርትፊኬት መርሀ-ግብር**

እንደታየው፡፡"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ድህረምረቃ ትምህርት ቤት፣ ለኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡(ያልታተመ)

ትምህርት ሚኒስቴር (1986) ***አጠቃላይ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ*።** አዲስ አበባ፣ ት.ማ.ማ.ድ፡፡

**--------------------- (1994)** ***የትምህርት መስፋፋትና ጥራት ችግሮችና*** መፍትሄዎቻቸው፡፡ ለመምህራንና ርዕሳነ መምህራን በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ፡፡ (ያልታተመ)

***--------------------- (1996) ተከታታይ የመምህራን ሙያዊ እድገት (CPD) መርሀ-ግብር*።** አዲስ አበባ፣ በBESO ድጋፍ የታተመ፡፡

ኤልያስ አድማሱ *(1997)* ***በኦሮሚያ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር*፣** አዲስአበባ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረምረቃ ትምህርት ቤት ለኤምኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)

*ያለው* እንዳወቅ (2001) ***የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፣** አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

*አባሪ አንድ፡- የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ*

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ጥናት ትምህርት ክፍል**

**የድህረ-ምረቃ መርሀ-ግብር ቤት**

የዚህ የምልከታ ማረጋገጫ ቅጽ ዋና ዓላማ የአፋን ኦሮሞ መምህራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያተምሩ የሚደረጉ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎችን ማሳየት ነው፡፡ ተግባራቱ በ"አለ ወይም የለም "በሚል ተከፍለው የሚታዩ ባህሪያትን በነዚህ ቃላት ስር ምልክት በማድረግ መሙላት ነው፡፡

**የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራን የሚያመለክት የክፍል መከታተያ ቅጽ፤**

ክፍል አንድ፡-አጠቃላይ መረጃ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጁ /የትምህርት ቤቱ ስም__________________________________.

በምልከታ የታየው ትምህርት __________________.

በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር: ወንድ _______ሴት_________ጠቅላላ____________

የመምህሩ/ሯ የትምህርት ደረጃ _______________

በኮሌጁ ውስጥ በማስተማር ያለው ቆይታ_____________

| ቁጥር | አማራጮች | አለ | የለም |
|---|---|---|---|
| 1 | **የመማሪያ ክፍል ሁኔታ** | | |
| 1.1 | በቂ የመቀመጫና መደገፊያ አለ፡፡ | | |
| 1.2 | ለተማሪዎች ሁሉ በቂ ክፍተት አለ፡፡ | | |
| 1.3 | መቀመጫዎቹ ተንቀሳቃሽ ናቸው፡፡ | | |
| 1.4 | የመማሪያ ክፍሉ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር አመቺ ነው፡፡ | | |
| 1.5 | ክፍሉ መምህራን በቡድን ውስጥ እየተዘዋወሩ እገዛ ለማድረግ ያመቻቸዋል፡፡ | | |
| 1.6 | የተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ ጋራ የተመጣጠነ ነው፡፡ | | |
| 1.7 | የጥቁር ሰሌዳው ጽህፈት ለሁሉም ተማሪዎች የሚታይ ነው፡፡ | | |
| 1.8 | ወንወበሮች በረድፍ ተደርድረዋል፡፡ | | |
| 1.9 | በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ በቂ ብርሃን አለ፡፡ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.10 | የክፍሉ ወለልና ግርግዳ ንጹህ ነው፡፡ | | |
| 2 | **የመምህራን ተግባራት** | | |
| 2.1 | መምህራን የተለያዩ የትምህርት መርጃ ማሪያዎችን እየተጠቀሙ ነው፡፡ | | |
| 2.3 | ተማሪዎቹን ለተለያዩ ተግባራት እያዘጋጃቸው ነው፡፡ | | |
| 2.4 | የትምርቱን ዓላማ ያብራራሉ፡፡ | | |
| 2.5 | የተለያዩ ብልሃቶችን እየተጠቀሙ ናቸው | | |
| 2.6 | ተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ያነሳሳሉ፡፡ | | |
| 2.7 | ስለሚሰሩት ተግባራት በቅደም ተከተል መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ | | |
| 2.8 | በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን ያግዛሉ፣ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ | | |
| 2.9 | ከተማሪዎች የበለጠ መምህራኑ በንቃት ተሳታፊ ነው፡፡ | | |
| 2.10 | በቡድን ውስጥ እየተንጎራደዱ ተማሪዎቹን ያበረታታሉ፡፡ | | |
| 3 | **የተማሪዎች ተግባራት** | | |
| 3.1 | በተለያዩ መልመጃዎች ላይ እየተወያዩ ናቸው፡፡ | | |
| 3.2 | ሀሳባቸውን በነፃ ይገልፃሉ፡፡ | | |
| 3.3 | ዝም ብለው የመምህራቸውን ንግግር ያዳምጣሉ፡፡ | | |
| 3.4 | እርስ በርስ በብጤ እየተማማሩ ናቸው፡፡ | | |
| 3.5 | የክፍል ስራ ወይም የተሰጣቸውን ስራዎች እየሰሩ ናቸው፡፡ | | |
| 3.6 | የሰሩትን ስራዎች እያቀረቡ ናቸው፡፡ | | |
| 3.7 | ማስታወሻ እየፃፉ ናቸው፡፡ | | |
| 3.8 | የግል ስራ እየሰሩ ናቸው፡፡ | | |
| 3.9 | በፀጥታ እያነበቡ ናቸው፡፡ | | |
| 4 | **የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በተመለከተ** | | |
| 4.1 | መምህራን የተለያዩ የትምህርት መርጃ ማሪያዎችን እየተጠቀሙ ነው፡፡ | | |
| 4.2 | የትምህርት መርጃ መሳሪያዎቹ በቂ አይደሉም፤፡ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4.3 | አፋን ኦሮሞን ለማስተማር ሁልጊዜ የተለየ መርጃ መሳሪያዎች ይዘጋጃሉ፡፡ | | |
| 4.4 | መምህራን ሃባቸውን ለማብራራትና ጽንሰ ሀሳቦችን ለመግለጽ በተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡ | | |
| 4.5 | የተለያዩ ይዘቶችን ለማብራራት ሰልጣኞች ራሳቸው የትምህርት መሳሪያዎችን ያዘጋጃሉ፡፡ | | |
| 4.6. | በቂ የማስተማሪያ መፃህፍት ወይም ሞጁሎች አሉ፡፡ | | |
| **5** | **የምዘና ስልት** | | |
| 5.1 | መምህራን የክፍል ስራ ወይም መልመጃዎችን ይሰጣሉ፡፡ | | |
| 5.2 | የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፡፡ | | |
| 5.3 | ተማሪዎቻቸውን በቡድን ስራ ይመዝኗቸዋል፡፡ | | |
| 5.4 | ሰልጣኞች ደብተራቸውን በመለዋወጥ ወይም ስራዎቻቸውን በመቀያየር ያርማሉ፡፡ | | |
| 5.5 | መምህሩ የተማሪዎቹን የተለያዩ ተሳትፎና ተግባራት ላይ ገንቢ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ | | |
| 5.6 | መምህራን ተማሪዎቹን በተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃት ውስጥ ተሳትፎ ይመዝናቸዋል፡፡ | | |
| 5.7 | መምህሩ የራሳቸውን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በተማሪዎቻቸው ምላሽ ይጠቀማሉ፡፡ | | |
| 5.8 | መምህራን ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ በጥቁር ሰሌዳ ይጽፋሉ፡፡ | | |

## አባሪ ሁለት፡- ከሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ዲን ጋራ የተደረገ ቃለ-መጠይቅና መልስ ናሙና

በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ዲን ጋራ በ20/07/2004 ዓ.ም ከረፋዱ 3፡20 ላይ ቃለ-ላቅርብላቸው ተገናኝተን ነበር ። በቅድሚያ ጥናት ስሜንና የጥናቴን ርዕስ ካስተዋወኩ በኋላ የእሳቸውን ስምና የስራ ኀላፊነታቸውን እንዲገልፁ ጥያቄ ቀረበላቸው።

መ.ስሜ - ይባላል። የስራ ድርሻዬ በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ዋና ዲን ነኝ።

ጥ.በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ ዕጩ መምህራን እንዴት እየሰለጠኑ ይገኛሉ?

መ...በሮቤ መ/ም/ት/ኮ/ውስጥ መማር-ማስተማሩ የሚካሄድበት መንገድ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ወይም ንቃት በተላበሰ መንገድ ነው። ንቃት በተላበሰ ማለት ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ በመሳተፍ እውቀት የሚገበዩበት መንገድ ማለት ነው። በአጭሩ በተብራራው መንገድ ስለሚማሩ የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እየተገበርን ነው። ይህ ሲባል በቀድሞው እና በተለምዶአዊው የመምህር-ተኮር አቀራረብ ስርዓተ-ትምህርት ውስጥ መምህራን ንቁ በመሆን ተማሪዎች በበኩላቸው ፍዝ ሆነው መማር-ማስተማሩ ይከናወን ነበር። በዚህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ግን መምህሩ ሁኔታ አመቻች፣ ማብራሪያ ሰጪ፣ ረጂ የሆነበት ስርዓተ-ትምህርት ነው። ስለዚህ በዚህ አቀራረብ ማስተማሩ የግድ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎች በራሳቸው ትምህርት ውስጥ ተሳታፊ ሆነው እየተማሩ ነው።

ጥ. በመምህራን ኮሌጁ ውስጥ የመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪ ተኮር ከሆነ አሰልጣኝ መምህራኑ ስልጠናውን ከየት ያገኙት ይመስልዎታል? ወይስ የስራ ላይ ስልጠና ተሰጥቷቸው ነው?

መ.በዚህ ኮሌጅ ውስጥ ተመድበው የሚመጡት በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ቆይታ አድርገው ነው። እነዚህ መምህራን የቅድመ ስራላይ ስልጠና አግኝተው ነው። እኛ ኮሌጅ ውስጥ ከተመደቡ በኋላ ደግሞ በተለያዩ መርሀ-ግብሮች ስልጠና ያገኛሉ። ከመርሀ-ግብሮቹ ውስጥ እንደአብነት የሚጠቀሱት የከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP)መማር ይጠበቅባቸዋል። ይህ ትምህርት ደግሞ መምህራን የመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ንቃት የተላበሰን መንገድ ስራ ላይ እንዲያውሉ፣ የተለያዩ የአገማገምና ምዘና ዘዴዎችን ፣በክፍል መማር ማስተማር ውስጥ የቡድን አመሰራረትን፣የክፍል ውስጥ ቁጥጥር፣ በመሳሰሉት ዙሪያ ለአንድ አመት ስልጠና ይሰጣቸዋል። በዚህ ዓመት ውስጥም የመጡትም መምህራን ቢሆኑ ይህ የከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP) ስልጠና እየተሰጣቸው ይገኛል።ከዚህም በተጨማሪ በራሳችን መምህራን የስታፍ ውስጥ ስልጠና (In-Stuff Traing) ይሰጣል። ይህም በመማር-ማስተማር ሂደት፣ በተከታታይ ምዘና፣ በICT፣ ልምድ ባላቸው መምህራን እርስበርስ ይሰለጣጠኑበታል። በዚህ

መንገድ በመማር-ማተማር ሂደት ወቅት ንቃት የተላበሰ ወይም ተማሪ-ተኮር አቀራረብን እየተገበሩት ይገኛሉ። ይህ የስታፍ ውስጥ ስልጠና( In-Stuff Traing) በስትሪምም የልምድ ልውውጥ በኮሌጃችን ውስጥ አለ። ይህ ማለት በአንድ ስትሪም ውስጥ የተለያዩ ኮርሶችን የሚያስተምሩት መምህራን በራሳቸው ፊልድ ያገኙትን ልምዶች ለሌሎች ጓደኞቻቸው ያካፍላሉ።እንግዲህ በዚህ ዓይነት መንገድ ስልጠናዎች ሲገኙ ነበር።

ጥ. የተማሪ-ተኮር አቀራረብ መምህራን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩት ምን ዓይነት የመማር ብልሃቶችን (Stratejies) ይጠቀማሉ?

መ. እሺ መምህራን በዚህ ስትራቴጂ ይጠቀማሉ ማለት አስቸጋሪ ቢሆንም እንግለፀው ከተባለ መምህራን በስራ ላይ ስልጠና፣በዩኒቨርሲቲ ቆይታ፣በከፍተኛ ዲፕሎማ (HDP) ስልጠና፣ በስታፍ ውስጥ ስልጠና ( In-Stuff Traing) የተወሰዱትን ስልጠናዎች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ጥበባቸውን ይጠቀማሉ። ይህ ተግባራዊ የሚያደርጉበት ጥበብ ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል። ቢሆንም እንደ አጠቃላይ ስንወስደው እንደ የመምህራን ሙያ ትምህርት ክፍል ተመሳሳይ ኮርስ የምናስተምር መምህራን በየትምህረቱ ምዕራፍ ምን መስራት እንደአለብን ማዕቀፍ (ማንዋል) አዘጋጅተን በዚያ እየተመራን በክፍል ውስጥ እንተገብራለን። በየትኛውም የመማር-ማስተማር ዘዴ በመጠቀም እንደአለብን፣ ተከታታይ ምዘናን እንዴት መጠቀም እንደአለብን፣ እናወጣለን። እንደ አብነት ከመማር-ማስተማር ዘዴዎች ውስጥ እረፍት ባለው ገለፃ መጠቀም፣በቡድን ውይይት፣ በጓደኛ ማስተማር (Peer Teaching) በፕሮጀክት የማስተማር ዘዴ፣ በሙከራዊ ዘዴ ማስተማር፣ በፓናል ውይይትና በመሳሰሉት ተግባር ላይ እናውላለን። ይሁን እንጂ የአተገባበር ጥበቡን የትምህርቱና ይዘቱ ሊወስነን ይችላል።

አባሪ ሶስት፡- በሮቤ/መ/ም/ት/ኮ የአካዳሚክ ም/ዲን ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ

ዕለቱ 8/02/06 ዓ.ም፣ቦታ ሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአካዳሚክም/ዲን ቢሮ

ሰዓት፡-4፡00-4፡30

ጥ.በዚህ ኮሌጅ ውስጥ የመማር-ማስተማሩ ሂደት እንዴት እየተካሄደ ነው?

መ.በኮሌጃችን ውስጥ የመማር ማስተማሩ-ሂደት ተማሪን ማዕከል በሚያደርገው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተከናወነ ነው፡፡እያንዳንዱ መምህር የተዘጋጀለትን ሞጁል ሲያስተምሩ ተማሪዎች በራሳቸው በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እየተሳተፉ እንዲማሩ ያደርጋሉ፡፡በመማሪያ ሞጁሉ ላይ የቀረቡት መመሪያዎችና የትምህርት ይዘቶች ራሳቸው ተማሪን ማዕከል ተደርገው ስለተዘጋጁ ሰልጣኝ መምህራኑ በቡድን በቡድን ሆነው ተወያይተው የደረሱበትን ሀሳብ ለሚያስተምሯቸው መምህራን ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡የሚሰሩት ተግባራት በቡድን ብቻ ላይሰሩ ይችላሉ፡፡ለምሳሌ በግል፣በጥንድ፣በቡድን እና ከሙሉው የክፍል ተማሪዎች ጋራ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡በሞጁሉ ውስጥ የቀረቡት ትዕዛዛት ተማሪዎቹ በምን አይነት የመማር ብልሃቶች ስለሚጠቁሙ በዚያ መሰረት ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ተግባራቱን ይከውናሉ፡፡ስለዚህ የመማር-ማስተማሩ ሂደት እየተተገበረ ያለው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው፡፡

ጥ.በሞጁሉ ዝግጅት ወቅት ተማሪዎች እንዲሳተፉ ታደርጋላችሁ?

የምናስተምርበት ሞጁል የሚዘጋጁት በኦሮሚያ ውስጥ የሚገኙት ሁሉም የመምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጆች መምህራን በአንድነት እንደሚያስተምሩት የትምህርት አይነት በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አስተባባሪነት በአንድ ቦታ ተሰባስበው ያዘጋጃሉ፡፡ሞጁሎቹ ሲዘጋጁም በቅድሚያ ከትምህርት ሚኒስቴር በአገሪቱ ውስጥ ያሉት የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች ሁሉ ማስተማር የሚገባቸውን የትምህር ይዘቶች በመርሀ-ትምህርት አማካይነት ይሰጥና እንደ ክልሉ የማስተማሪያ ቋንቋ ይዘጋጃሉ፡፡እኛም በተጠራን ጊዜ ከየትምህርት ክፍሉ የኛን መምህራን መርጠን እንዲዘጋጁ ይደረጋሉ፡፡ተማሪዎችን ታሳትፋላችሁ ወይ ላልከው በሞጁሉ ዝግጅት ውስጥ ተማሪዎችን ታሳቢ አድርገን እናዘጋጃለን እንጂ አሳትፈናቸው አናውቅም፡፡የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮም ተማሪዎች ከኛጋራ ሆነው እንዲያዘጋጁ ሁኔታዎችን አላመቻቹም፡፡ስለዚህ በኛው መምህራን ብቻ ተሳትፈን እናዘጋጃለን፡፡

ጥ.በ2006 ዓ.ም የተዘጋጀው የስርዓተ-ትምህርት ካለፈው ለየት ይላል ሲባል ተሰምቷል፡፡እስቲ ዕጩ ሰልጣኞችን እንዴት ልታስተምሩ ተዘጋጃችሁ?

መ.በዘንድሮው 2006ዓ.ም ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ይዋል የተባለው ስርዓተ-ትምህርት በትምህርት ሚኒስቴር ፀድቆ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ተቀባይነት አግኝቶ የፀደቀ ነው፡፡ይህም ስርዓተ-ትምህርት ያስፈለገበት ምክንያት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን እየሰለጠኑበት

ያሉበት የትምህርት ይዘቶችና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰጡት የትምህርት ይዘቶች እንዲጣጣሙ ተደርገው የቀረቡ ናቸው፡፡

በተጨማሪም ከማስተማር ልምምድ ይቶች ጋር ተጣጥመው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ለምሳሌ ከአሁን በፊት በኮሌጅ ደረጃ ሲለማመዱበት የነበረውን የፕራክቲከም ይዘቶች ሦስተኛ ዓመት ላይ የማስተማር ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት የሚያጋጥማቸው የትምህርት ይዘት ጋራ ያለመጣጣም ሁኔታ ነበር፡፡ ይህም ከግምት ውስጥ ገብቶ በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ ተደረገ፡፡ በአጭሩ በኮሌጁ ውስጥ ዘንድሮ የሚገቡት ዕጩ መምህራን አንደኛ ዓመት ላይ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚሰጡ የትምህርት ይዘት ጋራ መጣጣም እንዲችል ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ለምሳሌ በዚህ ዓመት ወደ ኮሌጁ የሚገቡት ዕጩ ሰልጣኝ መምህራን እንደ ቀድሞ ስትሪም መርጠው የሚገቡ ሳይሆን በመጀመሪያ ዓመት የጋራ ኮርስ(Common Course) ይማራሉ፡፡ በነዚህ ኮርሶች ውስጥ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩትን የትምህርት ይዘቶች ያገኛሉ፡፡…በቋንቋ አፋን ኦሮሞ እንግሊዘኛና አማርኛ ያገኛሉ፡፡ ስለዚህ ከዚህ ሁኔታ ላይ በመነሳት የዘንድሮ (2006ዓ.ም )ዕጩ መምህራን እንደ ድሮው ሳይሆን እዚህ ግቢ ገብተው በአንደኛ ዓመት ላይ በሁለቱም ሴሚስቴር ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ላይ ስትሪም(የትምህርት ክፍል)ይመርጣሉ ማለት ነው፡፡

ጥ.እንግዲህ በሚቀጥለው ጊዜ የመማር-ማስተማሩ ዘዴ ምን አይነት ይሆናል ብለው ያስባሉ?

መ. እዚህ ኮሌጅ ውስጥ ሁሉም መምህራን የሚያስተምሩበት የማስተማር አቀራረብ የተማሪ-ተኮር ነው፡፡ በዕቅዳቸው ውስጥ አስገብተው እየሄዱበት ይገኛሉ፡፡ምክንያቱም እነዚህ ዕጩ መምህራን ነገ ህፃናትን የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ወሳኝ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እዚህ ኮሌጅም ሆነ ትምህርት ቤት ሄደው ሲያስተምሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ (ንቃት በተላበሰ)መንገድ ያስተምራሉ፡፡ ይህን መተግበር ግዴታ ነው፡፡እኛም ለመምህራን ግምገማ ትልቅ ፐርሰንት የምንሰጠው ለዚህ ነው፡፡ ይህን አቀራረብ ስራ ላይ ማዋላችን ለመምህራንም ይሁን ለተማሪው ጥቅም ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች በዚህ አቀራረብ ሲማሩ እውቀት ይከፋፈላሉ፣በነፃነት ይማራሉ፣የውስጣቸውን ሀሳብ ለሌሎች ይገልፃሉ፡፡ ይህ በቡድን በመማር አንዱ አንዱን እያጠናከሩ በትምህርቱ ውስጥ መነሳሳት እንዲኖር ያደርጋቸዋል፡፡ መምህራን ደግሞ የሚሰሩትን ስራ ዕቅድ አውጥተው ዓላማ ነድፈው እንዲተገብሩ ቅድሚያ የሚሰሩትን እንዲያስቡበት ይረዳቸዋል፡፡ በትምህርት ቤትም ሲሄዱ ይህንኑ ስለሚተገብሩ በሚገባ እየተተገበረ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

**ጥ.እንደ እርስዎ ሀሳብ ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በአግባቡ ተተግብሯል ብለው ያስባሉ?**

**መ.** እንደሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሁሉም መምህራን በሁሉም ትምህርቶች ውስጥ በሚገባ እየተተገበረ ነው፡፡ ይህንንም ስል በመምህራን መካከል ልዩነት እስካለ ድረስ በአተገባበር ላይ ልዩነት አይኖርም ማለት አይቻልም፡፡ በተጨማሪም በሚሰጡት የትምህርት ይዘቶች መካከልም ልዩነት ሊኖር ይችላል፡፡ ከነበነዚህ ምክንያቶቸ የአተገባበር ልዩነት ሊኖር ይችላል፡፡

**ጥ.በዙሪያችሁ በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን የተማሪ-ተኮር አቀራረብን እንዴት እየተገበሩት እንዳሉ የሚገልጽ ያጠናችሁት ጥናት ይኖር ይሆን?**

መ.እኛ ከዚህ ኮሌጅ ተመርቀው የወጡ መምህራን በትምህርት ቤታቸው ውስጥ እንዴት እየሰሩ እንደሚገኙ የምንከታተልበት መንገድ አለን፡፡ተከታታይ ምዘናን እንዴት ስራ ላይ እንደሚያውሉት ትልቅ ምርምር ባናደርግም በተለያየ ጊዜ ምልከታ በማድረግ የታየውን ክፍተት በማየት ዕቅድ አውጥተን የተለያዩ ስልጠናዎችን እንሰጣቸዋለን፡፡ ለምሳሌ በ2005 ዓ.ም ውስጥ በአምስቱም ስትሪሞች ውስጥ እነሱ ከዚህ ተምረው የወጡትን ትምህርቶች መሰረት በማድረግ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስልጠና ሰጥተናቸዋል፡፡ በዚህ ዓይነት በታዩት ክፍተቶቸ ዙሪያ የተከታታይ ሙያ ማበልፀጊያ(CPD)ስልጠና እየሰጠናቸው እንገኛለን፡፡

እሺ በጣም አመሰግናለሁ

እኔም አመሰግናለሁ ከዲር ገቢ 8/02/06ዓ.ም

## *አባሪ አራት፡-የአፋን ኦሮሞ ትምህርት በኮሌጅ ውስጥ የሚደረገው አሰለጣጠን*

*ዕለቱ* 1/09/05

*ምስጋናና የጥናቱ ዓላማ ከተገለፀ በኋላ ወደ ቃለ-መጠይቁ ለማምራት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህ ኮሌጅ ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዴት እያከናወናችሁ ናችሁ? ተብሎ ለኮሌጁ የቋንቋ ስትሪም ተጠሪና ለአፋን ኦሮሞ መምህር ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፡- የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪን ያማከለ* (*ተማሪ-ተኮር* ) *ሲሆን በንቃት ላይ የተመሰረተ የመማር-ማስተማር ሁኔታ ነው፡፡ ስለዚህ የኛ መምህራን በተለይም የከፍተኛ ዲፕሎማ* (HDP) *የሚል መርሀ-ግብር በመኖሩ ከዚያ የምናገኘነው እውቀት ወደ ስራ እንቀይረዋለን ማለት ነው፡፡ እኛ እንደ ቋንቋ መምህራን የተለያዩ ስልጠናዎችን ከተለያዩ ተቋማት እናገኛለን፡፡ እነዚህ ተቋማት መንግስታዊና* (None Governement)*የሆኑም አሉ፡፡ እንደ የአሜሪካ መንግስት መሰረታዊ ትምህርት እርዳታ ድርጅት* (USAID) *ስልጠና ወስደን የአንደኛ ደረጃ መምህራንን ተመልሰን እናሰለጥናለን፡፡ በሌላ በኩል እኛም እንደቋንቋ ትምህርት ክፍል የእንግሊዘኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ማዕከል* (Elic) *የሚባል በመኖሩ በዚህ ስር በዚህ ክፍል ተዘጋጅቶ ለአንደኛ ደረጃ መምህራን እንሰጣለን፡፡ በተለይም በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎቻችንን* E-Lesson *የሚባለውን በዚሁ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት እያስተማርን እንገኛለን፡፡*

*ወደ አፋን ኦሮሞ ትምህርት ክፍል ስንመለስ የተለያዩ ኮርሶችን እንሰጣለን፡፡ በእነዚህ የተለያዩ ትምህርቶች ውስጥ የተለያዩ የማስተማር ብልሃቶችን እንሰጣለን፡፡ ይኸውም ተማሪዎቻችን በክፍል ውስጥ በቡድን በቡድን ሆነው መምህራቸው ያቀረቡትን ጥያቄዎች የሚመልሱበት ነው፡፡ በሌላ በኩል በአሁኑ ሰዓት በኮሌጃችን ውስጥ የግብረሀይል ስራዎች ይኖራሉ፡፡ ይህ የግብረ-ሀይል ስራዎች እንደመማሪያ ክፍልና ከ1ኛ-3ኛ ዓመት ተብሎ ይገኛል፡፡ በዚህ ውስጥ ደግሞ አንድ ለአምስት ሬሾ አለ፡፡ እነዚህም የቡድኑ አባላት ተደባልቀው የሚመሰርቱት ነው፡፡ ጎበዞች ከደካሞች፣ ሴቶች ከወንዶች ወዘተ ማለት ነው፡፡ በዚህ በኩል የተማሪ-ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ በተማሪዎች በኩልም ይህ ሁኔታ በሚገባ ታውቆ በስራ ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ በክፍል ውስጥ፣ በተለያዩ መጠለያዎች ስር፣በጥላ ስር ሆነው በአንድ ለአምስት ያጠናሉ፡፡ ይህ ሁሉ ድርጊት እንደቀድሞ በተናጥል የሚጓዙና የሚሰሩ ሳይሆን በጋራ ስለሚሰሩ ነው፡፡ከዚህም ውጭ ቤተ-መፃህፍትም የሚገቡበት አለ፡፡ከዚህም ውጭጪ በክፍል ውስጥም በግብረ-ሀይላቸው መርሀ-ግብር መሰረት የሚያጠኑ ናቸው፡፡ እኛ የምናስተምረው ተግባር እንግዲህ በንቃት ማስተማር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ይህም የምናስተማረው የኮርስ ባህሪ ይወስነናል፡፡ ሆኖም ግን በሁሉም ኮርሶች ውስጥ ይህን እንጠቀማለን፡፡ በአብዛኛው ግን እንጠቀማለን፡፡ይህ የትምህርት ግብረ-ሀይል* ከ2004 *ይልቅ* በ2005 *ይሻላል፡፡ በአጭሩ እየተሻሻለ መጥቷል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ዕጩ መምህራን ገና ወደዚህ ኮሌጅ እንደመጡ በዚህ በግብረ-ሀይል የመማር መርሀ-ግብር ይታቀፋሉ፡፡ አምስት ተማሪዎች በክፍል*

ውስት ይመረጣሉ። የተለያዩ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ። የስነ ስርዓት፣ የስርዓተ ፆታ፣ የተማሪዎች ነጥብ አሻሻይ ኮሚቴ የቋቋማሉ። ቲቶሪያል ይሰጣጣሉ፣ከ1ኛዓመት እስከ 3ኛ ዓመት ድረስ ይህ ሁኔታ ይታያል።

አንድ ዕጩ ሰልጣኝ ወደ መምህርነት እስከሚሰማራ ድረስ የሚወስዳቸው የአፋን ኦሮሞ ኮርሶች ምንድን ናቸው?1ኛ ዓመት ላይ የአፋን ኦሮሞ ስነ-ጽሁፍ ፣የአፋን ኦሮሞ ሰዋስው፣ በሳል ድርሰት አንድና ሁለት፣የአፋን ኦሮሞ ክሂሎች አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የያዘ ነው። ቀጥሎየአሮሞ አፋዊ ስነ-ቃል የሚል አለ። ይህ ስለአባባልና ፈሊጣዊ አነጋገር ፣እንቆቅልሽ፣ ተረት ይገኙበታል። ሌላም የአፋን ኦሮሞ ትኩረት፣ የአሮሞ ልቦለዶች የተካተቱበት ኮርሶችም አሉበት። በዚህ የአፋን ኦሮሞ ልቦለዶች ስር በአጭርና ረዥም ልቦለዶች ተብለው ይማሩታል። ይህም በንድፈሀሳብ-የተማሩትን ወደ ተግባር እንዲለውጡ የሚደረግበት ትምህርት ነው። በዚህ ውስጥ የተለያዩ በአፋን ኦሮሞ የተፃፉ ልቦለዶች ይዳሰሳሉ፤ይገመገማሉ፤ጥንካሬና ድክመቱን ለይተው ያሳያሉ። በሌላ በኩል Syrvey of ormo literature በሚባለው ኮርስ ውስጥ ደግሞ በአፋን ኦሮሞ የተፃፉ ታሪኮችን ማጤን ላይ ያተኩራል።ሶስተኛ ዓመት ላይ የሚሰጡ ኮርሶች ውስጥ የኦሮሞ በሳል ድርሰት ና ቋንቋና ህብረተሰብ የሚለውን ኮርስ ይወስዳሉ። ይህ አንድ ህብረተሰብ ከቋንቋ ጋራ አስተሳስሮ እንዲመለከቱ የሚያደርግ ነው። በአጠቃላይ በኮሌጅ ውስጥ ቆይታ ውስጥ ዕጩ መምህራኑ የሚወስዱት ኮርሶች እነዚህን ይመስላሉ።

ጥ. በአንድ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ስንት ዕጩ መምህራን ይመደባሉ?

እንደ አፋን ኦሮሞ በትኩረት (Focus) ጊዜ ይለያሉ። በዚህ በሚለዩበት ጊዜ ከ21-26 ይደርሳሉ። 1ኛዓመቶች 23 ሲሆኑ 2ኛ ዓመቶች ደግሞ 27 ሶስተኛ ዓመቶች 32 ናቸው። እነዚህ አፋን ኦሮሞን የሚማሩ ናቸው።ይህ በመሆኑ ለክፍል ቁጥጥር አመቺ ናቸው።ይህ እንግዲህ ተማሪዎች ገና ሲመረጡ በ70/30 ወደ ቋንቋ ይመጣሉ።እንደ ቋንቋ ስትሪም English Focusና አፋን ኦሮሞ Focusበመባል በሁለት ይከፈላሉ።

ጥ.የዕጩ መምህራን የትምህርት ክፍል ምደባ በምን ላይ የተመሰረተ ነው?

ገና በምርጫ ቦታ እያሉ ይመረጡና እዚህ ኮሌጅ ከመጡ በኂላ በፍላጎታቸው ምርጫ ይወሰናል።ይህ ፍላጎት ላይ የተመሰረተው የዲሞክራሲ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ለማለት ነው።

ጥ. በስልጠና ወቅት አፋን ኦሮሞ የሚሰጥበት አግባብ እንዴት ነው?

እኔ እስከአሁን ልገልፅ የሞከርኩት እንጂ ወደ መምህርነት እንዲያመሩ የሚያደርጉ የተለያዩ ኮርሶች አሉት፡፡ በተለይም "ፕራክቲከም" ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡የእንግሊዘኛ ቋንቋም በጋራ ኮርስነት ይሰጣል፡፡

ጥ.አፋን ኦሮሞን ስታተምሩ በክፍል ውስጥ የምትጠቀሙት ብልሃቶች ምንድን ናቸው?

በዘህ በኩል የምንጠቀመው ብልሃቶቻችን (Modular Approach) ነው፡፡ ከዚህ ውጪም የተለያዩ ተግባራት ተሰጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ቤተ-መፃህፍት ይገባሉ፣ የተለያዩ ቦታሄደው የተሰጣቸው ስራ ይሰራሉ፣ በሞጁሉ ላይ ደግሞ ትኩረት ስናደርግ ያንን ስራ የሚያጠናክሩ መልመጃ እንሰጣቸዋለን፡፡ በሞጁሉ ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነዚሂያ በሞጁሎቹ ውስጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተመስርተን ካስተማርን በኂላ ያንን ስራ የሚያጠናክሩ ፕሮጀክቶች እንሰጣቸዋለን ወይም አንድ ርዕስ አዘጋጅተን በዚያ ርዕስ ላይ ተመስርተው ከሰሩ በኂላ ለክፍል ጓደኞቻቸው ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ ይህን ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት የቡድን አደራጅ፣ ፀሐፊና አባላት ይኖራሉ፡፡ አሁን እንግዲህ ያ የቡድን አደራጅ ሁሉም አባላት ተሳትፈው ስራውን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ ይህም ሁሉም የቡድኑ አባላት ተራ በተራ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል፡፡ የቡድን ኂላፊው ሁሌ በቡድን ኂላፊነት መቀጠል የለበትም፡፡ ፕሮጀክቱን የክፍሉ የቡድን አባላት ሁሉ ተሳታፊ ሆነው እንዲማሩ እናደርጋለን፡፡ ከዚያም ውጭ የቤት ስራወይም ቴስቶች ልንሰጥ እንችላለን፡፡ ይህንንም ሰርተው ሲመጡ የሚፃፍ ከሆነ በግላቸው ሊጽፉ ይችላሉ ወይም መስክ ወጥተው በኮሌጁ አንድ ቦታ ወይም ለወደፊት ሊመደቡበት በሚችሉት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሄደው ያዩትንና የተገነዘቡትን ዘገባ ያቀርባሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ሁሉ ማንኛውም የክፍሉ የቡድን አባላት ተሳትፎ ውጪ በግልም ተግባራት እንደሚፈፀሙ እንገነዘባለን፡፡ ቡድን መምራት፣ፀሐፊ መሆን፣ እንደዚያ እንሄድበታለን፡፡

ጥ.ዕጩ መምህራኑ በቂ የስልጠና ግብዓት አግኝተዋል ብላችሁ የምታምኑት መቼ ነው?

...እሺ እውነት ነው ይህ የቡድን ስራ ውስጥ አንዱ በአንዱ ላይ ጥገኛ የመሆን ነገር ይታያል፡፡ ሁል ጊዜ በቡድን ውስጥ  እከሌ የተባለ ተማሪ ብቻ አቅራቢ ከሆነ ሌሎች የቡድኑ አባላት ተሳትፎ ስላላደረጉ ትምህርቱን በሚገባ ተሳተፉበት ለማለት አያስደፍርም፡፡ ስራውን ተራ በተራ የሚያቀርቡት ከሆነ ግን ሁሉንም እየተማሩ መሆናቸውን ስለምንረዳ ጥሩ ግብዓት ማግኘታቸውን እንረዳለን፡፡ ስራዎቹ ውስጥ የቡድን ብቻ ሳይሆን የግል ስራም ይገኝበታል፡፡ በግል ራ ውስጥም ካቀረቡ በኂላ ሁሉም ሐሳብ መስጠቱን እንረዳለን ማለት ነው፡፡ሰዎች ፊት ወጥተው መናገር ፣ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ በማድረግ ነው፡፡

የመማር-ማስተማር ዘዴ ውስጥ በአፋን ኦሮሞና በእንግሊዘኛ ቋንቋ አለ፡፡ እነዚህን ኮርሶች ይወስዳሉ፡፡ስለዚህ እነዚህን ኮርሶች ከወሰዱ በኂላ በተግባር እንዲለውጡ ከኮርሱ ጋራ የሚሄዱ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንሰጣቸዋለን፡፡ እነሱም እንደ አንድ መምህር ሆነው ማዳመጥና፣መናገርን መፃፍና ማንበብን እንዲያስተምሩ እናደርጋለን፡፡በዚህም ብቃታቸውን እንገመግማለን፡፡ ግምገማውንም የምናካሄደው የቡድን ስራና የግል ስራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ነው፡፡ ከዚያም የሴሚስተር ግማሽ ፈተና (Mid-exam)ና የማጠቃለያ ፈተና አለ፡፡ ይህንንም በብቃት ከተወጡ ብቁ ሆነዋል ማለት ነው፡፡

ጥ.ይህን የተማሪ-ተኮር ከመተግበር አንፃር ምን አይነት ችግሮች ያጋጥማችኂል?

በዚህ በኩል አንድን ስራ በምናከናውንበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ እንከን ሳይኖር እፈጽመዋለው ማለት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ዕጩ መምህራን የሚሰጣቸውን የጽሁፍ ስራ በሌሎች ዕጩዎች እያሰሩ የሚመጡበት ጊዜ አለ፡፡ ሆኖም እንዲህ ያለሁኔታ ሲከሰት የምንቆጣጠረው ወረቀቱን ለሚያቀርበው ዕጩ መምህራን የተለያዩ መስቀለኛ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንደርስባቸው እንደገና አዲስ ስራ እንዲሰሩ እናደርጋቸዋለን፡፡

## አባሪ አምስት፦በሮቤ መ/ ት/ ኮሌጅ የሶስተኛ ዓመት የአፋን ኦሮሞ ዕጩ መምህራን የቡድን ተኮር ውይይትና ውጤቱ

በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ውስጥ በአፋን ኦሮሞ ትምህርት ሁለት ዓመት ተምረው ሶስተኛውን ዓመት የጀመሩ ዕጩ መምህራን በአፋን ኦሮሞ መማር-ማስተማር አቀራረብ ዙሪያ እየተማሩበት የሚገኙ በመሆናቸውና ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ በማለት ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥ.በዚህ ኮሌጅ ቆይታችሁ ወቅት አፋን ኦሮሞን ስትማሩ የነበረው በምን ዓይነት አቀራረብ ነው?ተብለው ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ

ተ1፦አፋን ኦሮሞን በተለያዩ ብልሀቶች እየተማርን እንገኛለን፡፡ለምሳሌ በውይይት፣በጥያቄና መልስ፣በክርክርና አንዳንዴ ደግሞ ሊነሱ ይችላሉ ተብለው ለሚታሰቡ ሀሳቦች በጥልቀት በመነጋገር እየተማርን እንገኛለን፡፡በአጭሩ ተማሪን ማዕከል በሚያደርገው የተማሪ-ተኮር አቀራረብ እየተማርን እናገኛለን ማለት ነው፡፡ይህም ተማሪዎች ራሳችን በራሳችን ሀሳቦችን አደራጅተን ጥገኛ ሳንሆን ለሌሎች ጓደኞቻችን ትምህርት እየተሰጣጣን እውቀት የምንገበይበት መንገድ ነው ማለት ነው፡፡

ተ2.ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አሁን ባለንበት ደረጃ በሚገባ እየተተገበረ ነው ማለት ይቻላል፡፡ይህም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ መማራችንን የሚያለክተን የምንማረውን የትምህርት ርዕስ ለተማሪዎች ይሰጥና እያንዳንዳችን በዚያ ርዕስ ላይ በቡድን ሆነን በጥልቀት ተወያይተን ሀሳብ ካመነጨን በኋላ ከየቡድኑ ሀሳቦች ቀርበው በመጨረሻ መምህራን በተነሱት ሀሳቦች ዙሪያ ማጠቃለያ ይሰጣሉ፡፡ በዚህ መንገድ እየተማርን በመሆናችን ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተተግብሯል ማለት ነው፡፡

ተ.3.ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ወይም (Active learning) የምንለው የማስተማሪያ አቀራረብ በዚህ ኮሌጅ ውስጥ እየተተገበረ ነው፡፡አቀራረቡ መተግበሩ ደግሞ እኛም ከዚህ ኮሌጅ ስልጠና ጨርሰን በየትምህርት ቤት ስንመደብ እንድንተገብረው በማሰብ ነው፡፡አቀራረቡ የሚተገብርበት መንገድ ከይዘት ይዘት ሊለያይ ይችላል፡፡ከዚህ በመነሳት አንዳንዴ በቡድን የምንሰራው ስራ ሊኖር ይችላል፤በግል መስራት አለ፤ሌሎችን ብልሃቶች ልንጠቀም እንችላለን፡፡በዚህ አቀራረብ መማራችን ተማሪዎች ራሳቸው የዕውቀት ምንጭ እንደሆኑ በማሰብ ሀሳባችንን እንድንሰጥ እንደረጋለን፡፡ለሁሉም ይህን ይመስላል፡፡

ጥ.በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስትማሩ በትግበራው ውስጥ ያጋጠማችሁ ችግሮች ይኖር ይሆን?

ተ.3.በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስንማር የራሱ የሆኑ ጠንካራን ደካማ ጎኖች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ ከድክመቱ ብንጀምር ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎችን ሁሉ ተሳታፊ

አያደርግም። ምክንያቱም በቡድን ውይይትም ይሁን በሌሎች ዘዴዎች ስንማር ደፋሮችና ተናጋሪዎች ተጽእኖ ስለሚያደርሱ አይን-አፋሮችና ንግግር ላይ የሚያዘግሙት ሳይሳተፉበት ይቀራሉ። እነዚህ ተሳታፊ ያልሆኑት ተማሪዎች ባለመሳተፋቸው ከነሱ የሚጠበቀውን ሀሳቦች ማለት አጎደሉ ማለት ነው። ጠንካራ ጎኑ ደግሞ አብዛኛው ተማሪ በቡድን ውይይት ስለሚሳተፉ የንግግር ችሎታቸው እንዲያድግ ያደርጋል። በአጭሩ በኔ በኩል ጥንካሬና ደካማ ጎኑ ይህን ይመስላል። ተጨማሪ...

ተ.2.እንደኔ ይህ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ውስጥ ተሳትፎ ጥረት በሚያደርጉ ተማሪዎች ላይ ብቻ ትኩረት ይደረጋል። ለምሳሌ አንድ ቡድን ተግባር እንዲሰራው ሲደረግ በዚያ ቡድን ውስጥ የቡድኑ መሪ አወያይ፣ሀሳብ ሰጪ፣ ፀሀፊም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በሁሉም ቦታ ላይ በሚያደርገው ተሳትፎ ለራሱ ሰፊ ዕውቀት እንዲያገኝ ያደርገዋል ማለት ይቻላል። በስተመጨረሻም ስራውን ሪፖርት ለማድረግ ከዚያ ተማሪ የተሻለ አቅራቢ ስለማይኖርና የስራው ሁኔታ ውጤት ስለሚያስገኝ ቡድኑን ወክሎ ዘገባውን ያቀርባል። በዚህ መንገድ እንዲህ አይነት ተማሪ እውቀቱ እየጨመረ ሲሄድ ተሳታፊ ያልሆኑት ግን ባለመሳተፋቸው አዝጋሚ ሊሆኑ ይታያል። በዚህ አይነት ሁኔታ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ድክመት ያሳያል።

ጥ.የቤት ስራዎችና የቡድን ስራዎች በሚሰሩበት ወቅትስ የታዘባችሁት ነገር አለ?

ተ1ለምሳሌ አንድ ስራ ለአራት ወይም ለአምስት እንዲሰራ ሊሰጥ ይቸላል። ይህ ስራ በአንድነት ተቀምጦ በጋራ የመስራት ችግር በአንዳንድ ተማሪዎች ላይ አለ። የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዓላማ ተማሪዎች በቡድን ትብብር እየሰሩ አንዱ ለሌላው ያለውን እውቀት እንዲያዋጣና የድርሻውን ይወጣ የሚል ቢሆንም አንዳንዴ የተማሪዎች ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ይታያል። በቡድን ከመስራት ይልቅ በግል መስራትን የመምረጥ ሁኔታ አለ።የቤት ስራም ቢሆን በስምምነት የመስራት ሁኔታ አይስተዋልም። ሁሉም በአንድነት በስራው ላይ የመረባረብ ችግር አለ።ቡድን ስራ ላይም ሁሉም ተማሪዎች ካልተገኙ ሁለት ወይም ሶስቱ ተማሪዎች ሰርተው ምንም ነገር ያልሳተፉትን እንደሰሩ ተደርገው ስማቸው ተመዝግቦ ለመምህራን ይቀርባል ። ይህ እንግዲህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ውስጥ ያጋጠሙኝ ችግሮቸ ናቸው።

ጥ.በተማሪ-ተኮር አቀራብ ያለውን ፋይዳና እስከ 3ኛ ዓመት ድረስ አፋን ኦሮሞን ስትማሩበት ያስገኘላችሁ ጥቅሞች ምንድናቸው?

ተ.1.እሺ በአሁኑ ሰዓት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማሬ ያገኘሁት ለምሳሌ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሆኜ በዚህ አቀራረብ አልተማርኩም ነበር። በግሌ ተምሬ በግሌ አሳርሜ ውጤት አገኝ ነበር። እዚህ ኮሌጅ ከገባሁ ጊዜ ጀምሮ በግሌ ስሰራ የነበረው አካሄድ ተቀይሮ የኔ እውቀት ለሌሎች ጓደኞቼ የጓደኞቼ ሀሳብ ደግሞ ለእኔ በመሆኑ ይህን በህብረት ያገኘሁትን እውቀት በማጎልበት እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ።

ለምሳሌ እዚህ ኮሌጅ ከቦረና፣ከባሌ፣ከምዕራብ አርሲ፣ከአርሲ ተሰባስበን የመጣን ነን፡፡ በክፍል ትምህርቱ ሂደት ወቅት በቡድን ስንማማር ባህሎቻችንንም የምንለዋወጥበት ሁኔታ አለ፡፡በአፋን ኦሮሞ ትምህርት ወቅት የምንጠቀምባቸው ቃላት እንደ ዘዬ አይነቶችን ሳይቀሩ አካባቢያችን ስለሚያመለክቱ ይህንንም እንድናወቅ አግዞናል፡፡ ለምሳሌ እኔ ከቦረና ስለመጣሁ የባሌ ተማሪዎች እንዴት አይነት ቃላት እንደሚጠቀሙ ትምህርት አግኝቻለሁ፡፡እነሱም ከኔ ትምህርት አግኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የማናውቃቸውን ቃላት እንዲሁም ባህል እንድንለዋወጥ አግዞኛል ማለት እችላለሁ፡፡ተጨማሪ…

ተ2.ሌላው በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማሬ በግሌ ያገኘሁት ነገር በአራቱም የቋንቋ ክህሎት በሚገባ መሻሻሎች ማሳየት እንድችል አግዞኛል ማለት ይቻላል፡፡ለምሳሌ እርስ በርስ ስንደማመጥ የማዳመጥን ክህሎት አሳድጋለሁ፡፡ስናገር ንግግሬን አሻሽላለሁ፤በጽህፈት በኩልም እንደዚያው ነው፡፡በንባብም የተለያዩ የቤት ስራዎችን ለመስራት ከተለያዩ ጽሁፎች ከርዕሴ ጋራ የሚመሳሰሉትን ጽሁፎች በማንበብ አቀናጅቼ አቀርባለሁ፡፡የዚህ ሁሉ አካሄድ በኔ ላይ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለውጥ ስላመጣልኝ ነው፡፡በአጠቃላይ የሚያጋጥሙኝን ችግሮች በተለያየ ዘዴዎች ለመፍታት እንድችልና ከሌሎች ተማሪዎች ጋራ ትብብር ማድረግ እንድችል ያበቃኝ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማሬ የተገኘ ነው፡፡

ተ3.ከላይ ተ.1 እንደተናገረው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማሬ የተለያዩ ፋይዳዎችን አግኝቻለሁ፡፡ ከነዚህ ውስጥ የተለያዩ የዘዬ አነጋገሮችን ከተለያዩ ዞኖች አውቂያለሁ፣ለምሳሌ በቦረና አነጋገር ውስጥ አይነኬ የሆነው ቃል በባሌ ውስጥ ሁሉም የሚጠቀሙበት መደበኛ ቃል መሆኑን አስተምሮኛል፡፡በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪው እንደ አንድ የዕውቀት ምንጭ በመሆን በትምህርቱ ውስጥ ትኩረት ማግኘቱ እንደፈለግሁት የራሴን ሀሳብ ለመስጠት ረድቶኛል፡፡ ይህ ሁኔታ አቅጣጫዎች ሁሉ ወደ ተማሪዎች በመሆናቸው የኔ አስተዋፅኦ በመማር-ማተማሩ ሂደት ውስጥ ቦታ እንዳለው አመላክቶኛል፡፡

ጥ….እንግዲህ በዚህ ከተናገርካቸው ነጥቦች በመነሳት ለወደፊት በፕራክቲከም የመማር-ማስተማር ልምምድ ውስጥ በሚገባ ተማሪ-ተኮርን እተገብራለሁ ብለህ ታስባለህ?

ተ3.አዎ በሚገባ እተገብራለሁ፡፡

ጥ. ስለተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጥንካሬ በተወሰነ ደረጃ እስከአሁን ተነጋግረናል፡፡ እስቲ በመምህራን ዘንድ፣በሞጁል ዝግጅት፣ በተማሪዎች ተሳትፎ አጠቃላይ ሀሳብ ብትሰጡኝ?

ተ3. ይህ ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጥንካሬው እንዳለሆኖ ደካማ ጎኑ ረዥም ጊዜ መውሰዱ አንዱ ነው፡፡ይህም ተማሪዎች እንዲሰለቹ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

ተ.2.ሌላው በተ3 ላይ የምጨምረው አንድ መምህር በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምር አንድን ኮርስ እስከሚያጠናቅቅበት ድረስ አስተምራለሁ ብሎ አቅዶ

እቅዱን ሳያጠናቅቅ ለትምህርቱ የተጠው ጊዜ ተጠናቆ ሳያስተምር ሊያቋርጥ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ባለመማራችን ልንጎዳ እንችላለን፡፡ ወይም መምህራን መጀመሪያው ምዕራፍ አካባቢ በሚገባ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አስተምረውን የሴሚስተሩ መጨረሻ ሲደርስ በመምህር-ተኮር አቀራረብ ሲያስተምሩ ይስተዋላል፡፡ይህም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስንማር የጊዜ እጥረት እንደሚከሰት ያሳያል፡፡

…እሺ ተጨማሪ…

ተ1.ሁለቱ ጓደኞቼ ብዙዎቹን ነገሮች ገልፀዋል፡፡ እኔም የምጨምርበት ነገርና ትኩረት ማግኘት ያለበት ጉዳይ በውይይት፣በክርክር፣በጥያቄና መልስ ዘዴም እንማር ሊታሰብበት የሚገባው ነገር ይህ የጊዜ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ነው ወደ ኋላ ያስቀረን፡፡ ለምሳሌ በአንድ ሞጁል ስንማር በመጀመሪያዎቹ ምዕራፍ ላይ አብስለን፣አብስለን፣ አብስለን እንማርና በስተመጨረሻው ከዚህ ገጽ አስከዚህ ድረስ ተማሪዎች ያስተምሩ ተብለን ወደ እኛ ይገፋል፡፡ በዚህም ሁኔታ ያንን ትምህርት በሚገባ ሳንረዳው እናጠናቅቃለን፡፡ ይህ እንዳይከሰት የሞጁሉ ገጽ ማነስ ወይም የትምህረቱ ጊዜ እንዲጨመር ያስፈልጋል፡፡

ጥ.ከዚህ ሌላ የተማሪዎቹ ቁጥር ችግር ፈጥሮባችሁ ያውቃል?

ተ1.እንደኔ የተማሪዎች ቁጥር በክፍላችን ውስጥ ችግር አልፈጠረብኝም፡፡ነገር ግን በውይይት ሂደት ወቅት አንዱ ቡድን ሲወያይ ሌላውን ቡድን የመረበሽ ሁኔታ አለ ይህን ትንሽ እንደችግር አየዋለሁ፡፡

ጥ.አፋን ኦሮሞ እንድትማሩበት የተዘጋጁት ሞጁሎች ውስጥ ለስራው የሚሰጡት መመሪያዎችና ሌሎችም ችግሮች ካሉ ቢጠቀስተ?

ተ1.የተዘጋጁት ሞጁሎች ግልጽ በሆነ መንገድ ተዘጋጅተዋል፡፡ነገር ግን ለኛ ሀሳቡ ግልፅ ባልሆነበት ቦታ ላይ ከመምህሮቻችን ላይ ማብራሪያ እየጠየቅን እንረዳለን፡፡

ጥ….መምህራን እስካሉ ድረስ ችግር የለባችሁም ማለት ነው?

እሺ ስለሰጣችሁኝ መረጃ ደግሜ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

እኛም ስለመረጡን እናመሰግናለን፡፡

## *አባሪ ስድስት፡- በኪጸጠቴ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ*

*በ07/09/05 ዓ.ም ከ8፡00 ጀምሮ*

*…ከሰዓት በኋላ ስምንት ሰዓት ነው፡፡ የአፋን ኦሮሞ መምህር ከሆኑትና ሰባተኛ ክፍልን ከሚያስተምሩት ጋራ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ አተገባበር አስመልክቶ ቃለ-መጠይቅ አድርገናል፡፡በመጀመሪያ የስም ልውውጥ ካደረግን በኋላ ለምን እንደፈለኳቸው፣የቃለ-መጠይቁ ዓላማ ተገልፆ ወደ ጥያቄዎቹ አመራን፡፡*

ጥ.አፋን ኦሮሞን ለስንት ዓመት ያህል አስተምረዋል?

መ.አፋን ኦሮሞን ማስተማር የጀመርኩት በ1985 ጀምሮ ነው፡፡

ጥ.የመምህርነት ሙያ ስልጠና የወሰዱት መቼ ነው?

መ.ስልጠና የወሰድኩት በበባለፈው መንግስት ውስጥ ነው፡፡

ጥ.በባለፈው ስርዓት ውስጥ የመምህርነት ሙያ ስልጠና ወስደው በአዲሱ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ ለማስተማር ችግር አላጋጠምዎትም?

መ. "አዎ" ምንም ችግር አልፈጠረብኝም፡፡ምክንያቱም ቋንቋው የራሴ በመሆኑና አፌን የፈታሁበት በመሆኑ ውስጣዊ ደስታ እየተሰማኝ ሳስተምር ነበር፡፡በዚህም ለአፋን ኦሮሞ በአንደኛ ደረጃ የትምህርት አጀማመር ውስጥ የራሴ አስተዋፅኦ አለው ማለት ነው፡፡

ጥ.በአሁኑ ጊዜ አፋን ኦሮሞ በምን አይነት የማስተማር ዘዴ እየተሰጠ ይገኛል?

በአሁኑ ሰዓት እንደትምህርት ቤታችንና እንደመንግስትም ትኩረት ተደርጎበት ትምህርቱ የሚሰጠው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እያስተማርኩ እገኛለሁ፡፡ በዚህ ዘዴ ሳስተምር ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት በምናስተምረው ትምህርት ይዘት ላይ በቡድን ተወያይተው ዘገባ እንዲያቀርቡ አደርጋለሁ፡፡ ይህን ዘገባ ከተቀበልኳቸው በኋላ መስተካከል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ሀሳብ ሰጥቼ ትምህርቱን እያቀረብኩ እገኛለሁ፡፡ ይህን ግንዛቤ በመጨበጤ ያለምንም ችግር እየሰራሁበት እገኛለሁ፡፡

ጥ.በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር ለተማሪዎች የሚሰጠው ፋይዳ ምንድ ነው?

መ.ሁሉም ተማሪዎች ነገሮችን የመገንዘብ አቅም ደረጃቸው እኩል አይለም፡፡ ተማሪዎች በቡድን ሲደራጁ አንዱ በፍጥነት ነገሮችን የሚረዳ ሲሆን ሌላው በመካከለኛና በማዝገም ነገሮችን የሚረዱ ናቸው፡፡ በዚህ አቀራረብ ሲማሩ ግን የተማሪዎች እርስ በርስ መተጋገዝ፣ራሳቸውን መርዳት፣ እውቀት መሰጣጣት ሁኔታ ይታያል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የተማሪዎች ችሎታ ከፍ እንዲል ያደርጋል ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ ጥቅሙ ይህነው ማለት ይቻላል፡፡

ጥ.በዚህ ዘዴ ሲያስተምሩ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚጠቀሙበት የማተማር ብልሃት ምንድነው?

መ.እኔ አፋን ኦሮሞን የማስተምርበት ብለሃቶች የተለያዩ ናቸው። አንዳንዴ ተማሪዎችን ዘና በማድረግ፣ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ በተቀረፀው ትምህርት ላይ ብቻ ተወስኜ ሳይሆን በጥልቀት ከትምህርቱ ጋር ተያያዥ ከሆኑት ነገሮች ጋር አያያዤ በስነቃል፣ በተረት፣ በእንቆቅልሽ ጋር አያይዘው እንዲማሩ አደርጋለሁ። አንድ ቀን ትምህርቱን ካቀረብኩኝ ሌላ ቀን በመልመጃ ላይ ትኩረት አደርጋለሁ። ያንንም የመልመጃ ስራ አርማለሁ። ተማሪዎችም በዚህ አቀራረቤ ደስ እያላቸው ነው።

ጥ.ተማሪዎችዎ እንዲማማሩ የሚያደርጉበት ብልሃትስ ምንድነው?

መ.በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን በቡድን በቡድናቸው ውስጥ ተጠሪዎቻቸውን አስመርጥና ያ የተመረጠው ተጠሪ ለአባላቱ ቁጥር ይሰጣቸዋል። አንድ ቀን አንድ ተማሪ ተነስቶ ሐሳብ የሚሰጥ ከሆነ ሌላ ቀን ደግሞ ሌላው አባል ሐሳብ እንዲሰጥ አደርጋለሁ።በዚህ ዓይነት ትምህርቱን የምናቀርብበት ጊዜ አለ። በተጨማሪም አንዳንዴ እስቲ እናንተ አስተምሩ ብዬ ሀሳብ ሳቀርብላቸው በሚገባ ያስተምራሉ። እንደዚያ እንዲያስተምሩ ያደረኩበት ምክንያት በሰዎች ፊት ቀርበው ሀሳባቸውን ያለፍርሃት እንዲያቀርቡ ለማድረግ፣ በሰዎች ፊት የጽህፈት ችሎታቸውን ለማሳደግ እንዲችሉና የቃላት ዕውቀታቸው እንዲሰፋ ለማድረግ ነው።

ጥ.በክፍል ውስጥ ትገቡ የአንድ ክፍለ-ጊዜ እርዝማኔ 40 ደቂቃ ነው።ቨለመሆኑ ይህን 40 ደቂቃ እንዴት ተግባራዊ ያደርጋሉ? እኔ ይህን ያህል ደቂቃ ተጠቅሚያለሁ ብለህ አስበው ያውቃሉ?

መ.አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ አደርጋለሁ ብዬ አስባለሁ። በትምህርት ዕቅዴ ላይ እንደምተገብረው አድርጌ አዘጋጃለሁ። ለምሳሌ አንዳንዴ ትምህርት ቤታችን ከመማሪያ ሰዓት እየቀነሰ መጨረሻ ላይ መርሀ-ግብር ሊኖረው ይችላል። እንዲህ አይነት ጉዳዮች ሲያጋጥሙን የተሰጠኝን ሰዓት ላልተገብረው እችላለሁ እንጂ እተገብረዋለሁ። በሌላ በኩል በዕቅዴ መሰረት በቡድን በቡድናቸው ሪፖርት የሚያቀርቡበት ጊዜ ቡድኑም ብዛት ስላለው አምስትም ስድስትም ደቂቃ ተሰጥቷቸው እንዲማማሩ ይደረጋል። በመጨረሻም እነሱ ተናግረው ሲጨርሱ የቀረችዋን ጊዜ እኔም እናገርና አጠቃልላለሁ።በአጠቃላይ ከተመደበው ደቂቃዎች አብዛኛውን ለተማሪዎቸቹ እሰጣለሁ ማለት ነው።

ጥ.በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር ችግር የለበትም?

መ."አዎ"በተማሪዎች መካከል ፍቅር እንዲኖርና እርስ በርሳቸው እንዲተጋገዙ ያደርጋል። አንዱ አንዱን በማክበርና ያሉባቸውን ችግሮች ለመፍታትና መፍትሄ ለማፈላለግ ያስችላቸዋል። አንዱ ተማሪ ተነስቶ ሀሳብ ለመስጠት ቢፈልግ ብቻውን ሲሆን ሊፈራ ይችላል። ከቡድን ጓደኞቹ ጋራ ሲሆን ግን የፈለገውን ጥያቄ ወይም አስተያየት መስጠት

ይችላል፡፡ እስቲ አንተ ይህን ጠይቅ ወይም ጠይቂ እየተባባሉ በየተራ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ የሚሰሩት ስራዎች ሁሉ ግልፅ በግልፅ ነው የሚሆነው፡፡

ጥ.የተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ በብዛት መኖር በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ እንቅፋት ሆነውብዎት ያውቃሉ?

መ.በበኩሌ በክፍል ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ እንቅፋት ፈጥረውብኝ አያውቅም፡፡ ችግር የፈጠሩብኝ የመቀመጫና የአግዳሚዎች ሁኔታ ነው፡፡ አግዳሚዎችና መቀመጫዎች ከተማሪዎች ቁጥር ጋራ ስለማይመጣጠን የጥበት ሁኔታና ማስታሻ ለመውሰድ ያስቸግራል፡፡ እኛ በክፍል ውስጥ የምናስተምራቸው ተማሪዎች በቁጥር ከ50-70ይደርሳሉ፡፡ ለዚህም የመቀመጫዎቹ ሁኔታ ያስቸግራል፡፡

ጥ.በባለፈው የክፍል ምልከታ ወቅት የተመለከትኳቸው የተማሪዎች ቁጥር ከ50 አይበልጥም ነበር ይህን እንዴት አሰቡት?

"አዎ"ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ በክፍል ውስጥ አይገኙም፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ሙሉ ቁጥር ተገኝቶም አይታወቅም፡፡ በዚያ ቀን ቁጥራቸው ያነሰው እንጂ ሙበሙሉ የሚኖሩት ሰባ ተማሮወች ናቸው፡፡

ጥ.የአንድ ቡድን የአባላት መጠን ምን ያህል ነው?

መ.በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ቡድኖች ስድስት ይሆናል፡፡ እነዚህም አስር አባላት ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

ጥ.የአፋን ኦሮሞ የተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ስርጭት በበቂ ሁኔታ አለ ብለው ያስባሉ?

መ.በ2005 ውስጥ በበቂ ሁኔታ አለ ማለት ይቻላል፡፡

ጥ.የክፍል ውስጥ የቡድን አመሰራረታችሁ ቋሚ ነው ወይስ በየጊዜው የሚለዋወጥ ነው?

መ.የቡድን አመሰራረታችን  ይለዋወጣል፡፡ዓመቱን ሙሉ በመጀመሪያ በተመሰረተው አባላት ጋራ ከተጓዝን እነሱም ይናናቃሉ፡፡ ከሴቶችና ወንዶች እንዱም እንደ ተማሪዎቹ ችሎታ በማመሳጠር እንመሰርታል፡፡

ጥ.በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ የስራ ላይ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ?

መ.በኔ በኩል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቶኝ  አያውቅም፡፡ በተለይም በአፋን ኦሮሞ ማስተማር ዙሪያ ምንም ስልጠና አላገኘንም፡፡ ያው እንግዲህ መምህር ስለሆንን  በዚያው የቅድመ ስራ ስልጠና እያስተማርን እንገኛለን፡፡

ጥ.በአፋን ኦሮሞ መማር ማስተማር በኩል ያሉብኝ ጉድለቶች ሊኖሩብኝ ይችላሉ ይህንንም ጉድለት ለመቅረፍ ምን ቢደረግ የተሻለ ይሆናል ብለው ያስባሉ?

መ.በኮሌጅ መምህራን፣ በዘርፉ እውቀት ካላቸው ምሁራን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዙሪያ ስልጠና ባገኝ አሁን ከማስተምረው በላይ በሚገባ አስተምራለሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ እኔም ዕውቀቱን አግኝቼ ለተማሪዎቼም ሙሉ ዕውቀት እንዲያገኙ አደርጋለሁ፡፡

ጥ.በክፍል ውስጥ ተማሪዎቻችሁን የምትመዝኑበት ብልሃት ምንድነው?

በክፍል ውስጥ ተማሪዎቻችንን የምንመዝንበት የተከታታይ ምዘና ብልሃት ነው፡፡ ይህም በሙከራዎች፣ ፈተና፣የቤት ስራ፣የክፍል ስራዎች፣ የቡድን ስራዎችና ፕሮጀክቶች ይገኙበታል፡፡በዚህ ነው ተማሪዎቻችንን የምንመዝነው፡፡በነዚህ በተለያዩ መንገዶች ከመቶ እስ 60% ድረስ ጨርሰን በመጨረሻም 40%ቱን የማጠቃለያ ፈተና በመስጠት እንለያቸዋለን፡፡

ጥ.መቼነው በመምህርነት ሙያ የተመረቁት?

መ. በ1982 ነው፡፡

ጥ.በዚያ ጊዜ የደርግ ስርዓት የነበረበት የትምህርትና የስልጠናው ዓይነት ከአሁኑ ይለያል፡፡ ለመሆኑ እንዴት ነው የተማሪ-ተኮር አቀራረቡን ያለችግር የሚተገብሩት?

እኔ አፋን ኦሮሞን ያለምንም ችግር በተማሪ-ተኮር አቀራረብ እያስተማርኩ ቆይቻለሁ፡፡ ቋንቋው የራሴ በመሆኑና ደስ ብሎኝ ስለማስተምር ችግር ገጥሞኝ አያውቅም፡፡ በመጀመሪያ በአማርኛ ቋንቋ ስልጠና ወስጄ  በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥም የማስተምረው አማርኛን ነበር፡፡ በኋላ ላይም 7ኛና 8ኛ ክፍልን እንግሊዘኛ ቋንቋ ነበር የማተምረው፡፡ ይህን አፋን ኦሮሞን ስለምናገር እንጂ ስልጠና ወስጄበት አይደለም የማስተምርበት፡፡ ልክ አፋን ኦሮሞ በክልሉ ውስጥ እንደአፍ መፍቻ በትምህርትነት እንዲሰጥ ከተባለ በኋላ ደስ ብሎኝ ስላስተማርኩት በሁለቱ ስርዓት ውስጥ የነበረው የስልጠና ልዩነት ምንም ችግር አልሆነብኝም፡፡

ጥ.የምታስተምሩበት የመማሪያ ክፍል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር አመቺ ነው?

መ.ይህ በብሎኬት የተሰራው የመማሪያ ክፍል (እያሳዩኝ)7ኛ ክፍል የማስተምርበት በማሪያ ክፍል በጣም አመቺ ነው፡፡ ይህ ክፍል በመንግስት በጀት የተሰራ ነው፡፡ ስታንደርዱ ተጠብቆ የተሰራ ነው፡፡ ወንበሮቹም በተመሳሳይ መንገድ ለክፍሉ እንዲመቹ ተደርገው የተሰሩ ናቸው፡፡ ሌላው ለምሳሌ እዚያ ያለው ከጭቃ (ህዝብ አዋጥቶ የሰራውን እያመለከቱ) በዝናብ ጊዜ ጭቃ ይሆናል፣በበጋ ጊዜ ደግሞአቧራማ ነው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ውስጥ ለማስተማር በጣም ያስቸግራል፡፡

ጥ.አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስታስተምሩ ያጋጠማችሁ ችግሮች ካሉ ቢዘረዝሩልኝ?

መ.ለማስተማር ሁሌ መታደስ አስፈላጊ በመሆኑ በተወሰነ ደረጃ የማስተማር ብቃት ይጎድለኛ ይሆን ብዬ እሰጋለሁ፡፡ ሌላው ለብዙ ጊዜ የመማሪያ መጽሐፍት እጥረት ነበረብን ነገር ግን ከ2005 ዓ.ም በኋላ በመጠኑ ተቀርፏል፡፡ እንደገና የክፍለጊዜ ብዛት (Work

load)እንደተፈለገው ሊያሰራኝ አልቻለም። ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ድረስ አስተምራለሁ። እንግዲህ በዚህ የክፍለጊዜ ብዛት ምክንያት እንደፈለኩት ተማሪዎች በመማር-ማተማሩ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ አላደረኩም ብዬ አስባለሁ።

ጥ.ተማሪዎች በቡድናቸው ውስጥ በጋራ ሲሰሩ ብዙ ጊዜ ያጋጠምዎት ችግሮች ምንድን ናቸው?

መ.ተማሪዎች በዚህ ባሉበት የትምህርት ደረጃ ዕድሜያቸው አስራ ስድስት ነው።ትልቁ ዕድሜያቸው ማለት ነው።በዚህ ላይ የገጠር ልጆች ናቸው። አጠገባቸው የሚቀመጡትን ሴቶችና ጓደኞቻቸውን የማጫወት፣ እርስበርስ መላፋት ሁኔታ ይታያል። እንጂ በስራ ላይ ያገጠመኝ ችግ የለም።

ጥ.በመጨረሻ በተማሪ-ተኮር አተገባበር ዙሪያ ማለት የሚፈልጉት ነገር ካለ ቢገልፁ?

መ.ይህን ነገር በተረት ልጨርስልህ" ሁለት ሰዎች ፈረስ ተፈናጠው አብረው ይጓዛሉ። ብዙ ከሄዱ በኋላ ፈረሱ መሄድ አቃተውና ማዝገም ሲጀምር ከፊት የተሳፈረው ተፈናጣጩን እስቲ ፈረሷን ቼ በለው ይለዋል። ተፈናጣጩም አንተ ከፊት ስላለህ ለፈረሱ ጆሮ ትቀርባለህና ጠጋ ብለህ ቼ በለው አለው" ይባላል። ይህን የተናገርኩት ለስርዓተ-ትምህርቱ ቀረፃና የመማር-ማስተማር ችግሮች ፍተሻ የምታውቁት እናንተ ናችሁ። በዚህ ላይ የትምህተ ኋላፊዎችን ጋር ቅርበት ይኖራቸዋል። እናንተው ግለፁ እኛ ጋ የሚገኘውን ተናግሬያለሁ ብለው ዝም አሉ። በማስከተል እናንተ ጥሩ የትምህት ብቃት አላችሁ በተጣመመ ቦታ ላይ ከሌሎች አገሮች ጋር አነፃፃራችሁ ማስተካከል ስለምትችሉ ወደታችም መጥታችሁ እንደአሁኑ አነጋግራችሁን በጋራ ለተከሰቱት ችግሮች መፍትሄ መስጠት ይኖርብናል። በተለይም የመማር ዕድል እንኳን ባናገኝ ስልጠና የሚሰጡን አካላት ቢያስቡበት ለሙያዊ እገዛችን ወሳኝ ነው።

አመሰግናለሁ።

እኔም አመሰግናለሁ።

## *አባሪ ሰባት፡- በኪጽጠቴ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ከ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ጋራ የተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት*

**በ07/09/05 ዓ.ም ከ7፡00 ጀምሮ**

በመጀመሪያ ጥናት አቅራቢው ለምን ዓላማ ጥናት ለማድረግ እንዳስፈለገውና ተማሪዎቹ የሚሰጡት ምላሽ ለጥናት ዓላማ ስኬት ወሳኝ በመሆኑ ሁሉም ያለምንም ፍራቻና ጭንቀት ለተጠየቁት ጥያቄዎችና የሚያውቁትን ሀሳብ እንዲሰጡ ስምምነት ላይ ይደረሳል፡፡ከዚህ በኋላ በአጥኚው ሀሳብ አመንጪነት ጥያቄዎች በሚከተሉት መንገዶች ቀርበው ምልሽ ተገኝቷል፡፡

ጥ.በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ አፋን ኦሮሞን በምን አይነት የመማር-ማስተማር አቀራረብ እየተማራችሁ ነው?

መ.ተማሪ ሀ.እሺ ...እንደክፍላችን የአፋን ኦሮሞ መምህራችን ስለምንማረው ትምህርት አንዳንድ ነጥቦችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ከፃፉ በኋላ በቡድን በቡድን ሆነን እንድንወያይበት ያደርጉና የተሰጠንን ጉዳይ አብስለን እናቀርባለን፡፡

...በተጨማሪ...በተማሪ ለ.የኔ ሐሳብ እንደትምህርት ቤታችን አፋን ኦሮሞን ስንማር በመማሪያ መፃህፍ ውስጥ የቀረቡትን እንደመመሪያው እየተወያየንበት የምንማር ሲሆን ከመጽሐፉ ውጪም አንዳንድ የሚጠቅመን ጉዳይ ላይ እየተወያየን እንማራለን፡፡ ትምህርቱንም በልዩልዩ ዘዴዎች በመፍጠር 1ለ5 በሚባል ቡድን አመሰራረት እያስተማሩን ይገኛሉ ማለት ነው፡፡

ጥ.ይህ አንድ ለአምት የሚባል የትምህርት ግብረሐይል ፋይዳው ምንድነው?

መልስ በተማሪ ለ. የዚህ የትምር ግብረሐይል ፋይዳው በትምህርት ደከም የሚሉ ተማሪዎችን በዚያ ቡድን ውስጥ በማወያየት የመማር አቅማቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያደርግ ነው፡፡ሁሉም ተወያዮች በዚህ ሐሳብ ተስማምተዋል፡፡

ጥ.የአፋን ኦሮሞ መምህራችሁ ትምህርቱን ሲያቀርብላችሁ ምን አይነት ብልሃቶችን ይጠቀማሉ?

መልስ.በተማሪ መ.መምህራችን የአፋን ኦሮሞ ትምህርቱን ሲያቀርቡልን በመጀመሪያ እኛ እርስ በርሳችን እየተወያየን ያገኘነውን እውቀት እንድንከፋፈልና ከህብረተሰቡ የሰማነው እኛም በአጠቃላይ እውቀት ያገኘነውን እንድንከፋፈል ያደርጉናል፡፡

ተጨማሪ...በተማሪ ሐ.በቡድን በቡድናችን ካስቀመጡን በኋላ በተሰጠን ርዕስ ላይ እንድንወያይ ያደርጉንና ከቡድናችን ውስጥ ሪፖርት እናቀርባለን፡፡ከዚያም መምህሩ አጠቃላይ ሐሳብ ሰጥቶን ወደሚቀጥለው ስራ እንገዛለን፡፡ይሄ እንዲህ ነው እያልን እርስበርሳችን እንማማራለን ማለት ነው፡፡መምህሩም በስተመጨረሻው የሚሰጡን አስተያየት ስህተታችንን የሚያስተካክል ሀሳብ ይሰጡናል፡፡ስህተትም ከሌለብን ተጨማሪ ሀሳብ አክለው ያጠቃልላሉ፡፡

ጥ.አፋን ኦሮሞ ስትማሩ እንደተማሪነታችሁ ምን ተግባራትን ታከናውናላችሁ?

መ.በተማሪ መ.አብዛኛውን ጊዜ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተለያዩ መልመጃዎች ስለሚቀርቡ እኛ የምንጽፈውን ተግባራት እዚያው ውስጥ የተገለፀውን በአይናችን አይተን እንድናውቀው ነው፡፡መልመጃዎቹም የተለያዩ ናቸው፡፡በመጨረሻም መምህራችን ትምህርቱን ምን ያህል እንደተገነዘብን ጥያቄ ሲጠይቁን እንመልሳለን፡፡

…እስቲ ተጨማሪ ሀሳብ ያለው ሰው…

ተማሪሠ….ለምሳሌ የአፋን ኦሮሞ ትምህርት ንባብን ስንማር በዚህ ጊዜ ከምንባቡ ውስጥ በአካባቢያችን የሚነገሩ ቃላትን ፍቺ እንድንሰጥና አረፍተነገር እንድንሰራ ሲደረግ ተሳትፎ እናደርጋለን፡፡

ጥ.አፋን ኦሮሞን ስትማሩ የውስጣችሁን ሀሳብ ሳትደብቁ እንድትገልፁ የሚያደርጉ ጉዳዮች ይኖራሉ?

መ.በተማሪ.ሰ. በውስጣችን ያሰብነውን እንዳንናገር የሚያደርገን ተፅዕኖ ምንም የለብንም ፡፡ነገርግን ብንናገር መምህራችን ተሳሳትክ ይለኛል ብዬ ስለማስብ ለመናገር እፈራለሁ፡፡አንዳንዶቻችን ፍራቻም የሚሰማን አለን፡፡ያም ሆነ ይህ ሀሳብችን እንድናወጣ ይፈልጋሉ እንጂ ሌላ ተፅዕኖ የለብንም፡፡

…ተጨማሪ…ሁሉም በዚህ ሀሳብ በመስማማቸው ወደ ሌላ ጥያቄ…

ጥ.በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማራችሁ ያገኛችሁት ፋይዳ ምንድነው?

መ.በተማሪ .ሰ….በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በመማራችን ያገኘነው ፋይዳ ራስንና ቤተሰብን በመለወጥ ወደ አገር እድገትም ያመራል ማለት ነው፡፡በአጭሩ የራሳችንና የአገሪቱንም ችግሮች በዚህ መንገድ እንድንፈታ እገዛ ያደርግናል ማለት ነው፡፡ቋንቋ ማለት የአንድ ማህበረሰብ ማንነት ገላጭ እንደመሆኑ መጠንና አንድን አገር የምናሳድግበት መንገድ በመሆኑ የበለጠ በቋንቋችን እንድንጠቀምና የአገሪቱን ችግሮች የምንፈታበት ዘዴን ስለምናገኝበት ፋይዳው ከፍተኛነው ማለት ይቻላል፡፡

ጥ.በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ የሚገኙት የተማሪ ቡድኖች በቁጥር ስንት ይሆናሉ?አባላቱስ ስንት ናቸው?

መ.በተማሪ .ሀ. እንደመማሪያ ክፍላችን ቡድኖቹ ዘጠኝ ሲሆኑ በእነዚህ ቡድኖች ውስጥ ያሉት የአባላት ብዛት ከሰብሳቢው ጋር ስድስት ናቸው፡፡

ጥ. የመማሪያ ክፍላችሁ አፋን ኦሮሞን እንድትማሩበት አመቺ ናቸው?

መ.በተማሪለ. የምንማርበት የመማሪያ ክፍል አመቺ ነው፡፡ንጽህናውም በሚገባ የተጠበቀ ነው፡፡የቤቶቹ አሰራር በሁለት መንገድ ነው፡፡አንዱ የጭቃ ሲሆን ሌላው የብሎኬት

ነው፡፡በብሎኬቱ ውስጥ ስንማር በጣም ይመቻል፤ነገር ግን የጭቃው የክፍሉ ጥበትና አቧራማ ወለል በመሆኑ አመቺ አይደለም፡፡

…ሁሉም በዚህ ሀሳብ ተስማምተዋል…

ጥ.በአጠቃላይ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በምትማሩበት ጊዜ ያጋጠማችሁ ችግሮች ምንድናቸው?

መ.በተማሪ ሀ…ተማሪዎች በቡድን ውይይት ወቅት አንዱ አንዱን የመናቅ፣አንዳንዶች ደግሞ ካለ እኔ ማንም አይናገር በማለት ጫና ማድረግ፣አንዳንዶች የሰሩትን ስራ ሪፖርት ለማድረግ ያለመፈለግ፣የቤት ስራና የተለያዩ ስራዎችን ለመሳተፍ ያለመፈለግ ነገር ግን ስማቸውን ከሰሩት ተማሪዎች ጋር እንዲፃፍ ማስገደድ እንደችግር የሚያጋጥሙን ነጥቦች ናቸው፡፡

*ሁሉም በዚህ ተስማምተዋል*

ጥ.በአፋን መማሪያ የሆነው የተማሪው መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለመማር አመቺ ነው?

መ.በተማሪ ሐ. "አዎ" በሚገባ የተዘጋጀ ነው፡፤ነገር ግን ስለተለያዩ ነገሮች እውቀት ቢሰጠንም ስለቋንቋው የሚያስተምረው በጣም ጥቂት ነው፡፡በፈተና ላይ የሚወጡት ጥያቄዎች በቋንቋ ላይ ትኩረት ስለሚያርጉ በመማሪያ መፃህፍት ውስጥም ይሄው ቢካተት መልካም ነው፡፡

…የሁሉም ሃሳብ ነው…

ጥ.አፋን ኦሮሞን ስትማሩ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ውስጥ በሚገባ ተሳትፈናል ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ?

መ.በተማሪ ረ.በቋንቋዬ ስለምማር በይይት በተሰጠኝ ድርሻ ሁሉ ውስጥ ያለፍርሃት እየተሳተፍኩ እገኛለሁ፡፡

ተጨማሪ በተማሪ ሐ.አዎ እየተሳተፍን እንገኛለን ቋንቋችን ስለሆነ የሚያግደን ነገር ስሌለ በሚገባ እንሳተፋለን፡፡

ተማሪ ሀ.በበኩሉ በአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ውስትየቀረቡት መልመጃዎች የሚወጡት ከቀረቡት ምንባባት ውስጥ በመሆኑ ምንባቡን በሚገባ አንብቤ ከውስጡ የወጡትን ጥያቄዎች በሚገባ እሰራለሁ፡፡ በአጠቃላይ የምማርበትም፣ የምናገርበትና የምጽፍበት ቋንቋዬ በመሆኑ በሚገባ እየተሳተፍኩ እየተማርኩ እገኛለሁ፡፡

…እሺ…

ጥ.በአጠቃላይ አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስትማሩ በመማር -ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚታዩ ችግሮች ካሉ ብታብራሩ?

መ.በተማሪ ረ. አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሲሰጥ ያጋጠሙን ችግሮች እንደ እኔ…ማጠቃለያ ሲሰጥ እኛ ያልተማርነውን አካተው ያጠቃልላሉ፡፡ በመሆኑም እኛ ያልተማርነውን ከማጠቃለል እኛ ካወቅንው ወይም ከተወያየንበት በኋላ ቢያጠቃልሉ የተሻለ ይሆናል፡፡ በተረፈ ምንም ችግር የለም፡፡ እሺ ስለሰጣችሁኝ ምላሽ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፡፡ እኛም እናመግናለን፡፡

## ምልከታ ስምንት፡-ምልከታ የተደረገባቸው የመማሪያ ክፍልና ተማሪዎች ናሙና




የሐውሾ ትምህርት ቤት 7ኛሀ መማሪያ ክፍልና ተማሪዎች




የዜይበላ ትምህርት ቤት 7ኛለ መማሪያ ክፍልና ተማሪዎች




የአሊቢራ ትምህርት ቤት 7ኛለ መማሪያ ክፍልና ተማሪዎች



**የኪጵጠቴ ትምህርት ቤት 7ኛሀ መማሪያ ክፍልና ተማሪዎች**



**የ3ኛ ዓመት የአፋን ኦሮሞ ዕጩ መምህራንና የመማሪያ ክፍላቸው**

## *አባሪ ዘጠኝ ፡-በዜይበላ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ- መጠይቅ*

1.አፋን ኦሮሞን ለስንት ዓመት ያህል አስተምረዋል?

2. የመምህርነት ሙያ ስልጠና የወሰዱት መቼ ነው?

3. በባለፈው ስርዓት ውስጥ የመምህርነት ሙያ ስልጠና ወስደው በአዲሱ የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ ለማስተማር ችግር አላጋጠምዎትም?

4. በአሁኑ ጊዜ አፋን ኦሮሞ በምን አይነት የማስተማር ዘዴ እየተሰጠ ይገኛል?

5. በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ማስተማር ለተማሪዎች የሚሰጠው ፋይዳ ምንድ ነው?

6.በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን ሲያስተምሩ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚጠቀሙበት የማተማር ብልሃት ምንድነው?

7.ተማሪዎችዎ እንዲማማሩ የሚያደርጉበት የተማሪ-ተኮር ብልሃትስ ምንድነው?

8. በክፍል ውስጥ ስትገቡ የአንድ ክፍለ-ጊዜ እርዝማኔ 40 ደቂቃ ነው፡፡ለመሆኑ ይህን 40 ደቂቃ እንዴት ተግባራዊ ያደርጋሉ?እኔ ይህን ያህል ደቂቃ ተጠቅሚያለሁ ብለው አስበው ያውቃሉ?

9. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን ማስተማር ችግር የለበትም?

10.የተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ በብዛት መኖር በመማር-ማስተማሩ ሂደት ላይ እንቅፋት ሆነውብዎት ያውቃሉ?

11. የአንድ ቡድን የአባላት መጠን ምን ያህል ነው?

12. የአፋን ኦሮሞ የተማሪው የመማሪያ መጽሐፍ ስርጭት በበቂ ሁኔታ አለ ብለው ያስባሉ?

13. የክፍል ውስጥ የቡድን አመሰራረታችሁ ቋሚ ነው ወይስ በየጊዜው የሚለዋወጥ ነው?

14. በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ዙሪያ የስራ ላይ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ?

15. በአፋን ኦሮሞ መማር ማስተማር በኩል ያሉብኝ ጉድለቶች ሊኖሩ ይችላሉ ይህንንም ጉድለት ለመቅረፍ ምን ቢደረግ የተሻለ ይሆናል ብለው ያስባሉ?

16. በክፍል ውስጥ ተማሪዎቻችሁን የምትመዝኑበት ብልሃት ምንድነው?

17. የምታስተምሩበት የመማሪያ ክፍል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር አመቺ ነው?

18.አፋን ኦሮሞን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስታስተምሩ ያጋጠማችሁ ችግሮች ካሉ ቢዘረዝሩልኝ?

19. በመጨረሻ በተማሪ-ተኮር አተገባበር ዙሪያ ማለት የሚፈልጉት ነገር ካለ ቢገልፁ?

## *አባሪ አስር፦በሐውሾ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት የአፋን ኦሮሞ መምህር ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ*

## ከ3፡30-4፡10

በመጀመሪያ የስም ትውውቅ ካደረግን በኂላ ለምን እንደተገናኘንና የጥናቱ ዓላማና እሳቸው የሚሰጡኝ እውነተኛ ምላሽ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ወሳኝ በመሆኑ ለምጠይቃቸው ጥቄዎች እውነተኛ ምላሽ እንደሚሰጡኝ በመግለፅ ወደ ጥያቄዎቹ ገባሁ፡፡

ስም በየነ ቀልቤሳ፣የትምህርት ደረጃ አፋን ኦሮሞ በማስተማር ዲፕሎማ፣የአገልግሎት ዘመን 3ዓመት፣አሁን የያዙት ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜ 26፣

ጥ.አፋን ኦሮሞን ለስንት ዓመት አስተማሩ?ስንተኛ ክፍሎችንስ እያስተማሩ ይገኛሉ?

መ.የማስተምረው ከ5ኛ-8ኛ ክፍሎች ሲሆን በሳምንት የማስተምረው 26 ክፍለጊዜ ነው፡፡

ጥ.አፋን ኦሮሞን ለምን ያህል ዓመት አስተምረዋል?

መ.ከኮሌጅ ከተመረቅኩኝ 3ዓመቴ በመሆኑ ያስተማርኩትም ሶስት ዓመት ነው፡፡

ጥ.አፋን ኦሮሞን ስታስተምር የትኛው የማስተማር አቀራረብ ትጠቀማለህ?

መ.በኮሌጅ ውስጥ ተምሬ በወጣሁት መሰረት የማስተምረው በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ነው፡፡

ጥ.በተማሪ-ተኮር አቀራረብ አፋን ኦሮሞን የሚያስተምሩ ከሆነ የተማሪ-ተኮሩ ለተማሪዎች የሚሰጠው ጥቅም ምንድንነው ብለው ያስባሉ?

መ.ተማሪዎች ራሳቸው በራሳቸው በመተማመን እንዲማማሩ ያደርጋል፣የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል፡፡የመፃፍ፣የማንበብ፣የመናገርና የማዳመጥ ችሎታቸው ሁሉ እንዲያድግ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡በአጠቃላይ አራቱንም የቋንቋ ክህሎቶች ጊዜ እንዲያሳድጉ ያግዛቸዋል፡፡

ጥ.ይህ ለውጥ መምጣቱን ገምግማችሁ ደርሳችሁበታል ማለት ነው?መ.አዎ

ጥ.የተማሪ-ተኮርን በክፍል ውስጥ የሚተገብሩ ከሆነ የሚጠቀሙበት የማስተማር ዘዴ ምን ዓይነቶች ናቸው?

መ.ብዙ ጊዜ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እንዲወያዩ አድርገን ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡በተጨማሪም በክርክርና ውጭ ወጥተው ታላላቆችን ጠይቀው ዘገባም የሚያቀርቡበትም ዘዴ አለ፡፡በተማሪዎቹ የአፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም አንዳንድ ቦታ ላይ በዚህ ዘዴ አስተምሩ የሚል ጥቆማ ተጽፎ ይገኛል፡፡በዚያ መሰረት በክፍል ውስጥ ዘዴዎችን እየተጠቀምኩ እገኛለሁ፡፡

ጥ.በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር እገዛ ያደረገልዎት ተቋም ወይም ድርጅት ካሉ እነማን ናቸው?

መ.አንዱ በኮሌጅ ደረጃ የተማርኩት ነው፡ሌላው አንድ ኢማጂናይዴ የሚል ድርጅት በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብና በተከታታይ ምዘና ዙሪያ ስልጠና ሰጥቶናል፡፡

ጥ.ከዚህ የስራ ላይ ስልጠና ጥቅም አገኝተዋል?

መ.በሚገባ ጥቅም አግኝቻለሁ፣ያገኘሁትን ጥቅሞች በተማሪዎቼ ላይ እየተገበርኩ ነው፡፡

ጥ.በክፍል ውስጥ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ከእርስዎና ከተማሪዎችዎ  ማነው ብዙውን ሰዓት በንግግር የሚያሳልፈው?

መ.ያው እኔ ነኝ፡ለተምሪዎች አንዳንድ ነገሮችን የግድ ማብራራት ስላለብኝ እኔ ረዥም ሰዓት እፈጃለሁ፡፡

ጥ.በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትምህርት ሲቀርብ መምህሩ ቁጥብ ነው የሚባለውስ?

መ.እንደዚያ ቢባልም ያው እኔማስረዳት ስላለብኝ እየተጠቀምኩ ነው፡፡

ጥ.በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ሁሌ ሲያስተምሩ ሲያጋጥሙ የነበሩት ችግሮች ምንድናቸው?

መ.ከችግሮቹ ውስጥ ተማሪዎች ለመምህራን ጥሩ አመለካከት የላቸውም፡፡ምክንያቱም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ስናስተማር ሁሌ በራሳቸው ሀሳብ እንዲያመነጩ፣ እንዲወያዩ፣ ቅድሚያ እንዲናገሩ ስለምናደርግ መምህራን እውቀት እንደሌላቸው አድርገው የመቁጠር ሁኔታ ይታያል፡፡የተማሪ-ቤተሰብ በበኩላቸው ልጆቻችንን አንድ ላይ በማጎር ታያላችሁ የሚል ሀሳብ አለ፡፡ይህ ሁኔታ እንደችግር አድርጌ ወስጄዋለሁ፡፡ሌላው ደግሞ በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች መብዛት የሁሉንም ተማሪዎች ሀሳብ ሳንቀበል ለትምህርቱ የተዘጋጀው

ክፍለጊዜ ይጠናቀቃል፡፡የማቴሪያል አቅርቦት ችግርም አለ፡፡የማሪው መማሪያ መፃህፍት በበቂ ሁኔታ ቢኖርም የመምህሩ መምሪያና የትምህርቱ መርሀ-ትምህርት የለም፡፡አንዳንድ በትምህርቱ ይዘቶች ውስጥ የሚያጋጥሙንን ችግሮች ለመፍታት ስንፈልግ ችግር ያጋጥመናል፡፡እኔ አሁን ሀያ ስድት ክፍለጊዜ በሳምንት አስተምራለሁ፣በቀን ከአምስት ክፍለጊዝ በላይ ማለት ነው፡፡ከ5-8ኛ ክፍል አስተምራለሁ ስለዚህ በተፈለገው መጠኝ ተማሪዎችን አስተምሪያለሁ ለማለት እቸገራለሁ፡፡በአጭሩ እንዲህ አይነት ችግሮች ናቸው የሚያጋጥሙን፡፡

ጥ.በትምህርት ቤታችሁ እርስዎ የሚያስተምሩትን ጨምሮ ስንት ክፍል ነው ያለው?

መ.5ኛ 2፣6ኛ 2፣7ኛ2፣8ኛ2 ናቸው ሁሉም ክፍሎች ሁለት ሁለት ማለት ነው፡፡

ጥ.በመማሪያ ክፍልዎ ውስጥ የሚገኙት የተማሪዎች ቡድን ቁጥር ስንት ነው?እንዚህንም ቡድኖች እንዴት አደራጇቸው?ቡድኑስ በቋሚነት የሚቀጥሉ ናቸው?

መ.በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚገኙት የተማሪዎች ቁጥር ስልሳ በመሆናቸው ለስራችን አስሩን በአንድ ቡድን ስላደራጀናቸው ስድስት ቡድኖች አሉ ማለት ነው፡፡የነዚህ ቡድኖች አንድ ለአምስት በሚባል አደረጃጀት የተመሰረቱ ናቸው፡፤ይህ ማለት ጎበዝ ተማሪዎች ከሌሎች ጋራ በማሰባጠር እንዲማማሩ ሁኔታዎችን እናመቻቻለን፡፡የቡድኑ አመሰራረት በቋሚነት ነው፡፡ነገር ግን በየአመቱ ይቀያየራል፡፡በስብጥር ደረጃ ሴቶችን ከወንዶች ለማመጣጠን ተችሏል፡፡

ጥ.ይህ የቡድን አመሰራረቱ አመቱን ሁሉ በቋሚነት መኖር በተማሪዎች መካከል ጎበዙ ብቻ እንዲናገር ደከማ የምንላቸው ደግሞ ጥገኛ የመሆን ሁኔታን አይፈጥርም?

መ.ይህ ሁኔታ ይፈጠራል፤በአመትም የሚቀያየረው ለዚህ ነው፡፡ያልከው ሁኔታ እንዳይፈጠር ግን አለ፡፡

ጥ.በዚህ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ደረጃ ስልጠና ወስጃለሁ ብለዋል እስቲ በምን ሁኔታ ላይ ስልጠና ወሰዱ?

መ.በቡድን ውይይት አመሰራረት ላይ፣በተማሪ-ተኮርና በተከታታይ ምዘና ላይ ስልጠና ወስጃለሁ፡፡

ጥ.የተዘጋጁት የተማሪው አፋን ኦሮሞ የመማሪያ መፃህፍት በበቂ ሁኔታ አሉ?

መ.በበቂ ሁኔታ በመዳረሳቸው ለያንዳንዱ ተማሪ ተሰጥቷል፡፡

ጥ.እነዚህ የመማሪያ መፃህፍት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ለማስተማር አመቺ ናቸው?

መ.አንዳንድ ቦታ ላይ ተማሪዎች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ትዕዛዝ የሚሰጥ ቦታ አለ፡፡አንዳንድ ቦታ ላይ ግን ምንም ግልጽ ያልሆነ ትዕዛዛት የሚታይበት ሁኔታ አለ፡፡በአጭሩ ሙሉ በሙሉ አመቺነው ማለት አይቻልም፡፡መመሪያ የለውም፡፡

ጥ.ተማሪዎችን የምትገመግሙበት የምዘና ሁኔታ ምን ይመስላል ?

መ.ምዘና በተከታታይ ምዘና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ከክፍል ተሳትፎ ይጀምራል፣የቡድን ስራዎች ፣የቤት ስራዎች ወዘተ ተማሪዎች ከፈተና ውጪ የሚመዘኑበት ስልት ነው፡፡ፈተና ከመቶው 30 %ብቻ ነው፡፡70%ቱ ልዩ ልዩ የተማሪዎች ተሳትፎዎች ላይ ያተኩራል፡፡እኛም በዚህ እየተጠቀምን ነው፡፡

ጥ.አጠቃላይ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዙሪያ ያሉትን ጠናካራና ደካማ ጎኖች አብራሩ?

መ.ተማሪዎች በራሳቸው ተማምነው እንዲማሩ፣የፈጠራ ጽሁፎን ለመፃፍ ያስችላቸዋል፣ለመምህራን ደግሞ ከስራ ጫና ያርፋል፡፡

እንደ ድክመት ደግሞ የሚነበቡ ማቴሪያሎች ችግር፣ስልጠናው በየጊዜው ቢሰጥ፣የሚሰጡት ስልጠናዎች ላይ የሚሳተፉት እኛን በቀጥታ ማሳተፍ እየተቻለ ተያያዥ ያልሆኑ ሰዎች ስልጠና የመውሰድ ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡ይህ ሁኔታ መሻሻል ይኖርበታል፡፡

እሺ አመስግናለሁ

እኔም አመሰግናለሁ

## አባሪ አስራ አንድ፡- ለባሌ ዞን የመምህራን ልማት ሃላፊ የቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የአፋን ኦሮሞ ትርጉም፣

**Gaaffii Afaanii I/G/Misooma Barsisota/Godina Baaleetiif Dhihaate.**

1..Barumsa Ittiin Eebbiffamte-------------

2, Bara Tajaajila Keetii-----------------------

3.Godina Balee Keessa M/b/sd/tokkoffaa Meeqaatuu Jira?

4.Adeemsi Baruu Barsiisuu Haala Kamiin Kennamaa jira?

5.Ogummaa Barsiisootaa Guddisuuf Akka Goddina keessanitti Maaltuu Hojjatamaa Jira?

6.Barsiisoota Go/keessaniitiif Leenjii Kennitanii Beektani?Yoo keenniitanii jiraattan Maalirratti?

7.Barsiisoota Sadarkaa tokkooffaatiif Addatti Leenjiin Kennameefi Jiraa?

8.Barsiisoonni Afaan Oromo Mala Barataa Giddu Galeeffateen Akka Barsiisan leenjii'in Hojiirraa Kanameefiijira?Yoo Keennameef eessati? Mataduree Maaliirratti?

9. Mala Barataa Giddu Galeeffateen Barsiisuun Barattootaaf Faayidaa Maal Kenna?

11. Akka I/G/W/B/G/Baaleetti Mala Barataa Giddu Galeeffatee Akka Barsiisoonni hundu Hojiirra Olchan Gargaartanii Beektuu?

12. Akka I/G/W/B/G/Baaleetti Mala Barataa Giddu Galeeffatee kana Daree keessatti Hojiirra Olchuu isaanii Akkamitti Hordoftu?

14.GodinaKeessan Keessatti Barsiionni Afaan Oromo Mala Barataa Giddu Galeeffatee yoo Hojiirra Olchuu Baatan Sababii isaa Maal sitti Fakkaata?

15.Kitaaboonni Afaan Oromoo Barattota Mala Barataa Giddu Galeeffateen Barachuuf Mija'aa Sitti Fakkaata?

16. Godina Keessan Keessatti Barsiionni Afaan Oromo Barsiisan Toftaan Madaallii isaanii Maali?

## *አባሪ አስራ ሁለት፡-የ7ኛ ክፍል የተማሪው አፋን ኦሮሞ መማሪያ መጽሐፍ ግምገማ*

የ7ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ መማሪያ የተማሪው መጽሐፍ ከተማሪ-ተኮር አቀራረብ አንፃር የተደረገ ፍተሻ፡፡

ክፍል 7ኛ፣ የህትመት ዘመን፡-1996፣አዘጋጅ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣የምዕራፉ ርዕሶች ብዛት 24፣የያዘው ገጽ ብዛት 107፤

**የመልመጃዎቹ ዓይነት**

***ምዕራፍ አንድ***፡-የምንባቡ ርዕስ ሀንዱራ /Handhuuraa/ (ገጽ፣1) የሚል ሲሆን ለቀረበው ምንባብ አራት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በመልመጃ አንድ ስር ተጠይቀዋል፡፡እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው እንዲመልሱ የሚጋብዙ ናቸው፡፡ መልመጃ ሁለት፣ሶስት፣አራት፣ አምስት እና ስድስት(ገጽ፣1-3) ደግሞ በግል የሚሰሩ ተግባራት ሲሆኑ፤መልመጃ ሰባት(ገጽ፣4) እንደገና ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው የሚመልሱት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በምዕራፉ ስር የቀረቡት መልመጃዎች ሲገመገሙ ከቡድን ውይይት ይልቅ ወደ ግላዊ ትግበራ የሚያደሉ ናቸው፡፡፡

***ምዕራፍ ሁለት***፡-የምንባቡ ርዕስ ጉቺ/Guchii/(ገጽ፣5)የሚል ነው፡፡ለቀረበው ምንባብ ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው በቃል የሚመልሱት በመልመጃ አንድ ስር ቀርቧል፡፡በሌላ በኩል በመልመጃ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ሰባት እና ስምንት በግል የሚሰሩ ጥያቄዎች ናቸው (ገጽ፣6-9)፡፡በክሂል  ደረጃ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የንግግር እና የጽህፈት ክሂሎች ትኩረት ያገኙ ናቸው ፡፡

***ምዕራፍ ሶስት***፡-የምንባቡ ርዕስ እድሜ/Umrii/ (ገጽ፣10) ሲሆን በምዕራፉ ስር አስር መልመጃዎች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ መልመጃ ስምንት(ገጽ፣13) ብቻ ለውይይት የሚጋብዝ ትዕዛዝ ያለበት ሲሆን ሌሎች ዘጠኙ መልመጃዎች ግን በግል የሚሰሩ ተግባራት የያዙ ናቸው፡፡

***ምዕራፍ አራት***፡-የምንባቡ ርዕስ በቂ ውሃ መጠጣት/Bishaan Gahaa Dhuguu/ (ገጽ፣15-19) በሚል የቀረበ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስር ሰባት መልመጃዎች የሚገኙ ሲሆን ሁሉም ለግል ስራ በቀረቡ ትዕዛዛት የሚመሩ ናቸው፡፡

***ምዕራፍ አምስት***፡-የምንባቡ ርዕስ ኤድስ/Eedsii/(ገጽ፣20-21)የሚል ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ስር ዘጠኝ ምዕራፎች ይገኛሉ፡፡ከነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ስምንቱ በግል የሚተገበሩ ሲሆኑ ምእራፍ ዘጠኝ (ገጽ፣24)ላይ ብቻ ተማሪዎች ተወያይተው የሚመልሱት ሶስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም ጥያቄዎች በጥንድ ይሁን በቡድን

ወይም ከሙሉው ክፍል ባልተገለፀበት ከማን ጋራ እንደሚወያዩ ባለመገለፁ ትዕዛዙ ችግር አለበት ማለት ይቻላል፡፡

**ምዕራፍ ስድስት**፡-የምንባቡ ርዕስ ዝሆን ሰላምታ ይጠያየቃል /Arbilee Nagaa Walgaafata)/ (ገጽ፣25-29)በዚህ ምዕራፍ ስር ዘጠኝ መልመጃዎች ይገኛሉ፡፡ከዘጠኙ መልመጃዎች ውስጥ (ገጽ25) መልመጃ አንድ የቅድመ ንባብ ተግባራት ነው፡፡ይህም ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ ስለ ዝሆን የሚታወቁትን ነገሮች መናገር ነው፡፡ሌሎች መልመጃዎች መልመጃ ሁለት፣ሶስት፣አራት፣የግል ስራዎች ናቸው፡፡ምዕራፍ አምስት ግን ስለጥገኛ ምዕላዶች እርስ በርስ እንዲረዳዱና በጋራ እንዲሰሩ ይፈቅዳል፡፡መልመጃ ስድስት ደግሞ በግል የሚሰራ ተግባራት ይገኙበታል፡፡መልመጃ ሰባትና ስምንት ደግሞ ከጓደኛ ጋር ተወያይተው የመሚመልሱት ስራ ነው፡፡በመጨረሻም መልመጃ ዘጠኝ በግል አንቀጽ ጽፌው እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ አለው፡፡በአጠቃላይ ምዕራፉ በግልና በቡድን ስራ ላይ ያተኮረ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**ምዕራፍ ሰባት**፡-የምንባቡ ርእስ የህዝብ ብዛት/Baayina Ummataa/(ገጽ፣30) የሚል ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ስር አስር መልመጃዎች ይገኛሉ፡፡በመልመጃ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አምስት፣ በግል የሚሰሩ ተግባራት ሲሆኑ መልመጃ ስድስት እና ሰባት በቡድን ውይይት ላይ ተመስርቶ ሀሳብ የሚያመነጭ ተግባራት ይከናወኑበታል፡፡ በተለይም መልመጃ ሰባት በክርክር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ተማሪዎችን በንቃት በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያደርግ ስለሆነ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ በግልጽ ይታይበታል ማለት ይቻላል፡፡በዚህ ምዕራፍ መልመጃ ስምንት ባይኖርም መልመጃ ዘጠኝ (ገጽ፣35) ደግሞ የቀረበው ትዕዛዝ ተማሪዎች ከመምህራንና ከጓደኞቻቸው ጋር የሰበሰቡትን ጥምር ቃላት ላይ ተወያይተው ሊደርሱበት የሚችሉበትን ሀሳቦች እንዳሉ ያመለክታሉ፡፡መልመጃ አስር ደግሞ በግል የተሰራውን ተግባር ለመምህራን ማሳየትና እርምት መውሰድ የሚል አንደምታ እናገኛለን፡፡

**ምዕራፍ ስምንት**፡-የምንባቡ ርእስ የኦሮሞ ቆጠራ/Dhaha Oromoo/(ገጽ፣36-37)በምዕራፍ ስምንት ስር ስድስት መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡መልመጃ አንድ ቅድመ ንባብ ሲሆን በግል የሚመለሱ ሶስት ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡መልመጃ ሁለት እና ሶስት፣በምንባቡ መሰረት የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡መልመጃ ሶስት ሁለት አንኳር ክፍሎችን ይዟል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል አዛምድ ከማለት ውጪ ተገቢ የሆነ ግልጽ መመሪያ የለውም፡፡ክፍል ሁለት ላይ ግን ልምምድ አንድ ብሎ" የሚከተሉት አረፍተነገሮች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡በነዚህ አረፍተነገሮች ውስጥ የአራቱን የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ተገንዘብ (የጥያቄ ምልክት፣አንድ ነጥብ፣ትዕምርተ-ጥቅስና ሁለት ነጥብ በጋራ ተገንዘቡ'(ገጽ፣38) የሚል ትዕዛዝ አለው፡፡ትዕዛዙ በአንድ በኩል በግል ተማሪው እንዲገነዘብ ሲያመለክት በሌላ በኩል በጋራ ወይም በቡድን ባልተለየ መንገድ ተገንዘቡ ይላል፡፡ይህም ተማሪዎች በትዕዛዙ አማካይነት ሊደነጋገሩ እንደሚችሉ ያሳየናል፡፡ሌሎች መልመጃ አራት፣አምስትና ስድስት በግል የሚሰሩ መልመጃዎች ናቸው፡፡

**ምዕራፍ ዘጠኝ**፡-የምንባቡ ርእስ ኑሮና አካባቢ/Jireenyaa fi Naannoo /(ገጽ፣40-41) የሚል ሲሆን በምዕራፉ ስር ዘጠኝ መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡መልመጃ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣አራት፣ተማሪዎች በግል እንዲሰሩ የቀረቡ ትዕዛዛት ናቸው፡፡ መልመጃ አምስት ደግሞ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡አንዱ በ"A'ሌላው "B' የተከፈለ ነው (ገጽ፣43)፡፡የመጀመሪያው "A'በቡድን በመወያየት በአረፍ ተነገር ውስጥ የታዩ ሰበብና ውጤት መለየት የሚል የቀረበ ትዕዛዝ ነው፡፡በ"B'ስር የቀረበው ትዕዛዝ ደግሞ በመጀመሪያ ከጓደኞቻቸው ጋራ ተመካክረው ከዛፉ በኂላ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያነቡ የሚል ነው፡፡ይህም ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያደርግ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ቀጥሎ የቀረቡት መልመጃ ስድስትና ሰባት ሲሆኑ በግል የሚሰሩ ተግባራትን የያዙ ናቸው፡፡የመጨረሻዎቹ መልመጃ ስምንትና ዘጠኝ ሲሆኑ በቡድንና በጥንድ የሚሰሩ መልመጃዎችን የያዙ ናቸው፡፡መልመጃ ዘጠኝ የሰሩትን ተግባራት በብጤ እርማት ስህተታቸውን እንዲያስተካክሉ የሚያዝ ትዕዛዝ ያለበት ነው፡፡

**ምዕራፍ አስር**፡-የምንባቡ ርዕስ የንግግርና የውይይት ስርዓት/Sirna Haasaa fi Marii/(ገጽ፣45-47) የሚል ነው፡፡በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረቡት መልመጃዎች በርዕሱም እንደተገለፀው መልመጃው ሳይጠቀስ በንግግርና ውይይት ላይ ያተኮረ ጥያቄዎችን በማቅረብ ይጀምራል፡፡በማስከተል የውይይት ስርዓት መመሪያዎችን በዝርዝር እናገኛለን፡፡ከዚያም በቀረቡት የውይይት ስርዓት መመሪያ መሰረት መልመጃ አንድ(ገጽ፣1)ተማሪዎች በቡድን ውይይት እንዲያከናውኑ ትዕዛዙ ተጽፏል፡፡በዚህ መልመጃ ውስጥ የውይይት ፍሬ ሀሳብና የተወያዮቹ ተማሪዎች መቋጫ ሀሳቦች ይገለፁበታል፡፡ይህ ክፍል በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ከተዘረዘሩት ብልቶች አንዱ ውይይት በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት እንደ አንድ ርዕስ ለትምህርት መቅረቡ ለሌሎች መልመጃዎችም ስራ በአግባቡ ለመማር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡በመልመጃ ሁለት (ገፅ፣46)ላይ የንግግር ስርዓት መመሪያ ቀርቧል፡፡ይህም ርዕስ እንደ መልመጃ አንዱ የውይይት መመሪያ በቀረበላቸው የንግግር መመሪያ መሠረት በአንድ ርዕስ ላይ ተዘጋጅተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ የቀረበ ትዕዛዝ ነው፡፡ተማሪዎች በነፃነትና በራሳቸው መተማመን ንግግር እንዲያደርጉ ማስቻል አንዱ የተማሪ-ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታ በመሆኑ በዚህ ዓይነት መቅረቡ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ሌሎቹ መልመጃዎች ለምሳሌ መልመጃ ሶስት፣አራትና አምስት በግል ግንዛቤ የሚሰሩ ተግባራት ናቸው፡፡ይህም በግል የሚሰሩ ተግባራት ቢሆኑም የግል ስራን ለሌሎች ጓደኞች ማንበብና የሌሎችንም ስራ ማዳመጥ እንዲሁም የተረዱትን ድምፆች ለይቶ ማውጣት በመሆኑ በጥልቀት የቋንቋውን ድምፆች የሚያስለይ ተግባራትን ያከተቱ ናቸው፡፡ ይህም ተማሪን በትምህርቱ ሂደት ውስጥ ያሚያሳትፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ምዕራፍ አስራ አንድ**፡-የምንባቡ ርዕስ በራስ መተማመን/Ofitti Amanuu/(ገጽ፣48-50) የሚል ነው፡፡በምዕራፉ ስር ስምንት መልመጃዎች ይገኛሉ፡፡መልመጃ አንድ ቅድመ-ንባብ ሲሆን መልመጃ ሁለት ደግሞ ድህረ-ንባብ ጥያቄዎችን አካቷል፡፡መልመጃ

ሶስትና አራት በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ ጥያቄዎች የያዙ ናቸው፡፡መልመጃ አምስት፣ስድስት፣ሰባትና ስምንት ከምንባቡ ውጪ የተለያዩ ክህሎትን እንዲያሳድጉ ተብሎ የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡በተለይም ተማሪዎች በራሳቸው ተማምነው የተለያዩ ድርጊቶችን ማከናወን የሚችሉት በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ትግበራ ወቅት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ትምህርቱ በዚህ መንገድ መቀረቡ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

**ምዕራፍ አስራ ሁለት**፡-የምንባቡ ርዕስ የስራ ባህል/Adaa Hojii/ (ገጽ፣51-54)የሚል እናገኛለን፡፡በዚህ ምዕራፍ ስር ስድስት መልመጃዎች ይገኛሉ፡፡ስድስቱም መልመጃዎች ከመልመጃ ሶስት ክፍል ሁለት በስተቀር በግል የሚሰሩ ናቸው፡፡መልመጃ ሶስት ክፍል ሁለት ግን ከተዘረዘሩት ምሳሌዎች በመነሳት በግልና በጋራ የትኛው ድምጽ የትኛውን እንደቀየረው አንዱ ለአንዱ እንዲናገር ያዛል፡፡በአጠቃላይ በደምሳሳው ሲታይ በጋራ ተማሪዎች እዲሳተፉ ማድረጉ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ የተጠው ይመስላል፡፡

**ምዕራፍ አስራ ሶስት**፡-የምንባቡ ርዕስ ከሌባ የሚበልጥ ሌባ /Gamna Gamna Caalu/(ገጽ፣55-58)በሚል የሚመራ ነው፡፡ በምዕራፉ ስር ስድስት መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡መልመጃ አንድ የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ከነዚህ ውጪም መልመጃ ሁለት፣ሶስት፣አራት፣አምስት እና ስድስት በተመሳሳይ መንገድ በግል የሚሰሩ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ምንባቡ ተማሪዎችን ዘና እያደረገ እነሱም በተራቸው የሚያውቁትን ተረት እንዲናገሩ የሚያደርግ በመሆኑ ትምህርቱን ከአካባቢው ጋር እያገናኘ የማህበረ ባህሉን እያመላከተ የሚያቀርብ ነው፡፡ይህ ዓይነቱ አቀራረብ በተማሪ-ተኮር ስርዓተ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

**ምዕራፍ አስራ አራት**፡-የምንባቡ ርዕስ የህፃናት ምግብ እጥረት /Hanqina Nyaata Daa'immanii/(ገጽ፣59-62)የሚል ነው፡፡ምዕራፉ ስር በስምንት መልመጃዎች የተከፋፈለ ነው፡፡እነዚህ መልመጃዎች በአብዛኛው በግል የሚተገበሩ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡በአብዛኛው የንግግር እና የመፃፍ ክህሎትን የሚያጎለብቱ ናቸው፡፡መልመጃ ስምንት ላይ የቀረበው ጥያቄ ግን ከአገራችን ህብረተሰብ አንፃር ለህፃናት አመጋገብ ያለውን ደካማ ጎን ላይ ተወያይታችሁ ሀሳባችሁን አቀናጅታችሁ ፃፉ የሚል ነው፡፡ ውይይቱ በጥንድ፣በቡድን ወይም ከሙሉው ክፍል ጋር መሆን አለመሆኑ አልተገለፀም፡፡

**ምዕራፍ አስራ አምስት**፡-የምንባቡ ርዕስ ሞኝነት/Gowwummaa/ (ገጽ፣63-64) የሚል ነው፡፡በዚህ ምዕራፍ ስር ስምንት መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡መልመጃዎቹ የአንብቦ መረዳት፣የቃላትና የአረፍተነገር አመሰራረት፣የመናገር እና የመፃፍ ክህሎትን የሚያሳድጉ ናቸው፡፡አቀራረባቸው ግን ሁሉም መልመጃዎች በግል ተግባር ላይ መመስረታቸው እንደ ድክመት እንዲታይ አድርጎታል፡፡

**ምዕራፍ አስራ ስድስት**፡-የምንባቡ ርዕስ የግብርና ልማት/Misoma qonnaa/ (ገጽ፣68-69)በሚል የሚመራ ነው፡፡በምዕራፉ ስር ስድስት መልመጃዎች ይገኛሉ፡፡ከስድስቱ

ውስጥ መልመጃ አንድ፣ሁለት፣አራት፣አምስት በግል ተሰርተው እርምት የሚፈልጉ ናቸው። መልመጃ ሶስት ግን በግል የተሰራው ተግባር ጓደኛ ከሰራው ተግባር ጋራ የሚነፃፀር ነው።ከዚያ በተለያዩት መልሶች ዙሪያ እንዲወያዩ የሚያደርግ ነው።መልመጃ 6.3 ደግሞ ከመልመጃ ሶስት ጋራ የተመሳሳይነት ሁኔታ ያሳያል።ከሰሌዳ ላይ የተረዱትን መረጃዎች ወደ ጥያቄ የሚቀይሩበት ትዕዛዝ አለ።ይህ ጥያቄ በግል ከተፃፈ በኋላ ጓደኛ ከፃፈው ጥያቄ አፃፃፍ ጋራ ይነፃፀራል የሚል ነው(ገጽ፣70-71)።ሁለቱ መልመጃዎች ከግል ስራ ወደ ጥንድ ውይይት ስራ በማምራት የመማር-ማስተማሩን ሂደት አሳታፊ አድርጎታል።ይህ ደግሞ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደትን በተለያዩ ብልሃት መጠቀም አግባብነት እንዳለው ያመለክተናል።

**ምዕራፍ አስራ ሰባት**፡-የምንባቡ ርዕስ ህክምና /Wal'aansa/ (ገጽ፣73-74)በሚል የሚመራ ነው።በዚህ ምዕራፍ ስር ዘጠኝ መልመጃዎች ቀርበዋል።ዘጠኙ ምዕራፎች የተለያዩ ክሂሎችን የሚያሳድጉ ተግባራት አካተዋል።ከነዚህ ውስጥ በግል የሚሰሩት መልመጃዎች መልመጃ አንድእና ሁለትA ሲሆኑ ሁለት B(ገጽ74)ላይ ግን "ከዚህ በላይ ከተነበበው ምንባብ መልዕክት ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ፃፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ'የሚል ትዕዛዝ ቀርቧል።ትዕዛዙን ስናጤን ጉድለት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል።" ከተወያያችሁ'የሚለው ፅንሠ-ሀሳብ በጥንድ፣ በቡድን፣ከክፍሉ ተማሪዎች ጋራ ተብሎ ሊለይ ይገባ ነበር ነገር ግን እንዲሁ በደፈናው ተወያዩ የሚለው ግልፅ መመሪያ አይደለም። መልመጃ ሶስት እና አራት ደግሞ በግል የሚሰሩ ተግባራትን የያዙ መልመጃዎች ናቸው።መልመጃ አምስት ደግሞ በግል ሰዎችን በመጠየቅ ወይም ከመዝገበ-ቃላት ውስጥ ሁለት ትርጉም ያለው ቃል በመምረጥ ለክፍል ጓደኞችህ ጋራ ተወያዩበት ስለሚል ተማሪዎችን በትምህርቱ ውስጥ እርበርስ እንዲራከቡ የሚያደርግ ክፍል ነው።መልመጃ ስድስትና ሰባት የግል ስራ ሲሆን በመልመጃ ሰባት ስር ልምምድ ሶስት ስር ደግሞ "ቀጥሎ በቀረቡት የአረፍተ ነገሮቹ ሀሳብ ላይ በመወያየት ሀሳብ ተለዋወጡ (ገጽ፣77)'ብሎ የተሰጠ ትዕዛዝ አለ።ይህም ትዕዛዝ ተማሪዎች ማን ከማን ጋራ ሀሳብ እንደሚለዋውጡ የገለፀው ነገር የለም። በጥንድ፣ በቡድን፣ከክፍሉ ተማሪዎች ጋራ ተብሎ በመለየት ወደ ትግበራው ማስገባት ነበረበት በመሆኑም በዚህ በኩልም ግልጽ መመሪያ ባለመስጠቱ እንደ ድክመት ሊታይ ያስችላል።መልመጃ ስምንት ላይ ግን ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ ስለሚል በተወሰነ ደረጃ ግልፅ መመሪያ ተሰጥቷል።መልመጃው መጀመሪያ በግል ቀጥሎ በቡድን የሚያሰራ ሆኖ የቀረበ ነው።መልመጃ ዘጠኝ ግን ሙሉ በሙሉ በግል የሚሰሩ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው።

**ምዕራፍ አስራ ስምንት**፡-የምንባቡ ርዕስ አዞ/Naacha/(ገጽ፣79-80)የሚል ነው።በዚህ ምዕራፍ ስር ስድስት መልመጃዎች አሉ። ሁሉም በግል የሚሰሩ ትግባራትን የያዙ ናቸው።ምንም እንኳን በግል የሚሰሩ ቢሆኑም ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተማር ብቃታቸውን የሚያጎሉብቱበት ናቸው።

**ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ**፡-የምንባቡ ርዕስ ቦሰኑ/Bosonuu/(ገጽ፣82-84)የሚል ነው፡፡በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረቡት ወደ ምንባቡ እያንደረደሩ የሚያስገቡ የመልመጃ አንድ ጥያቄዎች ጀምሮ መልመጃ ሁለት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡መልመጃ ሶስት በበኩሉ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በመገመት ፍቺ የሚሰጡበት ናቸው፡፡ መልመጃ አራት፣አምስት እና ስድስት የተለያዩ ክህሎቶችን የሚያስገኙ ተግባራት ናቸው፡፡በአጠቃላይ መልመጃዎቹ ሲጤኑ ምንም እንኳን የተለያዩ ክህሎቶችን የሚያጎናጽፉ ቢሆኑም የተማሪዎችን እውቀት ለሌሎች የሚያከፋፍሉበት ከቡድን ውይይት ይልቅ የግል ስራ አመዝኖ ታይቶበታል፡፡

**ምዕራፍ ሀያ**፡-የምንባቡ ርዕስ ደብዳቤ አፃፃፍ/Xalayaa Barreessuu/ (ገጽ፣85-89) የሚል ነው፡፡በምዕራፉ ስር አምስት መልመጃዎችን ቀርበዋል፡፡መልመጃ አንድ ስለ ደብዳቤ አፃፃፍ በቡድን ተወያይተው የሚሰሩት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡መልመጃ ሁለት ደግሞ በመልመጃ አንድ ላይ በተነጋገሩበት መንገድ በግል የሚሰሩ ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ከምንባቡ በኋላ የደብዳቤ ቅርጽ እንዲያዩ ያደርጋል፡፡ደብዳቤው የሚፃፍበት የአድራሻ አፃፍ፣የዘመድ ወዳጅ ደብዳቤና የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ልዩነትን በተግባር እየለዩ የሚጽፉበትን አቅጣጫ ያመለክታል፡፡ስለዚህ ተማሪዎች በሚያውቁት ነገር ላይ ተመስርተው እንዲጽፉ ያግዛቸዋል፡፡መልመጃ ሶስትም ከጓደኞቻቸው ጋር ደብዳቤ እንዲፃፃፉ ያደርጋል፡፡ይህም የመፃፍ ብቃታቸውን የሚያሳድግላቸው ተግባር ነው ማለት ይቻላል፡፡ መልመጃ አራትና አምስትም ምንም እንኳን በግል ቢከወኑ ለተማሪው ጥሩ የእውቀት ግንዛቤ ያስጨብጣሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

**ምዕራፍ ሀያ አንድ**፡-የምንባቡ ርዕስ ኦዳ/Odaa/(ገጽ፣93-94)በሚል ርዕስ የሚመራ የትምህርት ይዘት አለው፡፡በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረቡት መልመጃዎች አምስት ሲሆኑ ከመልመጃ አንድ እስከ መልመጃ አራት ድረስ በግል የሚተገበሩ ጥያቄዎች የሚገኙበት ናቸው፡፡መልመጃ አምስት ስር የተዘረዘሩት ጥያቄዎች ግን ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው የመሚመልሱት በመሆናቸው በዚህ ምዕራፍ ስር ያሉት ተግባራት ከቡድን ስራ ይልቅ የግል ተግባራት ያመዝኑበታል ማለት ይቻላል፡፡

**ምዕራፍ ሀያ ሁለት**፡-የምንባቡ ርዕስ የሰው ኑሮና ደን/Jireenya Namaa fi Bosona/ (ገጽ፣98-99) የሚል የያዘ ነው፡፡ በምዕራፉ ስር ሰባት መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው መልመጃ ተማሪዎች በውይይት ላይ ተመስርተው ሀሳብ እንዲሰጡና ወደ ምንባቡ መልዕክት እንዲያመሩ የሚያደርግ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ከመልመጃ ሁለት እስከ መልመጃ ስድስት የተለያዩ ክህሎትን በግል የሚያስገበዩ ጥያቄዎች ይገኛሉ፡፡ በሰባተኛው መልመጃ ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ለተከሰቱት ችግሮች ተማሪዎቹ ተወያይተው መፍትሄ እንዲፈልጉና ሀሳብ እንዲሰጡ የሚያነሳሱ ተግባራት ናቸው፡፡ በአጭሩ በምዕራፉ ስር ከቡድን ስራ ይልቅ በግል ጥረት የሚከወኑ ተግባራት ቢሆኑም የመጨረሻዎቹ ጥያቄዎች ችግር ፈቺ ብልሀት እንዲተገበር የሚያደርግ ነው፡፡ይህም በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ውስጥ ከሚታዩት ብልሃቶች አንዱ በመሆኑ የሚበረታታ ነው፡፡

***ምዕራፍ ሀያ ሶስት***፡-የምንባቡ ርዕስ ወፎችና ኤሊ/Qocaa fi Simbirroota/ (ገጽ፣103-104)የሚል ነው፡፡በምዕራፉ ስር አምስት መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ሁሉም መልመጃዎች የራሳቸው ዓላማዎች የያዙ ናቸው፡፡ መልመጃ አንድ ወደ ምንባቡ(ተረት ተረት) ከማምራታቸው በፊት ራሳቸው የሚያውቁትን እንዲናገሩ የሚያነሳሳ ነው፡፡ይህ ደግሞ የንግግር ክሂል ኢንዲተገበር አድርጓል፡፡በመልመጃ ሁለት ላይ ደግሞ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችና የቃላት ዕውቀት እንዲጎናፀፉ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡በመልመጃ ሶስት ላይም ይህ የቃላት እውቀት ወደ ምሳሌያዊ አነጋገር እውቀት ያመራበት ሁኔታ ይታያል (ገጽ፣105)መልመጃ አራትና አምስት በበኩላቸው በመልመጃ ሶስት ላይ የተጀመረውን ምሳሌያዊ አነጋገር በተለያዩ መንገዶች የሚማሩበት ክፍል ነው፡፡መልመጃ ስድስት ደግሞ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሰሙትን ወይም የሚያውቁትን ተረት ክፍል ውስጥ እንዲናገሩ ያበረታታል፡፡ከዚህም በተጨማሪ አምስት ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣አምስት እንቆቅልሽ፣የልጆች ጨዋታ፣ ቀልዶች፣ የባህላቸውን የዘፈን ግጥም ጽፈው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ የሚያደርግ ነው(ገጽ፣106)፡፡በአጠቃላይ ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች ዕውቀታቸውን የሚያወጡበት አውድ እዲፈጥሩ የሚያስደርጉ ተግባራት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ይህ ደግሞ የተማሪ-ተኮር ስርዓተ ትምህርት አንዱ አካል ነው፡፡

***ሀያ አራት***፡-የምንባቡ ርዕስ ማዳመጥ /Dhaggeeffachuu/ (ገጽ፣107-108)በዚህ ምዕራፍ ስር ሶስት መልመጃዎች የቀረቡ ሲሆን መልመጃ አንድ ላይ ለሚነበበው ምንባብ ግምት በመስጠት የሚያለማምድ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በመልመጃ ሁለት ላይ የቀረቡት ምንባቡን አዳምጠው የሚመልሱት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመልመጃ ሶስት ላይም በምንባቡ ውስጥ ታሪካቸው የተነገረው ሰዎች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ውስጥ ለማዳመጥ ክሂል ትኩረት ተደርጎ በዚህ ዓይነት መቅረቡ ለቋንቋው ትምህርት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## አባሪ አስራ ሶስት፡- ለት/ቤት ርዕሳነ መምህራን የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

## Gaafii Afaanii Durabu'oota Mana barumsaatiif dhihaate.

1.Maqaa Mana Barumsaa--------

2.Barumsa Ittiin Eebbiffamte-------------

3.Waytii Trbaniitti Barsiistu--------------

4.Mana Barumsaa keessan Keessatti Adeemsi Baruu-Barsiisuu Mala kamiin Keennamaa Jira?

5.Mala Armaan Olitti Maqaa Dhooyittan Kana akka hojiirra Olchan Beekumsa Issa Argatan?

6.Mala Barataa Giddu Galeeffateen Yeroo Barsiisan Toftaalee Adda Addaatti Niffayyadamu?

7.Mana Barumsaa Keessan Keessatti Barsiisoonni Afaan Oromoo Barsiisan Mala Barataa Gidd u Galeeffateen Barsiisaa jiru?

8.Barsiisoonni Afaan Oromo Mala Barataa Giddu Galeeffateen Akka Barsiisan leenjii'in Hojiir raa Kanameefiijira?Yoo Keennameef eessati? Mataduree Maaliirratti?

9. Mala Barataa Giddu Galeeffateen Barsiisuun Barattootaaf Faayidaa Maal Kenna?

10. Mana Barumsaa Keessan Keessatti waa'ee Mala Barataa Giddu Galeeffatee Barattootaafi B arsiisoota Hubachiisuuf Wanti Hojjatame Nijiraa?

11. Akka Hogganaa Mana Barumsaatti Mala Barataa Giddu Galeeffatee Akka Barsiisoonni hu ndu Hojiirra Olchan Gargaartanii Beektuu?

12. Akka Hogganaa Mana Barumsaatti Mala Barataa Giddu Galeeffatee kana Daree keessatti Hojiirra Olchuu isaanii Akkamitti Hordoftu?

13. Mana Barumsaa Keessan Keessatti Barsiionni Afaan Oromo Mala Barataa Giddu Galeeffat ee yoo Hojiirra Olchuu Baatan Sababii isaa Maal sitti Fakkaata?

14.Kitaabileen Afaan Oromoo Barattota Mala Barataa Giddu Galeeffateen Barachuuf Mija'aa Sitti Fakkaata?

13. Mana Barumsaa Keessan Keessatti Barsiionni Afaan Oromo Barsiisan Toftaan Madaallii is aanii Maali?